# ጀማሪ ክፍል 3


## ትክክለኛውን ምረጥ ለ

ከአራት እስከ ሰባት ዕድሜ ያላቸውን ልጆች ለማስተማር

አሳታሚው የኋለኛው ቀን ቅዱሳን
የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሶልት ሌክሲቲ፤ ዩታ

© 2000 by Intellectual Reserve, Inc.
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
በተባበሩት የአሜሪካን መንግሥታት ታተመ
እንግሊዝኛው የፀደቀው፣ ህዳር 1993
ትርጉሙ የፀደቀው፣ 1999

Translation of *Primary* 3
Amharic


CTR

# ማውጫ


| የትምህርቱ ቁጥር እና አርዕስት | | ገፅ |
|---|---|---|
| የአስተማሪ መርጃዎች | | vii |
| 1 | ትክክለኛውን ምረጥ | 1 |
| 2 | የሰማይ አባት እቅዱን እንደምንከተል ይተማመንብናል | 4 |
| 3 | ትዕዛዛቶች ትክክለኛውን እንድንመርጥ ይረዱናል | 9 |
| 4 | የዮሴፍ ስሚዝ የልጅነት ጊዜ | 15 |
| 5 | የመጀመሪያው ራእይ | 20 |
| 6 | የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልሷል | 24 |
| 7 | እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ | 29 |
| 8 | የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚያስተምሩን ነቢያት አሉት | 35 |
| 9 | የክህነት ስልጣን በረከቶችና ስርአቶች | 40 |
| 10 | ንስሀ | 46 |
| 11 | ጥምቀት | 50 |
| 12 | የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ | 56 |
| 13 | የጥምቀት ቃል ኪዳን | 60 |
| 14 | የጥበብ ቃል | 65 |
| 15 | የመፅሐፈ ሞርሞን አመጣጥ | 69 |
| 16 | ታዛዥ በመሆን እምነታችንን ማሳየት እንችላለን | 74 |
| 17 | መፅሐፈ ሞርሞን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን | 79 |
| 18 | የሰማይ አባት እንድንታዘዘው ይረዳናል | 83 |
| 19 | ስንፀይል የሰማይ አባት ይረዳናል | 88 |
| 20 | መንፈስ ቅዱስ እውነቱን እንድናውቅ ይረዳናል | 93 |
| 21 | በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታችን ታላቅ በረከትን እንቀባላለን | 97 |
| 22 | የኢየሱስ ክርስቶስ የኀጢአት ክፍያ | 102 |
| 23 | እርስ በርስ ይቅር መባባል | 106 |
| 24 | ጌታ ወንጌላዊያኖችን ይረዳቸዋል | 111 |
| 25 | ወንጌላዊ መሆን እችላለሁ | 116 |
| 26 | መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን ይችላል | 121 |
| 27 | የተጠያቂነት ዕድሜ | 127 |
| 28 | ወላጆቻችን እንድንማር ይረዱናል | 133 |
| 29 | በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን | 137 |
| 30 | ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዳችንን ይወደናል | 142 |
| 31 | ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው እንድንወድ ይፈልጋል | 148 |
| 32 | ቅዱስ ቁርባንን ስንወስድ ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ | 154 |
| 33 | ቅዱስ ቁርባን ቃልኪዳናችንን ያስታውሰናል | 159 |
| 34 | ወደ ሰማይ አባታችን መፀለይ እንችላለን | 164 |

| | | |
|---|---|---|
| 35 | ዘለዓለማዊ ቤተሰብና ቤተመቅደስ | 169 |
| 36 | ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን ማሳየት | 173 |
| 37 | ሌሎችን በማገልገል ኢየሱስ ክርስቶስን አገለግላለሁ | 177 |
| 38 | ንጹህና ቅዱስ መሆን እችላለሁ | 182 |
| 39 | ለወላጆቻችን ፍቀርን ማሳየት | 188 |
| 40 | ቤተክርስቲያን ውስጥ ማምለክ | 193 |
| 41 | ጾም ወደ ሰማይ አባትና ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀርበናል | 199 |
| 42 | አስራት | 204 |
| 43 | የሰማይ አባትንና ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ማክበር | 209 |
| 44 | ለሌሎች አድርግ | 213 |
| 45 | ለቤተሰቦቼ መልካም ምሳሌ መሆን እችላለሁ | 218 |
| 46 | ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም መኖር እንድንችል አድርጓል (ፋሲካ) | 225 |
| 47 | አየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ተወልዷል (የገና በአል) | 231 |
| የመዝሙሮች ቃላት | | 000 |

# የአስተማሪ መርጃዎች

**ዓላማው**

ይህ መምሪያ የተፃፈው የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ በመከተል፣ ትክክለኛውን መምረጥ፣ መጠመቅ፣ እና የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን እንደሚችሉ ልጆቹን ለማስተማር እንዲረዳዎት ነው።

**ለጀማሪ ክፍል አስተማሪዎች መልዕክት**

የሰማይ አባታችን ልጆችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንዲያስተምሩና እንዲያከብሩት እንዲረዷቸው የተቀደሰ ጥሪ ነው የሰጥዎት። ልጆቹን ሲያገለግሉ እና እያንዳንዳቸውን "ወደ ክርስቶስ እንዲመጡ" ሲጋብዟቸው፣ ህይወታቸውን ይባርካሉ። የሰማዩ አባትን በረከት ማወቅ እንዲጀምሩ እና የወንጌልን ምስክርነት እንዲቀበሉ ሊረዷቸው ይችላሉ። እርሶም በግልዎ ያድጋሉ ከእነርሱም ይማራሉ። በጀማሪዎች ክፍል አገልግሎትዎ ታላቅ ደስታን ሊያመጣልዎ ይችላል። የጀማሪ ክፍል ህፃናትን በማገልገል፣ የሰማይ አባትዎንም እያገለገሉ ነው (ሞዛያ 2፥17 ይመልከቱ)።

የወንጌልን መሰረተ ሃሳቦች ሲያከብሩ፣ ቅዱሳን መፃህፍትን ሲያጠኑ፣ የክህነት ስልጣን መሪዎችን ምክር ሲከተሉ፣ እና በጸሎት አማካኝነት ወደ ሰማዩ አባት ሲቀርቡ፣ የሚያስተምሯቸውን ልጆች በተመለከተ የመንፈስ መነሳሳት ከመንፈስ ቅዱስ ይቀበላሉ። በተደጋጋሚ ለልጆች ይመሥክሩላቸው፣ እናም በዚህ ጠቃሚ ጥሪ መንፈስ ቅዱስ በእርሶ አማካኝነት እንዲሰራ ያርጉ። ይህንን ሲያደርጉ፣ መንፈስ ይመራዎታል ስለዚህም በጀማሪዎች ክፍል የሚሰሩት ሁሉ የሰማዩ አባታችን ለልጆቹ የሚፈልገውን ይሆናል።

**የክፍል መረጃ**

በዚህ መምሪያ ፊት ለፊት የሚገኙት፣CTR ጋሻ እና CTR ቀለበት በብዙ ትምህርቶች ውስጥ ይጠቀማሉ። CTR የሚወክለው "ትክክለኛውን ምረጥ የሚለውን ነው። የ CTR ቀለበት በብዙ ትምህርቶች እና አስፈላጊ ተሳትፎዎች ተገልጿል እናም ለባለቤቱ መልካምን እንዲመርጥ እንደ ማስታወሻ ያገለግላል። የ CTR ቀለበት በአካባቢዎ የሚገኝ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ አንዳንድ ለመግዛት ጳጳሱን ወይም የቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን ገንዘብ እንዲሰጡ ይጠይቁ።

**የክፍል ጊዜ**

**ፀሎት**

እያንዳንዱን ክፍለ ጊዜ በፀሎት ይክፈቱ እና ይዝጉ። ፀሎት እንዲፀልዩ ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ አይነት ዕድል ይስጡ። ለፀሎት መመሪያዎችን በመስጠት እና ሃሳቦችን በማቀረብ እናም ልጆቹ በፀሎት ውስጥ ሃሳቦችን እንዲያጠቃልሉ በመጠየቅ ፀሎት ለክፍሉ ትርጉም የሚሰጠው ክፍል እንዲሆን ያድርጉ። በክፍል ውስጥ በቅርብ በሚያስፈልጉ ሃሳቦች እና በትምህርቱ መልዕክት ላይ ትኩረት ስጡ።

**ትምህርት ማስተማር**

ልጆቹን እንዲገባቸው እና እንዲደሰቱበት እናም የመንፈስ መመሪያ እንዲኖሮት እያንዳንዱን ትምህርት በጥንቃቄ እና በፀሎት ያዘጋጁ። ትምህርቱን ለልጆቹ አያንብቡላቸው። በራስዎ ቃላት ቢያቀርቡት የተሻለ ይመልሳሉ።

ከትምህርቱ ለክፍልዎ ተገቢ የሆኑትን መሣሪያዎች ይምረጡ። በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ የተዘረዘሩት ገንቢ ተሳትፎዎች የቀረቡትን ትምህርት ለማቀረብ ተስማሚ ሆኖ ስታገኙት እንድትጠቀሙበት ነው። ሁሉም የትምህርት መሣሪያዎች ወይም ገንቢ ተሳትፎዎች ለክፍልዎ ተገቢ አይሆኑም። ክፍልዎ በደንብ የሚሰሩበትን ይምረጡ። በክፍልዎ ውስጥ በዕድሜ ያነሱ ልጆች ካሉዎት፣ ብዙ ጊዜ በትምህርት ወቅት አተኩሮታቸውን ለመጠበቅ እንዲረዳዎት

መዝሙሮችንና የጣት ጨዋታዎችን መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል። ልጆቹ ከተደሰቱበት በተግባር የሚታየውን ክፍል ብዙ ጊዜ ይደግሙት ይሆናል። በቃላት መስመሮች ፈንታ በዕድሜ ላነሱ ልጆች፣ ስዕሎችን መሳል ወይም የቃላት መስመሮቹ የሚያስተምሩትን ሃሳብ በምሳሌ ለማስረዳት አንዳንድ መፅሔቶችን መቆራረጥ ይችላሉ።

የማስተማሪያ መመሪያ መፅሃፍ መምሪያ *[Teaching—No Greater Call]* ትምህርቱን በአስፈላጊው ሁኔታ እንዲያስተምሩ ሊረዳዎት ይችላል።

የክፍሉ አባላት የወንጌልን መልዕክት የበለጠ በመንፈስ እንዲያዳምጡ እና እንዲመልሱ ሁልጊዜ አጭር የሆነ፣ የግልዎን ምስክርነት ይስጡ።

### በክፍል ውስጥ ሙዚቃ

ሙዚቃ የጌታን መንፈስ ወደ ክፍል ሊጋብዝ ይችላል። በክፍል አንድ ላይ መዘመር ልጆች የትምህርቱን ሃሳቦች የተሻለ እንዲያስታውሱ ሊረዳቸውና ትምህርትዎን የበለጠ የሚስብ ያደርገዋል።

ከአንድ ጊዜ በላይ የተጠቀሱት የመዝሙሮች ቃላት በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተፅፈዋል። በመምሪያው አንድ ጊዜ ብቻ ያገለገሉት የመዝሙሮች ቃላት ከትምህርቶቹ ጋር ተጠቃለዋል። የነዚህ መዝሙሮች ሙዚቃ በልጆች የመዝሙር መፅሐፍ ውስጥ ሊገኝ ይችላል። ከልጆች የመዝሙር መፅሐፍ የተቀዱ ሙዚቃዎች በቴፕ ካሴቶች ይገኛሉ።

ክፍሉን ሽልማት በሚያሰጥ ልምድ እንዲዘምሩ ለማድረግ ችሎታ ያለው ሙዚቀኛ መሆን አያስፈልግዎትም። በትምህርት ዝግጅት ክፍል መዝሙሮቹን በቤት ይለማመዷቸው እና ይወቋቸው። ልዩ ዕርዳታ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የሙዚቃ መሪውን ወይም አብሮ የሚጫወተውን ይጠይቁ።

በተለይ በዕድሜ ትንሽ ከሆኑ ልጆች ጋር፣ ለመዝሙሮቹ የሚስማሙ እንቅስቃሴዎችን መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል። ከመዘመር ይልቅ ቃላቶቹን መናገር ይችላሉ።

### የእምነት አንቀጾች

የእምነት አንቀጾች በጀማሪዎች ስርዓተ ትምህርት ውስጥ አስፈላጊው ክፍል ነው። በትምህርቱ የተጠቀመውን የእምነት አንቀጽ ሁሉንም በቃላቸው መያዝ የሚችለውን እያንዳንዱን ልጅ ያበረታቷቸው።

### ቅዱሳን መፃህፍት

በየሳምንቱ ቅዱሳን መፃህፍትዎን ያምጡ፣ እናም ለልጆቹ ስታነቧቸው እና እነርሱም ሲያስተምሩ እንዲያዩት ያድርጉ። ልጆቹ የራሳቸው የሆኑ ቅዱሳን መጻህፍት ካላቸው፣ በየሳምንቱ ወደ ክፍል ይዘዋቸው እንዲመጡ ያበረታቱአቸው። በዕድሜ ከፍ ያሉትን ልጆች በትምህርቱ ላይ የተጠቀሙት ምንባብ እንዲያገኙና እንዲያነቡት ይርዷቸው። አልፎ አልፎ ስለ ቅዱሳን መጽሐፍት ጥቅም ያለዎትን ምስክርነት ይስጡ።

### የማስተማሪያ መርጃዎች

*ስዕሎች*። በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሙት አብዛኛዎቹ ስዕሎች ከመምሪያው ጋር በፓኬት ውስጥ ተቀጥረዋል እናም ተጠቃለዋል። እነዚህ ስዕሎች ከመምሪያው ጋር መሆን ይገባቸዋል። በፀሎት ቤታችሁ ቤተመፅሐፍት ውስጥ ሊገኙ ለሚችሉ ትልቅ መጠን ላላቸው ስዕሎች የቤተመፃህፍቱ ቁጥር በትምህርቶቹ ላይ ተዘርዝረዋል። የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ ቁጥሩ በጥራዙ ለተጠቃለሉት ስዕሎች ተዘርዝረዋል።

*ሙዚቃ*። “በክፍል ውስጥ ሙዚቃ” የሚለውን ከላይ ይመልከቱ።

*የተቆራረጡ ስዕላዊ መገለጫዎች*። ስእሎቹን ቆራርጡ እና በትምህርቱ ውስጥ በተገቢው ቦታ ይጠቀሙባቸው። ከመምሪያው ጋር ያድርጓቸው።

*ምግብ*። ትምህርቱ ምግብ የመጠቀምን ሃሳብ በሚያቀርብበት በማንኛውም ጊዜ፣ እባክዎን ከልጆቹ አንዳቸውም የምግብ አለመስማማት ወይም አካላዊ ጠባይን የሚያውክ ሁኔታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ በቅድሚያ ከልጆቹ ወላጆች ያረጋግጡ።

*ሌሎች የማስተማሪያ መርጃዎች*። በትምህርቱ በቀረበው ሃሳብ ሌላ ቀላል የማስተማሪያ መርጃዎችን፣ እንደ የቃላት መስመሮችን፣ ሰንጠረዦችን፣ እና የሚታደሉ ፅሁፎችን መስራት ያስፈልግዎታል። እነዚህን መርጃዎች በኋላ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር እና በሚቀጥሉት ዓመታት ለመጠቀም ያስቀምጡት።

### በሐሳብ ልውውጥ ጊዜ የሚቀርቡ

አንዳንድ ጊዜ በጀማሪዎች ክፍል የሐሳብ ልውውጥ ጊዜ ክፍልዎ ቀላል የወንጌልን መልእክት ያቀርባል። እንደነዚህ አይነት መልእክቶች ከትምህርቱ መወሰድ አለባቸው። ትምህርቱን ሲያዘጋጁና ሲሰጡ ለሐሳብ ልውውጥ ጊዜ ተስማሚ ሃሳቦችን ይመልከቱ። ልጆች በቀርብ በቀዱስ ቁርባን ስብሰባ ላይ ካቀረቡት መሰረተ ሃሳብም መምረጥ ይችላሉ።

በሐሳብ ልውውጥ ጊዜ ልጆች የወንጌልን መሰረተ ሃሳብ እንዲያስተምሩ ማድረግ ያንን መሰረተ ሃሳብ እንዲማሩ እና እንዲያካፍሉ ለመርዳት ውጤታማው መንገድ ነው። የክፍሉን ክፍል ጊዜ ግማሹን የሚቀርቡትን ለማዘጋጀት መጠቀም ይችላሉ።

በሐሳብ ልውውጥ ጊዜ የሚቀርቡት ቀላል እና ብዙ ልምምድን የማይጠይቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። የሚከተሉት ሃሳቦች ውጤታማ፣ ቀላል የክፍል አቀራረቦችን ለመስጠት ሊረዱዎት ይችላሉ፣

1. ከትምህርቱ ውስጥ አንድን ታሪክ ወይም ሁኔታን በተግባር ያሳዩ።
2. "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ አሳዩና ግለጹ (ትምህርት 7 ይመልከቱ)።
3. ልጆቹ ስለመጪው ጥምቀታቸው የሚሰማቸውን እንዲገልጹ ያድርጉ። አንድ ልጅ ዕድሜው ስምንት ከደረሰና ከተጠመቀ፣ ስለ ጥምቀቱ ያለውን ስሚቶቹን እንዲያካፍል ይጠይቁ።
4. ስዕሎችን፣ የቃላት መስመሮችን፣ ወይም ተቀርጠው የወጡ ስዕሎችን በመጠቀም ከትምህርቱ ውስጥ ታሪክ ይናገሩ።
5. የዕምነት አንቀፅን እንደገና ግለጹ። *ከልጆች የመዝሙር መጽሐፍ፣ ገፅ 122–33 ላይ* ከእምነት አንቀፅ መዝሙሮች አንዱን መዘመር ይፈልጉ ይሆናል።

ለተጨማሪ ዕርዳታ፣ *የጀማሪዎች ክፍል የሐሳቡ ልውውጥ ጊዜ መምሪያ [Primary Sharing Time Resource Manual]* (33231) ይመልከቱ።

### ከልጆች ቤተሰቦች ጋር መካፈል

ልጆቹ በጀማሪዎች ክፍል የተማሩትን ለቤተሰቦቻቸው እንዲያካፍሉ ያበረታቷቸው። አንዳንድ ጊዜ ትምህርቶቹን ለማበልፀግ ወላጆች ክፍልዎን እንዲጎበኙና እንዲሳተፉ ይጋብዟቸው። የጀማሪዎች ክፍልን ለልጆቻቸው የበለጠ ትርጉም ያለው ለማድረግ እንዲረዳ ከወላጆች ለሚሰጠው ሃሳብ ግለጽ ይሁን።

### ለጥምቀት መዘጋጀት

በክፍልዎ ውስጥ ዕድሚያቸው ሰባት የሆኑ ልጆች ካሉዎት፣ አንዳንዶቹ በዓመቱ ውስጥ ይጠመቃሉ። እንደ ጀማሪ ክፍል አስተማሪያቸው፣ የልጆቹን ቤተሰቦች መደገፍና የክፍሉ አባላት ለጥምቀታቸው እንዲዘጋጁ መርዳት ይችላሉ። ይህን ለማድረግ እንዲረዱዎት የሚከተሉትን ሃሳቦች ይመርምሩ፣

1. ከተቻለ፣ ከክፍልህ የመጀመሪያው ልጅ ከመጠመቁ በፊት ጥምቀትን በተመለከተ አንዳንድ ትምህርቶችን አስተምሩ (ትምህርት 11፣ 13፣ 21፣ 32፣ እና 33)።
2. እሁድ ከእያንዳንዱ ልጅ ጥምቀት በፊት የዚህን ስርዓት አስፈላጊነት ለመወያየት ከክፍል ጊዜ ትንሽ ደቂቃ ይውሰዱ።
3. ከተቻለ፣ ከጀማሪ ክፍል አመራር እና ሊገኙ ከሚችሉ ከማንኛውም የክፍል አባላት ጋር የእያንዳንዱ ልጅ ጥምቀት ላይ ይገኙ።
4. ልጆቹ ጥምቀትን በተመለከተ በሐሳብ ልውውጥ ክፍለ ጊዜ ትምህርት እንዲያዘጋጁ ይርዷቸው።

**ልጆቹን ማወቅ**

በጳጳሳት አመራርዎ ወይም በቀርንጫፍ ፕሬዚዳንትዎ አማካኝነት ልጆችን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል እንዲያስተምሩ የተሰጥዎት ጥሪ የተቀደሰ የአደራ ጥሪ ነው። እነዚህን ልጆች በህይወታቸው ሙሉ አዳኝን እንዲከተሉት ታላቅ ተፅዕኖ ሊያሳድሩባቸው ይችላሉ። አስታውሱ። የክህነት ስልጣን መሪዎች ከሰማይ አባታችን በመንፈስ በመነሳት መረጡዎት፤

ሁልጊዜ ለክፍሉ ቀን የሆነ ሁኔታና ለልጆቹ ፍቅርን ያሳዩ። የእያንዳንዱን ልጅ ተሰጥዎ፣ ፍላጎት፣ እና ችሎታ ይወቁ። ማንበብና መፃፍ የሚጠይቁትን የትምህርት ተሳትፎዎች ለልጆቹ ችሎታ እንዲመች አድርጉ።

እነሱን በማድመጥ እና በተቻለ መጠን ለእያንዳንዱ አትኩሮት በመስጠት ልጆቹ እርግጠኛ የሆነ የራስ ጠቃሚነትን ስሜት እንዲገነቡ እርዷቸው።

እነዚህ ትምህርቶች የተጻፉት ተመሳሳይ ዕድሜ ላላቸው ቡድኖች ክፍሎች ወይም የተቀላቀለ ዕድሜ ላላቸው ቡድኖች ክፍሎች ከአራት እስከ ሰባት ዕድሜ ለሆኑ ነው። ቢሆንም፣ እርሶ በልዩ ክፍልም እንደ ዕድሚያቸው አኳያ ማስማማት ይፈልጉ ይሆናል። ክፍልዎ እንዴት እንደተደራጀ ከመመልከት ባሻገር፣ የልጆቹን የዕድሜ ባህሪ መረዳት የበለጠ በውጤታማነት እንዲያስተምሩ ይረዳዎታል። ይህ ልጆቹ እንደሚያደርጉት ለምን ራሳቸውን እንደሚመሩና የበለጠ ሊማሩበት በሚችሉበት መንገድ እንዴት ማስተማር እንደሚቻል እንዲያውቁ ሊረዳዎት ይችላል። ልጆቹን መረዳትም በክፍሉ ውስጥ እርግጠኛ የሆነ ስሜትን እንድትጠብቅ ሊረዳህ ይችላል። ትምህርትዎን ሲያዘጋጁ የሚከተሉትን ባህሪዎች ይከልሱ። ይሁን እንጂ፣ እያንዳንዱ ልጅ የሚበስለው በራሱ ወይም በራሷ ፍጥነት እንደሆነ፣ ያስታውሱ። እነዚህ አጠቃላይ መመሪያዎች ብቻ ናቸው።

### አራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው

አራት ዓመት የማወቂያ ዕድሜ ነው። አብዛኛውን ጊዜ የአራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች የሚጠቀሙበት ሁለቱ ቃላቶች *ለምን* እና *እንዴት* ናቸው። አራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች አድራጊዎችና ቀልጣፎች ናቸው። የሚከተሉት አራት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች አጠቃላይ ባህሪይ ናቸው፥

1. የሶስት ዓመት ዕድሜ ካላቸው ልጆች የበለጠ በቀላሉና በመተማመን መሮጥ፣ መዝለል እና ከፍ ያለ ነገር ላይ መውጣት ይችላሉ።
2. ኳስ መወርወር ወይም መምታት እናም ከሽክላ ቤት መገንባት ይችላሉ።
3. “ያንን ከዚህ በፊት አድርጌዋለሁ፣ አሁን አዲስ የሆነ ነገር መስራት እችላለሁ” የሚሉ ዓይነት ነገሮችን ማለት ይወዳሉ።
4. ከሌሎች ልጆች ጋር መጫወትን ይወዳሉ ነገር ግን ከሌሎች ጋር አብረው በትልቅ ቡድን ለመጫወት ብቁ አይደሉም።
5. ምንም እንኳን አብረዋቸው የሚጫወቱ ሌሎች ልጆች ቢያስፈልጋቸውም፣ በብዛት የሚጫወቱት በየግላቸው ነው። በአንድነት ሊሮጡና ሊደንሱ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሌሎች ልጆች እንዴት እየተጫወቱ እንደሆነ ለማየት ትኩረት አይሰጡም።
6. ብዙ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ በተጨማሪ፣ ከሌላ ልጅ ወይም አዋቂ ጋር መነጋገር ይችላሉ።
7. ዋናው ልምዳቸው ቤት ውስጥ ስለነበረ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚያወሩት ስለ ቤታቸውና ቤተሰብ ነው። በዚህ ዕድሜ ያሉ ልጆች ለአስተማሪው ስለቤተሰቦቻቸው መናገርን ይወዳሉ። የሌሎች ልጆችን ታሪክ ከማዳመጥ ይልቅ ሁልጊዜ የራሳቸውን ታሪክ ይናገራሉ። በቤተሰብ ላይ የሚያተኩሩ ትምህርቶችን እና ተሳትፎዎችን ይወዳሉ።
8. ሙሉ በሙሉ የሚኖሩት ለዚህና ለአሁን ነው። ትላንትና እና ነገ ማለት ጥቂት ናቸው። ቢሆንም፣ ወደፊት ለሚሆኑ ሁኔታዎች ታላቅ፣ ደስታን ያሳያሉ፣ እናም እስከአሁን የጊዜን ትርጉም ስላላገኙ፣ አንዳንድ የወደፊት ሁኔታዎችን ሊጠይቁ ይችላሉ፣ “ነገ ነውን?”

9. ታሪኮችን እና የሕፃናት ግጥሞች ማዳመጥ ይወዳሉ። የሚወዷቸውን ታሪኮች ያለምንም ለውጥ ደግመው ደጋግመው መስማት ይፈልጋሉ። ታሪኩን ከሰሙ በኋላ፣ ባህሪዎቹን በቲያትር መለወጥ ይወዳሉ።

10. በትንሽ ዕርዳታ መፀለይን መማር ይችላሉ።

**አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው**

አምስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች በራሳቸው የበለጠ እርግጠኞች የሆኑ እናም በአጠቃላይ እምነት የሚጣልባቸው ናቸው። በቤታቸው መስራት የሚጠበቅባቸውን ተምረዋል። ከሌሎች ልጆች ጋር በደንብ ይጫወታሉ፣ ነገር ግን ብቻቸውንም እንጣጥ እንጣጥ በማለት ወይም ስዕል በመሳል፣ ራሳቸውን በብዙ መንገድ ማስደሰት ይችላሉ። የሚከተሉት የአምስት ዓመት ዕድሜ ላላቸው የተለመደ ባህሪ ነው፣

1. ትልቁ የጡንቻቸው መተባበር መሻሻሉን ይቀጥላል። አሁን መዝለል፣ መገለባበጥ፣ እና በአንድ እግርም እንኳን. . . . እንጣጥ እንጣጥ ማለት ይችላሉ። ጋሪን ወይም የጭነት ተሽከርካሪን በጥቂቱ መጎተት ይችላሉ።

2. ምንም እንኳ ስርዓት መጠበቁ ለእነሱ አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ትንሹ የጡንቻቸው መተባበር እንዲያሽጉ፣ ስዕሎችን ቆርጠው እንዲያወጡ፣ የተሳሉ ስዕሎችን ቀለም እንዲቀቡ ይፈቀድላቸዋል። ብዙዎቹም ጫማቸውን ማሰር ይችላሉ።

3. አራት ዓመት ዕድሜ ካላቸው የበለጠ ታማኞች እና እምነት የሚጣልባቸው ናቸው። ሁልጊዜ በቤታቸው አካባቢ መርዳትን ይወዳሉ እናም ከወላጆቻቸው ጋር መስራት ሲችሉም ደስተኞች ናቸው።

4. “ያ ለምንድነው?” ወይም “ይህ የሚሰራው እንዴት ነው?” ብለው ሲጠይቁ በቁምነገር ነው ልባዊ፣ ታማኝ መልስን መቀበልን ይፈልጋሉ እናም አለባቸው፣ ነገር ግን ሊረዱት በማይችሉት ቋንቋ ወይም ዝርዝር መሆን የለበትም።

5. አስተማሪዎቻቸውን ይወዳሉ ከእነርሱ አጠገብ መቀመጥንም መብት እንደሆነ ያስባሉ። አስተማሪዎች በትምህርቱ ላይ ስዕል በመያዝ ወይም ለመርዳት ሌላ ነገር እንዲያደርጉ ሲጠይቋቸው ይደሰታሉ።

6. ስለ ቤትና ቤተሰብ አነስተኛ የቡድን ስራዎችን እናም ቲያትር መስራትን ይወዳሉ።

7. ታሪኮችን መስማትና መናገርን ይወዳሉ፣ እናም ተመሳሳይ የሆነ ታሪክን ደግመው ደጋግመው ይጠይቃሉ። ድግግሞሽ የሚማሩበት ዋነኛው መንገድ ነው። ብዙ ጊዜ የአንድን መፅሐፍ ገጾች በማገላበጥ ቃል በቃል ታሪኩን መናገር ይችላሉ።

8. አብዛኛውን ጊዜ ጓደኞች፣ ተስማሚዎች፣ አፍቃሪዎች፣ እና ረጂዎች ናቸው፣ ነገር ግን የራሳቸውን ዘዴ ካላገኙ፣ አምባጓረኞች ሊሆኑ ይችላሉ።

9. ትልቅ እንደሆኑና እንዳደጉ ለማሳየት አዳዲስ ልዩ መብቶችን መቀበል ይወዳሉ።

10. ከአስር እስከ አስራሁለት ደቂቃዎችን በሚወስድ ጊዜ ትኩረታቸውን፣ ከአንዱ ተሳትፎ ወደ ሌላው በፍጥነት መቀየር ይችላሉ። የጣት ጨዋታዎች ለትናንሽ ሕጻናት እንደሆኑ ማሰብ ይጀምራሉ እናም የበለጠ ያደጉ ተሳትፎዎችን ወይም የእረፍት ልምምዶችን ይፈልጋሉ።

11. ሁልጊዜ ሌላ ልጅ በሚጫወትበት ነገር ላይ የመጫወት መብት እንዳላቸው ይጠይቃሉ። እንደዚህ ዓይነት ነገሮችን በጥንቃቄ ለመያዝ ይሞክሩ፣ ልጆቹ ተራ እንዲጠብቁ ያስተምሯቸው።

12. እጅግም ማህበራዊ አይደሉም እናም ከትልቅ ቡድኖች ይልቅ ትንሽ ቡድኖችን ይመርጣሉ። አስር ሰዎች ካሉበት ቡድን ጋር ከመሆን ይልቅ አንድ ጥሩ ጓደኛ ቢኖራቸው ይመርጣሉ።

13. በግምት እና በእውነታ መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅን እስከአሁን አልተማሩም። ስለዚህም፣ አንድ ልጅ ሰዓቴ የተሰራው ከወርቅ ነው፣ ከማንም አባት የበለጠ አባቴ ትልቅ ነው፣ እናም ያጠመደው አሳ ከመጠን ያለፈ ረዥም ነው ሊል ይችላል። ይህ በአንድ ልጅ ህይወት ውስጥ የተለመደ የዕድገት ጊዜ እንደሆነና እውነት በሆነውና ባልሆነው መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ለማወቅ ጊዜ እንደሚወስድ አዋቂዎች ማገናዘብ አለባቸው። ይህ የዕድገት ጊዜ ህፃኑ ሲያድግ ያልፋል።

14. ጉጉ ተማሪዎች ናቸው። የሰማዩ አባት ለእነሱ በጣም እውነት ስለሆነ፣ ለእርሱ በጣም ፍቀር አላቸው እናም ስለ እርሱ ብዙ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ። በዚህ ዕድሜ ያሉ ልጆች በመፀለይ ይደሰታሉ እናም ያለ ዕርዳታ ሊፀልዩ ይችላሉ።

**ስድስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው**

ስድስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሰውነታቸውን በደንብ ይቆጣጠራሉ እናም አዲስ ዕውቀትን በመማር እና ያገኙትን በማስተካከል ላይ ለማዋል ታላቀ ሃይል አላቸው። ለምሳሌ፣ ገመድ መዝለል፣ ኳስ ማንጠር፣ ማፏጨት፣ የተወጠረ የዕጅ ሽቦን ማዞር፣ እና ብስክሌት መንዳት፣ መማር ይችላሉ። ስድስት አመት ዕድሜ ያላቸው ትንሹ ጡንቻቸውን የመጠቀም ችግር አሁንም ሊኖርባቸው ይችላል፣ ነገር ግን የራሳቸውን የስም ፊደሎች፣ እና ሌሎች ጥቂት ቃላቶችን ለመጻፍ መማር ይችላሉ። የሚከተሉት የስድስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች አጠቃላይ ባህሪ ነው፣

1. የትኩረታቸው ስፋት ይጨምራል። ምንም እንኳ አረፍት የሌላቸው ቢሆንም፣ እንደየዝንባሌያቸው በአንድ ተሳትፎ ላይ ለአስራ አምስት ወይም ሃያ ደቂቃዎች ትኩረት መስጠትም ይችላሉ።
2. ዛፍ ላይ መውጣት፣ በመጫወቻ መሬት ላይ የሚያስፈልግ ዕቃ ማዘጋጀት፣ ወይም የሩጫ ውድድሮች የመሳሰሉትን የመላ ሰውነት እንቅስቃሴ ያስደስታቸዋል።
3. ጨዋታዎችን እና የጓደኝነት ውድድሮችን ይወዳሉ።
4. የአስተማሪው አስተያየት ለእነርሱ በጣም አስፈላጊ ነው። ከአስተማሪው አጠገብ መቀመጥ እና በትምህርቱ ላይ ስዕሎችን በመያዝ ወይም ቁሳቁሶችን ወደ ቤተመፃህፍት በመመለስ ለመረዳት ይፈልጋሉ።
5. ታሪኮችን መስማት፣ በቲያትር መለወጥ፣ እና ማስመሰል አሁንም ይወዳሉ። ብዙዎቹም የዓዋቂ ልጆች ልብሶችን መልበስ ይፈልጋሉ።
6. የራሳቸው አቀጣጫ እስካላገኙ በጣም ለጋሾች፣ አፍቃሪዎች፣ እና ተስማሚዎች ናቸው፣ እና ከዚያም አምባጓረኞች ሊሆኑ ይችላሉ።
7. ግብዣዎችን ይወዳሉ።
8. መዝለልን፣ መጋለብን፣ እና እንጣጥ እንጣጥ ማለትን ሊያንፁ ይችላሉ፣ እናም እነዚህን ዕውቀቶች በጨዋታዎች ውስጥ መጠቀምን ይወዳሉ።
9. ጥሩው ፀባይ ምን እንደሆነና መጥፎው ፀባይ ምን እንደሆነ ለማወቀ ይጨነቃሉ።
10. በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸው እምነት ይጨምራል። ብዙዎቹ የስድስት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ልጆች በቤት ውስጥ ወይም በሌላ ክፍሎች ቀደም ሲል ልምድ ካላቸው ብቻቸውን መፀለይ ይችላሉ።

**ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው**

ልጆች፣ በሰባት ዓመታቸውም ለወላጆቻቸው ቀርብ ናቸው እናም ትኩረታቸውን፣ ፍቀራቸውን፣ እና ርህራሄያቸውን ይወዱታል፣ ነገር ግን ከቤት ውጪ ካሉ ሰዎች እና ሁኔታዎች ጋር የበለጠ መዛመድ ይጀምራሉ። የግል ፍላጐት አላቸው እናም የራሳቸው የሆነ አንዳንድ ውሳኔ ለመወሰን እንዲፈቀድላቸው ይፈልጋሉ። ንቁዎች፣ ጉጉዎች፣ እናም ስለ እነርሱ በህይወት ታላቀ ዝንባሌ አላቸው። ብዙ ተሳትፎዎችን መርምረው ያገኛሉ እናም ደስታ የሚሰጣቸውን መድገም ይወዳሉ። የሚከተሉት የሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሌሎች አጠቃላይ ባህሪይ ናቸው፣

1. ትልቁ ጡንቻቸውን በደንብ ይቆጣጠራሉ፣ እናም ልጆቹ የበለጠ ሞገስ ያላቸው፣ ፈጣኖች፣ እና ቀልጣፎች ይሆናሉ።
2. የትንሹ ጡንቻቸው መቆጣጠሪያ ያድጋል። የበለጠ በቀላሉ እና በትክክል መፃፍ ይችላሉ።
3. ብዙዎቹ ደግመው ደጋግመው፣ ተመሳሳይ ርህራሄ የሌለበት እና በሃይል የመውደቀ ጨዋታን መጫወት ይወዳሉ።

4. በሃይል የተሞሉ ናቸው ነገር ግን በቀላሉ ይደክማሉ። የእረፍት ክፍለጊዜዎች ጠቃሚዎች ናቸው።
5. ሁልጊዜ ዕረፍት የሌላቸው እና ቁንጥንጦች ናቸው።
6. ነገሮችን መሰብሰብ እና ስለ እነርሱም ማውራት ይወዳሉ። በእራሳቸው ወይም በቡድን ስለሰሩት ነገሮች ማውራትም ይወዳሉ።
7. የሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው የአትኩሮታቸው ስፋት ያድጋል፣ በዚህ ዕድሜ ያሉ ልጆች ምንም እንኳ ከሃያ እስከ ሃያ አምስት ደቂቃ ቢወስድባቸውም ካስፈለጋቸው አንድን ስራ መፈፀም ይችላሉ። በብዙ ትምህርቶች የተሳትፎ ለውጥ አሁንም ያስፈልጋቸዋል።
8. ከተቃራኒ ፆታ አባላት ጋር በመጠኑ መግባባት ይጀምራሉ።
9. የራሳቸውን መንገድ ለመያዝ ያነሱ እና እውቀት የሚያንሳቸው ይሆናሉ።
10. በአስተሳሰባቸው የበለጠ ራሳቸውን የሚችሉ እና አስተዋዮች ይሆናሉ።
11. የበለጠ ትክክለኛውን እና ስህተቱን ያውቃሉ እናም እነሱ ትክክል ነው ብለው የሚያስቡትን ለማያደርጉ ሰዎች በጣም ተከራካሪ ናቸው።
12. ጥምቀትን በጉጉት ይጠብቃሉ።
13. ብቻቸውን መፀለይ ይችላሉ እናም ሁልጊዜ ለፀሎታቸው ፈጣን መልስን ይጠብቃሉ።
14. በፆም ቀን ቢያንስ ለአንድ የምግብ ሰዓት መፆም በመቻላቸው እና አስራት መክፈል በመቻላቸው በዚህ እውነት ይኮራሉ።

---

**አካለ ስንኩል የሆኑ ልጆችን የሚያጠቃልል ልዩ መምሪያ**

ጌታ አካለ ስንኩል ለሆኑ ሰዎች ርህራሄን በማሳየት እና በመሰማት ምሳሌ አስቀምጦልናል። ከትንሳኤው በኋላ ኔፊዎችን ሲጎበኝም፣ እንዲህ ብሎ ነበር፣

“በመሃከላችሁ የታመሙ አሏችሁን? ወደ እኔ አምጧቸው። ሽባ የሆኑ፣ ወይም የታወሩ፣ ወይም አፋቸው የተያዘ፣ ወይም አካለ ስንኩል፣ ወይም ለምጻም፣ ወይም የሰለሉ፣ ወይም የደነቆሩ ወይም በማንኛውም ነገር የተጎዱ አሏችሁን? ወደ እኔ አምጧቸው እናም እኔ እፈውሳቸዋለሁ፣ ለእናንተ ርህራሔ ስለአለኝ” (3 ኔፊ 17፥7)።

እንደ ጀማሪ ክፍል አስተማሪነትዎ፣ ርህራሔን ለማሳየት በጣም ጥሩ ቦታ ላይ ነዎት። ምንም እንኳ የባለሙያ ዕርዳታ ለመስጠት የሰለጠኑ ባይሆኑም፣ አካለ ስንኩል የሆኑ ልጆችን መርዳት እና ማሳደግ ይችላሉ። በተቻለ መጠን፣ የእያንዳንዱ ክፍል አባል አላማ፣ እውቀት፣ እና የማጠቃለል ፍላጎት፣ በመማሪያ ተሳትፎዎቹ አስፈላጊዎች ናቸው።

አካለ ስንኩል የሆኑ ልጆች የዕውቀታቸው ደረጃ ምንም ያህል ቢሆን በመንፈስ ሊነኩ ይችላሉ። ምንም እንኳ አንዳንድ ልጆች የጀማሪዎችን ክፍል ጊዜ በሙሉ መካፈል ባይችሉም፣ መንፈስ እንዲሰማቸው በአጭሩም ቢሆን የመካፈል ዕድሉ እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል። ለልጁ ፍላጎት የሚሰማውና በጀማሪዎች ክፍል ጊዜ ልጁ ከቡድኑ መራቅ በሚፈልግበት ጊዜ አብሮት የሚሆን ጓደኛ መኖሩ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

አካለ ስንኩል የሆኑ የክፍል አባላት በመማር ችሎታ ማነስ፣ በእውቀት ማነስ፣ በቋንቋ ወይም በመናገር ችግር፣ በማየት ወይም በመስማት ማነስ፣ በባህሪ እና ማህበራዊ ችግር፣ በአእምሮ ህመም፣ በመራመድ እና በመንቀሳቀስ ችግር፣ ወይም ብዙ ጊዜ በሚቆይ በሽታ ድካም ይፈተናሉ። አንዳንዶቹ ቋንቋው እና ባህላዊ ነገሮች ያልተለመዱ እና አስቸጋሪ ሊሆኑባቸው ይችላሉ። ከየግል ሁኔታቸው በተመለከተ፣ እያንዳንዱ ልጅ ለመወደድ እና ተቀባይነትን ለማግኘት፣ ወንጌልን ለመማር፣ መንፈስ እንዲሰማቸው፣ በውጤታማነት ለመሳተፍ፣ እና ሌሎችን ለማገልገል ተመሳሳይ ፍላጎቶችን ይካፈላሉ። የሚከተሉት መምሪያዎች አካለስንኩላን የሆነ ልጅን ሊያስተምሩት ይረዳዎታል።

- ልጁን እወቁ እናም የችሎታውን ማነስ ከበስተጀርባው ይመልከቱ። የምትግባቡ ጓደኛ፣ እና ተስማሚ ሁኑ።
- ስለ ልጁ ልዩ ጥንካሬ እና ስለሚፈትኑት ነገሮች ይወቁ።
- እያንዳንዱን የክፍል አባል ሁሉንም የክፍል አባላት ለማክበር ያላትን ወይም ያለውን ኃላፊነት ለማስተማርና ለማስታወስ ያለውን ጥረት በሙሉ ያድርጉ። አካለ ስንኩል የሆነ አንድ የክፍል አባልዎን መርዳት ለክፍሉ ሁሉ የክርስቶስ አይነት የትምህርት ልምድ ሊሆን ይችላል።
- ልጅን ለማስተማር ቤተሰብን፣ ሌሎች የቤተሰብ አባላትን፣ እና፣ ተገቢ ሲሆን፣ ልጁን በማነጋገር የተሻሉ ዘዴዎችን ይፈልጉ።
- አካለ ስንኩል የሆነን ልጅ እንዲያነብ፣ እንዲፀልይ፣ ወይም ካለበለዚያ እንዲሳተፍ ከመጥራትዎ በፊት፣ በክፍል ውስጥ ስለመሳተፍ የሚሰማትን ወይም የሚሰማውን ይጠይቁ። የእያንዳንዱን ልጅ ችሎታዎች እና ተሰጥዎች አጥብቀው ያሳስቡ እናም እያንዳንዳቸው በምቾትና በደስታ ሊሳተፉ የሚችሉበትን መንገዶች ይፈልጉ።
- የእያንዳንዳቸውን አካለ ስንኩል የሆኑ ልጆችን ፍላጎት ለማሟላት የትምህርት ቁሳቁሶችን እና በአካባቢ ያሉ ነገሮችን እንዲስማሙ ያድርጉ።

አካለ ስንኩል የሆኑ ልጆችን ማስተማሪያ ተጨማሪ ቁሳቁሶች በቤተክርስቲያን ማከፋፈያ ማዕከል ይገኛሉ (“አካለ ስንኩል ለሆኑ ቁሳቁሶች” የሚለውን ከአካባቢዎ የማከፋፈያ ማዕከል ዝርዝር ላይ ይመልከቱ)።

---

**ተገቢ ባልሆኑ አድራጎቶች ችግሮች ላይ መወያየት**

እንደጀማሪ ክፍል አስተማሪነትዎ፣ በክፍልዎ፣ ውስጥ በስሜታዊ ወይም አካላዊ ተገቢ ባልሆኑ አድራጎቶች የሚሰቃዩ ልጆችን ሊያውቁ ይችላሉ። በክፍልዎ ስላለ አንድ ልጅ ካሰቡ፣ ከጳጳስዎ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንትዎ ጋር ይማከሩ። ትምህርት ስታዘጋጁ እና ስታቀርቡ፣ ከጌታ መመሪያን እና አቀጣጫን ለማግኘት ፀልዩ። በክፍልዎ ያሉ እያንዳንዱ ልጅ እሱ ወይም እሷ የሰማይ አባት የከበሩ ልጆች እንደሆኑ እና የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዳችንን እንደሚወዱንና ደስተኛ እንድንሆንና እንድንጠበቅ እንደሚፈልጉ እንዲሰማቸው ይርዷቸው።

# ትክክለኛውን ምረጥ

ትምህርት

1

**ዓላማው** ትክክለኛውን መምረጥ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ሊረዳቸው እንደሚችል ልጆቹ እንዲማሩ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የስም ምልክት ወይም የመለያ ምልክት ፎርም ለእያንዳንዱ ልጅ እና ለእራስዎ ያዘጋጁ። በስም ምልክቱ ላይ ስምዎትን ይጻፉ፣ ነገር ግን በሌሎቹ ላይ ምንም ነገር አይጻፉ።
2. "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ለማንበብ ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ፣* ገፅ 160)፣ ቃላቶቹ በመምሪያው በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
3. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፡
   ሀ. አንድ መጽሃፍ ቅዱስ
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ ከለር ወይም እርሳስ።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ልጅ ማጣበቂያ ወይም ስፒል።
   መ. እያንዳንዱ ልጅ የሚያቀልመው የት.ም. አርማ፣ አርማው በመምሪያው ፊት ለፊት ተጠቃሏል።
   ሠ. ባለፈው ዓመት ላልተቀበሉ ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ የት.ም. ቀለበት።
   ረ. ስዕል 3-1፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ (62133፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 208)።
4. ለምትጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

**ስሜን ማክበር**

የአትኩሮት ተሳትፎ

እራስዎን ለልጆቹ ያስተዋውቁ። ስምዎን ይንገሯቸው፣ እናም የስምዎን ምልክት ያሳዩአቸው።

ለእያንዳንዱ ልጅ የስም ምልክት እና እርሳስ ወይም ከለር ስጡ፣ እናም እያንዳንዱ ልጅ በምልክቱ ላይ የራሱን ወይም የራሷን ስም እንዲጽፉ ያድርጉ። ስማቸውን መጻፍ የማይችሉትን ይርዷቸው። ምልክቶቹን በልጆቹ ልብስ ላይ በማጣበቂያ ወይም በስፒል ያያይዙ።

- ስሞቹ የሚያስፈልጉት ለምንድነው? (ስም አንድን ሰው ከሌሎች መለያ መሆኑን እንዲያውቁ እርዷቸው።)

ልጆቹ የሚያውቋቸውን እና የሚያከብሯቸውን የብዙ ሰዎችን ስሞች፣ ለምሳሌ የወላጆቻቸውን ስሞች፣ የጳጳሱን፣ የአንድ ወንጌላዊን፣ እና የቤተክርስቲያኑን ፕሬዚዳንት ስም የመሳሰሉትን ድምፅዎትን ከፍ አድርገው ይጣሩ። ስለአንዳንድ ስሞች ሲሰሙ ምን እንደሚያስቡና የእነዚያ ስሞች ባለቤት ስለሆኑት ሰዎች ምን እንደሚሰማቸው ይጠይቋቸው። አንድ ስም አንድን ሰው ከሌላው መለየቱን ልጆቹ እንዲያውቁት እርዷቸው፣ አንድ ልጅ የአንድን ሰው ስም ሲያውቅ፣ ስሙን መስማት እና ሰውየው ምን እንደሚመስልና ድርጊቱ ምን እንደሚመስል ማሰብ ይችላል።

እያንዳንዱ ልጅ የራሱን ወይም የራሷን ስም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲጠሩ ያድርጉ።

- ሰዎች ስምዎትን ሲሰሙ ምን እንዲያስቡ ይፈልጋሉ?
- ስምዎት መልካም ነገርን እንዲያመለክት ማድረግ የሚችሉት እንዴት ነው?

ልጆቹ ስለስማቸው ክብር እና ጥሩ ስሜት ሊሰማቸው የሚችሉበትን ብዙ መንገዶች ሃሳብ እንዲያቀርቡ ያድርጉ። የጋራ ስራዎቻቸውን እንደመስራት፣ ፍቀርን ማሳየት፣ ተሑት መሆን፣ ታማኝ መሆን፣ ወላጆቻቸውን መታዘዝ፣ ትዕዛዛትን መታዘዝ፣ እና ህጎችን እና ደንቦችንም እንደ መታዘዝ የመሳሰሉት ናቸው። ትክክለኛውን ስንመርጥ ስለ ራሳችን ጥሩ ስሜት እንደሚሰማን፣ እና ሰዎች ስማችንን ሲሰሙ መልካም ነገሮችን እንደሚያስቡ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

**ትክክለኛውን መምረጥ ስለ ስሜ ጥሩ ስሜት እንዲሰማኝ ይረዳኛል**

ተሳትፎ — ከመምሪያው ፊት ለፊት የት.ም.ን አርማ ያሳዩ።

- ት.ም. የቆመው ለምንድነው? (ትክክለኛውን ምረጥ።)

ትክክለኛውን በመምረጥ፣ ልጆቹ ስለራሳቸው ስም ጥሩ ስሜት እንደሚሰማቸው ይግለጹ። *ትክክለኛውን ምረጥ* የሚሉትን ቃላት ከእርስዎ ጋር እንዲደግሙት ያድርጉ።

ታሪክ — በጣም ጠቃሚ ምርጫ መምረጥ ስለነበረበት አንድ ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፣

ሬንዲ እና ጓደኛው ዳዊት በጎረቤታቸው አጥር ግቢ ውስጥ ይጫወቱ ነበር። የጎረቤታቸው ቤተሰቦች ቤት አልነበሩም፣ እናም ሁለቱ ልጆች በልጆቹ አንዳንድ አሻንጉሊቶች በመጫወት እየተደሰቱ ነበር። በዥዋዥዌው ላይም እርስ በርሳቸው እየተገፋፉ እያለ፣ ተበጠሰና መሬት ላይ ወደቀ። ራንዲ እና ዳዊት ምን እንደሚያደርጉ አያውቁም ነበር፣ ስለዚህም ሮጡ። እዚያም ማንም እንዳላያቸው ተስፋ አደረጉ።

ራንዲ እሱ እና ዳዊት ዥዋዥዌውን በመበጠሳቸው ጥሩ አልተሰማውም ነበር። ስለዚህ ጉዳይም በቀሪው ቀን ብዙ ጊዜ ያስብ ነበር ነገር ግን ምን እንደሚያደርግ መወሰን አልቻለም ነበር። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ ራንዲ ት.ም. ምን ማለት እንደሆነ አስታወሰ። ራንዲ በጀማሪ ክፍል የተማራቸውን ቃላት ተናገራቸው፣ "ትክክለኛውን ምረጥ"፣ ከዚያም ራንዲ ስለጎረቤቶቹ ዥዋዥዌ አሰበ።

በፍጥነት ልብሱን ለበሰና ወደ ጎረቤቶቹ ቤት ሄደ። በራቸውን ለማንኳኳት ትንሽ ፈርቶ ስለነበር ለትንሽ ጊዜ ውጭ ቆመ። በመጨረሻም አንኳኳ።

እናትየው ወደ በሩ ስትመጣ፣ ምን እንደተከሰተ ነገራት። ስለተበጠሰው ዥዋዥዌ ታሪክ ሲናገር፣ አዳመጠችው። ሲጨርስም፣ እጇን በቀስታ ትከሻው ላይ አደረገችና ስሙን ጠየቀችው። ስሙ ራንዲ እንደሆነ ነገራት። ዓይኑን አየችው እና እንዲህ አለች፣ "ራንዲ፣ አንተን በማይበት ጊዜ ወይም ስምህን ሳስብ፣ ታማኝ ስለሆነ አንድ ሰው አስባለሁ።"

- ራንዲ ለማድረግ የመረጠው ምንድን ነበር?
- ራንዲ ያንን ውሳኔ እንዲወስን የረዳው ምንድን ነበር?

ት.ም. የሚለውን አርማ ለልጆቹ ያሳዩ።

- ትክክለኛውን መምረጥ መልካም ስም እንዲኖረው ራንዲን የረዳው እንዴት ነው?

መዝሙር — "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ድምፅዎትን ከፍ አድርገው ከልጆቹ ጋር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ያንብቡ።

**ኢየሱስ ክርስቶስ ትክክለኛውን እንድመርጥ ይፈልጋል**

ውይይት — ስለ ሌላ ስም እያሰቡ እንደሆነ ለልጆቹ ይግለጹላቸው። እርሱም ትክክለኛውን እንዲመርጡ የሚፈልግ የአንድ ሰው ስም ነው። እንደዚህ ያሉትን ፍንጮች ሲሰጧቸው ልጆቹ ማንን እያሰቡ እንደሆነ እንዲገምቱ ያድርጉ—

1. ይወደናል።
2. ትክክለኛውን እንዴት እንደምንመርጥ አስተምሮናል።

የምታስቡት ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ለልጆቹ ንገሯቸው። ሁልጊዜ ትክክለኛውን እንድንመርጥ አስተምሮናል። እሱ በተጠመቀበት ተመሳሳይ መንገድ እንድንጠመቅም አስተምሮናል።

- ኢየሱስ እንዴት እንደተጠመቀ የምታስታውሱት ምንድነው?

የስእል ውይይት

መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ ስዕል 3-1 ያሳዩ። የማቴዎስ ወንጌል 3፥16 የመጀመሪያውን ግማሽ፣ *ከውሃ ወጣ* ከሚሉት ቃላት በኋላ የሚጨርሰውን ድምፅዎትን ከፍ አድርገው አንብቡ። ኢየሱስ የተጠመቀው በመስጠም እንደነበረ፣ ይህም ማለት በውሃ ስር ገብቶ እንደነበረ ይግለጹ።

- የሰማይ አባትና ኢየሱስ እንድትጠመቁ የሚፈልጉት እንዴት ነው? (ልክ እንደ ኢየሱስ፣ በመስጠም።)

ልጆቹ ዕድሚያቸው ስንት እንደሆነ ጠይቋቸው። ልጆቹ ዕድሚያቸው ስምንት ሲሆን፣ ለመጠመቅ ዕድሚያቸው እንደበቃ ያስገንዝቡ። ለራሳቸው ምርጫም ሃላፊዎች ይሆናሉ። በመጠመቅና ትዕዛዛትን በማክበር፣ ትክክለኛውን ይመርጣሉ።

- መጠመቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
- መጠመቅ ትክክለኛውን መንገድ እንደመረጡ የሚያሳየው እንዴት ነው?

ለመጠመቅ ሲመርጡ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆንና ስሙን ለመውሰድ እንደሚመርጡ አስረዱ። የራሳቸው ስም እሱን እንዲወክል ለማድረግ ቃል ይገባሉ። እርሱን ለመምሰል ለመሞከርና እርሱ የሚያደርጋቸውን ነገሮች ለማድረግ ቃል ይገባሉ። ትክክለኛውን በመምረጥ፣ ስለራሳቸው ስም ጥሩ ስሜት እንደሚሰማቸውና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እና የቤተክርስቲያኑን ስም እንደሚያከብሩ እንዲያውቁት ይርዷቸው።

የአስተማሪ ምስክርነት

ሁልጊዜ ትክክለኛውን ስለ መምረጥ አስፈላጊነት ያለዎትን ምስክርነት ለልጆቹ ይስጡ።

መዝሙር እና ቀለበት

ልጆቹ “ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ” የሚለውን መዝሙር፣ ለክፍሉ እንዲዘምሩ ይርዷቸው። ከዚያም ባለፈው ዓመት ላልተቀበለ ለእያንዳንዱ ልጅ የት.ም. ቀለበት ይስጧቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ ሊሰሩ የሚችሉትን ይምረጡ። በእራሱ በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች።” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. እያንዳንዱ ልጅ ትክክለኛውን ስለ መረጠበት ወይም ስለ መረጠችበት ጊዜ እንዲናገሩ እና እርሱ ወይም እርሷ ምርጫውን ከመረጡ በኋላ እንዴት እንደተሰማቸው እንዲያስረዱ ይጋብዙ።
2. እያንዳንዱ ልጅ በዚህ መምሪያ ፊት ለፊት የሚገኘውን የት.ም. አርማ እንዲያቀልሙ ያድርጉ።
3. ልጆቹ ትክክለኛውን መምረጥ የሚችሉበትን መንገድ ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ።
4. ልጆቹ ተራ በመውሰድ ቤተሰቦቻቸው የሚሰጧቸውን የስራ ድርሻ በመስራት ላይ እንዳሉ እንዲያስመስሉ እና ይህ እንዴት ትክክለኛውን መምረጥ እንደሆነ እንዲያስረዱ ያድርጉ።

ትምህርት
2


# የሰማይ አባት እቅዱን እንደምንከተል ይተማመንብናል

**ዓላማው**

የሰማይ አባት እያንዳንዱ ልጅ ትክክለኛውን እንደሚመርጥ ወይም እንደምትመርጥ እንደሚተማመንባቸው እንዲረዱት ለመርዳት ነው።

### ዝግጅት

1. አብርሃም 3፥22–28 ያጥኑ።
2. እንደተመለከተው አንድ ለእራስዎት እና ለእያንዳንዱ ልጅ የመለያ ምልክት ያዘጋጁ፥




በመለያ ምልክትዎ መሃከል፣ ት.ም. የሚሉትን ፊደላት ይጻፉ።

3. “ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ” የሚለውን መዝሙር ሁለተኛ ቁጥር ለማስተማር ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 160)፤ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ልጅ ከለር ወይም እርሳስ።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ መለያ ምልክት ማጣበቂያ ወይም ስፒል።
   ሐ. በመምሪያው ፊት ለፊት የት.ም. አርማ።
   መ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ (ወይም ሌላ የመጻፊያ ገጽ)።
   ሠ. ስዕል 3-2፣ የሰማይ አባት ዕቅዱን ሰጥቶናል።
5. ለሚጠቀሙባቸው ለማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው፣ ይከታተሏቸው።

### የታላቁ ንጉስ ልጆች ነን

የአትክሮት ተሳትፎ

ስለ ታላቁ ንጉስ ወንድ ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

አንድ ጊዜ፣ ልዑል፣ ወንድ ልጁ፣ የተያዘበትና ከቤቱ ርቀ የተወሰደበት አንድ ንጉስ ነበር።

ማራኪዎቹ ልዑሉን ስህተት እንዲሰራ ሊያስገድዱት ሞከሩ። በአካባቢው ላሉ ሰዎች ደግ ያለመሆንን ሊያስተምሩት ሞከሩ። መጥፎ ቋንቋዎችን ይጠቀሙ ነበር እናም መሃላ እንዲምል ሊያደርጉት ሞከሩ። እንዲዋሽ፣ እንዲያታልል፣ እና እንዲሰርቀ ሊያስገድዱት ሞከሩ። ለጤንነቱ መልካም ያልሆኑ ምግቦችን እና መጠጦችን እንኳን እንዲወስድ ሊያስገድዱት ሞከሩ። ነገር ግን ልዑሉ አንድም ጊዜ ማንኛውንም እነዚህ መጥፎ ነገሮችን አላደረገም። በመጨረሻም፣ ከስድስት ወር ከዚህ አሳዛኝ ምርኮ በኋላ፣ ማራኪዎቹ ልዑሉን "እኛ እንድታደርግ የምንፈልገውን የማታደርገው ለምንድነው?" ብለው ጠየቁት፣

እርሱም፣ "የንጉስ ልጅ ስለሆንኩ፣ እና አባቴ ትክክለኛ የሆነውን እንዳደርግ ስላስተማረኝ እናንተ የምትጠይቁኝን ላደርግ አልችልም። የተወለድኩት ንጉስ እንድሆን ነው፣" በማለት መለሰላቸው።

ውይይት

ልዑሉ የንጉስ ልጅ እንደሆነ እና እርሱም እራሱ ሲያድግ ንጉስ መሆን እንደሚጠበቅበት ያውቀ እንደነበር ያስረዱ።

የንጉሱ ልጅ ዛሬ በክፍል ውስጥ እንደሚገኝ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ግጥም

የዚህ ታላቀ ንጉስ ልጅ ማን እንደሆነ ለማግኘት ግጥሙን እንዲያዳምጡ ልጆቹን ይጠይቁ። የሚከተለውን ግጥም ያንብቡ ወይም ከልጆቹ አንዱ እንዲያነብ ያድርጉ፥

"የንጉሳዊ ትውልድ ልጅ ነኝ።
አባቴ የሰማይና የምድር ንጉስ ነው።
መንፈሴ የተወለደው በላይኛው ቤተመንግስት ነው።
ተወዳጁ ልጅ ልዕልት (ወይም ልዑል) እኔ ነኝ"
(ሉና ጆንሰን፣ "የንጉሳዊ ትውልድ ልጅ ነኝ፣" *Children's Friend*፣ ጥቅምት 1959፣ ገፅ 29)።

- የንጉሳዊ ትውልድ ልጅ ማነው? (እያንዳንዳችን።)
- ንጉሱ ማነው? (የሰማይ አባት።)

በክፍል ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ሰው ልዑል ወይም ልዕልት እንደሆኑ ልጆቹ እንዲረዱት ይርዷቸው። ሁላችንም ከነገስታት ሁሉ የታላቁ ንጉስ፣ የሚወደን የሰማይ አባታችን ልጆች ነን። ልክ በታሪኩ ላይ ያለው ልዑል እንዳደረገው፣ ትክክለኛ የሆነውን እንድናደርግ ይፈልጋል።

**የሰማዩ አባት ይተማመንብናል**

የጥቁር ሰሌዳ ተሳትፎ

*እምነት* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ።

- *እምነት* ማለት ምን ማለት ነው?

ልጆቹ እንዲመልሱ ይፍቀዱላቸው።

ታሪክ

- በጣም ጨለማ ባለበት ቦታ ሆነህ ታውቃለህን?

የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

ሱዛን ዕድሜዋ ዘጠኝ ሲሆን፣ አባቷ ከቤታቸው አጠገብ ወደአለው አንድ ዋሻ ለምርምር ወሰዳት። ዋሻው ውስጥ ሲገቡ፣ ጨለማና አዲስ ነገር ስለነበር ሱዛን ትንሽ ፈርታ ነበር። አባቷ እጇን በመያዝና ወደ ውስጥ ሲጓዙ ከእርሷ ጋር በመነጋገር ፍርሃቷን እንድታረጋጋ ረዳት። በእጆቿ ግድግዳዎቹን መዳሰስ እና በወጣገባው መሬት ላይ እግሮቿን ማንሸራተት አስተማራት።

ቀስ በቀስ በዋሻው ውስጥ በጨለማ መንገዳቸውን አጋመሱ። ሱዛን ፈርታ ነበር እናም አንዳንድ ጊዜ ወደ ኋላ ለመመለስ ትፈልግ ነበር፣ ነገር ግን አባቷ ሁልጊዜ ከአጠገቧ ይሆንና ወደፊት እንድትሔድ ያበረታታት ነበር።

ወዲያውም ሱዛን ከፊት ለፊቷ ከላይ ብርሃን አየች። እሱም የዋሻው ሌላኛው መጨረሻ መውጫ ክፍል ነው። በድፍረት ተሞልታ፣ በፍጥነት ወደ መውጫው ተራመደች እናም ስላደረገችው ታላቀ ኩራት ተሰማት። አባቷም ፈገግ አለ። ከዚያም በዋሻው ውስጥ ጉዞውን ብቻዋን ተመልሳ ማድረግ የምትችል እንደሆነ ሱዛንን ጠየቃት። ሱዛን ብቻዋን ተመልሳ መሄድ

በሚለው ሃሳብ ትንሽ ፈርታ ነበር ነገር ግን ለመሄድ ፈቃደኛ ነበረች። የሱዛን አባትም በዋሻው መንገድ ውስጥ ምንም እንደማትሆንና ብቻዋን ለማድረግ በችሎታዋ ታላቅ እምነት እንዳለው ገለፀላት። በዋሻው መንገድ ሌላኛው መጨረሻ ላይ እንደሚጠብቃትም አረጋገጠላት።

ሱዛን ልክ አባቷ እንዳስተማራት፣ ግድግዳዎቹን በእጆቿ እና መሬቱን በእግሮቿ እየዳሰሰች፣ ረጋ ባለ ጥንቁቅ አረማመድ ወደ ዋሻው ውስጥ ተመልሳ ገባች። ሱዛን ወደ ዋሻው ሌላኛው መጨረሻ በቀስታ ስትቃረብ አዲስ ደስታ ተሰማት። ወደ ዋሻው ሌላኛው መጨረሻ ወደ ፀሃይ ብርሃኑ ስትወጣ እናም አባቷ እጁን ዘርግቶ ሲጠብቃት በጣም ተደሰተች።

ልክ ሱዛንን አባቷ በዋሻው ውስጥ መንገዷን እንዴት እንደምታገኝ እንዳስተማራት፣ የሰማዩ አባትም በሕይወት ውስጥ እንዴት መንገዳችንን እንደምናገኝና ወደ እርሱ እንደምንመለስ እንደሚያስተምረን ለልጆቹ ይንገሯቸው። የሱዛን አባት ብቻዋን ወደ ዋሻው ውስጥ እንድትመለስ ሲልካት፣ መውጪያ መንገዷን ለማግኘት ግድግዳዎቹንና መሬቱን እንደምትዳስሳቸው ይተማመንባት ነበር። የሰማዩ አባታችንም ወደ እርሱ የሚመልሰንን መንገድ ማግኘት እንድንችል ትክክለኛ ምርጫዎችን እንደምንመርጥ ይተማመንብናል። ወደ እርሱ እንድንመለስም እየጠበቀን ነው።

ውይይት

- ወደ ምድር ከመምጣታችን በፊት የት ነበርን? (ከሰማይ አባታችን ጋር እንኖር ነበር፣ አብርሃም 3፥22–23 ይመልከቱ።)

የሰማዩን አባት እንደምንወደውና፣ እርሱም እንደሚወደን እንደምናውቅ ይግለጹ። እዚያ ደስተኞች ነበርን። የሰማይ አባት እርሱን እንድንመስል እንደሚፈልግና ይህንን ግብ እንድናከናውን እኛን ለመርዳት ዕቅድ እንዳለው ነግሮናል።

ስዕል

የሰማዩ አባት ዕቅዱን ሲሰጠን የሚለውን ስዕል 3-2 ያሳዩ፣ እናም ኢየሱስ በዚያ ከእኛ ጋር እንደነበር ይጠቁሙ። ሁላችንም እዚያ አንድ ላይ ነበርን።

የሰማዩ አባት ዕቅድ ምድርን ለእኛ መፍጠሩንም ያጠቃልላል። በምድር ላይ በትክክለኛውና በስህተት መካከል ያለውን ልዩነት እንማራለን እናም ለእራሳችን የምንሰራውን እንመርጣለን። የሰማይ አባታችን እንደምንሳሳት ያውቃል። ነገር ግን እነሱን እንድንቋቋም እንዲረዳን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮታል። (አብርሃም 3፥24–27 ይመልከቱ።)

የሰማዩ አባት ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲረዳን የመረጠበት ምክንያት እርሱ ታዛዥና የሰማዩ አባትን ዕቅድ ለመከተል ስለፈለገ እንደሆነ ይግለጹ። የሰማዩ አባታችን ይህን ምድር ለእኛ እንዲፈጥርልንም መርጦታል።

ሉሲፈር የሚባል ሌላ ወንድም ነበረን። ከሰማዩ አባታችን ይልቅ እርሱን እንድንከተለው ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ሉሲፈርን መከተሉ ለእኛ ጥሩ አይሆንም ነበር። የሰማዩ አባት ይህን ያውቅ ነበር እናም እቅዱን እንዲያሳካ ኢየሱስን መረጠው። ያም ሉሲፈርን በጣም አናደደው። (አብርሃም 3፥27–28 ይመልከቱ።)

- ሉሲፈር ያደረገው ምንድን ነበር? (ከሰማዩ አባት ይልቅ ብዙ ሰዎች እርሱን እንዲከተሉት አሳመናቸው።
- እኛ ለመከተል የመረጥነው ማንን ነበር? (የሰማይ አባትን እና ኢየሱስን። አካልን የሚቀበሉት የሰማዩን አባትን እና ኢየሱስን ለመከተል የመረጡት ብቻ እንደሆኑ ያስረዱ። ሉሲፈርን ለመከተል የመረጡት አካልን አያገኙም።)
- በሉሲፈር ላይ ምን ተከሰተ? (ከሰማይ ተጣለ እናም ሰይጣን ወይም ዲያቢሎስ በመባል ይታወቃል። ስህተት እንድንሰራ ሊፈትነን ይሞክራል። ልክ ከሰማዩ አባት ጋር ሁላችንም ስንኖር እንዳደረገው አሁንም ከሰማዩ አባት እና ከኢየሱስ፣ ይልቅ እርሱን እንድንከተል ሊያጠምደን እንደሚሞክር ያስረዱ።)

የሰማዩን አባት እና ኢየሱስን መከተልን መምረጥ ትክክለኛ ምርጫ እንደነበረና የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ በውሳኔያችን ደስተኞች እንደነበሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው። የሰማዩ አባት ከእርሱ ጋር ለመኖር መመለስ እንድንችል እዚህ ምድር ላይ የእርሱን ዕቅድ መከተልን እንድንመርጥ ይፈልጋል።

**ትክክለኛውን በመምረጥ የሰማዩን አባት ዕቅድ መከተል እንችላለን**

ጨዋታ

ዘወትር ትክክለኛውን ለመምረጥ ብዙ መንገዶች እንዳሉ ለልጆቹ ያስረዱ። “የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?” የሚለውን ጨዋታ እንዲጫወቱ ይርዷቸው።

ከሚከተሉት ጥያቄዎች አንዱን እንዲመልሱ ለእያንዳንዱ ልጅ ተራ ይስጡ። አስፈላጊ ከሆነ እያንዳንዱ ልጅ የሚያደርገውን ወይም የምታደርገውን የመምረጥ ዕድል እንዲኖራቸው ተጨማሪ ጥያቄዎችን ይጨምሩ። ጥያቄዎቹን ለክፍልዎ ተገቢ እንዲሆኑ ያድርጉ።

1. አንድ ምሽት በጣም ቢደክመኝ እና ፀሎቴን ሳልፀልይ ወደ መኝታ ለመሄድ ብፈልግ የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?
2. እናቴን እደምረዳት ቃል ብገባላት፣ ነገር ግን ጓደኛዬ መጥቶ በምትኩ እንድጫወት ቢጠይቀኝ የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?
3. የሌላ ሰው የሆነ ነገር ባገኝ የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?
4. ጓደኛዬ የሚወዳትን መጫወቻ በድንገት ብሰብር የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?
5. ለእናቴ በተወሰነ ሰዓት ቤት እንደምገኝ ቃል ብገባላት የሰማዩ አባት እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድነው?

መዝሙርና ውይይት

“ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ” የሚለው ሁለተኛው ቁጥር ትክክለኛውን መምረጥ የምንችልበትን አንዳንድ መንገዶችን እንደሚገልጽ እና የሰማዩ አባት በእኛ እንዲተማመንብን ብቁ መሆናችንን እንደሚያሳይ ለልጆቹ ይንገሩ። የቁጥር ሁለትን ቃሎች ስትደግሙት እንዲያዳምጡ ያድርጉ።

- ትክክለኛውን ለመምረጥ ማድረግ የምንችለውን መዝሙሩ የሚነግረን ምንድነው? (ፀሎት፣ እምነት መኖር፣ ንሰሃ፣ እና መታዘዝ።)

እነዚህን ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይጻፏቸው። ለህፃናት ልጆች፣ ቃላቶቹን ድምፅዎን ከፍ አድርገው ይበሉ እናም እነርሱም ቃላቶቹን ከእርሶ ጋር እንዲደግሙት ያድርጉ። እነዚህ ቃላት ምን ማለት እንደሆኑ ልጆቹን ይጠይቋቸው። እንደአስፈላጊነቱ በሀሳባቸው ላይ አስፉት፣

1. *ፀሎት* ማለት የሰማዩን አባት ማነጋገር ነው። ስለ ሰጠዎት በረከት ሁሉ ማመስገን፣ እና ትክክለኛውን ለመምረጥ እንዲረዳዎት መጠየቅ ማለት ነው።
2. *እምነት* መኖር ማለት የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዱዎት እና እንደሚረዱዎት ማመን ማለት ነው።
3. *ንስሃ* ስህተት ለሰሩት ለማንኛውም ነገር ማዘን፣ የሰማዩ አባት ይቀር እንዲልዎ መጠየቅ፣ እና እንደገናም ያለመስራት ማለት ነው።
4. *መታዘዝ* ማለት የሰማይ አባት እንድንሰራ የጠየቀንን መስራት ማለት ነው።

- የኢየሱስን ትምህርቶች የምናከብር ከሆነ ምን እንሆናለን ነው የሚለው መዝሙሩ? (ደስተኞች እንሆናለን።)

ቃላቶቹን ብዙ ጊዜ በመደጋገም እንዲማሯቸው ልጆቹን ይርዷቸው። ከዚያም መዝሙሩን ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ። ልጆቹዎ ከተማሯቸው በኋላ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ያሉትን ቃላት ማጥፋት ይፈልጉ ይሆናል።

**ማጠቃለያ**

የመለያ ምልክት

መፃፍ የሚችሉ ከሆነ ለእያንዳንዱ ልጅ የወረቀት መለያ ምልክት እና ከለር ወይም እርሳስ ይስጡ። “የሰማዩ አባት እኔንም ይተማመንብኛል—” የሚሉትን ቃላት ድምፅዎን ከፍ አድርገው በሉ።

- የሰማዩ አባት ምን እንድናደርግ ነው የሚተማመንብን? (መልካሙን እንድንመርጥ።)

ልጆቹ አድሚያቸው ስምንት ሲሆን፣ ለመጠመቀ መምረጥ እንደሚችሉ እንዲያውቁት ይርዷቸው ምክንያቱም ትክክለኛውን ከስህተቱ ለይቶ ለማወቅ ይደርሳሉ። የሰማዩ አባትም ትክክለኛውን እንደሚመርጡ ይተማመንባቸዋል።

በመምሪያው ፊት ለፊት የሚገኘውን የት.ም. አርማ ለልጆቹ ያሳዩአቸው። በቀለበታቸው ላይ ያሉትን የት.ም. ፊደሎችን ልታስታውሳቸውም ይፈልጉ ይሆናል።

አንድ ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ ለ"ትክክለኛውን ምረጥ" የቀሙትን ቃላት በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲፅፍ ያድርጉ። ልጆቹ የመለያ ምልክትዎን ከፊደሎቹ ጋር በመሃከል እንዲመለከቱ ያድርጉ። የሚችሉ ከሆነ ፊደሎቹን በራሳቸው የመለያ ምልክት ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ እናም መለያ ምልክቱን በልብሳቸው ላይ ለማያያዝ ይርዷቸው።

ምስክርነት

በክፍል ውስጥ ያሉት ልጆች በሙሉ የሰማይ አባት ልጆች እንደሆኑ ምስክርነት ይስጡ። ከምድር ካለ ከማንኛውም ንጉስ የበለጠ ኃያል ነው። የሰማይ አባት እያንዳንዳቸው ትክክለኛ የሆነውን እንደሚሰሩ ይተማመንባቸዋል ስለዚህም ከእርሱ ጋር እንደገና ለመኖር መመለስ ይችላሉ።

የመዝጊያ ፀሎት የሚሰጠው ልጅ ትክክል እንደምንሰራ ለሚተማመንብን ለሚወደን የሰማዩ አባት ምስጋና እንዲሰጥ ሃሳብ ያቀርቡ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርት ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪ መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. ለልጆቹ ለጥቂት ጊዜ ከክፍል ውጪ እንደሚወጡ፣ ነገር ግን ከማድረግዎ በፊት፣ በእያንዳንዱ ልጅ ጆሮ አንዳንድ መመሪያዎችን ያንሾካሽኩ ይንገሯቸው። እነዚህ መመሪያዎች የሰማዩ አባታቸውን የሚያስደስተውን ነገር እንደሚነግሯቸው ልጆቹ እንዲያውቁ ያድርጉ። የሚፈልጉዎት ከሆነ፣ በቀርብ እንደሚገኙ ይንገሯቸው። መመሪያዎችዎን ከተከተሉ ደስተኛ እንደሚሆኑ ይንገሯቸው።

   ለእያንዳንዱ ልጅ ተመሳሳይ መመሪያዎችን ቀስብለው ይንገሩ፣ "እጅህን አጣምር፣ አይንህን ጨፍን፣ እናም ስለ ሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ አስብ።"

   ክፍሉን ለቀው በሩ አጠገብ ይቁሙ። ለጥቂት ሴኮንዶች በዚያ ይቆዩ። ወደ ክፍሉ ሲመለሱም፣ መመሪያዎችዎን የተከተሉትን ልጆች አመስግኗቸው። የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ መመሪያዎችን እንደሰጡን፣ እናም እንድንከተላቸው እንደሚፈልጉ ይግለጹ። ይህን ካደረግን፣ አንድ ቀን በሰላም ወደ እነርሱ እንመለሳለን።

2. እያንዳንዱ ልጅ የሰማዩን አባት ዕቀድ ለመከተል ማድረግ የሚችሉትን ነገር ስዕል እንዲስሉና እንዲያቀልሙ ያድርጉ።

# ትዕዛዛቶች ትክክለኛውን እንድንመርጥ ይረዱናል

**ዓላማው** የሰማዩ አባት ትዕዛዛትን የሰጠን ትክክለኛ ምርጫዎችን እንድንመርጥ ሊረዳን እንደሆነ እያንዳንዱ ልጅ እንዲያውቀው ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ሞዛያ 2፥22 በፀሎት መንፈስ ያጥኑ።
2. ለእያንዳንዱ ልጅ "የትዕዛዛት መንገድ ምልክቶች" የሚል የሚታደል ፅሁፍ ግልባጭ ያዘጋጁ (በትምህርቱ መጨረሻ ተጽፏል)። ተጨማሪ ግልባጮችን ስሩ እና በቁራጭ ካርቶን ላይ ያጣብቁት። በሚታደል ጽሑፉ ላይ የተዘረዘሩትን ጥቀሶች ያንብቡና የያዙትን ማንኛውንም አስቸጋሪ ቃላት ለማስረዳት ይዘጋጁ።
3. ልጆቹ ፍንጮችን፣ ምልክቶችን፣ ወይም የተደበቀውን ዕቃ ወደሚያገኙበት መንገድ የሚያመለክት ቁራጭ ወረቀት እንዲከተሉ የሚፈቅድላቸውን ቀላል ዕቃ የመደበቅ ጨዋታ ያቅዱ። የተደበቀው ዕቃ የመጽሐፈ ሞርሞን ቅጂ፣ የስዕል፣ ወይም የት.ም. ቀለበት ሊሆን ይችላል።
4. "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 160)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል። "ትዕዛዛትን ጠብቅ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመርም ይዘጋጁ" (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 146)።
5. የሚያስፈልጉ መሠሪያዎች፥
   ሀ. ማንበብ ለሚችል ለእያንዳንዱ ልጅ አንድ የመጽሐፈ ሞርሞን ቅጂ። በክፍልህ ውስጥ ማንበብ የሚችሉ ልጆች በዚህ ትምህርት ላይ እንዲረዱ ያድርጉ።
   ለ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ እና ማጥፊያ (ወይም ሌላ መፃፊያ ገፅ)።
   ሐ. ስዕል 3-3፣ ቀድመ ምድር ህይወት፣ ስዕል 3-4፣ አንድ ወንድ ልጅ እና የእግር ኳስ መጫወቻ ኳሱ።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ያበረታታችኋቸው ከሆነ ይከታተሏቸው።

**ትዕዛዛት ትክክለኛውን እንድንመርጥ ይረዱናል**

የአትኩሮት ተሳትፎ — ያዘጋጁትን ፍንጭ በመጠቀም ልጆቹ የተደበቀውን ዕቃ እንዲፈልጉ ይፍቀዱላቸው።

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ — ልጆቹ አንዳንድ ጠቃሚ ወረቀቶችን እንዲያመጡልዎት ወደ አንድ ሰው ቤት እንደላኳቸው እንዲገምቱ ያድርጉ። ሰውየው ርቀ እንደሚኖር እና መንገዱን እንዲያገኙ ለመርዳት ማንም ሰው ከልጆቹ ጋር መሔድ እንደማይችል ያስረዷቸው።

- ወደቤት የሚወስደውን መንገድ ለማግኘት የሚረዳዎት ምንድነው?
- መንገዱ ቀስትና ምልክት ከተደረገበት፣ መንገድዎን ማግኘት ይችላሉን? የሰማይ አባት ወደ ምድር ሲልከን፣ ጠቃሚ ወደ ሆነ ቦታ እንደላከን ለልጆቹ ይንገሯቸው። ወደ እርሱ የሚመልሰንን መንገድ እንድናገኝም ይፈልጋል።

**ስዕል**

የቅድመ ምድር ሕይወት ስዕል 3-3፣ ለክፍሉ ያሳዩ።

- ከመወለዳችን በፊት እንኖር የነበረው የት ነበር? (ከሰማዩ አባት ጋር።)
- ወደ ምድር የሰማዩን አባት ትተነው የመጣነው ለምንድነው?

የሰማዩን አባትን ትተን የመጣነው አካልን መቀበል እንድንችል፣ ልምድ እንዲኖረንና፣ ትክክለኛውን መምረጥ እንድንማር እንደሆነ ለልጆቹ ይግለጹ።

**የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ**

የሰማዩ አባት እርሱን እንድንተው እና በዚህ ምድር ላይ እንድንኖር ሲያቀድ፣ ሁላችንም ወደ እርሱ እንድንመለስና እንደገና ከእርሱ ጋር እንድንኖር እንደፈለገ ይግለጹ። ወደ እርሱ ለመመለስ ትክክለኛ ምርጫዎችን መምረጥ እንዳለብንና ትክክለኛውን መምረጥ ደስተኞች እንደሚያደርገን ያውቅ ነበር።

ትክክለኛ ምርጫዎችን ለመምረጥ እንዲረዱን ትዕዛዛትን ሰጠን።

- ትዕዛዛት ምንድናቸው? (የሰማይ አባት እንድናደርጋቸው የነገረን ነገሮች ናቸው።)
- አንዳንዶቹ ትዕዛዛት ምንድናቸው?

ትዕዛዛት መንገዳችንን ለማግኘት እንደሚረዱን የመንገድ ላይ ምልክቶች እንደሆኑ ይግለጹ። ወደ ሰማዩ አባት ለመመለስ የምንከተለውን ትክክለኛ መንገድ ያሳዩናል።

**መዝሙር**

"ትዕዛዛትን ጠብቅ" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃሎቹን በሉ፥

ትዕዛዛትን ጠብቅ፣ ትዕዛዛትን ጠብቅ!
በዚህ ጥበቃ አለ፣ በዚህ ሰላም አለ።
በረከትን ይልካል፣ በረከትን ይልካል።
ትዕዛዛትን ጠብቅ፥ የነብዩ ቃል።
በዚህ ጥበቃና ሰላም አለ።

**ተሳትፎ**

"ትዕዛዛት የመንገድ ላይ ምልክቶች" የሚለውን ያዘጋጁትን ሰንጠረዥ ያሳዩ። በመንገድ ምልክቶች ላይ ስላሉት እያንዳንዱ ጥቀሶች ወይም ፅሁፎች በአጭሩ ያንብቡት ወይም አንድ ነገር ተናገሩ። እርሶ አንድ ሁኔታን እንደሚገልጹ እናም ልጆቹ ከመንገድ ላይ ምልክቱ የትኛው ትዕዛዝ ትክክለኛውን እንዲመርጡ እንደሚረዳቸው እንደሚወስኑ ያስረዱ። ልጆቹ ሊረዱት አስቸጋሪ የሆነውን ማንኛውንም ቃላት ያስረዱ። ትክክለኛውን መንገድ የሚያሳዩትን የተለያዩ ትዕዛዛት ለመጠቀም ልጆቹ ተራ እንዲይዙ ያድርጉ።

የሚከተሉት በሀሳቡ የቀረቡ ሁኔታዎች ናቸው፥

1. ሌላኛው ጓደኛህ ሲያገኝህ ከጓደኛህ ቤት ወደ ቤትህ እየሄድክ ነው። ለመጫወት ወደ እርሱ ቤት እንድትመጣ ጠየቀህ። ነገር ግን እናትህ በቀጥታ ወደ ቤት እንድትመጣ ጠይቃዛለች፣ እናም እንደምትመጣ ቃል ገብተሃል። ጓደኛህም ትንሽ ዘግይቶ ቤት መድረስ ምንም እንደማይጎዳ ይነግርሃል። የትኛው ትዕዛዝ ነው ትክክለኛውን እንድትመርጥ የሚረዳህ?
2. ወላጆችህ ተጨማሪ ስራ በመስራት ኳስ ለመግዛት ብር እያጠራቀምክ ነው። መደብሩ የሚሸጥ ኳስ አለው፣ ነገር ግን ከአስራትህ ካልተበደርክ በስተቀር አሁንም በቂ ገንዘብ የለህም። ትክክለኛውን ለመምረጥ የሚረዳህ ትዕዛዝ የትኛው ነው?
3. መሽቷል እናም ቤተሰቦችህ ገና ቤት መመለሳቸው ነው። ደክሞሃል እናም ወደመኝታ መሄድ ፈልገሃል። ከዚያም ሁሉም ወደ መኝታቸው ከመሄዳቸው በፊት ፀሎት መፀለዩን ቤተሰቦችህ እንደረሱት አስታወስክ። ትክክለኛውን ለመምረጥ የሚረዳህ ትዕዛዝ የትኛው ነው?
4. በጣም ጥሩ ጓደኛህ በሰንበት ወደ ፊልም ቤት እንድትሄዱ ይጋብዝሃል። ያንን ፊልም ለማየት ለብዙ ጊዜ ፈልገህ ነበር። ትክክለኛውን ለመምረጥ የሚረዳህ ትዕዛዝ የትኛው ነው?
5. ከጓደኞችህ ጋር እየተጫወትክ ነው። መጥፎ ነገሮችን የተናገረህ አንድ ልጅ ይመጣና እሱም መጫወት ይፈልጋል። ትክክለኛውን እንድትመርጥ የሚረዳህ ትዕዛዝ የትኛው ነው?

6. ከጥቂት ጓደኞችህ ጋር ነህ እናም አንዳንዶቹ አንዳቸው ከቤት ያመጡትን ጥቂት የአልኮል መጠጥ እንድትጠጣ ይፈልጋሉ። አልኮልን መጠጣት ስህተት እንደሆነ ወላጆችህ አስተምረውሃል። ትክክለኛውን እንድትመርጥ የሚረዳህ ትዕዛዝ የትኛው ነው?

ስለ መልካም መልሳቸው ልጆቹን ያመስግኗቸው።

**ትክክለኛውን ስንመርጥ፣ ጥሩ ስሜት ይሰማናል**

ውይይት

ትክክለኛውን መምረጥ ጥሩ ስሜት እንደሚሰጣቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ተጨማሪ ጥያቄዎችን በመጠየቀ እነዚህን ሁኔታዎችን ይከልሱ። ለምሳሌ፣ የሚከተሉት ጥያቄዎች እና ውይይቶች ከመጀመሪያው ሁለት ተሳተፎዎች ሊመጡ ይችላሉ።

1. እናትህ ከጓደኞችህ ጋር ለመጫወት በመሄድ ፈንታ ወደቤት እንድትሄድ ስለጠየቀችህ ብትሄድ ምን የሚሰማህ ይመስልሃል?

   ከጓደኞችህ ጋር በመጫወት እየተደሰትክ ይሆናል። ነገር ግን እየተጫወትክ እያለህ እንኳን፣ ለእናትህ የገባኸውን ቃል ስለማፍረስህ ደስተኛ ያለመሆን ስሜት ሊኖርህ ይችላል። ምንም እንኳ ትክክለኛውን መምረጥና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድታደርግ የጠየቀህን መስራት ከባድ ቢሆንም፣ በማንኛውም ሁኔታ ካደረግከው፣ በውስጥህ ጥሩ ስሜት ይሰማሃል። ስለመረጥከው ምርጫም ስለራስህ ጥሩ ስሜት ይሰማሃል።

2. ከአስራት ገንዘብህ ጥቂቱን በመጠቀም አዲስ ኳስ ብትገዛ ምን የሚሰማህ ይመስልሀል? በኳሱ ስትጫወት ጥሩ ስሜት ይሰማሃልን?

   ከጓደኞችህ ጋር በመጫወትህ ትደሰት ይሆናል፣ ነገር ግን የሰማዩ አባት እንዳዘዘው አስራትህን ለመክፈል ስላልመረጥክ ስለራስህ ጥሩ ስሜት አይሰማህም።

ሌሎቹን ሁኔታዎች በተመሳሳይ መንገድ ይከልሷቸው። ልጆቹ የጌታን ትዕዛዛት ሲታዘዙ—በተለይ ለመታዘዝ አስቸጋሪ በሚመስልበት ጊዜ በውስጣቸው የሚሰማቸውን ጥሩ ስሜት አጥብቀው ያሳስቡ። ያ ጥሩ ስሜት መንፈስ ቅዱስ የሰማዩ አባት በድርጊታቸው እንዲደሰቱ ሲነግራቸው እንደሆነ ይግለጹላቸው።

የተሳሳቱ ምርጫዎችን ሲመርጡ የሚኖራቸውን ስሜት ለልጆቹ ያስታውሷቸው። አብዛኛውን ጊዜ የባዶነት፣ ያለመደሰት ስሜት ነው። ይህም ስሜት መንፈስ ቅዱስ ንስኃ እንድንገባና ትክክለኛ ምርጫዎችን እንድንመርጥ ሲነግረን ሊሆን ይችላል።

ስዕል እና ታሪክ

ወንድ ልጅ እና የእግር ኳስ መጫወቻ የሚያሳየውን ስዕል 3-4ን፣ ያሳዩ።

ትክክለኛውን መምረጥ ጁሊዮን እንዴት እንዲሰማው እንዳደረገው ለማየት ልጆቹ ታሪኩን እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣

የጁሊዮ አክስት ማሪያ የእግር ኳስ መጫወቻ ኳስ ስትሰጠው፣ የራሱ እንደሆነ ማመን አልቻለም። አክስቱ ማሪያ ብዙ ገንዘብ እንደሌላት ያውቃል። ነገር ግን ኳሱን ባይወስድ መጥፎ ስሜት እንደሚሰማት ጁሊዮ ያውቅ ነበር።

“አመሰግናለሁ፣” አለ በለስላሳ ድምፅ። “ነገር ግን ለምንድነው ለእኔ የሰጠሽኝ?”

አክስቱ ማሪያም “ምክንያቱም በጣም ስለረዳኸኝ ነው፣” አለች። ለእኔ ጠቃሚ አገልግሎትን አድርገሃል የአጥር ጊቢዬንም በማጽዳት ረድተኸኛል። የምጠየቀው ነገር ቢኖር ለምን ያንተ እንደሆነ ሁልጊዜ እንድታስታውስ ብቻ ነው። አሁን ሂድ ተጫወት።”

ጁሊዮ በእግር መንገዱ ኳሱን እፊት ለፊቱ እየመታ ሲሄድ፣ አክስት ማሪያ ስላለችው ነገር ተገረመ። “ለምን ያንተ እንደሆነ አስታውስ፣” ነበር ያለችው።

ጁሊዮ እግር ኳስ መጫወት ይወዳል፣ እናም ጎበዝ ነበር። አንድ ቀን ለብራዚል ብሔራዊ ቡድን ለመጫወት ተስፋ ያደርጋል። *አክስት ማሪያ ያንን ታውቃለች*፣ ምናልባት ለዚያ ይሆናል ኳስ የሰጠችኝ፣ ብሎ አሰበ።

ወዲያው፣ አንቶኒዮ ከጁሊዮ ጋር ለመጫወት ወጣ። ብዙም ሳይቆይ፣ ሌሎች ልጆች እነሱን ተቀላቀሏቸው፣ እናም ከትንሽ ጊዜ በኋላ የእግር ኳስ ጨዋታን ለመጀመር በቂ ልጆች ነበሩ።

ጁሊዮ አንድ ዕድሚው ትንሽ የሆነ ወንድ ልጅ ከእግር መንገድ ሆኖ እግር ኳስ ጨዋታውን ሲመለከት ተመለከተው። “እንዴ፣ አይሆንም!”፣ “ፓውሎ እየመጣ ነው አለ አንቶኒዮ። እንዲጫወት አትፍቀድለት! እሱ ሁልጊዜ ጨዋታ ያበላሻል። እሱ የሚጫወት ከሆነ እንሸነፋለን!” በማለት ለጁሊዮ አንሾካሾከለት።

ፓውሎ ጎበዝ ተጫዋች ያለመሆኑ ትክክል ነው። ነገር ግን ፓውሎ ምን ያህል መጫወት እንደሚወድ ጁሊዮ ያውቀ ነበር።

ፓውሎ ተስፋ በማድረግ “መጫወት እችላለሁ?” ብሎ ጠየቀ።

- ምንድነው የምትለው?

ጁሊዮ ወዲያው መልስ አልሰጠም። ወደ አክስት ማሪያ መስኮት ለአንድ ሰከንድ ተመለከተ፣ እናም እሱን ስትመለከተው ማየት ይችል ነበር። የጁሊዮን መልስ በማሰብ የምትመለከት ነው የምትመስለው።

“ለምን ያንተ እንደሆነ አስታውስ።” ቃላቶቿ ወደ ጁሊዮ አዕምሮ መጣ። ወደ አክስት ማሪያ አንዴ እንደገና ተመለከተ። እሷን ለመርዳት ጥረትንና ጊዜውን አካፍሏል፣ እናም ማካፈሉን እንዲቀጥል ልትነግረው እየሞከረች እንደሆነስ በማለት ተገረመ።

ጁሊዮ ከአክስት ማሪያ ወደ ፓውሎ ተመለከተና እንዲህ አለ፣ “አዎን፣ መጫወት ትችላለህ።” ከዚያም ይህንን ጨመረ፣ “አንቶኒዮ ጎበዝ ተጫዋች ይኸውና፣ እናም ስለጨዋታው የበለጠ እንድትማር ይረዳሃል።”

አንቶኒዮ ወደ ጁሊዮ ተመለከተና ፈገግ አለ። “አዎ፣ እኔም ደስተኛ እሆናለሁ! ሁላችንም ታላቅ የእግር ኳስ ተጫዋቾች እንድትሆን እናስተምርሃለን፣” አለው ፓውሎን። “ሁላችንም አንተ እንድትማር ለመርዳት ደስተኞች ነን።”

ሁሉም ልጆች እንደገና መጫወት ጀመሩ። ጁሊዮ ወደ አክስት ማሪያ መስኮት ቀና ብሎ ተመለከተ። አክስት ማሪያ ፈገግ ብላ ነበር። ከዚያም ጁሊዩ አክስቱ ለምን አዲስ የእግር ኳስ መጫወቻ እንደሰጠችው አወቀ። (ከ ሻሪ ጆንሰን, “The Soccer Ball,” *Friend,* ሰኔ 1973, ከገጽ 10–12 የተገኘ)

**ውይይት**

- ጁሊዮ ማካፈልን ከመረጠ በኋላ የተሰማው እንዴት ነበር? (በውስጡ ደስታና ጥሩ ስሜት ተሰምቶት ነበር።)
- ባያካፍል ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? (ፓውሎን ገሸሽ በማድረጉ መጥፎ ስሜት ይሰማው ነበር፣ ፓውሎም መጥፎ ስሜት ይሰማው ነበር።)
- ጁሊዮ የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያደርግ የሚፈልጉትን አድርጓልን?

በህይወታችን ዘመን ውስጥ ብዙ ምርጫዎችን እንደምንመርጥ አስረዱ። እነዚህ ምርጫዎች ጥሩ ስሜት ወይም መጥፎ ስሜት እንዲሰማን ያደርጋሉ። ትዕዛዛት ለመታዘዝ መምረጥ ሁልጊዜ ጥሩ ስሜት እንዲሰማን ያደርገናል።

### ማጠቃለያ

**ቀለበትና ት.ም. አርማ**

የት.ም.ን አርማ ለልጆቹ ያሳዩ። የት.ም. ቀለበታቸው ትክክለኛውን መምረጥን እንዲያስታውሱ ሊረዳቸው እንደሚችል ያስታውሷቸው።

**የሚታደል ፅሁፍ እና ውይይት**

“የትዕዛዝ መንገድ ምልክቶች” የሚለውን ግልባጭ ለእያንዳንዱ ልጅ ይስጡ። በመንገድ ምልክቶቹ ላይ የተዘረዘሩትን ትዕዛዛት አንድ ላይ አንብቡ። (በዕድሜ ላነሱ ልጆች፣ ምልክቶችንና ምን ማለት እንደሆኑ ያስረዷቸው።)

ዘወትር ትክክለኛ ምርጫዎችን መምረጥ ቀላል እንዳልሆነና አንዳንድ ጊዜ በተሳሳተ መንገድ ልንሄድ እንደምንችል ለልጆቹ ይንገሯቸው። ትክክለኛ ምርጫዎችን እየመረጥን መሆኑን እንድናውቅ የሰማዩ አባት ትዕዛዛት የምንሄድበትን ትክክለኛ መንገድ እንድናገኝ ሊረዱን እና ጥሩ ስሜት ሊሰጡን ይችላሉ። ወደ ሰማዩ አባታችን ለመመለስም ይረዱናል። ትክክለኛውን ከመረጥን ስለምርጫዎቻችን እንደሰታለን።

ልጆቹ ወረቀቶቻቸውን ቤት እንዲወስዱና ከቤተሰቦቻቸው ጋር የመጽሐፈ ሞርሞንን ጥቀሶች እንዲያነቡ ዛሳብ አቀርቡላቸው። አንዳንዶቹን ትዕዛዛት እንዲያስታውሷቸው ወረቀቶቻቸውን ለማስቀረት ይፈልጉ ይሆናል።

| | |
|---|---|
| የአስተማሪው ምስክርነት | መጽሐፈ ሞርሞንን ማንበብ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ምስክርነትዎን ይስጡ። እሱን ማጥናት ሁልጊዜ ትክክለኛውን እንዲመርጡ ልጆቹን ይረዳቸዋል። |
| መዝሙር | "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ።<br>አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ እና ትክክለኛ ምርጫዎችን ለመምረጥ እንዲረዱን ትዕዛዛትን ስለሰጠን የሰማዩን አባት እንዲያመሰግን ይጋብዙ። |


---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪው መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. በክፍልዎ ውስጥ በሁለት ዕቃዎች መካከል ገመድ፣ ሲባጎ፣ ወይም ክር ይቋጥሩ (ለምሳሌ፣ በክፍልዎ ወንበርና በር ላይ)። ልጆቹ አይናቸውን ጨፍነው በክፍሉ ውስጥ መንገዳቸውን እንዲያገኙ እንዲረዳቸው ገመዱን በመጠቀም ተራ እንዲይዙ ይፍቀዱላቸው። በገመዱ መጨረሻ ለእያንዳንዱ ልጅ አንዳንድ ሽልማት ሊኖርዎት ይችላል። ልክ ይህ ገመድ በክፍሉ ውስጥ እንደመራን፣ ትዕዛዛትም ወደሰማዩ አባት ለመመለስ እንደሚመሩን ይግለጹ።
2. በ1ኛ ኔፊ 8–11 ላይ እንደተመዘገበው የሊሃይን ህልም በአጭሩ ይናገሩ። (በተለይ 1 ኔፊ 8፥9–30፣ 11፥1–25 ይመልከቱ)። የብረት ዘንጉ የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚያመለክት ያስረዷቸው። የህይወት ዛፍ የእግዚአብሔርን ፍቀር እንደሚያመለክት፣ እና የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ፍቀሩ እንዲሰማን እንዴት እንደሚረዳን ተወያዩ።
3. አዳምና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-5 ለመሸፈን በቂ የሆነ ሉክ ወረቀት አዘጋጁ። ወረቀቱን ወደ ዘጠኝ እኩል ቁርጥራጭ ቆራርጠውና እያንዳንዱን ቁራጭ ስዕሉን በሚሸፍኑበት ቦታ አጣብቁት። ከወረቀቱ በስተጀርባ የተደበቀው በጣም ጠቃሚ መልዕክት እንደሆነ ያስረዷቸው። ወላጆቻቸው ወይም ሌላ አዋቂ ሰው ስላስተማራቸው ሊታዘዟቸው የሚችሉትን ትዕዛዛት ልጆቹ በሚጠሩበት ጊዜ፣ አንድ ቁራጭ ወረቀትን ማንሳትና መልዕክቱን ለማግኘት መሞከር ይችላሉ። ሁሉም ቁርጥራጮች ሲነሱ፣ ወላጆች፣ አስተማሪዎች፣ እና ሌሎች መሪዎች ልጆች ትዕዛዛትን መታዘዝን እንዲማሩ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ተወያዩ።

# የትዕዛዝ መንገድ ምልክት





አስራትን መክፈል
(3ኛ ኔፊ 24፥10 ይመልከቱ)

ወላጆቼን መታዘዝ
(ሞዛያ 13፥20 ይመልከቱ)




ዘወትር መፀለይ
(2ኛ ኔፊ 32፥9 ይመልከቱ)





የሰንበትን ቀን
በቅድስና መጠበቅ
(ሞዛያ 13፥16 ይመልከቱ)

ሌሎችን
በርህራሄ መንከባከብ
(3ኛ ኔፊ 12፥44 ይመልከቱ)



# የዮሴፍ ስሚዝ የልጅነት ጊዜ

ትምህርት
4

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ ኢየሱስን በመከተልና ጥሩ የቤተሰብ አባል በመሆን የዮሴፍ ስሚዝን ምሳሌ እንዲከተሉ ለማበረታታት ነው።

**ዝግጅት**

1. የዮሴፍ ስሚዝን ታሪክ—ለጥኑ 1፥1–12።
2. የዮሴፍ ስሚዝን ስዕል ለመሸፈን በቂ የሆነ ቁራጭ ወረቀት አዘጋጁ። ለሁሉም ልጅ ለአንዳንድ መጫወቻ የሚበቃ እንዲሆን፣ ወረቀቱን ለብዙ ቁርጥራጮች ቆራርጡት። ስዕሉን ማየት እስከማይቻል ድረስ ቁርጥራጬን ወረቀት በዮሴፍ ስሚዝ ስእል ላይ ያድርጉ። (ዕድሚያቸው ከፍ ላለ ልጆች፣ በእያንዳንዱ ቁርጥራጭ በስተጀርባ ስለ ዮሴፍ ስሚዝ ያለውን እውነት ፃፉላቸው።)
3. የሚከተሉትን የቃላት መስመሮች አዘጋጁ፥

| |
|---|
| መታዘዝ |
| አገልግሎት |
| ፍቅር |
| ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ |
| መፀለይ |

4. ፍቅር በቤት የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ይዘጋጁ (*መዝሙር*፣ [Hymns] ቁ. 294)።
5. የሚከተሉትን ቁሳቁሶች ያዘጋጁ፥
   ሀ. ማጣበቂያ።
   ለ. ስዕል 3-6፣ ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ (62002፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 401)፣ ስዕል 3-7፣ የዮሴፍ ስሚዝ ቤተሰብ፣ ስዕል 3-8፣ ዮሴፍ ስሚዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ፈለገ (የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 402)፣ እና ስዕል 3-9፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (62572፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 240)።
6. ለሚጠቀሙባቸው ለማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ዛሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ ባለፈው ሳምንት ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**ዮሴፍ ስሚዝ ጥሩ ቤተሰብ ነበረው**

የአትኩሮት ተሳትፎ — የተሸፈነውን የዮሴፍ ስሚዝን ስዕል ለልጆቹ አሳዩአቸው። ከወረቀቱ ስር ያለው የሰማዩን አባት የሚወድ እና የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች የተከተለ ሰው ስዕል እንደሆነ ይንገሯቸው።

ለልጆቹ ከሚከተሉት እውነቶች አንዱን ይንገሯቸው፣ እናም አንድ ልጅ ከተሸፈነው ስዕል ላይ አንድ ቁራጭ ወረቀት እንዲያነሳ ይጠይቁ። ይህንን ሂደት ሁሉም ቁርጥራጮች እስከተነሱና ልጆቹ ስዕሉን ማየት እስከሚችሉ ድረስ ቀጥሉ። (ዕድሚያቸው ከፍ ላለ ልጆች ክፍል፣ እነዚህን እውነቶች በቁርጥራጭ ወረቀቶቹ ጀርባ ለመጻፍ እና ቁራጭ ወረቀቱን ለማንሳት ልጆቹ ተራ እንዲይዙ እና በስተጀርባ ያለውን መረጃ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይፈልጉ ይሆናል።)

- ስለ ዮሴፍ ስሚዝ እውነቶች፡
- ጨዋታዎችን መጫወት ይወድ ነበር።
- ሰማያዊ አይኖች ነበሩት።
- የተወለደው ታህሳስ 23 ነበር።
- የእናቱ ስም ሉሲ ነበር።
- የቤተሰቦቹ አባላት ሃብታሞች አልነበሩም፣ ነገር ግን ደስተኞች ነበሩ።
- ጠንካራ ሰራተኛ ነበር።
- የተሰየመው በአባቱ ስም ነበር።
- ታማኝ ነበር።
- በመላዕክቶች ተጎብኝቶ ነበር።
- የባለቤቱ ስም ኢማ ነበር።
- ጠንካራ ሰው ነበር።

ከዚያም ልጆቹን ጠይቋቸው፡

- ይህ ማነው?
- ስለ ዮሴፍ ስሚዝ ሌላ ምን ታውቃለህ?

ልጆቹ ስለ ዮሴፍ ስሚዝ ጥያቄዎች ካሏቸው፣ በአጭሩ ተወያዩዋቸው። የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንት እና የመጀመሪያው ነቢይ እንደነበረ ያስረዷቸው። በጣም ደግ እና፣ ሰው የሚወድ፣ ሰው ነበረ። ልጆቹ በሚመጣው ትምህርት ስለ ዮሴፍ ስሚዝ በበለጠ እንደሚማሩ ግለጹላቸው።

**ስዕልና ታሪክ**

የዮሴፍ ስሚዝን ቤተሰብ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3–7 ለልጆቹ ያሳዩ፣ እናም ስለ ዮሴፍ ስሚዝ የልጅነት ጊዜ የሚከተለውን ይንገሯቸው፡

በስዕሉ ላይ፣ በስተቀኝ ነጭ ሸሚዝ ያደረገው ወንዱ ልጅ ዮሴፍ ስሚዝ ነው። ሰማያዊ አይንና ብሩህ ቡናማ ጸጉር ነበረው። ብዙ ወንድሞች እና እህቶች ነበሩት። ዮሴፍ ፍልቅልቅ፣ ደስተኛ፣ መሳቅ፣ ኳስ መጫወት፣ መታገል፣ በበረዶ ላይ መንሸራተትና ጨዋታዎችን መጫወት የሚወድ ልጅ ነበር።

ዮሴፍ ወጣት በነበረበት ጊዜ፣ በአቀራቢያቸው ትምህርት ቤት ስላልነበረ ቤተሰቦቹ ቤት ውስጥ ትምህርት ቤት አዘጋጁለት። በኋላም፣ ዮሴፍ እና ወንድሞቹ እናም እህቶቹ የበለጠ ማንበብ፣ መፃፍ፣ እና ሒሳብ ወደ ተማሩበት ትምህርት ቤት ሄዱ።

የዮሴፍ ቤተሰብ በኒዮርክ፣ በደቡብ ፓልሚራ ለሰሩት ትንሽ የግንድ ቤት የገዙትን መሬት በከፊል አፀዱ። ከግንድ የተሰራው ቤት ትንሽ የመስታወት መስኮት እና የእንጨት ጥርብ ወለል ነበረው። ክፍሎቹ የሚሞቁት ወጥ ቤት ከሚገኘው፣ ከድንጋይ ከተሰራ፣ ትልቅ የእሳት ቦታ ነበር። ምንም ኤሌክትሪክ ስላልነበረ የስሚዝ ቤተሰቦች ብርሃንን የሚጠቀሙት በውስጡ የእንስሳት ስብ ካለበት መቀረዝ ነበር። ስንዴ፣ በቆሎ፣ ባቄላ እና ተልባ ይዘሩ ነበር። ሉሲ ስሚዝ እና ሴት ልጆቿ ተልባውን የናይለን ጨርቅ ለማምረት ይጠቀሙበት ነበር። ወንዶቹ ከመሬታቸው ላይ ዛፎችን በመቁረጥ ለማንደድ እና አሙዱን ለሳሙና መስሪያ ለመሸጥ እንዲደርቁ ወደ አንድ ጎን ያስቀምጧቸዋል። የስሚዝ ቤተሰቦች የእንጨት ተገጣጣሚ ወንበሮችና ቀርጫቶችን ይሰሩ

ነበር። ሉሲ በራሳቸው እንደስትሪ በዕቃ የተሞላ ንፁህ አመቺ ጠንካራ ቤት መስራት እንደቻሉ ትናገራለች። (See Donald L. Enders, “A Snug Log House,” *Ensign,* ነሐሴ 1985, ከገጽ 14–22 እና Dale L. Berge, “Archaeological Work at the Smith Log House,” *Ensign,* 1985, ከገጽ 24–26 ይመልከቱ።)

- ቤትህ የዮሴፍ ስሚዝን ቤት የሚመስለው እንዴት ነው?
- ቤትህ ከዮሴፍ ስሚዝ ቤት የሚለየው እንዴት ነው?

የዮሴፍ ስሚዝ አባት ግብርናን ጨምሮ፣ ለመኖሪያ የሚሆን ብዙ ነገሮችን ሰርቷል። ዮሴፍ ጥራጥሬ፣ ፍራፍሬዎችን እና አትክልቶችን ለማሳደግ ከአባቱ ጋር ጠንክሮ ይሰራ ነበር። ቤተሰቡም ከብት፣ አሳማዎች፣ እና ዶሮ ያረቡ ነበር። በርሚሎች፣ ባልዲዎች፣ እና የቤት መጥረጊያዎችን ይሰሩ ነበር። የዮሴፍ እናትና እህቶችም ምግብ በማብሰል፣ ልብስ በመስፋት፣ በፅዳት፣ ልጆችን በመጠበቅ፣ አይብና ቀቤ በማውጣት፣ እና ወጥ ቤትን፣ የአትክልት ስፍራን በመጠበቅ፣ እና ላሞችን በማለብ ጠንክረው ይሰሩ ነበር። በአንድ ዓመት የስሚዝ ቤተሰብ ከማፕል ፍሬ በሰሩት የበለጠ ጥራት ያለው ጣፋጭ የፍራፍሬ መጠጥ በሀገሩ ውስጥ ሽልማት አግኝተው ነበር።

- ቤተሰብህ በአንድነት የሚሰሩት ስራ ምን ዓይነት ነው?
- ቤተሰብህን ለመርዳት ምን ማድረግ ትችላለህ?

ዮሴፍ ስሚዝ ወጣት በነበረበት ጊዜ፣ ጥቂት ሆስፒታሎች እና መድሃኒቶች ይገኙ ነበር። ዶክተሮች የታመሙ ሰዎችን ለመርዳት ቤታቸው ይሄዱ ነበር።

ዮሴፍ ስሚዝ ልጅ በነበረበት ጊዜ፣ በጣም ታሞ ነበር። የዮሴፍ እግር በቁስል አመረቀዘ እና አበጠ። በጣም ህመም ነበረው። ዶክተሩ በሽታ የያዘውን እግር ከፍቶ ያመረቀዘውን ቁስል ለመጥረግ ሲቆርጠው ህመሙ የከፋ ነበር። በአቅራቢያው ምንም ሆስፒታል አልነበረም፣ ስለዚህ ቀዶ ጥገናው በዮሴፍ ቤት ውስጥ መደረግ ነበረበት። በቀዶ ጥገናው ወቀት ህመሙን ለማስቀም ዮሴፍ ምንም መድሃኒት አልተደረገለትም፣ ስለዚህም ታላቀ ህመም ተሰምቶት ነበር።

የቁስል መመርቀዙ እንደገና ተመለሰ፣ እናም የዮሴፍ እግር ህመም እና እብጠት አልተወውም። በመጨረሻም፣ ዶክተሩ እግሩ እንደማይድን ወሰነ፣ ቁስሉ በመመርቀዙ ወደተቀረው የዮሴፍ ሰውነት እንዳይዛመትና እንዳይገድለው እግሩን መቁረጥ እንዳለበት አሰበ። በእርግጥም፣ የዮሴፍ ቤተሰቦች በጣም ተጨንቀው ነበር። እናቱ እግሩን ለማዳን አንድ ነገር ማድረግ እንዲቻል ፀለየች። ከዚያም ዶክተሩን አንዴ በእግሩ ላይ ያለውን የመረቀዘውን ቁስል አካባቢ ብቻ ለመቁረጥና ለማውጣት እንዲሞክር ጠየቀችው። ዶክተሩም ተስማማ።

ህመሙን ለማቀም ምንም መድሃኒት ስለሌለ፣ ህመሙን ለመታገል እንዲረዳው ዮሴፍ የአልኮል መጠጥ እንዲጠጣ ዶክተሩ ፈልጎ ነበር። ነገር ግን ዮሴፍ አልጠጣም። በቀዶ ጥገናው ወቀት እንዳይንፈራገጥ ዶክተሩ ዮሴፍን ከአልጋው ጋር አብሮ ሊያስረው ፈለገ። ነገር ግን ዮሴፍ መታሰሩን አልፈለገም። በምትኩ፣ አባቱ በክንዶቹ እንዲያቀፈው ፈለገ። ዮሴፍ በቀዶ ጥገናው ወቀት እናቱ ማየት እንዳትችል ወደ ውጭ እንድትወጣለት ጠየቀ። ለእሷ ማየቱ አስቸጋሪ እንደሚሆንባት ስለሚያውቅ ሊያስጨንቃት አልፈለገም።

በረዥሙና በሚያሰቃየው ቀዶ ጥገና ወቀት፣ የዮሴፍ አባት አጥብቆ ያዘው። ካለቀ በኋላ፣ ዮሴፍ ዝሎና ደክሞት ነበር፣ ነገር ግን የቁስል መመርቀዙ በሙሉ ተነስቶ ነበር። የዮሴፍ እግርም ዳነ።

- ዮሴፍ ስሚዝ ቤተሰቦቹን እንደሚወዳቸው ያሳያቸው እንዴት ነበር? እነርሱ ለእርሱ ያላቸውን ፍቅር ያሳዩትስ እንዴት ነበር?
- ቤተሰብህ የዮሴፍ ስሚዝን ቤተሰብ የሚመስለው እንዴት ነው?
- ዮሴፍ ስሚዝን መምሰል የምትፈልገው በምን አይነት መንገዶች ነው?

## ዮሴፍ ስሚዝ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች አክብሯል

የቃላት መስመሮች ተሳትፎ

የዮሴፍ ስሚዝ ቤተሰብ ምናልባት በብዙ መንገዶች የአንተን ቤተሰብ ሊመስሉ ይችላሉ። ብዙ ጊዜ በአንድነት ይፀልዩ ነበር። ሁልጊዜ በአንድነት ይዘምሩ፣ ቤተክርስቲያን ይሄዱ፣ እና መጽሐፍ ቅዱስን ያነቡ ነበር። የኢየሱስን ትምህርቶች ለማክበር ሞክረዋል።

የቃላት መስመር ፊት ለፊት በጠረጴዛው ላይ ወይም ወለሉ ላይ አስቀምጡት። ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ የአንድን ቃል መስመር እንዲመርጥና ድምጹን ከፍ አድርጎ ቃሉን እንዲናገር ወይም በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲያጣብቀው ይጠይቁ። የቃላት መስመሮቹ ዮሴፍ ስሚዝ የኢየሱስን ትምህርቶች የተከተለበተን መንገዶች እንደሚገልፁ ለልጆቹ ይግለጹ። እያንዳንዳቸውን የቃላት መስመሮች ሲመረጡ፣ ዮሴፍ ትምህርቱን ለመከተል ምን እንዳደረገ ለልጆቹ ይንገሩ እና እነርሱም እንዴት መከተል እንደሚችሉ ይወያዩ።

*መታዘዝ*። ዮሴፍ መጽሐፍ ቅዱስ፣ አባትና እናትህን አክብር እንደሚል ያውቅ ነበር (ዘፀአት 20፥12)። ዮሴፍ አፍቃሪ እና ታዛዥ በመሆን ወላጆቹን አከበረ።

- ወላጆቻችንን እንደምንወዳቸውና እንደምንታዘዛቸው ለማሳየት ልናደርጋቸው የምንችለው አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?

*ማገልገል*። ኢየሱስ ሌሎችን ማገልገል እንዳለብን አስተምሯል። ዮሴፍ ስሚዝ ጥሩ ሰራተኛ ነበር እናም ሁልጊዜ የስራ ድርሻውን ያለመነጫነጭ ለመስራት ይሞክር ነበር። ቤተሰቦቹን ጠቃሚ በመሆንና ጠንክሮ በመስራት አገልግሏቸዋል።

- በዚህ ሳምንት የቤተሰብህን አባላት ያገለገልከው እንዴት ነው?

*ፍቅር*። ከዮሴፍ ስሚዝ የልብ ጓደኞች አንዱ፣ ከእርሱ በስድስት አመት የሚበልጠው ወንድሙ ሂረም ነበረ። በዮሴፍ ቤተሰብ ውስጥ ሁሉም ወንድማማቾችና እህታማቾች አብዛኛውን ጊዜ የሚጫወቱት አንድ ላይ ነበር። አንዱ ለሌላው ፍቅርን ለማሳየት ሞክረዋል።

“ፍቅር በቤት” የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃሎቹን ተናገሩ፣

በዙሪያችን ውበት አለ<br>
ፍቅር በቤት ካለ፣<br>
በሁሉም ድምፅ ደስታ አለ<br>
ፍቅር በቤት ካለ።<br>
ሰላምም በዚህ አለ፣<br>
በየአቀጣጫው ፈገግታ አለ።<br>
ጊዜ በቀስታ ይሔዳል<br>
ፍቅር በቤት ካለ።

- ለወላጆችህ ለመጨረሻ ጊዜ እንደምትወዳቸው የነገርካቸው መቼ ነው? ለወንድሞችህ እና ለእህቶችህስ?
- ለቤተሰቦችህ አባላት ፍቅርን የምታሳያቸው እንዴት ነው?

*ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ*፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ጠቃሚዎች እንደሆኑ ዮሴፍ ያውቅ ነበር። ዘወትር ስለሰማዩ አባትና ስለኢየሱስ ያስብ ነበር። ስለ እነርሱ የበለጠ ለመማር ይፈልጋል። ስለዚህም ሁልጊዜ ከመፅሐፍ ቅዱስ ያነብና ይፀልይ ነበር። ዮሴፍ ስሚዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ሲፈልግ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3–8ን ያሳዩ።

- ቅዱሳን መጽሐፍትን ማንበብ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?

*ፀሎት*። ዮሴፍ ስሚዝ ታሞ በነበረበት ጊዜ፣ እናቱ ለእርዳታ ወደሰማዩ አባት ፀልያለች። የሰማይ አባት ፀሎቷን መለሰላት እና ዮሴፍን እንዲድን ረዳው።

- የሰማዩ አባት ምን እንድታደርግ እንዲረዳህ መጠየቅ ትችላለህ?
- ሌላ ስለምን ወደ ሰማዩ አባት መፀለይ ትችላለህ?

**ማጠቃለያ**

ስዕሎች

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝን የሚያሳየውን ስዕል 3-6ን፣ ለልጆቹ ያሳዩ። የት.ም. አርማንም ያሳዩአቸው እናም ስለ ት.ም. ቀለበታቸው ያስታውሷቸው። ዮሴፍ ስሚዝ ትክክለኛውን የመምረጥ ጥሩ ምሳሌ እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ለቤተሰቦቹ ጥሩ ነበረ እናም የኢየሱስን ትምህርቶች አክብሯል። ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3–9 ያሳዩ። ትክክለኛውን ስንመርጥ፣ ልክ ዮሴፍ ስሚዝ እንዳደረገው፣ ኢየሱስን እንከተላለን።

የአስተማሪው ምስክርነት

ዮሴፍ ስሚዝ ቤተሰቦቹን ይወድ እነደነበረና ታላቅ ነቢይ እንደነበረ ምስክርነትዎን ይስጡ። ትክክለኛውን መርጧል እናም የሰማዩን አባት አገልግሏል።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ። የሰማዩን አባት ስለ ዮሴፍ ስሚዝ ጥሩ ምሳሌዎች እንዲያመሰግን ወይም እንድታመሰግን እና በዚህ ሳምንት ያንን ምሳሌ መከተልን ለማስታወስ እንዲረዳን እንድትጠይቅ ወይም እንዲጠይቅ ይጠይቁ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ ለአስተማሪ መርጃዎች በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. በዚህ ሳምንት ልጆቹ የዮሴፍ ስሚዝን ምሳሌ ሊከተሉበት የሚችሉትን አንዱን መንገድ እንዲመርጡ አድርጉ። ሲወስኑ፣ እርሳስና ወረቀት አድሏቸው። በወረቀቱ ጫፍ ላይ ልጆቹ ስማቸውንና ምርጫቸውን እንዲፅፉ ያድርጉ። እንደአስፈላጊነቱ እርዷቸው። (ለምሳሌ፣ "በዚህ ሳምንት ደግ እሆናለሁ።") ከዚያም የዮሴፍ ስሚዝን ምሳሌ ለመከተል ለማድረግ የመረጡትን ለማሳየት እንዲጽፉ ወይም ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ።

   ልጆቹ ወረቀቶቻቸውን ቤት ወስደው ለወላጆቻቸው እንዲያሳዩ እና በሳምንቱ ውስጥ ሁልጊዜ ሊያዮት በሚችሉበት ቦታ እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው።

2. "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ"፣ የሚለውን መዝሙር በአንድነት ዘምሩ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

ትምህርት

# 5

# የመጀመሪያው ራእይ

**ዓላማው** እያንዳንዱን ልጅ ዮሴፍ ስሚዝ የሰማይ አባትንና ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየ እንዲያውቅ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የያዕቆብ መልእክት 1፥5 እና የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፥7–20 በፀሎት ያጥኑ።
2. የሚገኝ ከሆነ፣ (ለ15 ደቂቃዎች)፣ *ከቤተክርስቲያን ታሪክ አፍታዎች* (53145) ከሚለው ቪዲዮ ቴፕ ካሴት ላይ *የመጀመሪያውን ራእይ* ለማሳየት ያዘጋጁ። *[The First Vision], [Moments of Church History].*
3. "የዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ፀሎት" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ። (መዝሙር ቁ. 26)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስና የታላቁ ዕንቁ ዋጋ።
   ለ. ከለሮች እና ወረቀት።
   ሐ. ዮሴፍ ስሚዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ሲፈልግ የሚያሳየውን ስዕል 3-8፣ (የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 402)፣ እና የመጀመሪያው ራእይን የሚያሳየውን ስዕል 3-10፣ (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 403)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ለማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

**ዮሴፍ ስሚዝ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን አይቷል**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

የአትኩሮት ተሳትፎ

ዮሴፍ ስሚዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብን ሲፈልግ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-8 ያሳዩ።

- ይህ ማነው? (ዮሴፍ ስሚዝ።)
- እሱ ምን እያደረገ ነው?
- መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነበው ለምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ዮሴፍ ስሚዝ ዕድሜው አስራ አራት በነበረበት ጊዜ፣ በገጠር ከቤተሰቦቹ ጋር ይኖር እንደነበር ለልጆቹ ያስረዷቸው። በዚያን ጊዜ በአቀራቢያ የሚኖሩ ሰዎች የሃይማኖት ፍላጉት ነበራቸው። የተለያዩ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎች እምነታቸውን ለማስረዳት ብዙ ስብሰባዎችን ያካሂዱ ነበር። እያንዳንዱ አስተዳዳሪ የእርሱ ቤተክርስቲያን ትክክለኛ እንደሆነ በመናገር የሚቀላቀሏቸውን ሰዎች ለማግኘት ይሞክሩ ነበር። ዮሴፍ ስሚዝም የትኛው ቤተክርስቲያን በትክክል፣ እውነት እንደሆነ ለማወቅ ስለሚፈልግ፣ ወደ ተለያዩ ሃይማኖቶች ብዙ ስብሰባዎች ይሄድ ነበር። እያንዳንዱ አስተዳዳሪ ስለ እግዚአብሔር እና ቅዱሳን መጻሕፍት የተለያዩ ሃሳቦች እንደነበራቸው አወቀ።

- ዮሴፍ ስሚዝ ስለ እነዚህ ሁሉ የተለያዩ እምነቶች የተሰማው ምን ይመስላችኋል? (ግራ መጋባት።)

**የቅዱሳን መጽሐፍት ውይይት**

በክፍል ውስጥ ማንበብ የሚችል አንድ ልጅ ካለ፣ የሚከተለውን የዮሴፍ ስሚዝን—ታሪክ 1-10 እንዲያነብ ወይም እንድታነብ ይርዷት ወይም ራስዎ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡት፡ “ዮሴፍ ስሚዝ ሁልጊዜ ምን ማድረግ እደሚገባው እርሱን ይጠይቅ ነበር። ከሁሉም ቤተክርስቲያን የትኛው ትክክል እንደነበረ ወይም ሁሉም ስህተት ከሆኑ ለማወቅ ይጨነቅ ነበር። ከእነርሱ አንዱ ትክክል ከሆነ፣ እንዴት ማወቅ እንደሚችል ይጨነቅ ነበር።

ዮሴፍን ግራ ያጋቡትን ብዙ ሃሳቦች እና አስተያየቶች ይግለጹ። ከእነዚህ ቤተክርስቲያኖች የትኛው ትክክል እንደሆነ ወይም ሁሉም ስህተት ከሆኑ ለማወቅ ይጨነቅ ነበር። የዮሴፍ እናት፣ ሁለት ወንድሞቹ፣ እና አንድ እህቱ የፕሬስቤተሪያን ቤተክርስቲያን ተካፋይ ነበሩ፣ ዮሴፍ ግን ማንኛውንም ቤተክርስቲያን አይካፈልም ነበረ።

ለልጆቹ መጽሐፍ ቅዱስ አሳዩ እናም ዮሴፍ ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ሲያነብ እንደነበረ ይግለጹላቸው። አንድ ቀን በጣም ያስደነቀውን ጥቅስ አነበበ።

በእድሜ ከፍ ያለ ልጅ የያዕቆብ መልእክት 1፡5 ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲያነብ ያድርጉ ወይም እራስዎ ድምጽዎትን ከፍ አድርገው ያንብቡ።

- ጥበብ ማጣት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል? (ጥበብ ማጣት ማለት ምንም ነገር ያለማወቅ ወይም ያለመረዳት መሆኑን ልጆቹ ማወቃቸውን ያረጋግጡ።)
- እግዚአብሔርን መጠየቅ ማለት ምን ማለት ነው? (ለሰማይ አባት መጸለይ።)

ጥቅሱን ደግመው ያንብቡት። ይህ ጥቅስ ማለት ስለ አንድ ነገር ማወቅ እና መረዳት ስንፈልግ እንዲረዳን ወደ ሰማይ አባት ፀልየን መጠየቅ እንችላለን ማለት እንደሆነ ይግለጹላቸው።

ዮሴፍ ጥበብ እንደጐደለው ያውቅ ነበር። ግራ ተጋብቶ ነበር። የትኛው ቤተክርስቲያን እውነት እንደነበረ አያውቅም፣ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን ለማድረግ ወሰነ—ወደ ሰማይ አባት መጸለይ።

**የቪዲዮ ካሴት ወይም የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ**

*የመጀመሪያውን ራእይ [The First Vision]* ያሳዩ፣ ወይም የሚከተለውን ይናገሩ፡

በአንድ ፀደይ ጠዋት፣ ዮሴፍ ከቤቱ አቀራቢያ ወዳለው ጫካ ሄደ። ብቻውን መሆኑን ለማረጋገጥ አካባቢውን ከተመለከተ በኋላ፣ ዮሴፍ ለመፀለይ ተንበረከከ።

እየፀለየ እያለም፣ ከራሱ በላይ በአየር ላይ በጣም ብሩህ የሆነ ብርሃን ተመለከተ። ዮሴፍ ያየውን በዚህ መልክ ገልፆታል፡ “ብርሃኑ በእኔ ላይ ሲያርፍ ብሩህነታቸው እና ክብራቸው ሁሉንም የሚገልፅ ሁለት ሰዎች፣ ከእኔ በላይ በአየር ላይ ቆመው አየሁ” (የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፡17 ይመልከቱ)።

**ስዕልና ውይይት**

የመጀመሪያውን ራእይ፣ የሚያሳየውን ስእል 3-10 ያሳዩ።

ከሰዎቹ አንዱ ዮሴፍን በስሙ ጠራውና፣ ወደ ሌላው በመጠቆም፣ እንዲህ አለው፣ *“ይህ የምወደው ልጄ ነው። እርሱን ስማው!”* (የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፡17)።

- እነዚህ ሁለት ሰዎች እነማን ነበሩ? (የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ።)

ዮሴፍ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስን የትኛው ቤተክርስቲያን ትክክለኛ እንደሆነ እና የትኛውን መካፈል እንደሚገባው ጠየቃቸው። ሁሉም ስህተት ስለነበሩ የትኛውንም ቤተክርስቲያን እንዳይካፈል ተነገረው። ዮሴፍም የኢየሱስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንዳልነበረ አወቀ።

ዮሴፍ ስሚዝ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስን ያየበት ቦታ በአሁኑ ጊዜ ቅዱሱ ጫካ ተብሎ ይጠራል።

- ዮሴፍ ስሚዝ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስን ከአየ በኋላ የተሰማው ስሜት ምን ይመስልሀል?

**ዮሴፍ ስሚዝ ከራእዩ ብዙ ነገሮችን ተምሯል**

ዮሴፍ ስሚዝ ከራእዩ ምን እንደተማረ ልጆቹን ይጠይቋቸው። የሚከተሉትን ነጥቦች አቀርቡ፡

1. ዮሴፍ የሰማይ አባት እና ኢየሱስን አየ። ስጋና አጥንት ያለው አካል እንዳላቸው አውቋል።

2. የኢየሱስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንዳልነበረ አወቀ።
3. የትኛውንም ቤተክርስቲያን መካፈል እንደሌለበት አውቋል። የትኛውም ቤተክርስቲያን እውነት እንዳልነበረ ይገለጹላቸው። (የሚቀጥለው ትምህርት ጆሴፍ ስሚዝ የኢየሱስን እውነተኛ ቤተክርስቲያን ወደ ምድር ለመመለስ እንዴት እንደረዳ እንደሚያስረዳ ለልጆቹ ሊነግሯቸው ይችላሉ።)
4. የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ስለ እኛ እንደሚጠነቀቁልን እና ፀሎታችንን እንደሚመልሱልን ተረድቷል።

መዝሙር — “የጆሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ፀሎት” የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ። ወይም መዝሙሩን ለልጆቹ የሚዘምር እንግዳ መጋበዝ ይችላሉ።

የእምነት አንቀፅ — ጆሴፍ ስሚዝ አንዴ ለአንድ ሰው ደብዳቤ ፅፎ ቤተክርስቲያኑ ምን እንደሚያስተምር አስረድቶት ነበር። የዚያ ደብዳቤ ክፍል የዕምነት አንቀጾች እንደሆኑ ይታወቃል።

በሰማይ አባት፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን የሚለውን ልጆቹ የመጀመሪያውን የእምነት አንቀጽ እንዲደግሙት ይርዷቸው።

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት — ጆሴፍ ስሚዝ አብን እና ወልድን እንዳየ ምስክርነትዎን ይስጡ፣ እናም ለጆሴፍ ስሚዝ ያለዎትን ምስጋና ይግለጹ።

በያዕቆብ መልእክት 1፥5 ያለው ቃልኪዳን እውነት መሆኑን ጆሴፍ እንዳወቀ ይመስክሩ። ጥበብ ከጐደለን፣ የሰማይ አባትን ጠይቀን መልስ መቀበል እንችላለን።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ሁላችንንም እንደሚወዱን ይመስክሩ። ልክ ጆሴፍ ስሚዝን እንደረዱት ለጥያቄዎቻችን መልስ እንድናገኝ ይረዱናል። መላዕክት ላይገለፁልን ይችላሉ፣ ነገር ግን ከልባችን ከጠየቅን፣ ለእኛ የተሻለ በሆነው መንገድ የሰማይ አባት ፀሎታችንን ይመልሳል።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ። የሰማይ አባትን ስለ ጆሴፍ ስሚዝና የሰማይ አባትን እና ኢየሱስን ስላየበት ራእዩ እንዲያመሰግን ወይም እንድታመሰግን ይጠይቋቸው።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች** — ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃዎች በሚለው ውስጥ የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. “ቅዱሱ ጫካ” የሚለውን የመዝሙር ቃላት ሲያነቡ ልጆቹ አይናቸውን እንዲጨፍኑ ያድርጉ። (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 87)። ስእል መሳል እንዲችሉ ስለ ጆሴፍ ልምድ በጥንቃቄ እንዲያስቡ ይጠይቋቸው።

   ቅዱሱ ጫካ ለምለም ነበር፣
   የጠዋት ፀሐይ የበራበት፣
   ጆሴፍ ከልብ ለፀሎት ሲንበረከክ፣
   ጆሴፍ ከልብ ለፀሎት ሲንበረከክ
   በተቀደሰው መሬት።

   አብና ወልድ ተገለፀ።
   በአንድ ድምፅ ተናገሩት።
   መልዕክታቸው ፍርሃቱን መለሰለት፣
   መልዕክታቸው ፍርሃቱን መለሰለት
   እናም ልቡን አስደሰቱት።

   እያንዳንዱ ልጅ ጆሴፍ ስሚዝን በቅዱሱ ጫካ ውስጥ ሆኖ የሚያሳይ ስዕል እንዲስልና “ጆሴፍ ስሚዝ በቅዱሱ ጫካ ውስጥ” የሚል ምልክት እንዲያደርጉበት ያድርጉ።

2. ድምፅዎትን ከፍ አድርገው የያዕቆብ መልእክት 1፥5 ለልጆቹ ደግመው ያንብቡላቸው እና ይህ ለችግሮቻችን መልስ እንድናገኝ እንዴት እንደሚያስተምረን ያስረዷቸው። “ጥበብ ሊጎድላቸው” እና “እግዚአብሔርን መጠየቅ” ሊያስፈልጋቸው የሚችልበትን ሁኔታ ለልጆቹ ይስጧቸው። ከጠየቁት የሰማዩ አባት በችግሮች ሊረዳቸው የሚችልበትን መንገዶች እንዲያስቡ እርዷቸው። እንደሚከተሉት ያሉትን ሁኔታዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፥

- አንተና የቀርብ ጓደኛህ በቀርብ ጊዜ ስለተጣላችሁ ተከፍተሃል። ነገሮችን እንዴት የተሻሉ ማድረግ እንደምትችል አታውቅም።
- ማታ በአልጋህ ላይ ስትሆን ብቸኝነት እና ፍርሃት ይሰማሃል።
- እናትህ ታማለች እናም የከፋት ትመስላለች። እንደገና ደስታ እንዲሰማት ልትረዳት ትፈልጋለህ።

ልጆቹ በሌላኛው ትምህርት የበለጠ ስለሚማሩት፣ የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ አብዛኛውን ጊዜ ፀሎታችንን የሚመልሱልን ሰላማዊ ስሜት በመስጠት እንደሆነ መግለፅዎትን እርግጠኛ ይሁኑ። ልጆቹ የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ፀሎታቸውን ለመመለስ እንዲገለፁላቸው መጠየቅ የለባቸውም።

ትምህርት

6

# የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ተመልሷል

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደተመለሰ እንዲገነዘብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ትንቢተ አሞፅ 3፥7 ያጥኑ።
2. በአካባቢህ የሚገኝ ከሆነ ከቤተክርስቲያን ታሪኮች አፍታዎች በሚለው የቪዲዮ ካሴት ላይ ዮሴፍ ስሚዝ፥ የሚለውን (ለ9 ደቂቃዎች) ለማሳየት ያዘጋጁ። *[Joseph Smith: The Man], [Moments From Church History].*
3. "የክህነት ስልጣን ተመልሷል" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ *[Children's Songbook]* ገፅ 89)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. ትምህርትና ቃልኪዳን እና መጽሐፍ ቅዱስ።
   ለ. እንደ አበባ፣ ዛኅል፣ ወይም ከፀሎት ቤት ቤተመጽሐፍት ቀንጆ ስዕል የመሳሰሉትን የሚስብ እቃ ወይም ስዕል።
   ሐ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   መ. ጥንደ ጥሩምባ የሚጠቀለል ሉክ ወረቀት።
   ሠ. የመጀመሪያውን ራእይ የሚያሳየውን ስዕል 3–10፣ (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 403)፣ መጥምቁ ዮሐንስ አሮናዊ የክህነት ስልጣንን ሲሰጥ የሚያሳየውን ስዕል 3-11፣ (62013፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 407)፣ የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መመለስ የሚያሳየውን ስዕል 3-12፣ (62371፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 408)፣ ልጁ ሲጠመቀ የሚያሳየውን ስዕል 3-13፣ (62018)፣ እና ልጅቷ አባልነቷ ሲፀድቅላት የሚያሳየውን ስዕል 3-14፣ (62020)።
5. ለምትጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሉአቸው።

**እውነተኛው ቤተክርስቲያን ተመልሷል**

የአትኩሮት ተሳትፎ — ለልጆቹ የዮሐንስ ራዕይ 14፥6–7 ያንብቡላቸው። በዚህ ጥቀስ ላይ ያለው መልአክ፣ ለዮሴፍ ስሚዝ የተገለጠው እና ወንጌሉ መመለሱን ያወጀው መልአኩ ሞሮናይ እንደሆነ ያስረዱ። ልጆቹ ሉክ ወረቀትን እንደ "ጥሩምባ" እንዲጠቀልሉት ያድርጉ። እያንዳንዱ ልጅ ቤተክርስቲያኑ መመለሱን ያወጀው መልአክ የሆነ በመሆን በማስመል እንዲሰራ ተራ ይስጧቸው።

ስዕል እና ውይይት — ልጁ ሲጠመቀ የሚያሳየውን ስዕል፣ 3-13 ያሳዩ።

- ማንም ሰው መጠመቀ ባይችል ምን ይሆን ነበር? (ማንም ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን መካፈል አይችልም ነበር።)

ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ፣ ሰዎች ትምህርቶቹን እንዲማሩና እንዲታዘዙ ይፈልግ እንደነበር ለልጆቹ ይንገሯቸው። እነዚህ ትምህርቶች ሰዎች ወደ እሱና ወደ ሰማዩ አባት ለመመለስ እና እንደገና አብረው ለመኖር ማድረግ ያለባቸውን እንዲማሩ ይረዷቸዋል። ኢየሱስ ቤተክርስቲያኑን ያደረጀው ሰዎች ትምህርቶቹን ማክበርን እንዲማሩ ለመርዳት ነው። ኢየሱስና ሃዋሪያቱ ከሞቱ በኋላ፣ ሰዎች ኢየሱስ ባስተማረው ትምህርት መሰረት አልኖሩም። ሰዎች ትምህርቶቹን ለወጧቸው ስለዚህም እውነተኛው ቤተክርስቲያን ጠፍቶ ነበር። ኢየሱስም በምድር ላይ ከነበሩ ሰዎች የክህነት ስልጣኑን ወሰደ። ይህም ማለት ሰዎች ከዚያ ወዲህ በትክክለኛው የክህነት ስልጣን መጠመቅ አይችሉም ነበር። ደግሞም ካለዚያ የክህነት ስልጣን፣ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ መቀበል፣ በቤተሰብ በቤተመቅደስ መተሳሰር፣ ወይም በምድር ላይ የሰማዩን አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያነጋግር ነቢይ ሊኖራቸው አይችልም።

**ስዕል እና ውይይት**

የመጀመሪያውን ራእይ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-10፣ ያሳዩ።

- በዚህ ስዕል ላይ ያለው ማነው? (የሰማይ አባት፣ ኢየሱስ፣ እና ዮሴፍ ስሚዝ።)
- ዮሴፍ ስሚዝ የትኛው ቤተክርስቲያን እውነተኛ እንደሆነ ለማወቀ ሲፀልይ ምን ተከሰተ? (የሰማይ አባትና ኢየሱስ ተገለጡለት። ኢየሱስ የትኛውም ቤተክርስቲያን እውነት ስላልሆነ ማንኛውንም ቤተክርስቲያን እንዳይካፈል ነገረው።)

በዚያን ጊዜ እውነተኛው ቤተክርስቲያን በምድር ላይ እንዳልነበረ ለልጆቹ አስረዱዋቸው። ኢየሱስ ትምህርቶቹ እና ቤተክርስቲያኑ በምድር ላይ እንዲመለስ ይፈልግ ነበር።

**በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት**

- *መመለስ* የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? (አንድን ነገር በፊት እንደነበረው መመለስ ማለት ነው።)

ልጆቹ ከመለሱ በኋላ፣ የሚከተለውን ምሳሌ ይስጡአቸው፣

ያመጡትን እቃ ወይም ስዕል ያሳዩ። ይህ ዕቃ የሚማርክ እና የሚጠቀም፣መሆኑ የተሰማዋት ለምን እንደሆነ ይግለጹ፣ እና ልጆቹ ስሜታቸውን እንዲያካፍሉ ይጠይቁ። ከዚያም አንድ ልጅ ዕቃውን እንዲወስድና ሌሎቹ ልጆች ሊያዩበት በማይችሉበት ቦታ እንዲይዘው ይጋብዙ።

- ይህን ቆንጆ ዕቃ ወይም ስዕል ልናይ በምንችልበት ቦታ ተመልሶ እንዲቀመጥ ተመኛላችሁን?

ልጁ ዕቃውን ለዕይታ መልሶ እንዲያመጣው ያድርጉ እና ለክፍሉ እንደገና ያሳዩ። ዕቃው ወደ ቀድሞ ቦታው *መመለሱን* ያስረዱ። *መመለስ* ማለት አንድን ነገር እንደነበረው እንዲሆን ማድረግ እንደሆነ ያስገንዝቡ። ምንም እንኳን ኢየሱስ በፈለገው መንገድ ቤተክርስቲያኑን ቢያደራጅም፣ ሰዎች ኢየሱስና ሃዋሪያቱ ከሞቱ በኋላ እውነቱን እንዳጠፉት ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ኢየሱስ ልክ እርሱ በምድር ላይ እንደነበረበት ጊዜ እንደነበረው ትምህርቶቹ፣ ቤተክርስቲያኑ፣ እና ሰዎችን የማጥመቅ ስልጣን እንዲመለሱ ይፈልግ ነበር።

**ውይይት**

የሰማዩ አባትና ኢየሱስ ታማኝ የሆነና እውነተኛውን ቤተክርስቲያን ለመመለስ እንዲረዳቸው ሊታመን የሚችል ታዛዥ የነበረ አንድ ወጣት ሰው እንደመረጡ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

- ይህ ወጣት ሰው ማን ነበር? (ዮሴፍ ስሚዝ።)

የመጀመሪያው ራዕይ ወደሚለው ስዕል እንደገና ይጠቁሙ፣ እናም እውነተኛው ቤተክርስቲያን በምድር ላይ ባለበት በማንኛውም ጊዜ፣ የሚመራውን አንድ ነቢይ ጌታ እንደሚመርጥ ያስረዱ። ኢየሱስ ዮሴፍ ስሚዝን የዚህ ዘመን የመጀመሪያው ነቢይ እንዲሆን መረጠው።

**ቪዲዮ ካሴት እና ውይይት**

የሚገኝ ከሆነ፣ ዮሴፍ ስሚዝ፥ ሰው የሚለውን ያሳዩ።

- ነቢይ ምንድነው?

አንድ ነቢይ ኢየሱስ ለቤተክርስቲያኑ መመሪያዎች የሚሰጠው ሰው እንደሆነ ይግለጹ።

**የቅዱሳን መጻሕፍት ውይይት**

ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ ድምጹን ከፍ አድርጎ ትንቢተ አሞፅ 3፥7 እንዲያነብ ይርዱት ወይም እራስዎ ያንብቡት። “ሚስጢሩን ይገልፃል” ማለት ለነቢዩ በራዕይ፣ በህልም፣ ወይም በሌሎች ራዕዮች አማካኝነት መመሪያዎችን ይሰጣል ማለት እንደሆነ ያስረዱ።

- ኢየሱስ ክርስቶስ መመሪያዎችን የሚሰጠው ለማን ነው? (ለህያው ነቢይ።)

ነቢይ ለሰዎች ኢየሱስ ምን እንዲያደርጉ እንደሚፈልግ እንደሚነግራቸው ያስረዷቸው። ነቢይ ትክክለኛውን እንድንመርጥ ይረዳናል ስለዚህም ከሰማዩ አባት እና ከኢየሱስ ጋር ለመኖር መመለስ እንችላለን።

የትምህርትና ቃልኪዳንን ቀጁ ለልጆቹ ያሳዩአቸው።

ኢየሱስ በዚህ መፅሐፍ የተፃፉትን ብዙዎቹን ቃላት ለዮሴፍ ስሚዝ እንደሰጠው ያስረዱ። ከእነዚህ ቃላት አንዳንዶቹ ስለ ኢየሱስ እውነኛው ቤተክርስቲያን ለዮሴፍ ነግረውታል። ከእነዚህ ቅዱሳን መጻሕፍት፣ ኢየሱስ እውነተኛውን ቤተክርስቲያን በዮሴፍ ስሚዝ አማካኝነት እንደመለሰ ልንማር እንችላለን።

## ዮሴፍ ስሚዝ የክህነት ስልጣንን ተቀብሏል

ውይይት

ዮሴፍ ስሚዝ ቤተክርስቲያኑን ለመመለስ ከመርዳቱ በፊት፣ ለኢየሱስ የመስራት መብት— ልዩ የሆነ ሃይልን መሰጠት እንደነበረበት ይግለጹ።

- ይህ ሃይል ምን እንደሚባል ታውቃላችሁን? (የክህነት ስልጣን።)

ስዕል እና ታሪክ

ዮሴፍ ስሚዝ እንዴት የክህነት ስልጣንን እንደተቀበለ የሚከተለውን ታሪክ ይንገሩ፥

ዮሴፍ ስሚዝ እና ጓደኛው ኦሊቨር ካውደሪ መጽሐፈ ሞርሞንን ሲተረጉሙ ስለ ጥምቀት ተማሩ። በእውነተኛው ቤተክርስቲያን ለመጠመቀም ፈለጉ። ተነበረከኩና ወደ ሰማዩ አባት ፀለዩ። ወዲያውም መልዕክተኛ ከሰማይ ተገለፀላቸው።

መጥምቁ ዮሐንስ አሮናዊ የክህነት ስልጣንን ሲሰጥ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-11 ያሳዩ።

መልዕክተኛው ኢየሱስን ያጠመቀው ሰው፣ መጥምቁ ዮሐንስ እንደነበረ ያስረዱ። ለዮሴፍ እና ለኦሊቨር በተገለጸላቸው ጊዜ፣ ስለ ጥምቀት አስተማራቸው። የማጥመቀ ስልጣንም ሰጣቸው። ይህ ስልጣንም አሮናዊ የክህነት ስልጣን ይባላል። በመቀጠልም፣ መጥምቁ ዮሐንስ እርሱ ኢየሱስን ባጠመቀበት መንገድ እርስ በእርሳቸው እንዲጠመቁ ነገራቸው። በመጀመሪያ፣ ዮሴፍ በአቀራቢያ ባለ ወንዝ ውስጥ፣ ኦሊቨርን አጠመቀው፣ እና ከዚያም ኦሊቨር ዮሴፍን አጠመቀው።

ልክ ኢየሱስ እንዳስተማረው፣ እውነተኛው የጥምቀት ዘዴ ወደ ምድር ተመልሷል።

ስዕልና ውይይት

የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መመለስን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-12 ያሳዩ።

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ ሌላ ሶስት የሰማይ መልዕክተኞች ለዮሴፍ እና ለአሊቨር እንደ ተገለፁላቸው ይግለጹ። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ በምድር ላይ ይኖር በነበረበት ጊዜ የነበሩ ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ የተባሉት ሶስቱ ሐዋሪያቱ ነበሩ። እጃቸውን በዮሴፍ እና በኦሊቨር ራስ ላይ ጫኑ እና የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣንን ሰጧቸው። ይህ የክህነት ስልጣን ከአሮናዊ የክህነት ስልጣን የሚበልጥ እና ለህሙማን ሰዎች በረከትን እንደመስጠት፣ ለልጆቹ በረከትን አባታዊ እንደመስጠት እና፣ የቤተመቀደስ ስርዓቶችን መፈጸም የመሳሰሉትን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ብዙ አስደናቂ ነገሮችን እንዲያደርጉ ስልጣን ይሰጣቸዋል።

የክህነት ስልጣን ኃይል እንድንጠመቀ እና የቤተክርስቲያን አባላት እንድንሆን ለማጽደቀ እና የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመስጠት ይፈቀደናል። ስዕል 3-13፣ ልጁ ሲጠመቀ፣ እና 3-14፣ ልጃገረድ ለአባልነት ስትፀድቀ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩ። ይህ ኃይል እነዚያን በሽተኞች ለመፈወስም ሊጠቀም ይችላል እና ቤተሰቦችን በቤተመቀደስ ለማስተሳሰር እናም በትክክል ከኖሩ ለዘላዓለም በቤተሰብ ይኖራሉ።

መዝሙር

“የክህነት ስልጣን ተመልሷል”፣ የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ።

የክህነት ስልጣን ዳግም በምድር ላይ እንዳለ ለልጆቹ ምስክርነትዎን ይስጡ። ለኢየሱስ ለማገልገል የሚያስችለው ሃይል የተመለሰው በዮሴፍ ስሚዝ አማካኝነት ነው። ዮሴፍ ስሚዝ ይህንን ሃይል የኢየሱስን እውነተኛ ቤተክርስቲያን ለመመለስ ተጠቀሞበታል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ይህ የክህነት ስልጣን ከእውነተኛው ቤተክርስቲያን ጋር ቀረ።

- እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚጠራው ምን ተብሎ ነው? (የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።)

ልጆቹ የቤተክርስቲያኑን ስም ደግመው እንዲሉ ያድርጉ። ኢየሱስ በኋለኛው ቀን የመለሰው እውነተኛ ቤተክርስቲያኑ ስለሆነ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንደሚባል ያስረዱ። የኋለኛው ቀን ማለት አሁን፣ ወይም አሁን እየኖርንበት ያለነው ጊዜ ማለት ነው።

**ማጠቃለያ**

የእምነት አንቀፅ

ኢየሱስ በምድር ላይ እያለ ባደራጀው ዓይነት ቤተክርስቲያን ውስጥ አባል የመሆን መብት እንዳለን ይግለጹ። አንዳንድ ጊዜ ኢየሱስ በዚያን ጊዜ ያደራጀውን ቤተክርስቲያን “የጥንቱ ቤተክርስቲያን” ብለን እንጠራዋለን። (የእምነት አንቀፅ 1፥6ን ይመልከቱ)።

ስድስተኛውን የእምነት አንቀፅ ይግለጹ እና ልጆቹ ከእርሶ ጋር ደግመው እንዲሉት ያድርጉ። ሁሉንም ወይም በከፊል ማስታወስ የሚችሉትን ያበረታቷቸው።

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

በምድር ላይ ላለው ብቸኛ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ለምን እንደፈለጉ አንዳንድ ልዩ የሆኑ ምክንያቶችን እንዲያስቡ ልጆቹን ይጠይቋቸው። እንደሚከተሉት ያሉትን፣ መልሶቻቸውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይዘርዝሩ፥

1. የሰማዩን አባት ለመታዘዝ።
2. የኢየሱስ ትምህርቶች እንዲመሩን ለማድረግ።
3. ለሃጢአታችን ምህረትን ለማግኘት።
4. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል።
5. ከሰማይ አባት እና ከኢየሱስ ጋር ተመልሰን ለመኖር።
6. በምድር ላይ ያለው የእግዚአብሔር መንግስት አባል ለመሆን።

ምስክርነት

የኢየሱስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባል መሆን መብት መሆኑ ለምን እንደሚሰማዎት ለልጆቹ ምስክርነትዎን ይግለጹላቸው። ቤተክርስቲያኑ ወደ ህይወትዎ ያመጣውን ደስታ እና የቤተክርስቲያኑ አባል በመሆንዎ ምስጋናዎትን ለልጆቹ ይግለጹላቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. እውነተኛው የኢየሱስ ቤተክርስቲያን ወደ ምድር ከተመለሰ ጊዜ ጀምሮ፣ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ያስተማረውን ዓይነት ነገሮች መማር እንደምንችል። ሁላችንም የእርሱ ቤተክርስቲያን አባል የመሆን መብት እንዳለን ለልጆቹ ይንገሯቸው።

   የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፣ ወይም ልጆቹ በቲያትር መልክ እንዲጫወቱት ያድርጉ፥

   “ስሜ ላ ሚሪ ጉዴይ ነው። ዕድሜዬ አስራ አራት ነው እናም ለአስራ አንድ ዓመታት ሙሉ ፖሊዮ ነበረብኝ . . .።የምኖረው በሶልት ሌክ ከተማ የጀማሪ ልጆች ሆስፒታል ነው—

   “ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የማስታውሰው፣ ወላጆቼ በሕይወቴ በጣም አስፈላጊው ነገር ቤተክርስቲያኔና የሰማይ አባቴ እንደሆኑ ሀሳቡን በአዕምሮዬ ውስጥ አስቀምጠዋል . . .ቤተክርስቲያኑን በሙሉ ልቤ መውደድን ተምሬያለሁ—

   “ወላጆቼ ጥምቀት እንዴት አስፈላጊ እንደሆነ አስተምረውኛል፣ ስለዚህ የራሴን ጥምቀት በጉጉት እጠብቅ ነበር። በመጨረሻም ስምንት ዓመት ሲሆነኝ፣ ሆስፒታል ነበርኩኝ እና ዕድሜዬ ለመጠመቅ ቢደርስም ከሆስፒታሉ መውጣት እንደማልችል የዶክተሩ አስተያየት ነበር። ልቤ አዝኖ ነበር እናም አባቴ አሁን በስምንት አመቴ እንዲያስጠምቀኝ ለመንኩት።

ነገር ግን ለመውጣት በደንብ ደህና እስክምሆን መጠበቅ ያለብኝ ይመስላል፤ ያም መቼ እንደሚሆን ማንም አያውቅም ነበር።

“ከዚያም፤ (ከዘጠኝ ዓመት ልደቴ በፊት)፤ ወላጆቼ . . . እና ሌሎች ዘመዶችና ጓደኞቼ ወደ ሆስፒታሉ መጡ፤ እና በአካል ህክምና ክፍላችን ባለው (የውሃ) ማጠራቂሚያ ውስጥ ተጠመኩ። ለምወደው ቤተክርስቲያን አባልነቴ ፀደቀልኝ . . .

“አሁን፤ ከስድስት ወር በኋላ፤ መጠመቅ ለእኔ እንዴት በጣም አስፈላጊ እንደነበር ለሌሎች ለማሳየት ይህን ታሪክ እንድፅፍ ተጠይቄአለሁ።

“ . . . የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል በመሆኔ ያለኝን ምስጋና . . .ለሁላችሁ ልነግራችሁ እወዳለሁ” (ላ ሚሪ ጉዴይ፤ “I Was Baptized in a Hubbard Tank” *Children's Friend*, ሰኔ 1963, ገጽ 30።)

2. ለምሳሌ የታላቅ እህታቸውን ወይም ወንድማቸውን ስላዩት ጥምቀት ልጆቹ እንዲናገሩ ያድርጉ።

3. የቤተክርስቲያኑን መመለስ የሚያስታውሳቸውን አንድ ነገር፤ መመለሱን እንዳመለክት ለማወጅ ጥሩንባ ወይም ዮሴፍ ስሚዝ በጫካ ውስጥ ሲፀልይ የመሳሰሉትን በስዕል እንዲያነሱ እና እንዲያቀልሙ ለልጆቹ ይፍቀዱላቸው።

# እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ

ትምህርት

7

**ዓላማው** እምነትን በኢየሱስ ክርስቶስ ማሳደግ የመጀመሪያው የወንጌል መሰረተ ሃሳብ መሆኑን እያንዳንዱ ልጅ እንዲገነዘብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የሚከተሉትን ጥቀሶች ለልጆቹ ለማቀረብ እና ለማስረዳት በፀሎት ያጥኑ እና ይዘጋጁ፣ የማርቆስ ወንጌል 10፥46–52፤ የማቴዎስ ወንጌል 3፥13–17፤ 3ኛ ኔፊ 11፥8–17፤ እና ት እና ቃ 76፥19–23።
2. በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ለጥቂት ደቂቃዎች ስለ አዳኝ ያላቸውን ስሜት እና ምስክርነት እንዲያካፍሉ ጠንካራ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነት ያላትን ወይም ያለውን አንድ ሰው ይጋብዙ። አንድን ሰው ከመጋበዝዎ በፊት የጳጳሱን ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን ፈቃድ ማግኘትዎን ያረጋግጡ እናም ደግሞ ለጀማሪዎች ክፍል ፕሬዚዳንት ያሳውቁ።
3. "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" በሚል ርዕስ ሰንጠረዥ ለማዘጋጀት ከስር ያሉትን መመሪያዎች ይከተሉ። (በትምህርቱ መጨረሻ ምሳሌ ተጠቅሷል።) ይህ ሰንጠረዥ በሚቀጥሉት አራት ትምህርቶች ውስጥ ያገለግላል፤ ስለዚህም ጠንካራ ወረቀት ላይ ሊያደርጉትና ሊያቀልሙት ይፈልጉ ይሆናል። ለክፍልዎ አባላት በሙሉ በቀላሉ እንዲታይ ሰንጠረዡን ትልቅ ያድርጉት። (አንዳንድ ጊዜ ሰንጠረዡን በማካፈያ ጊዜም መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል።)

   ሀ. የሚከተሉትን የቃላት መስመሮች ያዘጋጁ፣

   | |
   |---|
   | የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ |
   | ጥምቀት |
   | እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ |
   | ንስሃ |

   ለ. የቃላት መስመሮቹን በትምህርቱ ውስጥ እንደተመለከተው በደረጃቸው ይለጥፏቸው። ይህ ትምህርት የሚያገለግለው "እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ" ለሚለው ደረጃ ብቻ ነው።
4. ለእያንዳንዱ ልጅ "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ስለመሆን ምን እንደተማርኩ እኔን ጠይቁኝ" የሚል ፅሁፍ በትንሽ ቁራጭ ወረቀት ጻፍላቸው።
5. በክፍሉ ፊት ለፊት፤ የመደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍትን ግልባጭ ልጆቹ ሊያዩት በሚችሉት ቦታ ላይ ያስቀምጡ።
6. "የአዳኜ ፍቅር ይሰማኛል" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ለማለት ይዘጋጁ። (የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ፣ ገፅ 74)፤ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
7. አራተኛውን የእምነት አንቀፅ የተቻላቸውን ያህል ማስታወስ የሚችሉትን ልጆች ይርዷቸው።

8. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሞርሞን፣ ትምህርት እና ቃልኪዳን፣ እና የታላቁ ዕንቁ ዋጋ።

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-9፣ (62572፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 240)፣ አውሩ ሲፈወስ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-16 (62145፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 213)፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ የሚያሳየውን ስዕል 3-1 (62133፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 208)፣ ኢየሱስ በምዕራቡ ክፍለ አለም ሲያስተምር የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-17 (62380፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 316)፣ የመጀመሪያውን ራእይ የሚለው ስዕል 3-10፣ (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 403)፣ እና ፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖውን የሚያሳየውን ስዕል 3-18።

9. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**እምነትን መረዳት**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-9 ያሳዩ። ስዕሉን በትምህርቱ ሁሉ ማሳየትዎን ይቀጥሉ።

- ይህ ማነው?

የጎብኚው ምስክርነት

እንግዳዎትን ያስተዋውቁ እና ይህ ሰው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰማውን በአጭሩ እንዲነግራቸው የጋበዙት መሆኑን ለልጆቹ ይንገሯቸው። የእያንዳንዱ ሰው ምስክርነት ከሌሉ ስለ ኢየሱስ የሚሰማውን እንደሚያጠቃልል ይግለጹ። እንግዳዎትን እንደጨረሰ አመስግኑ እናም እንዲሄድ አሰናብቱት። እርሱ ከሄደ በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፣

- የዛሬው እንግዳችን ማን ነበር?
- እንግዳው እዚህ እንደነበረ የምታውቁት እንዴት ነው?

በክፍሉ ያልተገኘ አንድን ልጅ ወይም አንድ ሌላ ሰውን አስቡ እና በክፍት ቦታው ላይ የልጁን ስም በመጠቀም፣ የሚከተሉትን ጥይቄዎች ይጠይቁ፣

- ___________ የክፍላችንን እንግዳ ዛሬ አይቶ ነበርን?
- ___________ ዛሬ በክፍላችን ጎብኚ እንደነበረን እንዴት ሊያውቅ ይችላል?

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ያልነበረ ሰው እንግዳ እዚህ ማየት እንዳልቻለ ልጆቹ እንዲገነዘቡት እርዷቸው። ቢሆንም፣ ክፍሉ እንግዳው መጥቶ እንደነበረ ከገለጸ፣ ምናልባት ሰውዩው ሊያምን ይችላል። ምንም እንኳ እራሳችን ባናየውም ትክክለኛ እና እውነት በሆነ ነገር ማፈን ማለት እምነት መኖር ማለት ነው።

ሰንጠረዥ

"የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ ያሳዩ። የሰንጠረዡን ርዕስ ከልጁ ጋር ያንብቡት። በዕድሜ ያነሱ ልጆች ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ከእርሶ ጋር እንዲደግሙት ያድርጉ።

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት መኖር ወይም ማመን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን የመጀመሪያው ደረጃ እንደሆነ ይግለጹ። በሰንጠረዡ የመጀመሪያ ደረጃ ላይ "እምነት" በኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለውን የመጀመሪያ የቃል መስመር ያስቀምጡ። (እድሜያቸው ትንሽ ለሆኑ ልጆች፣ ምን እንደሚል እንዲያስታውሱ ከቃላት መስመሮቹ ጋር የኢየሱስን ስዕል ሊያሳዩአቸው ይችላሉ።) በእድሜ ከፍ ያሉ ልጆች ቃላቶቹን ከእርሶ ጋር እንዲያነቡ ያድርጉ። በዚህ ትምህርት ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

**መጽሐፍ ቀዱስ እና መጽሐፈ ሞርሞን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራሉ**

**የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ**

- ምንም እንኳን ኢየሱስን ባናየውም፣ እንደሚወደን እና እንዳለ እንዴት ልናምን ወይም እምነት ሊኖረን ይችላል? (ሌሎች ሰዎች ኢየሱስን አይተውታል እናም ስለ እርሱ ሊነግሩን ይችላሉ።)

በጠረጴዛው ላይ ያሉትን መጽሐፍት ያመልክቱና እነዚህ መፃሕፍቶቹ ቅዱሳን መጽሐፍት እንደሚባሉ ይግለጹ። ቅዱሳን መጻሕፍቱ ኢየሱስን ስላዩት ወይም ስላነጋገሩት ብዙ ሰዎች ይናገራል።

መጽሐፍ ቅዱሱን ከፍ አድርገው ይያዙት። ግማሹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ኢየሱስ በምድር ላይ ስለኖረበት ጊዜ፣ ትምህርቱን ለሕዝቡ ስለሰጠበት ጊዜ፣ እና ቤተክርስቲያኑን ስላደራጀበት ጊዜ እንደሚናገር ይጠቁሙ። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን ስለሚያውቁት ሕዝቦች ስላወቁት እና ብዙዎቹን ስለረዳበት መንገድ ይናገራል።

**ስዕል እና የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ**

እውሩ ሲፈወስ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3፥16 ያሳዩ። በኢየሱስ ጊዜ ይኖር ስለነበረው እውሩ ሰው፣ በርጤሜዎስ ታሪክ ለልጆቹ ይንገሯቸው (ማርቆስ 10፥46–52 ይመልከቱ)።

በርጤሜዎስ ኢየሱስ እንደሚመጣ ሲሰማ፣ ምህረት እንዲያደርግለት ወደ ኢየሱስ እንዳለቀሰ ይግለጹ። ብዙ ሰዎች በርጤሜዎስ ኢየሱስን እንዳይረብሸው እና ፀጥ እንዲል ነገሩት። ነገር ግን ኢየሱስ በርጤሜዎስን ሰማውና በርጤሜዎስን ወደ እርሱ እንዲያመጡት ጠየቃቸው። በርጤሜዎስም ማየት እንዲችል እንዲፈውሰው ኢየሱስን ጠየቀው”።

በርጤሜዎስ ምን እንደሆነ ለማወቅ የማርቆስ ወንጌል 10፥52 ሲያነቡ ልጆቹ እንዲያዳምጡዎት ይጠይቋቸው።

- በርጤሜዎስ ምን ሆነ? (ኢየሱስ ፈወሰው፣ በርጤሜዎስም ማየት ቻለ።)

ኢየሱስ በርጤሜዎስ በእምነቱ ምክንያት ተፈውሷል አለ። በርጤሜዎስ ኢየሱስ ሊፈውሰው እንደሚችል አምኗል።

- የበርጤሜዮስ ታሪክ ስለ ኢየሱስ እንድናውቀ የሚረዳን ምንድን ነው? (ኢየሱስ ይወደናል እናም በእርሱ እምነት ካለን ይረዳናል።)

**ስዕል እና የቅዱሳን መጽሐፍ ውይይት**

መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-1 ከበርጤሚምስ ስዕል በላይ ያስቀምጡት።

- በዚህ ስዕል ላይ ምን እየሆነ ነው? (መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን እያጠመቀ ነው።)

የማቴዎስ ወንጌል 3፥17 ያንብቡ።

- ኢየሱስ ሲጠመቀ፣ ከሰማይ፣ “በእርሱ ደስ የሚለኝ፣ የምወደው ልጄ ይህ ነው” ብሎ የተናገረው ማን ነው? (የሰማይ አባት።)

የሰማይ አባት ከተናገረው ስለ ኢየሱስ የምንማረው ምንድነው? (ኢየሱስ ልጁ እንደሆነ።)

ኢየሱስ ልጁ እንደሆነ የሰማይ አባት ምስክርነትን እየሰጠ እንደነበረ ይግለጹ።

መፅሐፈ ሞርሞንን ከፍ አድርገው ይያዙ። በዚህ መጽሐፈ ሞርሞን በሚባለው ቅዱስ መፅሀፍ ውስጥ፣ በአሜሪካ ውስጥ ኢየሱስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ስላዩትና ስለሰሙት ትልቀ የኔፊ የሰዎች ቡድን ማንበብ እንደምንችል ይግለጹ።

3ኛ ኔፊ 11፥8 ያንብቡ። ኢየሱስ በምዕራባዊው ክፍለ አለም ሲያስተምር፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-17 የኢየሱስን ጥምቀት ከሚያሳየው ስዕል በላይ ያስቀምጡት። 3ኛ ኔፊ 10፥9–11 ያንብቡ። ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ፣ ነቢያት ይመጣል ያሉት አዳኝ እንደሆነ ለሰዎች እንደነገራቸው ይግለጹ።

ኢየሱስ እመጣለሁ እንዳለው በመምጣቱ ኔፊዎች የተሰማቸውን ደስታ ልጆቹ እንዲገነዘቡት ይርዷቸው። ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሳ እንዲያምኑ እጆቹን እና እግሮቹን እንዲነኳቸው እና እንዲዳስሱት ሰዎቹን ጠይቋቸዋል።

- ለኔፊ ሰዎች ከመገለፁ ስለ ኢየሱስ ልንማር የምንችለው ምንድን ነው? (እንደሞተና እንደተነሳ። እንዳለ።)

**የዚህ ዘመን ነቢያቶች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይመሰክራሉ**

ስዕል እና ውይይት

የታላቁ ዕንቁ ዋጋን ቅጂ ከፍ አድርገው ይያዙ። የዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ራዕይ ታሪክ በዚህ መፅሐፍ እንድተጻፈ ይግለጹ። ልጆቹ የሚችሉትን ያህል ስለ ዮሴፍ የመጀመሪያ ራዕይ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። (ልጆቹ የማያውቁት ከሆነ፣ የመጀመሪያውን ራዕይ ታሪክ ለመናገር ይዘጋጁ፣ የዮሴፍ ስሚዝ— ታሪክ 1፣7–19 ይመልከቱ።) ቀደም ሲል ከነበረው ስዕል በላይ፣ የመጀመሪያውን ራዕይ የሚያሳየውን ስዕል 3-10 ያስቀምጡ። ዮሴፍ ስሚዝ ኢየሱስን ያየው ከሞት ከተነሳ ከመቶዎች ዓመታት በኋላ መሆኑን አጥብቀው ያሳስቡ።

ስዕል እና ታሪክ

ፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖውን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-18 ያሳዩ። የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንት በነበረበት ጊዜ፣ በሶልት ሌክ ቤተመቅደስ ኢየሱስ በግል እንደጎበኘው ይግለጹላቸው።

አንድ ቀን ፕሬዚዳንት ሎሬንዞ ስኖው ከሴት ልጅ ልጁ ጋር ቤተመቅደስ ውስጥ እየተዛወረ እያለ፣ ስለ ልምዱ ነገራት። ስለ ንግግራቸውም የሚከተለውን ተናግራለች፣

“ክፍሉን ለቀን ከሄድን በኋላ እና ወደ ሰለስቲያል ክፍል በሚያመራው፣ (በአዳራሹ መንገድ) ትልቁ መተላለፊያ ላይ እያለን፣ አንዴ፣ ለአንድ አፍታ ቆይ፣ አንድ ነገር ልነግርሽ እፈልጋለሁ፣ ብሎ ሲያስቆመኝ፣ ከአያቴ ብዙ እርምጃዎችን ርቄ እየተራመድኩ ነበር። ፕሬዚዳንት ውድሩፍ በሞተበት ጊዜ ልክ እዚህ ቦታ ላይ ነበር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተገለፀልኝ. . .

“ከዚያም አያቴ አንድ እርምጃ ቀረብ አለ እና ግራ እጁን በመዘርጋት፣ ከወለሉ ሶስት ጫማ ገደማ ከፍ ብሎ፣ እዚህ ጋር ነበር የቆመው፣ አለ። በጠንካራ የወርቅ ሳሕን ላይ የቆመ ይመስል ነበር አለ።

“አያቴ አዳኝ ምን ያህል የከበረ ሰው እንደሆነ ነገረኝ እናም እጆቹን፣ እግሮቹን፣ገጽታውን እና እርሱን አትኩሮት ለማየት ያላስቻሉትን የተዋቡ ነጭ መጎናጸፊያዎቹን፣ ሁሉንም የነበሩትን የንጣቱ እና የብሩህነቱን ክብር ገልጾልኛል።

“ከዚያም አያቴ እርምጃ በመጨመር ወደ እኔ ቀረበ እና ቀኝ እጁን በራሴ ላይ ጭኖ እንዲህ አለ፣ ‘አሁን፣ ልጄ፣ ይህ በራሱ አፍ በዚህ ቤተመቅደስ ውስጥ በትክክል አዳኝን እንዳየው፣እና ፊት ለፊት እንዳነጋገረው፣ የነገረሽ የአያትሽ ምስክርነት እንደሆነ እንድታስታውሺ እፈልጋለሁ’ ” (Allie Young Pond, quoted by Ivan J. Barrett, in “He Lives! For We Saw Him,” *Ensign,* ነሐሴ 1975, ገጽ 20; also in Le Roi C. Snow’s “Remarkable Manifestation to Lorenzo Snow,” in *Church News,* 2 ሚያዚያ 1938, ገጽ 8)።

- የፕሬዚዳንት ስኖው ምስክርነት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድታውቀ የሚረዳህ ምንድነው? (እንዳለ፣ አካል እንዳለው፣ እና በእኛም ጊዜ ሰዎችን እንደሚያነጋግር።)

**በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖረን ይችላል**

ውይይት

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ብዙ ልጆችን ይጠይቁ

- ኢየሱስን አይተኸዋልን?
- ኢየሱስ እንዳለ እና እውነተኛ እንደሆነ የምታውቀው እንዴት ነው?

በወላጆቻቸው፣ በጀማሪ ክፍል አስተማሪያቸው፣ እና በቅዱሳን መጽሐህፍት ትምህርቶች ውጤት በኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ልጆቹ እንዲገልፁ ይፍቀዱላቸው።

ኢየሱስ እንዳለ እና እንደሚወደን በቀዱሳን መጽሐፍት ምክንያት እና በእውነተኛ ሰዎች ምስክርነት ምክንያት እምነት ሊኖረን እንደሚችል ልጆቹ እንዲገነዘቡ ይርዷቸው። ከሌሎች ሰዎች ምስክርነት፣የምናውቀው—

1. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ።
2. ኢየሱስ እንደሚወደን እና ሊረዳን እንደሚፈልግ።

3. ኢየሱስ በእርሱ እምነት እንዲኖረን እንደሚፈልግ።
4. ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ እና እንደገና እንደሚኖር።
5. ኢየሱስ አካል እንዳለው እና ሰዎችን እንደሚያነጋግር።

በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት መኖር የእውነተኛ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የመጀመሪያው ደረጃ እንደሆነ ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

መዝሙር — "የአዳኝ ፍቀር ይሰማኛል" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት በሉ።

**ማጠቃለያ**

የአስተማሪው ምስክርነት — በትምህርቱ ያገለገሉትን ስዕሎች መምረጥና ከስዕሉ ጋር በተዛመደው ልምድዎ ወይም ምስክርነትዎ ምክንያት በኢየሱስ ላይ ስላለዎት ዕምነት በአጭሩ መናገር ይፈልጉ ይሆናል።

ለምሳሌ፣ ኢየሱስ በምዕራባዊው ክፍለ ዓለም ሲያስተምር፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-17 ያሳዩ። ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ለኔፊ ሰዎች ስለተገለፀላቸው እና እጆቹን እና እግሮቹን እንዲነኩት ስላደረጋቸው፣ ሁሉንም ህዝቦች እንደሚወድ ማወቀዎን ያስረዱ።

ቤት የሚወሰድ — ለእያንዳንዱ ልጅ "የኢየሱስ ክርስቶስ አባል ስለመሆን ምን እንደተማርኩ እኔን ጠይቁኝ" የሚል ጽሁፍ የተፃፈበት ትንሽ ወረቀት ይስጧቸው። ይህን ወረቀት ለወላጆቻቸው እንዲሰጡ እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ስለ መኖር የሚያውቁትን እንዲያካፍሏቸው ያበረታቷቸው።

"ልጆቹ የሚከተለውን ደግመው እንዲሉ ያድርጉ፡ "በዘለዓለማዊ አባት እግዚአብሔር፣ እና በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን" (የእምነት አንቀፅ 1፥1 ይመልከቱ)። ከዚያም በይበልጥ አራተኛውን የእምነት አንቀፅ በቃላቸው ማጥናት የሚችሉትን ይርዷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪው መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. ትምህርትና ቃልኪዳንን ከፍ አድርገው ይያዙ። ዮሴፍ ስሚዝ ሌላ ጊዜ ኢየሱስን ስላየበት እንደሚናገር ይግለጹ። ዮሴፍ እና ሲድኒ ሪግደን ስለ ኢየሱስ እና ትምህርቶቹ ሲያጠኑ እና ሲያስቡ፣ ኢየሱስ ተገለፀላቸው።

   የዮሴፍ ስሚዝን ምስክርነት ሲያነቡ ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ። ትምህርት እና ቃል ኪዳን 76፥22 እና ከቁጥር 23 ላይ "ስላየነው" የሚሉትን ቃላት ያንቡት።

   - ከዮሴፍ ስሚዝ ምስክርነት ስለ ኢየሱስ መማር የሚችሉት ምንድን ነው? (ኢየሱስ እንዳለ።)

   ከቅዱሳን መጻሕፍት ማንበብ እና ኢየሱስን ስላዩት ሰዎች መማር በኢየሱስ እምነት እንዲኖረን እንደሚረዳን ይግለጹ። ምንም እንኳን ኢየሱስን በአይናችን ማየት ባንችልም፣ እርሱን ባዩት ሰዎች ምስክርነት ምክንያት እና በቅዱሳን መጽሐፍት ስለ እርሱ ስለሚነግሩን እንዳለና እንደሚወደን እምነት ሊኖረን ይችላል። የሰማይ አባታችንን በፀሎታችን ስንጠይቀው ኢየሱስ አዳኛችን እንደሆነ በልባችን ማወቀ እንችላለን።

2. ማንኛውም ልጅ ስለ ኢየሱስ የሚሰማውን መናገር የሚፈልግ ከሆነ ይጠይቁ። ስዕል መምረጥ እና በስዕሉ ላይ የሚታየው ነገር እምነታቸውን እንዴት እንዳጠነከረ መናገር እንደሚችሉ አስረዷቸው እያንዳንዱን ስዕል ከአንድ ጊዜ በላይ መጠቀም ይቻላል።

   እያንዳንዱ ልጅ ስለ ኢየሱስ የሚሰማውን ወይም የሚሰማትን ለማካፈል እድሉን ካገኙ በኋላ፣ ለጥምቀት ለመዘጋጀት አስፈላጊውን ደረጃ እየያዙ መሆናቸውን ይግለጹ።

   - ይህ ደረጃ ምንድነው? (እምነትን በኢየሱስ ክርስቶስ ማሳደግ።)

“እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ” የሚለውን ሰንጠረዥ አመልክቱ እና ልጆቹ እንዲያነቡት ወይም ቃላቶቹን ከእርሶ ጋር እንዲደግሙት ያድርጉ።

3. ልጆቹ ዛሬ ከተማሩት የቀዱሳን መጽሐፍ ታሪኮች አንዱን በስዕል እንዲስሉ ያድርጉ።




| | |
|---|---|
| የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ | እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ |
| ጥምቀት | ንስኃ |

# የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚያስተምሩን ነቢያት አሉት

ትምህርት

# 8

**ዓላማው** የነቢያትን ትምህርቶች የመስማትን እና የመታዘዝን አስፈላጊነት ልጆቹ እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የሉቃስ ወንጌል 1፥70ን በፀሎት ያጥኑ።
2. ከዋርድዎት ወይም ከቀርንጫፍዎት የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያለው አንድ ሰው ወደ ክፍሉ እንዲመጣ እና ንጉስ ቢንያምን በመሆን እንደሚያስመስል ለልጆቹ እንዲነግራቸው ይጠይቁ። (የንጉሱን መጎናፀፊያ ለማመልከት የመታጠቢያ ቤት መጎናፀፊያ ወይም ተመሳሳይ የሆነ ነገር በልብሱ ላይ መልበስ ይችላል።) እንደ ንጉስ ቢንያም ሆኖ እራሱን እንዲያስተዋውቅ ይጠይቁ። ለህዝቦቹ ሸክም ላለመሆን ራሱን ለመደገፍ በራሱ እጆች ጠንክሮ ይሰራ የነበረ ፃድቅ ንጉስ እንደነበረ ለልጆቹ እንዲያስረዳ ያድርጉ። ከቀርብ እና ከሩቀ የእርሱን መልዕክት ለመስማት ለሚመጡ ሰዎች ከፍተኛ ግንብ መገንባቱን በአጭሩ እንዲያስረዳ ይጠይቁት። ንጉስ ቢንያም ካስተማራቸው መሰረተ ሃሳቦች አንዱን በአጭሩ ለልጆቹ እንዲያስተምር ይጠይቁት። (ሞዛያ 2–5ን ይመልከቱ)።
3. የሚከተሉትን እያንዳንዱን የነቢያቶችን እና የቤተክርስቲያን ፕሬዚዳንቶች ትምህርቶች በተለያዩ ወረቀቶች ላይ ይፃፏቸው ወይም እያንዳንዱን የሚያመልክት ስዕል ያዘጋጁ። ወረቀቶቹን በማስቀመጫ ያስቀምጧቸው (ወይም ስዕሎቹን በአንድ ጠረጴዛ ላይ ገልብጠው ያስቀምጡት)። እያንዳንዱ ልጅ ተራ እንዲያገኝ አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ትምህርቶችን ይጨምሩ።

   "የቤተሰብ የቤት ምሽት ይኑራችሁ።"

   "ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት።"

   "ሁልጊዜ በሰንበት ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ።"

   "ዘወትር መፀለይ።"

   "የሌሎች የሆነውን ዕቃዎች አለመውሰድ።"

   "በቤት ውስጥ በመርዳት ወላጆችህን ማክበር"።

   "አስራት መክፈል።"

   "እርስ በርስ መፋቀር።"
4. የነቢዩን መልዕክት የያዘ የቤተክርስቲያን መፅሔት ግልባጭ በጠረጴዛው ላይ ወይም በክፍሉ ፊት ለፊት የሆነ ቦታ ላይ ያሳዩ። ከክፍሉ ፊት፣ በክፍሉ ዙሪያ በወንበር ስር፣ መስኮት ላይ፣ እና በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመሳሰሉት ቦታ የመፅሔትን ቦታ የሚጠቁም ፍንጭ የተፃፈበትን ወረቀት ይደብቁ። እያንዳንዱ ፍንጭ የሚከተለውን ፍንጭ የት እንደሚፈልጉ ለልጆቹ ሊነግሯቸው ይገባል። የመጨረሻው ፍንጭ ወደሚታየው መጽሔት መልሶ ሊመራቸው ይገባል ልጆቹን ሊገባቸው የሚችለውን የነቢይ አጭር መልዕክት በመጽሔቱ ውስጥ በተለያየ መንገድ ያስምሩባቸው ወይም ምልክት ያድርጉባቸው።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ።
   ለ. የአሁኑ ነቢይ ስዕል።
   ሐ. የፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ፣ ስዕል 3-19።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዙዋቸው ይከታተሏቸው።

### የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የሚመራው በአንድ ነብይ ነው።

የአትኩሮት ተሳትፎ

ዛሬ በክፍል ውስጥ አስፈላጊ እንግዳ እንዳላቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ስለ ፃድቁ ንጉስ እና ነቢይ ስለሚነግራቸው መልዕክቱን በፀጥታ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። እንግዳዎ ንግግሩን ከጨረሰ በኋላ፣ ልጆቹ እጁን እንዲጨብጡትና ስለመጣ እንዲያመሰግኑት ይጋብዟቸው።

የቅዱሳን መጽሐፍ ጥቅስ

ልጆቹ ጥቅሱን እንዲያዳምጡ እና ስለ ነቢያት አንድ ነገር መማር እንደሚችሉ እንዲያዩ ይጠይቋቸው። የሉቃስ ወንጌል 1፥70ን ያንብቡ። አንዳንድ ጊዜ ጌታ የሚያስተምረን ማወቀ የሚያስፈልገንን ለነቢያቱ በመንገር እንደሆነ እና፣ ቤተክርስቲያኑን ሁልጊዜ የሚመራው ነቢይ እንዳለው እንዲገነዘቡ እርዷቸው።

- በዚህ ምድር ላይ የመጀመሪያው ነቢይ ማን ነበር? (አዳም።)
- የመጀመሪያው የኋለኛው ቀን ነቢይ ማነው? (ዮሴፍ ስሚዝ።)
- አሁን የቤተክርስቲያን ነቢያችን እና ፕሬዚዳንታችን ማነው? (ስዕሉን ያሳዩ እና ልጆቹ ስሙን በመጥራት እንዲለማመዱት ያድርጉ።)
- ከመጽሐፍ ቅዱስ እና ከመጽሐፈ ሞርሞን ስማቸውን ማጥናት የማትችሉት ነቢያት እነማን ናቸው?
- ማንም ሰው ነቢይ መሆንን መምረጥ ይችላልን? የዮሐንስ ወንጌል 15፥16ን ይመልከቱ።)

እያንዳንዱ ሰው ነቢይ ለመሆን እንደማይጠራ ይግለጹ። ነቢይ እንዲሆን የሚመርጠው ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢይን ሲመርጥ፣ ቤተክርስቲያኑን ለመምራት የሚያስፈልገውን ስልጣን በሙሉ ይሰጠዋል። ይህ ነቢይ የቤተክርስቲያኑ ፕሬዚዳንትም ነው።

### የሰማይ አባት እንዲመሩን እና እንዲባርኩን ነቢያትን ሰጥቶናል

ተሳትፎ

ልጆቹ የሚከተሉትን ንግግሮች በደንብ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። በንግግሩ የሚስማሙ ከሆነ፣ መቆም አለባቸው። የማይስማሙ ከሆነ፣ መቀመጥ አለባቸው። ልጆቹ ያልተረዱትን ማንኛውንም ንግግር ለማስረዳት ጊዜ ውሰዱ። (ለሚከተሉት ንግግሮች መልሱ “እንስማማለን”፣ እስከሆነ ድረስ በእያንዳንዱ ንግግር መሃል ልጆቹ እንዲቀመጡ ያድርጉ። ተሳትፎው የታቀደው በክፍል ውስጥ እንቅስቃሴንና ትልቅ የጡንቻ ተሳትፎ እንዲሰጥ ነው።)

1. በአጠቃላይ ጉባኤ ላይ ከነቢያችን መልዕክት እንቀበላለን። (እንስማማለን። የነቢዩ አማካሪዎች እና አስራ ሁለቱ ሐዋርያትም ነቢያት እንደሆኑ ይግለጹ።)
2. ነቢያችን ስህተተ የሆኑ ነገሮችን እንድንሰራ በፍፁም አይነግሩንም። (እንስማማለን። ሁልጊዜ ነቢዩ የሚነግረን ትክክለኛውን እንድናደርግ መሆኑን እንደምናምን ይግለጹ።)
3. ፕሬዚዳንት (የአሁኑን ጊዜ ነቢይ ስም ይጥሩ) ነቢይና የቤተክርስቲያኑ ፕሬዝዳንት ነው። (እንስማማለን።)
4. ነቢያችን የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን ነገር ይነግረናል ስለዚህም ደስተኞች እንሆናለን እናም ከእነርሱ ጋር እንደገና መኖር እንችላለን። (እንስማማለን።)

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ነቢዩ በቤተክርስቲያን መፅሔቶች መልዕክት እንደሚሰጠን፣ በስብሰባዎች እንደሚናገር፣ እና ስብሰባዎችን እንደሚመራ እና ሌሎች የቤተክርስቲያን መሪዎችን እንደሚመራ እና እንደሚያስተምር ይግለጹ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ይኖር የነበረ ታላቅ ነቢይ እንደነበር ይግለጹ። ወንጌልን አስተምሯል። እናም ብዙ ተአምራትን ሰርቷል።

ስዕልና ታሪክ

ከኋለኛው ቀን ነቢያት አንዱ ስለነበረው፣ ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ ታሪክ ሊነግሯቸው እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። የኋለኛው ቀን ነቢያት ከዮሴፍ ስሚዝ ጀምሮ የኖሩት፣ ያሉ ወይም እኛ በምኖንርበት ጊዜ አቀራቢያ የነበሩ እና ያለ ነቢያት እንደሆኑ ይግለጹ። የሚከተለውን ታሪክ ሲናገሩ፣ ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይን የሚለውን፣ ስዕል 3-19ን ያሳዩ፣

ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ ነቢይ በነበረበት ጊዜ፣ የቤተክርስቲያን አባላትን ለመገናኘት እና ለመምራት በአብዛኛው ዓለም ተጉዟል። አብዴ ጀርመን በነበረበት ጊዜ፣ ሽባ ስለነበረች እናት ሰማ (ከፊሉን ሰውነቷን ማንቀሳቀስ አትችልም ነበር) እናም እሱ ሲናገር ለመስማት ወደ ጉባዔው መምጣት አልቻለችም።

ይህች እናት ሁለት ልጆች ነበሯት፣ እናም ወደ ጉባዔው እንዲሄዱና በሕይወት የነበረውን ነቢይ እንዲያዩትና እንዲሰሙት ፈለገች። በታላቅ እምነትም እንዲህ አለች፣ “ልጆቼን ከፕሬዚዳንት ማኬይ ጋር እንዲጨባበጡ ብልካቸው፣ እና ከዚያም እነሱ ቤት መጥተው እጆቼን ሲይዙ—ትንንሽ እጆቻቸውን በእጆቼ መያዝ ከቻልኩ—እንደሚሻለኝ አውቃለሁ።”

ሁለቱ ልጆቿ ወደ ጉባዔው መሄድ እንዲችሉ ተስተካከለላቸው። ልጆቹም ነቢዩን ለማየት ሲጓዙ በደስታ ስሜት ተዋጡ እና ተሸበሩ።

ጉባዔው ሲያልቅ፣ ፕሬዚዳንት ዴቪድ ኦ ማኬይ እዚያ ከነበሩት ብዙ ሰዎች ጋር ተጨባበጠ። እነዚህ ሁለት ልጆች መምጣታቸውን ያውቅ ነበር፣ እና ሲያያቸው፣ እጆቻቸውን ጨበጠ እና፣ “ይህንን መሐረብ ከቡራኬዬ ጋር ለእናታችሁ ትወስዱለታላችሁን?” አላቸው።

ልጆቹ መሃረቡን ለእናታቸው ወሰዱላት። በጣም ተደስታ ነበር እናም ስለመሃረቡ እና ፕሬዚዳንት ማኬይ በሁለቱ ልጆቿ አማካኝነት ስለላከላት ቡራኬ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን ታመሰግነው ነበር። ልጆቿ ቤት ከመጡ በኋላ ወዲያውኑ፣ ይሻላት ጀመር፣ እናም ብዙም ሳይቆይ ሰውነቷን ማንቀሳቀስ እና ልጆቿን መንከባከብ ቻለች። (See *Cherished Experiences from the Writings of President David O. McKay,* comp. Clare Middlemiss [Salt Lake City: Deseret Book Co., 1955], pp. 149–51.)

### ነቢዩን መከተል እንችላለን

የድብብቆሽ ጨዋታ

አንድ ቀላል የሚያሻሽል የድብብቆሽ ጨዋታ ይኑራችሁ።” አንዳንዴ በዚህ ክፍል ውስጥ የሆነ ቦታ ከቤተክርስቲያኑ ነቢይ ለዚህ ክፍል አባላት መልዕክት አለ። ማግኘት የምትችሉ ከሆነ ፈልጉ በማለት ጀምሩ።” ከዚያም የመጀመሪያውን ፍንጭ ለልጆቹ ይንገሯቸው። እያንዳንዱ ፍንጭ ሲገኝ፣ ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡት ወይም ማንበብ የሚችል አንድ ልጅ እንዲያነበው ያድርጉ። የመጨረሻው ፍንጭ እንደዚህ ያሉ ነገሮችን ሊገልፅ ይችላል፣ “የተፃፈው ወረቀት ላይ ነው። በወረቀቱ ሌላ ገጾች ላይ ነው። ቀለማማ ሽፋን አለው።” ልጆቹ መፅሔትን ሲያገኙት፣ ከመፅሔቱ ላይ ምልክት የተደረገበትን የነቢዩን መልዕክት ያንብቡት ወይም አንድ ልጅ እንዲያነብ ያድርጉ። በጥንቃቄ የተቀመጡት የነቢዩ ቃላት ምን ዓይነት እንደሆኑ አስረዱ። ወደ ሰማዩ አባታችን ተመልሰን መኖር እንድንችል ነቢያት እንዴት እንደምንኖር ሊነግሩን ይችላሉ።

ማጠቃለያ

በቅዱሳን መጻሕፍት ያሉትን የነቢያት ትምህርቶችን በማጥናት እና በሕይወት ያለውን ነቢይ በመታዘዝ ስላገኙት በረከት ምስክርነትዎን ይስጡ። የነቢዩ ትምህርት ሕይወትዎን እንዴት እንደቀየረው የግል ልምድዎትን ለማካፈል ይችላሉ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. "ነቢዩን ተከተለው" የሚለውን መዝሙር አዝማች ሲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ሲሉ ልጆቹ በመስመር እንዲቆሙና በፀጥታ በሰልፍ እንዲጓዙ ያድርጉ (*የልጆች መዝሙር* መጽሐፍ፣ ገፅ 110–11)። አዝማቹን በጨረሱ ቁጥር፣ ከፊት ለፊት ያለው ልጅ የነቢዩን ትምህርት እንዴት እንደሚከተል ወይም እንደምትከተል መናገር እና ወደ መጨረሻው መስመር መሄድ አለበት ወይም አለባት። እያንዳንዱ ልጅ በመስመሩ ፊት ለፊት ተራ እንደደረሳቸው ያረጋግጡ።


   ነቢዩን ተከተለው፣ ነቢዩን ተከተለው፣
   ወደ ጥፋት አትጓዝ፣ ነቢዩን ተከተለው።
   ነቢዩን ተከተለው፣ ነቢዩን ተከተለው፣
   መንገዱን ያውቃልና፣ ነቢዩን ተከተለው።

2. እንድናደርግ የሚጠይቀንን በማድረግ ነቢዩን ስንከተለው፣ እንደምንባረክ እና ከሰማይ አባት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተመልሰን መኖር እንደምንችል ይግለጹ። (በሚቀጥለው ገፅ የሚገኘውን ያመልከቱ) የውስብስብ መንገድ ምስል ግልባጭ ለእያንዳንዱ ልጅ ስጡአቸው እና ወደ ሰማዩ አባት እና ኢየሱስ የሚወስደውን ትክክለኛውን መንገድ እንዲያቀልሙ ይጠይቋቸው። ማንበብ የማይችሉ ልጆች አንዳንድ እርዳታ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

3. አሁን ያለውን ነቢይ ስዕል ሲያዩ ስለ እርሱ እውነታዎችንና ታሪኮችን ያካፍሉ።

4. ልጆቹ የተቻላቸውን ያህል አምስተኛውን የእምነት አንቀፅ እንዲያውቁት ይርዷቸው።

# ነቢዩን ተከተለው



ትዕዛዛትን
አክብር
የቤተሰብ የቤት ምሽት
ይኑርህ
ታማኝ ሁን
ሚሲዮናዊ ሁን
አስራትህን ክፈል
ቅዱሳን መጻሕፍትን አጥና
አባት እና
እናትህን አክብር
ቤተክርስቲያን
ተከታተል
ዘወትር ፀልይ
እውነትን ተናገር
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ

ትምህርት


# 9


# የክህነት ስልጣን በረከቶችና ስርአቶች

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ የክህነት ስልጣን በረከት እና ስርዓት አስፈላጊነቱን እንዲያገናዝብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የያዕቆብ መልዕክት 5፥14–15 እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 42፥44፣ 48–52 በፀሎት ያጥኑ። ምንም እንኳን እነዚህ ጥቅሶች በትምህርቱ ውስጥ ባያገለግሉም፣ ይህንን መሰረተ ሃሳብ ለማስተማር ቅዱሳን መጽሐፍታዊ መረጃዎችን ይሰጡዎታል።
2. በአትኩሮት ተሳትፎ ላይ ለመጠቀም የወረቀት የንፋስ ወፍጮ ያዘጋጁ። የወረቀት የንፋስ ወፍጮ ለማዘጋጀት፣ ከታች እንደተመለከተው አራት ማዕዘን ወረቀት ያዘጋጁ። በነጠብጣቡ መስመሮች ላይ ቁረጡት፣ እና ተቃራኒ ነጥቦቹን ወደ መሃከል ይጠፏቸው። ከዚያም በመሃከለኛው ነጥቦች ውስጥ እስፒል ያስገቡ፣ እና እስፒሉን ወደ እርሳስ ውስጥ ወይም ወደ እንጨት ውስጥ ይግፉት።





3. ልጆቹ “የክህነት ስልጣን ተመልሷል” የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ለማለት እንዲዘጋጁ ይርዷቸው። (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 89)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. ከቻሉ የሚከተለውን ደብዳቤ ግልባጭ እያንዳንዱ ልጅ ቤት እንዲወስደው አዘጋጁ። እያንዳንዱ ልጅ በባዶ ቦታው ላይ ለእዚያ ልጅ ተገቢ የሆነውን እንዲሞላ እርዱት ወይም አድርጉ (“እናት እና አባት የመሳሰሉትን”)። በቤታቸው ሁለቱም ወላጆች ለሌሏቸው ልጆች አስቡላቸው።

   ውድ_፣______________________________________________

   የክህነት ስልጣን በረከት ተሰጥቶኝ ያውቃልን? እባክዎን ስለዚህ ንገሩኝ።

   ወዳጅዎ፣

5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፦
   ሀ. ቀባ ቅዱስ የያዘ ጠርሙስ።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ ፊደሎቹ ላይ ምልክት የሚያደርጉበት ከለር ወይም እርሳስ።
   ሐ. መጥምቁ ዮሐንስ አሮናዊ የክህነት ስልጣንን ሲሰጥ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-11 (62013፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 407)፣ የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መመለስን የሚያሳየው ስዕል 3-12 (62371፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 408)፣ አባት በሽተኛ ልጁን ለመባረክ ሲዘጋጅ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-20 አባት ህፃን ልጁን ሲባርክ የሚያሳየውን ስዕል 3-21።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**የክህነት ስልጣን ተመልሷል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ከወረቀት የሰሩትን የንፋስ ወፍጮ ለልጆቹ ያሳዩአቸው (ለክፍልዎ ተገቢ መስሎ ከተሰማዎት እንዴት እንደተሰራ ለማሳየት የንፋስ ወፍጮውን ክፍል ውስጥ መስራት ይችላሉ)። እያንዳንዱ ልጅ በክፍሉ ፊት ለፊት እንዲመጣ እና የንፋስ ወፍጮው እንዲሽከረከር ለማድረግ አየር እንዲሰጠው ያድርጉ።

- የንፋስ ወፍጮው እንዲሽከረከር የሚያደርገው ምንድነው? (የንፋስ ሃይል።)
- ምንም ንፋስ ከሌለ ምን ይሆናል?

ንፋስ ጠንካራ ሃይል ሊሆን እንደሚችል ያስረዱ። ከመሬት ውስጥ ውሃ ማውጣት ይችላል፣ ወይም ለትላልቅ መሣሪያዎች ሃይል መስጠት ይችላል። ዛሬ ከንፋስ የበለጠ ጠንካራ ስለሆነው ኃይል እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው። በቀርብ ስለተማሩት የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን መመለስ ስለሚለው ትምህርት ያስታውሷቸው (ትምህርት 6ን ይመልከቱ)። የወንጌሉ መመለስ አስፈላጊው ምክንያት የክህነት ስልጣንን በምድር ላይ መመለስ ነበር።

- የክህነት ስልጣን በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ የመስሪያ ሃይል እንደሆነ ልጆቹ እንዲገነዘቡ እርዷቸው።)
- ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ መስራት ማለት ምን ማለት ነው? (እነርሱ የሚሰሩትን ነገሮች መስራት።)
- ኢየሱስ በምድር ላይ ከሰራቸው መልካም ነገሮች ጥቂቶቹ ምንድናቸው? (ተጠምቁል፣ ህሙማንን ፈውሷል፣ እውር እንዲያይ አድርጓል፣ ህፃናትን ባርኳል፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ቁርባንን አዘጋጅቷል፣ እናም የመሳሰሉት።)
- እነዚህ ነገሮች ዛሬ ሊሰሩ ይችላሉን? (አዎን፣ ሊሆኑ ይችላሉ እናም ዛሬ እየተደረጉ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ነገሮች የሚሰሩት የክህነት ስልጣንን በቀድስና በመጠቀም እና በእምነታችን አማካኝነት ብቻ እንደሆነ ልጆቹ እንዲገነዘቡት እርዷቸው።)
- እንግዲያስ የክህነት ስልጣን ምንድነው? የክህነት ስልጣኑን በቀድስና የሚያከብር አንድ ሰው ሊሰራ የሚችለው ምንድነው? (ወደ ሰማይ አባታችን ለመመለስ አንዳንድ ስርዓቶችን መቀበል እንደሚያስፈልገን ለልጆቹ ይግለጹላቸው። እነዚህ ስርዓቶች ሊከናወኑ የሚችሉት በክህነት ስልጣን እና በክህነት ስልጣን ሃይል ብቻ ነው።)
- የእነዚህ የክህነት ስልጣን አንዳንድ ስርዓቶች ምንድናቸው? (ቅዱስ ቁርባን፣ ጥምቀት፣ለአባልነት ማጽደቀ፣ በክህነት ስልጣን መሾም፣ በቤተመቀደስ መተሳሰር፣ እና የመሳሰሉት ናቸው። አስፈላጊ ከሆነ፣ እንደዚህ ዓይነት ሃሳብ አቀርብላቸው፣ "ዕድሚያቸሁ ስምንት ሲሆን ምን ይሆናል?")

  ሌሎች ስርዓቶች በዚህ ህይወት የሚረዱንን ባርኮት ይሰጡናል።

- የክህነት ስልጣን ካላቸው ሰዎች ልንቀበል የምንችለው በረከት ምንድነው? (መልሶች ህሙማንን መባረክ፣ አባታዊ ቡራኬ፣ እና ህፃናትን መሰየምን እና መባረክን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ። ፍንጮችን መስጠት ይፈልጉ ይሆናል።)

  እነዚህን ስርዓቶች እና በረከቶች የምናገኘው በእምነታችን፣ በፀሎት፣ እና በትክክለኛው የክህነት ስልጣን አማካኝነት እንደሆነ ይግለጹ።

ስዕሎች

መጥምቁ ዮሐንስ አሮናዊ የክህነት ስልጣንን ሲሰጥ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-11ን እና የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን መመለስን የሚያሳዩውን ስዕል 3-12ን ያሳዩ። እነዚህ በነቢዩ በረከቶች በዮሴፍ ስሚዝ አማካኝነት እንዲመለሱ ስለፈቀዱ ለሰማይ አባት እና ኢየሱስ

ክርስቶስ ምስጋናን ግለጹ። በዚህ ዓመት ጥምቀት ለአባልነት ማፅደቅን፣ ቁርባንን እና ቤተመቅደሶችን በተመለከተ ብዙ ትምህርቶች እንደሚኖሯቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። የሰማይ አባት ልጆች ከሚወዷቸው ቤተሰቦቻቸው ጋር ለዘለዓለም እንዲኖሩ፣ እና በእነዚህ ስርዓቶች አማካኝነት ወደ እርሱ መመለስ እንዲችሉ ለማድረግ እቅድ እንዳለው ለልጆቹ ያረጋግጡላቸው።

**የክህነት ስልጣን ሁሉንም ሰው መባረክ ይችላል**

ውይይት

- አባትህ ወይም ሌላ የክህነት ስልጣን ያለው ሰው እጁን በራስህ ላይ በመጫን በረከት ሰጥቶህ ያውቃልን? (ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ልጆቹን ያበረታቷቸው። በረከቱን ማን እንደሰጣቸው እና በረከቱ ለምን እንደሆነ ለማወቅ ጠይቁ።)

ስለ ባርኮት የሚከተሉትን ነጥቦች ከልጆቹ ጋር ይወያዩባቸው፣

1. በረከት የሚሰጠው የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ባለው ሰው ነው። የክህነት ስልጣን ያለው ሰው ለኢየሱስ ክርስቶስ የመስራት ሃይል አለው። ይህ ሰው አባትህ፣ ወንድምህ፣ አያትህ፣ ጳጳሱ ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ፣ ወንጌላዊያን፣ የቤት ለቤት አስተማሪህ፣ ወይም ማንኛውም ብቁ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያለው ሰው ሊሆን ይችላል።
2. በክህነት ስልጣን የሚሰጡን በረከቶች በሙሉ እኛን ለመርዳት ነው።
3. የተለያዩ ዓይነት በረከቶች አሉ።

ቀጥሎ ልዩ ስለሆኑ ሁለት የክህነት ስልጣን በረከቶች እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

**የክህነት ስልጣን ያላቸው ህፃናትን መሰየም እና መባረክ ይችላሉ**

ስዕል

አባት ህፃን ልጁን ሲባርክ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-21ን ያሳዩ።

- በዚህ ስዕል ላይ የምናየው ምንድን ነው? (አንድ ሕጻን እየተባረከ እና ስም እየተሰጠው ነው።)

  ህፃን ልጅ ሲባረክ ለመጨረሻ ጊዜ ያዩበትን ጊዜ ልጆቹን ይጠይቋቸው።

- ህፃኑ ልጅ ሲባረክ የተሰማህ ስሜት እንዴት ነበር? (ልማዳቸውን እና ስሜታቸውን እንዲያካፍሉ ልጆቹን ያበረታቷቸው።)

**የክህነት ስልጣን ያላቸው ህሙማንን መፈወስ ይችላሉ**

የእምነት አንቀፅ

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንደመሆናችን መጠን፣ ህሙማንን መባረክ በሚባለው ሌላ የበረከት ዓይነት እንደምናምን ለልጆቹ ይንገሯቸው። በረከትን ማስተላለፍ ማለት በረከትን መስጠት ማለት እንደሆነ ያስረዱ። ሰባተኛውን የእምነት አንቀፅ ድምጽዎን ከፍ አድርገው ያንብቡ እና “በመፈወስ ስጦታ እናምናለን” የሚለውን ሃረግ ልጆቹ ደግመው እንዲሉት ይርዷቸው። እንዲህ ዓይነት በረከት በመከተል ፈውስ ሊሆን የሚችለው የሰማይ አባት ፈቃድ ሲሆን እንደሆነ ልጆቹን ያስታውሷቸው።

ስዕል

አባት በሽተኛ ህፃን ልጁን ለመባረክ ሲዘጋጅ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-20ን ያሳዩ። አንድ ሰው ሲታመም፣ የክህነት ስልጣን ያላቸው በማንኛውም ጊዜ ልዩ በረከት ሊሰጡት ወይም ሊሰጧት እንደሚችሉ ያስረዱ። ስንታመም እንድንባረክ መጠየቁ ጥሩ ነገር ነው። ህሙማንን ስለመባረክ የሚከተለውን ያስረዱ፣

1. ብትታመም እና በረከት ቢያስፈልግህ፣ ለወላጆችህ መንገር ትችላለህ። አባትህ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ካለው፣ ምናልባት ሌላ ብቁ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያለው ሰው ለአንተ በረከት ለመስጠት እንዲያግዘው ከቤተክርስቲያን መጠየቅ ይችላል። አባትህ የመልከጼዴቅ የክህነት ሥልጣን ከሌለው፣ የቤት ለቤት አስተማሪዎችህን፣ አያትህን፣ አጎትህን፣ ጳጳሱን ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን፣ ወይም ሚሲዮናዊያንን ለበረከት መጠየቅ ትችላለህ።
2. ህሙማንን የሚባርኩ፣ ወይም በረከትን የሚሰጡ፣ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ባላቸው ሁለት አባላት የተቀደሰውን (ልዩ በረከት የተሰጠውን) ንፁህ የወይራ ዘይት ይጠቀማሉ። የቀባ ቀዱስ መያዣ ጠርሙስ ለልጆቹ ያሳዩአቸው።

3. ህሙማንን የመባረኪያ ሁለት ክፍሎች አሉ፥ መጀመሪያ፣ የክህነት ስልጣን ካላቸው ሰዎች አንዱ በታመመው ሰው ራስ ላይ ከላይ ትንሽ መጠን ያለው ዘይት ያደርግ እና አጭር ፀሎት ይፀልያል። ሁለተኛ፣ ሁለቱም የክህነት ስልጣን ያላቸው እጃቸውን በታመመው ሰው ራስ ላይ ይጭኑና፣ አንዱ ሌላ ልዩ ፀሎት በመፀለይ የተቀባውን በማያያዝ፣ የሰማይ አባት የተነሳሳውን በረከት አብሮ ይሰጣል።

እምነት ሲኖረን እና የክህነት ስልጣንን በረከት ስንቀበል፣ የሰማዩ አባት እንደፈቃዱ እንደሚባርከን ለልጆቹ ያስረዷቸው። ሁልጊዜ የሚያደርገው ለህይወታችን መልካም የሆነውን ነው።

የአስተማሪው ልምድ

በረከትን ከተቀበለ በኋላ ስለተፈወሰ በሽተኛ ሰው የነበረዎትን ወይም የሚያውቁትን የግል ልምድ ያካፍሉ። ለክህነት ስልጣን እና ለፈውስ ስጦታ እንዴት እንደምታመሰግኑ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

**አባታዊ በረከት**

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ በመናገር ስለሌላው ልዩ ዓይነት የክህነት ስልጣን በረከት ለልጆቹ ይንገሯቸው (ታሪኩን ሲናገሩ እና በታሪኩ የተካተቱትን መሰረተ ሃሳቦች ሲወያዩ የክህነት ስልጣን በረከት ሊሰጣቸው የሚችል አባት ለሌላቸው ልጆች አስቡላቸው)፣

ምንም እንኳ ለብዙ ጊዜ ስትጠብቀው ብትቀይም፣ መሊሳ ትምህርት ስለመጀመሯ ትጨነቅ ነበር። መሊሳ ከዚህ በፊት ትምህርት ቤት ሄዳ አታውቅም፣ እናም ምን እንደሚመስል አታውቅም ነበር። አስተማሪዋን አታውቅም፣ እናም ሌሎቹ ተማሪዎች አነማን እንደሆኑ አታውቅም ነበር።

ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ባለው ምሽት፣መሊሳ የምትለብሳቸውን ልብሶች አዘጋጀች እና ለመኝታ ተዘጋጀች። ወዲያውም ወደ ሳሎን፣ ሆዷን እያሸች መጥታ እንዲህ አለች፣ “ጤና አይሰማኝም፣ የታመምኩ ይመስለኛል።” የመሊሳ ወላጆች እንዲሻላት ሊረዷት እንደሚፈልጉ ነገሯት። እናቷ አቀፈቻት። አባቷ ትምህርት ቤት ስለመሔድ የተጨነቀች መሆኗን እንዳወቀ ነገራት።

በትምህርት ቤት የሚያስደስት ልምድ እንዲኖራት የሚረዳትን አንድ ነገር ሊሰጣት እንደሚችል። በክህነት ስልጣን ሃይል ልዩ አባታዊ በረከትን ሊሰጣት እንደሚችል ገለጸላት።

አባታዊ በረከት እንዲሰጣት እንደምትፈልግ መሊሳ ተናገረች። ስለዚህም የመሊሳ አባት በራሷ ላይ እጁን ጫነ እና በረከት ሰጣት። ብዙ ጓደኞች እንድታፈራ እና የሚወዳት እና እንድትማር የሚረዳት መልካም አስተማሪ እንዲኖራት ባረካት።

ከበረከቱ በኋላ፣ መሊሳ እጆቿን በአባቷ ላይ ጠመጠመች እና አባታዊ በረከትን ስለሰጣት አመሰገነችው። ተሽሎኛልም አለች።

- እርዳታ የፈለጋችሁበት ችግር ምን ነበር?
- ከእናንተ አባታዊ በረከት ስለተቀበላችሁበት ጊዜ መናገር የሚችል አለ?

የተለየ ችግር ሲኖርባቸው አባታቸውን አባታዊ በረከት እንዲጠይቁ ልጆቹን አበረታቷቸው። አባታቸው የክህነት ስልጣን የሌለው ከሆነ፣ ማንኛውም ብቁ የክህነት ሥልጣን ያለው፣ የቤት ለቤት አስተማሪያቸው፣ ጳጳሱ ወይም የቅርንጫፍ ፕሬዝዳንቱ፣ ወንጌላውያን፣ ወይም እንደ አጎት ወይም አያት ያሉ ሌሎች የክህነት ስልጣን ያላቸው ዘመዶች ባስፈለጋቸው ጊዜ ልዩ በረከት ሊሰጧቸው እንደሚችሉ አስረዷቸው። (የክህነት ስልጣን በቤታቸው ተቀባይነት ለሌለው ልጆች በጣም አስቡላቸው።)

መዝሙር

“የክህነት ስልጣን ተመልሷል” የሚለውን መዝሙሩ ይዘምር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ይበሉ።

**ማጠቃለያ**

ደብዳቤዎች

ያዘጋጁትን ደብዳቤዎች አስተላልፍ። ደብዳቤዎቹ ምን እንደሚሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። እያንዳንዱ ልጅ በትክክል እንዲናገረው እና በደብዳቤው ሥር ስሙን ወይም ስሟን እንዲፈርሙ ይርዷቸው። ልጆች ስለተቀበሏቸው የክህነት ስልጣን በረከት እና በጀማሪዎች ክፍል ስለተማሩት በረከት ከወላጆቻቸው ጋር እንዲነጋገሩ ያበረታቷቸው።

የአስተማሪው ምስክርነት

የክህነት ስልጣን ከሃይሉ ጋር በምድር ላይ እንደተመለሰ እና ህይወታችንን ለመባረክ ከሰማይ አባት የተሰጠን ልዩ ስጦታ እንደሆነ ምስክርነትዎን ይስጡ። በክህነት ስልጣን እና ኃይል አማካኝነት፣ ከሰማይ አባታችን ጋር ተመልሰን ለመኖር እና በምድር ላይ የተሻለ ህይወትን ለመኖር የሚያስፈልገንን በረከት እና ስርዓትን መቀበል እንችላለን።

አንድ ልጅ ልዩ ስለሆነው የክህነት ስልጣን በረከት የሰማዩን አባት በማመስገን የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. ልጆቹ በእጃቸው አካባቢ በወረቀት ላይ በከለር ምልክት እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው። ስንታመም፣ የክህነት ስልጣን ያለው ሰው በረከት ሊሰጠን የፍቀር እጆቹን በራሳችን ላይ መጫን እንደሚችል አስታውሷቸው። ሌላስ መቼ ነው እጆችን በራሳችን ላይ የሚጫኑት? (ዕድሚያቸው ከፍ ያለ ልጆች ምልክት በተደረገበት እጅ በእያንዳንዱ ጣት ላይ ለምሳሌ ለአባልነት ማፅደቅ፣ የክህነት ስልጣን ሹመቶች፣ እና አባታዊ በረከቶች። ዕድሚያቸው ትንሽ ለሆኑ ልጆች፣ በቀላሉ ስለ እነዚህ ሌሎች በረከቶች ይናገሩ።)

2. አንድ አባትና አዲስ ህፃን ልጁ ወደ ክፍል እንዲመጡና ከልጆቹ ጋር እንዲነጋገር ዝግጅት ያድርጉ። አባተየው ስለ ህጻኑ በረከት እንዲናገር ያድርጉ፣ ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፥
   - የህፃኑን ሙሉ ስም በበረከቱ ላይ ተጠቀመውት ነበርን? ምንድነው?
   - ህፃኑን የባረከው ማነው፣ እናም የያዘው ስልጣንስ ምንድን ነበር?
   - በባርኮቱ የረዳው ማነው፣ እናስ እንዴት ነበር የረዱት?
   - ይህ ለህፃኑ ልዩ ቀን የነበረው ለምንድነው?
   - ህፃኑ የተቀበለው ልዩ በረከት ምንድነው? (ይህንን የምትወያየው ተገቢ ሲሆን ብቻ ነው።)

3. በሚቀጥለው ገፅ ላይ እንዳለው ዓይነት፣ ለሚከተሉት ዕንቆቅልሾች መልሳቸውን የሚያመለክቱ ቀላል ስዕሎች አዘጋጁ እና ቆራርጡ። ያዘጋጁትን ስዕሎች አስተላልፍ። እያንዳንዱ ልጅ የራሱን ስዕል ከፍ አድርጎ እንዲይዝ እና ምንን እንደሚያመለክት እንዲናገር ያድርጉ።

   አንዳንድ እንቆቅልሾችን እንደሚያነቡ እና፣ ልጆቹ የትኛው ስዕል ለእንቆቅልሹ መልስ እንደሚሆን እንደሚወስኑ አስረዱ። ለእንቆቅልሹ መልስ የያዘውን ልጅ በተገቢው የበረከት ስዕል ላይ እንዲያስቀምጠው ያድርጉ። (አንዳንድ ስዕሎች ከአንድ በላይ በረከት ጋር ሊሔዱ ይችላሉ።)

   ሀ. የማገለግለው የታመመ ሰው በረከት ሲሰጠው ነው። የክህነት ስልጣን ያለው ሰው የኔን ትንሽ መጠን ጠብታ በታመመው ሰው ራስ ላይ ያደርጋል። እኔ ማን ነኝ? (ቀባ ቅዱስ።)


   ለ. መራመድ አልችልም፣ መናገር አልችልም፣ በጣም ልጅ ነኝ። በረከትና ስም እንዲሰጠኝ እፈልጋለሁ። እኔ ማን ነኝ? (ሕፃን ልጅ።)

   ሐ. ልዩ በረከት እፈልጋለሁ። ከፍተኛ ትኩሳት አለኝ። እንዲሻለኝ እንዲረዳኝ አባቴን በረከት እንዲሰጠኝ ጠየቅኩት። እኔ ማን ነኝ? (የታመመ ልጅ።)

መ. የክህነት ስልጣን የሚባል ልዩ ኀይል ተሰጥቶኛል። ልጆች አሉኝ። ለልጆቼ አባታዊ በረከት ልሰጣቸው እችላለሁ። እኔ ማነኝ? (አባት።)

ሠ. የታመመ ሰው በረከት ሲጠይቅ፣ ቢያንስ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን ያላቸው ሰዎች በረከቱን እንዲሰጡ ይጠራሉ። ያ ቁጥር እኔ ነኝ፣ እኔ ማነኝ? (ቁጥር 2።)

ረ. የክህነት ስልጣን ያለው ሰው ህፃንን ሲባርክ፣ ህሙማንን ሲባርክ፣ ወይም አባታዊ በረከትን ሲሰጥ እኔን ይጠቀማሉ። በሰውዬው ራስ ላይ ያደርጉኛል ወይም ህፃኑን ለመያዝ ይጠቀሙብኛል። እኔ ማን ነኝ? (እጆች።)



ትምህርት

# 10

# ንስሀ

**ዓላማው** የንስኃን መሰረተ ሃሳብ እና በህይወታቸው ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ልጆቹ እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

2. በትምህርት 7 የተዘጋጀውን “የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን” የሚለውን ሰንጠረዥ፣ “እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ” ከሚለው የቃል መስመር ጋር በቦታው ይጠቀሙ። “ንስኃ” የሚለውንም የቃል መስመር በዚህ ትምህርት ውስጥ ለመጠቀም ይዘጋጁ። (አራተኛውን የእምነት አንቀፅ ከልጆቹ ጋር ለመከለስ መዘጋጀት እና መሰረተ ሃሳቡን በትምህርቱ ውስጥ ስትወያዩበት ሁሉንም ወይም በከፊል በቃላቸው ማጥናት የሚችሉትን ልጆች መርዳት ጥሩ ሊሆን ይችላል።)

3.የሚከተሉትን የቃላት መስመሮች ያዘጋጁ (በትምህርት 22 እንደገና እንድትጠቀሙባቸው ያስቀምጧቸው)፣

| |
|---|
| መፀፀት |
| ምህረት መጠየቀ |
| ስህተትን ማረም |
| ስህተትን አለመድገም |

4. “ውዱ አባት፣ እርዳኝ” የሚለውን መዝሙር ሁለተኛውን ቁጥር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 99)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

5. ዕድሜያቸው ከስምንት ዓመት በታች የሆኑ ልጆች ተጠያቂዎች እንደማይሆኑ፣ ማናቸውም ልጆች ጥፋተኝነት ሊሰማቸው እንደማይገባ ያስታውሱ።

6. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ሞርሞን፣ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. ማጣበቂያ።
   ሐ. ፋሻ።

7. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካበረታቱአቸው ይከታተሏቸው።

## ስህተት የሆኑ ምርጫዎችን ስንመርጥ ንስኃ መግባት ይኖርብናል

የአትኩሮት ተሳትፎ

ፋሻውን ለልጆቹ ያሳዩአቸው።

- ከእናንተ ውስጥ ተቆርጦ የሚያውቅ አለን?
- እንዴት ነው የሚሰማው?
- ስንቆረጥ ማድረግ የሚገባን ምንድነው? (ማፅዳትና በፋሻ መጠቅለል።)
- የተቆረጠውን ማፅዳትና መጠቅለል ያለብን ለምንድነው? (በፍጥነት እንዲድን እንዲረዳው።)

ስህተት የሆነ ነገር ስንሰራ፣ እንደመቆረጥ ይመስላል። ስህተት እንደሰራን ስለምናውቅ ውስጣችንን ይጎዳናል እናም እንድንከፋ ያደርገናል። ንስኃ ስህተት ስንሰራ ይረዳናል። መንፈሳዊ ጉዳትን የምንፈውስበት እና የምናፀዳበት መንገድ ነው።

“ንስኃ” የሚለውን የቃል መስመር መሬት ላይ ለጥፍ።

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፦

ሪካርዶ ለእናቱ ትንሽ ክሮች ለመግዛት መደብር ነበር። በሱቁ የመሸጫ ጠረጴዛ ላይ አንዳንድ ከረሜላዎችን ተመለከተ። ጥቂት ፈልጎ ነበር ነገር ግን በቂ ገንዘብ አልያዘም። የመደብሩ ጠባቂ ክሩን መፈለግ ሲሔድ፣ ሪካርዶ ጥቂት ከረሜላዎችን ወደ ኪሱ ከተተ። የመደብሩ ጠባቂ ሲመለስ፣ ሪካርዶ የክሩን ሂሳብ ከፈለ። ከረሜላውን ወደ ቤቱ ሲሄድ በመንገድ ላይ በላው። በኋላም ሪካርዶ ወላጆቹ ስላስተማሩት አንድ ነገር ማሰብ ጀመረ።

ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ ዘፀአት 20፥15ን እንዲያነብ ያድርጉ ወይም እራስዎ ድምጽዎት ከፍ አድርገው ያንብቡ።

- ሪካርዶ የተሰማውን ስሜት ምን ይመስላችኋል (የማዘን ስሜት?)
- ሪካርዶ የሰራው ስህተት ምን ነበር? (ጥቂት ከረሜላዎችን ሰርቋል።)
- ከዚህ የማዘን ስሜት ለመውጣት ሪካርዶ ምን ማድረግ ይችላል? (ንስሃ መግባት።)

“ንስኃ” ከሚለው የቃል መስመር ስር “መፀፀት” የሚለውን የቃል መስመር ይለጥፉ።

ስህተት እንደሰራን ስንገነዘብ፣ ስህተት እንደሰራን ማመንና ስለሰራነው መፀፀት አለብን። ይህ ስሜት የሰማይ አባት ስህተት የሆነ ነገር እንደሰራን እንድናውቅ የሚረዳበት መንገድ ነው።

ሪካርዶ ማድረግ ያለበት ቀጣዩ ነገር ለሰራው ነገር ይቅርታ መጠየቅ እንደሆነ ያስረዱ። “ይቅርታ መጠየቅ” የሚለውን የቃል ካርቶን ሌላ ልጅ እንዲለጥፍ ያድርጉ።

- ሪካርዶ ይቅርታ መጠየቅ የሚያስፈልገው ማንን ነው (የሰማይን አባትን እና የመደብሩን ጠባቂ።)

ስህተት ስለሆኑት ምርጫዎቻችን ንስኃ ስንገባ፣ የሰማይ አባትን እና ስህተት የሰራንበትን ሰው ይቅር እንዲሉን መጠየቅ አለብን። ስህተት የሆነ ምርጫ እንደመረጥን ማፈር እና ስለሰራነው ይቅር እንድንባል መጠየቅ እንዳለብን ያስገንዝቡ።

- የሰማይ አባት ይቅር እንዲለን የምንጠይቀው እንዴት ነው? (በፀሎት እንጠይቃለን።)

ሪካርዶ ማድረግ ያለበት ሶስተኛው ነገር ስህተቱን ለማረም መጣር እንደሆነ ያስረዱ። “ስህተትን ማረም” የሚለውን የቃል መስመር ሌላ ልጅ ከሌሎቹ የቃላት መስመሮች ስር እንዲለጥፍ ያድርጉ። ስህተት በሆኑ ምርጫዎቻችን ምክንያት የፈጠርነውን ማንኛውንም ችግር ለማስተካከል መሞከር እንደሚያስፈልገን እንዲገነዘቡት እርዷቸው። አንዳንድ ጊዜ ችግሮችን ማስተካከል አንችልም (ለምሳሌ ያበላሸነውን ነገር መተካት)፣ ነገር ግን የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልገናል።

- ሪካርዶ ስህተቱን ማረም የሚችለው እንዴት ነው? (ወደ መደብሩ መመለስ እና ለከረሜላው መክፈል ወይም ለመደብሩ ጠባቂ ያለክፍያ አንዳንድ ስራዎችን መስራት።)

ሪካርዶ ማድረግ ያለበት ሌላው ነገር ያንን የስህተት ምርጫ ዳግም ላለመምረጥ መወሰን እንደሆነ አስገንዝቡ። “ስህተትን አለመድገም” የሚለውን የቃል መስመር ሌላ ልጅ ከሌሎች የቃላት መስመሮች ስር እንዲለጥፍ ያድርጉ። ሪካርዶ ያንን ስህተት ምርጫ እንደገና ላለመምረጥ በመወሰን ማጠቃለል አለበት። ስህተት በመስራቱ ከተፀፀተ፣ እና ለማመን ፈቃደኛ ከሆነ፣ ይቅር እንዲባል ይቅርታ ከጠየቀ፣ ስህተቱን ለማረም ከጣረ፣ እና ያንን ስህተት ምርጫ እንደገና ላለመምረጥ ከወሰነ በእውነት ንስኃ እንደገባ ያውቃል። እያንዳንዱን የንስኃ ደረጃ ስትሉ፣ ተገቢውን የቃል መስመር ያሳዩ።

| | |
|---|---|
| መዝሙር | “ውዱ አባቴ፣ እርዳኝ” የሚለውን መዝሙር ሁለተኛውን ቁጥር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ |

**ንስኃ የእውነተኛው ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን አንደኛው ደረጃ ነው**

| | |
|---|---|
| ሰንጠረዥ እና ውይይት | ኢየሱስ ክርስቶስ የእርሱ ቤተክርስቲያን አባላት ስንሆን ስለስህተቶቻችን ንስኃ መግባት እንድንችል፣ እንዴት ንስኃ እንደምንገባ እንድናውቅ እንደሚፈልግ አስረዱ። |

ከትምህርት 7 ላይ “የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን” የሚለውን ሰንጠረዥ ያሳዩ።

ቀደም ሲል በነበረው ትምህርት የእውነተኛው ቤተክርስቲያን አባል በመሆን በሚለው ላይ ወደ አንድ ደረጃ ስለሚለው እንደተማሩ ለክፍሉ አስታውሷቸው። ያ ደረጃ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። “ንስኃ” የሚለውን የቃል መስመር ከማሳያው አካባቢ አንሱ እና “እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ” ከሚለው የቃል መስመር በላይ ካለው ሰንጠረዥ ላይ አድርጉት።

የእውነተኛው ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን አስፈላጊ የሆኑትን እነዚህን ሁለት ደረጃዎች—ንስኃ እና እምነትን ልጆቹ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲሉ ያድርጉ።

ከተጠመቅን በኋላ ስህተት በምንሰራበት በማንኛውም ጊዜ በህይወታችን ሙሉ ንስሀ መግባት እንዳለብን ይግለጹ። በእውነት ንስኃ በምንገባበት ጊዜ፣ ይቅር እንደሚለን እና ኃጢአታችንን ዳግም እንደማያስታውሰው አዳኝ ቃል ገብቶልናል።

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 58፥42ን ለልጆቹ አንብቡላቸው።

- ንስኃ ከገባን ኢየሱስ ለእኛ የሰጠን ታላቁ ቃልኪዳን ምንድነው?

| | |
|---|---|
| የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ | ንስኃ የህይወታችን አስፈላጊው ክፍል መሆን እንዳለበት ያስረዱ። ዕድሚያችን ስምንት ከደረሰ በኋላ፣ ለምናደርጋቸው ምርጫዎች ኃላፊዎች እንሆናለን። ሁልጊዜ ትክክለኛ ምርጫዎችን እንደማንመርጥ ኢየሱስ ያውቃል። ይወደናል እናም የተሳሳቱ ምርጫዎቻችንን የምናሸንፍበትን መንገድ ሰጥቶናል። ከእርሱ እና ከሰማይ አባት ጋር ተመልሰን መኖር እንድንችል ንስኃ መግባት እንዳለብን ነግሮናል። |

**ማጠቃለያ**

| | |
|---|---|
| መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ | የ3ኛ ኔፊ 9፥22 የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ድምጽዎትን ከፍ አድርገው አንብቡት ወይም ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ እንዲያነበው አድርጉ። |

ንስኃ ከሰማይ አባታችን ጋር እንደገና ለመኖር እንድንዘጋጅ ሊረዳን የሚችል በጣም አስፈላጊው በረከት እንደሆነ ያስረዱ። ስህተታችንን ለማስተካከል የተቻለንን ካደረግን በኋላም እንኳ፣ የሰማይ አባት ምህረት የሚያደርግልን በኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ ምክንያት ብቻ እንደሆነ ያስረዱ። (2ኛ ኔፊ 25፥23ን ተመልከቱ።)

| | |
|---|---|
| የአስተማሪ ምስክርነት | ስለ ንስኃ መሰረተ ሃሳብ ምስክርነትዎን ይስጡ፣ እና ልጆቹ ንስኃን እንደገና ቤት ውስጥ እንዲያስረዷቸው ወላጆቻቸውን እንዲጠይቋቸው ይጋብዟቸው። በዚህ ምድር ላይ መደሰት እንድንችል እና በመጨረሻም አንድ ቀን ከእነርሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር እንድንመለስ ስህተታችንን ማረም እንዲቻል ስላደረጉ ለሰማዩ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለዎትን ምስጋና ይግለጹ። |


አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**


ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፤ “ለአስተማሪው ዕርዳታ” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. ለእያንዳንዱ ልጅ የሚከተለውን ሉክ ያዘጋጁ። ለንስኀ የተጠቀሙባቸውን አራት ደረጃዎች ልጆቹ እንዲጽፉ ያድርጉ። ዕድሜያቸው አነስተኛ ለሆነ ልጆች ለሁለት ፊቶች ክቦችን ሳሉላቸው እና ልጆቹ ራሳቸው በክቦቹ ውስጥ ፊቶች እንዲስሉ ያድርጉ። እንዴት ንስኀ እንደሚገቡ እንዲያስታውሳቸው እና የመከፋት ስሜታቸውን ወደ ደስታ ለመለወጥ ልጆቹ ይህን ወረቀት በቀላሉ ሊያዩት በሚችሉበት ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡት ሃሳብ ያቀርቡ።

ንስኀ ከገባሁ በኋላ የደስታ ስሜት ይሰማኛል።



1.
2.
3.
4.



2. ልጆቹ ለሰሩት አንዳንድ ስህተቶች የመፀፀት ስሜት ሲሰማቸው እና አንድን ሰው ይቅርታ ሲጠይቁ በተግባር እንዲያሳዩ ያድርጉ። ይቅርታ ስንጠይቅ ልባዊነት አስፈላጊ እንደሆነ ይግለጹ። ይህ ልባዊነት በብዛት የሚታየው በድምፃቸው ቀላፄ ነው። ከልብና ከልብ ያልሆነ ይቅርታ እንዴት እንደሚጠየቅ ሁለቱንም ያሳዩአቸው፤እና በትክክለኛው የድምፅ ቀላጼ እና የሰውነት አቋም ይቅርታ መጠየቅን እንዲለማመዱ ያድርጉ።

3. በራስዎ አባባል፤ የአልማ ወጣቱን እና የሞዛያ አራት ወንድ ልጆችን የንስኀ መግባት ታሪክ ይናገሩ (ሞዛያ 27ን ይመልከቱ)። ታሪኩን ሲናገሩ፤ እያንዳንዱን የንስኀ ደረጃ ይጥቀሱ።

ትምህርት

# 11

# ጥምቀት

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ የጥምቀትን አስፈላጊነት የበለጠ እንዲረዳው ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የማቴዎስ ወንጌል 3፥13–17ን፣ 2ኛ ኔፊ 9፥23ን፣ እና ትምህርት እና ቃል ኪዳን 20፥73–74ን በፀሎት ያጥኑ።
2. "የልደት ቀኔን እወዳለሁ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ለማለት ይዘጋጁ (የልጆች *የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 104)።
3. በትምህርት 7 መጀመሪያ የተጠቀሙበትን "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ ያቅርቡ። በሰንጠረዡ ቦታ ላይ "እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ" እና "ንስሃ" የሚለውን የቃል መስመር ይኑርዎት። "ጥምቀት" የሚለውን የቃል መስመር በትምህርቱ በሰንጠረዡ ላይ ለማድረግ አዘጋጁ።
4. ለስላሳ ኳስ ወይም ትንሽ የእንሰሳ ቅርፅ ያለው መጫወቻ አሻንጉሊት።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ፣ መፅሐፈ ሞርሞን፣ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. ልጁ ሲጠመቅ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-13 (62018)፣ እና መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-1 (62133፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 208)።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

ማስታወሻ፥ የተጠመቁ ልጆች ካሉ ሲያስፈልግ ይህ ትምህርት እንደ አስፈላጊነቱ እንዲሰጥ።

**ለትምህርት ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካበረታታችኋቸው ይከታተሏቸው።

**በስምንት ዓመት ዕድሜያችን መጠመቅ እንችላለን**

ሰንጠረዥ "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ ያሳዩ። አንድ ልጅ "ጥምቀት" የሚለውን የቃል ሰንጠረዥ በሶስተኛው ደረጃ ላይ እንዲያስቀምጥ ያድርጉ። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ጥምቀት ሶስተኛው ደረጃ እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

የአትኩሮት ተሳትፎ ልጆቹ ከመጠመቃቸው በፊት፣ አሳፈላጊ የሆነ ነገር መደረግ እንዳለበት ያስረዱ። ስለ ጥምቀት መዝሙር ሲዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት በሚሉበት ጊዜ እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። አንድ ቃል እንድምታስቀሩ ይንገሯቸው። ያም ቃል ቁጥርም ነው። ልጆቹ እንዲያዳምጡና የቀረውን ቃል ማወቅ እንደሚችሉ ለማየት ጠይቋቸው። ያስቀሩት ቃል ሲያውቁት እጃቸውን ያንሱ።

የልደት ቀኔን እወዳለሁ፣
ታላቅ ደስታን ይሰጡኛል።
ነገር ግን እስከ ስምንት አመቴ አልቆይም፣
ታያላችሁ እጠመቃለሁ።

- የጠፋው ቃል ምንድነው? (ስምንት።)

ሁላችንም የልደት ቀናችንን ሁሉ እንደምንጠብቅ ያስረዱ፣ ነገር ግን የስምንት ዓመት ዕድሚያችን ለመጠመቅ ስለምንደርስ ልዩ ትርጉም አለው።

**የመጠመቅን ትዕዛዝ ኢየሱስ ክርስቶስ ታዘዘ**

| | |
|---|---|
| የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ | የሰማይ አባት ሁሉም ሰው እንዲጠመቅ እንዳዘዘ ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ የሰማይ አባትን ትዕዛዛት ለመታዘዝ ፈለገ። |
| የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ | 2ኛ ኔፊ 9፥23 ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡ። የእስራኤል ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ ስም እንደሆነ ያስረዱ። |

ይህ ጥቅስ እንድንጠመቅ እንደታዘዘን እንደሚነግረን ያስረዱ። ቅዱሳን መጽሐፍም ካልተጠመቅን፣ በእግዚአብሔር መንግስት መዳን እንደማንችል ይነግሩናል፣ በሌላ አነጋገር፣ ከሰማይ አባት እና ከኢየሱስ ጋር እንደገና ለመኖር መጠመቅ አለብን።

ስዕል እና ውይይት — መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-1ን አሳዩ እና ታሪኩን ይናገሩ (የማቴዎስ ወንጌል 3፥13–17)። ልጆቹ መረዳት እንዲችሉ ይህን ጥቅስ የተቻለዎትን ያህል አንብላቸው።

- ኢየሱስን ያጠመቀው ማነው? (መጥምቁ ዮሐንስ።)

ኢየሱስ ለመጠመቅ ወደ ዮሐንስ የመጣው ዮሐንስ ለማጥመቅ የክህነት ሥልጣን ሀይል ስለነበርው እንደሆነ ያስገንዝቡ።

መጥምቁ ዮሐንስ፣ ኢየሱስን ለማጥመቅ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወሰደው። የጥምቀት ፀሎት ከፀለየ በኋላ፣ ዮሐንስ ሙሉ በሙሉ በውኃ ውስጥ አጠለቀው። ከተተው ከዚያም ዮሐንስ ከውሃው ውስጥ አወጣው።

ሙሉ በሙሉ በውሃ ውስጥ መግባት እና ከውሃ ውስጥ በመውጣት መጠመቅ ጥምቀት በመስጠም እንደሚባል ግለጹ። ልጆቹ *ጥምቀት በመስጠም* የሚሉትን ቃላት ደግመው እንዲሉ ያድርጉ።

**ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተጠመቀው እኛም መጠመቅ እንችላለን**

መዝሙር — “የልደት ቀኔን እወዳለሁ” የሚለውን መዝሙር ሁለተኛውን ቁጥር ሲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሚሉበት ጊዜ ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ። ከዚያም ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ከእርሶ ጋር ደግመው እንዲሉ ያድርጉ።

እንደ ኢየሱስ መጠመቅ
በእውነተኛው የክህነት ስልጣን
የእግዚአብሔርን ህግ ማክበር
ነው ማድረግ የምፈልገው

- በዚህ መዝሙር መስረት “ላደርገው የምፈልገው ነገር” ምንድነው? (እንደ “ኢየሱስ መጠመቅ።”)
- ኢየሱስ በተጠመቀው ዓይነት መንገድ የምንጠመቅ ከሆነ እንዴት ነው የምንጠመቀው? (መስጠም እና የክህነት ስልጣን ባለው ሰው።)

ስዕል እና ውይይት — መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቅ ከሚያሳየው ስዕል ቀጥሎ፣ ልጁ ሲጠመቅ የሚያሳየውን ስዕል 3-13ን ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ፣ ሙሉ በሙሉ በውሃ ተሸፍኖ ወይም ሰጥሞ ነበር። ዛሬ፣ ጥምቀት ሁልጊዜ የሚካሄደው በጸሎት ቤት በሚገኝ መጠመቂያ ገንዳ በሚባል ልዩ ኩሬ ውስጥ ነው። በአቀራቢያ የመጠመቂያ ገንዳ ከሌለ፣ ምንጮች ወይም ሌሎች የኩሬ ውሃዎችን መጠቀም ይችላል።

- መጥምቁ ዮሐንስ ለማጥመቅ ያለው ስልጣን ምን ነበር? (አሮናዊ የክህነት ስልጣን።)
- የሚያጠምቀን ሰው ለማጥመቅ ሊኖረው የሚገባው ስልጣን ምንድነው? (በአሮናዊ የክህነት ስልጣን ውስጥ ቄስ መሆን እና የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያለው መሆን አለበት።)

- የክህነት ስልጣን ያለው እና ማጥመቅ የሚችል ሰው ታውቃላችሁን?

**የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ** ዮሴፍ ስሚዝ ከኦሊቨር ካውድሪ ጋር መጽሐፈ ሞርሞንን ሲተረጉም፣ መጥምቁ ዮሐንስ መጥቶ ትክክለኛውን የማጥመቂያ መንገድ እንዳስተማራቸው ለልጆቹ ያስታውሷቸው። የክህነት ስልጣን ሰጥቷቸዋል ስለዚህም ሌሎችን ለማጥመቅ ስልጣን ነበራቸው። ክህነት ሊኖረን እንዲችል ስልጣን ለሌሎች ሰዎች ተሰጥቷል። ትክክለኛ የክህነት ስልጣን ባለው ሰው የመጠመቅ መብት።

**የእምነት አንቀፅ** እያንዳንዳቸውን የሚያጠምቃቸው ሰው ዮሐንስ መጥምቁ የነበረውን ዓይነት ስልጣን እንደሚኖረው ለልጆቹ ያስረዷቸው። አምስተኛው የእምነት አንቀፅ አንድ ወንድ ይህን ስልጣን እንዴት እንደሚቀበል ይነግረናል።

የሚከተለውን ድምጽዎን ከፍ አድርገው አንብቡ እና ልጆቹ እንዲደግሙት ያድርጉ፣

"አንድ ወንድ ስልጣኑ ባላቸው . . . በእግዚአብሔር ሊጠራ እንደሚገባው እናምናለን ።"

### የጥምቀት ስርዓት

**ስዕል እና ገልፃ** ልጁ ሲጠመቅ በሚያሳየው፣ ስዕል 3-13 ላይ፣ እጆችን አቀማመጥ ያመልክቱ። የሚከተሉትን መመሪያዎች ለልጆቹ ያስረዷቸው፡ ስትጠመቁ፣ እናንተ እና የሚያጠምቃችሁ ሰው ወደ ማጥመቂያ ገንዳ ውስጥ ትገባላችሁ። የሚያጠምቃችሁ ሰው ቀኝ እጃችሁን በግራ እጁ ይይዛል። አፍንጫችሁን በቀኝ እጃችሁ መያዝ እና በግራ እጃችሁ የሚያጠምቃችሁን ሰው ግራ እጅ መያዝ ትችላላችሁ። ከዚያም የሚያጠምቃችሁ ሰው ቀኝ እጁን ያነሳና የጥምቀት ፀሎት ቃላትን ይላል።

**የቅዱስ መጽሐፍ** የጥምቀት ፀሎት በቅዱሳን መጽሐፍት እንደሚገኝ ለልጆቹ ይንገሯቸው። የፀሎቱን ቃላት ሲያነቡ እንዲያዳምጡዎት ያድርጉ።

ትምህርት እና ቃል ኪዳን 20፡73ን "በተሰጠው ስልጣን" ከሚሉት ቃላት ጀምሮ ያንብቡ።

*ስልጣን መስጠት ማለት* "ለመወከል ስልጣን መስጠት" ማለት እንደሆነ ያስረዱ። እውነተኛ ጥምቀት የሚከናወነው ጥምቀትን በማከናወን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲወክል ስልጣን በተሰጠው ሰው ብቻ እንደሆነ ልጆቹ እንዲገነዘቡት ይርዷቸው። ጥምቀታቸው ኢየሱስ ቢያጠምቃቸው ሊኖረው የሚችለውን ዓይነት ዋጋ ይኖረዋል።

ፀሎት ከፀለየ በኋላ፣ የሚያጠምቀው ሰው ቀኝ እጁን በሰውየው ጀርባ ላይ ያሳርፍና ውሃው ሙሉ በሙሉ እስኪሸፍነው ድረስ በቀስታ ዝቅ አድርጎ እንዲሚያስገባው ይግለጹ። ከዚያም ሰውየውን ከውሃ ውስጥ ቀና አድርጎ ያወጣዋል።

በውሃ ውስጥ የሚቆዩት ለአጭር ጊዜ እንደሆነ እና የሚያጠምቃቸው ሰው አጠንክሮ እንደሚይዛቸው ልጆቹ እንዲገነዘቡት እርዷቸው። እንዳይተነፍሱ ወይም ምንም ውሃ እንዳይገባባቸው እጁን ይይዙታል እናም አፍንጫቸውን መያዝ ይችላሉ።

**የግል ልምድ** ከፈለጉ፣ ስለራስዎ ጥምቀት መናገር ይችላሉ። ወይም በክፍልዎ ውስጥ የተጠመቁ ልጆች ካሉ፣ ስለ ጥምቀታቸው እንዲናገሩ ይጋብዟቸው።

ልጆቹ ስለ ጥምቀት እና ጥያቄ እንዲጠይቁ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲያካፍሉ ያድርጉ። ጥምቀት ግሩም ልምድ ሊሆንላቸው እንደሚችል ልጆቹ እንዲገነዘቡት ያድርጉ።

### ስንጠመቅ ደስተኞች ነን

ስለ ጥምቀት አስፈላጊ ደረጃ የተማሩትን ለመከለስ ሊጠይቋቸው የሚፈልጉት አንዳንድ ጥይቄዎች እንዳሉዎት ለልጆቹ ይንገሯቸው። ኳስ ወይም የእንስሳ ቅርፅ ያለው ትንሽ መጫወቻ አሻንጉሊት ወደ አንዱ ልጅ ወርውሩ እና የሚከተሉት ጥያቄዎች አንዱን ይጠይቁ። እያንዳንዱ ልጅ መጫወቻውን ለመያዝ እና ጥያቄ ለመመለስ ተራ ማግኘቱን ያረጋግጡ።

- ስንጠመቅ ዕድሚያችን ስንት መሆን አለበት? (ስምንት።)
- መጠመቅ ያለብን ለምንድነው? (ትዕዛዝ ነው።)
- የምንጠመቀው የት ነው? (መጠመቂያ ገንዳ ውስጥ ወይም በሌላ የኩሬ ውሃ።)

- አንድ ወንድ ማጥመቅ ለመቻል ምን ሊኖረው ይገባል? (የክህነት ስልጣን።)
- የምንጠመቀው እንዴት ነው? (በመስጠም።)
- ስትጠመቁ የደስታ ስሜት የሚሰማችሁ ለምን ይመስላችኋል?

ልጆቹ እንዲመልሱ እና ስሜታቸውን እንዲያካፍሉ ይፍቀዱላቸው። የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል በመሆናቸው ደስተኛ እንደሚሆኑ፣ የእርሱን ምሳሌ እየተከተሉ መሆናቸውን በማወቃቸው ደስተኛ እንደሚሆኑ፣ እና ትዕዛዛቱን በመታዘዛቸው ደስተኛ እንደሚሆኑ ሊያብራሩላቸው ይችላሉ።

ታሪክ

ለመጠመቅ ትፈልግ ስለነበር አንዲት ልጃገረድ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፣

"የአሊስ እናት እና እህቶች የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ሲወስኑ፣ አሊስ እድሜዋ ስድስት ዓመት ብቻ ነበር እናም ከተቀሩት ቤተሰቦቿ ጋር ለመጠመቅ በጣም ልጅ ነበረች. . . ሁልጊዜ ስለ ጥምቀት አስደናቂ ልምድና የቤተክርስቲያን አባልነታቸው ስላመጣላቸው ደስታ ስለሚያወሩ፣አሊሳ እሷም መጠመቅ እንድትችል ዕድሜዋ ስምንት እስኪሆን መጠበቅ አልቻለችም።

"አሊስ በልደት ቀኗ እንዴት እንደምትጠመቅ ታቅድ እና ታልም ነበር። 'ከዚያ በኋላ በሌላ ቀን አይደለም፣ የፈለገችው፣ ነገር ግን በዚያው ቀን እንዲሆን ነበር የፈለገችው።

"ይሁን እንጂ፣ አሊስ ስምንተኛ ዓመቷ ሊሞላት ሶስት ቀን ሲቀረው፣ ራስ በሚከፍል ራስ ምታት ከእንቅልፍ ነቃች እና፣ በሚቀጥለው ቀን በጣም ስለታመመች ትምህርት ቤት መሄድ አልቻለችም ነበር።

"የተጠራው ዶክተር ቢያንስ ለሳምንት እቤት መቆየት እና መተኛት አለባት አለ። የአሊስ ትላልቅ አይኖች በተስፋ መቁረጥ እንባ ተሞሉ።

"በሚቀጥለው ቀን እንኳ አሊስ በጣም ደስተኛ አልነበረችም፣ እናም ምንም እንኳ ዶክተሩ መድሃኒት ቢያዝላትም የሰውነቷ ሙቀት ከፍተኛ ነበር። እናቷ ግራ ገብቷት ትጨነቅ ነበር፣ ነገር ግን አሊስ ከሁሉም ህመሚ እና ስቃይ እና ትኩሳቷ የበለጠ ብሶ የተሰማት ልክ በልደቷ የመጀመሪያ ቀን መጠመቅ ያለመቻሏ ነበር።

"ከአሊስ የልደት ቀን በፊት ባለው ከሰዓት በኋላ፣ እናቷ በሽተኛዋ ወደ ተኛችበት ክፍል ልትገባ መንገድ ጀመረች። ነገር ግን አሊስ በጥልቀ ስሜት በአልጋዋ ላይ ለፀሎት ስትንበረከክ አየቻት እና ቆመች። ይህች ትንሽ ልጅ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል የመሆን ታላቅ ፍላጎቷ እንዲሳካላት የሰማዩን አባት እየለመነች ነበር።

"በልደት ቀኗ ጧት፣ አሊስ ተነሳች፣ ለበሰች፣ እና ለጥምቀት ተዘጋጀች። ትኩሳቷ ለቀቃት እና ደኅንነት እና ደስታ ተሰማት። ከጥቂት ሰዓታት በኋላም እናቷ የአሊስን ሙቀት መረመረች እናም ትክክለኛ ነበር።

"(የሰማይ አባት) የአሊስን ልባዊ ፀሎት መለሰላት። የዚያን እለት ማታም አሊስ ተጠመቀች!" ("የልደት ቀን ጥምቀት፣" *Friend,* Oct. 1974, p. 33)።

- አሊስን ብትሆኑ ኖሮ ምን ይሰማችሁ ነበር?

ልጆቹ በትክክለኛው የልደት ቀናቸው ላይጠመቁ እንደሚችሉ ነገር ግን ከስምንት ዓመት የልደት ቀናቸው በኋላ በፍጥነት መጠመቅ እንዳለባቸው ይግለጹ፣ አብዛኛውን ጊዜ በዋርዱ ወይም በቀርንጫፍ ላሉ ልጆች በሙሉ በየወሩ አንድ የጥምቀት ቀን አለ። ከመጠመቃቸው በፊት በጳጳሱ ወይም በቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ቃለ መጠይቅ እንደሚደረግላቸው ይንገሯቸው። ልጆቹ ሲጠመቁ አሊስ የነበራትን ዓይነት የደስታ ስሜት እንዳደሚኖራቸው ያለዎትን ተስፋ ሁልጊዜ በአካባቢዎ ጥምቀት ሲኖር ይንገሯቸው ግለጹላቸው።

### ማጠቃለያ

ለመጠመቅ ዕድሜያቸው ስለሚደርስ ስምንት ዓመታቸው ልዩ ሊሆን እንደሚችል ለልጆቹ አስታውሷቸው።

"የልደት ቀኔን አወዳለሁ" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት ይበሉ።

በሰንጠረዡ ላይ ያሉትን ደረጃዎች ጠቁሙ እና ያንብቧቸው። ልጆቹ ከተጠመቁ በኋላ፣ የቤተክርስቲያን አባል ለመሆን የመጨረሻውን ደረጃ ለመውሰድ እንደሚዘጋጁ ያስረዷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ልትጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪው መርጃዎች በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. ለእያንዳንዱ ልጅ የልደት ቀን ኬክ ስዕል ገልብጡ ወይም ንደፉ። ልጆቹ በኬኩ ላይ ስምንት ሻማዎችን እንዲስሉ እና እንዲያቀልሙት ያድርጉ። "ዕድሜዬ ስምንት እስኪሆን መጠበቅ አልችልም" የሚለውን ስዕል ምልክት ያድርጉ።

   ክፍልዎ የልደት ኬክን ባህል የማያውቁ ከሆኑ፣ በብዙ ሀገሮች፣ ልጆች የልደት በዓላቸውን ሲያከብሩ፣ የልደት ኬክ እንደሚዘጋጅላቸው ያስረዱ። ከተወለዱበት ጀምሮ በየዓመቱ ሻማዎች በኬኩ ላይ ይደረጋሉ። ልጆቹ ዕድሜያቸው ስምንት ሲሆን፣ ስምንት ሻማዎች በኬካቸው ላይ ይኖራቸዋል።


2. ለጥምቀት ለመዘጋጀት ልጆቹ መውሰድ የሚያስፈልጋቸውን ደረጃዎች ይወያዩባቸው። የሚከተሉት እያንዳንዱ ሃሳቦች ሲጠቀሱ፣ በወለሉ ላይ ከወረቀት የተቆረጠ የእግር ኮቴ አስቀምጡ። የእግር ኮቴዎቹ ልጁ ሲጠመቅ ወደሚያሳየው፣ ስዕል 3-13 እንዲያመሩ ያድርጉ።

   - የጀማሪዎችን ክፍል እና የቅዱስ ቁርባንን ስብሰባ በየሳምንቱ ይከታተሉ።
   - ስለ ቅዱሳን መጻሕፍት እወቁ።
   - ታማኝ ሁኑ።
   - በየቀኑ ፀልዩ።
   - አስራትን ክፈሉ።
   - ለቤተሰቦቻችሁ እና ለጓደኞቻችሁ ሁኑ።
   - የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ ይከተሉ።
   - ዕድሜያችሁ ስምንት ዓመት ይሁን።
   - በጳጳሱ ወይም በቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ቃለመጠይቅ ይደረግላችሁ።

3. የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያለው ሰው ወደ ክፍልዎ እንዲመጣ እና በጥምቀታቸው ጊዜ ምን እንደሚደረግ ለልጆቹ እንዲነግራቸው ይጋብዙ። ትክክለኛውን የእጆቻቸውን አቀማመጥ እና የጥምቀት እንቅስቃሴዎችን እንዲያለማምዳቸው ያድርጉ።

4. "ጥምቀት—ኢየሱስን የመከተል ቃል ኪዳን" የሚለውን *የጀማሪዎች ክፍል ቪዲዮ ስብስብ* ከሚለው ላይ (ለ9 ደቂቃ) ለልጆቹ ያሳዩአቸው።

# ዕድሜዬ ስምንት እስኪሆነኝ መቆየት አልችልም



ትምህርት

12

# የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ

**ዓላማው** ልጆቹ የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታቸው ሲረጋገጥ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የመቀበል መብተን እንዲያደንቁ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ዮሐንስ ወንጌል 14፥16–17፣ 26ን ያጥኑ።
2. ከትምህርት 7 ላይ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ ያዘጋጁት። ከክፍሉ ፊት ለፊት፣ በሰንጠረዡ ትክክለኛ እና ቀደም ተከተል ላይ "እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ፣""ንስኃ ፣" እና "ጥምቀት" የሚሉትን የቃላት መስመሮች ያስቀምጡ። "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" የሚለውን የቃል መስመር በትምህርቱ ጊዜ ለመጠቀም ያዘጋጁት።
3. ልጅቷ አባልነት ሲረጋገጥላት (62020) የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-14ን በሳጥን ውስጥ ያስቀምጡ። ከተቻለ፣ ሳጥኑን ስጦታ ለማስመሰል ይጠቅልሉት።
4. "መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 105)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ።
   ለ. ልጅቷ አባልነት ሲረጋገጥላት (62020) የሚያሳየውን ስዕል 3-14፣ የመጨረሻውን እራት የሚያሳየውን ስዕል 3-22፣ (62174፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 225)፣ እና የመጀመሪያውን ራዕይ የሚያሳየውን ስዕል 3-10፣ (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 403)።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ከዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን መቀበል እንችላለን**

የአትኩሮት ተሳትፎ — "የስጦታውን" ሳጥን አሳዩ እና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ፥

- እርስ በእርሳችን ስጦታዎችን የምንሰጣጠው ለምንድነው?
- አንድ ሰው ስጦታ ሲሰጥህ ምን ይሰማሃል?

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ — የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል የሆንበት ቀን በህይወታችን ውስጥ በጣም አስፈላጊው ቀን እንደሆነ ያስረዱ። በዚያ አስደናቂ ጊዜ፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የከበረ ስጦታ ይሰጡናል።

ፍንጮች — ስጦታው ምን እንደሆነ እንዲውያቁ የሚረዷቸውን አንዳንድ ፍንጮች እንደሚሰጧቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ሁሉንም ፍንጮች እስከሚሰጧቸው ድረስ በፀጥታ እንዲያዳምጡ ይጋብዟቸው።

1. የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የሚሰጡን ስጦታ በገንዘብ ሊገዛ አይችልም።
2. ይህን ስጦታ እንደመፅሐፍ እና መጫወቻ በእጃችን ልንይዘው እና ልናየው አንችልም።

3. ይህ ስጦታ ሰው ሊቀበል ከሚችለው ማንኛውም ስጦታ በላይ ዋጋ አለው።
4. ብቁ የቤተክርስቲያን አባላት በህይወታቸው ሙሉ ይረዱበታል እናም ይፅናኑበታል።
5. ይህን ስጦታ የምንቀበለው የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን ያላቸው ወንዶች እጆቻቸውን በራሳችን ላይ ሲጭኑና የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆናችንን ሲያፀድቁልን ነው።

ስጦታው ምን እንደሆነ የሚያውቁት ሁሉ እጃቸውን እንዲያነሱ ይጠይቋቸው።

- ይህ ስጦታ ምንድነው? (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ።)

**ስዕል እና ውይይት**

ስዕሉን ለማወቅ አንድ ልጅ ስጦታውን እንዲከፍት ያድርጉ። ከዚያም ልጁ ሲረጋገጥለት የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩ። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንዴት እንደሚሰጥ ያስረዱ። በስዕሉ ላይ እንደተመለከተው፣ ከሰውየው ጥምቀት በኋላ፣ የመልከጼዴቅ የክህነት ስልጣን የያዙ ሰዎች እጃቸውን በሰውዬው ራስ ላይ ይጭናሉ። ከሰዎቹ አንዱ (አብዛኛው ጊዜ አባት፣ ጳጳሱ፣ ወንጌላዊ፣ ወይም አባልነት የሚረጋገጥለት ሰው ጓደኛ) ፀሎት ይፀልያል። በፀሎቱ ጊዜ፣ ሰውዬው የቤተክርስቲያን አባልነቱ ይረጋገጣል የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ይሰጠዋል።

- ስለመንፈስ ቅዱስ ምን ታውቃለህ?

ልጆቹ ስለመንፈስ ቅዱስ የሚያውቁትን በአጭሩ እንዲናገሩ ያድርጉ። የሚከተሉትን ነጥቦች ያቅርቡ፣

1. መንፈስ ቅዱስ እንደ እኛ የስጋና የአጥንት አካል የለውም። በሰው ቅርፅ መንፈሳዊ አካል አለው።
2. መንፈስ ቅዱስ ስለ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተምረናል እናም ስለ እነርሱ ስለተማርናቸው ነገሮች ምስክርነቱን ይሰጠናል።
3. እውነትን ስንማር የምንሰማው እውነት እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ ምስክርነቱን ይሰጠናል።
4. መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ለመምረጥ እንዲረዳን ከሰማይ አባት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ተልኳል።

**ሰንጠረዥ**

"የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል መሆን" የሚለውን ሰንጠረዥ ያሳዩ።

በሰንጠረዡ አራተኛ ደረጃ ላይ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" የሚለውን የቃል መስመር ያስቀምጡ። ዕድሚው ከፍ ያለ ልጅ ድምፁን ከፍ አድርጎ ቃላቶቹን እንዲያነብ ያድርጉ ወይም ራስዎ ያንብቧቸው፣ ከዚያም ሁሉም ልጆች ቃላቶቹን ከእርሶ ጋር ደግመው እንዲናገሩ ያድርጉ።

በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ የመቀበል መብት እንደሌላቸው ያስረዱ። በረከቱ ያላቸው የተጠመቁ እና የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባል እንዲሆኑ የተረጋገጠላቸው ብቻ ናቸው። አባልነት በሚረጋገጥበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ስንቀበል፣ የቤተክርስቲያኑ ግልጽ አባላት እንደምንሆን ያሳስቡ። እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ ከሚለው በመጀመር፣ በሰንጠረዡ ላይ ያሉትን ደረጃዎች ከልጆቹ ጋር ይከልሷቸው።

**የእምነት አንቀፅ ክለሳ**

በጥቁር ሰሌዳው ላይ የአራተኛውን የእምነት አንቀጽ ቃላትን ይፃፉ። ድምጽዎን ከፍ አድርገው ከልጆቹ ጋር ይድገሙት። ከዚያም ጥቂት ቃላቶችን አጥፉና ከእነርሱ ጋር ድምፅዎን ከፍ አድርገው ይድገሙት። ልምምዱ ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ ጥቂት ቃላቶች ማጥፋትዎን ቀጥሉ።

### ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ ቅዱስን ለመላክ ቃል ገብቷል

**ስዕል**

የመጨረሻውን እራት የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-22ን ያሳዩ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ምሽት፣ ከአስራ ሁለቱ ሐዋሪያቱ ጋር አንድ የመጨረሻ እራት እንደበላ ያስረዱ። በዚያን ጊዜም፣ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር አስተምሯቸዋል። እርሱ ሲሔድ ሐዋሪያቶቹ በጣም እንደሚያዝኑ ያውቅ ነበር። የእርሱ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቅ ነበር። ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ ብቻቸውን እንደማይተዋቸው ነገር ግን እንዲረዳቸውና እንዲያጽናናቸው አንድ አካል እንደሚልክላቸው ቃል ገብቶላቸዋል።

የቅዱስ መጽሐፍ ጥቅስ

ዕድሜው ከፍ ያለ ልጅ ከዮሐንስ ወንጌል 14፥16 ላይ ኢየሱስ ለሐዋርያቶቹ የነገራቸውን እንዲያነብ ይጠይቁ ወይም ራስዎ ያንብቡት።

- የኢየሱስ ለሐዋሪያት ለመላክ ቃል የገባው የአጽናኙ ሌላ ስም ማነው? (መንፈስ ቅዱስ።)

የዮሐንስ ወንጌል 14፥26ን ለልጆቹ ያንብቡላቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን እንዲረዳና እንዲያፅናና መንፈስ ቅዱስን እንደላከ ይግለጹ። ምንም እንኳን ሐዋሪያቱ መንፈስ ቅዱስን ማየት ባይችሉም፣ ሲረዳቸውና ሲያፅናናቸው ይሰማቸው ነበር። ለዚያም ነው አፅናኝ ተብሎ የሚጠራው።

መዝሙር

“መንፈስ ቅዱስ” የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት ይበሉ።

**መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን ይችላል**

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታችን፣ መንፈስ ቅዱስ ሐዋሪያትን እንደረዳን እና እንዳጽናናን እኛም የዚያኑ አይነት ተመሳሳይ መብት እንዳለን ያስረዱ። የመንፈስ ቅዱስ ጓደኝነት በዚህ ህይወት ልንደሰትበት የምንችለው አንድ ታላቁ ስጦታ እንደሆነ ግለጹ። ብቁ ከሆንን እና በቅድስና ከኖርን ሁልጊዜ ጓደኝነቱ ሊኖረን እንደሚችል ያስረዱ።

አስቸጋሪ ምርጫዎችን መምረጥ ሲኖርብን መንፈስ ቅዱስ ምን እንደምናደርግ እንድናውቅ እንደሚረዳን ለልጆቹ ይንገሯቸው። ሲፈሩ ወይም ሲጎዱ ከመንፈስ ቅዱስ የሚሰማቸውን ስሜት እንዲከተሉ ልጆቹን ያበረታቷቸው። ለምሳሌ ሊረዳቸው ለሚችል ሰው እንዲናገር በመገፋፋት፣ ማድረግ የሚገባቸውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ። ልጆቹ እንዲያዳምጡና ጃን የተባለችውን ልጅ መንፈስ ቅዱስ እንዴት እንደረዳት እና እንዳፅናናት ለማወቅ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው፡-

ጃን አብዛኛውን የህይወቷን ክፍል የኖረችው በትንሽ የገጠር መንደር ነው። መንደሩን እና እዚያ የሚኖሩትን ሰዎች ትወዳቸዋለች። ጃን የሚቀራረቡ ሰዎች ባሉበት መንደር መኖሩ ምን ያህል አስደናቂ እንደሆነ አብዛኛውን ጊዜ ታስባለች።

አንድ ቀን፣ የጃን አባት ከስራ ወደቤት መጣ እና ስራውን እንደሚቀይር እና ወደ ትልቅ ከተማ እንደሚዘዋወሩ ነገራቸው።

- ጃን የተሰማት እንዴት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ጃን ስለመልቀቀ ባሰበች ቁጥር መከፋት እና ሐዘን ይሰማት ነበር። በቅርብ ጊዜ ጓደኞቿን፣ ቤቷን፣ ትምህርት ቤቷን እና ዋርዷን ትታ እንደምትሔድ ማሰቡ ለእርሷ በጣም ከባድ ነበር።

ጃን ተጨንቃ ነበር። አዲስ ጓደኞችን ለማፍራት አስቸጋሪ ጊዜ ይኖረኛል ብላም ተጨነቀ ነበር። አዲሱ ቤቷ እና ዋርዷ ምን ይመስላል? የትምህርት ቤቷ ስራ በጣም ይከብዳታልን?

ከጭንቀት ስሜቷ እንድትወጣ የረዳት ማንም የለም። ጃን የሰማይ አባት እንዲረዳት ለመፀለይ እና ለመጠየቅ ወሰነች።

ጃን በሙሉ ልቧ ለሰማዩ አባት ፀለየች። እየፀለየች እያለ፣ አስደናቂ የሆነ ነገር መሆን ጀመረ። ሁሉም የፍርሃት እና የጭንቀት ስሜት ይለቃት ጀመር።

ጃን አንድ ሰው ያፅናናት እንደነበር ተሰማት።

- ጃንን ያፅናናት ማነው ብላችሁ ታስባላችሁ? (መንፈስ ቅዱስ።)

የጃን ቤተሰቦች ለቀቁ፣ እናም ሁሉም ነገር ጥሩ ሆነ። ሁልጊዜ ከሰማዩ አባት በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የተቀበለችውን የፍቅር ዕርዳታ ታስታውሰዋለች።

የአስተማሪው ልምድ እና ምስክርነት

በመንፈስ ቅዱስ ስለተፅናኑበት ጊዜ መናገር ትፈልጉ ይሆናል፣ ለምሳሌ በፈሩበት ጊዜ ወይም የሚወዱትን በአጡበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊያጽናናን እና ሊመራን እንደሚችል ምስክርነትዎን ይስጡ። ከጥምቀታችን ቀጥሎ የምንቀበለው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን የሰማይ አባት በሕይወታችን ሙሉ ትክክለኛውን ለመምረጥ እንዲረዳን ሁልጊዜ ሊሰጠን የሚችለው እጅግ ከከበሩ ስጦታዎች አንዱ ነው።

**ማጠቃለያ**

እንደ ቤተክርስቲያን አባልነታችን በመንፈስ ቅዱስ እንደምናምን ይግለጹ። ትዕዛዛትን ከታዘዝን የሚያስፈልገንን ዕርዳታ እና ማፅናናት እንደሚሰጠን እናውቃለን።

የእምነት አንቀፅ

የመጀመሪያው የእምነት አንቀፅ ስለመንፈስ ቅዱስ እንደሚያስረዳ ይግለጹ።የመጀመሪያውን የእምነት አንቀጽ ከልጆቹ ጋር ይድገሙት። መጀመሪያውን ራዕይ የሚያሳየውን ስዕል 3-10ን፣ እና ልጅቷ አባልነት ሲረጋገጥላት፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-14ን፣ የእምነት አንቀፅን ሲያነቡ በተገቢው ነጥቦች ላይ ያሳዩ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ፣ መንፈስ ቅዱስን እንድንቀበል ስላመቻቸልን የሰማዩን አባት እንዲያመሰግን ወይም እንድታመሰግን ያስታውሷቸው።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መረጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. ወደ ክፍልዎ ልዩ እንግዳ ይጋብዙ። እንግዳዎት በመንፈስ ቅዱስ የተፅናናበትን ወይም የተፅናናችበትን ልምድ እንዲያካፍሉ ጠይቁ። (እንግዳው ከዋርድዎ ወይም ከቀርንጫፍዎ ካልሆነ ከጳጳሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ ያግኙ።)

2. ልጆቹ በተለይ ሐዘን ሲሰማቸው ምቾት፣ ደስታ፣ ደህንነት እንዲሰማቸው የሚያደርጋቸው ሰው እንዳለ ይጠይቋቸው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች ሲከፋን እና ብቸኝነት ሲሰማን አንዳንዴ ሊያጽናኑን እንደሚችሉ ይግለጹ። መንፈስ ቅዱስ አንዳንዴ አፅናኝ እንደሚባል ያስረዱ። በህይወታችን ሙሉ ታላቅ መጽናናትን ሊሰጠን ይችላል። ስንከፋ እና ስንረበሽ ከእኛ ጋር እንዲሆን ኢየሱስ ክርስቶስ ላከው።

3. “በትንሽ ድምፅ እንኳ” የሚለውን መዝሙር የመጨረሻ ሁለት መስመሮች ይዘምሩ ወይም ያንብቡ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ፣ [Children's Songbook]* ገጽ 106)፧

   አድምጡ፣ አድምጡ (እጅን ጆሮ ላይ መክበብ)
   መንፈስ ቅዱስ ይናገራል። (አመልካች ጣትን ወደ ከንፈር ላይ ማስቀመጥ)
   አድምጡ፣ አድምጡ (እጅን ጆሮ ላይ መክበብ)
   ትንሹንም ድምፅ። (እጅ በልብ ላይ)

4. ረጋ ባለው በትንሽ ድምፅ እንኳ ሊመሩ እንደሚችሉ ለማሳየት የሚከተለውን የፀጥታ ጨዋታ ከልጆቹ ጋር ይጫወቱ፧

   ለዚህ ጨዋታ የሚደብቁትን ትንሽ ዕቃ ለልጆቹ ያሳዩቸው። ዕቃውን ሲደብቁ አንድ ልጅ ለአንድ ጊዜ ቡድኑን ለቆ እንዲሄድ ይጋብዙ። ልጁ ወደ ቡድኑ እንዲመለስ አድርጉ፣ እና ወደ ተደበቀው ዕቃ የሚወስደውን መንገድ ለማግኘት ማዳመጥ እንዳለበት ንገሩት። እንደ እርሳስ ማንኳኳት፣ በቀስታ እጅ ማጨብጨብ፣ ወይም መዝሙር በማንጎራጎር በመሳሰሉት ልጁ የተደበቀውን ዕቃ እንዲያይ በየትኛው መንገድ እንደሚሄድ ለማሳየት ፀጥ ያለ ድምፅ ይጠቀሙ። የሚጠቀሙባቸው ድምጾች ለስላሳ እና የተከበሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ልጁ ትክክለኛውን አቀጣጫ ሲመለከት በቀስታ ያንኳኩ። ልጁ ወደ ተደበቀበት ቦታ እየቀረበ ሲሄድ፣ ዕቃውን እስኪያገኘው ድረስ የበለጠ በፍጥነት ያንኳኩ።

   የመንፈስ ቅዱስን ትንሽ ድምፅ በመስማት በሕይወታቸው ሊመሩ እንደሚችሉ ለልጆቹ ይግለጹላቸው።

5. “ከሰማችሁኝ፣ ጣታችሁን በጉንጫችሁ ላይ አድርጉ በማለት ለልጆቹ በትንሽ ድምጽ ይናገሩ። ከሰማችሁኝ፣ ጣታችሁን አገጫችሁ ላይ አድርጉ።” ከዚያም በትንሽ ድምፅ፣ የሚናገር ሌላ ሰው እንዳለ፣ እና ያ ድምጽ የሚነግራቸውን በጣም በጥንቃቄ እንዲሰሙ ለልጆቹ ያስረዷቸው። ያ ድምጽ የሚመጣው ከመንፈስ ቅዱስ ነው።

ትምህርት

13

# የጥምቀት ቃል ኪዳን

**ዓላማው** ልጆቹ ሲጠመቁ ከሰማይ አባት ጋር ቃልኪዳን እንደሚገቡ እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት** ማስታወሻ፣ ይህ ትምህርት ለአራት፣ አምስት፣ እና ስድስት ዓመት ልጆች እንዲስማማ ለማድረግ ታላቅ ጥረትን ስለሚጠይቅ፣ ለማስተማር ልጆች ለጥምቀት ዝግጁ እስኪሆኑ ድረስ መቆየት ይፈልጉ ይሆናል።

1. ሞዛያ 18፥8–10 እና አልማ 7፥15–16ን በፀሎት ያጥኑ።
2. የሚከተሉትን የቃላት መስመሮች አዘጋጁ፣

| |
|---|
| ትዕዛዛትን መታዘዝ |
| ይቀር በለኝ |
| የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ |
| ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም መኖር |

3. ወረቀቱን በቁመቱ በማጠፍ ሁለት የወረቀት ምልክቶችን ያዘጋጁ፣ እና እንደተመለከተው ምልክት ያድርጉባቸው፣

| | |
|---|---|
| ቃል እገባለሁ | የሰማይ አባት ቃል ይገባል |

4. “ጥምቀት” የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ፣ ገፅ* 100)።
5. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. መጽሐፈ ሞርሞን
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ “ቃልኪዳኖቼን እጠብቃለሁ” የሚል ቃላት ያሉበት የወረቀት አርማ ይስጡ።
   ሐ. የአንድ ወንድ ልጅ እና ሴት ልጅን ስዕል ቁረጡ እና አውጡ (ተቆርጠው የወጡ ስዕሎች 3-1 እና 3-2)።
   መ. የቃላት መስመሮችን ለመያዝ በቂ የሆነ የወረቀት ቦርሳ።
   ሠ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   ረ. የተ.ም. አርማ እና የላሳር ቀለበት።
   ሰ. ልጁ ሲጠመቅ የሚያሳየው ስዕል 3-13 (62018)፣ የመጀመሪያውን ራዕይ የሚያሳየውን ስዕል 3-10 (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 403)፣ ልጁ ቅዱሳን መጻሕፍትን ሲያነብ የሚያሳየውን ስዕል 3-23፣ ልጁ ሲጸልይ የሚያሳየውን ስዕል 3-24፣ ወደ

ቤተክርስቲያን መሄድን የሚያሳየውን ስዕል 3-25፣ ልጁ አስራቱን ሲከፍል የሚያሳየውን ስዕል 3-26፣ ሦስት እግር ያለውን ብስክሌት መጋሪት የሚያሳየውን ስዕል 3-27 (62317)፣ ትክክለኛውን መምረጥ የሚያሳየውን ስዕል 3-28።

6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ዛሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**የተስፋ ቃል እና ቃል ኪዳን**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ከልጆቹ አንዱን እንዲረዳዎት ይጋብዙት። የሚጠይቁትን ከሰራ፣ ልዩ የሆነ ነገር እንደሚሰጡት ይንገሩት። ለምሳሌ ሁለት ጊዜ እንዲዞር እና እጅዎትን እንዲጨብጥ ማድረግ የመሳሰለውን ቀላል ሥራ እንዲሰራ ይጠይቁት። ሲሰራም የተቻለውን ያህል በጥሩ ሁኔታ ለመስራት ቃል እንዲገባ አድርጉ። ከዚያም እንዲሰራ ፍቀዱለት። ሥራውን ከሰራ በኋላ፣ እርሶ የቃል ኪዳንዎትን ክፍል እንደምትጠብቁ ይንገሩት “ቃልኪዳኔን መጠበቅ እችላለሁ” የሚሉ ቃላት ያሉበት አርማ በሸሚዙ ላይ በስፒል ወይም በማጣበቂያ አያይዙለት እና እርሶ እና የረዳዎት ልጅ ሁለታችሁም ቃልኪዳናችሁን እንደጠበቃችሁ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከዚያም የተቀሩት ልጆች ተመሳሳይ ነገር በማድረግ አርማ እንዲያገኙ ይፍቀዱላቸው።

- እያንዳንዳችን ምን ለማድረግ ነው ቃል የገባነው?
- ቃልኪዳንዎትን ሲጠብቁ ምን ተከሰተ?

ታሪክ

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

አንድ ጠዋት እናቱ ፖም የያዘ ቦርሳ ስትሰጠው ስቲፈን ለጨዋታ ሊወጣ ነበር።

“ይህ ፖም የያዘ ቦርሳ እታች መንገዱ ላይ ላለችው እህት ጆንስ ነው። ልትሰጥልኝ ትችላለህ? አለችው።

“አዎ!” አለ ስቲፈን ቦርሳውን ሲቀበል።

“ከመጫወትህ በፊት ፖሞቹን ማድረስህን እርግጠኛ ሁን፣ እናም ምንም መሬት ላይ እንዳይወድቅብህ ተጠንቀቅ፣፩ በማለት እናቱ አስጠነቀቀችው። ወደ እህት ጆንስ በቀጥታ ውሰዳቸው።”

“እወስዳቸዋለሁ። ቃል እገባለሁ!” አለ ስቲፈን።

ስቲፈን ፖም የያዘውን ቦርሳ ይዞ ከቤቱ ሲወጣ፣ ሁለት ጓደኞቹ እየጠበቁት ነበር። ጨዋታ ጀምረው ስለነበር እንዲጫወት ፈልገው ነበር።

“እነዚህን ፖሞች መጀመሪያ መስጠት አለብኝ፣” በማለት ስቲፈን መለሰ።

ከልጆቹ አንዱም እንዲህ አለ “ኦ፣ ያንን በኋላ ማድረግ ትችላለህ። ለአንድ ሰዓት ብቻ ነው የምንጫወተው፣ ስለዚህ መጀመር ያስፈልገናል።”

“አይሆንም፣ መጀመሪያ ይህንን አደርጋለሁ። ለእናቴ ቃል ገብቼላታለሁ።”

እየሄደ እያለ፣ ስቲፈን ፖሙን የያዘውን ቦርሳ በአየር ላይ ማወዛወዝ ጀመረ። ከዚያም የገባውን ቃል አስታወሰ። ቦርሳውን በአየር ላይ በጣም ቢያወዛውዘው ፖሞቹ ሊወድቁ እና ሊፈርጡ ይችላሉ። ወደ እህት ጆንስ ቤት የቀረውን መንገድ ሲሄድ ቦርሳውን በጥንቃቄ ያዘው።

ቦርሳውን ለእህት ጆንስ ሲሰጣት፣ ስቲፈን ፈገግ አለ።

- ስቲፈን ለእናቱ የገባላት ቃል ምንድን ነበር?
- ስቲፈን የገባውን ቃል በመጠበቁ የተሰማው እንዴት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

| | |
|---|---|
| የጥቁር ሰሌዳ ውይይት | *ቃል መግባት* የሚለውን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉት፣ እና ምን ማለት እንደሆነ ልጆቹ እንዲያስቡ ይጠይቋቸው። አንድን ነገር ለማድረግ ስትስማሙ ወይም አደርገዋለሁ ስትሉ፣ ቃል እየገባችሁ መሆኑን አስገንዝቡ። |
| የሁኔታው ውይይት | በሁለት በኩል ቃል መግቢያ፣ ሌላ አይነት መንገድ እንዳለ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ጂን እና አባቷ የተገባቡትን ቃል ለማወቅ እንዲችሉ ልጆቹ የሚከተለውን ሁኔታ በጥንቃቄ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣<br><br>ጂን በመደሰት ሰርከስ በከተማው እንደሚታይ ለአባቷ ነገረችው እና መሄድ እንደሚችሉ ጠየቀችው። አባቷ ለጂን ትናንትና የነፈሰው ነፋስ ብዙ ቆሻሻዎችን ወደ ግቢው እንዳመጣ እና፣ መፅዳት እንደሚያስፈልገው አስታወሳት። ጂን አኮረፈች። አባቷም በጠዋት ግቢውን ካፀዳች፣ ከሰዓት በኋላ ወደ ሰርከሱ እንደሚወስዳት ነገራት። ጂንም ግቢውን አፀዳለሁ አለች። ጂን እና አባቷ ሁለቱም ቃል ተገባቡ።<br><br>• ጂን የገባችው ቃል ድርሻ ምንድን ነበር?<br>• አባቷ የገባው ቃል ድርሻ ምንድን ነበር?<br>• ጂን የቃል ኪዳኗን ድርሻ ብታፈርስ፣ አባቷ የገባውን ቃል ድርሻ ይጠብቃልን? (አይጠብቅም)። |
| የጥቁር ሰሌዳ ውይይት | *ቃልኪዳን* የሚለውን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ፃፍ። ልጆቹ ከእርሶ ጋር እንዲሉት ያድርጉ።<br><br>• ቃልኪዳን ምንድነው?<br><br>ቃልኪዳን በሁለት በኩል ቃል መግባት እንደሆነ ያስረዱ። ከአንድ ሰው ጋር ቃል ኪዳን ሲገቡ፣ አንዳንድ ነገሮችን ለመስራት ይስማማሉ እና ያም ሰው አንዳንድ ነገሮችን ለመስራት ይስማማል።<br><br>**በጥምቀት ቃልኪዳን እንገባለን** |
| የጥቅስ ውይይት | ዕድሚያቸው ስምንት ሲሆን፣ በጣም አስፈላጊ የሆነ ቃልኪዳን መግባት እንደሚችሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ቃል ኪዳኑ ከማን ጋር እንደሚገባ እና እንዴት እንደሚገባ እንዲያውቁ የሚከተለውን ጥቅስ እንዲያዳምጡ ይገሯቸው። አልማ 7፡15ን ኑ እና ወደፊት ሂዱ ከሚለው ጀምሮ አንብቡ እና ግለጹ።<br><br>• በዚህ ጥቅስ መሰረት፣ ከማን ጋር ነው ቃል ኪዳን የምትገቡት? (ከሰማይ አባት።)<br>• ከሰማይ አባት ጋር ቃልኪዳን መግባታችሁን ለማሳየት ምን ማሳየት አለባችሁ? (መጠመቅ።) |
| ስዕል እና ውይይት | ልጁ ሲጠመቅ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-13ን አሳዩ። እየተነጋገርንበት ያለው ቃልኪዳን የጥምቀት ቃልኪዳን እንደሚባል ያስረዱ። ስንጠመቅ፣ ለሰማይ አባት ከእርሱ ጋር ቃልኪዳን እየገባን መሆናችንን እናሳየዋለን። አንድ ነገር ለማድረግ ቃል እንገባለን፣ እና የሰማዩ አባትም አንድ ነገር ለማድረግ ቃል ይገባል። |
| መዝሙር | “ጥምቀት” የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት በሉ።<br><br>ኢየሱስ ጥንት በይሁዳ፣<br>ወደ መጥምቁ ዮሐንስ መጣ፣<br>በመስጠም ተጠመቀ፣<br>በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ። |
| የቃላት መስመሮች እና ውይይት | የሚከተለውን መረጃ አስረዱ፣ እና ጥያቄዎችን ጠይቁ። ልጆቹ የሚችሉትን ያህል እንዲያስረዱ ይፍቀዱላቸው። ሲያስፈልግ እርዷቸው። በውይይቱ ጊዜ፣ ተገቢ የሆነውን የቃላት መስመሮች ያሳዩ። ከዚያም እጠፏቸው እና በወረቀት ቦርሳ ውስጥ ክተቷቸው።<br><br>ስንጠመቅ፣ ትዕዛዛቱን እንደምንታዘዝ ለሰማይ አባት ቃል እንገባለን። (የቃል መስመሩን አሳዩ።)<br><br>• የሰማይ አባት አንዳንድ ትዕዛዛት ምንድን ናቸው?<br>• ስንጠመቅ ለሰማይ አባት የምንገባው ቃል ምንድን ነው? (ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ።) |

ይህ የእኛ ቃል ኪዳን ድርሻ ነው። የገባነውን ቃል ከጠበቅን፣ የሰማይ አባት ንስኃ ስንገባ ይቀር እንደሚለን (የቃል መስመሩን አሳዩ) እና መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጠን ቃል ይገባልናል (የቃል መስመሩን አሳዩ)። ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንድምንኖር ቃል ይገባልናል (የቃል መስመሩን አሳዩ)።

- የሰማይ አባት የቃል ኪዳን ድርሻ ምንድን ነው? (ንስኃ ስንገባ ይቀር ይለናል። የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ይሰጠናል። ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንድንኖር ይፈቅድልናል።)

ተሳትፎ

የመጀመሪያውን ራዕይ፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-10ን እና ሁለቱ የተቆረጡትን ስዕሎች አሳዩ። አንድ ልጅ ከስዕሉ ላይ የሰማዩን አባት እንዲያመለክት ያድርጉ። ሁለቱን ምልክቶች አንብቡ እና አንድ ልጅ "ቃል አገባለሁ" የሚለውን ተቆርጠው ከወጡት ስዕሎች አጠገብ እንዲያስቀምጥ ያድርጉ፣ ከዚያም አንድ ልጅ "የሰማዩ አባት ቃል ይገባል" የሚለውን ከመጀመሪያው ራዕይ ስዕል አጠገብ እንዲያስቀምጠው ያድርጉ። እያንዳንዱ ልጅ የቃል መስመር ከቦርሳው እንዲያወጣ እና እንዲያነብ ያድርጉ (ወይም ራስዎ ያንብቡት)፣ እና በትክክለኛው ምልክት ፊት ለፊት አስቀምጡት። ሁሉም ቢያንስ አንድ ተራ እስኪያገኙ ድረስ ተሳትፎውን ይደጋግሙት ሁለቱን ዝርዝሮች ይከልሷቸው። ለመታዘዝ ቃል የገባናቸው ትዕዛዛት በጀማሪዎች ክፍል እና በቤት ውስጥ የተማርነውን የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች እንደሚያጠቃልሉ ያስረዱ።

**ማጠቃለያ**

ስዕሎች

ስለትዕዛዛት የሚያስረዱትን ስድስት ስዕሎች (ከስዕል 3-23 እስከ ስዕል 3-28)፣ የት.ም. ዓርማ፣ እና የCTR ቀለበት ያሳዩ። ስዕሎች እና ዓርማው የሚያስረዱትን ትዕዛዝ ልጆቹ እንዲናገሩ ያድርጉ። (ስዕሎቹ የሚያስረዱት ቅዱሳን መፃህፍትን ማንበብ፣ መፀለይ፣ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ፣ አስራትን መክፈል፣ ሌሎችን መውደድ፣ እና ትክክለኛውን መምረጥ ነው። ለመታዘዝ ቃል የገባናቸው ትዕዛዛት እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ ልጆቹ እንዲገነዘቡት ይርዷቸው። ስለሌሎቹ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ትፈልጉ ይሆናል።)

ልጆቹ የCTR ቀለበታቸውን እንዲመለከቱ እና ቀለበታቸውን በተመለከቱ ቁጥር ለሰማይ አባት የገቡትን ቃል እንዲያስቡ ያበረታቷቸው። መጠመቅ ትዕዛዛትን ለመታዘዝ ቃል መግባትን እንደሚያጠቃልል ማስታወስ አለባቸው።

የአስተማሪ ምስክርነት

ቃል የመጠበቅን አስፈላጊነት፣ በተለይ ከሰማይ አባታችን ጋር የምንገባቸው ቃሎች አስፈላጊነታቸውን ይግለጹ። የሰማይ አባት ልጆቹን ሁሉ እንደሚወድ እና የጥምቀት ቃልኪዳኑን ድርሻ ለመጠበቅ እንደሚፈልግ ምስክርነትዎን ይስጡ። ልጆቹ የገቡትን ቃል በመጠበቅ የጥምቀት ቃልኪዳንን እንዲገቡ እና እንዲጠብቁት ያበረታቷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ ሊሰሩ የሚችሉትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪው መረጃዎች" በሚለው ውስጥ የክፍል ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ።

1. "ጥምቀት—ኢየሱስን ለመከተል ቃል መግባት" (9ደቂቃዎች) የሚለውን *ከልጆች ክፍል ቪዲዮ ካሴት ስብስብ* (53179)፣ ከሚለው ላይ ለልጆቹ ያሳዩአቸው እና የሚከተሉትን ጥያቄዎች ተወያዩባቸው፣
   - ሉዊስ ለቤተሰቦቹ ቃል የገባው ምንድን ነው?
   - ሉዊስ ሲጠመቅ ለሰማዩ አባት የገባው ቃል ምን ነበር?
2. ለእያንዳንዱ ልጅ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተመለከተውን "የጥምቀት ቃልኪዳኔ" የሚለውን ግልባጭ ያዘጋጁ። ከልጆቹ ጋር ያንብቡት። እያንዳንዱ ልጅ በተሰጠው መስመር ላይ ስሙን ወይም ስሟን እንዲፅፉ ይርዷቸው። ሁልጊዜ እንዲያዩት እና ስለ እርሱ እንዲያስቡት የሚታደለውን ጽሁፍ ልዩ ቦታ እንዲያስቀምጡ ያበረታቷቸው።



# የጥምቀት ቃልኪዳኔ

፤ ________________________________ ፤ የሰማይ አባትን
ትዕዛዛት ለመታዘዝ ቃል እገባለሁ።
የዚህን ቃልኪዳን ድርሻዬን
ከጠበኩ፤ የሰማዩ አባት —
ቃል ይገባል።

1. ንስኀ ስገባ ይቀር እንደሚለኝ።
2. የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚሰጠኝ።
3. ከእርሱ ጋር ለዘለዓለም እንድኖር።

# የጥበብ ቃል

ትምህርት
14

**ዓላማው** በጥበብ ቃል የተሰጡትን ትዕዛዛት ስንታዘዝ ጌታ እንደሚባርከን እያንዳንዱ ልጅ እንዲገነዘብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 89ን እና ዳንኤል 1ን በፀሎት ያጥኑ።
2. አንድ ፈገግ ያለ ፊት የተሳለበት፣ እና አንድ የተከፋ ፊት የተሳለበት፣ ሁለት የወረቀት ቦርሳዎች፣ የወረቀት ቦርሳዎቹ የማይገኙ ከሆነ፣ በተለያዩ ወረቀቶች ላይ ፈገግ ያለ ፊት እና የተከፋ ፊት ስዕል ሳሉ።
3. ለእያንዳንዱ ልጅ ፈገግ ያለ ፊት ያለበት ትንሽ ክብ ወረቀት ይስሩ። ለእያንዳንዱ ልጅ በልብሳቸው ላይ ለማያያዝ ስፒል ወይም ማጣበቂያ ለማምጣት መምረጥ ይችላሉ።
4. ትናንሽ የምግብ ስዕሎችን ሳሉ ወይም (የሚገኝ ከሆነ) ከመፅሔት ላይ ቆርጠው አውጡ። እያንዳንዱ ልጅ ቢያንስ ሁለት ስዕሎች እንዲኖረው የሚበቃውን አቅርቡ። ልዩ ልዩ አይነቶች ሰፊ የጤንነት የምግብ አይነቶች እና፣ የትንባሆ፣ የሻይ ወይም የቡና፣ እና የአልኮል መጠጦች ምልክቶችን አጠቃል።
5. "ለጤንነት እና ለጥንካሬ፣" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ለማለት ተዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 21)።
6. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. የት.ም. አርማ እና የCTR ቀለበት።
   ሐ. ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-6 (62001፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 401)፣ ዳንኤል የንጉሱን ስጋ እና ወይን እምቢ ሲል የሚያሳየውን ስዕል 3-29 (62094፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 114)፣ ሶስት እግር ያለው ብስክሌትን መጋሪት የሚያሳየውን ስዕል 3-27 (62317)፣ ገመድ መዝለል የሚያሳየውን ስዕል 3-30 (62523)፣ ልጁ ከውሻ ጋር የሚያሳየውን ስዕል 3-31።
7. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አሳፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**የሰማዩ አባትና ኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ አካላቶች እንዲኖሩን ይፈልጋሉ**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ልጆቹ አይናቸውን እንዲጨፍኑ እና፣ እንደ ቡችላ ያለ ትንንሽ ለማዳ እንስሳ እያንዳንዳቸው እንዳላቸው እንዲገምቱ ጠይቋቸው። ለማዳ እንሰሳቸውን በጣም ይወዳሉ እናም ከነርሱ ጋር በብዛት ይጫወታሉ። አንድ ቀን ለማዳ እንስሳቱ የታመሙ እና የደከሙ ይመስላሉ እናም የሚወዱትን ምግብ አይበሉም።

- በግምታዊ እንሰሳህ ላይ ያለው ችግር ምን ሊሆን ይችላል?
- እንሰሳው መብላት ያልፈለገው ለምን ሊሆን ይችላል?

ለማዳ እንሰሳው መጥፎ የሆነ ነገር እንደበላ አስረዱ።

- እንስሳህን መርዳት የምትችለው እንዴት ነው? (መጥፎ የሆነ ነገር እንዳይበላ በማድረግ።)
- ለሰውነታችሁ ጥሩ ያልሆነ ነገር ብትበሉ ሰውነታችሁ ምን ይሆናል?

ጤናማ ያልሆኑ ነገሮችን በመብላት ሰውነታችንን ልንጎዳ እንደምንችል አስረዱ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ይህ ሊከሰት እንደሚችል ስለሚያውቁ፣ በጥንካሬ እና በደስታ እንድናድግ የሚረዱንን አንዳንድ ትዕዛዛት ሰጥተውናል።

### የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የጤንነትን ህግ ሰጥተውናል

ስዕሎች እና ውይይት

ነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝን የሚያሳየውን ስዕል 3-6ን አሳይ። ኢየሱስ ክርስቶስ መብላት ስለ ሚገባን እና መብላት ስለ ማይገባን አንዳንድ ምግቦች ለዮሴፍ ስሚዝ እንደነገረው አስረዱ። ዮሴፍ ስሚዝ እነዚህን ነገሮች እንዲመሩን ፅፏቸዋል። እነዚህ መመሪያዎች የጥበብ ቃል ይባላሉ፣ በትምህርት እና ቃል ኪዳን ክፍል 89 ውስጥ ይገኛሉ። (የትምህርት እና ቃልኪዳንን መጽሐፍ ግልባጭ ያዙ።)

መብላት የሚገቡን ምግቦች አትክልቶች፣ ባቄላዎች፣ ትንሽ ስጋ፣ ፍራፍሬዎች፣ እና እንደ ስንዴ (ዳቦ እና ፓስታ) እና ሩዝን እንድሚያጠቃልሉ አስረዱ።

ኢየሱስ ክርስቶስ አካላችንን ሊጎዱ ስለሚችሉ እንደ ትንባሆ፣ እንደ ሻይና ቡና ስላሉ ትኩስ መጠጦች እና ወይን እና ስለ ሌሎች የአልኮል መጠጦችም አስጠንቅቆናል። የቅርብ ጊዜ ነቢያቶችም ጎጂ የሆኑ ዕጾችን እንዳንጠቀም አስጠንቅቀውናል። (ልጆቹ፣ የሚያጨሱ፣ ሻይ፣ ቡና፣ ወይም አልኮል የሚጠጡ፣ ወይም ዕጾችን የሚጠቀሙ ሰዎች ሁሉ መጥፎ እንዳልሆኑ እንዲገነዘቡ እርዷቸው። አንዳንድ ሰዎች እነዚህ ነገሮች ለአካላቸው መጥፎ እንደሆኑ እንኳ አያውቁም።)

ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋን መጠቀም ያለብንም አንዳንድ ጊዜ እንደሆነ አስረዱ። ልዩ ልዩ አይነቶች፣ የጤንነት ምግቦችን መመገብ ለእኛ ጥሩ እንደሆነ አስረዱ።

ንቃት ያላቸውን ልጆች ስዕል አሳዩ (ሶስት እግር ያለውን ብስክሌት መጋራትን የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-27፣ ገመድ መዝለል የሚያሳየው ስዕል 3-30፣ ልጁ ከውሻ ጋር የሚያሳየውን ስዕል 3-31)። የጥበብ ቃል የተሰጠው አካላታችንን በጤንነት እና በጥንካሬ ለመጠበቅ እንደሆነ እናም መመሪያውን ስንታዘዝ ደስተኞች እንደምንሆን ልጆቹ መረዳታቸውን አረጋግጡ።

ጨዋታ

አንድ ፈገግ ያለ እና አንድ የተከፋ ፊት ሁለቱን ፊቶች (ወይም ቦርሳዎች)፣ ወለሉ ላይ አስቀምጡ። የምግብ እና መጠጥ ስዕሎችን አሳዩ። ልጆቹ የምግቡን ስዕል የመምረጥ ተራ እንዲይዙ አድርጉ። እያንዳንዱ ምግብ በየትኛው ቦርሳ ወይም ቁልል እንደሆነ እንዲወስኑ ፍቀዱላቸው። ሰውነታቸው እንዲጠነክር እና ጤናማ እንዲሆን የሚረዷቸው ምግቦች የትኞቹ እንደሆኑ ተወያዩ።

### የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ እና ጠንካራ እንድንሆን ይፈልጋሉ

ጥቀስ፣ ስዕል፣ እና ታሪክ

ዳንኤል የንጉሱን ስጋ እና ወይን እምቢ ሲል የሚያሳየን፣ ስዕል 3-29ን አሳዩ እና ስዕሉ የሚያስረዳውን ቅዱሳን መፃህፍታዊ ታሪክ ተናገሩ (ዳንኤል 1ን ተመልከቱ)። ዳንኤል የንጉሱ ጠቃሚ ስጋ እና ወይን ለሰውነቱ ጥሩ እንዳልሆነ እና እንደማያጠነክረው ያውቅ እንደነበር አስረዱ። ጎበዝ ነበር እናም የንጉሱን ስጦታ እምቢ አለ። ከአትክልቶችና ከጥርጣሬ የተሰሩ ምግቦችን (ጥራጥሬዎች) ለመብላት መረጠ እናም ንፁህ ውሃ ጠየቀ። በኋላም ንጉሱ ዳንኤል እና ሶስት ጓደኞቹ ከሁሉም ጤናማዎች እና ብልሆች መሆናቸውን እንዳወቀ አስረዱ። (ይህ ዳንኤል ንጉሱ ሲከለክለው ወደ እግዚአብሔር በመፀለዩ በአንበሶች ጉድጓድ የተጣለው እና በእግዚአብሄር ተአምር የዳነው ነው።)

ጥቀስ

ዳንኤል 1፥17ን ለልጆች አንብቡ፣ እና አካላቸውን በመጠበቃቸው የሰማይ አባት እንደሚባርካቸው አስረዱ።

ልጆቹ ለአካላቸው ጤናማ ያልሆነ ነገር ሲሰጣቸው የዳንኤልን ምሳሌ እንዲከተሉ አበረታቷቸው። ልጆቹ ትክክለኛውን ለመምረጥ ማድረግ የሚችሉትን በአጭሩ እንዲወያዩ ወይም በድራማ መልክ እንዲጫወቱ ይፍቀዱላቸው።

መዝሙር

"ለጤናና ለጥንካሬ" የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት በሉ። ልጆቹ ለዚህ አዲስ ካልሆኑ፣ ክብ ሰርታችሁ ለመዘመር መሞከር ትችላላችሁ፡

ለጤና እና ለጥንካሬ
እናም የእለት ምግብ
ስምህን እናሞግስ፣
ኦ ጌታ

**ማጠቃለያ**

የት.ም. አርማ ወይም የCTR ቀለበትን አሳዩ። አካላችንን በጥንካሬ ለመጠበቅ ትክክለኛውን መንገድ የመምረጥን አስፈላጊነት ግለጹ። እንደፈጣን ክለሳ እንደሚከተሉት ያሉትን ጥያቄዎች ጠይቁ፡

- ኢየሱስ አካላችንን በጤንነት እና በጥንካሬ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን አስተምሮናል። ይህን ከቅዱሳን መፃህፍት ውስጥ በየትኛው ማንበብ እንችላለን? (ትምህርት እና ቃል ኪዳን 89።)
- ይህን ______________________________ ብለን እንጠራዋለን። (የጥበብ ቃል።)
- የጥበብ ቃል የተባለው ለምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
- መብላት እና መጠጣት የሚገቡን አንዳንድ ጥሩ ነገሮች ምንድናቸው?
- ለአካላችን ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉት አንዳንድ ነገሮች ምንድናቸው?
- ዳንኤል ብርታቱን ያሳየው እንዴት ነበር? (ጤናማ ያልሆኑ ምግቦችን "አልበላም" በማለት።)
- አንድ ሰው ጤናማ ያልሆነ ነገር ሲሰጣችሁ ማድረግ የምትችሉት ምንድነው? (እንደ ሲጋራ፣ ዕፅ፣ ወይም ብዙ ከረሚላ እንኳ ቢሆን እንደነዚህ ስላሉ ልዩ ነገሮች ጠይቋቸው። እንደነዚህ ዓይነት ፈተናዎችን የሚመልሱበትን መንገድ እንዲማሩ እና እንዲለማመዱ ልጆቹን እርዷቸው።)

አጭር ማስታወሻ

ለእያንዳንዱ ልጅ ፈገግ ያለ ፊት ምስል ስጧቸው ጤናማ ምግቦችን ለመብላት ሲመርጡ ደስተኞች እንደሆኑ እንዲያስታውሳቸው (በስፒል ወይም በማጣበቂያ ልብሳቸው ላይ ማያያዝ ይችላሉ።)

የመዝጊያ ፀሎት የሚሰጠው ልጅ ስለጤናማ ምግቦች እና ጠንካራ አካሎች የሰማይን አባት እንዲያመሰግን ይጠይቁት።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ምረጡጥ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "ለአስተማሪው መርጃዎች" በሚለው ውስጥ የክፍል ጊዜ የሚለውን ተመልከቱ።

1. እንደ ፍራፍሬ ወይም ኬክ ያለ ትንሽ ጤናማ ቁርስ ከልጆቹ ጋር ለማካፈል ለማምጣት መወሰን ይችላሉ። (ይህን ከማድረግዎ በፊት ከልጆቹ አንዳቸውም የምግብ አላርጂክ ወይም ሌላ ያለመስማማት ሁኔታ እንደሌላቸው ለማረጋገጥ የልጆቹን ወላጆች አነጋግሩ። በጾም ሰንበት ምግብ አምጡ።)
2. "በተወዳጁ ደዘሬታችን" የሚለውን መዝሙር ሁለተኛ ቁጥር ከልጆቹ ጋር ዘምሩ ወይም የመዝሙሩን ቃላት በሉ (መዝሙር፣ ቁጥር 307)

   ረዥም ጊዜ ለመኖር
   ውብና ጠንካር ሆነው፣
   ሻይ እና ቡናን ትንባሆንም ይተዋሉ፣
   አልኮልንም አይጠጡም፣ ግን
   ትንሽ ስጋ ይበላሉ፣
   ታላቅ እና መልካም ብልህ ይሆናሉ። (መሆንን ይሻሉ።)

3. ዕድሚያቸው ትንሽ ለሆነ ልጆች፣ ከወረቀት ወይም ከጨርቅ የተሰራ አፍ በስፋት የተከፈተ ቀላል አሻንጉሊት ሊሰሩላቸው ይችላሉ። የምግብ ስዕሎችን አሳዩ ወይም ብዙ የምግብ ዓይነቶችን ግለጹ። ለጥሩ ምግቦች የአሻንጉሊቱን አፍ ሰፋ አድርገው ክፈቱ እናም ወደ አካላችን መግባት ለማይገባቸው ነገሮች አፉን ዝጉት። ወይም ልዩ ልዩ ምግቦችን ሲያሳዩአቸው ወይም ሲገልጹላቸው ልጆቹ አፋቸውን እንዲከፍቱ እና እንዲዘጉም መጋበዝ ይችላሉ። (See the *Friend*, Nov. 1993, p. 12.)

4. ዳንኤል እና ጓደኞቹ የንጉሱን ጠቃሚ ምግብ እምቢ ሲሉ እና የበለጠ ጤናማ መሆኑን የሚያውቁትን ቀላል ምግብ ለመብላት ሲመርጡ የሚናገረውን ታሪክ ልጆቹ በድራማ መልክ እንዲጫወቱ ጋብዟቸው።

# የመፅሐፈ ሞርሞን አመጣጥ

ትምህርት
15

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ መፅሐፈ ሞርሞንን እንዴት እንደተቀበልን እንዲገነዘብ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የዮሴፍ ስሚዝ—ታሪክ 1፥29–54፤ 59–60፤ ሞርሞን 8፥1፤4ን በፀሎት አጥኑ።
2. "ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎች" የሚለውን መዝሙር ተማሩ እና ለመዘመር ወይም የመዝሙሩን ቃላት ለማለት ተዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ*፤ ገፅ 86)።
3. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. ለእያንዳንዱ ልጅ የታላቁ ዕንቁ ዋጋ፤ ከተቻለም፤ መጽሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ሞሮናይ ለዮሴፍ ስሚዝ ክፍሉ ውስጥ ሲገለጽለት የሚያሰየን፤ ስዕል 3-32 (62492፤ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 404)፤ ዮሴፍ ወርቃማዎቹን ሰሌዳዎች ሲቀበል የሚያሳየው ስዕል 3-33 (62012፤ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ 406)፤ ሞርሞን ሰሌዳዎቹን ሲጠርዝ የሚያሳየውን፤ ስዕል 3-34 (62520፤ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ 406)፤ ሞሮናይ ሰሌዳዎቹን በኮሞራ ኮረብታ ሲደብቅ የሚያሳየውን ስዕል 3-35 (62462፤ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 320)፤ ወርቃማ ሰሌዳዎችን የሚያሳየውን ስዕል 3-36።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ሞርሞን በወርቃማ ሰሌዳዎች ላይ ጽፏል**

የአትኩሮት ተሳትፎ "ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎች" የሚለውን መዝሙር አንደኛውን ቁጥር አንጎራጉሩ።

- ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎችን የሚያሳየው ስዕል 3-36ን አሳዩ፣ "የማንጎራጉረውን መዝሙር ሊነግረኝ የሚችል ሰው አለ?" ብለህ ጠይቅ ("ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎች።")

ትምህርቱ ስለወርቃማው ሰሌዳዎች እንደሆነ አስረዱ።

ከብዙ ዓመታት በፊት፤ አንዳንድ አባቶች የቤተሰባቸውን ታሪክ ይጠብቁ እንደነበር ተናገሩ። አብዛኛውን ጊዜ፤ አባትየው ከመሞቱ በፊት፤ ታሪኩን መፃፍን ለሚቀጥለው፤ ወንድ ልጁ የቤተሰቡን ታሪክ ይሰጠዋል። ቤተሰቦች ለብዙ ዓመታት በዚህ መልኩ ታሪካቸውን ይጠብቃሉ። ነቢያቶችም በቤተሰባቸው የሆነውን ነገር ይፅፉ ነበር። ነገር ግን የሰማይ አባት እንዴት እንደረዳቸው እና በዚያን ጊዜ በአካባቢያቸው ይኖሩ ስለነበሩ ሰዎችም ይፅፉ ነበር።

የስዕል ውይይት ሞርሞን ሰሌዳዎቹን ሲጠርዝ የሚያሳየውን ፤ስዕል 3-34ን አሳዩ።

የህዝቦቹን ሁሉ ታሪክ እንዲሰበስብ፤ በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ክፍሎች እንዲገለብጣቸው፤ እና እንደ መፅሐፍ ገጾች በሚመስሉ በስስ የወርቅ ሉኮች ላይ እንዲፅፋቸው የሰማዩ አባት ሞርሞን የተባለ ነቢይ እንደጠራ አስረዱ። እነዚህም የወርቅ ሰሌዳዎች ይባሉ ነበር።

- ሞርሞን ታሪኮች በወረቀት ፈንታ በወርቅ ሉኮች ላይ የጻፈው ለምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ወርቅ የሚቆይ ብረት እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ወርቅ እንደወረቀት እና ሌሎች ቁሳቁሶች ተቀዶ አይወድቅም ወይም እንደ ሌላ ብዙ ብረቶች አይዝግም።

ሞርሞን የወርቅ ሰሌዳዎቹን የተጠቀመው ለብዙ ጊዜ ስለሚቆዩ እንደሆነ አስረዱ። በሰሌዳዎቹ ላይ ጽፎ ለመጨረስ ሞርሞን ብዙ ዓመት ወስዶበታል። ሞርሞን ከመሞቱ በፊት፣ ሰሌዳዎቹን ለልጁ ሞሮናይ ሰጥቶታል።

ስዕል

ሞሮናይ ሰሌዳዎቹን በኮሞራ ኮረብታ ውስጥ ሲደብቃቸው የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-35 አሳዩ።

ሞሮናይ በወርቅ ሰሌዳዎቹ ላይ መቼ ፅፎ እንደጨረሰ አስረዱ። የሰማይ አባትም ሰሌዳዎቹን በኮረብታ ውስጥ እንዲቀብራቸው ነገረው። የሰማይ አባት በወርቅ ሰሌዳዎቹ ላይ ያሉት ፅሁፎች ከብዙ ዓመታት በኋላ ለሚኖሩ ሰዎች አስፈላጊ እንደሚሆኑ ያውቅ ነበር። የሰማይ አባት ልጆቹ እንዲያነቡት እስኪፈልግ ድረስ እንዲጠብቁ ሞሮናይ ሰሌዳዎቹን ለመቀበር የድንጋይ ሳጥን ሰራ።

**ሞሮናይ ስለ ወርቅ ሰሌዳዎቹ ለዮሴፍ ስሚዝ መመሪያ ሰጠው**

መዝሙር

“ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎቹ” የሚለውን መዝሙር አንደኛውን ቁጥር ከክፍሉ ጋር ዘምሩ ወይም በሉ።

ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎች ተቀመጡ
በተራራ ውስጥ ተቀመጡ፣
አምላክ አንድ ታማኝ እስኪያገኝ፣
እምነት የሚጥልበት።

ጥንት የተጻፈው መዝገብ፣
በኔፊ የተዘጋጀው ታሪክ፣
ዳግም ተነገረ፣
በመፅሐፈ ሞርሞን።

- መዝሙሩ ወርቃማውን ሰሌዳዎች እንዲያመጣ የሰማይ አባት የሚፈልገው ሰው ምን ዓይነት ሰው ነው የሚለው? (ታማኝ ሰው።)

ታማኝ ሰው የሚታመንና ታዛዥ የሆነ ሰው እንደሆነ አስረዱ። የሰማይ አባት እንዲረዳው የመረጠው ታማኝ ሰው ዮሴፍ ስሚዝ ነው።

ስዕል እና ታሪክ

ሞሮናይ ዮሴፍ ስሚዝን ስለመጎብኘቱ ለልጆቹ ይንገሯቸው (የዮሴፍ ስሚዝን—- ታሪክ 1፥29–54፣ 59–60 ተመልከቱ)።

አንድ ምሽት ዮሴፍ ስሚዝ እየፀለየ እያለ፣ ብሩህ የሆነ ብርሃን ወደ ክፍሉ ገባ። ምሽት ነበር፣ ነገር ግን ክፍሉ ፀሀይ ሲወጣ ብሩህ ከሚሆነው ይልቅ ብሩህ ሆነ። ወዲያውኑ፣ ከወለሉ ትንሽ ከፍ ብሎ፣ ከዮሴፍ አጠገብ መልአክ ታየ።

ሞሮናይ ለዮሴፍ ስሚዝ በክፍሉ ውስጥ ሲታየው የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-32 አሳዩ።

መልአኩ ስሙ ሞሮናይ እንደሆነ ለዮሴፍ ነገረው እናም የሰማዩ አባት እሱ እንዲሰራ የሚፈልገው ልዩ ስራ እንዳለው ለዮሴፍ እንዲነግር እንደተላከ አስረዳው።

ሞሮናይ ለብዙ መቶ ዓመታት ስለተቀበረው አስደናቂ መፅሐፍ፣ ታሪክ ለዮሴፍ ነገረው። መፅሐፉ የተጻፈው በስስ የወርቅ ሉክ ላይ ነበር። ይህ መልአክ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ሰሌዳዎቹን የቀበረው ሞሮናይ ነው።

ትክክለኛው ጊዜ ሲመጣ፣ የወርቅ ሰሌዳዎቹን ከተደበቁበት ስፍራ ከኮሞራ ኮረብታ ሊወስዳቸው እንደሚፈቀድለት ሞሮናይ ለዮሴፍ ነገረው። በተጨማሪም ስለ የወርቅ ሰሌዳዎቹ ሌላ ጠቃሚ ነገሮችን እና ዮሴፍ እንዲሰራ ስለሚጠራበት ልዩ ስራም ሞሮናይ ለዮሴፍ ነገረው። ሞሮናይ ተናግሮ ሲጨርስ፣ ብርሃን ሞሮናይን ከበበው እናም ወደ ሰማይ ተመለሰ።

ዮሴፍ ጋደም ብሎ ስለሆነው ነገር እያሰበ እያለ፣ ብርሃኑ እንደገና ወደ ክፍሉ ገባ። ሞሮናይ ለሁለተኛ ጊዜ ለዮሴፍ ተገለፀ እና በመጀመሪያው ጉብኝት የሰጠውን ዓይነት መልዕክት እንደገና ሰጠው። ከዚያም መጀመሪያ በሄደበት ዓይነት መንገድ ሄደ።

ዮሴፍ የሆነውን ሁሉ ለመረዳት እንደገና በአልጋው ላይ ጋደም አለ። ከዚያም፣ ለዮሴፍ ታላቅ መደነቅ፣ ሞሮናይ በአልጋው አጠገብ ለሶስተኛ ጊዜ ተገለፀለት እና የወርቃማ ሰሌዳዎቹን ታሪክ

እና የዮሴፍን ልዩ ስራ ደገመለት። ሞሮናይ ሰይጣን ሰሌዳዎቹን ለገንዘብ ማግኛ እንዲጠቀምበት ዮሴፍን ለመፈተን እንደሚሞክር፣ ነገር ግን ዮሴፍ ሰሌዳዎቹን የሰማይ አባትን ስራ ብቻ ለመስራት ማግኘት እንደሚችል በመጨመር ተናገር።

- መልአኩ ሞሮናይ ለዮሴፍ ስሚዝ በዚያ ምሽት ሶስት ጊዜ የታየው ለምንድነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

በዚያ ምሽት ሞሮናይ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ብዙ ነገሮችን ለዮሴፍ እንደነገረው አስረዱ። ዮሴፍ መልዕክቱን በደንብ እንዲያውቅ መልዕክቱን ሶስት ጊዜ ሰጠው።

መልአኩ ሞሮናይ ለሶስተኛ ጊዜ ከሄደ በኋላ ወዲያውኑ፣ ዮሴፍ ጠዋት መሆኑን እንዲያውቅ፣ አውራ ዶሮ ጮኸ። የሞሮናይ ሶስት ጉብኝቶች የቀዩት ሌሊቱን ሙሉ ነበር። ዮሴፍ ከመኝታው ተነሳ ነገር ግን ምን እንደተከሰተ ለማንም ሰው አልተናገረም። ከቁርስ በኋላ፣ ከአባቱ ጋር ለስራ ወደ መስክ ሄደ። ዮሴፍ ከአጋጠመው ነገር እና እንቅልፍ ለማጣቱ ምክንያት በጣም ስለደከመው መስራት አልቻለም ነበር። አባቱም ታሟል ብሎ ስላሰበ፣ ወደ ቤት ላከው።

ዮሴፍ እየደከመው ወደ ቤት ጉዞውን ቀጠለ፣ ነገር ግን አጥሩን እየወጣ እያለ፣ ጥንካሬ ስለሌለው መንታ ላይ ወደቀ። ለአንድ ሰዓት ያህል እዚያ ከተንጋለለ በኋላ፣ ስሙን የሚጠራ ድምፅ ተሰማው፣ ያም መልአኩ ሞሮናይ ነበር።

ከዚያ በፊት ባለው ምሽት የነገረውን መልአኩ ለመጨረሻ ጊዜ ለዮሴፍ ደገመለት። ከዚያም ወደ አባቱ ተመልሶ እንዲሄድ እና ያየው እና የሰማውን ሁሉ ለአባቱ እንዲነግረው መልአኩ ነገረው።

የዮሴፍ አባት እያንዳንዱን ቃል አዳመጠው እና ልጁ እውነት እየተናገረ እንደሆነ አወቀ። መልዕክቱ ከሰማይ አባት ስለነበረ፣ ልክ መልአኩ እንዳለው እንዲያደርግ ለዮሴፍ ነገረው። ከዚያ ቀን በኋላ፣ ዮሴፍ የተቀበሩትን የወርቅ ሰሌዳዎች ለማግኘት ወደ ኮሞራ ኮረብታ ሄደ። ወደ ኮረብታው ሲደርስ፣ በቀጥታ ሰሌዳዎቹ ወደ ተቀበሩበት ስፍራ ሄደ።

ጥቅስ — እዚያ ምን እንዳገኘ ዮሴፍ የተናገረውን በራስዎ አባባል ተናገሩ ወይም ያንብቡት (የዮሴፍ ስሚዝን—ታሪክ 1፡52 ተመልከቱ)።

ዮሴፍ የድንጋይ ሳጥኑን ሲመለከት መልአኩ ሞሮናይ እንደተገለፀ አስረዱ። ዮሴፍ ሰሌዳዎቹን የሚወስድበት ጊዜ ስላልደረሰ ሰሌዳዎቹን እንዳያወጣቸው ለዮሴፍ ነገረው።

ዮሴፍ ለአራት ዓመታት በየዓመቱ ወደ ኮሞራ ኮረብታ እንዲመላለስ ሞሮናይ ነገረው። ዮሴፍ ይህን አደረገ፣ እናም ሊጎበኝ በሚሄድበት ጊዜ፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያውቅ የሚፈልጉትን ሊያስተምረው መልአኩ ሞሮናይ ሲጠብቀው ያገኘው ነበር።

ስዕል — ዮሴፍ የወርቅ ሰሌዳዎቹን ሲቀበል የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-33ን አሳዩ።

በመጨረሻ፣ ከአራት ዓመት በኋላ፣ ሰሌዳዎቹን ከሳጥኑ አውጥቶ የመውሰጃያው ጊዜ ደረሰ። ሽፋኑ ከድንጋይ ሳጥኑ ተነሳ እና፣ የወርቅ ሰሌዳዎቹ በዮሴፍ እጆች ተቀመጡ። ሞሮናይ ለዮሴፍ ስሚዝ በጣም እንዲጠነቀቅላቸው እና ከህይወቱ ጋር እንዲጠብቃቸው ነገረው።

- ሰሌዳዎቹን መጠበቁ ለዮሴፍ አስፈላጊነቱ ለምንድን ነበር? (ምክንያቱም ክፉ ሰዎች ከእርሱ ሊወስዷቸው ይሞክራሉ እናም የሰማይ አባት በሰሌዳዎቹ እንዲሰራ የሚፈልገው ነገር አይሰራም ነበር።)

### ዮሴፍ ሰሌዳዎቹን ተረጎመ

በሰሌዳዎቹ ላይ የነበሩት ፅሁፎች ዮሴፍ ማንበብ በማይችለው ቋንቋ እንደነበሩ ግለጹ። በሰሌዳዎቹ ላይ ያሉትን ፅሑፎች ለመተርጎም እንዲረዳው ዮሴፍ ልዩ መሳሪያ ተቀበለ።

- ኡሪምና ቱሚም ምን እንደሆነ ከእናንተ የሚያውቅ አለን?

ኡሪም እና ቱሚም በሰሌዳዎቹ ላይ ያሉትን የጥንት ፅሁፎች ለመተርጎም እንዲረዳው ዮሴፍ የሚመለከትበት እንደ ልዩ መነፅር እንደሆኑ አስረዱ። በሰማይ አባት እርዳታ እና ኡሪም እና ቱሚምን በመጠቀም፣ ዮሴፍ በሰሌዳዎቹ ላይ ያሉትን ቃላት እኛ ልንረዳቸው ወደምንችላቸው ቃላት ለመተርጎም ችሏል። ወደ እንግሊዝኛ መተርጎሙ ሲፈፀም፣ መፅሐፉ ታተመ። መፅሐፈ ሞርሞንም ተባለ።

መፅሐፈ ሞርሞን ከፍ አድርገው ያዙ። ይህ መፅሐፍ ዮሴፍ ስሚዝ ከወርቅ ሰሌዳዎቹ ላይ የተረጎመው እንደሆነ አስረዱ።

ዮሴፍ ስሚዝ መፅሐፈ ሞርሞንን ከተረጎመ በኋላ፣ ሰሌዳዎቹን ለሞሮናይ መለሰለት።

የጥቀስ ተሳትፎ — ለሌላቸው ልጆች የመጽሐፈ ሞርሞንን ግልባጭ አድሉ።

መፅሐፈ ሞርሞን ብዙ የተለያዩ መጽሐፎችን እንደያዘ አስገንዝቡ። በመፅሐፈ ሞርሞን ያሉት መጽሐፎች የተሰየሙት በሰሌዳዎቹ ላይ በፃፉት ነቢያት ስም ነው። የሞሮናይ መፅሐፍ እንዴት በምዕራፍና በቁጥር እንደተከፋፈለ ለልጆቹ አሳያቸው።

ዕድሚያቸው ከፍ ያለ ልጆች ሞርሞን 8ን እንዲያገኙ እርዷቸው። ከክፍሉ ጋር ሞርሞን 8 ቁጥር 1 እና 4ን፣ መሬት እስከሚለው ቃል ድረስ አንብቡ።

በወርቅ ሰሌዳዎቹ የሚገኙትን አብዛኛዎቹን ቃላት የፃፈው ሞርሞን ስለሆነ ይህን መፅሐፈ ሞርሞን ብለን እንደምንጠራው አስረዱ። መዝገቡን የጨረሰው የሞርሞን ልጅ ሞሮናይ ነበር።

**ማጠቃለያ**

የክለሳ ውይይት — በትምህርቱ ላይ ያሉትን ስዕሎች በሙሉ አሳዩ ወይም በመሬት ላይ አስቀምጧቸው። ጥያቄዎችን ሲጠይቁ ትክክለኛ የሆነውን ስዕል ለመጠቆም እያንዳንዱ ልጅ ተራ እንዲደርሰው አድርግ።

- የወርቅ ስሌዳዎቹን የሚያሳየው ስዕል የትኛው ነው?
- ሞርሞን በወርቅ ሰሌዳዎቹ ላይ ሲፅፍ የሚያሳየው ስዕል የትኛው ነው?
- ሞሮናይ የወርቅ ሰሌዳዎቹን ሲቀብር የሚያሳየው ስዕል የትኛው ነው?
- መልአኩ ሞሮናይ ዮሴፍ ስሚዝን ሲያነጋግር የሚያሳየው ስዕል የትኛው ነው?
- መልአኩ ሞሮናይ የወርቅ ሰሌዳዎቹን ለዮሴፍ ስሚዝ ሲሰጥ የሚያሳየው ስዕል የትኛው ነው?

መዝሙር — “ወርቃማዎቹ ሰሌዳዎች” የሚለውን መዝሙር ሁለቱንም ቁጥሮች ከክፍሉ ጋር ዘምሩ ወይም በሉ።

የመዝጊያ ፀሎት የሚሰጠው ልጅ ስለመፅሐፈ ሞርሞን የሰማይን አባትን እንዲያመሰግን ጠይቁት።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች** — ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ተመልከቱ።

1. ተገቢ የሆኑትን ስዕሎች በመጠቀም፣ ልጆቹ በዚህ ዓመት የሚማሩትን ጥቂት የመፅሐፈ ሞርሞን ታሪኮች ከልሱ። ለምሳሌ፣

   ሀ. ኔፊ አመፀኛ ወንድሞቹን ሲያሸንፍ፣ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-37ን አሳዩ (62044፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 303)። ምንም እንኳ ታላላቅ ወንድሞቹ ፀባያቸው መጥፎ ቢሆንበትም የሰማይ አባት ኔፊ መርከብ እንዲገነባ እንዴት እንደረዳው እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ለ. ሁለት ሺህ ወጣት ተዋጊዎችን የሚየሳየውን፣ ስዕል፣ 3-38 አሳዩ (62050፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 313)። ከሁለት ሺህ በላይ የሆኑ ወጣት ወንዶች የቤተሰቦቻቸውን ነፃነት ለመጠበቅ እንዴት እንደተዋጉ እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ሐ. ኢየሱስ በምዕራባዊ ክፍለ ዓለም ሲያስተምር፣ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-17ን አሳዩ (62380፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 316)። ኢየሱስ ክርስቶስ ኒፋይቶችን ስለመጎብኘቱ እንደሚማሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

2. ልጆቹ የወርቅ ሰሌዳዎችን እና የመፅሐፈ ሞርሞንን ስዕል እንዲስሉ አድርጉ። በስዕላቸው ላይ *የወርቅ ሰሌዳዎች* እና *መፅሐፈ ሞርሞን* ብለው ይፃፉ።

3. የጥንት ነቢያት በብረት ሰሌዳዎች ላይ እንዴት ይፅፉ እንደነበር ልጆቹ እንዲገነዘቡ ለመርዳት፣ እያንዳንዱ ልጅ የስሙን የመጀመሪያ ፊደል በቀርቀሮ ዕቃ ስር በሚስማር እንዲፅፍ ጋብዙ። አስተማሪው መጀመሪያ ይህን መግለፅ አለባቸው።

4. ስምንተኛውን የእምነት አንቀጽ ከልጆቹ ጋር ከልሱ። ከፊሉን ወይም ሁሉንም ማስታወሻ ማጥናት የሚችሉትን እርዷቸው።

ትምህርት

16

# ታዛዥ በመሆን እምነታችንን ማሳየት እንችላለን

**ዓላማው** ልጆች ትዕዛዛትን በማክበር በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያላቸውን እምነት ማሳየት እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. በ1ኛ ኔፊ 1–2 ያለውን የሌሂን እና የቤተሰቡን ታሪክ በፀሎት ያጥኑ።
2. የሌሂ ቤተሰብ ወደ በረሃ ለመሄድ ሲዘጋጁ መምረጥ የነበረባቸውን ንብረቶች የሚያመለክቱ የዕቃ ዝርዝሮች ወይም ስዕሎች።
3. “እምነት” የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ። (የልጆች *የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 96)።
4. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣
   ሀ. መጽሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ስዕል 3-39፣ ሌሂ ለኢየሩሳሌም ሕዝቦች ሲተነብይ (62517፣ የወንጌል ስዕል ኪኑ-ጥበብ ጥራዝ 300)፣ እና ስዕል 3-40፣ የሌሂ ቤተሰብ ኢየሩሳሌምን ሲለቁ (62238፣ የወንጌል ስዕል ኪኑ-ጥበብ ጥራዝ 301)፣ እና የዚህን ዘመን ነቢይ ፎቶግራፍ።
   ሐ. የCTR ጋሻና ቀለበት።
5. ለማንኛውም ለሚጠቀሙባቸው ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**ታዛዥ መሆን እምነትን የማሳያ መንገድ ነው**

የአክብሮት ተሳትፎ “እምነት” የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ። ከሕፃናት ክፍሎች ከታች ያሉ ድርጊቶችን መጠቀም ይችላሉ።

እምነት ፀሐይ እንደምትወጣ ማወቅ ነው፣ (እጆችን በጭንቅላት ላይ ግማሽ ክብ ማድረግ)
ሁሌ እንደምታበራ። (እጆች በርጋታ ወደ ተከሻ አካባቢ ይወርዳሉ)
እምነት ጌታ (እጆችን ለፀሎት እንደምናደርገው ባንድነት)
ጌታ እንደሚሰማኝ ማወቅ ነው። (እንደሚሰማ ማወቅ ነው እጆችን ከጆሮ በኋላ መክበብ)
እምነት እንደ ትንሽ ዘር ናት፣ (ግራ እጅን ማጎርጎድ እና በቀኝ እጅ ዘር የምንዘራ በማስመሰል ማሳየት)
ከተዘራ፣ ያድጋል። (ቀኝ እጅ ተክሉ ከጎረጎደው ግራ እጅ እያደገ እንደሆነ ያስመስላል)
እምነት በልቤ ሙሉ ነው። (እጆችን ልብ ላይ አስቀምጡ)
መልካምን ሳደርግ፣ (የቀኝ አመልካች ጣትን ወደ ላይ ማመልከት)
አውቃለሁ። (በቀኝ አመልካች ጣት ጭንቅላትን መንካት)

የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ነገር እንድናደርግ ሲጠይቁን፣ ትዕዛዝ ይባላል። ትዕዛዛትን ስናከብር፣ የሰማዩን አባትና ኢየሱስን እንደምናምናቸው እናሳያቸዋለን። እንደሚወዱን እና ማንኛውም የሚጎዳንን ነገር እንድናደርግ በፍፁም እንደማይጠይቁን እናውቃለን። ስንታዘዝ እምነታችንን እናሳያለን።

በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ማመን ማለት እምነት አለን ማለት እንደሆነ ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ምንም እንኳ በምድራዊ ሕይወታችን ባናያቸውም፣ እነርሱን ባዩአቸው በሌሎች ምስክርነት እምነት አለን። መንፈስ ቅዱስም ትክክለኛ እንደሆነ እና የስጋ እና የአጥንት አካል እንደሌለው ነገር ግን በሰው ምስል የመንፈስ አካል እንዳለው እናውቃለን።

**የእምነት አንቀጽ**

በዕድሜ ከፍ ያሉ ልጆች የመጀመሪያውን የእምነት አንቀጽ በቃላቸው አጥንተው እንዲይዙ ይርዷቸው፣ ትንንሾቹ ልጆች ከእርስዎ ጋር ደጋግመው ማለት ይችላሉ ምናልባትም ግማሹን በቃላቸው ይይዛሉ።

### ሌሂ እምነቱን ታዛዥ በመሆን አሳይቷል

**የቅዱሳን መጽሀፍት ታሪክ እና ስዕል**

እኛ የሰማዩ አባት ልጆች እንደሆንን እና በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዳለን ማሳየት እንደምንችል ይግለጹ። በመጽሐፈ ሞርሞን፣ ሌሂ የሚባለው ነቢይ ታዛዥ በመሆን በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ያለውን እምነት አሳይ።

የሚከተለውን የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ በራሳችሁ አባባል ተናገሩ፣

ከብዙ ዓመታት በፊት፣ ኢየሱስ ከመወለዱ ከስድስት መቶ ዓመት በፊት፣ ሌሂ የሚባል ነቢይ በኢየሩሳሌም ከቤተሰቡ ጋር ይኖር ነበር። የሌሂ ሚስት ሳራ ትባል ነበር። ሌማን፣ ሌሙል፣ ሳም፣ እና ኔፊ የሚባሉ አራት ወንዶች ልጆች ነበሯቸው።

ሌሂ እና ቤተሰቡ ባለፀጋዎች እና የተመቻቸ ኑሮ ያላቸው ነበሩ። ሌሂ የሰማዩን አባት እና ኢየሱስን ይወድ ነበር። ቤተሰቦቹም እንዲወዷቸው እና ትዕዛዛቶቻቸውን እንዲታዘዙ ለማስተማር ይሞክር ነበር።

ስዕል 3-39 ያመልክቱ፣ ሌሂ ለኢየሩሳሌም ሕዝብ ሲተነብይ።

በዚያን ጊዜ በኢየሩሳሌም ይኖሩ የነበሩት ሕዝቦች ኃጢአተኞች ነበሩ። ሌሂ ስለ ሰማዩ አባት እና ኢየሱስ እናም ስለ ትዕዛዛት ሊያስተምራቸው ሞከረ፣ ነገር ግን ሕዝቦቹ አልሰሙትም። አንድ ቀን ሌሂ ሲፀልይ፣ ሕልም ወይም ራዕይ አየ። ብዙ አስደናቂ ነገሮችን ተመለከተ። ሕዝቦቹ ንስኃ ካልገቡ በስተቀር ኢየሩሳሌም እንደምትጠፋ ተመለከተ። ሌሂ የሰማዩ አባት የኢየሩሳሌምን ሕዝቦች ማስጠንቀቅ እንደፈለገ ስለ አወቀ የሰማዩን አባት አመሠገነ። የሰማዩ አባት ስላየው ነገር ለሕዝቦቹ እንዲናገር ነገረው። ሌሂ እንደታዘዘው አደረገ። ለሕዝቦቹ ንስኃ ካልገቡ በስተቀር ኢየሩሳሌም እንደምትጠፋ ነገራቸው።

- ሌሂ በራዕዩ ያየው ምንድነው? (ብዙ ነገሮችን፣ የኢየሩሳሌምን መጥፋት በማጠቃለል፣ 1ኛ ኔፊ 1፥13ን ይመልከቱ።)
- ሌሂ ከራዕዩ በኋላ እንዴት ተሰማው? (የሰማይ አባትን አመሰገነ፣ ደስተኛ ነበር፣ 1ኛ ኔፊ 1፥14–15ን ይመልከቱ።)

ለኃጢአታቸው ንስኃ እንዲገቡ ለሰዎች መንገር ብርታትን ይጠይቃል። ይሁን እንጂ፣ ሌሂ የሰማይ አባት እንደሚጠብቀው እምነት ነበረው፣ ስለዚህም ሌሂ እንደታዘዘው አደረገ። ምክንያቱ ኃጢአተኞች እንደነበሩ መስማት ስላልፈለጉ ሕዝቦቹ አልሰሙትም እናም አሾፉበት ሊገድሉትም ሞከሩ።

- ሌሂ በሰማዩ አባት ላይ ያለውን እምነት ለማሳየት ምንድነው ያደረገው? (ታዘዘ እናም ለሕዝቦቹ ንስኃ እንዲገቡ ነገራቸው፣ 1ኛ ኔፊ 1፥4፣ 18ን ይመልከቱ።)
- ሌሂ ንስኃ እንዲገቡ ከነገራቸው በኋላ ሕዝቦቹ ያደረጉት ምንድነው? (አሾፉበት እናም ሊገድሉት ፈለጉ፣ 1ኛ ኔፊ 1፥19–20ን ይመልከቱ።)
- ሕዝቦቹ ስላልሰሙት ሌሂ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?

**የቅዱሳን መጻሕፍ ውይይት**

ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ የሰማዩ አባት ሌሂን ተናገረው። የሰማይ አባት እንዲያደርግ ባዘዘው ነገር ታማኝ ስለነበር እንደተባረከ ለሌሂ በሕልሙ ነገረው። ደግሞም ለሌሂ ቤተሰቡን ይዞ ወደ በረሃ እንዲሄድ ነገረው (ሌሂ እንዲያደርግ ያዘዘውን ልጆች እንዲሰሙት ያድርጉ)። (1ኛኔፊ 2፥1–2ን ይመልከቱ።)

- የሰማዩ አባት ሌሂን ያዘዘው ምን እንዲያደርግ ነበር? (ኢየሩሳሌምን እንዲለቅ እና ወደ በረሃ እንዲሄድ ነው።)

በረሃ ማለት አብዛኛውን ጊዜ ማንም የማይኖርበት ቦታ እና ቤቶች፣ ሕንፃዎች፣ ወይም መንገዶች የሌሉበት ቦታ መሆኑን ይግለጹ። የሰማይ አባት ሌሂ እና ቤተሰቡ ሁሉንም ወደ ኋላ ትተው ለራሳቸው ብቻ ወደሚኖሩበት ቦታ እንዲሄዱ አዘዛቸው።

- ሌሂ ቤተሰቡን ከኢየሩሳሌም እንዲያወጣ የታዘዘው ለምንድነው? (ክፉ) ኃጢአተኛ ሰዎች ሌሂን ለመግደል ሲያቀዱ ነበር፣ እናም ከተማዋም ልትጠፋ ነበር።)

ሌሂ ያደረገውን እንዲያዳምጡ ለልጆቹ ንገሩዋቸው፣ ከዚያም 1ኛ ኔፊ 2፥3–4 ያንብቡ። ሌሂ የጌታን ትዕዛዛት አከበረ። ቤቱን፣ ርስቱን፣ ወርቁን እና ብሩን ተወ። ቤተሰቡን፣ ስንቁን እና ድንኳኑን ብቻ በመውሰድ ወደ በረሃ ሄደ።

- ሌሂ ያደረገው ምንድነው? (በረሃ ውስጥ ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ጫነ እና ቤተሰቡን ከኢየሩሳሌም አወጣቸው።)

**የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ እና ስዕል**

ስዕል 3-40 ያመልክቱ፣ የሌሂ ቤተሰብ ኢየሩሳሌምን ሲለቁ።

ምንም እንኳን ሌሂ በኢየሩሳሌም ለረጅም ጊዜ ቢኖርም፣ ትውልድ ሃገሩን የመልቀቅ ትዕዛዝን ወዲያውኑ አከበረ። ሌሂ እና ቤተሰቡ የትውልድ ሃገራቸውን፣ መሬታቸውን፣ ብዙውን ልብሶቻቸውን፣ ወርቃቸውን እና ብራቸውን፣ እና ሌሎች ንብረቶቻቸውን ትተው ሄዱ። ምግብ፣ ጥቂት ልብስ፣ ድንኳኖች፣ እና በግመሎች ወይም በአህዮች ላይ መጫን የሚችሉትን ሌሎች አስፈላጊ ዕቃዎች ብቻ ወሰዱ። ከዚያም ለቀቁና ወደ ምድረ በዳ ሄዱ።

ለሌሂ መሄድ ቀላል እንዳልነበረ፣ ነገር ግን ይህንን ትዕዛዝ ለማክበር ፈቃደኛ እንደነበር ይጠቁሙ።

- ሌሂ በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዳለው የሚያሳይ ነገር ምን አደረገ? (ታዛዥ ነበር። ኃጢአተኛ ህዝቦችን አስጠነቀቀ፣ እና እንደዚሁ እንዲያደርግ ስለ ታዘዘ የትውልድ ሃገሩን እና ንብረቶቹን ትቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ።)

**ውይይት**

ልጆቹ የሌሂ ቤተሰብ እንደሆኑ አድርገው እንዲያስመስሉ ይንገሩዋቸው።

ወደ ምድረበዳ የሚሄዱ ቢሆን ኖሮ ይዘው ስለሚሄዱት ነገር እንዲያስቡ ያድርጉ። ምን ይዘው ሊሄዱ እንደሚፈልጉ እና ምን እንደሚያስቀሩ እንዲነግሩአችሁ አድርጉ። የሌሂ ቤተሰብ ከውስጡ ሊመርጡ የሚችሉአቸውን ዕቃዎች የሚያመለክቱትን ብዙ ዕቃዎች ወይም ስዕሎች ሊያሳዩዋቸው ይችላሉ፣ ለምሳሌ፣ ቀለበት ጌጣጌጥን ሊያመለክት ይችላል፣ ፍራንክ ገንዘብ ማለት ሊሆን ይችላል፣ ፖም ፍራፍሬ ለምግብ ሊመደብ ይችላል። ልጆቹ የሌሂ ቤተሰብ ያስፈለጋቸውን እንዲመረጡ ያድርጉ። ጥቂት ነገሮችን ብቻ መውሰድ እንደሚችሉ ያስታውሷቸው።

**ተሳትፎ**

ልጆቹ ከሌሂ ጋር ወደ ምድረበዳ የሚሄዱ ቢሆን ኖሮ ይዘው ሊሄዱ የሚመርጡትን እንዲወስኑ ያድርጉ። ከዚያም የመጀመሪያው ልጅ እንዲህ ይላል፣ “ከሌሂ ጋር ወደ ምድረ በዳ የምሄድ ብሆን ኖሮ፣ _ እወስድ ነበር።” (ልጁ ሊወስድ በመረጠው ነገር ባዶ ቦታውን ይሙላ።) የሚቀጥለውም ልጅ የመጀመሪያው ልጅ ያለውን ይደግማል ከዚያም የመረጠውን ተጨማሪ ዕቃ ይጨምራል። እያንዳንዱ የሚቀጥለው ልጅ ሁሉንም የበፊቶቹን ዕቃዎች ይደግምና አንድ የራሱን ይጨምርበታል። ሁሉም ልጅ (እና አስተማሪው) ቢያንስ አንድ ተራ እስክሚደርሰው ይቀጥላል።

- ጓደኞቻችሁን እና ንብረቶቻችሁን ዳግም ማየት እንደማትችሉ በማወቃችሁ ምን የሚሰማችሁ ይመስላችኋል?

- የሌሂ ቤተሰብ እንዴት የተሰማቸው ይመስላችኋል?

ኢየሩሳሌምን በመልቀቅ የሰማዩ አባትን መታዘዝ ታላቅ እምነትን ይጠይቃል። ሌሂ እና ቤተሰቡ ታዛዥ ስለነበሩ ታላቅ በረከትን ተቀበሉ።

**ትክክለኛውን ከመረጥን፣ ታዛዦች ነን**

የጨዋታ ተሳትፎ

የCTR ጋሻና ቀለበት ያሳዩ።

- ‘ት.ም.’ የሚሉት ፊደሎች የሚያመለክቱት ምንድነው? (ትክክለኛውን ምረጥ።)

ትክክለኛውን መምረጥ ማለት የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን ማድረግ እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

የሚከተሉትን ታሪኮች በራሳችሁ አነጋገር ይናገሩ፣ እና ልጆቹ ሁኔታውን በተግባር እንዲጫወቱ ያድርጉ።

1. እናንተ እና አንዳንድ ጓደኞቻችሁ ወደ ቤት ስትሄዱ የጎረቤታችሁን አጥር ግቢ ታልፉላችሁ። በአጥር ግቢው ውስጥ የፍሬ ዛፍ በጣፋጭ ፍሬ ተሸፍኖአል። ጓደኞቻችሁ ከእነርሱ ጋር መጥታችሁ አንዳንድ ፍሬዎችን ለመብላት እንድትቀጥፉ ይፈልጉአችኋል። ብዙ ፍሬ ስላለ ጥቂት ብንወስድ ምንም አይጎድልም ይላሉ።

   - የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ እንድታደርጉ የሚፈልጉት ምንድነው?

   ትክክለኛውን ሲመርጡ፣ ታዛዥ እንደሆኑ እና በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንደሚያሳዩ ለልጆች ይንገሯቸው።

2. በምትወዱት አሻንጉሊት መጫወት ትፈልጋላችሁ፣ ነገር ግን ወንድማችሁ ይዞታል።

   - የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ እንድታደርጉ የሚፈልጉት ምንድን ነው?

   የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን ስናደርግ፣ ትክክለኛውን እየመረጥን እንደሆን ይግለጹ።

   ጊዜ ካለ፣ የነቢዩን ፎቶግራፍ ያመልክቱ እና እሱ እንድናደርግ የሚጠይቀንን አንዳንድ ነገሮች እንዲዘረዝሩ ልጆቹን ይንገሩአቸው። እነዚህን ትዕዛዛት መታዘዝ እንዴት በረከት ሊያመጣ እንደሚችል ይወያዩ።

**ማጠቃለያ**

የት.ም. አርማ እና የCTR ቀለበት እንደገና ያሳዩ እና ልጆቹ ሁልጊዜ ትክክለኛውን እንዲመርጡ ያስታውሷቸው። ትክክለኛውን ሲመርጡ፣ እየታዘዙ ነው። ሲታዘዙ፣ በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት እንዳላቸው እያሳዩ ነው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**የዳበረ ተሳትፎ**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በጥሩ ሁኔታ የሚሰሩትን ምረጡ። በራሱ በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀምባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ “የአስተማሪ መረጃዎች በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ከዋርዳችሁ ወይም ከቀርንጫፋችሁ አባል አንዱ መታዘዝ እንዴት እንደረዳው ወይም እንደረዳት እንዲናገሩ ያድርጉ። ከሚሲዮናዊነት የተመለሰ፣ አዲስ አማኝ፣ ወይም በቀርቡ ቤተመቅደስ ውስጥ የነበረ አንድ ሰው ተገቢ ምርጫ ሊሆን ይችላል። ወደ ክፍልህ እንዲመጣ (እንድትመጣ) ግለሰቡን (ግለሰቧን) ከመጠየቅህ በፊት ከጀማሪ ክፍል ፕሬዚዳንት እና ከካህናት መሪያችሁ ፈቃድ ያግኙ።

2. ጫማ፣ ባርኔጣ፣ ጥላ፣ እና ወዘተ . . . የመሳሰሉትን መከላከያን የሚሰጡ ብዙ ዕቃዎችን ይሰብስቡ በክፍላችሁ ያሉ ሁሉም ልጅ ተሳታፊ መሆን እንዲችል በቂ ዕቃዎች ይኑራችሁ። ልጆቹ በየተራ፣ ዕቃ እንዲመርጡ እና ምን ዓይነት ጥበቃ እንደሚሰጡ እንዲናገሩ፣ ይንገሩአቸው (ጫማ እግሮችን ይጠብቃል፣ እና ወዘተ)። እኛም ወላጆቻችንን እና መሪዎቻችንን ስንታዘዝ፣ እንደምንጠበቅ ለልጆቹ ይንገሩዋቸው። ስለ አንዳንድ ህጎች እና እንዴት መከላከያ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይናገሩ።

3. እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱና ጣቶቻችሁን እንዴት ማንቀሳቀስ እንደምትችሉ ለልጆች ያሳዩ። የራሳችሁን እጆች እና ጣቶች ማንቀሳቀስ እንደምትችሉ፣ ነገር ግን የሌላውን ሰው ጣቶች ማንቀሳቀስ እንደማይችሉ ይግለጹ። እጆቻቸውን ወደ ላይ እንዲያነሱ፣ ጣቶቻቸውን እንዲያንቀሳቀሱ፣ እና እጆቻቸውን እንዲጨብጡ እና እንዲዘረጉ ልጆቹን ይንገሩአቸው። ልጆቹ እጆቻቸው ትክክለኛውን እንዲመርጡ ሲነግሯቸው እየታዘዙ እንደሆነ እንዲያውቁ ይርዷቸው።

4. "ሁለት ትንንሽ እጆች አሉኝ" የሚለውን መዝሙር ሁለተኛውን ቁጥር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ።

   ቸር አባት፣ ስለ እጆቼ አመሰግንኃለሁ
   እናም እንድትባርካቸው እጠይቀዛለሁ
   ልጆች ቀኑን ሙሉ የሚደሰቱት
   ሁለት ትንንሽ እጆች መታዘዝ ሲያውቁ ነው
   (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ *[Children's Songbook]* ገፅ 272)

5. በአስራ ሶስቱ የእምነት አንቀጽ ውስጥ የተጠቃለሉትን ትክክለኛውን መምረጥ የምንችልበትን ሁሉንም መንገዶች ይፈልጉ። ያንንም በማድረግ ልጆቹ ተካፋይ እንዲሆኑ ያድርጉ። እንዲቀጥሩ ያድርጉ፣ ለእነርሱ ያመልክቷቸው፣ወይም ይድገሟቸው። ለእነርሱ አስፈላጊ የሆነውን አንድ ወይም ሁለት ሐረግ በቃላቸው ማጥናት የሚችሉትን ልጆች ያበረታቷቸው።

# መፅሐፈ ሞርሞን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን እናምናለን

ትምህርት
17

**ዓላማው** ልጆችን የቀዱሳን መጻሕፍት ትዕዛዛትን እንዲያውቁ እና እንዲረዱ ሊረዷቸው እንደሚችሉ እንዲሁም ቀዱሳን መጻሐፍት ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲመጡ ሊረዷቸው እንደሚችሉ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. 1ኛ ኔፊ 3-4ን፣ 3ኛ ኔፊ 18፥19ን፣ እና ሞዛያ 23፥15ን በፀሎት ያጥኑ። የነሐስ ሰሌዳዎቹን እና የኔፊን ታሪክ ለመናገር ይዘጋጁ።
2. በጠረጴዛ ላይ አራቱን መደበኛ ቀዱሳን መጽሐፍት፣ እንደ ታሪክ መጽሐፍ፣ የምግብ መማሪያ መጽሐፍ፣ እና የማስተማሪያ መጽሐፍ የመሳሰሉትን ሌሎች ብዙ መጽሐፎችን፣ በተለያዩ የክፍሉ ማዕዘኖች ያስቀምጡ። የእያንዳንዱን ዓላማ እንዲረዱ ያሳዩትን ልዩ ልዩ ዓይነት መጽሐፎች ከልጆቹ ጋር ለመወያየት ይዘጋጁ።
3. "ስምንቱ የእምነት አንቀጾች" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 127)፣ ቃላቶቹ ከትክክለኛው የእምነት አንቀጽ ጋር አንድ ዓይነት ናቸው።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. አራቱ መደበኛ የቀዱሳን መጻሕፍት።
   ለ. የታሪክ መጽሐፍ፣ የምግብ መመሪያ መፅሐፍ፣ እና የማስተማሪያ መጽሐፍ የመሳሳሉት ሌሎች ብዙ መጽሐፎች።
   ሐ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ እና ማጥፊያ።
   መ. ስዕል 3-41፣ ላማን ሲሸሽ፣ ስዕል 3-42፣ ኔፊ በላባን ቤት አቅራቢያ፣ ስዕል 3-43፣ ኔፊ እና ዞራም፣ እና ስዕል 3-44፣ ሌሂ እና የነሐስ ሰሌዳዎቹ።
5. ለማንኛቸውም ለሚጠቀሙባቸው ጠቃሚ ተሳትሮዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርት ዕድገቱ የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዙዋቸው ይከታተሏቸው።

**ቀዱሳን መጽሐፍት የሰማዩ አባትን ትዕዛዛት ይዟል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ልዩ ልዩ ዓይነት መጽሐፎችን በተለያዩ የክፍሉ ማዕዘኖች ያስቀምጡ እና ስለ እያንዳንዱ ትንሽ ይናገሩ። ከዚያም ያሳዩትን መጽሐፎች በተመለከተ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ወይም ሌሎች ጥያቄዎችን ጠይቁ። ልጆቹ እያንዳንዱን ጥያቄዎች በትክክል ከመለሱ በኋላ፣ ያንን መፅሐፍ ወደ ያዘው የክፍሉ ማዕዘን እንዲሄዱ እና እንዲያመለክቱአችሁ አድርጉ።

- ከእነዚህ መጽሐፎች ኬክ እንዴት እንደሚሰራ የሚገልፀው የትኛው ነው?
- ከእነዚህ መጽሐፎች ታሪኮችን የሚያስመስለው የትኛው ነው?
- ከነዚህ መፅሐፎች ትዕዛዛትን እንድንጠብቅ የሚረዳንን የነቢያት ትምህርቶች የያዘው የትኛው ነው?

የሰማዩ አባት ትዕዛዛትን እንድናከብር እንደሚፈልግ ይግለጹ። እርሱ ትምህርቱን እና ትዕዛዛቱን ማወቅ እንድንችል ቃሉን እንዲፅፍ ለነቢያት ነግሯቸዋል።

- ነቢያት የጻፉበትን የተቀደሱ መጽሐፍት ምን ብለን እንጠራዋለን? (ቅዱሳን መጽሐፍት።)

ትዕዛዛት ምን እንደሆኑ እንድናውቅ ወንጌልን እና ሰዎች እንዴት እንዳከበሩት ብዙ ነቢያት እንደመዘገቡ ይግለጹ። እነዚህ ትዕዛዛት በአራቱ የቅዱሳን መጽሐፍቶቻችን ተመዝግበዋል። አንዳንዴ እነሱን መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት ብለን እንጠራቸዋለን።

**ኔፊ ቅዱሳን መጽሐፍቱን አገኘ**

ስዕሎች፣ የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ፣ እና ውይይት

ለኔፊ እና ለቤተሰቡ ቅዱሳን መጽሐፍት ምን ያህል አስፈላጊ እንደነበሩ የሚያሳየውን ታሪክ መጽሐፈ ሞርሞን እንደያዘ ይግለጹ።

ሌሂ ለወንዶች ልጆቹ—ለላማን፣ ለሌሙኤል፣ ለሳም፣ እና ለኔፊ—ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ላባን ከሚባለው ሰው አንዳንድ የነሐስ ሰሌዳዎችን እንዲያመጡ እንደሚፈልግ የነሐስ ሰሌዳዎች እንደነበራቸው ለልጆቹ ይንገሩ ከነሐስ የተሰሩ ገፆች ያሉት ቅዱሳን መጽሐፍት ነበሩ። ላማን እና ሌሙኤል ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው መሄድ አልፈለጉም እናም በጣም ተናደው ነበር፣ ነገር ግን ኔፊ እና ሳም ለመሄድ ፈቃደኞች ነበሩ።

ኔፊ የነሐስ ሰሌዳዎችን ለማምጣት ስለመሄዱ ምን እንደተሰማው፣ ለልጆቹ ለማሳየት፣ 1ኛ ኔፊ 3፥7ን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያንብቡ እና ከልጆቹ ጋር ይወያዩበት።

- ኔፊ ለመሄድ ፈቃደኛ የሆነው ለምን ነበር? (ጌታ የተሰጠውን ትዕዛዝ እንዲፈፅም መንገድ እንደሚያዘጋጅለት ያውቅ ስለነበረ ነው።)
- ኔፊ የገባው ቃልኪዳን ምንድን ነበር? (ጌታ እንዲያደርግ ያዘዘውን እንደሚያደርግ ነው።)

ኔፊ ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር እንዲሄዱ እንዳሳመናቸው ይግለጹ።

ወደ ላባን ቤት ለመሄድ የመጀመሪያው ላማን ነበር። ላባንን የነሐስ ሰሌዳዎቹን ጠየቀው። ላባን ሰሌዳዎቹን ለላማን አልሰጠውም ሊገድለውም አስፈራራው። ላማን ፈርቶ ወደ ወንድሞቹ ሸሸ። ስዕል 3-41 የሚለውን ላማን ሲሸሽ ያመልክቱ። ወደ አባታቸው ወደ ምድረበዳ ተመልሶ መሄድ ፈለገ።

ኔፊ የነሐሱን ሰሌዳዎች ለማግኘት ትዕዛዛቱን መታዘዝ አለባችሁ አላቸው። ኔፊ እና ወንድሞቹ ወደ ቀድሞ ቤታቸው በኢየሩሳሌም ተመልሰው ሄደው ወርቆቻቸውን እና ብሮቻቸውን አገኙ። ሐብቶቻቸውን በነሐስ ሰሌዳዎቹ ለመለወጥ አቀዱ።

ላባን ወርቆቻቸውን እና ብሮቻቸውን ወሰደ ነገር ግን ለኔፊ እና ለወንድሞቹ የነሐስ ሰሌዳዎቹን አልሰጠም። እንዲገድሏቸው የራሱን ሰዎች አዘዛቸው። ኔፊ እና ወንድሞቹ ሮጠው ተደበቁ።

ላማን እና ሌሙኤል ተናደዱ። ኔፊ እና ሳምን በዱላ ደበደቧቸው። መልአክ ተገለፀ እና እንዲያቆሙ አዘዛቸው። መልአኩም የነሐስ ሰሌዳዎችን ለማግኘት ጌታ እንደሚረዳቸው እና ኔፊን እንዲታዘዙት ነገራቸው።

ስዕል 3-42፣ ኔፊ በላባን ቤት አቅራቢያ የሚያሳየውን ያሳዩ።

በዚህን ጊዜ ኔፊ ሰሌዳዎቹን ለማግኘት ሄደ። እርሱ ወደ ላባን ቤት ሾልኮ ሲገባ ወንድሞቹ ከከተማ ውጪ ሆነው ጠበቁት። ኔፊ ላባን ሰክሮ መሬቱ ላይ ተኝቶ አገኘው። ኔፊ ላባንን እንዲገድለው መንፈስ ቅዱስ ነገረው። ኔፊ ማንንም መግደል ስላልፈለገ አመነታ።

ኔፊ የቅዱሳን መጽሐፍትን ታላቅ ጥቅም አስታወሰ፣ እናም ላባንን ካልገደለ በስተቀር የነሐስ ሰሌዳዎቹን ማግኘት እንደማይችል አወቀ። እናም መንፈስ ቅዱስ እንዲያደርግ የነገረውን አደረገ። ላባንን ገደለና የላባንን ልብሶች ለበሰ።

ከዚያም ራሱን ላባንን መሰለ።

ስዕል 3-43፣ ኔፊ እና ዞራም የሚለውን ያሳዩ።

ኔፊ ለላባን አገልጋይ ለዞራም የነሐስ ሰሌዳዎቹን እንዲያመጣለት እና እንዲከተለው ነገረው። ዞራምም ኔፊ ላባን ነው ብሎ በማሰብ ታዘዘው። በኋላም፣ ኔፊ እርሱና ወንድሞቹን የነሐስ ሰሌዳዎቹን እንዲያመጡ ጌታ እንዳዘዛቸው ለዞራም ገለፀለት። ዞራምም አመነው። እርሱም መታዘዝ ፈለገ። ከኔፊ እና ከወንድሞቹ ጋር ወደ ሌሂ ወደ በረሃው ሄደ።

ስዕል 3-44፣ ሌሂ እና የነሐስ ሰሌዳዎች የሚለውን ያሳዩ።

ሌሂ የነሐስ ሰሌዳዎቹን አነበበ። ሰሌዳዎቹ ትዕዛዛትን እና ስለ ሙሴ እና ሌሎች ነቢያት አንዳንድ ታሪኮችን ይዘዋል። የሌሂ ቤተሰብንም የዘር ግንድ ይዘዋል። ሌሂ የነሐሱን ሰሌዳዎቹን ወደ ቃልኪዳኑ መሬት ይዞ እንዲሄድ ታዘዘ።

- በነሐስ ሰሌዳዎቹ ላይ የነበረው የማን ጽሁፍ ነው?
- በነሐስ ሰሌዳዎቹ ላይ የተጻፈው ምንድነው?
- ሌሂ እና ቤተሰቡ የነሐስ ሰሌዳዎቹን የፈለጉት ለምንድነው ብለው ያስባሉ?

ለሌሂ ቤተሰቦች የተጻፉትን የትዕዛዛት መዛግብት የያዘውን ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር ይዘው መሄዱ ለምን እንዳስፈለገ ልጆች እንዲያውቁ ለመርዳት የሚከተለውን ጨዋት ይጫወቱ።

የጨዋታው ዓላማ የቅዱሳን መጽሐፍት ቃላቶች ባይጻፉ ኖሮ እንዴት ግራ ሊያጋቡ እንደሚችሉ ለማሳየት ነው።

ልጆቹ በክብ እንዲቀመጡ ያድርጉ። በቀኝዎ በኩል ላለው ልጅ፣ "የሰማይ አባትን ትዕዛዛት እታዘዛለሁ፣" በማለት በሹክሹክታ ይንገሩት። ከዚያም ያም ልጅ የሰማውን ወይም የሰማችውን በቀኙ ወይም በቀኟ በኩል ላለው ሰው በሹክሹክታ እንዲነግር ወይም እንድትነግር ያድርጉ። በክቡ (በዙሪያ) ያለው ሰው ሁሉ እስኪሰማ መልዕክቱን ማስተላለፍ ይቀጥሉ። የመጨረሻው ልጅ ተነስቶ እንዲቆም ወይም እንድትቆም እና የሰማውን ወይም የሰማችውን ቃላት ደግሞ እንዲናገር ወይም እንድትናገር ያድርጉ። ልጁ ምናልባት የመጀመሪያውን መልዕክት በትክክል ላይደግመው ይችላል። (መልዕክቱ አንድ አይነት ከሆነ፣ ልጆቹ እንዴት ጥሩ እንደሰሩ ሊያሞግሳቸው ይችላሉ። ከዚያም ሁለት ወይም ሶስት ዓረፍተ ነገሮች ያለው ሌላ መልዕክት ለማለት ይሞክሩ።) የጀመሩትን መልዕክት ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ያልተጻፉትን ታሪኮች ወይም መልዕክቶችን መርሳት ወይም ግራ መጋባት ቀላል እንደሆነ ይግለጹ። ነቢያት የሰማዩ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች እንዳይረሱ ጽፈውታል። እነዚህ ትምህርቶች በቅዱሳን መጻሕፍቶቻችን ላይ ይገኛሉ።

የሌሂ ቤተሰብ ትዕዛዛቱን እንዲያስታውሱ እና እንዲታዘዙ የነሐስ ሰሌዳዎቹ ያስፈልጋቸው ነበር።

### ቅዱሳን መጽሐፍት እንድንታዘዝ ይረዱናል

**የቅዱሳን መጽሐፍት ተሳትፎ**

ልክ እንደ ሌሂ ቤተሰብ እኛም ትዕዛዛትን ማወቅ እንደሚያስፈልገን ይግለጹ። ብዙ ትዕዛዛቶቻቸውን ስለያዙ ቅዱሳን መጽሐፍት የሰማዩ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንድንታዘዝ ሊረዱን ይችላሉ።

ሁለት ጥቀሶችን ሲያነቡ ልጆቹ በጥንቃቄ እንዲያደምጡ ያድርጉ። ጥቀሱ የሚያስተምረው ትዕዛዛት ምን እንደሆነ ሲያውቁ እጃቸውን እንዲያወጡ ይጠይቋቸው። 3ኛ ኔፊ 18፡19ን እና ሞዛያ 23፡15ን ያንብቡ እና ከልጆቹ ጋር ይወያዩባቸው።

ቅዱሳን መጽሐፍት ባይኖሩን ኖሮ፣ ትዕዛዛትን እንረሳ እና አንታዘዛአቸውም። እንዲሁም ትዕዛዛትን ከመጠበቅ የሚመጣውን በረከት አንቀበልም።

**የእምነት አንቀጽ እና መዝሙር**

"ስምንተኛው የእምነት አንቀጽ" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ ያድርጉ። ይህ የእምነት አንቀጽ የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ እና መጽሐፈ ሞርሞን የእግዚአብሄርን ቃል እንደያዙ፣ ማለትም እውነተኛውን ትምህርት ይዘዋል ማለት እንደሆነ ይግለጹ። የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ትምህርቶች ለወደፊት ትውልዶች እንዲጽፉ ነቢያትን አዘዋል።

ስምንተኛውን የእምነት አንቀጽ ክፍሉ ከእናንተ ጋር በድጋሚ እንዲሉት ያድርጉ። ዕድሚያቸው ከፍ ያለ ልጆች በቃላቸው እንዲያጠኑት ይረዷቸው ይሆናል። ቅዱሳን መጽሐፍት ስላለን ትክክለኛውን ለመምረጥ የሚረዱንን ትዕዛዛት መማር እና የጥምቀት ቃል ኪዳናችንን መጠበቅ እንደምንችል ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

**ማጠቃለያ**

ውይይት

ክፍሉ የሚከተለውን እንዲወያይ ያድርጉ፡

- በጸሎታችን የሰማይ አባታችንን ማመስገን ያለብን ስለምንድነው? (ሁሉንም መልሶች ይቀበሉ፣ ነገር ግን ቅዱሳን መጻሕፍትን ያሳስቡ።)
- በፀሎታችን እርሱን መጠየቅ ያለብን ለምንድን ነው? (ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ እንዲረዳን።)

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**የዳበረ ተሳትፎ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆቻችሁ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ"ለአስተማሪው መርጃዎች" "የክፍል ጊዜን" በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።

1. የነሐስ ሰሌዳዎችን ከላባን ለማግኘት የኔፊን እና የወንድሞቹን ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስ ታሪክ መናገር ይጀምሩ። ቀጥሎ ምን እንደሆነ በመናገር፣ እያንዳንዱ ልጅ በታሪኩ ላይ ዓረፍተ ነገርን እንዲጨምር ያድርጉ። ማስታወስ የሚችሉትን ያህል ብዙ ዝርዝሮችን እንዲሰጡ ያበረታቷቸው። ታሪኩን ለማስታወስ እንዲረዳቸው ስዕሎችን ይጠቀሙ። (ልጆቹ የተሳሳቱ መልሶችን የሚሰጡ ከሆነ ወይም ታሪኩን ከስርዓት ውጪ ደጋግመው የሚናገሩ ከሆነ፣ በተቻለ መጠን ወደ ትክክለኛው እንዲቀርቡ ስርዓቱን እንዲከተሉ ብቻ ይርዷቸው። ሁሉንም መልሶች ይቀበሉ እና ያበረታቱ።
2. አንድ ልጅ በሳምንቱ ውስጥ ትዕዛዛትን እንዴት እንደሚጠብቅ በጥቁር ሰሌዳው ላይ ወይም በቁራጭ ወረቀት ላይ እንዲስል እና ከዚያም ለማድረግ ያቀደውን ለቀሩት ልጆች እንዲነግር ያድርጉ። እያንዳንዱ ልጅ ስዕሉን የመሳል እና ለመግለጽ ዕድል እንዲኖረው ይህንን ለማድረግ ተራ አውጣ። ልጆቹ ቤተክርስቲያን መሄድን፣ መፀለይ፣ ቤተሰቦቻችውን መርዳትን፣ እና አሻንጉሊቶቻቸውን ማካፈልን እነዚህን የመሳሰሉትን ስዕሎች መሳል ይችላሉ።
3. ልጆቹ "የኔፊ ጉብዝና" የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን እንዲሉ ያድርጉ (የልጆች መዝሙር መጽሐፍ፣ ገፅ 120)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል። በቃላቶቹ አንዳንድ ድርጊቶችን ወይም ጨዋታዎችን ማድረግ ይፈልጉ ይሆናል።
4. ማንበብ ለሚችሉ ልጆች፣ በትምህርት 13 መጨረሻ ላይ ካለው የሚታደል ጽሁፍ ላይ "የጥምቀቴ ቃልኪዳን" የሚለውን ግልባጭ ያዘጋጁ። የሚታደለውን ጽሁፍ ከቃላቶቹ ሥር በመቁረጥ አራት ቦታ ቀራርጣቸው "እኔ፣ _ ፣ ቃል አገባለሁ፣" ከሚለው ቃላት ስር "የሰማይ አባትን ትዕዛዛት ለመታዘዝ፣" እና "የሰማይ አባት ቃል ይገባል" ከሚለው ቃላት ስር ቀራርጠው ቁራጮቹን ያደባልቋቸው እና ልጆቹ በትክክለኛው ቀደም ተከተል እንዲያስቀምጧቸው ያድርጉ። ልጆቹ ቁራጮቹን በአንድነት ካስቀመጡ በኋላ፣ የጥምቀት ቃልኪዳንን፣ ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ከክፍሉ ጋር ያንብቡ። የሰማይ አባት በጥምቀት ትዕዛዙን ለመታዘዝ የገባነውን ቃል ኪዳን እንድንጠብቅ እንደሚፈልግ ይግለጹ። ትምህርቶቹ እና ትዕዛዛቱን ማወቅ እንድንችል ቃሎቹን እንዲጽፉ ለነቢያት ነግሯቸዋል።

# የሰማይ አባት እንድንታዘዘው ይረዳናል

ትምህርት
**18**

---

**ዓላማው** ልጆቹ ትዕዛዛትን እንዲታዘዙ የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ እንደሚረዷቸው እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

---

**ዝግጅት**

1. 1ኛ ኔፊ 3፥7ን፣ 17ን፣ 18፥1–4ን በፀሎት ያጥኑ። ኔፊ መርከብ የመስራቱን ታሪክ ለመናገር ይዘጋጁ።
2. ከቻሉ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ የ1ኛ ኔፊ 3፥7ን የሚታደል ጽሑፍ ያዘጋጁ። የሚታደል ጽሑፉን ነጥብ በተደረገባቸው መስመሮች ላይ ለያይተው ይቁረጧቸው። የተቆራረጡትን ለእያንዳንዱ ልጅ በፖስታ ውስጥ ያድርጉላቸው።
3. "የኔፊ ጉብዝና" የሚለውን መዝሙር የመጀመሪያውን እና የሚቀጥለውን ቁጥሮች ለመዘመር ይዘጋጁ (የልጆች የመዝሙር መጹሐፍ፣ ገፅ 120)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. ከሚገኝበት፣ ለእያንዳንዱ ልጅ መጽሐፈ ሞርሞን፣።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ እና ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ።
   ሐ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ እና ማጥፊያ።
   መ. ስዕል 3-37፣ ኔፊ አመፀኛ ወንድሞቹን ሲያሸንፍ (62044፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 303)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸዋል።

**ኔፊ ትዕዛዛትን ጠብቋል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

እናንተ የምታደርጉትን እንዲያደርጉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከዚያም ተነስቶ እንደመቆም፣ እጆችህን ወገብህ ላይ እንደማድረግ፣ እንደመዞር፣ እና የመሳሰሉትን ብዙ ድርጊቶችን አድርጉ። እና እንደዚያ የመሳሰሉትን ይቀመጡ። ልጆቹ ስለመታዘዛቸው ያመስግኗቸው።

- መታዘዝ ማለት ምን ማለት ነው?

እንደተጠየቅነው ስናደርግ፣ እየታዘዝን እንደሆነ ወይም ታዛዥ መሆናችን እንደሆነ ይግለጹ።

ክለሳ

ታዛዥ ስለነበረ አንድ ሰው እያሰቡ እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከአባቱ ጋር ኢየሩሳሌምን ለመልቀቅ የጌታን ትዕዛዝ በፈቃደኝነት ታዘዘ።

የነሐስ ሰሌዳዎችን ለማምጣት እንደገና ወደ ኢየሩሳሌም የመመለስንም ትዕዛዝ በፈቃደኝነት ታዘዘ።

- ይህ ሰው ማን ነበር? (ኔፊ።)

ኔፊ የነሐስ ሰሌዳዎቹን ለማግኘት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ ሲታዘዝ፣ ይህንን ማድረግ ከባድ እንደሆነ ያውቅ ነበር፣ ነገር ግን እንደ መታዘዝ ለአባቱ እንደነገረ ይግለጹ። ታሪኩን ከትምህርት 17 ላይ በአጭሩ ይከልሱ።

የመጽሐፈ ሞርሞንን ግልባጭ ለልጆቹ ያሳዩ እና ኔፊ ለአባቱ ይነገሯቸው ቃላቶች በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደተጻፈ ይንገሩቸው። ማንበብ የሚችል እያንዳንዱ ልጅ የመጽሐፈ ሞርሞን ግልባጭ እንዳለው ይመልከቱ። 1ኛ ኔፊ 3፥7ን እንዲያገኙት ይርዷቸው።

**መዝሙር**

“የኔፊ ጉብዝና” የሚለውን መዝሙር የመጀመሪያውን ቁጥር ቃላቶች ከልጆቹ ጋር ይዘምሩት ወይም ይበሉ።

1ኛ ኔፊ 3፥7ን ለልጆቹ ያንብቡ። ኔፊ ለአባቱ፣ ጌታ ያዘዘውን ነገር ሄዶ እንደሚያደርግ ነገረው። ጌታ ለሰው ልጆች ያዘዛቸውን ነገሮች የሚፈፅሙበትን መንገድ ካላዘጋጀ በስተቀር ምንም ዓይነት ትዕዛዛት እንደማይሰጥ ያውቅ ነበር። እንደዚህ መዝሙር ሶስት የመጨረሻ መስመሮች አይነት ነገር እንደሚናገር ይግለጹ። ልጆቹ እነዚያን መስመሮች ደግመው እንዲዘምሩ ወይም እንዲሉ ያድርጉ። ልጆቹ ትዕዛዛቱን እንዲታዘዙ ጌታ እንሚረዳቸው እንዲያውቁ ይርዷቸው።

### ጌታ መርከብ እንዴት እንደሚሰራ ኔፊን አስተማረው

**የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ**

መጽሐፈ ሞርሞን ስለ ኔፊ ብዙ አስደናቂ ታሪኮችን እንደያዘ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከዚያም የሚከተለውን በራሳችሁ አባባል ይናገሩ፣

ሌሂ እና ቤተሰቡ ለስምንት ዓመታት በምድረበዳ ተጓዙ። በምድረበዳ መጓዝ እና መኖር አስቸጋሪ ነበር። ድንኳን ውስጥ መኖር እና ምግባቸውን ማደን ነበረባቸው። በመጨረሻም በባሕር ወደ አንድ ምድር መጡ። ያንንም ምድር ለጋስ ብለው ሰየሙት። እዚያ በመሆናቸው ደስተኞች ነበሩ ምክንያቱም የሚመገቡት ፍራፍሬ እና ማር ነበር። ድንኳናቸውን በባሕር ዳርቻ ተከሉ።

ሌሂ እና ቤተሰቡ በለጋስ ምድር ላይ ለብዙ ዓመታት ከቆዩ በኋላ፣ ጌታ ቤተሰቡ ባሕሩን አቋርጦ ወደ ቃልኪዳኑ ምድር ለመሄድ መርከብ እንዲሰራ ለኔፊ ነገረው። ኔፊም ጌታ እንደሚረዳው አመነ። ኔፊም መርከቡን ለመስራት የሚያስፈልጉትን መሳሪያዎች ለማዘጋጀት የብረት አፈር ከየት ማግኘት እንደሚችል ጠየቀው። ኔፊ የብረት አፈሩን ከየት እንደሚያገኝ ተነገረው እናም መሳሪያዎቹን ለመስራት ቻለ።

የኔፊ ወንድሞች ላማን እና ሌሙኤል መርከብ ሊሰራ መሆኑ ሲመለከቱ፣ ማጉረምረም ጀመሩ። ኔፊ መርከብ መሥራት ይችላል ብለው አላመኑም። ለመርዳትም እምቢ አሉ። ጌታ መርከብ እንዴት እንደሚሰራ ለኔፊ ይነግረዋል ብለው አላመኑም።

ነገር ግን ኔፊ ጌታ እንደሚረዳው ያውቅ ነበር። እርሱ ሁልጊዜ ትዕዛዛቱን እንድናከብር ይረዳናል። ኔፊ መመሪያዎቹን ታዟል።

ኔፊ ለላማን እና ለሌሙኤል ትዕዛዛቱን ቢታዘዙ እና ጌታ የጠየቀውን ቢያደርጉ፣ እነርሱንም እንደሚረዳቸው ነገራቸው። ላማን እና ሌሙኤል ማድረግ ያለባቸውን ኔፊ እንዲነግራቸው አልፈለጉም። ባህር ውስጥ ሊወረውሩት ፈለጉ፣ ነገር ግን ኔፊ በእግዚአብሔር ሃይል ተሞልቶ ነበር። ለወንድሞቹ እንዳይነኩት ነገራቸው። ላማን እና ሌሙኤል ፈሩ። ኔፊም ንስኃ እንዲገቡ እና ትዕዛዛትን እና ወላጆቻቸውን እንዲታዘዙ ነገራቸው።

ከዚያም ኔፊ ጌታ እንደሚረዳው እንዲያውቁ ወንድሞቹን ነካቸው እና አንቀጠቀጣቸው።

**የስዕል ውይይት**

ስዕል 3-37፣ ኔፊ አመፀኛ ወንድሞቹን ሲያሸንፍ የሚለውን ያሳዩ።

- ላማን እና ሌሙኤል የተሰማቸውን እንዴት ታስባላችሁ?

ላማን እና ሌሙኤል ንስኃ እንደገቡ ይግለጹ። ኔፊ መርከቡን እንዲሰራ ረዱት።

- ጌታ ኔፊን የረዳው እንዴት ነበር? (መሳሪያዎቹን እንዲሰራ የብረት አፈር ከየት እንደሚያገኝ ነገረው። መርከብ እንዴት እንደሚሰራ አስተማረው። ከወንድሞቹ ጠበቀው።)

ኔፊ ምንም እንኳን መርከብ እንዴት እንደሚሰራ ባያውቅም፣ ትዕዛዛቱን ካከበረ ጌታ እንደሚረዳው ማመኑን ይግለጹ።

“የኔፊ ጉብዝና” የሚለውን መዝሙር ሁለተኛ ቁጥር ከልጆቹ ጋር ይዘምሩት ወይም ይበሉት።

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

በጥቁር ሰሌዳው ላይ ትንሽ ፈገግታ ያለው ፊት እና ደስተኛ ያልሆነ ፊት ስዕል ይሳሉ። ስለአስደሰታቸው ነገር ከልጆቹ ጋር ይነጋገሩ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንደሰት እንደሚፈልጉ፣ እናም ትዕዛዛትን እንድንታዘዝ የሰጡንም ለዚህ እንደሆነ ልጆቹ እንዲያውቁ ይርዷቸው። ትዕዛዛትን ስለ መታዘዝ እንዴት ደስታን እንደሚያመጣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠይቁ፣

- ኔፊ መርከብን የመስራት ትዕዛዛትን ሲታዘዝ እንዴት እንደተሰማው ከእነዚህ ፊቶች የሚያሳየው የትኛው ነው?
- ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ደስታ እንዲሰማን የሚረዳን እንዴት ነው?
- የቤተሰባችን አባላትን መውደድ እና ማገልገል ደስተኛ እንድንሆን የሚረዳን እንዴት ነው?

**ጌታ ትዕዛዛትን እንድናከብር ይረዳናል**

ታሪክ

ጌታ ኔፊን እንደረዳ፣ በእርሱ እምነት ካለን እና ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ ፈቃደኞች ከሆንን እያንዳንዳችንም እንደሚረዳን ይግለጹ። አንዲት ወጣት ልጃገረድ የሰንበት ቀንን በቅድስና የመጠበቅን ትዕዛዝ ስትታዘዝ የሰማዩ አባት እንዴት እንደረዳት ስለሚናገረው ታሪክ ሲናገሩ ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ።

ሚሊንግ ከወንዝ አጠገብ መንገድ ላይ የሚሸጥ የምግብ መደብ ነበራት። ሁልጊዜ ሱቁ ለሚመጡ ሰዎች ሩዟን እና አሳዋን ትሸጣለች። ማታ ማታ ወደ ቤቷ በቤት ጀልባ ተመልሳ ያገኘችውን ገንዘብ ስትቆጥር፣ ለቤተሰቧ ሩዝ ለመግዛት እና በሚቀጥለው ቀን ለምትሸጠው አሳ ስለማይበቃት፣ ቁና ቁና ትተነፍስ እና እራሷን ታነቃንቃለች።

ሚሊንግ አንድ ቀን ወንጌላዊያኖችን አገኘች፣ እና ወንጌልን አስተማሯት። ስለሰማይ አባት ትዕዛዛት እና የሰንበት ቀንን በቅድስና ስለመጠበቅ አስተማሯት። ሚሊንግ የሰማይ አባትን በፀሎት አነጋገረች እና ከእንግዲህ በሰንበት ቀን መደቧን እንደማትከፍት ቃል ገባችለት። የሰንበት ቀንን በቅድስና መጠበቅ እና በሰንበት ቀን ላለመስራት ፈለገች።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ ሚሊንግ ማታ ማታ ገንዘቧን ስትቆጥር፣ ከዚያ በፊት ከምታገኘው ገንዘብ የበለጠ እንዳገኘች አወቀች። ከቤተሰቧ ጋር ልትካፈል የምትችለውን የበለጠ ምግብ መግዛት ቻለች፣ እናም የበለጠ የምትሸጠውን አሳ መግዛት ቻለች። ሚሊንግ የሰንበት ቀንን በቅድስና ስለጠበቀች የሰማዩ አባት ባረካት። ሚሊንግ ትዕዛዛቱን ስላከበረች ደስተኛ ነበረች።

ውይይት

- ሚሊንግ ያከበረችው ትዕዛዝ ምንድን ነበር?
- የሰማዩ አባት የረዳት እንዴት ነበር?

የሰማዩ አባት ልክ ኔፊን እና ሚሊንግን እንደረዳቸው፣ ትዕዛዛቱን የሚያከብሩትን ሁሉንም እንደሚረዳቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው።

**ማጠቃለያ**

የአስተማሪ ምስክርነት

ተገቢ ከሆነ፣ ትዕዛዝን እንዲታዘዙ ጌታ የረዳችሁ ጊዜ ለልጆቹ ይንገሯቸው። የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዱን እና ትዕዛዛትን እንድንታዘዝ እንደሚረዱን ምስክርነታችሁን ይስጡ።

ለእያንዳንዱ ልጅ ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ እና እርሳስ ይስጡ። ልጆቹ ፈገግታ ያለው ፊት እንዲስሉበት ያድርጉ። ከዚያም ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ ሰላምን መፍጠር፣ እናት እና አባትን መርዳት፣ ለወንድም ወይም ለእህት ደግ መሆንን፣ ወይም ከጓደኞች ጋር መካፈልን የመሳሰሉትን የሚያዙትን ትዕዛዝ እንዲመርጡ ያድርጉ፣። እያንዳንዱ ልጅ በካርዱ ላይ የመረጠውን ትዕዛዝ እንዲጽፍ ያድርጉ። ልጆቹ ሲታዘዙ እንዴት እንደተሰማቸው በሚቀጥለው ሳምንት መግለጫ ለመስጠት እንዲዘጋጁ ይንገሯቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ

**የዳበረ ተሳትፎ**

ከሚከተሉት ተግባራዊ ተሣትፎዎች ለልጆቻችሁ የተሻለ የሚሰሩትን ምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪው መርጃ” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. እንደ አክብሮት፣ ፀሎት፣ ደግነት፣ ታማኝነት፣ የጥበብ ቃል፣ እና ስለ መሳሰሉት ስለ አንዳንድ ትዕዛዛት ከልጆቹ ጋር ይነጋገሩ። እያንዳንዱ ሰው አንዳንድ ትዕዛዛትን መታዘዝ ከሌሎቹ ይልቅ ቀላል ሆኖ እንደሚያገኘው ይግለጹ። እኛ ትዕዛዛቱን መታዘዝ በእውነቱ የምንሞክር እና የእርሱን እርዳታ የምንጠይቅ ከሆነ የሰማይ አባት እያንዳንዳችንን እንደሚረዳን አጥብቀው ያሳስቡ።

2. ከልጆች ጋር፣ “ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ” የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ይበሉ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 160) እና ስለ ትዕዛዛት ሌሎች መዝሙሮች፣ እንደ “እርስ በርስ ተዋደዱ” (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 136) ወይም “ስንረዳዳ” (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 198)፣ የእነዚህ ሶስት መዝሙሮች ቃላቶች በዚህ መምሪያ በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል።

3. የባቄላ ሽፋን ወይም ትንሽ በጨርቅ የተሰራ እንስሳ ለአንድ ልጅ ይወርውሩ፣ ከዚያም እንደዚህ ያለ ጥያቄ ከትምህርቱ ውስጥ ይጠይቁ፣

   - ኔፊ እንዲሰራ ጌታ የነገረው ምንድን ነው?
   - ኔፊ መርከብ ስለመስራት ሲነግራቸው ላማን እና ሌሙኤ እንዴት ነው የሆኑት?
   - አሁን ልትታዘዙ የምትችሉትን ትዕዛዝ መጥራት ትችላላችሁን?
   - የሰማዩ አባትን እርዳታ ከፈለግን ማድረግ የምንችለው ምንድን ነው? (መፀለይ።)
   - ጌታ ለኔፊ እንዲያደርግ የነገረው ከባድ ነገር ምንድን ነበር?
   - ኔፊ መሳሪያዎችን ያገኘው እንዴት ነበር?

4. ልጆቹ የብረት አፈር ለማግኘት የሚቆፍሩ፣ መሳሪያዎችን የሚሰሩ፣ እና ኔፊ እንዳደረገው መርከብን የሚሰሩ እንዲያስመስሉ ያድርጉ።

5. እድሚያቸው ከፍ ላለ ልጆች፡ ለእያንዳንዱ ልጅ የ1ኛ ኔፊ 3፡7ን የጽሑፍ ግልባጭ ያዘጋጁ። በመስመሮቹ ለያይተው ቁረጡት እና ልጆቹ መስመሮቹን በቁራጭ ወረቀት ላይ በመደዳ እንዲያጣብቁቸው ያድርጉ።

# 1ኛ ኔፊ 3፥7

እኔ እሄዳለሁ ጌታ ያዘዘኝን

አደርጋለሁ፤ በእርግጥ

አውቃለሁ ጌታ ለሰዎች

ልጆች ምንም ትዕዛዞች

አይሰጥም፤ ትዕዛዞቹን

የሚፈፅሙበትን

መንገድ ካላዘጋጀላቸው

በስተቀር።

ትምህርት

# 19

# ስንፀልይ የሰማይ አባት ይረዳናል

---

**ዓላማው** ልጆቹ ሲፀልዩ ከሰማዩ አባት እርዳታን መቀበል እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

---

**ዝግጅት**

1. 1ኛ ኔፊ 18፥5–23ን እና 3ኛ ኔፊን 18፥20ን በፀሎት ያጥኑ።
2. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ እና ማጥፊያ።
   ስዕል 3-45፣ ሌሂ እና ሕዝቡ ወደ ቃልኪዳኑ መሬት ሲደርሱ (62045፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 304)፣ ስዕል 3–46፣ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ሲፀልይ (62175፣ የወንጌል ስዕል ኪነ-ጥበብ ጥራዝ 227)።
3. የሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ዛሳብ**


አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**ኔፊ ፀለየ እና ዕርዳታን አገኘ**

የአትኩሮት ተሳትፎ


ልጆቹን እያነጋገሩ እያለ የሚከተለውን ስዕል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይሳሉ፥



አንድ አባት እና ያገባው ወንድ ልጁ በጣም ከፍተኛ ከሆነው ተራራ ፊት ለፊት እንደሚኖሩ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

- ይህ አባት እና ልጁ ወደ ተራራው ጀርባ ሳይሄዱ እንዴት መገናኘት ይችላሉ?

ልጆቹ ያቀረቡትን ዛሳብ ለማሳየት የሚከተሉትን ስዕሎች ይሳሉ፥




- ለአባት እና ልጅ እርስ በእርስ መገናኘቱ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? (ከብቸኝነት ለመራቀ፣ ፍቀርን ለማሳየት፣ ዕርዳታን ለመቀበል እና ለመስጠት፣ ሃሳቦችን ለመካፈል።)
- እርስ በእርስ ባይገናኙ ኖሮ ምን ይፈጠር ነበር? (እርስ በእርስ መቀራረብ አይሰማቸውም ነበር ፍቀራቸውም ሊቀንስ ይችላል። እርስ በእርስም መረዳዳት አይችሉም።)

ልክ እኛ በምድር ላይ በከፍተኛ ርቀት ተለያይተን መገናኘት እንደምንችለው፣ ከሰማያዊ አባታችንም ጋር መገናኘት እንደምንችል ይግለጹ።

- ከሰማያዊ አባታችን ጋር የምንገናኘው እንዴት ነው? (በፀሎት አማካኝነት ነው።)
- ከሰማያዊ አባታችን ጋር መገናኘት ለምን አስፈለገ? (ለበረከታችን እንድናመሰግነው፣ በእርሱ ያለንን እምነት ለማሳየት፣ ዕርዳታውን እና በረከቱን ለመጠየቅ እና ለመቀበል፣ ለእርሱ ያለንን ፍቀር ለመጨመር ነው።)

ስዕል፣ የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ፣ እና ውይይት

ስለ ኔፊ መርከብ መስራት የተማሩትን ትምህርት ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ፀሎት ኔፊን እንዴት እንደረዳው ለመማር ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ።

የኔፊ መርከብ ሲያልቀ፣ የኔፊ አባት፣ ሌሂ፣ ቤተሰቡ ዘሮችን፣ ምግብን፣ እና ሌሎች ነገሮችን በመርከቡ እንዲያስገቡ እንዲያደርግ ታዘዘ። ከዚያም መርከቡን ተሳፍረው ወደ ቃልኪዳኑ መሬት ተጓዙ።

ስዕል 3-45፣ ሌሂ እና ሕዝቦቹ ወደ ቃልኪዳኑ መሬት ደረሱ የሚለውን ያሳዩ፣ እና በሌሂ እጅ ላይ ያለውን ሊያሆና ያመልክቱ።

ሊያሆና አቀጣጫ የሚያመለክት የመሳሪያ ዓይነት እንደሆነ ይግለጹ። በበረሃ ውስጥ ወደ የትኛው አቀጣጫ እንደሚጓዙ እና መርከቡን ወዴየት እንደሚመሩ ያሳያቸው ነበር። የሚሰራው ጻድቀ ሲሆኑ ብቻ ነበር።

ቤተሰቡ ለብዙ ቀናት መርከብ ላይ ከቆየ በኋላ፣ አንዳንዶቹ የኔፊ ወንድሞች መጥፎ ድርጊት ያደርጉ ነበር። ለወላጆቻቸው እና መርከቡ ላይ ላሉት ሌሎች ሰዎች በብልግና ይናገሩ ነበር። የሰማዩ አባት ምን ያህል እንደረዳቸው እና እንደባረካቸው ረሱ። ኃጢአታቸው ጌታን ያስቀጣዋል ብሎ ኔፊ ፈራ፣ እናም ስለ ባሕሪያቸው ተናገራቸው። ላማን እና ሌሙኤ ተናደዱ።

ማድረግ ያለባቸውን ነገር ታናሽ ወንድማቸው እንዲነግራቸው አልፈለጉም። ኔፊን አሰሩና የተሳሳተ መንገዳቸውን ቀጠሉ።

ልክ ኔፊ እንደታሰረ፣ ሊያሆናው መስራቱን አቆመ። ላማን እና ሌሙኤል መርከቡን በየትኛው አቅጣጫ እንደሚመሩ አላወቁም። ከፍተኛ ማዕበል ተነሳ። ለሶስት ቀናት መርከቡን መምራት በማይቻልበት ሁኔታ በባህሩ ላይ ተንገላታ ሕዝቦቹም እንሰምጣለን ብለው አሰቡ። ላማን እና ሌሙኤል ግን አሁንም ኔፊን አልለቀቁትም።

ማዕበሉ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ሄደ። በመጨረሻም ላማን እና ሌሙኤል በኃጢአታቸው ምክንያት በአደጋ ውስጥ እንዳሉ አወቁ። ንስኃ ካልገቡ በማዕበሉ እንደሚሞቱ አወቁ፣ ስለዚህም ኔፊን ፈቱት።

ምንም እንኳን የኔፊ ቁርጭምጭሚቶች እና የእጅ አንጓዎች ቢያብጡ እና በጣም ቢቆስሉም፣ ሰማይን አባት አላማረረም።

ኔፊ ከተፈታ በኋላ፣ ሊያሆናው እንደገና በፍጥነት መስራት ጀመረ። አሁን ኔፊ መርከቡን በትክክለኛው አቅጣጫ መምራት ቻለ።

ኔፊ ወደ ሰማዩ አባት ፀለየ። ንፋሱም መናፈሱን አቆመ ባሕሩም ፀጥ አለ።

ማዕበሉም ሲያቆም ሊያሆናውም እንደገና መስራት ሲጀምር፣ ኔፊ መርከቡን ወደ ቃልኪዳኑ መሬት በደህና መራ።

- ኔፊ ታስሮ በነበረበት ጊዜ ሊያሆናው ለምን አልሰራም?
- ኔፊ በታሰረበት ጊዜ ወደ ሰማይ አባት አቤቱታ ያላሰማው ለምን ይመስላችኋል?
- ከኔፊ ምሳሌ መማር የምንችለው ምንድን ነው?
- ኔፊ መርከቡ በማዕበል እንዳይሰጥም ለማዳን ያደረገው ምንድነው?
- የሰማይ አባት ኔፊን ለመርዳት ያደረገው ምንድን ነው?

### ሰማያዊ አባት ስንፀልይ ይረዳናል

ስዕል እና የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ

ስዕል 3-46፣ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ሲፀልይ የሚለውን ያሳዩ።

- በዚህ ስዕል ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እያደረገ ነው? (ወደ ሰማይ አባት እየፀለየ ነው።)
- ኢየሱስ የፀለየው ለምንድን ነው? (የሰማዩ አባት እንዲመራው እርዳታን ስለ ፈለገ ነው።)

ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ዘወትር ለሰማዩ አባት ይጸልይ እንደነበር ይግለጹ። እኛም ዕርዳታ ስንፈልግ ወደ ሰማዩ አባት መፀለይ እንችላለን።

ታሪክ

ለሌላ ሰው ፍላጎት ስለ ፀለየች አንዲት ወጣት ልጃገረድ እውነተኛ ታሪክ የሚከተለውን ይናገሩ፣

አንድ ቀን ማታ በጫጫታ ስትነቃ ሚሪ በአልጋዋ ላይ ተኝታ ነበር። ስታዳምጥ፣ የአራት ዓመት ወንድሟ ሆዱን እንደሚያመው በማልቀስ አቤቱታ እያሰማ መሆኑን አወቀች። እናቷ እንዲሻለው ለመርዳት በመሞከር ለስለስ ባለ ሁኔታ ስታፅናናው ይሰማታል፣ ነገር ግን ወንድሟ ማልቀሱን ቀጠለ። እዚያ ተኝታ አዘነችለት። እናቷ የሚቻላትን ሁሉ እያደረገችለት እንደሆነ አወቀች፣ ነገር ግን አሁንም ወንድሟ በጣም እያመመው መሆኑን ማወቁ ረበሻት። በመጨረሻም ማድረግ የምትችለው አንድ ነገር መኖሩን ወሰነች።

- ምን ያደረገች ይመስላችኋል?

በቀስታ ከአልጋዋ ወርዳ ለመፀለይ ተንበረከከች። ትንሽ ወንድሟ መዳን እና መተኛት ተመልሶ እንዲችል ደህና እንዲያደርገው የሰማዩን አባት ጠየቀች። በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ ወንድሟን እንቅልፍ ወሰደው። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት እንዴት እንደነበረ እናቷን ጠየቀቻት፣ እርሷም “ደህና ነው። ትናንትና ማታ እንቅልፍ ወስዶታል አሁንም ደህና ይመስላል” ብላ መለሰችላት።

እነርሱ ወይም የቤተሰባቸው አባል ለእርዳታ የፀለዩበትን ጊዜ ልምድ እንዲናገሩ ወይም እንዲያካፍሉ የክፍሉን አባላት ጋብዙ። የሰማዩ አባት ጸሎታቸውን እንዴት እንደመለሰው እንዲገልፁ ያድርጉ።

ታሪክ

ለዕርዳታ ስለፀለየው አንድ ሰው የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፣ ወይም የራሳቸውን ታሪክ ይናገሩ፥

አንድ በጋ ጂሚ ትንሽ የበግ ጠቦት ተሰጠው። ጠቦቱን ቡትስ ብሎ ጠራው እናም በፍቅር ይመግበው እና ይንከባከበው ነበር። ጂሚ እና ቡትስ ዘወትር የጂሚ አባት ፈረሳቸውን በሚያስቀምጡበት የታጠረ ሜዳ ውስጥ ይጫወቱ ነበር። የጂሚ እናት ጂምን ለእራት ስትጠራው አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ ምሽት ላይ ጂሚና ቡትስ በዚህ ሜዳ ውስጥ ይጫወቱ ነበር። ጂሚ ወደ በሩ ሮጠ እና በፍጥነት ከኋላው መለስ አደረገው።

ከእራት በኋላ ጂሚ እንደገና ከቡትስ ጋር ለመጫወት ወጣ። ነገር ግን በሩ ጋር ሲደርስ፣ ተከፍቶ ሲወዛወዝ አገኘው። ቡትስ እና ፈረሱ ሄደዋል። ጂሚም በሩ እንዳይወረወር በፍጥነት ዘጋው።

ጂሚ ከየት መፈለግ እንደሚጀምር አላወቀም። አባቱ የነገረውን አስታወሰ፣ ህፃን ልጅ በነበረበት ጊዜ፣ በተራራማ አካባቢ ጠፍቶ ነበር። አባቱም ተንበርክኮ እንዲረዳው የሰማዩ አባትን ጠየቀ። ወዲያው አንድ የበግ እረኛ ወደ ሰፈሩ ሲሄድ መንገዱ ላይ አግኝቶት ቤቱ እንዲደርስ ረዳው።

ጂሚ በሳሩ ውስጥ ተንበረከከ፣ አይኖቹን ጨፈነ፣ እና "የሰማዩ አባት፣ እርዳታህን እፈልጋለሁ። በሩን ስላልዘጋሁት የአባቴ ፈረስ እና ቡትስ ጠፉብኝ። አባክህ እንዳገኛቸው እርዳኝ።" በማለት ፀለየ።

ጂሚ መንገዱ ላይ የእንሰሳ ዱካዎች አገኘ። ቁጥቋጦው እግሩን እንዲጠብቀለት በመያዝ፣ ዱካዎቹን በኮረብታ ላይ መከተል ጀመረ። በመጨረሻም ቡትስ ስትጮህ ሰማ። ጂሚ ወደ ዳገቱ ወጣና ወዲያው ትንሿ የበግ ጠቦት በቁጥቋጦው ተይዛ አገኛት። ፈረሱም አጠገቧ ቆሟል። ጂሚ የቡትስን እግሮች ከጥሻው አላቀቃቸው። ቡትስ ለመቆም ሲሞክር፣ ተንገዳገደ። ጂሚም ከቡትስ እግሮች አንዱ እንደተሰበረ አወቀ።

ጂሚ እንደገና የሰማዩ አባት እንዲረዳው ጠየቀ። ቡትስን ለመሸከሚያ ማሰሪያ ለመስራት ጃኬቱን ተጠቀመ እና ተራራውን መውረድ ጀመሩ። ፈረሱም ቀጥ ባለው የእግር መንገድ ያገኘውን ከመንገዱ ላይ እየለቀመ በጥንቃቄ ተከተላቸው። ቡትስ በጣም ከባድ ነበረች፣ እና ጂሚ በመንገዱ ወደታች ሲወርድ ተደነቃቀፈ።

ሶስቱም ወደ ቤት ሲቃረቡ፣ የጂሚ ወላጆች ለእርዳታ ሮጠው ወጡ። የጂሚ አባት ለተጎዳው ጠቦት እንክብካቤ ሲያደርግ፣ እንዲህ አለ፣ "ብዙ ደም ከመፍሰሱ በፊት እዚህ ማምጣትህ ጥሩ ነገር ነው። ደሙ አልቆ ሊሞት ይችል ነበር።"

የጂሚ እናት እንዲህ በማለት ጠየቀች፣ "የት እንደምታገኛቸው እንዴት አወቅህ?"

"ልክ አባቴ እንዳደረገው አደረግኩኝ፣" ብሎ ጂሚ መለሰ።

"ያ ምንድነው፣ ልጄ?" ብሎ አባትየው ጠየቀ።

"የጠፋህበትን ጊዜ ታስታውሳለህ? ለእርዳታ ወደ ሰማዩ አባት ጸለይክ፣ እና እኔም ያደረግኩት ልክ ያንኑ ነው። ፀለይኩ፣ እናም የሰማዩ አባት ረዳኝ" (See "The Open Gate," *Friend,* Apr. 1977, pp. 28–30).

**ማጠቃለያ**

የጥቁር ሰሌዳ ተሳትፎ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ትምህርቱን ይከልሱ። አንድ ልጅ ጥያቄውን ከመለሰ በኋላ፣ ወደ ጥቁር ሰሌዳው እንዲመጣ ያድርጉት። ከእጆቹ በአንደኛው ዙሪያ ምልክት ያድርጉ እና ስሙን በዝርዝሩ ውስጥ እንዲጽፍ ያድርጉ።

- ሌሂ እና ቤተሰቡ የሚሄዱት የት ነበር? (ወደ ቃልኪዳኑ ሀገር ነው።)
- ሊያሆናው ሁልጊዜ ይሰራ ነበርን? (አይደለም፣ ሰዎቹ ጻድቅ ሲሆኑ ብቻ ነበር የሚሰራው።)
- ሊያሆና ኔፊን ሲያሳየው የነበረው ምንድን ነው? (መርከቡን በየትኛው አቅጣጫ እንደሚመራ ነው።)

- ኔፊ ከታሰረ በኋላ ምን ተከሰተ? (አስከፊ ማዕበል ተነሳ። ሊያሆናው መስራቱን አቆመ።)
- ኔፊ ከተለቀቀ በኋላ ምን ተከሰተ? (ማዕበሉ አቆመ። ሊያሆናው እንደገና መስራት ጀመረ።)
- ኔፊ ለሰማዩ አባት ዕርዳታ ለምን ፀለየ?
- የሰማያዊ አባትን እርዳታ ስንፈልግ ምን ማድረግ አለብን? (እንደሚረዳን በእምነት መፀለይ አለብን።)

እያንዳንዱ ልጅ እጁን እስኪያወጣ ድረስ በትምህርቱ ውስጥ ስላሉት ታሪኮች ጥያቄዎችን መጠየቅን ይቀጥሉ። እርዳታ ሰጪ ለሆኑት እጆቻቸው በሙሉ ልጆቹን ያመስግኑ።

ምስክርነት

የሰማዩ አባት ለእኛ ያለውን ፍቅር እና ለእርዳታው ከፀለይን እኛን ለመርዳት ስላለው ፍላጎት ምስክርነታችሁን ይስጡ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆቻችሁ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” “የክፍል ጊዜን” በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።


1. ልጆቹን ስለ ፀሎት አጭር ግጥም ያስተምሯቸው፣ እና ድርጊቶቹን ያሳዩ።

   ክንዳችንን እናጥፋለን፣ እራሳችንን እንደፋለን፣
   አይናችንን እንዘጋለን፣ አሁን ዝግጁ ነን።

   ወይም

   እጃችንን እናጥፋለን እራሳችንንም እንደፋለን
   ፀሎት ሲደረግም እናዳምጣለን።

2. የሚከተለውን የሚታደል ጽሑፍ ግልባጭ እና ከለር ወይም እርሳስ ለእያንዳንዱ ልጅ ይስጡ። ልጆቹ ስሞቻቸውን በሚታደል ጽሑፎቻቸው ላይ እንዲጽፉ ያድርጉ። ትምህርቱ ስለምን እንደሆነ ለማየት ኮከቦቹ ካሉበት ባዶ ቦታዎች ከለር እንዲቀቡት ይንገሯቸው። ሲጨርሱ፣ ቃሉን በአንድ ላይ እንዲሉት ያድርጉ። እርሳሶቹን እና የሚታደሉ ጽሑፎቹን ይሰብስቡ። ክፍለ ጊዜው ሲያልቅ የሚታደል ጽሑፎቹን ለልጆቹ ይመልሱ።




# መንፈስ ቅዱስ እውነቱን እንድናውቅ ይረዳናል

ትምህርት
20

**ዓላማው** የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች እውነት መሆናቸውን ለማወቅ መንፈስ ቅዱስ ሊረዳቸው እንደሚችል ልጆቹ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ሞዛያ 11፣ 12፥17–19ን፣ 13፥1–9ን፣ 18፥1–3ን፣ ሞሮኒ 10፥4–5ን፣ ት እና ቃ 130፥22ን በፀሎት ያጥኑ።
2. "መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቱን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 105)፤ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
3. እንደሚመለከተው አሥር ትንንሽ ካርዶችን ያዘጋጁ። ፊደሉን በአንድ በኩል እና ቁጥሩን በተቃራኒው በኩል ይፃፉ። ማንበብ ለማይችሉ ልጆች፣ ከቁጥሮቹ ጋር ለማመሳሰል ነጥቦችን ይጨምሩ።




ከተቻለ፣ ካርዶቹን ቀደም ተከተሉን በማመሳቀል ክፍሉ ሳይጀመር በልጆቹ ወንበር ላይ ከኋላው ይለጥፉት።

4. "አባቴ እንዳለ አውቃለሁ" የሚለውን መዝሙር የመጀመሪያውን ቁጥር ለመዘመር ይተዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 5)።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. ማንበብ ለሚችል ለእያንዳንዱ ልጅ የመፅሐፈ ሞርሞን ግልባጭ።
   ለ. ፊትን መሸፈኛ፣ ከተገኘ።
   ሐ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ፣ እና ማጥፊያ፣ ወይም መጻፊያ ወረቀት።
   መ. ስዕል 3–47፣ አቢናዲ በንጉስ ኖሀ ፊት (62042፣ የወንጌል ኪነጥበብ የስዕል ጥራዝ 308)።
6. ለማንኛውም ለምትጠቀሙባቸው አበልጻጊ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

### አልማ እውነቱን እንዲያውቅ መንፈስ ቅዱስ ረዳው

**የአትኩሮት ተሳትፎ**

ልጆቹ የተደበቁትን ካርዶች እንዲያገኙ ያድርጉ፣ እና መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ስም እንዲሰሩ እርዱአቸው። ትንንሾቹ ልጆች ካርዶቹን በቁጥር ቀደም ተከተል ሊያስቀምጧቸው ይችላሉ፣ ከዚያም ይገለብጧቸው እና ቃላቶቹን ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ማንበብ ይችላሉ። ስሙን እንደ ክፍሉ ይበሉት።

**የእምነት አንቀፅ**

ልጆቹ እንዲደግሙና ቀመው የመጀመሪያውን የእምነት አንቀፅ ከእናንተ ጋር እንዲሉ ያድርጉ።

**ጥቅስ፣ ስዕል እና ታሪክ**

ለልጆቹ ስዕል 3-47፣ አቢናዲን በንጉስ ኖህ ፊት የሚያሳየውን ያሳዩ። የሚከተለውን ታሪክ በራሳችሁ አባባል ስትናገሩ፣ መንፈስ ቅዱስ አልማን እንዴት እንደረዳው እንዲያዳምጡ ልጆቹን ይጠይቋቸው።

ሌሂ እና ቤተሰቡ ኢየሩሳሌምን ከለቀቁ ከብዙ ዓመታት በኋላ፣ ኖህ የሚባል አንድ ኃጢአተኛ ሰው የኔፊዎች ንጉስ እንደ ሆነ ይግለጹ። ንጉስ ኖህ መጥፎ ንጉስ ነበረ እናም የኔፊ ሕዝቦችን ሃጢአተኞች እንዲሆኑ አስተማራቸው።

ጌታ አቢናዲይ የሚባል ነቢይ ለኔፊዎች እንዲሰብክ ላከ። አቢናዲይ ለኔፊዎች እነርሱ እና ንጉሳቸው ሃጢአተኞች እንደሆኑ እና ጌታ ንስኃ እንዲገቡ እንደሚፈልግ ነግሮአቸዋል።

ንጉሱ ኖህ በአቢናዳ ተናደደ እና እንዲያዝ አደረገው። ከዚያም አቢናዳ በኃጢያተኛው ንጉስ ኖሃ እና ካህናቶቹ ፊት ቀረበ። አቢናዲን የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች አስተማራቸው። ሊሰሙት አልፈለጉም፣ ጌታ ግን አቢናዲን ባረከው፣ እና እንዲሰጥ የታዘዘውን መልዕክት እስኪሰጥ ድረስ ማንም ሰው ሊጎዳው አልቻለም። እነዚህ ትምህርቶች እውነት እንደነበሩ አቢናዳይ ነግሯቸዋል። ንጉስ ኖህ እና አብዛኛዎቹ ካህናቶች የአቢናዲን ቃሎች ለማመን ተቃወሙ። ለኃጢአታቸው ንስሐ ሊገቡ አልፈለጉም። ይልቁንስ፣ አቢናዲን ሊገድሉት ፈለጉ።

ከካህናቱ አንዱ፣ አልማ የሚባለው፣ አቢናዲን አመነው። አቢናዲ እውነቱን እየተናገረ እንደነበረ መንፈስ ቅዱስ አልማን እንዲያውቅ አደረገው። አልማ ንጉስ ኖሃ አቢናዲን እንዲሊቀው ለመነው። የአልማ ልመና እንደውም ንጉስ ኖሃን የበለጠ እንዲናደድ አደረገው። አልማ እንዲሰናበት አዘዘ። ከዚያም አገልግጋዮቹ አልማን እንዲገድሉት ላካቸው። አልማ ግን ከንጉስ ኖህ አገልጋዮች አምልጦ ተደበቀ። አልማ ተደብቆ ቆየ እና ለብዙ ቀናት ደህና ሆነ። አቢናዲ እንዲናገር የታዘዘውን ለንጉስ ኖሃ ነግሮ ሲጨርስ፣ ንጉስ ኖህ አቢናዲ እንዲገደል አደረገ።

አልማ ተደብቆ እያለ፣ አቢናዲ ያስተማረውን ትምህርቶች ጻፈ። አልማ እነዚህ ትምህርቶች እውነት እንደነበሩ ያውቃል። ስለ ኃጢአቶቹ ሁሉ ንስኃ ገብቶ ትዕዛዛቶችን መታዘዝ ጀመረ። አልማ ያወቀውን እውነት ለሌሎቹ በማካፈል ታላቅ ወንጌላዊ ሆነ።

- የአቢናዲ ቃላቶች እውነት እንደሆኑ አልማ ያውቀው እንዴት ነበር?

**በቃል የሚጠና ጥቅስ**

ልጆች ሞሮኒ 10፥5 እንዲያወጡ ያድርጉ፣ እና ይህ ጥቅስ መልስ እንደሚሰጣቸው ይግለጹ። ከፍ ያለ ልጅ ለክፍሉ እንዲያነበው ያድርጉ ወይም እራሳችሁ ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ አንብቡ። አቢናዲ እውነቱን መናገሩን አልማ እንዲያውቅ መንፈስ ቅዱስ እንደረዳው ይግለጹ።

“ቁጥሩን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ወይም በትልቅ ቁራጭ ወረቀት ላይ መፃፍ እና ተለቅ ተለቅ ያሉ ልጆችን በቃላቸው እንዲያጠኑት መርዳት ይችላሉ። ለጥቂት ጊዜያት ቁጥሩን በአንድነት ካነበባችሁ በኋላ፣ አንድ ወይም ሁለት ቃላቶችን ያጥፉ ወይም ይሸፍኑ እና ልጆቹ ደግመው በቃላቸው እንዲናገሩት ያድርጉ። እያንዳንዱን ቃላት ደግመው ካሉ በኋላ ጥቅሱ ሙሉ በሙሉ ጠፍቶ እስከሚያልቅ ድረስ ቃላቶቹን ማጥፋታችሁን ይቀጥሉ። (ማንበብ ለማይችሉ ልጆች፣ ቁጥሩን በአንድ ላይ ብዙ ጊዜ ይደጋግሙት። ያቁሙ እና ልጆቹ የሐረጎቹን ቁልፍ እንዲሞሉ ያድርጉ።) ልጆቹ ከፈለጉ ጥቅሱን ለክፍሉ የማለትን ዕድል ስጣቸው።

### መንፈስ ቅዱስ እውነቱን እንድናውቅ ሊረዳን ይችላል

መልካሙን ስንመርጥ መንፈስ ቅዱስ ጥሩ ስሜት እንደሚሰጠን ያሳስቡ። እውነተኛ ትምህርቶችንም ለማወቅ እንዲረዳን ጥሩ ስሜትን ይሰጠናል።

ታሪክ

በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እውነቱን ስላወቀ አንድ ወጣት ወንድ ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፣

ጄፍ ሚሲዮናዊያኖች ቤቱ ሲመጡ እነሱን በማዳመጥ ይደሰታል። ለእርሱ እና ለቤተሰቡ አስደናቂ ታሪኮችን ነግረዋቸዋል። በተለይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሩትን ታሪኮች ወዶታል። እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ወደ ምድር መመለሱን ሚሲዮናዊያኑ ሲነግሩት፣ ሰምቶ ከሚያውቃቸው ነገሮች በጣም ስሜትን የሚቀሰቅስ ዛሳብ ነው ብሎ አሰበ። እርሱ እና ቤተሰቡ ሚሲዮናዊያኖቹ ያስተማሩት እውነት እንደሆነ የሚያውቁት ወደ ሰማያዊ አባት ከፀለዩ እንደሆነ ሚሲዮናዊያኖቹ ነገሯቸው። ሚሲዮናዊያኑ ሞሮኒ 10፡5 “በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሁሉንም ነገሮች እውነት ማወቅ ትችላላችሁ” የሚለውን ጠቀሱ።

ጄፍ ሚሲዮናዊያኖቹ ያመጡት መልዕክት እውነት መሆኑን እንዴት ማወቅ እንደሚችል እርግጠኛ አልነበረም፣ ነገር ግን የጠየቁትን አደረገ። ጄፍ እውነቱን ለማወቅ እንዲረዳው ወደ ሰማዩ አባቱ ሲፀልይ እና የሚሲዮናዊያኖቹን ትምህርት ሲያዳምጥ፣ የጋለ፣ ሞቹ ስሜት በውስጡ ማደግ ጀመረ። ወዲያው ጄፍ ምንም ተጨማሪ ጥርጥር አልነበረውም። ሚሲዮናዊያኑ ያስተማሩት እውነት መሆኑን አረጋገጠ። ጥሩ ስሜትን፣ ምስክርነትን፣ ከመንፈስ ቅዱስ ተቀበለ።

- መንፈስ ቅዱስ ጄፍን እንዲያውቅ የረዳው ምንድን ነው? (ሚሲዮናዊያን ያስተማሩት ነገሮች እውነት እንደነበር ነው።)
- መንፈስ ቅዱስ ከጄፍ ጋር የተገናኘው እንዴት ነበር? (የጋለ፣ ጥሩ ስሜት ወደ ልቡ መጣ።)
- ጄፍ ከመንፈስ ቅዱስ ይህን ስሜት ለማግኘት ያደረገው ምንድን ነው? (የሚሲዮናዊያኑ መልዕክት እውነት መሆኑን ለማወቅ ፀለየ።)

በጀማሪ ትምህርት ወቀት፣ በቤተሰብ የቤት ምሽት ትምህርት፣ ወይም እውነት በሚነገራቸው በማንኛውም ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ሊሰማቸው እንደሚችል ለልጆቹ ይንገሯቸው። ብዙ ሰዎች ይህን ስሜት የሚያገኙት ቅዱሳን መጻሕፍትን ወይም የነቢያትን ቃላት ሲያነቡ ወይም ሲሰሙ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ በጆሮአችን ልንሰማቸው በምንችለው ቃላት ከእኛ ጋር እንደማይገናኝ ያሳስቡ፣ በምትኩ እውነት ስለሆነው ጥሩ ስሜትን ይሰጠናል።

መንፈስ ቅዱስ የመንፈስ አካል ብቻ ስላለው (ት እና ቃ 130፡20 ተመልከት)፣ አንዳንዴ መንፈስ ተብሎ እንደሚጠራ ይግለጹ። ሰዎች የእግዚአብሔር መንፈስ ከእነርሱ ጋር እንዲሆን ሲፀልዩ ሊሰሙ እንደሚችሉ፣ መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር እንዲሆን መጠየቃቸውን ለልጆቹ ይንገሯቸው። የዚህ መኖር ለሰማያዊ አባት ቀርብ መሆናችን እንዲሰማን፣ ትዕዛዛቱን እንድናውቅ እና መልካምን እንድንመርጥ ይረዳናል።

**ማጠቃለያ**

ምስክርነት

ከተቻለ፣ እውነቱን እንዲገነዘቡ ወይም እንዲያውቁ በመንፈስ ቅዱስ የተረዱበትን የግል ልምድ ያካፍሉ። መንፈስ ቅዱስ እውነቱን እና ትክክለኛውን እንዲያውቁ የሚረዳ የአብ፣ የወልድ፣ የመንፈስ ቅዱስ አንዱ አባል እንደሆነ ምስክርነታችሁን ለልጆቹ ያካፍሉ።

መዝሙር

ክፍሉ “አባቴ እንዳለ አውቃለሁ” የሚለውን መዝሙር የመጀመሪያውን ቁጥር እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ ያድርጉ።

አባቴ እንዳለ አውቃለሁ እንደሚወደኝም።
መንፈስ ይህንን ነገረኝ እውነት ነውም አለኝ፣
እውነት ነውም አለኝ።

- መዝሙሩ መንፈስ ቅዱስ ለእያንዳንዳችን ይነግረናል የሚለው ምንድን ነው? (የሰማዩ አባት እንዳለ እና እንደሚወደን።)

ልጆቹ መዝሙሩን እንደገና እንዲዘምሩ ወይም እንዲሉ ያድርጉ።

የሚከለስ ጥቅስ

ልጆቹ ሞሮኒ 10፡5 እንደገና በቃላቸው እንዲሉት ያድርጉ፣ እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲካፈሉት ያበረታቷቸው።

ምንም እንኳ ማንኛውም ሰው እውነትን ሲሰማ መንፈስ ቅዱስ ጥሩ ስሜትን ሊሰጠው ቢችልም፣ አንድ ሰው ልዩ ስጦታ ሊቀበል የሚችለው ጥምቀትን በመከተል በቤተክርስቲያን

አባልነት ሲፀድቅ መሆኑን ይግለጹ። ያ ስጦታ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው፤ ማለትም ያ ሰው በፅድቅ ከኖረ የመንፈስ ቅዱስ ተጽዕኖ ሁልጊዜ ሊሰማው ይችላል። በሌሎቹ ትምህርቶች የበለጠ ስለ መንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደሚማሩ ይንገሯቸው።

መዝሙር

"መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን መዝሙር ወይም ቃላት ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ ወይም ይበሉ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

**የዳበረ ተሳትፎ**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆቻችሁ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በራሱ በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፤ በ "ለአስተማሪው መርጃ" "የክፍል ጊዜ" ይመልከቱ።

1. "ትንሹ ድምፅ" የሚለውን መዝሙር ሁለት የመጨረሻ መስመሮች ይዘምሩ ወይም ይበሉ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፤ ገፅ 106)።

   አድምጡ፤ አድምጡ። (እጅን በጆሮ ላይ መክበብ)
   መንፈስ ቅዱስ ይናገራል። (አመልካች ጣት ከንፈር ላይ ማድረግ)
   አድምጡ፤ አድምጡ። (እጅን በጆሮ ላይ መክበብ)
   ትንሹንም ድምፅ። (እጅን ልብ ላይ ማድረግ)

2. የአቢናዲን ታሪክ በኖህ እና በካህናቱ ፊት ልጆቹ ድራማ እንዲሰሩ ያድርጉ። አቢናዲን የሚወክለው ሕፃን አንዳንዶቹን የሰማያዊ አባት ትዕዛዛትን ይዘረዝራል። አልማ ማመኑን ይቀበላል እናም የአቢናዲን ሕይወት ለማዳን ንጉሱን ይጠይቃል። በዚህ ምክንያትም፤ አልማ ይባረራል። አልማን የሚወክለው ልጅ እንዲደበቅ እና የአቢናዲን ትምህርት የሚጽፍ እንዲያስመስል ያድርጉ።

# በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታችን ታላቅ በረከትን እንቀበላለን

ትምህርት
21

---

**ዓላማው** የቤተክርስቲያን አባል መሆን ውጤቱ ታላቅ በረከት እንደሆነ ልጆቹ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

---

**ዝግጅት**

1. ሞዛያ 18ን እና ሔነስ 1ን በፀሎት ያጥኑ፣ እናም በእነዚህ በሁለቱ ምዕራፎች ያሉትን ታሪኮች ለመናገር ይዘጋጁ።
2. "መንፈስ ቅዱስ" *የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 105) እና "እርዳኝ፣ ወድ አባት" (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 99) የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩት ወይም ቃላቱን እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ፣ የእነዚህ መዝሙሮች ቃላት በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
3. ክፍሉ ከመጀመሩ በፊት፣ የሰበሰባቸውን ዕቃዎች ስዕል 3-13፣ 3-14፣ 3-48፣ እና 3-49ን በማጠቃለል (ከታች 4ኛውን፣ ይመልከቱ)— በጠረጴዛ ላይ ወይም በወለል ላይ ይዘርጓቸው፣ እናም በጨርቅ ይሸፍኗቸው።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. የሚከተሉት የቃላት ስብጥሮች፥

   | |
   |---|
   | የጥምቀት በረከቶች |
   | የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንሆናለን |
   | የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሰማያዊ አባት ይቅር ይለናል |

   ለ. ከተቻለ የሚከተሉትን ዕቃዎች ይሰብሰቡ፥ መጽሐፈ ሞርሞን፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ አንድ ትንሽ የኢየሱስ ክርስቶስ ፎቶግራፍ፣ እና የCTR ቀለበት።
   ሐ. የሰበሰቧአቸውን ዕቃዎች ለመሸፈን የሚበቃ ተለቅ ያለ ልብስ።
   መ. ስዕል 3-48፣ አልማ በሞርሞን ውሃ ውስጥ ሲያጠምቅ (62332፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 309)፣ ስዕል 3-13፣ ወንድ ልጅ ሲጠመቅ (62018)፣ ስዕል 3-14፣ ልጅቷ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሲፀድቅላት (62020)፣ እና ስዕል 3-49፣ ኤነስ ሲፀልይ (62604፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 305)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅቶች ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሠጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ያበረታቷቸው።

## የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት መሆን እንችላላን

**የአትኩሮት ተሳትፎ**

በጠረጴዛው ላይ ካለው ልብስ ስር አንዳንድ ዕቃዎች እንዳሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ልብሱን ለአስር ሴኮንዶች እንደሚያነሱት ይግለጹ። ልጆቹ የሚሉትን ያህል ብዙ ዕቃዎችን ለማስታወስ መሞከር እና ማስተዋል አለባቸው።

ክፍሉ በጠረጴዛ ዙሪያ እንዲሰበሰቡ ያድርጉ። ዕቃዎቹን ለአስር ሴኮንዶች ያህል አይሸፍኗቸው። ከዚያም ዕቃዎቹን እንደገና ይሸፍኗቸው። ልጆቹ ወደ መቀመጫቸው እንዲመለሱ ያድርጉ።

ልጆቹ ጠረጴዛው ላይ ያሉትን ዕቃዎች በሙሉ ለመጥራት ለመሞከር ተራቸውን እንዲወስዱ ይፍቀዱላቸው። ለመሞከር የፈለጉት የመመለስ ዕድሉ ካጋጠማቸው በኋላ፣ ምን ያህል ጥሩ እንደሰሩ ለማየት ልብሱን ያንሱት። እነዚህ እያንዳንዱ ዕቃዎች ስንጠመቅ ከሰማዩ አባት የምንቀበላቸውን በረከቶች ሊያስታውሱን እንደሚችሉ ይግለጹ።

**የቃላት ስብጥር**

አንድ ልጅ "የጥምቀት በረከት" የሚለውን የቃላት ስብጥር በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲለጥፍ ያድርጉ።

**ስዕል እና የቅዱሳ መጽሐፍት ታሪክ**

ስዕል 3-48፣ አልማ በሞርሞን ውሃ ውስጥ ሲያጠምቅ የሚለውን ያሳዩ።

የአልማን ታሪክ ከትምህርት 20 ላይ በአጭሩ ይከልሱ። አልማ ከኃጢያተኛው ንጉስ ኖዛ አሽከሮች ካመለጠ በኋላ፣ በምድረበዳ ውስጥ መደበቁን ለልጆቹ ያስታውሷቸው። እዚያ ሆኖ ነቢዩ አቢናዲ የተናገራቸውን ትምህርቶች ፃፈ።

ከብዙ ቀናት በኋላ፣ አልማ በህዝቦቹ መካከል ሄዶ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በምስጢር ያስተምራቸው ጀመር። ብዙዎቹ አልማን ሰሙት እና አመኑት። እርሱን ያመኑት ሞርሞን ወደሚባል ቦታ ሄዱ። በዚህ ቦታ አልማ ከንጉሱ ፈታሾች ቀን ቀን እራሱን የሚደብቅበት የንፁህ ውሃ ምንጭ እና የተንንሽ ዛፎች ጥሻ ነበር።

ብዙ ሰዎች አልማን ሊሰሙ ተሰበሰቡ። ስለ እምነት እና ንስኃ አስተማራቸው። አልማ መጠመቅ የሚፈልጉትን በሙሉ አጠመቀ፣ እና የኢየሱስ ክርስቶስ እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባላት ሆኑ።

**የቃላት ስብጥር**

አንድ ልጅ "የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላት እንሆናለን" የሚለውን የቃላት ስብጥር እንዲለጥፍ ያድርጉ።

## የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ሊኖረን ይችላል

**የቃላት ስብጥር እና ውይይት**

- ከተጠመቅን በኋላ የምንቀበለው ስጦታ ምንድን ነው? (የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው።)

አንድ ልጅ "የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ" የሚለውን የቃላት ስብጥር ከበፊቱ የቃላት ስብጥር ስር እንዲለጥፍ ያድርጉ።

ከተጠመቅን በኋላ፣ እጆች በላያችን ላይ በመጫን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንደምንቀበል ይግለጹ። ደግሞ ከሰማዩ አባታችን የምናገኘው በጣም ግሩም የሆነ ስጦታ ነው። መልካም የሆነውን ካደረግን፣ መንፈስ ቅዱስ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ይቀይና መልካም ነገሮችን እንድናደርግ ይነግረናል።

**መዝሙር**

"መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ።

**የእምነት አንቀፅ**

አራተኛውን የእምነት አንቀፅ ከልጆቹ ጋር ይከልሱት። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በቀድስና ከኖርን—-በሕይወታችን ሙሉ በረከት እንደሚሆንልን ይግለጹ።

**ታሪክ**

በራሳችሁ አባባል፣ መንፈስ ቅዱስ ቲምን እንዴት እንደረዳው ታሪኩን ይናገሩ፣

ቲም እናቱ ስትጨነቅ ያይ ነበር። አባቱ የደከመው እና ያዘነ ይመስላል። በወንጌላዊነት ከሚያገለግለው፣ ከወንድሙ ዋሊ ደብዳቤ ከደረሳቸው ትንሽ ጊዜ ሆኖታል።

ቲም ሳሎን ቤት ውስጥ ሶፋ ላይ ተቀምጧል። አባት እና እናቱ ወጥቤት ውስጥ ሆነው ሲነጋገሩ ይሰማል።

"ምን ዓይነት ሃይለኛ መቀሰፍት ነው የመሬት መንቀጥቀጥ ሲደርስ፣" እናም ዋሊ ወደሚሰራበት አካባቢ ቅርብ ለቅርብ ነው አለ አባቱ፣ እንዴት እንደሆነ በቅርቡ እንደምንሰማ ተስፋ አለኝ።"

ቲም ቀረብ ብሎ አዳመጠ። "የመሬት መንቀጥቀጥ . . . ዋሊ?" በማለት በራሱ አሰበ። ጉሮሮውን የሚያንቅ ነገር ተሰማው። ወንድሙ ተጎድቷል ወይም ከተፈነቃቀለ ብዙ ድንጋይ ስር ተቀብሯል በማለት ገመተ። በአግዳሚው ላይ ያለውን የዋሊን ፎቶግራፍ ተመለከተ፣ እና እንባ አይኖቹን ሞሉት። በፍጥነት ወደ ክፍሉ ሄዶ በሩን ዘጋ። ቲም ሁሉንም ዓይነት አስከፊ ነገሮች በመገመት ያን ሌሊት በሙሉ እና በሚቀጥለው ቀን ቀኑን በሙሉ ተጨነቀ። ስለ ዋሊ ወላጆቹን ለማነጋገር በሚሞክርበት ጊዜ ሁሉ፣ ጉሮሮውን ያንቀው እና ቃላቶቹን ማውጣት አይችልም ነበር።

የቲም ፍርሃት እየጨመረ ሄደ። ነገሮቹን ከአንድ ሰው መነጋገር እንዳለበት ተሰማው። አባቱ ምድር ቤት ውስጥ እየሰራ መሆኑን ያውቃል፣ ስለዚህ ቲም ወደ ምድር ቤት ሄደ።

ቲም መናገር ያቀደውን ለመጀመር አፉን ከፈተ። ነገር ግን ስለ ዋሊ መናገር ቀላል አልነበረም። እራሱን ደፋ፣ አይኖቹም በእምባ ተሞሉ።

"ስለ ዋሊ ተጨንቀሃል፣ አይደለም፣ ቲም?" በማለት አባቱ ጠየቀው። "ስለ መሬት መንቀጥቀጡ ስንሰማ፣ ተጨንቀን ነበር። እናትህ እና እኔ ለዋሊ ደህንነት ፀለይን። ሁሉም ደህና እንደሆነ እና መጨነቅ እንደሌለብን ከመንፈስ ቅዱስ ማጽናኛን ተቀበልን። አንተም የዚሁ አይነት ማጽናኛ ሊኖርህ ይችላል፣ ቲም።"

"እንዴት?" በማለት ቲም ጠየቀ።

"ወደ ሰማዩ አባት ፀልይ። ስለ ፍርሃትህ ንገረው። ዋሊ ደህና መሆኑን ለማወቅ እንዲረዳህ ጠይቀው። ማጽናኛ እንደምትቀበል እርግጠኛ ነኝ።"

ቲም አባቱ እንዲያደርግ የነገረውን አደረገ። ለዋሊ ደህንነት ፀለየ። ዋሊ ደህና መሆኑን እና በሕይወት መኖሩን ለማወቅ እንዲረዳው የሰማዩ አባቱን ጠየቀ። ቲም ፀሎቱን ሲጨርስ፣ ታላቅ የሰላም እና የመፅናናት ስሜት በላዩ ላይ መጣ። ከዚያ በኋላ ስለ ዋሊ መጨነቅን አቆመ። ሁሉን ነገር ደህና እንደሆነ አወቀ።

በመጨረሻ ዋሊ ደህና መሆኑን ለቤተሰቡ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ መጣ። ቲም ምንም አልተደነቀም ነበር። ዋሊ ደህና መሆኑን አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ቲም በመንፈስ ቅዱስ ተፅናንቶ ነበር።

- መንፈስ ቅዱስ ቲምን የረዳው እንዴት ነበር? (ጸጥ ያለ የመረጋጋት ስሜት ዋሊ ደህና መሆኑን የሚገልጽ።)

የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለቲም እና ለቤተሰቡ ታላቅ በረከት እንደነበረ ለልጆቹ ንገር። ለእኛም ታላቅ በረከት ሊሆን ይችላል።

### ከተጠመቅን በኋላ፣ የሰማዩ አባት ምህረት ያደርግልናል

የቃላት ስብጥር

አንድ ልጅ "የሰማዩ አባት ምህረት ያደርግልናል" የሚለውን የቃላት ስብጥር በጥቁር ሰሌዳው ላይ እንዲለጥፍ ያድርጉ።

ሌላው የጥምቀት ታላቅ በረከት ስህተት እና ጥፋት ስንሰራ ምህረት ሊደረግልን እንደሚችል መሆኑን ይግለጹ። የሰማዩ አባታችን ልጆቹ በሙሉ ስህተትን እንደሚፈጽሙ ያውቃል። ለመጥፎ ስራቸው ንስኃ እንዲገቡ ሁሉንም ሰው አዟል። ንስኃ ከገባን፣ ምህረት እንደሚያደርግልን እና ሌሎች በረከትን እንደሚሰጠን ቃል ገብቶልናል። የንስኃ ክፍል አንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት መኖር መሆኑን ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ሌላው ክፍል ኢየሱስ የበለጠ እንድንኖር እንደሚፈልገው ዓይነት መኖር፣ ይኸውም፣ ትዕዛዛቱን በደንብ ማክበር ነው። ቅዱሳን መጻሐፍትን በማጥናት ስለ ኢየሱስ እና ስለ ትዕዛዛቱ የበለጠ ማወቅ እንችላለን።

ስዕል እና የቅዱሳን መጻሐፍት ታሪክ

ስዕል 3-4፣ ኤነስ ሲፀልይ የሚለውን ያሳዩ

ኤነስ በመጽሐፈ ሞርሞን ስለ እርሱ ማንበብ የምንችለው ነቢይ እንደነበር ይግለጹ። የኤነስ አባት ቅዱሳን መጽሐፍትን እና የሕዝቦቹን ታሪክ የሚያጠቃልሉትን መዝገቦች እንዲጠብቅ ጠየቀው። ይህ ታሪክ የተፃፈው በብረት ሰሌዳዎች ላይ ነበር። የኤነስ አባት በእነዚህ መዝገቦች ላይ እንደያዘው ወንጌልን አስተማረው፣ እናም ኤነስ እንዴት መኖር እንዳለበት ያውቃል። አንድ ቀን ኤነስ ወደ ጫካ ሄደ እና ቀኑን በሙሉ እና ሌሊት ወደ ሰማዩ አባት ፀለየ። ላደረገው ስህተት ምህረት እንዲደረግለት ጠየቀ። ከዚያም አንድ አስደናቂ ነገር ተከሰተ።

የሰማዩ አባት ለኢነስ ምህረት እንዳደረገለት እና ሊባርከው ቃል እንደገባለት ይግለጹ። እንዲህ የሚል ድምጽ ወደ እርሱ መጣ፣ "ኢነስ፣ ለኃጢአትህ ምህረት ተደርጎልሃል፣ እና ተባርከሃል" (ኢነስ 1፥5)። በመዝገቦች ላይ ስላነበበው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ስለነበረው ኢነስ ምህረት ተደረገለት። ኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢያት ክፍያ መስዋዕትነት ስላመነ ምህረት ተደረገለት። የሰማዩ አባትም በተጨማሪ እነዚያ መዝገቦች በደንብ እንደሚጠበቁ እና አንድ ቀን ሌማናይቶች ቃላቱን ሊያነቡ እንደሚችሉ ለኢነስ ቃል ገባለት። መዝገቦቹ ስለ ኢየሱስ እንዲያውቁ፣ ትዕዛዛቱን እንዲጠብቁ፣ እና ስህተት ሲፈጽሙ ምህረትን እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

የተጻፉትን ነገሮች በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ ማንበብ ስለምንችል የሰማዩ አባት ለኢነስ የገባውን ቃል ኪዳኑን መጠበቁን በሰሌዳዎቹ ላይ እንደምናውቅ ይግለጹ።

ኢነስ ንስኃ ሲገባ የተቀበለው በረከት ምንድን ነው? (ማንኛውንም ትክክለኛ መልስ ተቀበል፣ ነገር ግን የሰማዩ አባት ምህረት እንዳደረገለት ያሳስቡ።)

ማንኛውም በእውነት ንስኃ የገባ ሰው ምህረት እንደሚደረግለት በማወቁ ምስጋናውን ይግለጹ። በኢየሱስ ክርስቶስ እምነትን ለማሳደግ እና ትምህርቶቹን ለማወቅ እኛን በመርዳት ቅዱሳን መጻሐፍትን ታላቅ በረከት ሊሆኑ እንደሚችሉ አጥብቀው ያሳስቡ።

መዝሙር — "እርዳኝ፣ ውድ አባት" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን እንዲሉ ይርዷቸው።

**ማጠቃለያ**

በቃላት ስብጥሮቹ ላይ እንደተዘረዘረው በቤተክርስቲያን ውስጥ የአባልነት በረከቶችን ይከልሱ። ከተጠመቅን እና ትዕዛዛቱን ከጠበቅን የሰማዩ አባት ታላቅ በረከትን ሊሰጠን ቃል እንደገባልን ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

በሚቀጥለው ጊዜ ቅዱስ ቁርባንን ሲወስዱ የሰማዩ አባት የሰጣቸውን በረከት እንዲያስቡ ልጆቹን ይጋብዙ። ለቅዱስ ቁርባን ፀሎት ልዩ ትኩረትን እንዲሰጡ እና ሲጠመቁ የሚገቡትን ቃል እንዲያስቡ ያበረታቱዋቸው። የተጠመቁት ከቅርብ ጊዜ በፊት ስለሆነው ጥምቀታቸው ማሰብ ይችላሉ።

ምስክርነት — የሰማዩ አባትን ከታዘዝነው ሁልጊዜ ለእኛ የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ ምስክርነታችሁን ይስጡ። በቤተክርስቲያን አባልነታችሁ ምክንያት በተለይ በመባረካችሁ የተሰማችሁን ልምድ ምናልባት ለልጆቹ ሊያካፍሉ ይችላሉ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆቻችሁ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የአስተማሪ መረጃዎች" በሚለው ውስጥ "ክፍለ ጊዜን" ይመልከቱ።

1. 3ኛ ኔፊ 11፥33 ላይ ያሉት ቃላቶች ያሉበትን ሰሌዳ ያዘጋጁ። በሰሌዳው ልክ ሌላ ቁራጭ ወረቀት ይቁረጡ፣ እና በላዩ ላይ "የጥምቀት በረከት" የሚለውን ይጻፉበት። ይህንን ቁራጭ ወረቀት እንደ መጫወቻ አድርገው በብዙ ቁራጮች ይቁረጡት። ሁሉም ቁራጭ ጥቅሱን እንዲሸፍን እያንዳንዱ ቁራጭ የተፃፈበትን ጥቅስ ሳይነካ በቀላሉ መልቀቅ እንዲችል ጥንቃቄ ያድርጉ።

   "የጥምቀት በረከት" የሚለውን መጫወቻ ለልጆቹ ያሳዩ፣ እና አርዕስቱን እንዲያነቡ ያድርጉ። ስለ ትምህርቱ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንደሚያነቡ ይግለጹ። ጥያቄውን በትክክል የመለሰ ማንኛውም ሰው የተሸፈነውን ቁራጭ መጫወቻ ያነሳል። በመጨረሻም ልጆቹ ከስር ያለውን ጥቀስ ይገልፃሉ። የሚከተሉት አንዳንድ በሃሳብ የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው፣

   በጥምቀት የምንገባቸው አንዳንድ ቃልኪዳኖች ምንድን ናቸው? (ሁልጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ፣ ስሙን በራሳችን ላይ ለመቀበል፣ እና ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ ናቸው።)

- አልማ በሞርሞን ውሃ ውስጥ ያደረገው ምንድን ነው? (መጠመቅ የፈለጉትን ሰዎች አጠመቀ።)
- አልማ እና ተከታዮቹ የየትኛው ቤተክርስቲያን ተከታዮች ናቸው፧ (የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን።)
- የቲም ፀሎት የተመለሰው እንዴት ነበር? (መንፈስ ቅዱስ ዋሊ ደህና መሆኑን እንዲያውቅ ረዳው።)
- ኤነስ የፀለየው ለምንድን ነው? (ለኃጢአቱ ምህረት እንዲደረግለት ስለ ፈለገ።)
- ከወርቃማው ሰሌዳዎች የተተረጎመው መጽሐፍ ምንድን ነበር? (መጽሐፈ ሞርሞን።)
- ለመጠመቅ በእድሜ የምትበቁት መቼ ነው? (ስምንት ዓመት ሲሆነን ነው።)

የመጫወቻዎቹ ቁራጮቹ ከለቀቁ በኋላ፣ ክፍሉ ጥቀሱን ከእናንተ ጋር እንዲያነቡ ያድርጉ። "የእግዚአብሔርን መንግስት መውረስ" ማለት ለዘለዓለም ከሰማዩ አባት ጋር መኖር እንደሆነ ይግለጹ።

2. "ባርኮትህን ቁጠር" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ (መዝሙር፣ ቁጥር 241)።

   ባርኮትህን ቁጠር፣<br>
   ዘርዝር በተራ።<br>
   ባርኮትህን ቁጠር፣<br>
   ተገንዘብ የአምላክን ስራ።<br>
   ባርኮትህን ቁጠር፣<br>
   ዘርዝር በተራ።<br>
   ባርኮትህን ቁጠር፣<br>
   ተገንዘብ የአምላክን ስራ።

3. "የአባልነት ባርኮት" በሚለው ለእያንዳንዱ ልጅ ከለር እና ምልክት ያለበትን ቁራጭ ወረቀት እንዲኖረው ያድርጉ። ከተጠመቁ እና በኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአባልነት ከፀደቁ በኋላ ሊቀበሉ የሚችሉትን በረከት እያንዳንዱ ልጅ እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡ ያድርጉ።

ትምህርት

# 22 የኢየሱስ ክርስቶስ የኃጢአት ክፍያ

**ዓላማው** ሰዎች ንስኃ መግባት የሚችሉት ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያታችን በመዋዠቱ ምክንያት እንደሆነ ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የሉቃስ ወንጌል 22፥39–46ን እና ሞዛያ 27ን በፀሎት ያጥኑት፣ እና የአልማን የንስኃ ታሪክ ለመናገር ዝግጁ ይሁኑ።
2. በትምህርት 10 የተጠቀሙበትን የቃላት ስብጥር ያምጡ (“መፀፀት ሲሰማ፣” “ምህረትን መጠየቅ፣” “ስህተትን ማስተካከል፣” “ስህተትን አለመድገም”)።
3. ከስምንት ዓመት ዕድሜ በታች የሆኑ ልጆች አሁንም ተጠያቂ እንዳልሆኑ እና ለኃጢያታቸው ንስኃ መግባት እንደሌለባቸው ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ሁልጊዜ መልካምን እንዲሰሩ ያበረታቷቸው።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፈ ሞርሞን እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. አንድ ትልቅ ድንጋይ ወይም ሌላ ከባድ ዕቃ እና ማስቀመጫ ከረጢት ከዚያም በተከሻው ላይ መሸከም የሚችል አንድ ልጅ። ድንጋዩን ወይም ዕቃው ላይ “መስረቅ” የሚለውን ምልክት ያድርጉበት።
   ሐ. ተቀርጠው የወጡ ስዕሎች፥ ወጣቱ አልማ (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-3)፣ አራቱ የሞዛያ ወንዶች ልጆች (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-4)፣ እና መልአክ (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-5)።
   መ. ስዕል 3-46፣ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ሲፀልይ (62175፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 227)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም አስፈላጊ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ከሆነ ይከታተሏቸው።

**ሰዎች ለተሳሳቱ ምርጫዎቻቸው ንስኃ መግባት ይችላሉ**

የአትኩሮት ተሳትፎ

የሚከተለውን ታሪክ ለክፍሉ ይንገሯቸው፥

ጆሽ እና እናቱ በግብይት ላይ እንዳሉ፣ ጆሽ ሳይከፍልበት የሆነ ነገር ከመደብሩ ወሰደ። ጆሽ ስህተት እንደሰራ አወቀ። ገና መጠመቁ ነበር እናም መልካምን መምረጥ እንደነበረበት ያውቃል።

ለልጆቹ በከረጢቱ ውስጥ ያለውን ትልቁን ድንጋይ (ወይም ሌላ ከባዱን ዕቃ) ያሳዩአቸው።

ጆሽ ስለሰረቀው ነገር ምን እንደተሰማው ክፍሉን ይጠይቁ። አንድ ልጅ ጆሽን እንዲመስል ያድርጉ። ልጁ ከረጢቱን በተከሻው ላይ እንዲሸከም ያድርጉ። ጆሽ ስለ መስረቁ ጥሩ ስሜት እንዳልተሰማው ይግለጹ። ሙሉ በሙሉ ደስተኛ እንዳይሆን ያገደው በውስጡ እንዳለው ከባድ ጭነት ነበር።

- ጆሽ ደስተኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? (ንስኃ በመግባት።)
- ጆሽ የተሳሳተ ምርጫውን ለማስተካከል ማድረግ የሚችለው ምንድን ነው? (ንስኃ መግባት ነው።)

አራቱን የቃላት ስብጥሮች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ያሳዩ። በቀደመው ትምህርቱ ስለ ንስኃ መማራቸውን እንደተማሩ ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

- ጆሽ ንስኃ ለመግባት ማድረግ የሚችለው ምንድን ነው? (መልሶቹ የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፣ የሰረቀውን መመለስ፣ ለሰረቀው ነገር መክፈል፣ ባለ ሱቁን ይቅርታ መጠየቅ፣እና ስህተቱን ለማረም ለባለ ሱቁ አንድ ነገርን ለመስራት መደራደር።)

ጆሽ እንዴት ንስኃ መግባት እንደሚችል ልጆቹ ከገለፁ በኋላ፣ ከባዱን ድንጋይ ከልጁ ከረጢት ውስጥ ያውጡ። ንስኃ ስንገባ፣ ከከባድ፣ ከሃዘን ስሜቶች እራሳችንን ነፃ እንደምናወጣ እና ደስተኞች እንደምንሆን ይግለጹ።

ንስኃ የመግባት እና ይቅር የመባል ዕድል ግሩም በረከት እንደሆነ ለክፍሉ ይንገሩ።

ስዕል — ስዕል 3-46፣ ኢየሱስ በጌቴሰማኒ ሲፀልይ የሚለውን አሳዩ። ሰዎች ምህረትን እንዲያገኙ ያስቻላቸው አዳኝ መሆኑን ለልጆቹ ይንገሯቸው።

### ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያታችን ቤዛ ሆኗል

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ — ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ ከተንሽ ጊዜ በፊት፣ እርሱ እና ሐዋሪያቱ ጌቴሰማኒ ወደሚባለው የአትክልት ቦታ እንደሄዱ ይግለጹ። ከሐዋሪያቱ ሶስቱ— ጴጥሮስ፣ ያዕቆብ፣ እና ዮሐንስ—ወደ አትክልቱ ቦታ ከእርሱ ጋር ሄዱ። ኢየሱስ ወደ አትክልቱ ቦታ ሄዶ ወደ ሰማዩ አባት ሲፀልይ ትንሽ ራቅ ብለው ጠበቁት። እኛ ንስኃ መግባት እንድንችል እና ለኃጢያታችን ምህረትን እንድናገኝ ኢየሱስ ለእኛ መሰቃየት እንደነበረበት ያውቅ ነበር። በጌቴሰማኒ የአትክልት ቦታ እና በመስቀል ላይ፣ ኢየሱስ ለእኛ ታላቅ ስቃይ ተሰቃየ። ለኃጢያታችን፣ ወይም ለምናደርገው ስህተት ነገሮች ተሰቃየ።

መዋዡት የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉት። መዋዡት ማለት እኛ ንስኃ መግባት እንድንችል እና ምህረትን እንድናገኝ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያታችን የከፈለው ዋጋ መሆኑን ይግለጹ። ይህን ያደረገው ስለሚወደን እና ንስኃ መግባት እና መንጻት እንዲቻለን ማድረግ ስለፈለገ ነው። ለኃጢያታችን እና ለተሳሳተ ምርጫችን ተዋዡ እንላለን። መዋዡት የሚለው ቃል ተማሪዎቹ እንዲሉት ያድርጉ።

የሰማዩ አባትም ይወደናል እናም እያንዳንዳችን ንስኃ እንድንገባ እና ከእርሱ ጋር እንደገና እንድንኖር ይፈልጋል። በኢየሱስ ክርስቶስ መዋዡት ምክንያት፣ ለኃጢያታችን እና ከስምንት ዓመት በኋላ ለምናደርጋቸው የተሳሳቱ ምርጫዎች ምህረትን ልናገኝ እንችላለን።

### ወጣቱ አልማ ንስኃ ገባ

የቅዱስ መጽሐፍ ታሪክ ከተቀራጭ ጋር — በእራስዎ አባባል፣ የአልማን ንስኃ መግባት እና መለወጥ ለክፍሉ ይናገሩ። ስለ እያንዳንዱ ባለታሪክ ሲናገሩ ተቀራጩን አሳዩ።

አልማ የሚባለው የመጽሐፈ ሞርሞን ነቢይ በጣም አመፀኛ እና ብዙ የተሳሳቱ ነገሮችን ሲሰራ የነበረ ወንድ ልጅ እንደ ነበረው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ይህ ነቢይ አልማ በአቢናዲ ታሪክ ውስጥ የምናውቀው ሰው ነው። መንፈስ ቅዱስን በመስማቱም በቤተክርስቲያን ውስጥ ታላቅ መምህር እና መሪ ሆነ። ወንድ ልጁም አልማ ተብሎ ይጠራ ነበር። አብዛኛውን ጊዜ ልጁን አልማ ብለን ስንጠራ ከአባቱ ጋር እንዳይምታታብን ወጣቱ አልማ ብለን እንጠራዋለን።

ከቀዱሳን መጻሐፍ ታሪክ በሞዛያ 27፥8–14 የሚገኙትን የሚከተሉትን ነጥቦች ያቅርቡ፣

1. ወጣቱ አልማ አባቱን አይታዘዝም ነበር። እርሱ እና አራት ጓደኞቹ ህዝቡን ስህተትን በማስተማር ቤተክርስቲያኑን ለማጥፋት በመሞከር ተሰማሩ።
2. ብዙ ሰዎች ወጣቱ አልማን በማመን ትዕዛዛትን መጠበቅን አቆሙ።
3. የወጣቱ አልማ አባት ስለ ልጁ እና ስለ ቤተክርስቲያኑ አባላት ተጨነቀ።
4. አባትየው ልጁ እውነትን እንዲያውቅ ፀለየ።

ውይይት
- የወጣቱ አልማን አባት ፀሎት የሰማዩ አባት የመለሰው እንዴት ነው? (አልማ እና ጓደኞቹ ንስኃ እንዲገቡ እንዲነግራቸው መልአክ ላከ።)

- ከዚያ በኋላ ምን እንደተከሰተ የሚያውቅ ሰው አለን?

ልጆቹ የቻሉትን ያህል ብዙ ታሪክ መናገራቸውን እንዲቀጥሉ ያድርጉ። የሚከተሉትን ነጥቦች ያቅርቡ፣

1. አልማ እና ጓደኞቹ መልአክ ሲያዩ በጣም ፈርተው መሬት ላይ ወደቁ።
2. አልማ የመናገር እና የመንቀሳቀስ ችሎታ አጣ።
3. ጓደኞቹ ወደ አባቱ ቤት ተሸክመው ወሰዱት እና የሆነውን ሁሉ ለአባቱ ነገሩት።
4. ለሁለት ቀናት የአልማ አባት እና የቤተክርስቲያን ካህናት አልማ እንዲበረታ እና እንዲያናግራቸው ጾመው ፀለዩ።
5. ፀሎታቸው ተመለሰ፣ እና ወጣቱ አልማ ቆመ እና አባቱ በጣም እንዲደሰት እና እንዲያመሰግን ያደረገውን አንድ ነገር ተናገረው።

ወጣቱ አልማ የተናገረውን ለማወቅ፣ የሚከተለውን ከሞዛያ 27፥24፥ "ለኃጢአቴ ንስኃ ገባሁ፣ አለ" የሚለውን ያንብቡ ወይም ተለቅ ያለ ልጅ እንዲያነብ ያድርጉ።

- አልማ እያደረገው ያለው ምንድን ነው?

**የክለሳ ተሳትፎ**

ልጆቹ አንዳንድ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እና ወጣቱ አልማ በእርግጥ ንስኃ መግባቱን እንዴት እንደምናውቅ እንዲወያዩ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው። ሲከልሱት የተለጠፉትን የቃላት ስብጥሮች ያመልክቱ።

- ወጣቱ አልማ ስላደረገው ነገር ፀፀት ተሰምቶት ነበረን?
- ወጣቱ አልማ ምህረት እንዲያደርግለት ለመጠየቅ የፈለገው ማንን ነው? (የሰማይ አባቱን፣ አባቱን፣ አልማ፣ እና ቤተክርስቲያን።)

ስህተቱን ለማረም፣ አልማ ከከተማ ወደ ከተማ በመሄድ ስለ እውነተኛው ቤተክርስቲያን ለሁሉም እንደነገረ ይግለጹ። ወንጌላዊ ሆነ።

- አልማ ትክክለኛ ንስኃ ገብቷል ብላችሁ ታስባላችሁ? (አልማ ንስኃ ከገባ በኋላ ሕይወቱ ሙሉ በሙሉ እንዴት እንደተለወጠ አጥብቀው ያሳስቡ።)
- አልማ ንስኃ ሲገባ ምህረትን ሊያገኝ የቻለው ለምንድን ነው? (በኋላ ለወጣቱ አልማ ኃጢያት በተሰቃየው፣ በኢየሱስ ክርስቶስ መዋዠት ምክንያት ነው።)

**ማጠቃለያ**

በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀር እና መዋዠት ምክንያት፣ ሰዎች የተሳሳተ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜ ንስኃ መግባት እንደሚችሉ፣ እና የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ምህረት እንደሚያደርጉ ለልጆች ይንገሯቸው። ንስኃ ላለመግባት የተሳሳቱ ነገሮችን አለማድረግ የበለጠ ጥሩ እንደሆነ ይግለጹ። ነገር ግን ኃጢያትን ስንሰራ፣ ንስኃ በመግባት ልንነፃ እና ልንፀዳ እንችላለን። በእውነት ንስኃ ከገባን የሰራናቸውን የተሳሳቱ ነገሮች ጭራሽ እንደማያስታውሳቸው ኢየሱስ ቃል ገብቶልናል (ት እና ቃ 58፥42ን ይመልከቱ)።

**የአስተማሪ ምስክርነት**

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መዋዠት እና ስለ ንስኃ አስፈላጊነት ምስክርነታችሁን ይስጡ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ጸሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**የዳበረ ተሳትፎ**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆቻችሁ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ "የአስተማሪ መረጃዎች" "ክፍለ ጊዜን" በሚለው ውስጥ ይመለከቱ።

1. ተለቅ ተለቅ ያሉ ልጆች ሶስተኛውን የእምነት አንቀፅ በቃላቸው እንዲያጠኑ ይርዷቸው። ይህንን የእምነት አንቀጽ ከትንንሾቹ ልጆች ጋር ይከልሱት። ልጆቹ የማይገባቸውን ማንኛውንም ቃላት ወይም ሃሳቦች ለልጆቹ ይግለጹላቸው።

2. ትምህርት እና ቃልኪዳን 19፥16ን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉት፣ እና ከክፍሉ በዕድሜ ትልቅ የሆኑት አባላት በአንድነት እንዲያነቡት ያድርጉ። በዚህ ቁጥር "እግዝአብሃሔር" ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት እንደሆነ ይግለጹ። ት እና ቃ 19፥16 ኢየሱስ ክርስቶስ በእነዚህ ነገሮች ለሁሉም ተሰቃየ እናም ንስኃ ከገቡ አይሰቃዩም። ልጆቹ ቁጥሩን በራሳቸው አባባል እንዲገልፁት ያድርጉ።

   የሰማዩ አባት እንደሚወደን እና ከእርሱ ጋር ዳግም ተመልሰን እንድንኖር እንደሚፈልግ ይግለጹ። ነገር ግን ከእርሱ ጋር ለመኖር ከመቻላችን በፊት፣ ለኃጢያታችን በሙሉ ንስኃ መግባት እና ምህረት ማግኘት አለብን።

   - ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዳችን ስቃይን ለመሰቃየት ፈቃደኛ የሆነው ለምንድን ነበር? (ምክንያቱም ስለሚወደን ነው።)
   - የኢየሱስ ክርስቶስ መሰቃየት እኛን የረዳን እንዴት ነው? (እርሱ ለእኛ ስቃይን ስለተሰቃየ፣ ንስኃ ልንገባ እና ምህረትን ልናገኝ እንችላለን።)

   ማንበብ እና መፃፍ ለሚችሉ ለእያንዳንዱ ልጅ ከታች ያለውን የሚታደል ጽሑፍ ግልባጭ እና እርሳስ ያከፋፍሏቸው። መልዕክቱን ከእነርሱ ጋር ያንብቡት። በባዶ ቦታው ላይ የሚሞሉትን ፊደሎች ማን ማወቅ እንደሚችል ይጠይቁ። የመጀመሪያዎቹ ሶስት ባዶ ቦታዎች ንስኃ ስገባ ለሚሉት ፊደሎች ነው፣ እናም ሁለተኛው አራት ባዶ ቦታዎች መዋዠት ለሚለው ነው። ልጆቹ በባዶ ቦታዎቹን እንዲሞሉት ያድርጉ። ልጆቹ መልዕክቱን ወደ ቤታቸው እንዲወስዱ፣ ለወላጆቻቸው እንዲያነቡት፣ እና በጀማሪ ክፍል የተማሩትን ገለፃ እንዲያደርጉ ይምከሩዋቸው። ከክፍሉ ተማሪዎች ጋር ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ መልዕክቱን በማንበብ ተሳትፎአችሁን ያጠቃሉ።

3. "መልካምን ለማድረግ ድፈር" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃሎቹን ይበሉት (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 158)፣ ቃላቶቹ በዚህ መመሪያ መጽሀፍ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

# ልዩ መልዕክት

---

በኢየሱስ __ __ __ __ ምክንያት እኔ በ __ __ __ __ __ __

ምህረት ላገኝ እችላለሁ።

ትምህርት

# 23

# እርስ በርስ ይቅር መባባል

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ ሌላውን ይቅር የማለትን ትዕዛዝ የመከተል ፍላጎት እንዲኖረው ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ትምህርት እና ቃልኪዳን 64፥9ን በፀሎት ያጥኑ።
2. ተስማሚ በሆነው ተቀርጦ የወጣ የጌታ ሥዕል ጀርባ ላይ *ተናዳጅ* ወይም *ደስተኛ* የሚለውን ቃል ይፃፉ (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-6)።
3. የወጣቱ አልማን ታሪክ ክፍሉ እንዲከልሱት ለመርዳት ዝግጁ ይሁኑ (ሞዛያ 27፤ ትምህርት 22ን ይመልከቱ)።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፧
   ሀ. ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. የወጣቱ አልማ ተቀርጦ የወጣ ስዕል (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-3)፤ አራቱ የሞዛያ ወንድ ልጆች (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-4)፤ እና ተናዳጅ እና ደስተኛ ፊቶች (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-6)።
   ሐ. ሀምራዊ ቀይ (ደማቅ ቀይ) ዕቃ፤ እንደ ልብስ ቁራጭ ወይም ወረቀት ነገር፤ እና ነጭ። ነጩ ዕቃ በተቻለ መጠን ንፁህ መሆኑን ያረጋግጡ።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዙዋቸው ይከታተሏቸው

### ኢየሱስ ክርስቶስን መከተል እንችላለን

የአትኩሮት ተሳትፎ

የሚያደርጉትን ልጆቹ እንዲያደርጉ እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው። ሲቆሙ፣ ሲዘረጉ፣ ፈገግ ሲሉ፣ ሲቀመጡ፣ እና እጅዎን ሲያጣምሩ እንዲከተሉዎ ያድርጉ።

እርሶ ያደረጉትን ነገር በሙሉ ስላደረጉ፣ እየተከተሉዎት እንደነበረ ይግለጹ። አንድ ሰው የሚከተሉ ከሆነ፣ እርሱ የሚያደርጋቸውን ነገሮች በተመሳሳይ ታደርጋላችሁ።

ኢየሱስ ክርስቶስን ሊከተሉ የሚችሉበትን በጣም አስፈላጊ ነገሮች እንዲማሩ ሊረዷቸው እንደሆነ ይንገሯቸው።

### ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል እናም ምህረት ያደርግልናል

የታሪክ ክለሳ

ስለ ወጣቱ አልማ መለወጥ የሚችሉትን ያህል በአጭሩ እንዲናገሩ ክፍሉን ይጠይቁ። ተቀርጠው የወጡ ስዕሎችን መጠቀም ይፈልጉ ይሆናል።

የሚከተለውን እንዲያቀርቡ ይርዷቸው፧

1. በመጀመሪያ አልማ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ እንደነበረ አላመነም ነበር። ብዙ መጥፎ ነገሮችን በማድረግ ከሰዎች ጋር ተነጋገረ። ትዕዛዛት እና የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን እውነት አይደሉም በማለት አስተማረ።
   - የአልማ አባት እና የቤተክርስቲያኑ አባላት የተሰማቸው እንዴት ነው ብለህ ታስባለህ?

2. ምንም እንኳን አልማ በጣም ኃጢያተኛ እና የተሳሳቱ ነገሮችን ቢያደርግም፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ይወደው ነበር።

   - ኢየሱስ ክርስቶስ ለወጣቱ አልማ ፍቅሩን ያሳየው እንዴት ነበር? (ንስኃ እንዲገባ አዘዘው፣ ሞዛያ 27፥11–16ን ይመልከቱ። እንዲሁም ኢየሱስ ለሁሉም ኃጢአት በመዋዠት ፍቅሩን አሳይቷል። ይህም ለአልማ ንስኃ እንዲገባ እና ምህረትን እንዲያገኝ አስቻለው።)
   - የአልማ አባት እና የቤተክርስቲያኑ ሰዎች ለአልማ ፍቅራቸውን ያሳዩት እንዴት ነበር? (እንዲድን ጾሙ እና ፀለዩ፣ ሞዛያ 27፥21–24 ይመልከቱ።)

3. ወጣቱ አልማ ላደረገው ነገር በመፀፀት ንስኃ ገባ።

   - ወጣቱ አልማ ንስኃ ከገባ በኃላ ኢየሱስ ክርስቶስ ያደረገው ምንድን ነው? (ለአልማ ምህረት አደረገለት፣ ሞዛያ 27፥28 ይመልከቱ)።
   - ወጣቱ አልማ ንስኃ ከገባ በኋላ ያደረገው ምንድን ነው? (በምድሩ ሁሉ በመገንዘብ የገጠመውን ለሕዝቡ ተናገረ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ስለ ቤተክርስቲያኑ እውነትነት አስተማራቸው፣ ሞዛያ 27፥32ን ይመልከቱ።)

ኢየሱስ ክርስቶስ ወጣቱ አልማን እንደወደደው እና ምህረት እንዳደረገለት፣ እኛንም ሁልጊዜ ይወደናል እናም ለምንሰራው ስህተት ንስኃ ስንገባ ምህረት ያደርግልናል።

**ሌሎችን ይቀር ማለት አለብን**

ውይይት

- አንድ ሰው ወደታች ሲረግጣችሁ ወይም ሲጎዳችሁ ምንድን ነው የሚሰማችሁ?
- አንድ ሰው ሲያሾፉባችሁ እና በማላገጥ ስሞች ሲጠራችሁ ምን ይሰማችኋል?
- ሌሎች ልጆች ከእነርሱ ጋር እንድትጫወቱ ሳይፈቅዱላችሁ ሲቀሩ ምን ይሰማችኋል?
- አንድ ሰው የእናንተ የሆነውን ነገር ቢሰብርባችሁ ምን ይሰማችኋል?

ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስን ይፍቀዱ። አንድ ሰው ጭካኔን ሲፈፅምብን ወይም ሲጎዳን፣ በአብዛኛው እንደምንናደድ ወይም ውስጣችንን እንደሚጎዳ ይግለጹ።

ተቆርጦ የወጣውን የተናደደ ፊት ስዕል ይለጥፉ። (ተለቀ ያሉ ክፍሎች ቃሉን በክብ ጎን መጠቀም ይችላሉ።)

ሲናደዱ እንዴት እንደሚሰማቸው ከልጆቹ ጋር ይወያዩ። በአንድ ሰው ሲናደዱ እንዴት ደስተኞች እንደማይሆኑ ለማሳሰብ ይሞክሩ።

- ይህ የመናደድ ስሜት ምን ማድረግ እንድትፈልጉ ነው የሚያደርጋችሁ? (ንዴት የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን ማድረግ እንድንፈልግ እንደማያደርገን ለማሳሰብ ይሞክሩ።)

  ልክ ኢየሱስ ይቀር እንደሚለን እኛም ሌሎቹን ይቀር ማለት እንዳለብን እንደነገረን ይግለጹ። ስንጎዳ ሌሎቹን ይቀር ማለት ሁልጊዜ ቀላል እንዳልሆነ ያውቃል፣ ነገር ግን የእርሱን ምሳሌ እንድንከተል ይፈልጋል።

- ይቀር ማለት ምን ማለት ነው? (አዳኝ ምህረት ሲያደርግልን፣ ንስኃ ከገባን ላደረግነው ኃጢአት የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ቀጣት ይሰርዛል። የበለጠ በቀድስና እንድንኖር ይረዳናል። ሌሎችን ይቀር ስንል፣ እንወዳቸዋለን እናም ባደረጉብን በማንኛውም በደል ምክንያት መጥፎ ስሜት ለእነርሱ አይኖረንም።)

  በሐምራዊ ቀይ፣ ወይም በደማቅ ቀይ የተቀለመውን ዕቃ ለልጆቹ ያሳዩአቸው። ከዚያም የሚከተለውን ከትንቢተ ኢሳያስ 1፥18 ላይ ያንብቡላቸው፡ “ኃጢያታችሁ እንደ አለላ ብትሆን፣ እንደ አመዳይ ትነፃለች።”

- ይህ ቁጥር ምን ማለቱ ይመስላችኋል? (ነጭ ሁልግዜ ንፅህናን ለማመልከት የሚጠቀም ቀለም መሆኑን ልጆቹን ያስታውሱ።)

ቀዩን ዕቃ በነጩ ይተኩት። አንተ ልክ ቀዩን ዕቃ የንፅሕና ምልክት በሆነው በነጩ እንደተካኸው፣ አዳኝም ንስኃ የገባውን ሰው ንፁህ እና የፀዳ እንደሚያደርገው ይግለጹ።

ከፍ ያለ ልጅ የሚከተለውን ከትምህርት እና ቃልኪዳን 64፥9 ላይ እንዲያነብ ያድርጉ፣ ወይም እራስዎ ያንብቡት፦ "እኔም እላችኋለሁ፣ እርስ በእርሳችሁ ይቀር መባባል አለባችሁ።"

- ሌሎች ሲጎዱን ወይም በአንዳንድ መንገድ ሲከፉብን፣ ይቀር በማለት የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ ለመከተል ምን ማድረግ አለብን? (ይቀር ማለት እና እነርሱን መውደድ አለብን።)

ሰው ወዳድ እና ይቀር ባይ መሆን—እንዳለብን ይግለጹ።

1. የንዴት ስሜትን እና በሌላ ሰው ላይ የመበቀል ፍላጎትን ማስወገድ አለብን።

2. ክፋትን መርሳት።

3. ሰውየውን በደግነት እና በፍቅር መንከባከብ።

በእውነት ሌሎችን ይቀር ስንል፣ የፈፀሙትን በደል ለመርሳት እና የንዴት ስሜታችንን በደግነት፣ በሰው ወዳድ ስሜት ለመተካት ፈቃደኞች እንደምንሆን ይቀጥሉ። ሌሎች ሰዎችን ይቀር ማለት ይቀር ከተባባሉ በኋላ ለእነርሱ ታላቅ ፍቅርን ማሳየትን ያጠቃልላል።

የተናደደውን ፊት በደስተኛው ፊት ይሸፍኑት (ወይም ቃሉን በከቡ ጎን ይጠቀሙ)።

ታሪክ እና ውይይት

ዮሐንስ ስለሚባለው ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ለልጆቹ ይንገሯቸው። እነርሱ በዮሐንስ ቦታ ቢሆኑ ምን እንደሚሰማቸው እና ምን ማድረግ እንደሚችሉ ለመገመት እንዲሞክሩ ይጠይቋቸው።

"ዮሐንስ እንደ ሌሎቹ ልጆች ትልቅ አልነበረም። አጭር ስለነበረ አንዳንዶቹ ልጆች ያሾፉበት ነበር። ጳውሎስ የሚባል አንድ ትልቅ ልጅ ሁልጊዜ እያሾፈበት ይገፈትረው ነበር።"

- ዮሐንስ የተሰማውን እንዴት ታስባላችሁ? (ሃዘን እና ንዴት)

"አንድ ቀን ዮሐንስ በተራራማ አካባቢ ይንሸራሸር ነበር፣ ያልተለመዱ ድንጋዮችን በመፈለግ። ድንጋይ እየሰበሰበ [እያስተካከለ] ነበር—ዮሐንስ ጥቂት ቀንጆ ድንጋዮች እቤቱ ነበረው። የበለጠ ነበር የሚፈልገው. . . .

"በድንገት የሚያውቀውን ድምጽ ሰማ። ጳውሎስ ነበር። እርሱም ድንጋይ ነበር የሚፈልገው። ጳውሎስ መጀመሪያ እዚያ ስለነበረ ዮሐንስን እዚያ እንዲሄድ ነገረው። ዮሐንስን በተራራማው አካባቢ ወደታች ያባርረው ጀመር . . . ወዲያውኑ ዮሐንስ በጣም የሚጮህ ድምጽ ከላይ ከዳገቱ ተሰማው። ወደ ኋላ ሮጦ ሲመለስ ጳውሎስን በአሰቃቂ ስቃይ ውስጥ አገኘው።" እግሩ በጣም ተጎድቶ ነበር።

- ጳውሎስ ሲያባርረው እና እንዲሄድ ሲነግረው ዮሐንስ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?
- የጳውሎስ እግር ተጎድቶ ሲያይ ዮሐንስን ምን የተሰማው ይመስላችኋል?

ልጆቹ የቀረውን ታሪክ እንዲያዳምጡ እና ዮሐንስ ያደረገውን እንዲያውቁ ያድርጉ፦

"ዮሐንስ ጳውሎስን ለመርዳት ሞከረ . . . ነገር ግን ጠንካራ አልነበረም. . . . የተቻለውን ያህል ጳውሎስን ምቾት እንዲሰማው አደረገ እና እርዳታ ለማግኘት ሮጠ።

"ዮሐንስ አባቱን ይዞ መጣ እና በአንድነት ጳውሎስን—ከተራራው ላይ ወደ ታች [ሊያመጣው] ቻሉ። ወደ ቤታቸው ወሰዱት። የዮሐንስ እናት የጳውሎስን እግር በማሰር ረዱት። የጳውሎስ ድንጋዮች ሲወድቁ ስለጠፉበት ዮሐንስ ያከማቸውን ድንጋይ ከጳውሎስ ጋር ለመካፈል ተስማማ።

"ጳውሎስ ስላደረጋቸው አስከፊ ነገሮች ዮሐንስን ይቀርታ ጠየቀው። ዮሐንስም ፈገግ አለ፣ እና [ጥሩ] ጓደኞች ሆኑ" (adapted from *Walk in His Ways: Basic Children's Manual, Part A* [1979], pp. 151–52).

- ዮሐንስ የይቀርታን ትዕዛዝ የተከተለው እንዴት ነው? (ይቀር ባይ ነበረ እናም ለእርሱ ክፉ የነበረውን ሰው በደንብ ይንከባከብ ነበር።)

- ይቀርታ ማድረጉን ለማሳየት ዮሐንስ ያደረገው ምንድን ነው? (ጳውሎስን ለመርዳት ሞከረ። አባቱ እንዲመጣ እና ጳውሎስን እንዲረዳው አመጣው። የጳውሎስ ጓደኛ ሆነ።)
- "ጳውሎስ በእርሱ ያደረገውን አስከፊ ነገሮች መርሳት እና ጳውሎስን መርዳት ለዮሐንስ ቀላል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁን?

ምንም እንኳ ጳውሎስ ያደረገውን አስከፊ ነገሮች መርሳት ለዮሐንስ በጣም አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ ተከተለ እና ይቀር ባይ ሆነ።

ድራማ

ልጆቹ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱን ወይም ከዚያ በላይ በሆነው ድራማ እንዲሰሩበት ያድርጉ። በክፍልዎ ውስጥ ያሉት ልጆች በሙሉ እንዲሳተፉ ይፍቀዱላቸው። በሁኔታው ሊኖራቸው የሚችለውን ስሜት እንዲገልጹ ያድርጉ እና ይቀር ባይ የመሆንን ትዕዛዝ ለመከተል ማድረግ የነበረባቸው ምን እንደሆነ እንዲገልፁ ያድርጉ። የንዴትን ስሜቶች በፍቅር እና በደግነት ስሜቶች መተካት እንዳለባቸው እንዲያውቁት ልጆቹን ለመርዳት ይሞክሩ እና ክፋትን ይርሱ፣ እና ሰዎችን በደግነት ይያዙ። ከእያንዳንዱ ሁኔታ በኋላ ጥያቄዎችን እንደ መመሪያ ይጠቀሙባቸው።

1. ጁሊ እና ታሚ ኳስ እየተጫወቱ ነው። ሱዛን እየሮጠች መጥታ ጁሊን መታች እና ጣለቻት። ስትወድቅ ጉልበቷ ተጎዳ፣ በኋላ በዚያኑ ቀን፣ ሱዛን እነ ጁሊ ቤት መጥታ ከጁሊ እና ከታሚ ጋር ኳስ መጫወት እንደምትችል ጠየቀች።
   - ሱዛን መታት ስትጥላት ጁሊ የተሰማት ምንድን ነው?
   - ሱዛን መጥታ ኳስ ለመጫወት ስትጠይቅ ጁሊ ሱዛንን ይቀር ማለቷን ለማሳየት ማድረግ ያለባት ምንድን ነው? ይቀርታ ባይጠይቁንም ወይም ደግሞ ላደረጉት ጥፋት እንኳን ፀፀት ባይሰማቸውም እኛ ሁሉንም ይቀር ማለት እንዳለብን በልጆቹ ጭንቅላት እንዲቀረጽ ያድርጉ።)
2. አንዲ እና ዳዊት ጨዋታ እየተጫወቱ ነው። ጨዋታውን እያሸነፈ ያለው አንዲ ነው። ዳዊት ተናደደ፣ መጫወቻውን በፍጥነት ከእርሱ ገፋበት፣ እና ሮጠ። በሚቀጥለው ቀን ዳዊት ጨዋታውን እንደገና ለመጫወት አንዲን ጠየቀው።
   - ዳዊት መጫወቻውን ሲገፋበት አንዲ የተሰማው ምን ይመስላችኋል?
   - ዳዊት ጨዋታውን እንደገና መጫወት ሲፈልግ አንዲ ማድረግ ያለበት ምንድን ነው? (እንደገና፣ "ይቀርታ" ቢሉንም ባይሉንም እኛ ሁሉንም ይቀር ማለት እንዳለብን ደጋግመው ያሳስቡ።)
3. አሊሲያ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት በመምጣት ላይ እያለች፣ የአክስቷን ልጅ ማትን፣ ለመጠየቅ ጎራ አለች። በእጇ ለእናቷ ስጦታ ይዛ ነበር። ማት ከእጇ ነጠቀው። ጣለው እና ሰበረው። የዚያኑ ምሽት ማታ ወደ አሊሲያ መጥቶ በጣም እንዳዘነ ነገራት።

- አሊሳን የሚሰማት ምንድን ነው?
- ማት ሲመጣ ማድረግ ያለባት ምንድን ነው?

**ማጠቃለያ**

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

አንድን ሰው ስንከተል፣ ያ ሰው የሚያደርጋቸውን ተመሳሳይ ነገሮች እንደምናደርግ ልጆቹን በማስታወስ ይደምድሙ። ኢየሱስ ክርስቶስን የምንከተል ከሆነ፣ ሌሎችን ይቀር ለማለት ትዕዛዙን መከተል አለብን። ተገቢ ከሆነ፣ አንድን ሰው ይቀር ያሉበትን እና ያንን በማድረግዎ ጥሩ የተሰማዎን ልምድ ለልጆቹ ማካፈል ይችላሉ። (ልጆቹ ምናልባት በግል የሚያውቋቸውን ሰዎች ስም አይጠቀሙ።) ልጆቹ ይቀር ለማለት የግድ ማድረግ ያለባቸውን እንዲከልሱ ያድርጉ።

1. የመናደድ ስሜትን እና ሌላ ሰውን የማስከፋት ፍላጎትን ማስወገድ አለብን።
2. ክፋትን መርሳት አለብን።
3. ሰዎችን በደግነት እና በፍቅር መንከባከብ አለብን።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ ሌሎችን ይቀር ማለት እንዲያስታውሱ እና በሚቀጥለው ሳምንት አንድን ሰው ይቀር ሲሉ ምን እንደተሰማቸው ለክፍሉ እንዲነግሩ ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ “የአስተማሪ መረጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍለ ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ወጣት ልጆች እንደ ሒፐፓተመስ የመሰለ፣ በጣም ረጅም ቃል ለማለት እንዲሞክሩ ያድርጉ፣። አንዳንድ ቃላቶችን መናገር አስቸጋሪ እንደሆነ ይንገሯቸው። አንድ ሰው ንዴት እና ሃዘን እንዲሰማን ሲያደርግ “እኔ ይቀር ብዬሀለሁ” ማለት ሊከብድ እንደሚችል ይግለጹ። አንዳንድ ጊዜ እነዚያ ሶስት ቃላቶች የሃዘንን ስሜታችን ወደ ደስታ ሊለውጡት እንደሚችሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

2. “እርዳኝ፣ ውድ አባት” የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃላቱን ይበሉ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 99)፣ ቃሎቹ በዚህ መምሪያ መጽሐፍ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

3. የሚከተለውን የጣት ጨዋታ ከልጆች ጋር ይጫወቱ። (አሻንጉሊት ለመስራት እጅዎ ላይ ካልሲ ማድረግ ይችላሉ እናም በካልሲዎቹ ላይ ትንንሽ አይኖችን አያይዙ።)

   ሁለት ትንንሽ ጓደኞሞች፣ አንዱ በግራ አንዱ በቀኝ (ሁለቱንም እጆች ለቡጢ ጨብጣችሁ ወደ ላይ ያዙ)
   ፀብ እና መጣላት ጀመሩ። (እርስ በእርሳችሁ ቡጢውን አንቀሳቅሱ)
   አሁን እነዚህ ትንንሽ ጓደኞሞች የዚያን ቀን ደስተኞች አልነበሩም፣
   ትክክለኛ የመጫወቻ መንገድን ስለተማሩ።
   ከዚያም አንደኛው ትንሹ ጓደኛ በእፍረት እራሱን አቀረቀረ፣ (የቀኙ በቡጢ የጨበጠውን እጅ በማዘቀዘቅ ዞር ይላል)
   ሌላኛውም እንደዚያው ያደርጋል፣ እሱም እንደዛው ስለተሰማው። (የግራውም በቡጢ የጨበጠውን እጅ በማዘቀዘቅ ዞር ይላል)
   የመጀመሪያው ጓደኛ እንዲህ አለ፣ “ምን እንደማደርግ አውቃለሁ (እጆቹን ያጨበጭባል)
   እንዳዘንኩ ለማሳየት ይቅርታን እጠይቃለሁ።”
   “እኔም በእውነቱ አዝኛለሁ፣” ይላል የሚቀጥለው
   “ቀሪውን ቀን እንጫወት እና እንደሰት።” (እጆቻቸውን አጣጥፈው ቁጭ ይላሉ)

4. የተሳሳተ ድርጊቶችን እና ምርጫዎችን ለማመልከት በቁራጭ ወረቀት ላይ ደማቅ የእርሳስ ምልክት ያድርጉበት (ወይም በጥቁር ሰሌዳው ላይ የጠመኔ ምልክት ያድርጉ)። ከዚያም ምንም ምልክት እንዳይቀር ሙሉ በሙሉ ያጥፉት። ንስኃ ስንገባ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአታችንን እንደሚያጠፋው ዓይነት እንደሆነ እና ምንም ምልክት እንደማይቀር ይግለጹ። (ይህንን ከክፍሉ ፊት መለማመድ ይፈልጉ ይሆናል።)

# ጌታ ወንጌላዊያኖችን ይረዳቸዋል

ትምህርት

# 24

**ዓላማው**

ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌላዊያኖችን ስለ እርሱ ቤተክርስቲያን ለሌሎች እንዲያስተምሩ እንደሚረዳቸው እያንዳንዱ ልጅ እንዲያውቅ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. አልማ 17–19 በፀሎት ያጥኑ።
2. በአሁኑ ጊዜ በማገልገል ላይ የሚገኝ አንድ ሚሲዮናዊ ከዋርድዎ ይምረጡ፣ ወይም ደብዳቤ ልትልኩለት የምትችሉትን፣ ሌላ የምታውቁትን ወንጌላዊ ይምረጡ። ልጆቹ ለእርሱ ወይም ለእርሷ ለመላክ የሚፅፉትን ነገር ወይም የሚስሉትን እንዲያስቡ ለመርዳት ይዘጋጁ።
3. "ሰባተኛውን የእምነት አንቀፅ" ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 126፣ ቃላቶቹ ከትክክለኛው የእምነት አንቀፅ ጋር አንድ ዓይነት ናቸው) እና "እውነቱን ለአለም እናመጣለን" (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 172)።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ ቁራጭ ወረቀት እና እርሳስ ወይም ከለሮች።
   ሐ. የወንጌላዊውን ስም የሚገልጽ ምልክት ያዘጋጁ።
   መ. ስዕል 3–50፣ አሞን የንጉስ ላሞናይን በጎች ሲከላከልለት (62535፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 310)።
5. ለሚጠቀማቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካደፋፈሯቸው ይከታተሏቸው።

**ኢየሱስ ክርስቶስ አሞን ጥሩ ወንጌላዊ እንዲሆን ረዳው**

የአትኩሮት ተሳትፎ

በፈቃደኝነት የሚረዳዎት አንድ ሰው ይጠይቁ። ፈቃደኛው በክፍሉ ከሌሎቹ ልጆች ፊት ለፊት እንዲቆም ያድርጉ።

- [የልጁ ስም] ወንጌላዊ ለመምሰል የሚያስፈልገው ምንድን ነው?

ስሙን የሚገልጸውን ምልክት በልጁ ወይም በልጅቷ ላይ ያድርጉ። እንደዚህ ዓይነት የስም ምልክቶች የሚጠቀሙት የኢየሱስ ክርስቶስን አገልጋዮች ለመለየት እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። *የቄስ* ወይም *የእህት* ማዕረጎች ምን ያህል የተቀደሱ እንደሆኑ ያስታውሷቸው። አጠቃላይ ባለስልጣናትም እንኳን ቄስ በሚለው ስም ነው የሚጠሩት።

ውይይት

ስንቶቻቸው በሙሉ ጊዜ ወንጌላዊነት ያገለገሉ ወንድሞች፣ እህቶች፣ ቅድመ አያቶች፣ ወይም አሁን በማገልገል ላይ ያሉ ሌሎች ዘመዶች እንዳሏቸው ልጆቹን ይጠይቋቸው። ልጆቹ በሚሲዮናዊነት በማገልገል ላይ ስላሉ ወይም ስላገለገሉ ዘመዶቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ። ምናልባት በወንጌላዊነት ስላገለገሉ ወላጆቻቸው መናገር ይፈልጉ ይሆናል። ወላጆቻቸው ወይም ሌሎች ዘመዶቻቸው የት እንዳገለገሉ እና በአገልግሎታቸው ላይ ምን እንደሰሩ ይጠይቋቸው።

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች በሙሉ እንደሚወድ ለልጆቹ ይንገሯቸው። እያንዳንዱ ሰው ስለ እውነተኛ ቤተክርስቲያኑ እንዲያውቅ ይፈልጋል። ወንጌላዊያኖች በሁሉም ቦታ ለሰዎች እውነትን ለማስተማር ፈቃደኛ ሲሆኑ ያስደስተዋል።

**ስዕል እና ታሪክ**

ስዕል 3-50፤ አሞን የንጉስ ላሞናይን በጎች ሲከላከልለት የሚለውን ያሳዩ። በራስዎ አባባል፤ ጥሩ ወንጌላዊ ስለሆነው አሞን ስለሚባለው ወጣት የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ (አልማ 17–19 ይመልከቱ)።

አሞን የኔፋይቶች ልዑል ነበረ። ሞዛያ ከሚባለው የፃድቁ ንጉስ ወንዶች ልጆች አንዱ ነበር። አሞን ንጉስ ከመሆን ይልቅ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ሌመናይቶችን ለማስተማር መረጠ።

አሞን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደደ እና በደንብ ሊያገለግለው ፈለገ። መንፈስ ከእርሱ ጋር እንዲሆን እና እንዲረዳው ፀለየ እና ጾመ።

አሞን ወደ ሌመናይቶች ሲሄድ፤ ጠላት ነው ብለው ስላሰቡ አስረው ወደ ንጉሳቸው ወሰዱት። አሞን ለንጉሱ አገልጋይ እንዲሆን ጠየቀ። ንጉስ ሌሞናይ አሞንን ወደደው እና እንዲኖር ፈቀደለት።

አንድ ቀን አሞን እና ሌሎች ጥቂት አገልጋዮች የንጉሱን በጎች ወደ ውሃ ሲወስዷቸው፤ አንዳንድ የንጉሱ ጠላቶች መጥተው በጎቹን በታተኗቸው። የንጉሱ አገልጋዮች ፈሩ። በጎቹ ከተሰረቁ ወይም ከጠፉ ንጉሱ እንደሚገላቸው ያውቃሉ።

አሞን ይህንን ሲሰማ፤ ለአገልጋዮቹ እንደሚረዳቸው ነገራቸው። በጎቹን እንዲሰበስቡ እና እሱ ዘራፊዎቹን እንደሚቆጣጠር ነገራቸው። መንፈስ እንደሚረዳው ያውቅ ነበር።

ዘራፊዎቹ አሞን ወደ እነርሱ መምጣቱን ባዩ ጊዜ፤ አልፈሩም፤ ምክንያቱም እነርሱ ብዙ ነበሩ እንዲሁም አሞን ብቻውን ነበር። መንፈስ አሞንን እንደሚረዳው ዘራፊዎቹ አላወቁም። አሞን በሚያስደንቃቸው ታላቅ ኃይል እና ጥንካሬ በወንጭፍ ድንጋዮችን ይወርውርባቸው ጀመር። ወዲያው አሞንም ሊመታቸው እንደሚችል አወቁ፤ እነርሱ በድንጋያቸው አሞንን ሊመቱት አልቻሉም። መንፈስ ይጠብቀው ነበር።

ዘራፊዎቹ አሞንን በዱላቸው አጠቁት። አሞን ግን ከጌታ ታላቅ ጥንካሬን በመቀበል እሱን ለመግደል ዱላውን ያነሳውን የእያንዳንዱን እጅ ለመቁረጥ ከጌታ ታላቅ ጥንካሬን አገኘ። ዘራፊዎቹ በጣም በመፍራት አመለጡ። አሞን ጌታ ስለረዳው የንጉሱን በግ ለመከላከል ቻለ።

**ውይይት**

- መንፈስ አሞንን የረዳው እንዴት ነበር? (አሞንን ከዘራፊዎቹ ጠበቀው እንዲሁም እነርሱን ለማሸነፍ የሚፈልገውን ኃይል እና ጥንካሬ ሰጠው።)

ወንጌላዊያኖች በአሁን ጊዜ ሌሎችን ስለ አዳኝ ቤተክርስቲያን ከማስተማራቸው በፊት መጣላት ወይም መዋጋት እንደማያስፈልጋቸው ይጥቀሱ። አሞን የተጣላው የንጉሱን በጎች ለመከላከል ስለሚያስፈልገው ብቻ ነበር።

ንጉስ ላሞናይ አሞን ያደረገውን ሲሰማ አሞንን ለማዳመጥ ፈቃደኛ እንደሆነ ይግለጹ። አሞን ታማኝ አገልጋይ እንደሆነ አወቀ። አሞን እውነቱን እንደሚነግረው ሊያምነው እንደሚችል አወቀ። አሞን ለንጉሱ እና ለሕዝቡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ነገራቸው።

**ጥቅስ**

የአልማ 18፥33ን የመጀመሪያውን አረፍተ ነገር ያንብቡ። አሞን የተናገረውን ከሰማ በኋላ ንጉስ ለሞናይ የተናገራቸው ቃላቶች እነዚህ ናቸው። አሞን የተናገረውን ንጉሱ ሌሞናይ ከሰማ በኋላ፤ አሞን የተናገራቸውን ቃላቶች በሙሉ አምኜአለሁ አለ። አሞን ከጌታ እንደተላከ ለማወቀ መፈለጉን ይግለጹ።

የንጉስ ለሞናይ እምነት በጣም ጠንካራ እንደነበረ እና ከዚያ በኋላ ስህተትን መስራት እንዳልፈለገ ለልጆቹ ይንገሯቸው። በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ አመነ እና ትምህርታቸውን መከተል ፈለገ። ንጉሱ ስለ ወንጌል በማወቁ በጣም ተደሰተ እና አሞን ያስተማረውን በሙሉ ሕዝቦቹን ማስተማር ጀመረ።

ምን እንደተከሰተ እንዲገነዘቡ አልማ 19፥35ን ሲያነቡ ልጆቹ እንዲያዳምጡዎት ያድርጉ። አሞን ጥሩ ወንጌላዊ እንዲሆን ጌታ ስለረዳው፤ ብዙ ሕዝቦች ቃሉን አምነው ተጠመቁ። የተቀደሱ ሰዎች ሆኑ፤እና ቤተክርስቲያንም በመሃከላቸው ተመሰረተ።

**መንፈስ ወንጌላዊያንን አሁን ይረዳቸዋል**

አሞን በጊዜው ለቤተክርስቲያኑ ጥሩ ወንጌላዊ እንደነበረ፣ ዛሬም ብዙ ወንጌላዊያን ስለ እውነተኛው ቤተክርስቲያን በመላው ዓለም ሕዝቦቹን ያስተምራሉ። መንፈስ እንደሚረዳቸው አሞንንም እንደረዳው ይግለጹ።

መዝሙር

ከልጆቹ ጋር፣ "እውነቱን ለዓለም እናመጣለን" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ይበሉ።

እንደ ጥንቱ ኔፊ፣ ተወለድን፣
ጌታን ለሚወዱ መልካም ወላጆች።
ተምረናል፣ እናም አውቃናል፣
ጌታ እንዳዘዘን ማድረግ እንዳለብን።
እንደ ሔልማን ሠራዊቶች ነን።
በልጅነታችን ተማርን።
የጌታ ሚሲዮናዊ እንሆናለን
እውነቱን ለዓለም ለማምጣት፣(ቃላት በጃኒስ ካፕ ፔሪ። © 1983
በጃኒስ ካፕ ፔሪ። በፍቃድ አገልግሎት ላይ ዋለ።)

ታሪክ

መንፈስ አንድን ወንጌላዊ እንዴት እንደረዳው የሚከተለውን ታሪክ ይንገሩ፣

አንድ ወጣት በቦሊቪያ ወንጌላዊነት እንዲያገለግል ተጠራ። ብዙ ሰዎች ወንጌልን መስማት ወደ ማይፈልጉበት ክልል እንዲያገለግል ተላከ። እርሱ እና ጓደኛው ጠንክረው ሰሩ፣ ነገር ግን ብዙ ውጤት አላገኙም። ከዚያም አንድ ቀን ማታ ከባድ ዝናብ ጀመረ። በመንገዱ የሚያልፈው ትንሽ ወንዝ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሞላ። ከተማውን ከዋናው መንገድ ጋር የሚያገናኘው ብቸኛ ድልድይ በጎርፉ ተወስዶ ነበር። ትርምስ ሁሉም ቦታ ነበረ።

ወጣቱ ወንጌላዊ ዕርዳታን የሚፈልጉ ጥቂት ሰዎችን አየ፣ እናም ሊረዳቸው ወደ ውሃው ውስጥ ሲዘል በፍጥነት ለዕርዳታ ወደ ሰማይ አባት ፀለየ። የሰማይ አባት ብዙ ሕይወትን እንዲያድን ረዳው፣ ሌሎች ብዙ የተጎዱትን ረዳ፣ ሌሎች ተርበው የነበሩትንም ረዳ።

በከፍተኛ አገልግሎቱ ምክንያት፣ በፊት እሱን እና ጓደኛውን የማይሰሟቸው ሰዎች አሁን ይሰሟቸው ጀመር። እርሱን መውደድ እና ደግሞ ወደቤቱ መምጣትን ተማሩ። የኢየሱስ ክርስቶስ ምስክርነቱን እና ወንጌል በነቢዩ ዮሴፍ ስሚዝ አማካኝነት መመለሱን ተቀበሉ። በጥቂት ወራት ብቻ፣ ብዙ ሰዎችን ወደ ቤተክርስቲያኑ ለማምጣት ረዳ። (See F. Melvin Hammond, "You Can Make a Difference," *New Era,* March 1991, pp. 44–47.)

- የሰማይ አባት ይህንን ወንጌላዊ የረዳው እንዴት ነበር?

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌላዊ እንደሚወዱ እና ሌሎችን ስለ ቤተክርስቲያኑ እንዲያስተምሩ እንደሚረዷቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ወንጌላዊያን የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን መቀረብ እንዲችሉ እና ሁልጊዜ መንፈስ ከእነርሱ ጋር እንዲሆን ይፀልያሉ አልፎ አልፎም ይጾማሉ።

የእምነት አንቀፅ

የቤተክርስቲያን አባላት፣ እና በተለይ ወንጌላውያን፣ ሁልግዜ የተለየ መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንደሚቀበሉ ይግለጹ። ሰባተኛው የእምነት አንቀጽ ከእነዚህ አንዳንዶቹን ስጦታዎች ይገልፃል።

ክፍሉ ሰባተኛውን የእምነት አንቀፅ ለጥቂት ጊዜ እንዲደጋግሙት ይርዷቸው። ከዚያም የሚከተሉትን ቃላት ያሳስቡ፣

"በልሳን ስጦታዎች፣ . . . [እናም] ልሳንን በመተርጎም እናምናለን።"

ታሪክ

የሚከተለው ታሪክ የልሳን ስጦታን ስለሚቀበል አንድ ወንጌላዊ እንደሆነ ለክፍሉ ይንገሯቸው። ቄስ ኪኩቺ፣ የአሁኑ የበላይ ባለስልጣን፣ ወንጌላዊ በነበሩበት ወቀት፣ ጃፓንኛ እና ትንሽ እንግሊዘኛ እንደሚናገሩ ይግለጹ። የሚከተለውን ይናገሩ፣

"ቤተክርስቲያኑን በመካፈል . . . ቄስ ኪኩቺ—የመንፈሳዊ ልምድ ነው ብለው የሚሰማቸውን ሁኔታ ባጋጠማቸው ቦታ በወንጌል ለማገልገል ጥሪ ተቀበሉ። . . .

“ቄስ ጎርደን ቢ. ሒንክሊ [የበላይ ባለስልጣን] በሆኑበት ጊዜ፣ ሚሲዮኑን ሲጎበኙ፣ እኔ በፍኩኦካ፣ ጃፓን፣ በማገልገል አገልግሎቴን ልጨርስ አጋማሹ ላይ ነበርኩኝ። እርሱ ለምስራቅ በሙሉ ተቆጣጣሪ ነበር። ለሚሲዮናዊያን ስብሰባ አደረግን።

“በዚያን ጊዜ፣ “እንደምን አደራችሁ፣” “ጤና ይስጥልኝ፣” “እንደምን ናችሁ” እና “አመሰግናለሁ” ማለት እችላለሁ ነገር ግን በእንግሊዘኛ መናገር የምችለው ያንን ብቻ ነበረ። በስብሰባው ምን እንደሚካሄድ ተስፋ በመቁረጥ ማወቅ ፈለኩኝ። መንፈስ የሚያነሳሳ ስብሰባ እንደነበረ መናገር እችላለሁ . . . መንፈስ ይሰማኝ ነበር ግን ቃላቶቹን ልረዳቸው አልቻልም ነበር።

“ቄስ ሒንክሊ ምስክርነቱን ሰጠ እና ሌሎቹም ሁሉም ወንጌላዊያኖች የራሳቸውን በተራቸው ሰጡ—ለማወቅ በጣም ሲፀልይ ከነበረው ቄስ ኪኩቺ በስተቀር። በመጨረሻ፣ ቄስ ሒንክሊ ተነስተው ቆሙና፣ ከአንድ ቄስ በስተቀር፣ ሁሉም ምስክርነቱን ሰጥቷል፣ አሉ ከዚያም ቄስ ኪኩቺን እንዲናገር ጋበዙት።

“ምን እንደተናገ ለላውቅም፣ አለ ቄስ ኪኩቺ፣ ጓደኛዬ ገፋኝ እና ቄስ ሒንክሊ ምን እንደተናገሩ ነገረኝ። እዚያ ቆሜ ጥሩ ተሰማኝ ግን ሁልጊዜ ጥርሴን በማፏጨት ለራሴ፣ “እንግሊዝኛን ለማወቅ እና ለመረዳት እፈልጋለሁ ምክንያቱም ቤተክርስቲያኑ በኦሪየንት እንዲያድግ መርዳት እፈልጋለሁ”።

“አንድ ወይም ሁለት አረፍተ ነገሮችን በጃፓንኛ መናገር ጀመርኩ። ከዚያም እንግዳ የሆነ ስሜት በአዕምሮዬ መጣ። ዝምብዬ በእንግሊዘኛ መናገር ጀመርኩኝ። በኋላም ሁሉም ቀንጆ እንግሊዝኛ ነበር አሉ ግን ምን እንዳልኩኝ ላውቀው አልቻልኩም። ጥሩ ምስክርነት እንደሰጠሁ አምናለሁ።

“ምስክርነት ከተሰጠ በኋላ፣ ቄስ ሒንክሊ ወጣቱ ወንጌላዊ እንደሚባረክ ቃል ገቡለት፣ ጽዮንን እዚህ (በኦሪየንት) በዚህ የወይን ተክል ክፍል ለመመስረት እንድረዳ፣ ጌታ ታላቅ ለሆነ ነገር፣ እያዘጋጀኝ እንደሆነ ነገረኝ፣ አለ ቄስ ኪኩቺ” (Gerry Avant, “War’s tragedies lead to gospel,” *Church News,* 29 Oct. 1977, p. 5)።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ቄስ ኪኩቺን በአገልግሎቱ ላይ የረዳው እንዴት ነበር?
- እናንተ ቄስ ኪኩቺን ብትሆኑ እና ይህ አጋጣሚ ቢያጋጥማችሁ ኖሮ ምንድን ነበር የሚሰማችሁ?

መዝሙር

ልጆቹ “ሰባተኛው የእምነት አንቀፅ” የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ ያድርጉ።

**ማጠቃለያ**

የጽሑፍ ተሳትፎ

ለእሱ ወይም ለእሷ ደብዳቤ በመጻፍ አንድ ወንጌላዊን መርዳት እንደሚችሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ስለ መረጡት ወንጌላዊ ለልጆቹ ይንገሯቸው ወይም ከዋርዳችሁ ከሚያገለግሉት ወንጌላዊ መሐከል አንዱን ለመምረጥ ልጆቹ እንዲረዱዋ ያድርጉ። ወንጌላዊያን ደብዳቤዎችን በመቀበል፣ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ሚሲዮናዊያንን እንደሚረዳ በመስማት እንደሚደሰቱ ይግለጹ። ልጆቹ ደብዳቤው ላይ ምን መፃፍ እንደሚፈልጉ እንዲያስቡ ያድርጉ፣ እና ሃሳባቸውን በመጠቀም የቡድን ደብዳቤ ይጻፉ። ወደ ቤት ይዘው የሚሄዱትን ወይም ከደብዳቤው ጋር አያይዘው የሚልኩትን ወንጌላዊ በመሆን የራሳቸውን ስዕል እንዲስሉ ይፈልጉ ይሆናል።

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ወንጌላዊያን ሌሎችን ስለ ወንጌል እንዲያስተምሩ መንፈስ እንደሚረዳቸው ምስክርነትዎን ይስጡ። እርሶ ወይም የሚያውቁት ሰው ወንጌልን ከአንድ ሰው ጋር ለመካፈል መንፈስ የረዳበትን አጋጣሚ ማካፈል ይፈልጉ ይሆናል።

ልጆቹ በሚቀጥለው ሳምንት ለአንድ ሰው ስለ ወንጌል በመንገር ወይም የመጽሐፈ ሞርሞንን ቅጂ በመስጠት ወንጌላዊያን እንዲሆኑ ይጋብዟቸው። (ለዚህ ክፍል የስራ ዕቀድ ከዋርዱ በጀት ሊገኝ ስለሚችለው ወጪ ከጳጳሱ ወይም ከቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ጋር ይነጋገሩ።)

የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ የተጋበዘውን ልጅ ወንጌላዊያን ሌሎችን ስለ እውነተኛው ቤተክርስቲያን እንዲያስተምሩ ስለሚረዳቸው የሰማይ አባትን እንዲያመሰግን ይጠይቁ።

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ “የአስተማሪ መረጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ከአገልግሎት የተመለሰ ወንጌላዊ ክፍልዎን እንዲጎበኝ እና በአገልግሎቱ ላይ ወይም በአገልግሎቷ ላይ የተረዳበትን ወይም የተረዳችበትን ልምድ ለክፍሉ እንዲያካፍል ወይም እንድታካፍል ይጋብዙ። (ግለሰቡ ከዋርዱ ውጪ የሚኖር ከሆነ ይህንን ለጳጳሱ ለመግለጽ አርግጠኛ ይሁኑ።)
2. “ለአገልግሎት እንደሚጠሩኝ ተስፋ አለኝ” የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ይበሉ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 169)፣ እነዚህ ቃላቶች በመምሪያው በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል። ይህን መዝሙር ልጆቹ ከተደሰቱበት በትምህርቱ ውስጥ ብዙ ጊዜ ሊጠቀሙበት ይፈልጉ ይሆናል።
3. ጥሩ ወንጌላዊ ለመሆን አሁን ሊዘጋጁበት ስለሚችሉት መንገዶች ከልጆቹ ጋር ይነጋገሩ። መልካም የሆነውን ሲያደርጉ እና ለሌሎቹ ደግ ሲሆኑ፣ ጥሩ ወንጌላዊያን ለመሆን እየተዘጋጁ መሆናቸውን እንዲያውቁት ይርዷቸው። መልካም የሆነውን ለማድረግ ስንሞክር፣ የሰማይ አባት እንደሚረዳን እና እንደሚባርከን ምስክርነትዎን ይስጡ።
4. “የመጽሐፈ ሞርሞን ታሪኮችን” የመጀመሪያውን እና አምስተኛውን ቁጥሮች (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 118) እንደ መዝሙር ወይም እንደ ድርጊት ግጥም ይጠቀሙ።

   አስተማሪዬ የሚነግረኝ የመጽሐፈ ሞርሞን ታሪክ
   በጥንት ታሪክ ስለ ሌመናይቶች ነው።
   ጥንት አባቶቻቸው መጡ ባህርን ተሻግረው፣
   በቅድስና በመኖራቸው መሬት ተሰጣቸው።

   አሞን ሌመናይቶችን ያገለግል ነበር፣
   የንጉስ ሌሞናይን በግ ለብዙ ጊዜ ሲጠብቀ።
   ዘራፊዎች መጡ፣ ተዋግቶ በጎቹን አዳነ።
   በቅድስና መኖር እንደሚችል አወቀ።

5. ለትንንሽ ልጆች፣ “ኢየሱስ ሁሉንም ልጆች ይወዳል።” የሚለውን ግጥም ያሳዩ በድርጊት ይጠቀሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ስለሚወድ፣ ሁሉም ስለ እርሱ እውነተኛ ቤተክርስቲያን እንዲያውቀ እንደሚፈልግ ይግለጹ።

   ኢየሱስ ሁሉንም ልጆች ይወዳል። (እጆቻችሁን አውጡ)
   ሕፃናቶቹ አሁንም ትንሽ ናቸው። (ከጉልበታችሁ ከፍ የሚል ልጅን ለማመልከት እጃችሁን ተጠቀሙ)
   በእቅፍ ውስጥ ያለው ሕፃን ነው (በእጆቻችሁ እቀፍን ስሩ እና ሕፃንን እሹሩሩ የምትሉ አስመስሉ)
   ትልቅ እና ረዥም የሚሆነው። (እጃችሁን ከራሳችሁ በላይ ከፍ አድርጉ)

ትምህርት

# 25 ወንጌላዊ መሆን እችላለሁ

**ዓላማው** ልጆቹ የወንጌላዊነትን ሥራ አሁን መስራት እንደሚችሉ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ትምህርት እና ቃል ኪዳን 133፡37ን በፀሎት ያጥኑ።
2. ለእያንዳንዱ ልጅ የወንጌላዊ ሴት ልጅ ወይም ወንድ ልጅ ግልባጭ (ግልባጩን ፈልገው አግኙ)
3. "ለአገልግሎት እንደሚጠሩኝ ተስፋ አለኝ" የሚለውን መዝሙር ለክፍሉ ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ (የልጆች መዝሙር መጽሐፍ፣ ገፀ 169)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. ትምህርትርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. ወረቀት፣ መቀስ፣ እና ከለሮች።
   ሐ. ስዕል 3-51፣ የተራራው ላይ ስብከት (62166፣ ኪነጥበብ ስዕል የወንጌል ጥራዝ 212)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ለማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ የተጋበዘውን ልጅ በዓለም ውስጥ ላሉት ወንጌላዊያን በሙሉ ፀሎት እንዲያደርግ ይጠይቁት።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለማስተማር መርዳት እንችላለን**

የአትኩሮት ተሳትፎ — በፈቃደኝነት የሚረዳዎትን አንድ ሰው ጠይቁ። ፈቃደኛው በክፍሉ ውስጥ ላሉት ለእያንዳንዱ ሰው ቁራጭ ወረቀት እንዲያድል እና "ጀምር" በሚባልበት ጊዜ እንዲጀምር ይጠይቁት፣ እያንዳንዱ ልጅ ቁራጩን ወረቀቶችን ከተቀበሉ በኋላ፣ ቁራጮቹን ሰብስቡ። ፈቃደኛው ከረዳቱ ጋር በፍጥነት መስራት መቻሉን ልጆቹን ይጠይቋቸው። ቁራጩን ወረቀቶቹን በማደል የሚረዳ ሌላ ቀጥሎ ፈቃደኛ የሚሆነውን ሰው ይጠይቁ። እያንዳንዱ ፈቃደኛ ቁራጩን ወረቀቶቹን በክፍሉ ላሉት ለግማሹ ማደል አለበት። ፈቃደኞቹ ረዳት ሲኖራቸው ስራቸውን የበለጠ በፍጥነት እንደሚያጠናቅቁ ይጥቀሱ። ቁራጩን ወረቀቶችን እንደገና ሲሰበስቡ ፈቃደኞቹ ወደ መቀመጫቸው እንዲመለሱ ያድርጉ። (ለትንሽ ክፍል፣ ፈቃደኞቹ ለእያንዳንዱ ልጅ ከአንድ በላይ የሆነ ቁራጭ ወረቀት እንዲሰጡ ይፈልጉ ይሆናል።)

ስዕል — ስዕል 3-51፣ የተራራው ላይ ስብከት የሚለውን ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን ለማስተማር እንድንረዳው እንደጠየቀን ይግለጹ። ከበቂ ረዳቶች ጋር፣ ትምህርቱ በምድር ላይ ላሉት ህዝቦች በሙሉ መድረስ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉም ሰው ትምህርቱን እንዲማር ይፈልጋል።

የጥቅስ ውይይት — ትምህርት እና ቃልኪዳን 133፡37ን ያንብቡ። *ወንጌል*፣ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች፣ ለሁሉም ሃገር እና ለሁሉም ሰዎች ወገን እንደሚሰበክ ይግለጹ። ወንጌል ለኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ሌላው ቃል እንደሆነ፣ ወገን፣ የሚዛመዱ ሰዎች ስብስብ እንደሆነ፣ ልሳን፣ የቋንቋ ሌላው ቃል እንደሆነ፣ እና ሕዝብ፣ ከተለየ ሀገር፣ ዘር፣ ወይም መንደር የመጡ ማለት እንደሆነ ይግለጹ።

- ይህ ጥቅስ ምን ይሆናል ነው ያለው? (ወንጌል ለሁሉም ሰው ይሰበካል።)
- ወንጌልን በማስተማር ለመርዳት በሰማይ አባት የተጠሩትን ምን ብለን ነው የምንጠራቸው? (ወንጌላዊያን።)

እያንዳንዱ የቤተክርስቲያን አባል፣ ሽማግሌ ወይም ወጣት ቢሆንም፣ ለሌሎቹ ስለወንጌል በመንገር ወንጌላዊ መሆን ይችላል።

ታሪክ

ወንጌላዊ ስለሆነው ሪያን ተብሎ ስለሚጠራው ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣

ሪያን ትምህርት ቤት በመሄድ ይደሰታል። በተለይ አስተማሪውን፣ ወይዘሪት ጆንሰንን ይወዳታል።

አንድ ቀን ልጆቹ ሲያድጉ ምን መሆን እንደሚፈልጉ ስዕል እንዲስሉ ወይዘሪት ጆንሰን ጠየቀቻቸው። ሪያን ምን እንደሚስል ለመወሰን ችግር አልነበረበትም። አንድ ሱፍ የለበሰ ሰው ቅዱሳን መጽሐፍቱን ተሸክሞ በመንገድ ላይ ሲሄድ ሳለ። ሪያን ሲያድግ ከሁሉም ነገር በላይ ወንጌላዊ መሆን ይፈልጋል፣ ልክ እንደ ታላቅ ወንድሙ።

የሪያን አስተማሪ ስዕሉን ስትመለከት፣ ምን እንደሳለ ሊገባት አልቻለም። ወይዘሪት ጆንሰን የቤተክርስቲያኑ አባል አልነበረችም፣ ስለዚህ በሪያን ስዕል ላይ የነበረው ሰውዬ ምን እንደሚሰራ አላወቀችም። ስዕሉን እንዲገልፅላት ሪያንን ጠየቀችው። ሪያን ሲያድግ ለኋላኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ወንጌላዊ መሆን እንደሚፈልግ ለአስተማሪው ነገራት። የልጁ ታላቅ ፍላጎት ፖሊስ፣ ዶክተር፣ ወይም ሌላ ስራ ከመሆኑ ይልቅ ወንጌላዊ መሆን በመሆኑ ወይዘሪት ጆንሰን በጣም ተደነቀች።

ከትምህርት ቤት በኋላ፣ ወይዘሪት ጆንሰን ሪያን ወንጌላዊ መሆን ለምን እንደፈለገ የበለጠ እንዲነግራት ጠየቀችው። ሪያን ቤተክርስቲያኑን ምን ያህል እንደሚወድ እና ወንድሙ በሌላ ሃገር ሌሎችን እንዴት ስለ ቤተክርስቲያኑ ያስተምር እንደነበር ነገራት። ትምህርቶቹ የኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቶች ስለሆኑ ቤተክርስቲያኑ እውነት መሆኑን እንደሚያውቅ ነገራት።

የዚያን ዕለት ማታ ሪያን ለወላጆቹ ስለ ወይዘሪት ጆንሰን እና ስለ ሳለው ስዕል ነገራቸው። ሚስስ ጆንሰንን እራት መጋበዝ የሚችል እንደሆነ እና ቤተሰቡ ተገናኝቷት ስለ ወንጌል ሊያናግሯት ይችሉ እንደሆን ወላጆቹን ጠየቃቸው።

በሚቀጥለው ቀን፣ ሪያን ወይዘሪት ጆንሰንን እቤቱ እራት ለመጋበዝ ማስታወሻ ወሰዱላት። ግብዣውን ተቀበለች እናም ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ሪያን ቤት ሄደች። ወይዘሪት ጆንሰን ሪያን እና ቤተሰቡን በጣም ስለወደደቻቸው በየጊዜውም ትጎበኛቸዋለች። ስለ ቤተክርስቲያኑ ብዙ ውይይት አደረጉ፣ እናም ከስድስት ወራት በኋላ ወይዘሪት ጆንሰን ተጠመቀች። ሪያን ስለቤተክርስቲያኑ ያለውን ፍቅር ስላካፈላት ሁልጊዜ ታመሰግነዋለች።

**ወንጌላዊያኖች ለመሆን ብዙ መንገዶች አሉ**

ክለሳ

ጥሩ ወንጌላዊያን ለመሆን ብዙ መንገዶች እንዳሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከእነዚህ ዘዴዎች አንዳንዶቹን የሚያውቁ መሆናቸውን ያያሉ። አንዳንድ አረፍተ ነገሮችን በቀርበት እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። አረፍተ ነገሩ ወንጌላዊ ለመሆን ጥሩ ዘዴ ከሆነ፣ ተነስተው መቆም አለባቸው። ወንጌላዊ ለመሆን ጥሩ ዘዴ ካልሆነ፣ መቀመጥ አለባቸው።

- የክፍል ጓደኛህ በትምህርት ቤት ከአንተ ጋር እንዲጫወት ታደርጋለህ።
- ጓደኛህን ወደ ጀማሪ ክፍል ትጋብዛለህ።
- አባል ላልሆነ ጓደኛህ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትነግራለህ።
- ለጎረቤትህ ስነ-ሥርዓት የሌለህ ትሆናለህ።
- ለወንጌላዊነት ተቀማጭ ጥቂት ገንዘብ ትቆጥባለህ።
- በቅዱስ ቁርባን ጊዜ በአክብሮት የተሞላህ ነህ።
- ትምህርት ቤት ውስጥ በፈተና ታታልላለህ።

- ሳትጠይቅ፣ ያንተ ያልሆነውን ነገር ትወስዳለህ።
- ወላጆችህን አትታዘዝም እናም ለጓደኞችህ ስለዚህ ትኩራራለህ።
- ጓደኛህን ለቤተሰብ የቤት ምሽት ቤትህ ትጋብዛለህ።
- ከጎረቤትህ አዲስ ሰውን ከአንተ ጋር እንዲጫወት ትጋብዛለህ።
- በክፍል ጓደኛህ እስከምታለቀስ ድረስ ታሾፍባታለህ።
- ለወንጌላዊያን ትፀልያለህ።

ወንጌላዊ ለመሆን ስለቻሉበት ዘዴ ለክፍሉ መንገር ይፈልጉ ይሆናል። ልጆቹ እነርሱ ወይም የቤተሰብ አባላቶቻቸው ወንጌልን በማካፈል የነበራቸውን ልምዶች እንዲያካፍሉ ይጋብዙ።

**ማጠቃለያ**

የሚታደል ጽሑፍ ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ልጅ የአንድን የወንድ ወንጌላዊ ልጅ ወይም የሴት ወንጌላዊ ልጅ የሚታደል ጽሑፍ ይስጡ፣ እና ልጁ በሚታደል ጽሑፍ ወይም ጽሑፉ ላይ የፊትን ስዕል እንዲስሉ አድርግ። ስማቸውን በስም መፃፊያ ምልክት ላይ እንዲያደርጉ እና "መጽሐፈ ሞርሞን" የሚለውን በመጽሐፉ ላይ እንዲጽፉ ይርዷቸው። ስዕሎቹን ከለር ከቀቡ በኋላ፣ ስዕሎቹን ቀርፈው እንዲያወጧቸው ያድርጉ።

መዝሙር

"ለአገልግሎት እንደሚጠሩኝ ተስፋ አለኝ" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ።

የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ የተጋበዘውን ልጅ ወንጌላዊያን ለመሆን ስላላቸው ዕድል የሰማይ አባትን እንዲያመሰግን ይጠይቁት።

---


**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**


ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ "የአስተማሪው መረጃዎች" "የክፍል ጊዜን" በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።

1. ወንጌል የተቀበሉትን ወደ ክፍል እንዲመጡ እና ስለ ቤተክርስቲያኑ እንዲማር ወይም እንድትማር ስለረዷቸው ሰዎች እንዲናገሩ ይጋብዟቸው። (ግለሰቡ ከዋርዱ ወይም ከቀርንጫፍ ውጪ ከሆነ ከጳጳሱ ወይም ከቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፍቃድ ለማግኘትዎ እርግጠኛ ይሁኑ። ግለሰቡ ከዋርዱ ወይም ከቀርንጫፉ ውስጥ ከሆነ ለጀማሪ ክፍል ፕሬዚዳንት ይናገሩ።)

2. ልጆቹ የሚከተሉትን ሁኔታዎች እንዲወያዩ፣ ከዚያም ድራማ እንዲሰሩበት ያድርጉ፥
   ሀ. የቤተክርስቲያኑ አባላት ያልሆኑት ጓደኞቻችሁ "የእግዚአብሄር ልጅ ነኝ" የሚለውን መዝሙር ስትዘምሩ ይሰሟችሁ እና የምትዘምሩት መዝሙር ምን እንደሆነ ይጠይቋችኋል። ስለ ቤተክርስቲያን እንደሆነ ልትነግሩቸው እና ወደ ጀማሪ ክፍል ለመጋበዝ ይህንን ዕድል መጠቀም የምትችሉት እንዴት ነው?
   ለ. በጎረቤቶቻችሁ አዲስ ልጅ ታያላችሁ። አይናፋር እና እስከአሁን ምንም ዓይነት ጓደኛ ያላበጀ ይሆናል። ጥሩ ወንጌላዊ መሆን የምትችሉት እንዴት ነው?
   ሐ. ወንድምህ እሁድ ጠዋት ይነሳና ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ አይፈልግም። ጥሩ ወንጌላዊ ለመሆን ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

3. የአሞንን ታሪክ ከትምህርት 24 ላይ፣ ስዕል 3-5ን በመጠቀም ደግመው ይናገሩ። አንድ ልጅ ላይ አንድ ኳስ ወይም ለስላሳ ዕቃን ይወርውሩ እና ስለ ታሪኩ ጥያቄ ይጠይቁት። በትክክል ከመለሰ፣ ቀሞ ኳሱን ወደ እርስ መልሶ እንዲወረውረው ያድርጉ። ሁሉም ልጆች እስኪቀሙ ድረስ ኳሱን መወርወር እና ጥያቄዎቹን መጠየቀዎን ይቀጥሉ።





# መንፈስ ቅዱስ ሊረዳን ይችላል

ትምህርት

26

**ዓላማው** መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን እንድናደርግ ሊረዳን እንደሚችል ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው። ከአደጋም ያስጠነቀቀናል።

**ዝግጅት**

1. 1ኛ ኔፊ 4፥1–6ን፣ 2ኛ ኔፊ 32፥5፣ ትምህርት እና ቃልኪዳን 8፥2ን በጸሎት ያጥኑት።
2. በትምህርቱ ውስጥ ላለው ጨዋታ በቁራጭ ወረቀት ላይ ዘጠኝ ጥያቄዎችን ያዘጋጁ። ጥያቄዎቹን በቦርሳ ውስጥ ያስቀምጡ።
3. "መልካሙን መንገድ ምረጥ" (የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ፣ ገፅ 160) እና "መንፈስ ቅዱስ" (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 105) የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ፣ የእነዚህ መዝሙሮች ቃላት በዚህ መምሪያ በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መጽሐፈ ሞርሞን እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. አይንን ለመሸፈን የሚጠቀም መሐረብ ወይም ቁራጭ ጨርቅ።
   ሐ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   መ. ስዕል 3-52፣ ፈረሱን በማቀም ልጁን የሚያድን አባት፣ እና ስዕል 3-53፣ የካሮሊና ፀሎት።
5. ለሚጠቀሚቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ጋብዝ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታታሃቸው ተከታታላቸው።

**መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳናል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

አንድ ልጅ በሚከተለው ተሳትፎ እንዲረዳዎት ይምረጡ፥

አንድ ልጅ በበሩ አጠገብ እንዲቆም ያድርጉ። አይኑን ይሸፍኑት፣ እና ወንበሩን ፈልጎ እንዲቀመጥ ይዘዙት። ምንም እርዳታ አያድርጉለት። (ነገር ግን፣ እራሱን ወይም ሌሎችን እንዳይጎዳ እርግጠኛ ይሁኑ።

ድርጊቱን ይድገሙት፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሌላ ልጅ አይኑ የተሸፈነውን ልጅ አቀጣጫዎችን በማሳየት እንዲረዳው ያድርጉ።

መሸፈኛውን ያንሱለት፣ እና ልጁ እንዲቀመጥ ያድርጉ።

- (የልጁ ስም) በሚቀጥለው ጊዜ ወንበሩን ለማግኘት ቀላል የሆነለት ለምንድን ነው?

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

*እርዳታ* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉ። ቃሉን ለልጆቹ ያንብቡላቸው፣ እና አንድ ሰው እርዳታን ሲቀበል፣ ግለሰቡ ሁልጊዜ መመሪያን እንደሚቀበል ወይም ምን እንደሚያደርግ ወይም ምን እንደሚል እንደሚነገረው ይግለጹ።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ ዕርዳታቸውን እና መመሪያቸውን እንደምንፈልግ እንደሚያውቁ ይግለጹ። የሚያነሳሳን አንድ ሰው እንደሚልኩልን ቃል ገብተውልናል።

ጥቀስ፣ ስዕል፣ እና ታሪክ

ትምህርት እና ቃልኪዳን 8፡2 ለልጆቹ ያንብቡላቸው። ጌታ በላያችን ላይ በሚመጣው እና በልባችን ውስጥ በሚኖረው፣ በመንፈስ ቅዱስ ሃይል፣ በአዕምሮአችን እና በልባችን እነግራችኋለሁ ማለቱን ይግለጹ። ከዚያም ስዕል 3-53፣ የካሮሊና ፀሎት ያመልክቱ እና የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፣

ካሮላና በስዊድን የምትኖር አንዲት ትንሽ ልጅ ነበረች። እርሷ እና ትንሽ ወንድሟ ኤሪክ ሁልጊዜ አብረው ነበሩ። ካሮሊና ትንሽ ወንድሟን ስለምትወደው ትንከባከበዋለች። ኤሪክ አራት ዓመቱ ነበር። ቤታቸው ከውቀያኖሱ የራቀ ስላልነበር ብዙ መርከቦች ወደሚኖሩበት የባሕር ወደብ ይመጣሉ። አንዳንዴ መርከቦቹ የምግብ ጭነቶችን ወይም መኪናዎችን ያጓጉዛሉ። ካሮሊና እና የኤሪክ አባት በእነዚህ መርከቦች ላይ ሰርተዋል።

አንድ ቀን ልጆቹ በኮረብታ ላይ ቆመው በውሃው ላይ በቀስታ የሚጓዘውን ትልቀ መርከብ ይመለከታሉ። ካሮሊና "ኤሪክ፣ ወደ ታች እንውረድ እና መርከቡን የሚያራግፉትን ሰዎች እንመልከተ አለችው። በጣም ትልቀ ነው፣ በላዩ ላይ ያለውን እስቲ እንመልከት። ከመንገዳቸው ወጥተን የሚሰሩትን ሰዎች ብንመለከት አባታችን ምንም አይለንም። ትልቁ ሳጥን ላይ ተቀምጠን፣ ሁሉንም ነገር ማየት እንችላለን።"

ኤሪክ የካሮሊናን እጅ በደስታ ያዘ፣ እና ቁልቁለቱን ሮጡ። ግን ከኮረብታው ስር ሲደርሱ፣ በሀዲዱ መንገድ መስመር ቢሄዱ የበለጠ የሚያስደስት ነው ብለው አሰቡ። ይህ ወደ ውሃው ለመውረድ የበለጠ ያፈጥናል።

በእግር መንገዱ ላይ ሲሄዱ፣ ካሮሊና አንዳንድ ቆንጆ ወፍ ዘራሽ አበባዎችን አየች። ከእነዚያም ትንሽ ለመቀጠፍ እንዲችል የኤሪክን እጅ ለቀቀችው።

በሐዲዱ ማሰሪያ መሐከል በጥንቃቄ እየረገጠ ኤሪክ እየዘለለ ቀድሚት ሄደ። ይህንን ጨዋታ መጫወት ይወዳል። በድንገት፣ ካሮሊና የስቃይ ጩኸት ሰማች። ችግሩ ምን እንደሆነ ለማየት ልክ ስትዞር፣ ኤሪክ "ካሮሊና! ካሮሊና! እግሬ ተይዟል። ልወጣ አልቻልኩም!" በማለት ወደ እህቱ ያለቅስ ነበር።

ካሮሊና አበባዎቿን ጥላ ልትረዳው ሮጠች። በዚህን ጊዜ ኤሪክ በስቃይ እና በፍርሃት ያለቅስ ነበር። ካሮሊና እግሩን ከቀዳዳ ውስጥ ለመንቀል በመሞከር፣ እጁን ጎተተ ጎተተ አደረገችው። ነገር ግን ልታንቀሳቀሰው አልቻለችም። እጆቿን በወገቡ ዙሪያ አደረገች እና ልታወጣው ሞከረች። ትንሹ ወንድሟ እግሩ ስለተጎዳ በስቃይ ጮኸ። ካሮሊና የበለጠ በሳበችው እና በጎተተችው ቁጥር፣ ኤሪክ የበለጠ ያለቅሳል። በመጨረሻም ካሮሊና፣ "ኤሪክ፣ እግርህን ማስለቀቅ አልቻልኩም፣ እግርህን ጎትቼ ለማውጣት አንድ የሚረዳኝ ሰው ሄጄ መፈለግ አለብኝ። እመለሳለሁ" አለችው።

በእግር መንገዱ ላይ ወደታች መሮጥ ጀመረች፣ ነገር ግን ወደ መታጠፊያው ዙሪያ ስትመጣ፣ ከርቀት ባቡር አየች። በጥቂት ደቂቃ ባቡሩ እዚያ ስለሚደርስ፣ ካሮሊና ለዕርዳታ ለመሄድ ሰዓት እንደሌላት አወቀች፣ እና ባቡር ነጂው ፍጥነቱን ለመቀነስ ትንሽ ወንድሟን በጊዜ ማየት አይችልም ይሆናል።

- ካሮሊና ማድረግ የምትችለው ምንድን ነው?

ካሮሊና ዞረች እና ወደ ኤሪክ ተመልሳ ሮጠች። በጣም ፈርታ ነበረ፣ እና እንደገና የኤሪክን እግር ስትጎትት፣ ለእርዳታ ትንሽ ፀሎት አደረገች፣ "የሰማይ አባታችን፣ እርዳኝ። ምን እንደማደርግ አላውቅም። አባክህን እርዳኝ!"

ወዲያውኑ ካሮሊና በጣም ረጋ ያለ ድምፅ "ጫማውን ፍቸለት" ሲል የሰማች መሰላት። በተንቀጠቀጡት እጆች የጫማውን ማሰሪያ ፈታች። ምንም እንኳ ጫማው አሁንም በሐዲዱ ማሰሪያ ስር በጥብቀ ቢያዝም፣ ካሮሊና በኃይል ስትስበው፣ የኤሪክ እግር በትክክል ከውስጡ ወጣ። በአጠገቢ ወደቀ፣ እና ሁለቱም መሬቱ ላይ ወደቁ። ከሀዲድ ላይ ዘለሉ፣ እና ባቡሩ ጭሱን በመጠምዘዣው ዙሪያ እያወጣ በአጠገባቸው አለፈ።

ባቡሩ ከሄደ በኋላ፣ ኤሪክ ማልቀስ ጀመረ፣ "ኦ፣ ጫማዬን አይው!" ጫማው በአስከፊ ሁኔታ ተይዟል፣ ካሮሊና ግን ጠምዝዛ ልታላቀቀው ቻለች። ካሮሊና በእጆቿ ኤሪክን አቀፋ እንዲህ አለችው "ስለጫማህ አትጨነቀ። የሰማይ አባት ፀሎቴን ስለ ሰማኝ ብቻ አመስግን። እርሱ ባይረዳኝ ኖሮ ምን እንደማደርግ በፍፁም አላውቅም ነበር።"

ካሮሊና ትንሽ ወንድሟን አቀፈች፣ ሕይወቱን ለማዳን በመብቃቷ ተደሰተች። ከዚያም፣ እጅ ለእጅ በደንብ ተያይዘው፣ የሰማይ አባት፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል አማካኝነት የካሮሊና ፀሎት ለዕርዳታ እንዴት እንደመለሰላት ለአባታቸው ሊነግሩ ሄዱ።

ውይይት

- ካሮሊናን የረዳት ማነው?
- መንፈስ ቅዱስ ወንድሟን እንድታድን ካሮሊናን የረዳት እንዴት ነበር?

መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች እንደሚረዳ ያስገንዝቡ። አብዛኛውን ጊዜ ለአእምሮአችን ይናገራል። ይህንን ሲያደርግ፣ የምናደርገውን እንድናውቅ ሊረዳን የሚችል ስሜትን ወይም ሃሳብን እናገኛለን። ሆኖም አንዳንዴ፣ ሰዎች የሚናገሩቸውን እና እርዳታን የሚሰጣቸውን ድምፅ በትክክል ይሰማሉ።

መዝሙር

“መንፈስ ቅዱስ” የሚለውን መዝሙር ከልጆች ጋር ዘምር ወይም ቃሎቹን በል።

**መንፈስ ቅዱስ ትክክል የሆነውን እንድናደርግ ይረዳናል**

መንፈስ ቅዱስ ትክክለኛውን ለማድረግ እንዴት እንደረዳቸው ልጆቹ የሚከተሉትን የአኒን እና የጆርጅን ታሪክ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው።

ታሪክ እና ውይይት

በአንድ በጋ መጀመሪያው ላይ፣ ከአኒታ ጓደኞች አንዷ አብረው ወደ ዋና እንዲሄዱ ጋበዘቻት። ከመሄዷ በፊት፣ አኒታ ያለፈው ዓመትን የዋና ልብሷን ሞከረች። ምን ያህል እንዳደገች በማየቷ ተደነቀች። በዚህም ምክንያት፣ የዋና ልብሷ መሆን እንደሚገባው አልሸፈናትም እናም አስነዋሪ ነበር።

አኒታ ጓደኛዋ እንድትመጣ እንደምትጠብቃት ታውቅ ነበር፣ እናም አኒታ በፍጥነት ወደ ቤቷ ሄዳ መጫወት ፈለገች። ነገር ግን፣ ምን እንደምታደርግ እንድትወስን የሚረዳት ሃሳብ በአዕምሮዋ መጣ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ትሁት እንድትሆን እንደሚፈልጉ አስታወሳት። ይህንን የዋና ልብስ አድርጋ ወደ ጓደኛዋ ቤት ሄዳ ቢሆን ኖሮ፣ በጓደኛዋ ቤተሰቦች አካባቢ ጥሩ ስሜት አይሰማትም ነበር። በተለየ ሁኔታ መልበስ እንዳለባት ታውቅ ነበር።

አኒታ በፍጥነት ታላቅ እህቷን አገኘቻት እና የሚሆናት የዋና ልብስ እንዳላት እና መዋስ እንደምትችል ጠየቀቻት። በአንድ ላይ አኒታን በደንብ የሚሆናትን አሮጌ የዋና ልብስ ፈልገው አገኙ። አኒታ እህቷን አመሰገነች፣ ወዲያውኑ ቀየረች፣እና ወደ ጓደኛዋ ቤት ሮጠች፣ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ በመምረጧ ተደሰተች።

- አኒታ ትክክለኛ የሆነውን ነገር እንድታደርግ መንፈስ ቅዱስ የረዳት እንዴት ነው?

ታሪክ እና ውይይት

ጆርጅ እና ጓደኞቹ የእግር ኳስ ጨዋታ ይወዳሉ። በትምህርት ቤት ይጫወቱታል፣ በቴሌቪዥን ይመለከቱታል፣ እንደውም መጽሔቶች በመግዛት ስለሚወዷቸው ቡድኖች ያነባሉ። ጨዋታዎችን መከታተል እና ስለሚያስደስቱ ጨዋታዎች መነጋገር ይወዳሉ።

የአጠቃላይ ውድድር ጨዋታ ቀርቦ ነበር። የሚያስደስት ጨዋታ እንደሚሆን ጆርጅ ያውቅ ነበር፣ እናም ለማየት ፈለገ። ነገር ግን ጨዋታው በቴሌቪዥን የሚተላለፈው እሁድ ልክ በቤተክርሲያኑ ስብሰባ ሰዓት ነበር።

ጓደኞቹ እቤት በመሆን ከአባቶቻቸው ጋር ጨዋታውን ለማየት ወሰኑ። ጆርጅም ከእነርሱ ጋር በመሆን ጨዋታውን እንዲከታተል ተጋብዞ ነበር ነገር ግን የቤተክርስቲያኑን ስብሰባ መቀረት እንደሌለበት ተሰማው።

ከዚያም ቤት መቀረት እና ጨዋታውን መከታተል ትክክል መሆኑን መጠራጠር ጀመረ። “በኋላም፣” “በየሳምንቱ ቤተክርስቲያን መሄድ እችላለሁ፣ ብሎ አሰበ ነገር ግን አጠቃላዩ ውድድር በዓመት አንዴ ብቻ ነው የሚመጣው። በእርግጥ ከቤተክርስቲያን ይሄን ብቻ አንዴ ብቀር ችግር አይፈጥርም፣” ብሎ አሰበ።

የሚለው ሐሳብ በአእምሮው ሲመጣ ቤተክርስቲያን ለመቀረት ሙሉ በሙሉ እራሱን አሳምኖ ነበር፣ “የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደርግ የሚፈልጉት ምንድን ነው?”

ጆርጅ ይህንን ጥያቄ ሲመልስ፣ ምርጫው ምን እንደሚሆን ያውቃል። ቤተክርስቲያን መሔድ አለበት።

- ጆርጅን የሚረዳው ማን ይመስላችኋል?
- መንፈስ ቅዱስ ጆርጅን የረዳው እንዴት ነበር?

መንፈስ ቅዱስ አኒታን ተሑት እንድትሆን እና ጆርጅን ቤተክርስቲያን እንዲሄድ እንዳነሳሳቸው ይግለጹ። ሁለቱም ልጆች ግፊቱን ተከትለው ትዕዛዛቱን አከበሩ። መንፈስ ቅዱስ እንደሚገፋፋን እና ትክክለኛውን በመምረጥ እሱን መከተል እንዳለብን ያስገንዝቡ።

CTR ቀለበት

CTR ቀለበትን ማድረግ ትክክለኛውን መምረጥን ለማስታወስ እንደሚረዳቸው ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

መዝሙር

"ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃላቶቹን ይበሉ።

**የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት ስንታዘዝ እንባረካለን**

ስዕል እና ታሪክ

የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት ስናዳምጥ እና ስናከብር በጣም እንደምንባረክ ይግለጹ።

ስዕል 3-52፣ አንድ አባት ፈረሱን አቁሞ ልጁን ሲያድን የሚለውን ያሳዩ። ብሩስ አር ማኮንኪ እና አባቱ የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት ስላከበሩ የሰማይ አባት እንዴት እንደባረካቸው ይናገሩ፣

"ከቀድሞ የልጅነት ትዝታዎቼ አንዱ በፖም ተክል ውስጥ ፈረስ መጋለብን ነው። ፈረሱ ለማዳ እና ለመጋለብ የሰለጠነ ነበር፣ እንዲሁም በኮርቻው ላይ እንደልቤ ለመሆን ቻልኩ።

"ነገር ግን አንድ ቀን አንድ ነገር ፈረሴን አስደነገጠው፣ እና በተክሉ ውስጥ ሸመጠጠ። በተንጠለጠለ ቀርንጫፎች ከኮርቻው ወደቀኩኝ፣ እናም አንድ እግሬ ከእርካቡ ሾልኮ ወጣ።"

በስዕሉ ውስጥ እርካቡን ያመልክቱ።

"ተስፋ በመቁረጥ ፈረሰኛ እርካቡን ለማሰር በሚጠቀምበት [ገመድ] ሊበጠስ ትንሽ የቀረው የቆዳ መጫኛ ላይ ተንጠለጠልኩ።"

"ክብደቴ መጫኛውን መበጠስ ነበረበት፣ ነገር ግን እንደምንም ለትንሽ ያዘ። ሌላኛው የሚዘለው ወይም ከሁለቱ በድንገት የሚበረግገው እና የሚፈረጥጠው ፈረስ ቢሆን መጫኛውን ይበጥሰው ነበር ወይም ከእጆቼ ይመነጥቀው እና እግሬ በእርካቡ እንደተያዘ ወደ ጉዳት ወይም ሞት ጎትቶ ይወስደኝ ነበር።

"በድንገት ፈረሱ ቆመ፣ እና አንድ ሰው ልጓሙን አጥብቆ መያዙን እና የሚንቀጠቀጠውን እንስሳ ለማረጋጋት መሞከሩን አወኩ። ወዲያውኑ የአባቴን ክንዶች ለመያዝ ተፍጨረጨርኩ።

"ምን ተከሰተ? ከደነበረው ፈረሴ ኮቴ ስር ከመውደቄ በፊት ከመቀፀበት አባቴን ያመጣው ምንድን ነው?

ወደ ተክሉ ሩጥ!"]በማለት [መንፈስ ቅዱስ] በጆሮው ሹክ ሲልበት "አባቴ ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ጋዜጣ ያነብ ነበር።

"ካለምንም ጥርጣሬ፣ አባቴ ለምን ወይም በምን ምክንያት እንደሆነ ለማወቅ ሳይጠብቅ ሮጠ። ለምን እዚያ እንደደረሰ ሳያውቅ እራሱን ተክሉ ውስጥ በማግኘት፣ የደነበረውን ፈረስ ተመለከተ እናም *ይህንን ፈረስ ማቆም አለብኝ*፣ ብሎ አሰበ።

"እንደዚያም አደረገ እና እኔን አገኘኝ። እናም ከሞት ወይም ከከፍተኛ አደጋ ልድን የቻልኩት እንደዚህ ነው" (Bruce R. McConkie, "Hearken to the Spirit," *Friend,* Sept. 1972, p. 10)።

ውይይት

- መንፈስ ቅዱስ ወጣቱን ብሩስ ማኮንኪን ከከባድ አደጋ ያዳነው እንዴት ነው?
- የብሩስ አባት የመንፈስን ሹክ ማለት በፍጥነት ባይታዘዙ ኖሮ ምን ይከሰት ነበር? (ብሩስ አር ማኮንኪ በኋላ ከሰባዎቹ አንዱ እና ከዚያም ሐዋርያ በመሆን እንደተጠራ ይግለጹ፣ ይህ ጠቃሚ መሪ አይኖረንም ነበር።)
- እንዲህ ዓይነቱ ልምድ የአንድን ሰው ምስክርነት የሚያጠነክረው እንዴት ነው?

አንዳንዴ የመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳትን ከማዳመጥ የሚመጡትን በረከቶች በፍጥነት ማየት እንደማንችል ለልጆቹ ይንገሯቸው። ይሁን እንጂ፣ ወደ እኛ የሚመጣውን የመንፈስ ማነሳሳት ከታዘዝን እንደምንባረክ፣ እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

**ማጠቃለያ**

የጥያቄ ጨዋታ

ካዘጋጁት ከረጢት ጥያቄን በመምረጥ እና ከዚያም መልሱን በመመለስ ተራ እንዲይዙ ልጆቹን ይጋብዟቸው። ለትንንሾቹ ልጆች ጥያቄዎቹን ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ማንበብ ያስፈልግዎታል። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይጠቀሙ። እያንዳንዱ ልጅ ከከረጢቱ ውስጥ ጥያቄን ለመምረጥ ዕድል እንዲኖረው ካስፈለገ የራስዎን አንዳንድ ተጨማሪ ጥያቄዎች ይጻፉ።

1. አንድን ሰው ማነሳሳት ማለት ምን ማለት ነው? (አቀጣጫን መስጠት ወይም ለአንድ ሰው ምን እንደሚያደርግ መንገር።)
2. የሚያነሳሳን ማነው? (መንፈስ ቅዱስ።)
3. መንፈስ ቅዱስ የሚያነሳሳን እንዴት ነው? (ሐሳብን ወይም ስሜቶችን በመስጠት ወይም እያናገረን ያነሳሳናል።)
4. መንፈስ ቅዱስ የሚረዳን እንዴት ነው? (ትክክለኛውን ነገር ማድረግን እንድናውቅ በመርዳት።)
5. መንፈስ ቅዱስ ሌቲታን የረዳው እንዴት ነበር? (ትሑት እንድትሆን በመገፋፋት።)
6. መንፈስ ቅዱስ ጆርጅን የረዳው እንዴት ነበር? (የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያደርግ የፈለጉትን እንዲያደርግ—ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄድ አነሳሱት።)
7. ካሮሊናን መንፈስ ቅዱስ ያነሳሳት ምን እንድታደርግ ነው? (እግሩን ጎትታ ማውጣት እንድትችል የወንድሟን ጫማ በመፍታት ነው።)
8. አባቱ የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት ስላዳመጠ እና ስለታዘዙ ወጣቱ ብሩስ አር ማኮንኪ የተባረከው እንዴት ነበር? (ከአደጋ ወይም ከሞት ዳነ።)
9. ከመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳትን ስንቀበል ምን ማድረግ አለብን? (ማዳመጥ፣ መታዘዝ፣ እና ትክክለኛውን መምረጥ።)

ምስክርነት

በህይወትዎ ለመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳት ምስጋናዎን ይግለጹ። በመንፈስ እንደተመሩ፣ መንፈስ ቅዱስ እርሶን ወይም ሌላ የሚያውቁትን ሰው ስላነሳሳበት ጊዜ የግል ልምድዎን ያካፍሉ።

መንፈስ ቅዱስ ስሕተት የሆነውን ነገር ማንኛውንም እንድናደርግ በፍፁም እንደማያነሳሳን ይግለጹ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን እንድናደርግ ይረዳናል።

የእምነት አንቀፅ

ልጆቹ የመጀመሪያውን የእምነት አንቀፅ ደግመው እንዲሉት ያድርጉ።

ከተጠመቅን እና የቤተክርስቲያን አባልነታችን ከተረገገጠልን በኋላ የምንቀበለው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ልዩ ስጦታ እንደሆነ ይግለጹ።

የመዝጊያ ፀሎት የሚሰጠው ልጅ ለመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳት ምስጋናን እንዲገልፅ ይጠይቁት። እያንዳንዱ የክፍል አባል የመንፈስ ቅዱስ ማነሳሳትን ሲቀበል እንዲያውቀው የሰማይ አባት እንዲረዳቸው እንዲጠይቁ ሃሳብ ያቅርቡ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ “የአስተማሪ መረጃ” “የክፍል ጊዜን” በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።

1. ልጆቹ ስለ ቂስ ቶማስ ኤስ ሞንሰን የሚከተለውን ታሪክ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣

ከጥቂት ጊዜ በፊት፣ ቄስ ሞንሰን እና ሚስቱ የሳሞአን ደሴት እንዲጎበኙ በነቢዩ ተላኩ።

እዚያ በነበሩበት ጊዜ፣ በሳውኒያቱ መንደር የሚኖሩትን የአንድ ክፍል ልጆች ጎበኙ።

ቄስ እና እህት መንሰን ሁለቱም ለክፍሉ ንግግር አደረጉ። ንግግራቸውን ከጨረሱ በኋላ እና የልጆቹ አስተማሪ የመዝጊያውን መዝሙር ሲያስተዋውቁ፣ ወደ ቄስ ሞንሰን አዕምሮ አንድ ሐሳብ መጣ። በግሉ እያንዳንዳቸውን 247ቱን ልጆች ሰላም ለማለት ተነሳሳ።

ይሁን እንጂ፣ ሰዓቱን ሲመለከት፣ እንደረፈደ እና እያንዳንዱ ልጅ በግል ሰላም ለማለት ሰዓት እንደሌለው አወቀ።

ሐሳቡን ከአዕምሮው ለማውጣት ሞከረ፣ ነገር ግን አልቻለም።

ከመዝጊያ ፀሎት በፊት፣ የእያንዳንዱን ልጅ እጅ ለመጨበጥ ሰዓት ለመውሰድ እንደገና ተነሳሳ።

በመጨረሻ ወደ አስተማሪው ዞረና እንዲህ አለ፣ “የእያንዳንዱን ወንድ ልጅ እና የእያንዳንዷን ሴት ልጅ እጅ መጨበጥ በጣም እፈልጋለሁ። ይህ ይቻላልን?” አለ

አስተማሪውም ፈገግ አለና፣ በሳሞአን ቋንቋ፣ ለልጆቹ ነጋራቸው። በጉጉት እና በፈቃደኝነት እራሳቸውን ነቀነቁ። ልጆቹ ፈገግታ ያሳዩበትን ምክንያት ለቄስ ሞንሰን ነገረው። ከሐዋርያቱ አንዱ በሳሞአ እንዲጎበኟቸው የቤተክርስቲያኑን ፕሬዚዳንት እንደጠየቀ አስተማሪው ሲያውቅ፣ እያንዳንዳቸው ከልብ ከፀለዩ እና በመጽሐፍ ቅዱስ እና በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ እንዳሉት ሰዎች እምነት ካላቸው፣ ሐዋርያ መንደራቸውን እንደሚጎበኝ፣ ደግሞም የእያንዳንዱን ልጅ እጅ ለመጨበጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚነሳሳ አስተማሪው ነግሯቸው ነበር (see Thomas S. Monson, “Talofa Lava,” *Friend,* May 1972, pp. 12–13)።

- ቄስ ሞንሰንን ያነሳሳው ማነው?
- መንፈስ ቅዱስ ቄስ ሞንሰንን ያነሳሳው እንዴት ነበር?

መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን በተለያዩ መንገዶች እንደሚያነሳሳ ይጠቁሙ። ብዙ ጊዜ ለቄስ ሞንሰን እንዳደረገው ለአዕምሮአችን ይነግረናል።

ቄስ ሞንሰን የመንፈስ ቅዱስን ማነሳሳት ወይም ትዕዛዝ በመስማታቸው ምክንያት፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያደርግ የፈለጉትን ማድረግ እንደቻለ ይግለጹ።

2. ልጆቹ የመንፈስ ቅዱስን መመሪያ ሲቀበሉ የተሰማቸውን ስለ ማንኛውም የህይወት ልምዶቻቸው እንዲናገሩ ያድርጉ።

# የተጠያቂነት ዕድሜ

ትምህርት
27

**ዓላማው** ልጆች በስምንት ዓመታቸው ለድርጊታቸው ተጠያቂ መሆን እንደሚጀምሩ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. አልማ 23 እና 24ን በፀሎት ያጥኑ።
2. በድራማ ለመጠቀም ትንሽ ገንዘብ ያምጡ፣ ወይም ትንሽ የመጫወቻ ገንዘብ አዘጋጁ።
3. "መልካምን ለማድረግ ድፈር" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃላቶቹን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 158)፤ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ ጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. ማንበብ ለሚችል ለእያንዳንዱ ልጅ መጽሐፈ ሞርሞን።
   ለ. የሕፃን ልብስ ዕቃ፣ እንደ ጫማ፣ ባርኔጣ፣ ወይም ሹራብ የመሳሰሉት።
   ሐ. አማራጭ (ይህንን ተሳትፎ ጠቃሚ ነው ብለው ካሰቡ እና እነዚህን ዕቃዎች ከባድ ባልሆነ ወጪ ለማግኘት ከቻሉ ብቻ ይጠቀሙ)፤ አንድ መጽሐፍ፣ አንድ ኳስ፣ እና አንድ ቦርሳ ከረሜላ ወይም ሌላ ተገቢ የሆነ ምግብ።
   መ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   ረ. ስዕል 3-54፣ ፀረ ኔፋይ ሊሃይ ጎራደዎቻቸውን ሲቀብሩ (62565፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 311)።
5. ማንኛውም ለሚጠቀሙባቸው ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከተሏቸው።

**ስምንት ዓመት ሲሞላን፣ ተጠያቂ ነን**

የአትኩሮት ተሳትፎ — ያመጡትን የሕፃን ልብስ ዕቃ ከፍ አድርገው ይያዙት።

- ይህ ለአንዳችሁ ይሆናልን? (አንዳንዶቹን ልጆች ትንንሾቹን ልብሶች ለመልበስ እንዲሞክሩ ልታደርግ ትጠይቃቸው ይሆናል፣ ከዚያም እንደማይሆናቸው ይመልሳሉ።)
- ለምን አልሆናቸውም? (በጣም ትንሽ ስለሆነ።)

በአንድ ወቀት እንደነዚህ ዓይነቶቹ ልብሶች የሚሆናቸው ትንንሾች እንደነበሩ፣ ነገር ግን አሁን ሰውነታቸው እንዳደገ ከልጆቹ ጋር ተወያይ። ልክ በሰውነት መጠን እንዳደጉ፣ በሌላም መንገዶች፣ ልብስ መልበስን የመሰሉ ነገሮችን በማድረግ ችሎታቸውም እንደሚያድጉ ይግለጹ።

- ሕፃን ሆናችሁ ልታደርጉ የማትችሉት ነገር አሁን ልታደርጉ የምትችሉት ነገር ምንድን ነው?

እነዚህ ነገሮች ልጆቹ እያደጉ መሄዳቸውን እና የበለጠ እየተማሩ መሄዳቸውን እንደሚያሳዩ ይግለጹ። እነዚህን ነገሮች ማድረግን የተማረ ሰው አብዛኛውን ጊዜ ትክክለኛውን ነገር ከስህተት ለይቶ ለማወቅም የደረሰ ትልቅ ነው።

ውይይት — የሰማይ አባት ጠቢብ መሆኑን ልጆቹን ያስታውሷቸው። የትኛው ትክክል እና የትኛው ስህተት እንደሆነ መማር እንዳለብን ያውቃል። በደንብ ስናድግ እና ስለ ትክክለኛው እና ስህተት ነገሮች

በደንብ ስናውቅ፣ ለምናደርገው ነገር ተጠያቂ እንሆናለን። ተጠይቂ መሆን ማለት ለምናደርገው ስህተት ኃላፊነቱን መውሰድ አለብን፣ እናም ለምናደርገው ትክክለኛ ነገር እንባረካለን ማለት ነው።

- ለምናደርገው ነገር በሰማይ አባት ተጠያቂ መሆን የምንጀምረው በስንት አመት ነው? (ስምንት።)

  ለድርጊታችን ኃላፊ ለመሆን ዕድሚያችን የበቃ መሆኑን የሰማይ አባት ስለሚያውቅ፣ ስምንት ዓመት ሲሆነን አንድ አስፈላጊ ነገር እንዲደረግ መፍቀዱን ይግለጹ።

- ስምንት ዓመት ሲሆነን የሚከተለው ነገር ምንድን ነው? (እንጠመቃለን፣ ትምህርት እና ቃልኪዳን 68፥27 ይመልከቱ።)
- ጥምቀት አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (ምክንያቱም ስንጠመቀ እና አባልነታችን ሲረጋገጥ፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን እንቀበላለን እናም ትዕዛዛቱን ለማክበር ከሰማይ አባት ጋር ቃል ኪዳን እንገባለን።)

  መጠመቀ ማለት ዳግም ስህተትን አናደርግም ማለት እንዳልሆነ ይግለጹ። ያ ማለት ለምርጫዎቻችን ኃላፊ ለመሆን ዕድሚያችን በቂ ነው ማለት ነው። በትክክለኛው እና በስህተት መካከል ያለውን ልዩነት ለማወቅ እድሚያችን ደርሷል።

የእምነት አንቀፅ

- ለራሳችን ኃጢአቶች ኃላፊ መሆናችንን የሚነግረን የእምነት አንቀፅ የትኛው ነው? (ሁለተኛው የእምነት አንቀፅ። ልጆቹ የማይገባቸውን ማንኛውንም ቃላት መግለፅ ይፈልጉ ይሆናል።)

ክፍሉ ሁለተኛውን የእምነት አንቀፅ በአንድነት በድጋሚ እንዲሉት ያድርጉ። በራሳቸው መድገም ለሚችሉ ለማናቸውም ልጆች ይፍቀዱላቸው።

**ትክክለኛውን ለመምረጥ ኃላፊዎች ነን**

የክፍል ቀለበት

- በክፍል ቀለበታችን ላይ ያሉት ፊደሎች የሚወክሉት ምንድን ነው?

ልጆቹ “ትክክለኛውን ምረጥ” የሚለውን ቃላት እንዲደግሙት ያድርጉ። ልጆቹ ትክክለኛውን ለመምረጥ ኃላፊ መሆንን ለማወቅ ዕድሚያቸው እስኪደርስ እንደሚያድጉ እንዲያውቁት ቀለበቶቻቸው ሊረዷቸው እንደሚችል ይግለጹ።

ለመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ትክክለኛውን ከስህተት መምረጥን መማር በማደግ ከፍተኛው ደረጃ እንደሆነ ይግለጹ። የሰማይ አባታችን ትክክለኛውን እንድናደርግ አያስገድደንም። ከትክክለኛው እና ከስህተት መሐከል ለራሳችን እንድንመርጥ እና የገባነውን ቃልኪዳን ለመጠበቅ ኃላፊ ለመሆን ነፃነትን ይሰጠናል። ማደግ እና መማር የምንችለው ለእራሳችን ለመምረጥ ነፃነትን በማግኘት ብቻ እንደሆነ ያውቃል።

ትክክለኛውን መምረጥ የሚለውን በጥቁር ሰሌዳው ላይ ይፃፉ። እነዚህ ፊደሎች የቆሙት ለምን እንደሆነ ልጆቹ እንደገና እንዲነግሩዎ ያድርጉ። ልጆቹ የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ እና የትኛው ስህተት እንደሆነ መማር እንደሚችሉ እና ለድርጊቶቻቸው ኃላፊ እንደሚሆኑ ያሉዎትን እምነት ይግለጹ።

ተሳትፎ

ከልጆቹ ለአንዱ ወይም ለሁለቱ ያመጡትን መጽሐፍ ይስጡ። ለመጽሐፉ የመጠንቀቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ይንገሯቸው። እነዚህ ልጆች በትምህርት ጊዜ ለዚያ መጽሐፍ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ለክፍሉ ይግለጹ። ከጠፋ፣ ከተቀደደ፣ ወይም በሌላ መንገድ ከተጎዳ፣ መልሱን ለእርሱ መስጠት አለባቸው። ለመጽሐፉ በእርሶ ተጠያቂ ይሆናሉ።

ለሌላ ልጅ ኳስ ይስጡ። ሌሎቹ ልጆች ለመጽሐፉ ኃላፊ እንደሆኑ ይህም ልጅ ለኳሱ ኃላፊ እንደሚሆን ይግለጹ።

ለሶስተኛው ልጅ ከረሜላ ወይም ሌላ ተስማሚ ምግብ ይስጡት። ይህንን በሚገባ ማካሄድ የሚችለው ልጅ ለመምረጥዎ እርግጠኛ ይሁኑ። ልጁ ከመዝጊያ ጸሎት በኋላ ከረሜላውን ወይም ምግቡን በክፍሉ ላሉት ለሁሉም እንዲያካፍል ይንገሩት። ልጁ የመካፈያው ሰዓት እስከሚደርስ ምግቡን በደህና ለመጠበቅ ሃላፊ ነው።

- (የልጁ ስም) ይህንን ከረሚላ በሙሉ ብቻውን ለመብላት መምረጥ ይችላልን? (አዎ፤ ልጁ አስተማሪውን ያለመታዘዝን መምረጥ እና ለመካፈል ከመቆጠብ ይልቅ መብላት ይችላል።)

ይህ ልጅ የሚያደርገውን የመምረጥ ነፃነት እንዳለው፤ ነገር ግን ልጁ ለዚያ ምርጫ ተጠያቂ መሆኑንም አጥብቀው ያሳስቡ።

ይህ ከሕይወት ጋር እንደሚመሳሰል ይግለጹ። የሰማይ አባት ዓላማ ምርጫዎችን ይሰጠናል። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ትክክለኛውን ወይም ስህተትን መምረጥ እንችላለን። ነገር ግን ለምርጫችን እና ለውጤቶቹ ኃላፊዎች እኛ ነን።

የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ

መጽሐፈ ሞርሞንን ያሳዩ። በመጽሐፈ ሞርሞን ሰዎች በጣም አስቸጋሪ ምርጫ መምረጥ እንደነበረባቸው፤ እና ትክክለኛውን ለመምረጥ እንደወሰኑ ለልጆቹ ይንገሯቸው። የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፤

አሞን ለተወሰኑ የሌመናይቶች ወገን ንጉስ፤ ለንጉስ ሌሞናይ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች የገለፀ ወንጌላዊ ነበረ። ንጉስ ሌሞናይ እነዚህን ትምህርቶች አምኖ ወንጌልን ተቀበለ ሕዝቡ አሞን እና ወንድሞቹን እንዲሰሟቸው ጠየቀ። ንጉስ ሌሞናይ እነዚህ ሰዎች እውነትን እንደሚናገሩ ያውቃል።

አሞን እና ወንድሞቹ ሌመናይቶችን እያስተማሩ ከከተማ ወደ ከተማ እና ከቤት ወደ ቤት ሄዱ። ሌመናይቶች ወንጌልን አያውቁም፤ እናም በጣም ኃጢያተኞች ነበሩ። ብዙ ሰዎች የአሞንን እና የወንድሙን ትምህርቶች አመኑ እና ተለወጡ። የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል እውነት እንደነበር አወቁ፤ እና ከኃጢያተኛ መንገዳቸው ንስሀ ገቡ።

እነዚህ ህዝቦች ስማቸውን ከሌመናይቶች ወደ ፀረ ኔፋይ ሌሂዎች ለመለወጥ ወሰኑ። ይህንን ያደረጉት የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች ከማይከታተሉት ኃጢአተኞች ሌመናይቶች ራሳቸውን ለመለየት ነበር።

እነዚህ ህዝቦች ንስኃ ከመግባታቸው በፊት፤ ብዙ ሰዎችን በሰይፎቻቸው ገድለዋል። ላደረጉት ስህተት ነገሮች ተፀፅተው ንስኃ መግባት ፈለጉ። ሰይፎቻቸውን ዳግም በማንም ሰው እንዳያነሱ ወይም በፍፁም እንዳይጣሉ ለሰማይ አባት ቃል ኪዳን መግባትን መረጡ።

ጥቀስ

እነዚህ ከሕዝቦች ሌላ ውሳኔም እንደወሰኑ ይግለጹ። አልማ 24፥17–18ን ሲያነቡ ልጆቹ እንዲከታተሉ ያድርጉ። ሰይፎቻቸውን እና ሁሉንም መሳሪያዎቻቸውን ወስደው መሬት ውስጥ በጥልቀት ቀበሯቸው። ይህንን ያደረጉት የሰዎችን ደም ለማፍሰስ ዳግም በፍፁም መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ለእግዚአብሔር ምስክርነት ነው። የወንድሞቻቸውን ደም ከማፍሰስ ይልቅ፤ የራሳቸውን ሕይወት እንደሚሰጡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ገቡ።

- ፀረ ኔፋይ ሌሂዎች የመረጡት ምርጫ ምንድን ነው? (ሰይፎቻቸውን መሬት ውስጥ መቅበርን መረጡ።)
- ይህንን ያደረጉት ለምንድን ነው? (ምክንያቱም ዳግም እንዳይገሉ ቃል ኪዳን ወይም ቃለ መሐላ ስላደረጉ።

ስዕል እና ታሪክ

ስዕል 3-54፤ ፀረ ኔፋይ ሌሂዎች ሰይፎቻቸውን ሲቀብሩ የሚለውን ያሳዩ።

ታሪኩን ይቀጥሉ፤

ፀረ ኔፋይ ሌሂዎች ሰይፎቻቸውን ከቀበሩ በኋላ፤ ኃጢአተኞቹ ሌመናይቶች ሊወጓቸው መጡ። ፀረ ኔፋይ ሌሂዎች አስቸጋሪ ውሳኔ መወሰን ነበረባቸው። ከሰማይ አባት ጋር የገቡትን ቃል ማፍረስ እና ለመዋጋት ሰይፎቻቸውን መጠቀም፤ ወይም ላለመዋጋት መወሰን መቻል እና ምናልባትም መገደል ነበረባቸው። ሌሎች ሰዎችን በመቃወም ሰይፎቻቸውን ላለመጠቀም ቃልኪዳናቸውን ለመጠበቅ ወሰኑ። ብዙዎቹ በሌመናይቶች ተገደሉ። እነዚህ ሰዎች መሳሪያ እንደሌላቸው እና እንደማይዋጉ ሌመናይቶች ሲያዩ፤ ተደነቁ። ብዙዎቹ የራሳቸውን ጎራዴዎች አስቀመጡ ምክንያቱም እነሱም ሠዎችን በመግደል ታላቅ ስህተት እየሰሩ መሆናቸውን ተገነዘቡ። ብዙ ሌመናይቶች ንስኃ ገቡ እና ከፀረ ሌሂዎች ጋር በቀድስና ተቀላቀሉ።

ፀረ የኔፊ ሌሂዎች ሌሎች ሰዎች ሊገድሏቸው ሲሞክሩ እንኳ ለቃል ኪዳናቸው ታማኞች ነበሩ።

- ፀረ ኔፊ ሌሂዎች ላደረጉት ነገር ሃላፊ የሚሆኑት እንዴት ነበረ?
- ከፀረ ኔፊ ሌሂዎች ትክክለኛውን ስለመምረጥ የምትማሩት ምንድን ነው?

**በስምንት ዓመት ዕድሚያችን በሰማይ አባት ተጠያቂ እንሆናለን**

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

ተጠያቂ መሆን ማለት ለሚያደርጉት ነገሮች ሃላፊዎች ናቸው ማለት እንደሆነ ለልጆች ያስታውሷቸው።

ተጠያቂ የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ፣ እና ቃሉን ድምጽዎን ከፍ አድርገው ይበሉት። ልጆቹ እንዲደግሙት ያድርጉ። ስምንት ዓመት ሲሆናቸው፣ የሰማይ አባት ለድርጊታቸው ተጠያቂ መሆን ለመጀመር ዕድሚያቸው እንደደረሰ እንደሚያስብ ይግለጹ።

መዝሙር

“መልካምን ለማድረግ ድፈር” የሚለውን መዝሙር ከልጆቹ ጋር ይዘምሩ ወይም ቃሎቹን ይበሉ።

ሁኔታ

ስምንት ዓመት ሲሆናቸው ተጠያቂ እንዲሆኑ ለልጆቹ ይግለጹላቸው። ነገር ግን ስምንት ዓመት ያልሆናቸው ወላጆቻቸውን በመርዳት እና ለሌሎች የገቡትን ቃል ኪዳን በመጠበቅ አሁን ሃላፊ መሆንን መለማመድ ይችላሉ። የሚከተለውን ሁኔታ ይናገሩ (አንድ ልጅ ድርጊቶቹን እንዲፈፅም ይፈልጉ ይሆናል)፣

እናትህ እንደ ታመመችና ቤቱን በከፊሉ እንድታፀዳ እንደጠየቀችህ አስመስል። መጫወት ትፈልጋለህ፣ ስለዚህ ከጓደኞችህ ጋር ለመሆን ወደ ውጭ ትሮጣለህ።

ተመልሰህ ወደ ውስጥ ስትመጣ፣ እናትህ በአልጋዋ ሆና ትጠራሀና፣ “እንድታፀዳ የጠየኩህን ከፊሉን ቤት አፅድተሃል ወይ?” ብላ ትጠይቅሃለች።

አዎን ብለህ ትመልሳለህ፣ እና ከዚያም በፍጥነት ባፀዳህበት አካባቢ ጥቂት ነገሮችን ታስተካክላለህ።

ውይይት

ልጆች ወላጆቻቸው የሚሰሩትን ስራ ሲሰጧቸው፣ ያንን ስራ ለመስራት ሃላፊ እና ተጠያቂ ለመሆን ዕድሚያቸው ደርሷል ማለት እንደሆነ ይግለጹላቸው።

- ከጀማሪ ክፍል፣ ከጓደኛ ቤት፣ ወይም ከትምህርት ቤት ስትመለስ ከወላጆችህ አንዱ፣ “ንገረኝ ዛሬ ያደረከው ምንድን ነው” ብለውህ ያውቃሉን?

ልጆች ለወላጆቻቸው መረጃን ሲሰጡ እና ያደረጉትን ሲነግሯቸው፣ ልጆቹ ለድርጊታቸው እንደሚጠየቁ ያስገንዝቡ። ወላጆች ልጆቻቸውን ይወዳሉ ለዚህም ነው። ወላጆች ልጆቻቸውን በቤት ውስጥ፣ በትምህርት ቤት፣ እና በጨዋታ ቦታ ምን እንደሚያደርጉ ማወቅ የሚፈልጉት።

የእምነት አንቀፅ

ልክ እንደ ወላጆቻችን፣ የሰማይ አባታችንም ይወደናል፣ ለምናደርጋቸው መልካም እና መጥፎ ነገሮች መረጃ እንድንሰጥ እና በእርሱ ተጠያቂ እንድንሆን ይፈልጋል። እንደ መስረቅ፣ መዋሸት፣ ወይም አንድ ሰው መጉዳት የመሳሰሉትን መጥፎ ነገሮች ስንሰራ . . .ስምንት ዓመት ከሆነን በኋላ፣ ኃጢአቶች ተብለው ይጠራሉ። ክፍሉ ሁለተኛውን የእምነት አንቀፅ በአንድነት እንዲደግሙት ያድርጉ።

በጥቁር ሰሌዳው ላይ *ተጠያቂ* የሚለውን ቃል ያመልክቱ፣ እና ልጆቹ ቃሉን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲሉት ይጠይቋቸው። በሰማይ አባት ተጠያቂ ለመሆን በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ይንገሯቸው፣ ምክንያቱም ስምንት ዓመት ሲሆናቸው ሃላፊነትን ለማሳየት እና ትክክለኛውን ከስህተት ለማወቅ ዕድሚያቸው ይደርሳል።

**ማጠቃለያ**

ተሳትፎ

ተጠያቂ የሆኑበትን እና ሌሎች ተጠያቂ የሚሆኑበትን ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት አንዳንድ ጥያቄዎችን ይጠይቋቸው። መልሱን በአንድነት እንዲመልሱ ያድርጉ።

1. መፀለይ እንዲያስተምሯችሁ ተጠያቂው ማነው?
2. ፀሎታችሁን ለመፀለያችሁ ተጠያቂው ማነው?

3. በጀማሪ ክፍል ትምህርታችሁን እንዲያስተምሯችሁ ተጠያቂው ማነው?
4. የጀማሪ ክፍል አስተማሪያችሁ የሚያስተምረውን ለማወቅ ተጠያቂው ማነው?
5. በጀማሪ ክፍል ለምታደርጉት ድርጊት ተጠያቂው ማነው?
6. የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድታደርጉ የሚፈልጉትን ለማድረግ ተጠያቂው ማነው?
7. የጥምቀት ቃልኪዳናችሁን ለመጠበቅ ተጠያቂው ማነው?

**ውይይት**

ልጆቹ ተጠያቂ የሆኑበትን ወይም የሚሆኑበትን ብዙ መንገዶች እንዲናገሩ ያድርጉ። ይህ ለጓደኛ ደግ መሆንን፣ እውነት መናገርን፣ ትሑት መሆንን፣ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን መከታተልን፣ ጎጂ መጠጦችን፣ አደንዛዥ ዕፆችን፣ እና ትንባሆን ማስወገድን፣ ወይም የገቡትን ቃልኪዳንን መጠበቅን ያጠቃልላል።

**ተሳትፎ እና የአስተማሪ ምስክርነት**

መጽሐፍ እና ኳስ የሰጧቸው ልጆች ከእቃዎቹ ጋር ድርጊታቸውን እንዲገልጹልዎ ያድርጉ። ዕቃዎቹን እንዲመልሱልዎ ያድርጉ፣ እና ጥሩ ከሰሩ ያሞግሷቸው።

ይህ በሕይወታቸው አስፈላጊ ጊዜ እንደሆነ፣ ነገር ግን ብቻቸውን እንዳልሆኑ በመንገር ያጠቃሉ። የሚመሯቸው እና የሚረዷቸው ወላጆች እና መሪዎች አሉዋቸው። በተጨማሪም የሚወዷቸው እና የሚመሯቸው የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ አሉላቸው። ከጥምቀት በኋላ፣ ያለማቋረጥ የሚያነሳሳቸው መንፈስ ቅዱስ አላቸው። ልጆቹ ሃላፊ መሆንን እና ለሚያደርጉት ነገር መግለጫ መስጠትን የበለጠ እየተማሩ መሆናቸውን ለማሳየት ያበረታቷቸው። ስህተትን እንደሚሰሩ እንዲያውቁት ይርዷቸው። ሁሉም ስህተት ያደርጋል። ነገር ግን ንስኃ መግባት እና በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ሁልጊዜ የተሻለ መስራት ይችላሉ።

የሰማይ አባት ልጆቹን በሙሉ እንደሚወድ ምስክርነትዎን ይስጡ። በዚህም ምክንያት፣ እንድናድግ እና የበለጠ እንደ እርሱ እንድንሆን መንገድ አቀዶልናል። የበለጠ ሃላፊ ለመሆን እርሱ ወይም እርሷ በምታደርገው በእያንዳንዱ ልጆች ያለብዎትን እምነት እንደገና ይግለጹ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ከመዝጊያ ፀሎት በኋላ፣ ከረሜላ የያዘው ልጅ መግለጫ እንዲሰጥዎ ያድርጉ። ከዚያም ልጁ አንዳንድ ከረሜላ ለእያንዳንዱ የክፍል አባል እንዲሰጥ ያድርጉ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ በ “የአስተማሪው መርጃዎች” የሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ከሚከተሉትን ተሳትፎዎች አንዱን ልጁ ሃላፊ የሆነበትን በሚያሳይ መንገድ እንዲጨርሱ ለእያንዳንዱ ልጅ ተራ ይስጡ። (የሚከተሉትን ሁኔታዎች መጠቀም ወይም የራስዎን ማዘጋጀት ይችላሉ።)
   ሀ. ውጭ ልትጫወት ነው። በጣም ይበርዳል። እናትህ ኮት እንድታደርግ ትነግርሃለች።
   ለ. ቀዳሚ ጠዋት ቤቱን በከፊሉ ማፅዳትን የምታስታውስ ከሆነ፣ የዚያን ዕለት ማታ ወደ ኳስ ጨዋታ ከእርሱ ጋር መሄድ እንደምትችል አባትህ ይነግርሃል።
   ሐ. ጓደኞችህ አሻንጉሊትህን ከእነርሱ ጋር እንድትጋራ ይፈልጋሉ። እነርሱ ከአንተ ጋር ይጋራሉ።
   መ. እናትህ ትንሿ እህትህን እንድትጠብቅ ተጠይቀሃለች።
   ሠ. እናትህን ብስኩቶችን በማብሰል ትረዳታለህ። መጥበሻው እስከሚበርድ ድረስ እንዳትነካው ታስታውስሃለች።

ረ. ጓደኛህ ወይም ታላቅ ወንድሙ ትንሽ ቢራ እንድትጠጣ ይጠይቅሃል።

ሰ. በሚገባ አለበስክም እናም ወደ ውጪ መሄድ ትፈልጋለህ።

ሸ. አባትህ በአትክልት ሥፍራ እንድትረዳው ይጠይቅሃል። ትጮህበት እና ከጓደኞችህ ጋር ለመሆን ሮጠህ ትሄዳለህ።

ቀ. የጀማሪ ክፍል አስተማሪህ በአክብሮት ተቀምጠህ መዝሙሮችን እንድትዘምር ይጠይቅሃል። አንተ አትፈልግም።

2. ልጆቹ በማድረጋቸው የሚጠየቁበትን ነገሮች ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ። ስዕሎቹን “ተጠያቂ ለመሆን እየተማርኩ ነው” በማለት ምልክት ያድርጉባቸው።

# ወላጆቻችን እንድንማር ይረዱናል

ትምህርት
28

**ዓላማው** ልጆቹ ወላጆቻቸው ወይም አሳዳጊዎቻቸው ትዕዛዛትን መታዘዝ እንዲማሩ እንዴት ሊረዷቸው እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ሞዛያ 53፥10–22፤ 56፥3–10፤ 46–48፤ 55–56፤ 57፥24–25፤ ትምህርት እና ቃልኪዳን 93፥40፤ እና መጽሐፈ ሙሴ 6፥58ን በፀሎት ያጥኑ።
2. "በብርሃን መጓዝን አስተምረኝ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃሎቹን ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 177)። ለክፍልዎ ተገቢ ከሆነ አንድ ልጅ የመጀመሪያውን ቁጥር እንዲዘምር ይጠይቁ ይሆናል።
3. አንድ እናት በመጀመሪያው ክፍል ጊዜ ሕፃን ልጇን እንድታመጣ ይጋብዙ። (ይህ የማይቻል ከሆነ፣ የእናት እና የሕፃን ልጇን ስዕል መጠቀም ይችሉ ይሆናል።)
4. በዚህ ትምህርት ውስጥ፣ ምናልባት ከሁለቱም ወላጆቻቸው ጋር ለማይኖሩት ልጆች ወይም ወላጆቻቸው ትዕዛዛትን እንዲታዘዙ ለማያስተምሩዋቸው ልጆች ይሰማዎ።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፣
   ሀ. መደበኛ ቅዱሳን መጽሐፍት።
   ለ. የባቄላ ሽፋን፣ ትንሽ ኳስ፣ ወይም ሌላ ለስላሳ ዕቃ።
   ሐ. ስዕል 3-38፣ ሁለት ሺህ ወጣት ጦረኞች (62050፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 313)፣ ስዕል 3-5፣ አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**እንድንማር የሚረዱን ወላጆች አሉን**

የአትኩሮት ተሳትፎ

እናትየውን እና ሕፃኑን ለልጆቹ ያስተዋውቁ። ልጆቹ ሕፃኑን ለአጭር ጊዜ እንዲመለከቱት ያድርጉ እና ከዚያ በኋላ ይህን ጥያቄ ይጠይቋቸው፣

- ሕፃኑ ለራሱ ማድረግ የሚችለው ምንድን ነው?
- እናት ለሕፃኑ የምታደርገው ምንድን ነው?
- ሕፃኑ መናገር የሚማረው እንዴት ነው?
- ሕፃኑ መራመድ የሚማረው እንዴት ነው?

አንድ ሰው ለሕፃኑ መጠንቀቅ እንዳለበት ይግለጹ። እርሱ ወይም እርሷ በሁሉም ነገር የሚመኩት በወላጆቹ ወይም በወላጆቿ ላይ ነው። ሕጻኑን ይወዱታል፣ እናም ቀናቸውን አንዳንዴም ለሊቱን እርሱን በመጠበቅ ያሳልፋሉ።

- ከሕፃንነታችሁ ጀምሮ የተማራችኋቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?
- ያስተማራችሁ እና የተንከባከባችሁ ማነው?

እናትየው ከሕፃን ልጇ ጋር ወደ እዚህ ክፍል በመምጣቷ ያመስግኗት፣ እና በዚህ ጊዜ ይቀርታ ይጠይቋት።

**ወላጆቻችን ትዕዛዛትን መታዘዝ እንድንማር ይረዱናል**

ስዕል እና ታሪክ

ስዕል 3-5፣ አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ የሚለውን ያሳዩ።

አዳም እና ሔዋን፣ በምድር ላይ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል የተማሩ እና ለልጆቻቸው እንዲያስተምሩ የተነገራቸው የመጀመሪያዎቹ ወንድ እና ሴት ናቸው። መፅሐፈ ሙሴ 6፥58 የመጨረሻውን ቃል በማስቀረት ድምጽዎን ከፍ አድርገው ያንብቡት።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለወላጆች የሰጠው ትዕዛዝ ምንድን ነው? (ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ። ወላጆች ማስተማር ያለባቸው ነገሮች የወንጌልን እውነት ነው፣ ት እና ቃ 93፥40 ይመልከቱ።)

መዝሙር

"በብርሃን መጓዝን አስተምረኝ" የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ ወይም ቃሎቹን ይበሉ። ልጆቹ "በብርሃን መጓዝ" ምን ማለት እንደሆነ ማወቅ መቻላቸውን ለማየት እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው።

በፍቀሩ ብርሃን መጓዝን አስተምረኝ፣
ወደ አባቴ መፀለይ አስተምረኝ፣
መልካም ነገሮችን እንዳውቅ አስተምረኝ፣
አስተምረኝ፣ ልማር፣ በብርሃን ለመጓዝ።

ና፣ ትንሹ ልጅ፣ በአንድ ላይ እንማር
ትዕዛዛቱን፣ ከዚያ እንድንመለስ
በእርሱ መኖሪያ፣ በአይታው ለመኖር
ዘወትር፣ ዘወትር፣ በብርሃን ለመጓዝ።

የሰማይ አባት፣ ተመስገን ዛሬ
በፍቀርህ አመራር መንገድ ስላሳየኸን።
በደስታ፣ መዝሙር እናወድስሃለን!
በደስታ፣ በብርሃን እንጓዛለን።

- "በብርሃን መጓዝ" ማለት ምን ማለት ነው? (የሰማይ አባታችንን መታዘዝ ማለት ነው።)

በዚህ ምድር ላይ የተወለድነው እንድንማር እንደሆነ፣ እና የሰማይ አባት በቤተሰብ መሐል ያስቀመጠን ከወላጆቻችን መማር እንድንችል መሆኑን ይግለጹ። ወላጆች እንድንዘጋጅ ሊረዱን ታዘዋል ስለዚህ አንድ ቀን ከሰማይ አባታችን ጋር ተመልሰን መኖር እንችላለን።

የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ እና ስዕል

መጽሐፈ ሞርሞን ወላጆቻቸው ትዕዛዛትን እንዲያከብሩ ስላስተማሩዋቸው አንዳንድ ወጣት ወንዶች ታሪክ እንደሚናገር ግለፅ። የሚከተለውን በራስህ አባባል ተናገር፥

ወንጌል የተቀበሉት ሌመናይቶች ከቀሩት ሌመናይቶች ጋር እንዳይደባለቁ ፀረ ኔፊ ሌሂ ብለው ራሳቸውን እንደሰየሙ ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ፀረ ኔፊ ሌሂዎች ሲለወጡ፣ የጦር መሳሪያቸውን ለውጊያ ላለመጠቀም ከሰማይ አባት ጋር ቃልኪዳን ወይም ቃለ-መሀላ አደረጉ። ቃለ መሃላቸውን መጠበቃቸውን ለማሳየት ጎራዴዎቻቸውን ቀበሩ።

ኔፊዎች ለፀረ ኔፊ ሌሂዎች የሚኖሩበትን መሬት ሰጧቸው እና ከሌመናይቶች ተከላከሏቸው። ፀረ ኔፊ ሌሂዎች በቅድስናቸው እና በታማኝነታቸው የታወቁ ሆኑ። የኔፊዎችን የጦር ሠራዊት ለመርዳት ልብስ እና ምግብ ሰጡ።

ብዙ ዓመታት አለፉ። ኃጢያተኞቹ ሌመናይቶች ኔፊዎችን መሬቶች እንደገና መውረር ጀመሩ እና አንዳንድ የኔፊዎችን ከተሞች ሃብት ወሰዱ። ኔፊዎች ከተማቸውን ለመከላከል ችግር ነበረባቸው። ፀረ ኔፊ ሌሂዎች ኔፊዎች ከተማቸውን እና ፀረ ኔፊ ሌሂዎች ለመጠበቅ እንዴት በጣም እንደሚዋጉ ሲያዩ፣ በጣም ተጨነቁ። ፀረ ኔፊ ሌሂዎች ቃለመሃላቸውን አፍርሰው ኔፊዎችን በውጊያ መርዳት እንዳለባቸው ግራ ተጋቡ።

ሔለማን የሚባል አንድ ጀግና የኔፊዎች መሪ ቃልኪዳናቸውን እንዳያፈርሱ ነገራቸው። ቃልኪዳንን መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ ያውቃል። እነዚህ የተቀደሱ ሰዎች ቃል ኪዳኑ በተደረገበት ወቅት በጣም ወጣት የነበሩ ብዙ ወንዶች ልጆች እንደነበሯቸውም ያውቃል። እነዚህ ወንዶች ልጆች ከሰማይ አባት ጋር ቃል ኪዳን አልገቡም፣ ስለዚህ ኔፊዎች ከተማዎቹን እና ወላጆቻቸውን ለመከላከል ሲዋጉ መርዳት ይችላሉ። ከእነዚህ ጠንካራ ወጣት ሰዎች ሁለት ሺዎቹ ከሂለማን ጋር አንድ ላይ በመሆን ለመዋጋት ፈቃደኛ ሆኑ።

ስዕል 3-38፣ ሁለት ሺህ ወጣት ጦረኞች የሚለውን ያሳዩ። ከዚያም ታሪኩን ይቀጥሉ።

እነዚህ ወጣት ወንዶች ታማኝ እና እምነተ ሊጣልባቸው የሚችሉ መሆናቸውን ይግለጹ። በሰማይ አባት እንዲታመኑ እና ትዕዛዛቱን እንዲያከብሩ እናቶቻቸው አስተምረዋቸዋል። እነዚህ ወጣት ጦረኞች እንደዚያ ካደረጉ፣ የሰማይ አባት እንደሚጠብቃቸው ያውቃሉ። የእናቶቻቸውን ትምህርት አምነው ስለተከተሉ፣ ሔለማንን መከተል አልፈሩም። ለነፊዎች
በብዙ ውጊያ ላይ ተዋግተውላቸዋል። በጀግንነት ተዋጉ እናም ለኔፊዎች ጦር ሠራዊት ታላቅ ረዳት ነበሩ።

አልማ 56፥47ን ድምፅዎን ከፍ አድርገው ለልጆቹ ያንብቡላቸው፣ እነዚህ ወጣት ወንዶች ተዋጊዎች ካልተጠራጠሩ፣ እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው እናቶቻቸው እንደተማሩ ይግለጹ። ለሔለማን የእናቶቻቸውን ቃል ነገሩት እና እናቶቻቸው እውነቱን እንደሚያውቁ አንጠራጠርም አሉ (አልማ 56፥47–48 ይመልከቱ)።

ልክ ወላጆች ልጆቻቸውን እንዲሚወዷቸው ሔለማን እነዚህን ወጣት ወንዶች እንደወደዳቸው ይግለጹ። ከአንድ ከባድ ጦርነት በኋላ፣ ብዙ ሰዎች ተገደሉ። ከእነዚህ ወጣት ወንዶች አንዳንዶቹ ይገደላሉ ብሎ ሔለማን ተጨነቀ። ሲቆጠሩ፣ አንዳቸውም ሳይሞቱ ስላገኘ ተደሰተ። ወጣቶቹ ወንዶች በእግዚአብሔር ስለታመኑ እና የእናቶቻቸውን ትምህርቶች ስለተከተሉ፣ የሰማይ አባት ከሌመናይቶች ጠበቃቸው።

**ውይይት** ልክ እነዚህ ወጣት ወንዶች እንዳደረጉት እኛም ከወላጆቻችን ትዕዛዛትን መማር እንደምንችል ይጥቀሱ። ከዚያም የተማርነውን መታዘዝ አለብን። ስለ ሰማዩ አባት ትዕዛዛት እኛን በማስተማር፣ ስንጠመቅ የገባናቸውን ቃል ኪዳኖች ለመጠበቅ የግድ ማድረግ ያለብን ምን እንደሆን እንድናውቅ ወላጆቻችን ይረዱናል።

- በወላጆቻችን እና በሌሎች የተማርናቸው አንዳንድ ትዕዛዛት ምን ምን ናቸው? (ልጆቹ እንዲመልሱ ይፍቀዱላቸው። በውይይትዎ፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስን መውደድ፣ እርስ በእርስ መዋደዱ፣ ወላጆቻችንን ማክበር፣ ሌሎችን ይቀር ማለት፣ መጠመቅ፣ መጸለይ፣ አስራትን መክፈል፣ መፆም፣ የጥበብ ቃልን መታዘዝ፣ ታማኝ መሆን፣ የሰንበትን ቀን በቅድስና መጠበቅ፣ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን መካፈል፣ እና ቅዱሳን መጽሐፍትን ማጥናት የሚሉትን ትዕዛዛት ያብራሩ።)

### ማጠቃለያ

ልጆቹ ወላጆቻቸው ሲያስተምሯቸው እንዲያዳምጡ እና ትዕዛዛትን እንዲታዘዙ ይጋብዟቸው። ስለ ትዕዛዛት ሲያስተምሩ ልጆቹ ወላጆቻቸውን እንዲያመሰግኗቸው ያበረታቷቸው።

**የአስተማሪ ምስክርነት** የሰማይ አባት ሁላችንንም እንደሚወደን ምስክርነትዎን ይስጡ። በዚህ ፍቅር ምክንያት፣ የምድር ወላጆቻችንን እንዲጠብቁን፣ እንዲጠነቀቁልን፣ እና ለመኖር ትክክለኛውን መንገድ እንዲያስተምሩን አዘዛቸው። ወላጆቻችን የሰማይ አባት እንደሚፈልገው ለመኖር ሲሞክሩ፣ ሁልጊዜ ትክክለኛውን መንገድ መምረጥ ከእነርሱ መማር እንችላለን።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ጸሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

## አስፈላጊ ተሳትፎዎች

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መረጃዎች” በሚለው ውስጥ “ክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ልጆቹ ወላጆቻቸው እንዲሰሩ ያስተማሯቸውን አንዳንድ ነገሮች እንዲያስቡ ያድርጉ። ከዚያም የሚከተለውን ጨዋታ አብረዋቸው ይጫወቱ፥

   “የእኔ (እናት፣ አባት፣ ወይም ወላጆች) (ለምሳሌ፥ ኬክ መጋገርን) አስተማሩኝ፣” ይበሉ። ከዚያም አንድን ልጅ በስሙ ይጥሩ፣ የባቄላውን ከረጢት ወደ እርሱ ወይም ወደ እርሷ ይወርውሩ፣ እና “ወላጆችህ ምን መስራት ነው ያስተማሩህ?” በማለት ይጠይቁ።

   ልጁ “የእኔ (እናት፣ አባት፣ ወይም ወላጆች) (ለምሳሌ፥ ስሚን መጸፍ) አስተማሩኝ” በማለት ይመልሳል። ከዚያም ልጁ የባቄላውን ከረጢት መልሶ ወደእርሶ ይወረውረዋል።

   እያንዳንዱ ልጅ አንድ ወይም ሁለት ተራዎች እስከሚደርሱት ድረስ ጨዋታውን ይድገሙት።

2. የሚከተለውን ግጥም ለልጆቹ ያንብቡላቸው። ልጆቹ እንዲቆሙ ያድርጉ፣ እና ከዚያም *ሰማይ* ወይም *ቤት* የሚለውን ቃል በሰሙ ቁጥር እጆቻቸውን በእራሶቻቸው ላይ እንዲያደርጉ በመንገር፣ ግጥሙን እንደገና ያንብቡላቸው።

   በሰማይ ቤት ነበረኝ

   በሰማይ ቤት ነበረኝ፣<br>እናቴ ነገረችኝ፣<br>በጣም ሩቅ አይደለም<br>ከሰማይ አባት ጋር ኖሬአለሁኝ።

   በሰማይ ኖሬአለሁኝ፣<br>አባቴ እውነት ነው አለኝ<br>የሰማይ አባት እዚህ እንደላከኝ<br>እንዳድግ፣ እና እንድማር፣ እና እንድሰራ።

   የሰማይ ቤቴን እወደዋለሁኝ፣<br>አሁን ግን እዚህ በመሆኔ እደሰታለሁኝ<br>ከራሴ ቤተሰብ ጋር እንድኖር፣<br>ከጓደኞቼ እና ከውድ ጎረቤቶቼም ጋር።

3. “ደስተኛ ቤተሰብ” የሚሉትን ቃላት ከልጆች ጋር ይዘምሩት ወይም ይበሉት (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገጽ 198)፣ ቃላቶቹ በዚህ መመሪያ በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል።

   አንድ ልጅ እናት እንድትሆን እና አንዱ አባት እንዲሆን ይምረጡ። “እናት” በማለት ስትዘምሩ ወይም ስትሉ እናትን የምትወክለዋ ልጅ ትቆማለች። “እኔ፣ የሚለውን ስትዘምሩ ወይም ስትሉ እያንዳንዱ ልጅ ወደራሱ ይጠቁማል “አባት፣” የሚለውን ስትዘምሩ ወይም ስትሉ አባትን የሚወክለው ልጅ ይቆማል።

# በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን

ትምህርት


29

**ዓላማው**

በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የልጆቹን እምነት ለማጠንከር ነው።

**ዝግጅት**

1. ሞዛያ 4፥21፣ አልማ 32፣ ኢተር 2–3፣ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን 29፥6ን በፀሎት ያጥኑ። ኢተር 2፥17፣ 23፣ 3፥6፣ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን 29፥6 በትምህርት ጊዜ ለማጥናት ይዘጋጁ።
2. ጥቂት ትንንሽ የፀዱ ድንጋዮችን ያግኙ፣ ወይም ድንጋዮቹን ለመወከል ከጠንካራ ወረቀት በክብ ይቁረጡ። ከታች እንደሚታየው፣ በድንጋዮቹ ወይም በወረቀቶቹ ስር አንድ ፊደል በእያንዳንዱ ድንጋይ ላይ በማስቀመጥ "እምነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለውን ይፃፉ።




   ከክፍሉ በፊት የድንጋዮቹን ወይም የወረቀቶቹን ፊደል አስተካክለው በጠረጴዛ ላይ ወይም በወለል ላይ ገልብጠው ያስቀምጡት።
3. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. ለእያንዳንዱ ልጅ ከተቻለ መጽሐፈ ሞርሞን እና ትምህርት እና ቃልኪዳን፤።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀት እና እርሳስ (ወይም ከለር)።
   ሐ. የሚያስደስት ዕቃ (ከተቻለ፣ ከትምህርቱ ጋር የተያያዘ ነገር)፣ ለመደበቂያ ከሚሆን ቁራጭ ጨርቅ ጋር።
   መ. ስዕል 3-55፣ የያሬድ ወንድም የጌታን ጣት አየ (62478፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 318)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ለማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ሊኖረን ይችላል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

በራስዎ አባባል፣ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

አንዲት ትንሽ ሴት ልጅ አባቷ በጥልቀ የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ሲሰራ ምሳ ወሰደችለት። ምንም እንኳን አባቷን ታች በጉድጓዱ ጨለማ ውስጥ ማየት ባትችልም፣ ስትጠራው መለሰላት፣ ስለዚህ እዚያ እንደነበር አወቀች። አባቷ የምሳውን ዕቃ ጉድጓዱ ውስጥ ወርውሪው አላት፣ እንደሚይዘው ነገራት። ያዘው፣ ከትንሽ ጊዜ በኋላም ጠራት እና ምሳው ለአንድ ሰው ብዙ እንደሆነ ነገራት፣ እና አብራው እንድትበላ ጋበዛት። "ዝለይ፣" "እና እኔ እይዝሻለሁ አላት።

አንቺ ልታይኝ አትችይም፣ እኔ ግን ላይሽ እችላለሁ፣ እና እንድትወድቂ አላደርግም።” ወደ ጨለማው ጉድጓድ ዘለለች እናም በአባቷ ጠንካራ ክንድ ላይ በደህና አረፈች። በአንድነት ምሳውን በመካፈል ጥሩ ጊዜ ነበራቸው።

ትንሿ ሴት ልጅ ምንም እንኳን ልታየው ባትችልም አባቷ እንደሚይዛት እንዳመነችው ለልጆቹ ይግለጹ። ይህ ማመን እንደ እምነት ነው። እምነት ልታዩት በማትችሉት ነገር ማመን ነው። ነገር ግን እውነት እንደሆነ ታላቅ ተስፋ አላችሁ (ኢተር 12፥6ን ይመልከቱ)።

የትምህርቱ ዓላማ

ለልጆቹ በቁራጭ ጨርቀ የተሸፈነውን ዕቃ ያሳዩ።

- ከዚህ ስር አንድ ነገር አለ ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?

ልጆቹ ዕቃው ምን ይሆናል ብለው ያሰቡትን እንዲገምቱ ያድርጉ። ከዚያም ዕቃውን ይግለጹት። ዕቃውን ማየት ባይችሉም እንኳ እዚያ፣ ማመናቸውን ያስገንዝቡ።

ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስን ባናየውም፣ እዚያ እንዳለ እንደምናምን ይግለጹ። በዓለም በየትም ቦታ የፈጠረውን ስንመለከት፣ በሰማይ ያሉትን ከዋክብት ስናይ፣ እና በተለይ ቀዱሳን መጻሐፍትን ስናነብ መኖሩን እናረጋግጣለን። እንዳዩት የነገሩንም ነቢያት አሉን። ዛሬ ከመጽሐፈ ሞርሞን ሙሉ በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስን ማየቱን ታላቅ እምነት ስለነበረው አንድ ሰው እንደምንማር ለልጆቹ ይንገሯቸው።

### የያሬድ ወንድም እና ያሬዳውያን እምነት ነበራቸው

የቀዱሳን መጻሐፍት ታሪክ እና ውይይት

በመጽሐፈ ሞርሞን ውስጥ ስለ ኔፋውያን እና ሌመናይቶች ሲማሩ እንደነበረ ለልጆቹ ያስታውሷቸው። የሌላ ሕዝብ ወገንም ወደዚያው ሃገር እንደመጡ ይግለጹላቸው። ከሌሂ ቤተሰብ በፊት ብዙ ቀድመው ነው የመጡት። ያሬዳውያን ይባላሉ። መሪያቸው ያሬድ የሚባል ሰው ነበር። ያሬድ ታላቅ እምነት የነበረው ወንድም ነበረው። ኢየሱስ ክርስቶስ ያሬድን ወንድም ፀሎት ሰማ እና ሕዝቡን ባረከ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ያሬዳውያንን ቤተሰቦቻቸውን እና ንብረታቸውን በሙሉ፣ ከብቶቻቸውን እና ሁሉንም ዓይነት ዘሮች አንድ ላይ እንዲሰበስቡ እንደነገራቸው ይግለጹ። ሁሉንም ነገር አንድ ላይ ከሰበሰቡ በኋላ፣ ወደ ቃል ኪዳኑ መሬት እንደሚልካቸው ነገራቸው።

ያሬዳውያን ታማኝ እና ኢየሱስን የሚታዘዙ ነበሩ። ከዳመና ውስጥ ከያሬድ ወንድም ጋር ተነጋግሮ ያሬዳውያንን ወደ በረሃ መራቸው። ብዙ ውሃዎችን አቋርጠው ወደ ታላቁ ባሕር ተጓዙ።

የያሬድ ወንድም ታላቅ እምነት ስለነበረው እንደተባረከ ልጆቹን ያስታውሷቸው። ሕዝቡን እንዲረዳ የሰማይ አባትን በመጠየቅ እና ከዚያም የሰማይ አባት ያዘዘውን በማድረግ እምነቱን አሳይቷል።

የያሬድን ወንድም ታሪክ መናገሩን ይቀጥሉ፣

ኢየሱስ ክርስቶስ የያሬድ ወንድም ያሬዳውያንን ውቅያኖስን አቋርጠው ወደ ቃል ኪዳኑ ምድር እንዲያጓጉዟቸው። እንደ ጀልባ ወይም መርከቦች የመሳሰሉ ያሬዳውያን መመሪያዎቹን ተከትለው የጭነት መርከቦቹን ሰሩ።

የጭነት መርከቦቹ አንዳንድ ጊዜ በውሃ ስር ሊሆኑ ስለሚችሉ፣ ውሃ ሊገባ በማይችልበት ዓይነት መሰራት እንዳለባቸው አዳኝ ለያሬድ ወንድም ነገረው።

የቀዱሳን መጻሐፍት ንባብ

ማንበብ የሚችሉ ልጆች ኢተር 2፥17ን በመጽሐፈ ሞርሞን ቅጂያቸው እንዲፈልጉ ይርዷቸው። ቁጥር 17 የያሬዳዊያንን የጭነት መርከብን የሚገልጸውን አንድ ላይ አንብቡት፣ የጭነት መርከቦቹ ውሃን መያዝ እንዲችሉ እንደ ሳህን ዓይነት ተደርገው ጠብቀው መሰራታቸውን ይግለጹ። ስሩ፣ ጎኑ፣ እና ጫፉ እንደ ሳህን ውኃ የማያስገቡ ናቸው፣ እና ጫፎቹም ሹሎች ናቸው። እያንዳንዱ የጭነት መርከብ የዛፍ ቁመት አለው፣ በሩም ሲዘጋ፣ እንደ ሳህን ጥብቅ ነበር።

ልጆቹ እጆቻቸውን በአንድ ላይ እንደ መርከብ እንዲያስቀምጡ፣ እና ወደ የዕቃ መርከቦቹ አንድ ጎድጓዳ ሳህን በሌላው ላይ እንደተቀመጠ ዓይነት ወደ ፈለግነው በኩል እንዴት ሊዞሩ እንደሚችሉ ለማሳየት ወደ አንድ በኩል ከዚያም ወደ ሌላ እንዲዞሩ አድርጓቸው።

የስዕል ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳሶችን ወይም ከለሮችን እና ወረቀት ያከፋፍሉ። በቅዱሳን መጻሕፍት ካነበባችኋቸው አገላለፅ የጫነት መርከቦቹ ይመስላሉ ብለው ያሰቡትን ልጆቹ በስዕል እንዲስሉት ይጠይቋቸው። ልጆቹ ስዕሉን ሲስሉ እንደ አስፈላጊነታቸው እንደገና ያንብቡት።

ልጆቹ ስዕላቸውን ለክፍሉ እንዲያሳዩ ይፍቀዱላቸው፤ ከዚያም ስዕሎቹን እና የመጽሐፈ ሞርሞን ቅጂዎችን ይሰብስቡ። ከጀማሪ ክፍል በኋላ ስዕሎቻቸውን እንደሚመልሱላቸው ይንገሯቸው። የጫነት መርከቦች በትክክል ምን እንደሚመስሉ በእውነቱ እንደማናውቅ ይግለጹ።

**የያሬድ ወንድም ኢየሱስ ክርስቶስን አይቷል**

የጫነት መርከቦቹ ጥብቅ ከመሆናቸው የተነሳ፤ ምንም ብርሃን በውስጡ እንደሌለ፤ የጫነት መርከቡ ውስጥ ለህዝቦቹ እና ለእንሰሳዎቹ ንፁህ አየርም መግባት እንደማይችል ይግለጹ። ህዝቦቹ ውቅያኖሱን ሲያቋርጡ እንዴት ማየት ወይም መተንፈስ እንደሚችሉ ግራ ገባቸው። በእያንዳንዱ የጫነት መርከብ ጫፍ እና ስር ቀዳዳ እንዲያወጡ ኢየሱስ ክርስቶስ አዘዛቸው። እነዚህ ቀዳዳዎች መዘጋት ይችላሉ። ከዚያም፤ የጫነት መርከቦቹ በውሃው ላይ ሲሆኑ፤ ያሬዳውያኑ ንፁሕ አየር እንዲገባ የጫፉን ቀዳዳ መክፈት ይችላሉ። ውሃ መግባት ከጀመረ፤ ቀዳዳውን እንደገና መዝጋት ይችላሉ።

የያሬድ ወንድም አሁንም መርከቦቹ ውስጥ ብርሃን እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃል። ብርሃንን ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ፀለየ እና ጠየቀ።

የቅዱሳን መጻሕፍት ውይይት

ኢተር 2፥23ን ድምፅዎን ከፍ አድርገው ያንብቡ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ለያሬድ ወንድም ያለውን ይግለጹ። ጌታ የያሬድን ወንድም በጫነት መርከቦቹ ውስጥ ብርሃን እንዲኖር ጌታ ምን እንዲያደርግ እንደፈለገ ጠየቀው። መስኮቶች ሊኖሩ አይችሉም፤ ስለሚሰበሩ፤ እና ሕዝቦቹ እሳትን ሊጠቀሙ አይችሉም (ኢተር 2፥23ን ይመልከቱ)። ኢየሱስ ለያሬድ ወንድም መልስ እንዳልሰጠው ነገር ግን በዚያ ፈንታ ምን ዓይነት ዕርዳታ እንደሚፈልግ እንደ ጠየቀው ይግለጹ።

- የያሬድን ወንድም ብትሆኑ ኖሮ ልታስቡ የምትችሉት አንዳንድ መፍትሔዎች ምንድን ናቸው?

የቅዱሳን መጻሐፍት ታሪክ እና ዓላማዎቹ

የያሬድ ወንድም ወደ ተራራ እንደሄደ እና አስራ ስድስት ትንንሽ፤ ንፁህ ከአለት የወጡ ድንጋዮችን እንዳቀለጠ ይግለጹ።

ትኩረታቸውን ወደ አሳዩአቸው ድንጋዮች (ወይም የወረቀት ድንጋዮች) ይመልሱ። ያዘጋጃቸው ድንጋዮች እንደ ብርጭቆ ነጭ እና ንፁህ፤ እንደነበሩ ይግለጹ።

የያሬድ ወንድም ድንጋዮቹን ወደ ተራራ ጫፍ ይዞ ሄደ እና ፀለየ። በፀሎቱ ጌታ ድንጋዮቹን ከነካ፤ ብርሃን እንደሚሰጡ እንደሚያውቅ ተናገረ። በዚህ መንገድ ባህሩን ለማቋረጥ ሲነዱ መርከባቸው ውስጥ ብርሃን ሊኖራቸው ይችላል። ፀሎቱን ከጨረሰ በኋላ፤ አንድ ግሩም ነገር ተከሰተ።

የቅዱሳን መጽሐፍት ንባብ

ኢተር 3፥6ን ለክፍሉ ያንብቡ (*ጣት* ከሚለው ቃል ከመጀመሪያው ምሳሌ በኋላ ያቁሙ)። ጌታ እጁን ዘርግቶ ድንጋዮቹን አንድ በአንድ በጣቱ እንደነካ ይግለጹ።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ድንጋዮቹን ያደረገው ምንድን ነው? (በጣቱ ነካቸው።)

ስዕል እና የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ

ስዕል 3-55ን ያሳዩ፤ የያሬድ ወንድም የጌታን ጣት አየ።

የያሬድ ወንድም የኢየሱስ ክርስቶስ ጣት ድንጋዮቹን መንካቱን ሲመለከት፤ በጣም ስለተደነቀ መሬት ላይ ወደቀ። ለምን መሬት ላይ እንደወደቀ ጌታ ሲጠይቀው፤ የያሬድ ወንድም የጌታ ጣት የሰውን እንደሚመስል አላውቅም ነበር አለ። ከዚያም ኢየሱስ ጌታ የተናገራቸውን ቃሎች በሙሉ ያምን እንደሆነ የያሬድን ወንድም ጠየቀው። የያሬድ ወንድም አዎን ሲል፤ ጌታም በታላቅ እምነቱ ምክንያት፤ ጌታ እራሱን ለእርሱ ማሳየት እንደሚችል ነገረው። ከዚያም ኢየሱስ ለያሬድ ወንድም እራሱን አሳየ እና እርሱ እንደነበረው እምነት ዓይነት አንድም ሰው አሳይቶ እንደማያውቅ ነገረው።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለያሬድ ወንድም እራሱን ያሳየው ለምንድን ነው? (ምክንያቱም የያሬድ ወንድም ከፍተኛ እምነት ስለነበረው።)

የጃሬድ ወንድም ኢየሱስ ክርስቶስ ድንጋዮቹን ከነካ፣ በስምንቱ የጭነት መርከቦች ውስጥ ብርሃን እንደሚሰጡ እንደሚያውቅ፣ እናም እንደሆነ ይግለጹ።

ጃሬዳውያንም በኢየሱስ ክርስቶስ ከፍተኛ እምነት ነበራቸው። ጃሬዳውያን ወዲያውኑ በመርከባቸው ተሳፈሩ። በእርሱ ባላቸው እምነት ምክንያት፣ ወደ ቃልኪዳኑ ምድር በደህና ተመሩ።

### እንደ ጃሬድ ወንድም ዓይነት እምነት ሊኖረን ይችላል

የመምህሩ ትምህርት አቀራረብ

ሰዎች ዛሬ የጃሬድን ወንድም ዓይነት እምነት ሊኖራቸው እንደሚችል ይግለጹ። እምነት በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እና መመካት ማለት ነው። በመታዘዝ እና በመፀለይ እምነታችንን እናሳያለን። ለትክክለኛ ነገር በእምነት ከጠየቅን፣ ጸሎታችን ሊመለስልን እንደሚችል ቃል ተገብቶልናል (ሞዛያ 4፥21 ይመልከቱ)።

የእምነት አንቀፅ

ልጆቹ አራተኛውን የእምነት አንቀጽ የቻሉትን ያህል እንዲሉ ይርዷቸው።

የቅዱሳን መጻሐፍት ውይይት

ትምህርት እና ቃልኪዳን 29፥6ን ለክፍሉ ያንብቡ። እርሱ እንዳዘዘን በጸሎት በመተባበር፣ በእምነት የጠየቅነውን ማንኛውም ነገር እንደምንቀበል ጌታ መናገሩን ይግለጹ።

ወደ ሰማይ አባታችን ስንፀልይ እምነት እንደምንፈልግ ይግለጹ። በእምነት ከጠየቅነው ፀሎታችንን ሊመልስ የሰማይ አባት ቃል ገብቶልናል። ፀሎታችንን መፀለይ ብቻ በቂ አይደለም። ጥሩ በሆነው መንገድ ፀሎታችንን እንደሚመልስ ማመን ያስፈልገናል።

ሁኔታዎች እና ውይይት

የሚከተለውን የግምት ሁኔታዎች ለክፍሉ ያንብቡ። በእያንዳንዱ ሁኔታ ውስጥ ዋነኛው ባሕሪ እምነትን እንዴት እንደሚያሳይ ልጆቹ እንዲነግርዎት ያድርጉ።

1. ባርት የCTR ቀለበቱ በትምህርት ቤት መጫወቻ መሬት ላይ ጠፋበት። በዚያ ሁሉ ኮረት እና አሸዋ ውስጥ ለማግኘት የሚችልበት ዕድል እንደሌለው፣ የቅርብ ጓደኛው፣ ጂም ነገረው። ባርት ተጨማሪ ዕርዳታ እንደሚያስፈልገው ያውቃል። ቀለበቱን ማግኘት ፈለገ። የዚያን ዕለት ማታ ፀለየ እና የሰማዩ አባትን ዕርዳታ ጠየቀ። ፀሎቱን ሲጨርስ፣ ቀለበቱን ለማግኘት ከሰማይ አባት፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ እና ከመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታን እንደሚያገኝ ተሰማው እናም በውስጡ ጥሩ ስሜት ነበረው። በሚቀጥለው ቀን ቀለበቱን አገኘ።
   - በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነት ለማሳየት ባርት ያደረገው ምንድን ነበር?
   - የባርት እምነት የተመለሰው እንዴት ነበር?
2. ሴሊ በሚቀጥለው እሁድ በጀማሪ ክፍል ንግግር እንድታደርግ ተጠይቃ ነበር። ከዚህ በፊት ይህን አድርጋ አታውቅም፣ እናም በጣም ፈርታ ነበር። በሳምንቱ ውስጥ ሴሊ ንግግሯን በማዘጋጀት በጣም ለፋች። እሁድ ሲመጣ፣ አሁንም ስለፈራች ንግግሯን ስለመስጠቷ እርግጠኛ አልነበረችም። ልክ ከቤት ከመውጣቷ በፊት፣ በአልጋዋ አጠገብ በመንበርከክ የሰማይ አባት ለመረጋጋት እንዲረዳት ጠየቀች። ለንግግሩ በጣም እንደለፋች ታውቃለች፣ እና የሰማይ አባት እንደሚረዳት ተሰማት።
   - ሴሊ እምነት ለማሳየት ያደረገችው ምን ነበር?
   - እምነቷ የተመለሰው እንዴት ይመስላችኋል?

በእምነት ከጠየቁት ጸሎታቸው እንደሚመለስ ልጆቹን ያስታውሷቸው። አንዳንዴ ፀሎታችን እኛ በፈለግነው መንገድ አይመለስም። በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነት ካለን፣ ለእኛ ጥሩ የሆኑት መልሶች እንደሚሰጡን እናውቃለን።

#### ማጠቃለያ

ጨዋታ

በትምህርቱ ያሳዩአቸውን ድንጋዮች ወይም ወረቀቶች በመጠቀም የሚከተለውን ጨዋታ ተጫወቱ። ፊደሉን ቃላቶች ለመገመት ልጆቹ ተራ እንዲወስዱ ያድርጉ። አንድ ልጅ በድንጋዮቹ ላይ ካሉት ፊደሎች አንዱን በግምት ካወቀ፣ ፊደሉን ለማሳየት ያንን ድንጋይ ይገልብጡት። አንድ ልጅ በጨዋታው ውስጥ ሁለቴ ያለውን አንድ ፊደል ከመረጠ፣ ሁለቱንም ድንጋዮች ይገልብጧቸው ሁሉም ንባብ "እምነት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለው ሁሉም ሐረግ

ተገልፆ እስከሚያልቀ ድረስ ጨዋታውን መጫወታችሁን ቀጥሉ። ሀረጉን ከክፍሉ ጋር ያንብቡ፤ ከዚያም የሚከተለውን ጥያቄ ይጠይቁ፥

- በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እምነታችንን ልናሳይ የምንችልባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

የአስተማሪ ምስክርነት

በእምነት ስንጠይቀ የሰማይ አባት ፀሎታችንን እንደሚሰማን እና እንደሚመልስልን ምስክርነትዎን በመስጠት ትምህርቱን ያጠቃሉ። ስለተመለሰልዎ ፀሎት የግል ልምድዎን ማካፈል ይችላሉ። ልጆቹ እምነታቸውን እንዲያጠነክሩ ያበረታቷቸው።

- የጃሬድ ወንድም እምነቱን ያጠነከረው እንዴት ነው? ( መልሶቹ የሚያጠቃልሉት፥ ለእርዳታ በመጸለይ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በመስማት፤ የተሰጠውን ትዕዛዛት በማመን እና በማክበር ነው።)

በጀማሪ ክፍል መጨረሻ፤ የጭነት መርከቡን ስዕሎች ለልጆቹ ይመልሱ እና ወደ ቤት ይዘው መሄድ ይችላሉ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፤ በ “የአስተማሪው መረጃዎች” “የክፍለ ጊዜን” በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።

1. ለእያንዳንዱ ልጅ እንደ ጃሬድ ወንድም እምነት እንዲኖራቸው በትምህርቱ ውስጥ ከተጠቀማችኋቸው ድንጋዮች አንዱን እንደ ማስታወሻ ይስጧቸው። እያንዳንዱ ልጅ በድንጋዩ ላይ *እምነት* የሚለውን ቃል እንዲጽፍ ይፈልጉ ይሆናል።

2. ልጆቹ አራተኛውን የእምነት አንቀፅ የመጀመሪያውን ክፍል እንዲደግሙ ያድርጉ፥ “የወንጌል የመጀመሪያው መሰረተ ሃሳቦች እና ስርዓቶች፥ መጀመሪያ፤ እምነት በኢየሱስ ክርስቶስ” እንደሆነ እናምናለን።

3. “እምነት” የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ወይም ቃሎቹን በድርጊት ለማለት ከልጆች ጋር ይቁሙ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፤ ገፅ 96)፥

   እምነት ፀሐይ እንደምትወጣ ማወቀ ነው፤ (እጆችን በጭንቅላት ላይ ግማሽ ክብ ማድረግ)
   ሁሌ እንደምታበራ። (እጆች በቀስታ ወደ ትከሻ አካባቢ ይወርዳሉ)
   እምነት ፀሎቴን (እጆችን ለፀሎት እንደምናደርገው ማጣመር)
   ጌታ እንደሚሰማኝ ማወቀ ነው። (እጆችን ከጀሮ በኋላ መክበብ)
   እምነት እንደ ትንሽ ዘር ነው፥ (ግራ እጅን ጎድጎድ ማድረግ እና በቀኝ እጅ ዘር የምትዘራ በማስመሰል ማሳየት)
   ከተዘራ፤ ያድጋል። (ቀኝ እጅ ተክሉ ከጎረጎደው ግራ እጅ እያደገ እንደሆነ ያስመስላል)
   እምነት በልቤ ሙሉ ነው። (እጆችን ልብ ላይ አስቀምጡ)
   መልካምን፤ (የቀኝ አመልካች ጣትን ወደ ላይ ማመልከት)
   አውቃለሁ። (በቀን አመልካች ጣት ጭንቀላትን መንካት)

4. ለልጆቹ ዘርን ያሳዩ። ሲተከል እና እንክብካቤን ሲያገኝ ምን እንደሚከሰት ልጆቹን ይጠይቋቸው። እያንዳንዱ ልጅ ዘሩን በአፈር በተሞላ የወረቀት ኩባያ ውስጥ እንዲተክል መርዳት ይችላሉ። ተክሎቹ ሲበቅሉ በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ልጆቹ ለተክሎቹ እንክብካቤ እንዲያደርጉላቸው ሙከራ ይስጧቸው።

   - ይህ ዘር እንዲያድግ ለመርዳት ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?

   እነዚያ ዘሮች በሚገባ እንክብካቤን ሲያገኙ እንደሚያድጉ እምነት እንዳለን ይግለጹ። በተመሳሳይ መንገድ፤ ትዕዛዛቱን ከጠበቅን እና በእምነት ከፀለይን የሰማይ አባት ፀሎታችንን እንደሚመልስም እምነት አለን።

ትምህርት

# 30

# ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዳችንን ይወደናል

**ዓላማው** ኢየሱስ ክርስቶስ በየትም ቦታ ያሉ ልጆችን እንደሚወድ እና እንደሚባርክ ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የማርቆስ ወንጌል 10፥13–16 እና 3ኛ ኔፊ 17 ያንብቡ እና በፀሎት ያጥኑ።
2. እንደሚታየው ለእያንዳንዱ ልጅ የሚታደል ጽሑፍ ያዘጋጁ፥

   ኢየሱስ
   ክርስቶስ
   ይወደኛል

3. የሚከተሉትን የቃላት ጽሑፎች ያዘጋጁ፥

   | ሆላንድ |
   | ፊጂ |
   | ሜክሲኮ |

4. የሚከተሉትን አቀማመጦች በዓለም ካርታ ላይ ለማመልከት ይዘጋጁ ሀ) ሀገርዎን፣ (ለ) ኢየሩሳሌምን፣ (ሐ) አሜሪካንን፣ (መ) ሆላንድን (ኒዘርላንድን)፣ ሠ) ፊጂን፣ እና (ረ) ሜክሲኮን።
5. "በዓለም ሁሉ ያሉ ልጆች" የሚለውን መዝሙር ለማስተማር ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 16)።
6. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. የሚከተሉት ተቀርጦ የወጡ ስዕሎች ልጆች በትውልድ ሃገራቸው የአለባበሳቸውን ታሪኮች ለማብራራት ነው፥ የደች ወንድ ልጅ (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-7)፣ የፊጂ ሴት ልጅ (ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-8)፣ ሁለት የሜክሲኮ ወንዶች ልጆች (3-9 እና 3-10 ተቀርጦ የወጡ ስዕሎች)።
   ለ. ስዕል 3-56፣ ክርስቶስ እና ልጆች (62467፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 216)፣ ስዕል 3-57፣ ኢየሱስ ኔፊዎች ልጆች ሲባርክ፣ እና ስዕል 3-58፣ የዓለም ካርታ፣ ወይም ከተገኘ የአለም ሉል።
7. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅቶች ያድርጉ።

**ለትምህርቱ እድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድን ነገር እንዲያደርጉ ካዘዟቸው ይከታተሏቸው።

**ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ልጆች ይወዳል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ስዕል 3-58፣ የዓለምን ካርታ የሚለውን ያሳዩ፣ እና የሚኖሩ ሀገር ያመልክቱ። ስለ ሌሎቹ በዓለም ውስጥ ስላሉት አንዳንድ ሃገሮች እንዲማሩ እንደሚፈልጉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። (ከሚከተሉት ምሳሌዎች አሁን ከምትኖሩበት ሀገር አንዱ ከሆነ፣ ሌላ ሀገር ይምረጡ።)

"ሆላንድ" የሚለውን የቃላት ጽሑፍ እና ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-7ን የሳዩ። ሆላንድን (ኔዘርላንድን) በካርታ ላይ አመልክት። አብዛኛውን የዚህ ሀገር መሬት በአንድ ወቀት በውሃ ተሸፍኖ እንደነበር ይግለጹ። ሕዝቦቹ ውሃውን በመግፋት ውሃው እንዲወጣ ግድቦችን ሰሩ። የውሃውን መወገድ ለማካሄድ በአንድ ወቀት የንፋስ ወፍጮዎችን ይጠቀሙ ነበር። ሕዝቦቹ ቱሊፕ የሚባለውን ተክል እና ሌሎች ቆንጆ ቆንጆ አበባዎችን በማሳደግ የታወቁ ነበሩ። በእርሻ አካባቢዎች እና በአሳ ማጥመጃ መንደሮች ያሉ አንዳንድ ሰዎች *ክሎምፐን* የሚባል የእንጨት ጫማዎችን ያደርጋሉ። እነዚህ ጫማዎች በጠንካራ ወለሎች ወይም በሌሎች ቦታዎች ላይ ድምፅ ያሰማሉ፣ ነገር ግን ከቆዳ ጫማዎች የበለጠ የሰዎቹን እግር ከእርጥብ መሬት ይከላከላሉ።

"ፊጂን" የሚለውን የቃላት ጽሑፍ እና ተቀርጦ የወጣ ስዕል 3-8ን ያሳዩ። ፊጂን በካርታው ላይ ያመልክቱ። በፊጂ ያሉ ልጆች በውቅያኖስ በተከበበ መሬት ላይ እንደሚኖሩ ይግለጹ። ሕዝቦቹ ሙዝ፣ ኮኮናት፣ እና ሸንኮራ አገዳን ይተክላሉ። ሞቃታማው የአየር ጠባይ በጣም ይመቻል። አንዳንድ ሰዎች ይህንን ቆንጆ የፀሐይ መውጫ መሬት ብለው ይጠሩታል፣ ፊጂያውያኖች ግን ሃገራቸውን የደስታ ደሴት ብለው ይጠሯታል፣ ምክንያቱም ሰዎቹ ደሴት ሃገራቸውን የሚወዱ ይመስላሉ።

"ሜክሲኮ" የሚለውን የቃላት ጽሑፍ እና ተቀርጦ የወጣ 3-9ን እና 3-10ን ያሳዩ። ሜክሲኮን በካርታው ላይ ያመልክቱ። በሜክሲኮ ያሉ ሰዎች ስፓኒሽኛ እንደሚናገሩ ይግለጹ። ከረጅም ጊዜ በፊት በቆሎ እንዴት እንደሚተክሉ ተማሩ፣ እና በጣም አስፈላጊው ምግባቸው ሆነ። ከገና በዓል በፊት በዘጠነኛው ሌሊት፣ ጓደኛሞች እና ጎረቤታሞች ይሰበሰቡ እና የማርያምን እና የዮሴፍን ጉዞ ወደ ቤተልሔም በድርጊት ያሳያሉ። ቀጥሎ፣ ልጆቹ ፒናታ የሚባለውን ጨዋታ ይጫወታሉ። ፒናታ ማለት ከሸክላ ወይም ከወረቀት የተሰራ መያዣ ወይም በእንስሳ ቅርፅ ተሰርቶ በከረሜላ፣ በፍራፍሬ፣ እና በአሻንጉሊቶች የተሞላ እንደሆነ ይግለጹ። አይናቸው በተሸፈነ ልጆች፣ ራስ ላይ ይሰቀል እና ፒናታውን በዱላ መትቶ ለመስበር ተራ ይይዛሉ። ፒናታው ከተሰበረ በኋላ፣ ከረሜላውን እና ሌሎቹን ዕቃዎች ይሸከማሉ።

በእነዚህ በተለያዩ ሃገሮች የሚኖሩ ልጆች በአንዳንድ መንገዶች አንድ ዓይነት እና በሌሎች ነገሮች የተለያዩ እንደሆኑ ይግለጹ። ነገር ግን ተመሳሳይ ቢሆኑም ባይሆኑም ችግር የለውም፡ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ልክ እናንተን እንደሚወዱ ይወዷቸዋል። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በየትም ቦታ ሁሉንም ልጆች ይወዳሉ እናም ይጠብቃሉ።

መዝሙር

"በዓለም ሁሉ ያሉ ልጆች" የሚለውን መዝሙር ለልጆቹ ያስተምሯቸው። አንደ ወይም ሁለቴ በሙሉ እንዲዘምሩት ወይም እንዲሉት ያድርጉ።

በዓለም ሁሉ በመጨረሻው ቀን፣
የሰማይ አባት ልጆች ይፀልያሉ፣
ሁሉም በራሳቸው የተለየ መንገድ
እናመሰግንሀለን እያሉ።
"ግራሲያስ።" "ማሎ።" "ቪር ዳንከን ዲር።"

በዓለም ለስላሳ ድምጾች ይሰማሉ።
አንዳንዶቹ "ታክ፣" ሌሎቹ "ሚርሲ፣"
"ካንሻ ሺማሱ፣" እናመሰግንሀለን።

የሰማይ አባታችን ይሰማቸዋል፣
እያንዳንዱን ቋንቋ ያውቃል።
የሰማይ አባታችን ያውቃቸዋል፣
ይወዳቸዋል፣ ይወዳቸዋል፣ ሁሉንም።

ስዕል እና የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ

ስዕል 3-56 ክርስቶስ እና ልጆች የሚለውን ያሳዩ፣ እና በዓለም ካርታ ላይ ኢየሩሳሌምን ያመልክቱ። ይህ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የኖረበት እንደነበረ ይግለጹ። የኢየሱስን፣ የሐዋሪያቱን፣ እና በማርቆስ ወንጌል 10፥13–16 ላይ የሚገኘውን የሕፃናት ልጆች ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፣ የሚከተሉትን ነጥቦች ይጠቁሙ፥

1. ብዙ ህዝቦች ሲያስተምር ለመስማት በኢየሱስ ዙሪያ ተሰበሰቡ።
2. አንዳንድ ሰዎች ልጆቻቸውን እንዲባርክላቸው ወደ ኢየሱስ ማምጣት ፈለጉ።
3. ሐዋሪያቶች ስለ አዳኝ ደህንነት ስለተጨነቁ፣ ልጆቹን ማስወጣት ፈለጉ።
4. ኢየሱስ ለሐዋሪያቶች ልጆቹን እንዲያመጡ ነገራቸው።
5. ኢየሱስ ልጆችን ይወዳቸዋል እንዲሁም ይባርካቸዋል።

ስዕል እና የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ

ስዕል 3-57፣ ኢየሱስ የኔፊዎችን ልጆች ሲባርክ፣ የሚለውን ያሳዩ። እና በዓለም ካርታ ላይ አሜሪካንን ያመልክቱ። የሚከተለውን ታሪክ ከ3ኛ ኔፊ 17 ላይ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

ኢየሱስ ክርስቶስ ከተሰቀለ እና ከተነሳ እንዲሁም ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ፣ በአሜሪካ የኔፊ ህዝቦችን ጎበኛቸው እና ብዙ አስፈላጊ ነገሮችን አስተማራቸው።

ኢየሱስ የመሄጃ ጊዜው ሲደርስ፣ ህዝቦቹ ስለወደዱት እና ለእነርሱ ያለው ታላቅ ፍቅር ስለተሰማቸው ማልቀስ ጀመሩ። ብዙ እንዲቆይ ፈለጉ።

በሕዝቦቹ እምነት እና ፍላጎት ምክንያት፣ አዳኝ ብዙ ቆየ።

ከዚያም ኢየሱስ ለአባቶች እና ለእናቶች ሕፃናት ልጆቻቸውን ወደ እርሱ እንዲያመጡ ነገራቸው። ወዲያው ህፃናቶቹ ሁሉም በኢየሱስ ዙሪያ ተሰበሰቡ።

አንድ በአንድ በእጆቹ እየወሰደ ባረካቸው። ከዚያም ለልጆቹ ወደ ሰማይ አባታችን ፀለየ።

ከዚያም በኋላ ለአባቶች እና ለእናቶች፣ "ሕፃናቶቻቸውን እንዲመለከቱ ነገራቸው (3 ኔፊ 17፥23)። ወላጆቻቸው ሲመለከቱ፣ ሰማያት ተከፈቱ፣ መላእክቶች ወረዱ፣ ልጆቹን ከበቧቸው፣ እና በመሃከላቸው ሄዱ።

ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም እና በአሜሪካን ያሉትን ልጆች እንደወደደ እና እንደባረከ፣ በዛሬ ጊዜ በዓለም ሁሉ ያሉትንም ልጆች እንደሚወድ እና እንደሚባርክ ይግለጹ።

**ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬ ይወደናል እናም ይባርከናል**

ተቆርጠው የወጡ ስዕሎች እና ታሪክ

በትውልድ ሃገራቸው አለባበስ የልጆችን ተቆርጦ የወጣ ስዕል ያሳዩ። በተለያዩ ሃገር ስላሉ ልጆች ታሪኮች እና በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደተባረኩ ልጆቹ እንዲያዳምጡ እንደሚፈልጉ ይግለጹ።

አንድ ልጅ ተቆርጦ የወጣው የደች ወንድ ልጅን ስዕል በዓለም ካርታ ላይ ከሆላንድ አጠገብ እንዲለጥፍ ይርዱት። ከዚያም የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

"የአስራ አንድ ዓመቱ ዮሐንስ ሩዞፍ በሆላንድ፣ በሮተርዳም ይኖር ነበር። በአንድ ወቅት ትምህርት ቤት እና ቤተክርስቲያን በመሄዱ፣ ከጓደኞቹ ጋር በመጫወቱ፣ እና አንድ ወንድ ልጅ የሚደሰትበትን ነገሮች በሙሉ በማድረጉ ደስተኛ ነበር። ከዚያም፣ አሰቃቂ የአይን በሽታ የአይን ብርሃኑን እንዲያጣ አደረገው። ከዚያ በኋላ ትምህርት ቤት መሄድ ወይም ማንበብ አቆመ። ከጓደኞቹ ጋር እንኳን ለመጫወት ማየት አልቻለም። እያንዳንዱ ቀን በጨለማ እና በስቃይ የተሞላ ነበር።

“ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ኤፍ ስሚዝ በሆላንድ ያሉትን የኋለኛው ቀን ቅዱሳንን ሊጎበኙ ይመጣሉ የሚለው ወሬ ደርሶ ነበር። ዮሐንስ ስለዚህ ነገር ለብዙ ጊዜ አሰበበት፣ እና ከዚያም ለእናቱ—ወደ ስብሰባው ይዘሽኝ ከሄድሽ አይኖቼን ማየት ስለሚችል፣ እንደምድን አምናለሁ አላት።

“በሚቀጥለው እሁድ በስብሰባው መዝጊያ ላይ፣ ፕሬዚዳንት ስሚዝ ሰዎቹን ሰላም ለማለት እና የእያንዳንዱን እጅ ለመጨበጥ ወደ ትንሹ የፀሎት ቤት በስተኋላ ሄዱ። እህት ሩዞፍ ዮሐንስን ረዳችው፣ አይኑ ታሽጓል፣ ተወዳጅ መሪያቸውን ለማነጋገር ከሌሎች ጋር ሄደ።

“ፕሬዚዳንት ስሚዝ የታወረውን ልጅ በእጃቸው ወስደው በታላቅ ርሕራሔ ፋሻውን አንስተው በህመም የተሞሉትን የዮሐንስ አይኖች ተመለከቱ። ነቢዩም ዮሐንስን ባርከውት እንደገና ማየት እንደሚችል ቃል ገቡለት።

“ቤት ሲደርስ፣ የዮሐንስ እናት ዶክተሮች እንደነገሯት ልታጥበው ፋሻዎቹን ከዓይኖቹ ላይ አነሳች። ይህንን ስታደርግ ኦ፣ እናቴ፣ አይኖቼ ድነዋል። አሁን በደንብ ማየት እችላለሁ—እና በርቀትም አያለሁ፣ ምንም ሕመምም አይሰማኝም! በማለት ዮሐንስ በደስታ አለቀሰ!” (“President Smith Took him by The Hand,” *Friend,* Aug. 1973, p. 36)።

- በዮሐንስ የተከሰተው ምንድነው? (ነቢዩ እንደገና እንዲያይ ባረከው፣ እና የሰማይ አባት አዳነው።)
- የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀራቸውን ለዮሐንስ ያሳዩት እንዴት ነው?

### ተቀራርጠው የወጡ ስዕሎች እና ታሪክ

አንድ ልጅ ተቀርጦ የወጣውን የሜክሲኮ ልጆችን ስዕል በካርታው ላይ ከሜክሲኮ አጠገብ እንዲለጥፍ ይርዱት። የልጆቹ ስም ሚጉዌል እና ቶማስ እንደሆነ እና እናታቸው የምትተዳደረው ለሌሎች ሰዎች ልብስን በማጠብ እንደሆነ በመግለፅ ታሪኩን ያስተዋውቁ፣

“አንድ ቀን [እናታቸው] አጠባውን አስረክባ ስትመጣ፣ ተስፋ ቆርጣ ነበር። በጣም ሰርታ ነበር፣ ነገር ግን የዚያን ቀን ማንም ሊከፍላት አልቻለም ነበር፣ እናም ዳቦ የምትገዛበት ምንም ገንዘብ አልነበራትም። ልጆቹ ማታ ለእራት ትንሽ ዳቦ ከበሉ ጊዜ ጀምሮ ምንም ስላልበሉ ምን ያህል እንደተራቡ ታውቃለች። ሚጉዌል፣ የሚባለው ታላቀየው፣ እስከዚያን ጊዜ እርቧት፣ ለምን በቂ ምግብ እንዳልበላች በጣም ትንሽ ልጅ በመሆኗ ለመረዳት ለማትችለዋ፣ ማሪያ፣ ትንሹን ዳቦውን አካፈላት። ቶማስ እናትየው እንዳልበላች አወቀና የዳቦውን ግማሽ ሰጣት።

“ሚጉዌል እና ቶማስ መርዳት ፈለጉ። ሚጉዌል ስለ ኢየሱስ [ክርስቶስ] ሕዝቦቹን ለዕርዳታ እንዲጸልዩ ያስተማራቸውን እናቱ የነገረችውን ታሪክ አስታወሰ። ሚጉዌል እና ቶማስ እርዳታን ይፈልጋሉ፣ ስለዚህ በአንድነት ተንበርክከው ፀለዩ። ከፀለዩ በኋላ፣ ሚጉዌል እና ቶማስ ወደ አንድ ዳቦ ቤት ሄዱ እና ሲኞር አሎንዛን አንዳንድ ነገሮችን በመላላክ ለእርሱ መሥራት ይችሉ እንደሆነ ጠየቁት። ሲኞር አሎንዞ፣ ወንዶቹ ልጆች ምን ያህል እንደተራቡ ባለማወቅ፣ እነርሱ የሚሰሩት ምንም ስራ እንደሌለው ተናገረ። ስራ መፈለጋቸውን ቀጠሉ። ሲመሽ ጥቂት ገንዘብ አገኙ ነገር ግን በቂ አልነበረም።

“ሁለቱ ቅር የተሰኙት እና የተራቡት ወንዶች ልጆች ወደ ቤታቸው አመሩ። በመንገድ ላይ ሲኋዙ፣ በአጠገባቸው ቢስክሌቱን እየነዳ አንድ ሰው አለፈ። ተጋጨ፣ እና የሆነ ነገር ከቅርጫቱ ውስጥ ወደቀ። ሚጉዌል ተከትሎት ሮጦ እንዲቆም ጠራው፣ ሰውየው ግን ዝምብሎ ሄደ። ቶማስ ምን እንደወደቀ ለማየት ጥቀሉን አነሳ። ትኩስ ዳቦ ነበር። ወደ ሲኞር አሎንዛ ዳቦ መጋገሪያ በፍጥነት ተመለሰው የሆነውን ገለፁለት። ሲኞር አሎንዞ ሰውየው ማን እንደሆነ አስታውሶ በሚቀጥለው ጊዜ ወደ መደብሩ ሲመጣ ሌላ ዳቦ እሰጠዋለሁ አለ። ከዚያም በትንሹ የተጎዳውን ዳቦ በግማሽ ዋጋ እንደሚሸጠው ለልጆቹ ነገራቸው። ሚጉዌል እና ቶማስ በፍጥነት ገንዘባቸውን ቆጠሩ፣ በቂ ነበራቸው። ልጆቹ ዳቦውን ገዝተው በፍጥነት ወደ ቤታቸው ሄዱ።

“እናትየው ዳቦውን በማየቷ ተደነቀች። ልጆቹ ፀሎታቸው እንዴት እንደተመለሰ ገለጹ። የዚያን ዕለት ማታ የተራበው ቤተሰብ ተንበረከከ እና ለሚበሉት ምግብ ለ[ሰማይ አባት] ምስጋናን ሰጡ” (*Walk in His Ways Basic Manual for Children, Part B* [1979], p. 25)።

- የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ሚጉዌል እና ቶማስን የረዱት እንዴት ነበር? (ፀሎታቸውን በመመለስ።)

*የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ*

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ልጆችን በዓለም ውስጥ በሚኖሩበት በየትኛውም ቦታ ሁሉ እንደሚባርኳቸው ለልጆቹ ይግለጹ። እውነተኛው የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በዓለም ሁሉ አንድ ዓይነት ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ልጆች በአለም ዙሪያ ሁሉ አንድ ዓይነት መዝሙር የሚዘምሩበት እና አንድ ዓይነት ትምህርት የሚሰሙበትን ጀማሪ ክፍል የመሳተፍ ዕድል እንዳላቸው ይግለጹ። በዓለም ሁሉ፣ ከእናንተ ክፍል ጋር ተመሳሳይ ዕድሚ ያላቸው ልጆች ትክክለኛውን መምረጥን ለማስታወስ እንዲረዳቸው CTR ቀለበት ያደርጋሉ። በቤተክርስቲያኑ ያሉ ልጆች የትም ቦታ ቢኖሩ ስምንት ዓመት ሲሆናቸው ይጠመቃሉ። በቤተክርስቲያኑ የፀሎት ቤት በመጠመቂያ ገንዳ ውስጥ፣ በበረዷማ ሐይቅ፣ በውቅያኖስ፣ ወይም በትንሽ ወንዝ ወይም ኩሬ መጠመቅ ይችላሉ፣ ነገር ግን ጥምቀታቸው ሁልጊዜ በመነከር እና የክህነት ስልጣን ባለው አንድ ሰው ዘውትር ይከናወናል።

**ማጠቃለያ**

ጥቅስ እና የአስተማሪ ምስክርነት

2ኛኔፊ 26፥23፣ "ሁሉንም ወደ እርሱ እንዲመጡ ጋበዘ" ከሚሉት ቃላት በመጀመር ለልጆቹ ያንብቡ። ጌታ ሁሉም ሰው ወደ እርሱ እንዲመጣ እና ቸርነቱን እንዲካፈሉ፣ ፤ ነጭ ቢሆኑም ጥቁር፣ በእስራት ወይም በነፃነት፣ ወንድ ወይም ሴት ወደ እርሱ የሚመጡትን ማንንም ሳይቀበል እንዳልቀረ ይግለጹ። እግዚአብሄርን የማያውቁትን አስታወሰ፣ እናም አይሁዳዊ እና አህዛብ፣ ለእርሱ ሁሉ አንድ ዓይነት ናቸው (2ኛኔፊ 26፥33 ይመልከቱ)። ከዚያም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳቸው እንዴት እንደሚያውቁ ልጆቹ በተራ እንዲነግሩዎ ያድርጉ።

የሰማይ አባት ምንም ቢሆኑ፣ ወይም የሚኖሩበት ቦታ፣ ወይም የትኛውም ዓይነት ቤት ውስጥ ቢኖሩ፣ ወይም የጸጉራቸው፣ የዓይናቸው፣ ወይም የቆዳቸው ቀለም የትኛውም ዓይነት ቢሆን ሳይገድበው ሁሉንም ልጆች እንደሚወድ ምስክርነትዎን ይስጡ። የሰማይ አባት ሁላችንም ደስተኞች እንድንሆን እና ዳግም ከእርሱ ጋር ለመኖር እንድንመለስ ይፈልጋል።

መዝሙር

"በዓለም ሁሉ ያሉ ልጆች" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃሉን እንዲሉ ያድርጉ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ጸሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

የሚታደል ጽሁፍ

"ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደኛል" የሚለውን የሚታደል ጽሑፍ ሲዬዱ ለልጆቹ ይስጧቸው። ልጆቹ ኢየሱስ በዓለም ሁሉ ልጆችን ስለመውደዱ የተማሩትን ለቤተሰቦቻቸው እንዲነግሩ ይጋብዟቸው።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የክፍለ ጊዜ" "የአስተማሪው መርጃዎች" በሚለው ውስጥ ይመልከቱ።

1. ባዶ የለስላሳ መጠጥ ጠርሙስ ያምጡ። ልጆቹን ወለሉ ላይ በክብ አስቀምጧቸው። ጠርሙሱን ካሽከረከሩት በኋላ፣ ይቆም እና ወደ አንዳቸው እንደሚያመለክት ይንገሯቸው። ያ ልጅ ኢየሱስ እንደሚወደው የሚያሳየውን አንድ ነገር ይጠራል። ከዚያም ያ ልጅ ጠርሙሱን ያሽከረክራል። ተራ የደረሰውን ከክቡ ትንሽ ወደ ኋላ ዞር እንዲል በመጠየቅ ለእያንዳንዱ ልጅ ተራ ለመስጠት ይሞክሩ።

2. የሚከተለውን ግጥም እና ድርጊቶች ለልጆቹ ያስተምሯቸው፣

   ኢየሱስ ትንንሽ ልጆችን ይወዳል

   አንዳንድ ልጆች አቧራ መንገድ ላይ ይሮጣሉ፣ (በቦታው ይሩጡ)
   በትንንሽ እግሮቻቸው እየፈጠኑ፣ ( ወደ እግሮች ያመልክቱ)
   በተጨናነቀ ሕዝብ መሐል ቦታ ለመፈለግ (በተጨናነቀ ሕዝብ መሐል ቦታ እንደሚፈልግ ክርኖቻችሁን አውጡ)
   ወደ ኢየሱስ ቀረቡ፣ ፊቱን ለማየት። (በእግራችሁ ጣቶች ቁሙ እና ዙሪያውን ተመልከቱ)
   አንዳንድ አዋቂዎች፣ "አስወጧቸው" አሉ። (እጆቻችሁን ከደረቶቻችሁ ወጣ አድርጉት)
   "ዛሬ ከልጆች ጋር ለመሆን አይችልም።" (ግንባሩን ኮስተር አደረገና ነቀነቀው) ነገር ግን ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ተዋቸው ወደ እኔ ይምጡ። (በእጅ ተጣሩ)" ያባቴ መንግስት የእነርሱ ነው እና በእሱ እና በእኔ ተወደዋል።"(ራሳችሁን እቀፉ)

3. በእድሚያቸው ከፍ ካሉ ካደጉ ልጆች ጋር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ያለውን ፍቅር የሚያሳየውን የሚከተሉትን መሠረተ ሀሳቦች መወያየት ይፈልጉ ይሆናል። የምንኖርበትን ቦታ ሳይገድብን እነዚህ በረከቶች ለሁላችንም እንደሚገኙ ያሳስቡ።

   - ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለመምራት ትዕዛዛትን ሠጥቶናል።
   - የሚመሩን ነቢያት አሉን።
   - ኢየሱስ ክርስቶስ ለኛ ኃጢአቶች ስለተዋዠ ንስሐ መግባት እንችላለን።
   - የክህነት ስልጣን በረከቶችን መቀበል እንችላለን።

4. ከፍ ከፍ ካሉት ልጆች ጋር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ

4. ልጆቹ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዳቸው የሚያሳየውን አንድ ነገር በስዕል እንዲስሉ እና ቀለም እንዲቀቡት ያድርጉ (እንደ ቤተሰብ፣ ዛፎች፣ አበባዎች፣ ወይም እንሰሳዎች የመሳሰሉትን)።

5. ልጆቹ በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ ለአንድ ሰው የደግነት ተግባርን እንዲያደርጉ እና ምን እንደሆነ ለክፍሉ ለመናገር እንዲዘጋጁ ያበረታቷቸው። ከተቻለ፣ ይህንን በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ ሊያስታውሷቸው ይፈልጉ ይሆናል።

ትምህርት

# 31

# ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው እንድንወድ ይፈልጋል

**ዓላማው** ልጆቹ ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ በዘለዓለማዊነት ያላቸውን ጥቀም እንዲያውቁት ሌሎችን በመርዳት ፍቀርን ማሳየት እንደሚችሉ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው

**ዝግጅት**

1. የዮሐንስ ወንጌል 13፥34ን እና 3ኛ ኔፊ 17፥18–25ን በፀሎት ያጥኑት።
2. ልጆቹ "እርስ በእርስ ተዋደዱ" የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገጽ 136፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተ ጀርባ ተጠቃለዋል) እናም "ያንን ጣፋጭ ታሪክ ሳነብ አስባለሁ" (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 56)።
3. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፥
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ጥቁር ሰሌዳ፣ ጠመኔ እና ማጥፊያ።
   ሐ. ስዕል 3-57፣ ኢየሱስ የኒፋይቶችን ልጆች ሲባርክ።
4. ለምትጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

**ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ሰው እንድንወድ ይፈልጋል**

የአትኩሮት ተሳትፎ ለአንድ ሰው ደግነትን ለማሳየት በቀርቡ ያደረጉትን እንዲናገሩ ልጆች ይጋብዟቸው (ትምህርት 30፣ አበልፃጊ ተሳትፎ 5ን ይመልከቱ)።

- ለሌሎች ደግ ስትሆን እንዴት ይሰማሃል?
- የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን እንድንከባከብ ያዘዙን እንዴት ነው?

የጥቀስ ውይይት መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞንን ከፍ በማድረግ ይያዙ። ቅዱሳን መጽሐፍት ሌሎች ሰዎችን እንዴት መንከባከብ እንዳለብን እንደሚያስተምሩ ይግለጹ።

የዮሐንስ ወንጌል 13፥34ን ድምጾን ከፍ በማድረግ ያንብቡ።

- ይህ ጥቀስ ምን እንድናደርግ ነው የሚነግረን? (እርስ በእርስ እንድንዋደድ።)

ይህ ትዕዛዝ በቀዱሳን መጻሐፍት ብዙ ጊዜ ስለተደጋገመ እርስ በእርሳችን መዋደድን መማራችን ጠቃሚ መሆኑን አጥብቀው ያሳስቡ። የሰማይ አባት እያንዳንዱን የራሳችንን ቤተሰብ እንድንወድ እንደሚፈልግ ሁሉ፣ ሁሉንም ልጆቹን እንድንወዳቸው ይፈልጋል።

መዝሙር "እርስ በእርስ ተዋደዱ" የሚለውን መዝሙር ዘምሩ ወይም ቃላቶቹን በሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎችን እንድንወድ እንደሚፈልግ አጥብቀው ያሳስቡ።

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት *ፍቅር* የሚለውን ቃል በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀሩን ለሌሎች ያሳየው በምን ዓይነት መንገድ ነው? (የልጆቹን መልሶች በጥቁር ሰሌዳ ላይ መጻፍ ይፈልጉ ይሆናል።)

የኢየሱስን ምሳሌ በመከተል እና እርሱ ያስተማረንን በማድረግ ለሌሎች ያለንን ፍቀር በምን ዓይነት መንገድ ነው ማሳየት የምንችለው? (እነዚህን መልሶች በጥቁር ሰሌዳው ላይ ከቀድሞው ጥያቄ ዝርዝር በመቀጠል መፃፍ ይፈልጉ ይሆናል።)

## ለኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል እንደሆንን እንድናውቅ ቅዱሳን መጽሐፍት ይረዱናል

ስዕል፣ ጥቅስ እና ውይይት

ኢየሱስ ክርስቶስ ኒፋይቶችን በአሜሪካ በጎበኘ ጊዜ፣ ተደስተው እና በእርሱ ፊት በመገኘታቸው ተከብረው እንደነበረ ግለጹ። በአጠገቡ መሆንን እና ትምህርቱን ማድመጥን ወደው ነበር።

ኢየሱስ የኒፋይት ልጆችን ሲባርክ የሚያሳየውን ስዕል 3-57 ያሳዩ።

3ኛ ኔፊ አዳኝ ኒፋይቶችን ስለ መጎብኘቱ እንደሚነግረን አስረዱ። አንድ በአንድ ትናንሽ ልጆቻቸውን ወሰደ እና ባረካቸው እናም ስለ እነርሱ ወደ አብ ዘንድ ፀለየ። (3ኛ ኔፊ 17፥21 ይመልከቱ)።

ስዕሉን አመልክቱ እና የሚከተለውን ጠይቁ—

- በዚህ ስዕል ላይ ትንሿ ልጃገረድ የተሰማት እንዴት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

ልጆቹ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ከተሠበሠቡት ልጆች ጋር እንዳሉ አድርገው እራሳቸውን እንዲገምቱ ይጠይቋቸው።

- ኢየሱስ እጆቹን በራሳችሁ ላይ ቢጭንባችሁ ምን ይሰማችኋል?

መዝሙር

ልጆቹ "ያንን ጣፋጭ ታሪክ ሳነብ አስባለሁ" የሚለውን መዝሙር ሁለቱንም ቁጥር እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ አድርጉ።

የኢየሱስን ታሪክ ሳነብ አስባለሁ፣
እንዴት ሕፃናትን እንደጠራ፣
ኢየሱስ ከሰዎች ዘንድ ሳለ፣
ጠቦቶቹን ወደ በረቱ እንደሚጠራ፣
ከእርሱ ጋር መሆንን ተመኘሁ።

እጆቹን በራሴ እንዲጭን ተመኘሁ፣
በክንዶቹም እንዲያቀፉኝ፣
ሩህሩህ አስተያየቱን እንዳይ
ሕፃናትን ወደ እኔ ኑ ሲል

## ሌሎች ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ጥቅም እንዲሰማቸው መርዳት እንችላለን

ታሪክ

ማርክ መወደዱ እንዲሰማው ሌኒ እንዴት እንደረዳው ልጆቹ እንዲያዩ የሚከተለውን ታሪክ እንዲሰሙ ይጠይቋቸው፥

ሪች እና ጀሪ በመቸኮል በጓዳ በር ሲገቡ. . . ሌኒ ምሳውን እየጨረሰ ነበር።

" 'እንሂድ!' በማለት ሪች አሳሰበ . . .

"ነገር ግን፣ ዶሌኒ ጓደኞቹ የተሸከሙትን የቤዝ ኳስ መሳሪያን ሲመለከት፣በመደነቅ እንዲህ አለ፣ 'ከሰዓት በኋላን ከማርክ ጋር የምናሳልፍ መስሎኝ ነበር።'

" 'ያ ይህንን ጨዋታ ከማግኘታችን በፊት ነበር። ቀኑን በዝምታ! ማሳልፍ በጣም መልካም ነው!'

"ሌኒ ሰሃኑን እና ብርጭቆውን በማጠቢያው ውስጥ ሲያስቀምጥ አመነታ።

"ጓደኞቻቸው፣ ማርክ ዊልሰን፣ ከሆስፒታል ገና መውጣቱ ነበር። ከብዙ ወራት በፊት [በጣም ታሞ ነበር] ። [ሃኪሞች] ማርክ እንደገና እንደሚሮጥ እና እንደሚጫወት እርግጠኞች ነበሩ ነገር ግን ትንሽ ሊቆይ ይችላል አሉ። ከበሽታው በፊት፣ ማርክ በቡድናቸው —[ይጫወት ነበር]።"

ሌኒ ውሳኔ መወሠን እንደነበረበት ይግለጹ። ከዚያም ታሪኩን ይቀጥሉ፥

" 'ሌኒ፣ ና! እንሂድ!' በማለት ሪች ድርቀ አለ። ነገር ግን ሌኒ እራሱን ነቀነቀ።

" 'ለማርክ እናት እንደምመጣ ቃል ገብቻለሁ፣ ብሎ ነገራቸው። 'እናንተ ልጆች ከፈለጋችሁ ሂዱ።'

“ ‘ነገር ግን ሌኒ’ ተቃወሙ፣ ‘አንተ ካሉን ጥሩ ተጫዋች አንዱ ነህ።’

“ ‘አዝናለሁ፣’ አለ ሌኒ በጥብቅ።

“ሪች በመሰልቸት አኮረፈ።

“ ‘ቡድኑን ተበድለዋለህ ብዬ በፍፁም አስቤ አላውቅም! . . .’

“ወንዶቹ ልጆቹ ወጥተው [ሄዱ] በኋላ፣ ሌኒ ፎቁ ላይ እናቱን ህፃኑን ከምታስተኛበት በመጥራት አላት። ቻዎ

“ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሌኒ ወደ ማርክ ቤት በርጋታ አዘገመ. . . . ሌኒ በእውነት መጫወት ፈልጎ ነበር. . . . ቡድኑንም በመዳከሙ በጣም ጥሩ ነገር አልተሰማውም፣ ነገር ግን ስለ ማርክ ሀዘን ተሰማው። እነዚያ ረዥም ጊዜያት በሆስፒታል ለእርሱ ብዙም የዋዛ አልነበሩም።

“ ‘ሪች እና ጄሪ የት ናቸው?’በማለት ሌኒን እንዲገባ ስትጋብዘው የማርክ እናት ጠየቀችው።

“ ‘መምጣት አልቻሉም፣’ (አለ) ሌኒ።

“የማርክ እናት ተነፈሰች እናም ሌኒ በቀንጆው አይኖቿ ዙሪያ ያለውን የድካም መስመር ማየት ይችል ነበር። የማርክ በሽታ ለቤተሰቦቹም ከባድ ነበር። ከዚያም ‘ነገር ግን ሌኒ፣ አንተ እዚህ በመሆንህ ደስተኛ ነኝ ስትል ፈገግ አለች። ማርክም እየጠበቀ ነው።’

“ሌኒ ማርክ የገረጣ እና ትንሽ ያዘነ መሆኑን አስተዋለ። በአንድ እግሩ እብጠት ነበረው፣ ነገር ግን ታላቅ ጥረት በማድረጊ ሌኒን ለመገናኘት መራመድ ችሎ ነበር።

“ወይዘሮ ዊልሰን ወንዶቹን ልጆች ለብቻ በመተው ለመነጋገር ሳሎን ቤት አረፍ አሉ። ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ማርክ ዝም አለ እና ሌኒ በፀደይ ከሰዓት በመስኮት ወደ ውጪ ይመለከት እንደነበር አወቀ።

“ ‘አባባ አንድ ቀን እንደገና ትጫወታለህ ብሎኛል። ‘በእርግጥ በቀርቡ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ’ አለ በተስፋ።’

“ወዲያውኑ ሌኒ አንድ ሀሳብ ተፈጠረበት።

“የማርክን እናት ለመፈለግ ወደ ማዕድ ቤት በመጣደፍ፣ “ቶሎ እመለሳለሁ በማለት፣ የማርክን መንፈስ በመቀስቀስ አረጋገጠለት።

“ ‘ጨዋታ ለመጫወት የሚቀጥለው የተሻለው ነገር አንድን ነገር መመልከት ነው፣’ ሌኒ ዕቅዱን ከነገራት በኋላ አብራራ።

“ ‘ለምን እንደማይሰራ አይታየኝም፣ ሌኒ፣’ አለች፣ ለማርክ ‘ብዙ መልካም ነገሮችን ያደርግለታል ብዬ አስባለሁ!

“ለሌኒ ደስታዋ ሊሰማውም ይችላል። ወደ ሜዳው ለመድረስ ያሉት አራቱ ክልሎች . . . ለማርክ በእግሩ ሄዶ ለመሄድ ሩቅ እንደሆኑ ስለሚያውቅ ወደ ጋራዥ ሄደ እና የማርክን . . . ሰረገላ አወጣ።

“ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ሌኒ በሰረገላው ማርክን ወደ ሜዳው ገፋው። ሲደርሱ አንዳንዳንዶቹ ወንዶች ልጆች ሲደርሱ በመደነቀ ተመለከቷቸው፣ ነገር ግን ወዲያው ማርክን ሠላም ለማለት ወደ እርሱ መጡ።

“ ‘አንተ [ትጫወታለህ]?’ በማለት ከእነርሱ አንዱ ሌኒን ጠየቀው።

“ ‘አዎን . . .! በማለት ማርክ አስታወቀ።

“ሪች በፍርሃት ወደፊት መጣ ጄሪም ከኋላው ተከተለው።

“አሁን እየተጫወትኩ አይደለም፣ ሌኒ፣’ በማለት ጄሪ ቀረብ አለ፣ እና ከማርክ ጋር አወራለሁ፣ አለ።”

“ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማርክ በፍፁም ብቻውን ሆኖ አያውቅም እናም ጄሪ እና ሪች ስለነበራቸው ሁኔታ እንዳዘኑ ሌኒ ያውቃል።

“የሚያስደንቅ ጨዋታ ነበረ ካበቃም በኋላ ሊኒ ከሰረገላው አጠገብ ሲራመድ ጀሪ እና ሪች ማርክን ወደ ቤት [ለመግፋት] ተራ በተራ ተነሱ” (Eva Gregory de Pimrentg “Bad Weather Friends,” *Friend,* Apr. 1975, pp. 8–10)።

- ማርክ ተወዳጅ እና ተፈላጊ መሆኑ እንዲሰማው ሊኒ የረዳው እንዴት ነው?
- ማርክ ወደ ጨዋታው ሲመጣ ሌሎቹ ወንዶች ልጆች የተንከባከቡት እንዴት ነው?

ታሪክ

ልጆቹ የሚከተለውን ታሪክ እንዲያዳምጡ ጠይቋቸው፥

ሊሊኒ እና ቤተሰቧ ወደ ዋርዱ ከሌላ አገር ገና መዛወራቸው ነበር። ሊሊኒ ወደ ጀማሪ ክፍል ስትመጣ፣ በክፍሏ ያሉት ልጆች በአለባበሷ እና አነጋገሯ ያፌዙባት ነበር። ብቻዋን በመቀመጥ እንዳልተቀበሏት ተሰማት።

የወንድም ሃርማን የጀማሪዎች ክፍል ትምህርት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሁሉም እንዴት ደግ እንደነበር እና እያንዳንዱ ተወዳጅነት እና ዋጋ እንዳለው እንዲሰማው እንዴት ሲያደርግ እንደነበረ ነው። ካረን፣ ከሊሊኒ የክፍል ጓደኞች አንዷ፣ እርሷ እና ሌሎቹ ሊሊኒን ስለ ተንከባከቡበት ሁኔታ መጥፎ ስሜት ተሰማት።

- ሊሊኒ መወደዷ እንዲሰማት ካረን ምን ማድረግ ትችላለች?

ካረን ስለ ሊለኒ ፍላጎት እና ተሰጥዎ ለማወቀ ወሠነች። አነጋገረቻት እና ሊሊኒ በሂሳብ በጣም ጎበዝ መሆኗን አወቀች። ካረን በሂሳብ ችግር ስላላት፣ ሊሊኒ አብረው ማጥናት ይችሉ እንደሆነ ጠየቀቻት። ሊሊኒን በቋንቋ ትምህርቷ ተረዳታለች ሊሊኒም በሂሳብ ተረዳታለች። አብረው ሲያጠኑ፣ ብዙ ተመሳሳይ ነገሮችን ማድረግ እንደሚወዱ አወቁ፣ ጥሩ ጓደኛሞችም ሆኑ።

ውይይት

- ሊሊኒ ተፈላጊነት እንዲሰማት ካረን የረዳቻት እንዴት ነው?

ሌሎችን ስለራሳቸው መልካም እንዲሰማቸው ለመርዳት ብዙውን ጊዜ ከባድ ጥረት እንደማይወስድ ይግለጹ። ለእነርሱ መልካም በመሆን እና ለሌሎች ጥቅም ያላቸው እንደሆኑ ለእነርሱ በማሳየት ልናደርገው እንችላለን።

ሁኔታዎች

የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይግለጹ፣ እና ልጆች እንዲወያዩበት ያድርጉ። እያንዳንዱን ሁኔታዎች ልጆቹ እንዲጫወቱ ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል ከዚያም እንዴት እንደተሰማቸው ለክፍሉ እንዲያካፍሉ ይጠይቋቸው።

1. ከጓደኞችህ ጋር በጓሮህ የወፍ ጎጆ እየሰራህ ነው። ትንሽ ወንድምህ መጥቶም ሊረዳህ የሚችል ከሆነ ይጠይቀሃል።
   - ወንድምህ ስለራሱ ጥሩ እንዲሰማው ለማድረግ ምን ማድረግ ትችላለህ፣ ታደርጋለህ? (ሚስማር እና ሳንቃ በቦታው በመያዝ እንዲረዳህ ፍቀድለት።)
   - ትንሹ ወንድ ልጅ አንተ ብትሆን እና ትልቁ ወንድምህ የወፍ ጎጆ ለመስራት እንድትረዳው ቢፈቀድልህ ምን ይሰማሃል?
2. የጀማሪ ክፍልዎ የአገልግሎት ፕሮጀክት አቀደዋል። ከሄዘር በስተቀር እያንዳንዱ የራሱን ወይም የራሷን ሃሳብ ይሰጣሉ። ስለምታፍር ብዙም አትናገርም። ወዲያውኑ ሄዘር መናገር ትጀምራለች፣ ነገር ግን በአንድ ሰው ስለተቋረጠች ልትናገር የነበረውን መጨረስ አልቻለችም።
   - ስለ ሔዘር ማሰብህን እና ጠቃሚ መሆኗ እንዲሰማት መፈለግህን ለማሳየት ምን ማድረግ ትችላለህ?
   - ሔዘርን ብትሆን እና አንድ ሰው ለምትናገረው ነገር ዋጋ እንደሰጠው ሲያሳይህ እንዴት ይሰማሃል?
3. ከትምህርት ቤት ውጪ እየተጫወትክ ነው፣ እናም አንዳንድ ልጆች ለሌላው ልጅ በጨዋታቸው እንዳይጫወት ሲነግሩት ታያለህ። ለዚያ ልጅ ክፉ ይሆናሉ።

- ለዚያ ወይም ልጅ ጠቃሚ መሆናቸውን ለማሳየት ምን ታደርጋለህ?
- ሌሎች ልጆች እንድትጫወት ሳይፈቀዱልህ አንድ ሰው እንድትጫወት ቢጠይቅህ እንዴት ይሰማሃል?

4. በጀማሪ ክፍልህ ውስጥ አዲስ ልጃገረድ አለች፤ እናም ከሌሎቹ የክፍል ልጆች በተለየ ሁኔታ ስለምትለብስ አንዳንድ ልጃገረዶች ያሾፉባታል።
   - አዲሷ ልጃገረድ ተፈላጊነት እና ተቀባይነት እንዲሰማት ለማድረግ ምን ታደርጋለህ?
   - በቤተክርስቲያን አዲስ ብትሆን እና አንድ ሰው ሊያነጋግርህ ጊዜ ቢወስድ እና የእንኳን ደህና መጣህ ስሜት እንዲሰማህ ቢያደርግ እንዴት ይሰማሃል?

ሌሎች ለእኛ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆኑ በየዕለቱ ለማሳየት ሁላችንም ብዙ ዕድሎች እንዳሉን ለልጆቹ ንገሯቸው።

**ማጠቃለያ**

የግል ልምድ እና ምስክርነት

አንድ ሰው ያዳመጠዎት ወይም አትኩሮት የሰጠዎትን እና ጥሩ እንዲሰማዎት ያደረገበትን ጊዜ መናገር ይፈልጉ ይሆናል። ለምሳሌ፤ በክፍልዎ ያለ ልጅ በመደብር ወይም በመንገድ ፈገግታ ሲሰጥዎት እና እጁን ሲያውለበልብልዎት እንዴት ጥሩ ስሜት እንዲሰማዎት እንዳደረገ መናገር ይችላሉ።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እያንዳንዳችንን እንደሚወዱን ምስክርነትዎን ይስጡ። ለእነርሱ ከፍ ያለ ዋጋ ያለን ነን። ለእኛ የሚያደርጉልን ማንኛውም ነገር እኛን ለመርዳት ነው። ከእነርሱ ጋር ለዘለዓለም ለመኖር ሁላችንም ወደ እነርሱ እንድንመለስ ይፈልጋሉ። ሌሎችን በመውደድ እና በዙሪያችን ያሉት በእኛ እና በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ዋጋ እንዳላቸው እንዲሰማቸው ማድረግ ልንረዳቸው እንችላለን።

ልጆችን አንድ ሰው ስለራሳቸው መልካም እንዲሰማቸው ያደረገበትን ወይም አንድን ሌላ ሰው ተወዳጅነት እና ዋጋ እንዳለው እንዲሰማው ያደረጉበትን ልምድ እንዲያካፍሉ ይጋብዟቸው።

የእምነት አንቀፅ

እንደ ቤተክርስቲያን አባልነት፤ ለሁሉም ሰው መልካምን በማድረግ እንደምናምን ለልጆቹ ይንገሯቸው። ይህ የአስራ ሶስተኛው የእምነት አንቀፅ ክፍል መሆኑን ይግለጹ።

ልጆቹ የሚከተለውን ሐረግ ከእርሶ ጋር እንዲደግሙት አድርጉ፣ “ለሁሉም ሰው መልካምን በማድረግ . . .እናምናለን።”

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ሰው ተወዳጅነት እና ስለራሱ ጥሩ እንዲሰማው ለማድረግ እንዲሞክሩ ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ጋብዙ።

---

**አስፈላጊ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በደንብ ይሰራል የሚሉትን ተሳትፎዎች ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።


1. ከልጆቹ አንዱ በክፍሉ መካከል ላይ በወንበር ላይ እንዲቀመጥ በማድረግ ልዑል ወይም ልዕልት በፊት ላይ የተቀመጡ እንዲያስመስሉ አድርጉ። ሌሎቹ ልጆች ስለ እርሱ ወይም እርሷ የሚያስቡትን መልካም የሆነውን ማንኛውንም ጥሩ ነገር ሲናገሩ፣ ልዕልቷ ወይም ልዑሉ መናገር አይፈቀድላቸውም። ምናልባት “ጥሩ ፈገግታ አላት”፣ “የፀጉሩን ቀለም እወደዋለሁ”፣ “በክፍል ውስጥ ስርዓት አላት”፣ “ከለር ከእኔ ጋር ይዋዋሳል፣” የመሳሰሉትን ነገሮች ማለት ይችላሉ። ለልዑሉ ወይም ለዕልቲቱ ቀለል ያለ ዘውድ ያድርጉላቸው። ለእያንዳንዱ ልጅ ልዑል ወይም ልዕልት የመሆን ተራ ይስጡዋቸው።

2. ጥሩ አድማጭ መሆን ሌሎች ዋጋ እንዳላቸው እንዲያውቁ እንደሚረዳ ይግለጹ። ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ፣ ልጆቹ ሳያቋርጡ ቀርበው ማዳመጥ አለባቸው። ልጆቹ የሚከተለውን ታሪክ በደንብ እንዲያዳምጡ እና ምናልባት ሊሆን የማይችለውን ነገር ሲናገሩ እጃቸውን እንዲያነሱ ይጠይቋቸው።

   ሚቼል ቤተክርስቲያን የመሄጃ ሰዓት ከመድረሱ አምስት ደቂቃ ቀደም ብላ ተነሳች። ፈጥና ካልተዘጋጀች፣ ልክ ከአልጋ እንደወጣች በመምሰል መሄድ ይኖርባታል። በፍጥነት ወደ መታጠቢያ ቤት ሮጠች እና ፊቷን በእህል ታጠበች። ወደ መኝታ ክፍሏ ተመልሳ ስትሮጥ፣ በመደናቀፍ የእንስሳት አሻንጉሊቶቿ ላይ ቆመች "ሚቼል፣ ከሁለት ደቂቃ በኋላ ነው የምንሔደው፣" በማለት አሻንጉሊቷ ከፍ ባለ ድምፅ ተጣራች። ሚቼል በፍጥነት ልብሷን አበጠረች ለበሰችም፣ ምርጥ የሆነውን የፀጉር ቡሩሿን አደረገች፣ እና ውጪ ሮጠች።

   ልጆቹን በጥሞና ሳያቋርጡ ስላዳመጡ ያመሰግናቸው። ከዚያም ታሪኩን ደግመው አንብቡት እና ልጆቹ ትክክል ባልሆኑት ቃላት ትክክል የሆነውን እንዲያስገቡ ያድርጉ።

3. የሲባጎ የወረቀት አሻንጉሊት ለእያንዳንዱ ልጅ ያዘጋጁ (ማብራሪያውን ይመልከቱ)። አሻንጉሊቶቹ የክፍሉን አባላት ወይም የቤተሰብ አባላትን እንዲመስሉ አድርገው እንዲቀልሟቸው ያድርጉ። መወደዳቸው እንዲሰማቸው እርስ በርሳቸው እንዴት መረዳዳት እንደሚችሉ ተነጋገሩ። (እርስ በእርስ ደግ ነገር መነጋገር፣ ሲጫወቱ ሰዎችን አለማግለል፣ ጥሩ አድማጮች መሆን፣ እና ችግር ሲኖር እርስ በእርስ መረዳዳት ይችላሉ።)



4. "ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ እንዴት ፍቀርን እንደሚያሳይ" በሚል ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው በአንደኛው ረድፍ ዝርዝር ያዘጋጁ። ከዚያም በሌላኛው ረድፍ "እኛ ለሌሎች ፍቀርን እንዴት ማሳየት እንደምንችል" በሚል ርዕስ ዝርዝር ያዘጋጁ። በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ ላሉት ጥያቄዎች ልጆቹ መልሶች ሁለት ዝርዝሮችን ይፍጠሩ። ለእያንዳንዱ ልጅ በየተራ የባቄላ ጥቅል ወርውሩ፣ የተወረወረበትም ልጅ የባቄላውን ጥቅል ወደ እርሶ መልሶ ከመወርወሩ በፊት ከዝርዝሩ ለአንዱ የሆነ ነገር ሐሳብ እንዲያቀርብ ይጋብዙት።

ትምህርት

# 32

# ቅዱስ ቁርባንን ስንወስድ ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ

**ዓላማው** ልጆቹ ቅዱስ ቁርባንን ሲወስዱ ኢየሱስ ክርስቶስን እና የጥምቀት ቃል ኪዳናቸውን ዘወትር እንዲያስታውሱ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. 3ኛ ኔፊ 18፥1–11፣ 20፥1–9፣ እና የማቴዎስ ወንጌል 26፥17–30ን ያጥኑ።
2. ብዙ ትናንሽ ነገሮችን የያዘ ቦርሳ ያዘጋጁ።
3. ከትምህርት 30 ላይ "ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ልጆች ይወዳል" በሚለው ርዕስ ሥር የኢየሱስን እና የኔፊዎችን ልጆች ታሪክ ይከልሱ።
4. "የአዳኜ ፍቀር ይሰማኛል" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መጽሐፍ*፣ ገፅ 74)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ላይ ተጠቃለዋል።
5. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. ስዕል 3-57፣ ኢየሱስ የኔፊዎችን ልጆች ሲባርክ፣ ስዕል 3-22፣ የመጨረሻው ራት (62174፣ የወንጌል የስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 225)፣ ስዕል 3-1፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀ (62133፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 208)፣ ስዕል 3-51፣ የተራራው ስብከት (62166፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 212)፣ ስዕል 3-56፣ ክርስቶስ እና ልጆች (62467፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 216)፣ ስዕል 3-10፣ የመጀመሪያው ራዕይ (62470፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 403)፣ እና ስዕል 3-59፣ ቅዱስ ቁርባንን ማሳለፍ (62021)።
   ሐ. ከተቻለ፣ የቁርባን ሰዛን ለዳቦ እና ለውሃ።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳተፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** **ቅዱስ ቁርባን ኢየሱስ ክርስቶስን እንድናስታውስ ሊረዳን ይችላል**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ጸሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

የአትኩሮት ተሳትፎ ካዘጋጁት ቦርሳ፣ አንድ በአንድ፣ አንድ ትንሽ ዕቃ ይወስዱ። እያንዳንዱን ዕቃ በአጭሩ ይግለፁ። ሲጨርሱ፣ መጀመሪያ፣ ሁለተኛ ሶስተኛ እና በመቀጠል ያወጡት የትኛውን ዕቃ እንደሆነ ልጆቹ እንዲነግርዎ ያድርጉ።

ይህ ተሳትፎ ምን ያህል በደንብ ማስታወስ እንደሚችሉ ለማየት እንደሚረዳቸው ለልጆቹ ይገለፁላቸው።

ስዕል 3-57፣ ኢየሱስ የኔፊዎችን ልጆች ሲባርክ የሚያሳየውን ያሳዩ። ስለዚህ ሁኔታ ምን እንደሚያስታውሱ ልጆቹ እንዲናገሩ አድርጉ። ለሚሉት ነገር ያመስግኗቸው።

ስዕል እና ውይይት ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ከሐዋሪያቶቹ ጋር በነበረበት ጊዜ፣ ጴጥሮስ እና ዮሐንስን ልዩ የሆነ እራት ለእርሱ እና ለአስራ ሁለቱ ሐዋሪያት እንዲያዘጋጁ እንደላካቸው ይግለፁ (የማቴዎስ ወንጌል 26፥17–30ን ይመልከቱ)።

የመጨረሻውን እራት የሚያሳየውን ስዕል 3-22፣ ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋሪያቶቹ ይህ ከእነርሱ ጋር የሚበላበት የመጨረሻው ጊዜ መሆኑን እንደነገራቸው ያስረዱ። በቀርቡም እንደሚሞት ያውቅ ነበር። እራቱም ከተበላ በኋላ፣ ኢየሱስ ከዚህ ቀደም በምድር ላይ በፍጹም ተደርጎ የማይታወቅ ነገር አደረገ። ቁዱስ ቁርባንን ባርኮ አሳለፈ። ሕብስቱን ቆረሰ እና ሲበሉት የተቆረሰውን አካሉን እንዲያስታውሱ ለሐዋሪያቶቹ ነገራቸው። ወይንም ሰጣቸው እናም በመሬት ላይ ለእነርሱ የፈሰሰውን ደሙን እንዲያስታውሱ ነገራቸው። ለዘለዓለም እንድንኖር ህይወቱን መስጠቱን ማስታወስ እንዳለባቸው ነገራቸው።

**የቅዱሳን መፃሕፍት ታሪክ**

ኢየሱስ ኔፊዎችን በጎበኘ ጊዜ፣ ቅዱስ ቁርባንም እንደሰጣቸው ይግለፁ (3ኛ ኔፊ 18፥1–11 ይመልከቱ)። በኢየሩሳሌም እንዳደረገው፣ ኢየሱስ አስራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ሕብስት እና ወይን እንዲያመጡ ላካቸው። (ዛሬ ለቅዱስ ቁርባን በወይን ፋንታ ውሃ እንደምንጠቀም ይግለፁ።) ደቀመዛሙርቶቹ ሲሄዱ፣ ኢየሱስ ለሕዝቡ በሜዳው ላይ በዙሪያው እንዲሰበሰቡ ነገራቸው።

ደቀመዛሙርቶቹ ወይን እና ሕብስት ይዘው ሲመለሱ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ህብስቱን ቆራረሰ እና ባረከው። ለእያንዳንዱ ደቀመዛሙርት የተቆረሰውን ህብስት እንዲበሉ ሰጣቸው። ከዚያም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቶቹ ለቀሩት ህዝቦች ህብስቱን እንዲያሳልፉ አዘዛቸው። ይህ ከተደረገ በኋላ፣ ኢየሱስ ወይኑን ባርኮ ለደቀመዛሙርቶች አሳለፈ እና ከዚያም ለሕዝቡ እንዲያሳልፉ አደረጋቸው። ቅዱስ ቁርባንን ለቤተክርስቲያኑ አባላት በሙሉ ለመባረክ እና ለማሳለፍ ስልጣን እንደሚሰጣቸው ገለፀ።

እንደገና፣ እያንዳንዱ ሰው ቅዱስ ቁርባንን ከወሰደ በኋላ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋሪያቶቹ በኢየሩሳሌም እንዳደረገው ዓላማውን ገለፀላቸው።

**የቅዱሳን መፃሕፍት ንባብ እና ውይይት**

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔፊዎች ቅዱስ ቁርባንን ሲሰጥ ቅዱስ ቁርባኑን ለእነርሱ ያሳያቸውን አካሉን በማስታወስ መውሰድ አለባችሁ አላቸው። ቅዱስ ቁርባን ዘወትር ኢየሱስን እንደሚያስታውሱት ለአብ ምስክርነት ይሆናል። ዘወትር እርሱን ካስታወሱ፣ መንፈሱ ከእነርሱ ጋር ይሆናል (3ኛ ኔፊ 18፥7) የሚለውን ከመፅሐፈ ሞርሞን ለልጆቹ ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ያንብቡላቸው።

- ኔፊዎች ቅዱስ ቁርባንን ሲቀበሉ ስለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰማቸው ምን ይመስላችኋል?

**በዕቃዎች ውይይት**

ቅዱስ ቁርባን ማሰላፍን፣ የሚያሳየውን ስዕል 3-59 አሳዩ።

በቅዱስ ቁርባን አገልግሎት ወቀት የሚከሰተውን ከልጆቹ ጋር ይወያዩ። የሚከተሉትን ሀሳቦች ለማቀረብ ጥያቄዎችን ተጠቀሙ፣

1. ዘወትር የቅዱስ ቁርባንን መዝሙር እንዘምራለን።
2. የክህነት ስልጣን ያላቸው (አብዛኛውን ጊዜ ካህናች) ህብስቱን ይቆርሳሉ። ለልጆቹ የሕብስቱን ማቀረቢያ ሰሃን ለልጆች ያሳዩአቸው።
3. የክህነት ስልጣን ያለው (አብዛኛውን ጊዜ አንድ ካህን) በመንበርከክ ለህብስቱ የቅዱስ ቁርባን ፀሎት ያደርጋል። (በሞሮናይ 4 እና 5 እና በትምህርት እና ቃልኪዳን 20፥77፣ 79 ላይ የሚገኘውን የቅዱስ ቁርባን ፀሎት ቃላቶች ማንበብ ይፈልጉ ይሆናል።)
4. የክህነት ስልጣን ያላቸው (አብዛኛውን ጊዜ ዲያቆናች) ሕብስቱን ያሳልፋሉ።
5. የክህነት ስልጣን ያለው (አብዛኛውን ጊዜ ካህን) በመንበርከክ ለውሃው የቅዱስ ቁርባን ፀሎት ያደርጋሉ። (ለውሃው የቁርባን ሰሃን ያሳዩ።)
6. የክህነት ስልጣን ያላቸው (አብዛኛውን ጊዜ ዲያቆናች) ውሃውን ያሳልፋሉ።

- ቅዱስ ቁርባን ሲሰጥ ማሰብ የሚገባን ስለምንድን ነው? (ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ምን ያህል እንደሚወደን።)

**በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ ይገባናል**

ውይይት

- በቅዱስ ቁርባን ወቅት ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ ምን ማድረግ እንችላለን?
- በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ስለ አዳኙ የምናስባቸው አንዳንድ ታሪኮች ምን ምንድን ናቸው?
- በቅዱስ ቁርባን ጊዜ የምናስባቸው አንዳንድ መዝሙሮች ምን ምንድን ናቸው?

በቅዱስ ቁርባን ጊዜ፣ እንድናስታውሰው እና እንድንወደው እንዲረዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምናውቀውን ነገሮች ማሰብ እንችላለን።

መዝሙር

ልጆቹ "የአዳኜ ፍቀር ይሰማኛል" የሚለውን መዝሙር ቃላቶቹን እንዲሉት ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው።

የዚህን መዝሙር ቃላቶች በሚሉበት ጊዜ ወይም ሲዘምሩት እንዴት ይሰማዎታል?

በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ስለዚህ መዝሙር ቃላቶች ቢያስቡ እንዴት ይሰማዎታል?

የስዕል ውይይት

ለልጆቹ ብዙ ስዕሎች እንዳለዎት እናም ስለ እያንዳንዱ እንዲነግርዎት እንደሚፈልጉ ይንገሯቸው። ስዕሎቹን ያሳዩአቸው እናም እያንዳንዱን ከልጆቹ ጋር በአጭሩ ይወያዩባቸው። በተቻለ መጠን እያንዳንዱን ልጅ ለማካተተ ይሞክሩ። ስዕል 3-1፣ መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀ፣ ስዕል 3-51፣ የተራራው ስብከት፣ ስዕል 3-56፣ ክርስቶስ እና ልጆች፣ እናም ስዕል 3-10፣ የመጀመሪያው ራዕይን የሚያሳዩትን ተጠቀሙ።

ልጆቹ ስለእርሱ የሚናገሩ ታሪኮችን በማስታወስ እና ምን ያህል እንደሚወዳቸው በማሰብ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማሰብ እንደሚችሉ ያስታውሷቸው።

የጨዋታ ተሳትፎ
እና ውይይት

ልጆቹ በቁርባን ወቅት እንዴት መሆን እንዳለባቸው ለማስታወስ እንዲረዳቸው ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ይንገሯቸው። በሚከተለው መንገድ በየጊዜው ሁለት ልጆች በየተራ እንዲጫወቱ ይምረጡ። በክፍሉ ፊት ለፊት እንዲወጡ ያድርጓቸው። ለእያንዳንዱ ምን ማድረግ እንዳለበት ይንገሩት። ሌሎቹ ልጆች እንዲመለከቱ ያድርጉ እና ከዚያም በቅዱስ ቁርባን ጊዜ በየትኛው መንገድ ማድረግ እንዳለባቸው ይምረጡ። ሁለቱ ተሳታፊዎች ስለምን እንደሚያስቡ እንዲናገሩ ያድርጉ። መልካሙ ባህሪ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ በአክብሮት እንዲያስቡ የሚፈቅድላቸው ለምን እንደሆነ ከልጆቹ ጋር ይወያዩባቸው።

| | |
|---|---|
| 1. ስዕልን የሚስሉ ወይም የሚያቀልሙ ያስመስሉ። | በአክብሮት በመቀመጥ ከቅዱሳን መፃሕፍት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪኮች አስብ። |
| 2. ለጓደኛህ ቀስ ብለህ የምትናገር አስመስል። | በአክብሮት ተቀመጥ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል እንደሚወድህ አስብ። |
| 3. በአሻንጉሊት የምትጫወት እና በእርሱ ድምፅ የምታሰማ አስመስል። | በአክብሮት ቅዱስ ቁርባንን ተቀበል እናም ከዚያም በአክብሮት አሳልፍ። |

**ማጠቃለያ**

የቅዱሳን መጽሐፍት
ንባብ

ልጆቹ ቅዱስ ቁርባንን ሲቀበሉ እና በቀሪው ሳምንትም ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ እንዳለባቸው ያስረዷቸው። ልጆቹ ዘወትር ኢየሱስን የሚያስታውሱ ከሆነ መንፈሱ እንደሚኖራቸው አስታውሷቸው (3ኛ ኔፊ 18፥7 ይመልከቱ)።

የአስተማሪው
ምስክርነት

ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ ስንሞክር እና ትምህርቶቹን ስንታዘዝ የሰማይ አባታችን በእኛ እንደሚደሰት ምስክርነትዎን ይስጡ። በሚቀጥለው ጊዜ ልጆቹ ቅዱስ ቁርባንን ሲወስዱ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያስቡ አበረታቷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ጋብዙ።

---

**ገንቢ**
**ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የአስተማሪ መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. ከተቻለ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን አነስተኛ ስዕሎች ያግኙ እናም በጀርባው ላይ አጠር ያለ፣ የግል ማስታወሻ ይፃፉ። ኢየሱስን እና ለእነርሱ ያለውን ፍቅር ማስታወስ በሚችሉበት ቦታ ላይ ስዕሉን ማስቀመጥ እንደሚችሉ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

2. "የኢየሱስን ታሪክ ንገረኝ" የሚለውን መዝሙር አንብቡ ወይም ዘምሩ (*የህፃናት የመዝሙር መፅሀፍ*፣ ገፅ 57)።

    የኢየሱስን ታሪክ ንገረኝ መስማት እወዳለሁ፣
    እዚህ ቢኖር እንዲነግረኝ የምጠይቀውን
    የመንገድ ዳር ትርኢት፣ የባህሩን ታሪክ፣
    የኢየሱስን ታሪኮች፣ ለእኔ ንገረኝ።

    ኦ፣ ልጆች በዙሪያው እንዴት እንደቆሙ ላዳምጥ።
    በላዬ የሚያርፈውን በረከት ልመልከት፣
    ደግነትና ፀጋን የሞላው ስራዎቹ
    ሁሉም በፍቅር ብርሃን በኢየሱስ ፊት።

    ባህሩን እንዴት እንዳረጋጋው ንገረኝ
    በገሊላ በወጀቡ ጀልባውን ሲቀዝፍ
    ጌታ፣ እንዴት ዝግጁ ቀን እንደሆነ፣
    ማዕበሉን ፀጥ ሲያሰኝ ንፋሱን ሲያቀም

3. በሚቀጥለው ጊዜ ቅዱስ ቁርባን ሲያልፍ ስለ ኢየሱስ የሚያስበውን አንድ ነገር እያንዳንዱ ልጅ ክፍሉን ሲለቀ በጆሮዎ እንዲነግርዎት ይጋብዙ። በጆሮ ቀስ ብሎ መናገር ሌሎች የሚሉትን ዝም በቀላሉ እንዳይደጋግሙ ያደርጋል እናም ክፍሉን ሲለቁ በአክብሮት እንዲለቁ ይረዳቸዋል።

4. ኢየሱስን በማስታወስ ስለተጠቀመው ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ልጆቹ እንዲያዳምጡ አድርጉ፣

    "ስኮት እና ቤተሰቡ ወደ አንድ አዲስ ከተማ ገና መዛወራቸው ነበር። በአዲሱ ቤት የመጀመሪያው ቀን የስምንተኛው ዓመት ልደቱ ነበር፣ ነገር ግን እንደቀድሞው አብረውት የሚጫወቱ ጓደኞች አልነበሩትም እናም ቀድሞ እንደነበረው ከቀድመ ዓያቶቹ ወይም ከአጎቱ እና ከአክስት ልጆቹ የሚጠይቀው አልነበረም።

    "እናቱም፣ 'አትጨነቀ፣ ስኮት፣ ትምህርት ቤት በሚቀጥለው ሳምንት ይጀምራል እናም ብዙ አዲስ ጓደኞችን ታፈራለህ አለች።'

    "ትምህርት ቤት ተከፈተ፣ ነገር ግን ስኮት የበለጠ ብቸኝነት ተሰማው። ወንዶቹ ልጆች በሙሉ የራሳቸው ጓደኞች ያላቸው ይመስላል። አንድ ላይ ይሳሳቃሉ እናም ይቀልዱ ነበር። ነገር ግን ስኮት ከእነርሱ ጋር እንዲሆን አልተጋበዘም። ዳር ሆኖ ይመለከት ነበር። ሁልጊዜ ትምህርት ሲያልቅ፣ ወደ ቤት ለብቻው በእግሩ ይጓዛል. . . .

    "ስኮት በኋላ ይህን የብቸኝነት ጊዜ መለስ ብሎ በማየት እንዲህ አለ፣ "ወደዚህ ከመምጣቴ በፊት፣ የጀማሪ ክፍል አስተማሪዬ ትንሽ፣ በፎቶ ማስቀመጫ ውስጥ ያለ የኢየሱስን ስዕል ሰጥቶኝ ነበር። ይህን ከአልጋዬ አጠገብ አስቀመጥኩት። ሁልጊዜ ይህን ስዕል ስመለከት፣ ጥሩ ይሰማኛል። ኢየሱስ ልጆችን እንደሚወድ አስታውሳለሁ። እንደሚወደኝ ይሰማኛል እና እንዴት እንደተሰማኝ ያውቃል" (የቤተሰብ የቤት ምሽት መምሪያ ቁጥር 1 [1972] ገፅ 140)።

    - ኢየሱስን ማስታወስ ስኮትን የረዳው እንዴት ነው?
    - ክርስቶስን ማስታወስ እንዴት ሊረዳን ይችላል?

5. ልጆቹ ለአንድ ደቂቃ ፀጥ ብለው እንዲቆዩ እና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያስቡ ይጠይቋቸው።

6. "ስለ ኢየሱስ ማሰብ" የሚለውን መዝሙር አንብቡ ወይም ዘምሩ (*የልጆች የመዝሙር መፅሀፍ*፣ ገፅ 71)።

   በእርጋታ መቀመጥ ከባድ አይሆንም፣
   ስለ ኢየሱስ ማሰብ፣ መስቀሉን በኮረብታ፣
   ስለ እኔ የተሰቃየውን እናም ያረገልኝን፣
   በፀጥታ መቀመጥ ከባድ አይሆንም

   አዝማች፥
   ከባድ አይሆንም፣ ትንሽም ብሆን፣
   ስለ ኢየሱስ ማሰብ፣ በጭራሽ አያስቸግርም።

# ቅዱስ ቁርባን ቃልኪዳናችንን ያስታውሰናል

ትምህርት
33

**ዓላማው** ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ የጥምቀት ቃልኪዳናቸውን እንዲያስታውሱ እንደሚረዳቸው ልጆቹ እንዲገነዘቡ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ሞሮናይ 4፥3 እና 5፥2 ያንብቡ
2. ልጆቹ ሶስተኛውን የእምነት አንቀፅ እንዲሉ እና እንዲያውቁ ለመርዳት ይዘጋጁ።
3. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ት.ም. አርማ እና ቀለበት።
   ሐ. ስዕል 3-13፣ ልጁ ሲጠመቅ (62018)፣ ስዕል 3-59፣ ቅዱስ ቁርባን ሲያልፍ (62021)፣ ስዕል 3-9፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (62572፣ የወንጌል ኪነጥበብ ስዕል ጥራዝ 240)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት አድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**የቅዱስ ቁርባን ፀሎት የጥምቀት ቃልኪዳናችንን ያስታውሰናል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ልጆቹ በጥሞና እንዲያዳምጡ ይንገሯቸው። በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ማሰብ ወይም ማድረግ ስላለባቸው ነገሮች አንድ ነገር ከተናገሩ ቀና ብለው መቆም አለባቸው። በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ማድረግ ወይም ማሰብ ስለሌለባቸው ነገር ከተናገሩ፣ ማጎንበስ አለባቸው።

ለልጆቹ እንዲመልሱ ጊዜ በመስጠት አንድ በአንድ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያንብቡ።

1. የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወዱን አስታውሱ። (ቁሙ)
2. ሽርሽር ስለመሄድ አስቡ። (አጎንብሱ)
3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሽተኞችን እንደፈወሰ አስታውሱ። (ቁሙ)
4. አጠገባችሁ ላለው ሰው ቀስ ብላችሁ ሹክ በሉ እና ተናገሩ። (አጎንብሱ)
5. ተቁነጥነጡ በወንበር አካባቢ ተንቀሳቀሱ። (አጎንብሱ)
6. ወደ ሰማዩ አባት ፀልዩ። (ቁሙ)
7. ስዕሎችን ሳሉ ወይም በአሻንጉሊት ተጫወቱ። (አጎንብሱ)
8. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ታሪኮችን አስታውሱ። (ቁሙ)

የስዕል ተሳትፎ

ስዕል 3-13፣ ልጁ ሲጠመቅ፣ እና ስዕል 3-59፣ ቅዱስ ቁርባን ሲያልፍ የሚያሳየውን ስዕል ያሳዩ። ልጆቹ ለመጨረሻ ጊዜ ቅዱስ ቁርባን የወሰዱበትን ጊዜ እንዲያስቡ ይጠይቋቸው። በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ያደረጉትን እና ያሰቡትን ለማስታወስ እንዲሞክሩ ያድርጓቸው። የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለራሳቸው እንዲመልሱ ይንገሯቸው፣ ድምጽ በማሰማት አይሁን፥

- በቅዱስ ቁርባን ጊዜ በአክብሮት ተሞልተህ ነበርን?
- በቅዱስ ቁርባን ወቅት ስለ ሰኛኝ ታስባለህ?
- የቅዱስ ቁርባንን ፀሎቶች ቃላቶችን ታዳምጣለህ?

**መጽሐፍ ቅዱስ እና ውይይት**

ሞሮናይ 4፥3ን ድምፅዎን ከፍ በማድረግ አንብቡ እና ልጆቹ ቅዱስ ቁርባንን ሲወስዱ ለሰማዩ አባት የሚገቡትን ሁለት ቃልኪዳኖች እንዲሰሙ አድርጉ። እነዚህን ሁለት ቃልኪዳኖች ለማውጣት እንዲረዳቸው ቃላቶቹን እንደ አስፈላጊነቱ አብራሩዋቸው።

እኛ ለ—ቃል እንገባለን

1. ዘወትር ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ። (አንድ ልጅ) ስዕል 3-9 ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያሳየውን እንዲያሳይዎ ያድርጉ።)
2. ትዕዛዛትን ለመታዘዝ። (አንድ ልጅ) የት.ም. አርማ እና CTR ቀለበት እንዲያሳይ ያድርጉ። ት.ም. ምንን እንደሚያመለክት ከልጆቹ ጋር ይከልሱ።)

የሚገቡትን ሁለት ቃልኪዳኖች ለመስማት በየሳምንቱ የቅዱስ ቁርባንን ፀሎቶች በጥሞና እንዲያዳምጡ ልጆቹን ያበረታቷቸው፣

1. ዘወትር ኢየሱስ ክርስቶስን አስታውስ።
2. ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ።

እነዚህ ስንጠመቅ የገባናቸው አይነት ቃልኪዳኖች እንደሆኑ ይግለፁ። ልጆቹ እነዚህን ሁለት ቃልኪዳኖች ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እንዲደግሙት ያድርጉ። የሰማዩ አባታችን ለእርሱ የገባነውን ቃልኪዳን እንደምንጠብቀ እንደሚያምነን ይግለፁ፣ እናም የሰማዩ አባት ለኛ የገባውን ቃልኪዳኑን ዘወትር እንደሚጠብቅ እናውቃለን።

ቃልኪዳናችንን ሁልጊዜ ማስታወስ ቀላል እንዳልሆነ ይግለፁ። ዘወትር እሁድ ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ እና የቅዱስ ቁርባንን ፀሎት መስማት ለሰማዩ አባት የገባነውን ቃልኪዳናችንን እንድንጠብቅ ለማስታወስ ይረዱናል።

**የእምነት አንቀፅ**

ልጆቹ ሶስተኛውን የእምነት አንቀጽ በቃል እንዲያነቡት እርዷቸው። ከሰማዩ አባት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ተመልሰን መኖር የምንችለው ትዕዛዛቶቻቸውን ከታዘዝን ብቻ መሆኑን ያስረዱ።

**ታሪክ**

የዮናታንን ታሪክ በራስዎ አባባል ተናገሩ፣ የቅዱስ ቁርባን ጥቀም የተሰማው አንድ ልጅ፣

ዮናታን በታላቅ የከብት ማርቢያ ቦታ ላይ ከወላጆቹ ጋር ይኖር ነበር። የራሱ የሆነ ትንሽ ፈረስ ነበረው፣ እናም አብዛኛውን ጊዜ አባቱን በማርቢያው ፈረሶችን በመንከባከብ ይረዳው ነበር። አንድ ቀን ዮናታን ከፈረሱ ወደቀ እና ጀርባው ክፉኛ ተጎዳ። ዶክተሩ ከመረመረው በኋላ፣ ለዮናታን እና ለወላጆቹ ዮናታን ይሻለዋል ነገር ግን ለብዙ ሳምንታት በአልጋ ላይ ማሳለፍ አለበት አላቸው።

ዮናታን ከአደጋው ከሁለት ወራት ቀደም ብሎ የቤተክርስቲያኑ አባል በመሆን ተጠምቆ ነበር። ከሰማዩ አባት ጋር ትዕዛዛቱን እንደሚጠብቅ የተስፋ ቃል፣ ወይም ቃልኪዳን ገብቷል። ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ ዮናታን ቃልኪዳኑን እንዲያስታውስ ረድቶታል። የቅዱስ ቁርባንን ፀሎት በጥሞና ያዳምጣል ቅዱስ ቁርባንም ሲያልፍ በአክብሮት ይቀመጣል። ዮናታን በየጊዜው፣ ዘወትር ኢየሱስን እንዲያስታውስ እና ትዕዛዛቱን እንዲጠብቅ—ስለቃል ኪዳኑ የሚናገሩትን ቃላቶች ያዳምጥ ነበር። ዮናታን “አሜን” ሲል እና ቅዱስ ቁርባኑን ሲወስድ፣ በተቻለው መጠን ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ቃልኪዳኑን ለመጠበቅ መጣር አለበት ማለት እንደሆነ ያውቃል።

አሁን ያ ዮናታን በአልጋ መቆየት ነበረበት፣ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ እና ቅዱስ ቁርባን መውሰድ አይችልም። ዮናታን ቅዱስ ቁርባን ሲባረክ እና ሲያልፍ ያለው የጥሞና እና የአክብሮት ጊዜ ቀረበት። የገባቸውን ቃልኪዳኖች ሁልጊዜ ማስታወስ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያውቃል። የሰማዩ አባት መንፈስ ከእርሱ ጋር እንዲሆን ይፈልጋል። ዮናታን ጳጳሱን ቅዱስ ቁርባንን በሰንበት ቤቱ ማምጣት የሚቻል እንደሆን ለመጠየቅ ወሰነ።

ጳጳሱ ዮናታን ቅዱስ ቁርባን እንዲቀርበት እንደማይፈልግ እና ከሰማዩ አባት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር የገባውን ቃልኪዳን ማስታወስ እንደሚፈልግ በማወቃቸው ተደሰቱ። ሁለት የክህነት ስልጣን ያላቸው ዮናታንን እሁድ በክብት ማርቢያው እንዲጎበኙት እና ቅዱስ ቁርባንን ለእርሱ እንዲያዘጋጁለት አደረጉ።

- ዮናታን ወደ ቤተክርስቲያን አለመሄዱ ቀር ያለው ለምንድን ነው? (ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ ስለሚፈልግ።)
- ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ የፈለገው ለምንድን ነው? (የጥምቀት ቃልኪዳኑን እና የሰማይ አባት መንፈስ ከእርሱ ጋር እንዲሆን ያለውን ቃል ኪዳን እንዲታወሰው ስለሚፈልግ።)

## የጥምቀት ቃልኪዳኖችን ማስታወስ የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች እንድንታዘዝ ይረዱናል

ሁኔታዎች እና ውይይቶች

በየቀኑ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የምናስብ ከሆነ፣ የበለጠ ትምህርቱን እና እርሱን ለመታዘዝ የገባነውን የተስፋ ቃል ወይም ቃልኪዳን ማስታወስ እንደምንችል ይግለጹ። ልጆቹ የሚከተሉትን ሁኔታዎች በጨዋታ መልክ እንዲጫወቱ ይጋብዟቸው፣ እናም እያንዳንዱን እንዴት መፍታት እንደሚችሉ እንዲወስኑ ያድርጉ፣

1. አና እና ግሬችን እህትማማቾች ናቸው። የአና ጓደኛ ለመጫወት መጣች። ግሬችን ከእነርሱ ጋር ለመጫወት ትፈልጋለች፣ አና ግን እንድትጫወት አትፈልግም። አና ምን ማድረግ አለባት?
    - ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ አናን ትዕዛዛትን እንድትታዘዝ ሊረዳት የሚችለው እንዴት ነው?
    - መታዘዝ ያለባት ትዕዛዝ የትኛውን ነው?
2. ዳረን ያለፈቃድ የወንድሙን ሸሚዝ ለበሰ እና ቆሻሻ አገኘበት። ዳረን ምን ማድረግ አለበት?
    - ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ ዳረን ትዕዛዛትን እንዲታዘዝ ሊረዳው የሚችለው እንዴት ነው?
    - ምን ዓይነት ትዕዛዝ ነው የሚታዘዘው?
3. አን ከቤቱ ውጪ መጫወቻ መኪና አገኘ። ሊወስደው ፈለገ፣ ነገር ግን ከመንገዱ ዳር የሚኖረው የጓደኛው የዲ እንደሆነ እርግጠኛ ነበር፣ አን ምን ማድረግ ነበረበት?
    - ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ አን ትዕዛዛትን እንዲታዘዝ ሊረዳው የሚችለው እንዴት ነው?
    - አን የሚታዘዘው ትዕዛዝ ምንድን ነው?
4. ያዕቆብ ውጪ ለመጫወት ሊሄድ ነው። እናቱ ቤቱን ለማፅዳት እየሞከረች ነው። ያዕቆብ ለመጫወት ወደ ውጪ ሲወጣ፣ እናቱ በጣም የደከመች እንደምትመስል አስተዋለ። ያዕቆብ ምን ማድረግ አለበት?
    - ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ ያዕቆብ ትዕዛዙን እንዲታዘዝ እንዴት ሊረዳው ይችላል?
    - ያዕቆብ መታዘዝ ያለበት ትዕዛዝ ምን ዓይነት ነው?

ለመልካም አስተሳሰባቸው ልጆቹን አመስግናቸው።

## ማጠቃለያ

በተጠመቀን ጊዜ፣ ዘወትር ኢየሱስ ክርስቶስን ለማስታወስ ቃል መግባታችንን ለልጆቹ ያስታውሱ (አንድ ጣት ወደ ላይ ያውጡ)። ትዕዛዛቱንም ለመጠበቅ ቃል ገብተናል (ሁለት ጣቶችን ወደ ላይ ያውጡ)። እጆቻቸውን ሲመለከቱ እና CTR ቀለበታቸውን ሲያዩ፣ ከቀለበቶቻቸው ጣት ቀጥሎ ያለውን ሁለቱን ጣቶች ማየት ሲጠመቁ የሚገቡትን ሁለቱን ቃልኪዳኖች እንዲያስታውሱ ሊረዳቸው እንደሚችል ይንገሯቸው።

ከትምህርት 32 ላይ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ቁርባንን የመባረክ እና የማሳለፍ ታሪክ የቅዱሳን መፃሕፍት ታሪኮችን ይከልሱ።

**የአስተማሪው ምስክርነት**

ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚወደን እና እንድናስታውሰው እንደሚፈልግ ምስክርነትዋን ለልጆቹ ይስጡ። በቅዱስ ቁርባን ወቀት ፀጥ በማለት፣ የቅዱስ ቁርባንን ፀሎት በማሰብ፣ እና ኢየሱስን በማስታወስ ሲጠመቁ ለሚገቡት ቃልኪዳኖች እንዲዘጋጁ ያበረታቷቸው። ከተጠመቁ በኋላ፣ በየጊዜው ቅዱስ ቁርባንን ሲወስዱ ቃልኪዳናቸውን መጠበቅ እንደሚፈልጉ ለሰማይ አባት እንደሚያሳዩ ያስታውሷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ጸሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

## ገንቢ ተሳትፎዎች

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍለ ጊዜ” ይመልከቱ።

1. በቅዱስ ቁርባን ጊዜ በፀጥታ ለመቀመጥ እና የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ያህል እንደሚወዷቸው ለማሰብ ተዘጋጅተው ወደ ቅዱስ ቁርባን ስብሰባ መሄድ እንዳለባቸው ለልጆች ይንገሯቸው።

   የሚከተለውን ግጥም ለልጆቹ ያስተምሯቸው፣

   እጆቼን አጥፋለሁ፣ ራሴን አጎነብሳለሁ፣<br>
   እናም በፀጥታ፣ ፀጥ ብዬ፣<br>
   ቅዱስ ቁርባን ሲባረክ፣<br>
   አስታውስሃለሁ።

   ግጥሙን ለልጆቹ ይበሉላቸው። ከዚያም እንደተጠቀሰው እጆችዎን በማጠፍ እና ራስዎን በማጎንበስ ከእነርሱ ጋር ይድገሙት።

   - የምናጣጥፈው ምንድን ነው? (እጆቻችንን።)
   - የምናጎነብሰው ምናችንን ነው? (ራሳችንን)
   - በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ዝም ማለት አለብን ወይስ መንጫጫት?
   - በቅዱስ ቁርባን ጊዜ ማንን ማስታወስ አለብን? (ኢየሱስን።)

   ግጥሙን እንደገና ይበሉት፣ ልጆቹ በደንብ እስኪያውቁት ቃላቶቹን እንዲሞሉ እና እንቅስቃሴዎቹን እንዲያደርጉ ይፍቀዱላቸው። ከዚያም ከልጆች ጋር ይድገሙት።

2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንደሚያውቁ ልጆቹን ይጠይቋቸው። እነዚህ በቅዱስ ቁርባን ወቀት ሊያስቧቸው የሚችሉት አንዳንድ ነገሮች ናቸው። ስዕል 3-46፣ ኢየሱስ በጌተሰማኒ ሲፀልይ የሚያሳየውን አሳዩ፣ እና በአትክልቱ ቦታ ምን እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው (የማቴዎስ ወንጌል 26፥36–46 ይመልከቱ)። ልጆቹን ስለዚህ የተቀደሰ ሁኔታ ለማስተማር መንፈስ እንዲረዳዎት ያድርጉ።

3. መቀስ፣ ማጣበቂያ፣ እና የሚከተሉትን የሚታደሉ ፁሁፎች ግልባጭ ለልጆቹ ይስጡ። ከክፍሉ ጋር የገፁን የላይኛውን ክፍል ያንብቡ። ነጠብጣብ ያለበትን መስመር በመከተል እንዲቆርጡ ቃላቶቹንም በተገቢው ስርዓት እንዲያስቀምጡ ይዘዟቸው። ልጆቹ ይህን ካደረጉ፣ ቃላቶቹ እንዲህ በመባል መነበብ አለባቸው። “ዘወትር ኢየሱስ ክርስቶስን አስታውስ” እና “ትዕዛዛቱን ታዘዝ።” ዓረፍተ ነገሩን ለማሟላት የቃሉን ቁርጥራጭ በቦታው እንዲያጣብቁቸው ያድርጉ።

# ኢየሱስ ክርስቶስን ማስታወስ

ቅዱስ ቁርባንን ስካፈል፣ ከሰማይ አባት ጋር ቃልኪዳኔን አድሳለሁ።

ለ ________ _________ ________ _________ እናለ _________

_______ ________________ ቃል እገባለሁ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ትዕዛዛት | ኢየሱስ | የ | መታዘዝ | አስታውስ | ዘወትር | ክርስቶስ |

ትምህርት

# 34

# ወደ ሰማይ አባታችን መፀለይ እንችላለን

**ዓላማው**

ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገው የእያንዳንዱን ልጅ ወደሰማዩ አባት የመፀለይ ፍላጎት ለማጠንከር ነው።

**ዝግጅት**

1. በፀሎት 3ኛኔፊ ከ 17 እስከ 19 ያለውን ያጥኑ።
2. "ውዱ አባቴ፣ አመሰግንሃለሁ" የሚለውን መዝሙር ቃላቶቹን ለማለት ወይም ለመዘመር ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 7)
3. እንደሚከተለው ለእያንዳንዱ ልጅ ሉክ ወረቀት ያዘጋጁ፣

| አመሰግንሃለሁ | እጠይቃለሁ |
|---|---|
| | |

4. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ ወይም ከለር።
   ሐ. ስዕል 3-60፣ ልጅቷ ስትፀልይ (62310)፣ እና ስዕል 3-61፣ ኢየሱስ ከኔፊዎች ጋር ሲፀልይ (62542)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ጠቃሚ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ከሰማዩ አባታችን ጋር መነጋገር እንችላለን**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ልጅቷ ስትፀልይ የሚያሳየውን ስዕል 3-60 ያሳዩ።

- ከሰማዩ አባታችን ጋር እንዴት መነጋገር እንችላለን?
- ወደ ሰማዩ አባታችን የምንፀልየው ለምንድን ነው?
- ወደ ሰማዩ አባታችን መፀለይ የምንችለው መቼ ነው?

የሰማዩ አባት በጣም ስለሚወደን፣ ከእርሱ ጋር መነጋገር እንድንችል አደረገ። ለበረከታችን እንድናመሰግነው ይፈልጋል። እርዳታ በሚያስፈልገን በየትኛውም ወቀት ዕርዳታውን እንድንጠይቀም ይፈልጋል።

### የሰማዩ አባታችንን ማመስገን እንችላለን

ውይይት

ስንፀልይ፣ ለበረከቶቻችን የሰማዩ አባትን ማመስገን እንዳለብን ይግለጹ።

- የሰማይ አባት እንድናመሰግነው የሰጠን አንዳንድ በረከቶች ምን ምንድን ናቸው? (መልሶቹ ቤታችንን፣ ቤተሰባችንን፣ ቆንጆውን ዓለም፣ ምግብን፣ እና ልብስን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።)

ከሰማይ አባት ጋር ስንነጋገር፣ የተለዩ ቃላቶችን እንጠቀማለን። ስናመሰግነው፣ "እናመሰግንሃለን" እንላለን።

ልጆቹ ልዩ ለሆነ በረከት የሰማዩን አባት እንዴት እንደሚያመሰግኑ ለክፍሉ እንዲናገሩ ይፍቀዱላቸው። እያንዳንዱን ልጅ የሰማዩ አባትን ለማመስገን *አመሰግንሃለሁ* የሚሉትን ቃላት በመጠቀም የሚያመሰግኑበትን አንድ ነገር እንዲያስቡ ይጠይቁቸው።

ታሪክ

ስለ ጃን የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል በሚናገሩበት ጊዜ የሰማዩን አባት ማመስገንን እንዴት እንዳስታወሰች ልጆቹ እንዲያዳምጡ ያድርጉ።

በኢንግላንድ የጦርነት ወቀት ነበር። ጨለማ ነበር እናም ጃን በጣም ፈርታለች። ሴት አያቷ በለንደን አቀራቢያ፣ በትንሽ መንደር ትኖር ነበር፣ ጃንም እርሷን ለመጐብኘት በመንገድ ላይ ነበረች። ወደ ዋናው መንገድ ለመድረስ ለሁለት ማይሎች ብስክሌቷን መርገጥ ነበረባት። ጃን በሙሉ ልቧ በደህና እንድትደርስ ጸለየች።

ብስክሌቷን ስትረግጥ እና ስትፀልይ፣ ሀይለኛ ቀዝቃዛ ነፋስ ትንፋሿን ቀረጠው። እንደገና ጃን ለደህንነቷ እና መንገዱን ለማየት እንድትችል ፀለየች።

ወዲያው በኮረብታው ላይ ብርሃን ታየት፣ ጃን ወደ ብርሃኑ ረገጠች። ብርሃኑ ለቀረው መንገዷ በፊት ለፊቷ ቀየ።

ጃን በጣም አመሰገነች። የሰማይ አባት ፀሎቷን እንደመለሰ አወቀች። ስለ እርሱ ባስታወሰች ቁጥር፣ የሰማዩን አባት እንደገና ታመሰግናለች። (See Lucile C, Reading, "The Light," *Children's Friend,* Aug. 1965, p. 45.)

ጃን የሰማይ አባትን ማመስገንን እንዳስታወሰች፣ እያንዳንዳችን ስለሚሰጠን ነገር ሁሉ እና ስላገኘነው እርዳታ እርሱን ማመስገንን ማስታወስ እንዳለብን ይግለፁ።

መዝሙር እና ውይይት

"አመሰግንሃለሁ፣ ውድ አባቴ" የሚለውን ቃላቶች የመጀመሪያ ቁጥር ከልጆች ጋር ዘምሩ ወይም በሉ።

የሰማይ፣ አባቴ አመሰግንሃለሁ፣
ለደግነትህ ለፍቀርህም።
ስለመኖሪያዩ፣ እና፣ ወላጆቼም፣
ለሁሉም በረከት የምደሰትበት።

የሰማይ አባትን ያመሰገኑበትን ሌሎች በረከቶች እንዲያካፍሉ ልጆቹን ይጠይቁቸው።

### የሰማይ አባትን ለእርዳታ መጠየቅ እንችላለን

ስዕል እና ምስክርነት

ልጅቷ ስትጸልይ፣ የሚያሳየውን፣ ስዕል 3-60 ያመልክቱ።

ምንም ዓይነት ችግር ቢኖርብንም፣ በሚያስፈልገን ጊዜ የሰማዩን አባት ለእርዳታ መጠየቀ እንደምንችል ምስክርነትዎን ይስጡ።

- የሰማይ አባት እንዲረዳን ልንጠይቀው የምንችለው አንዳንድ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? (ልጆቹ እንዲያስቡ ጊዜ ስጧቸው። መልሶቹ ንግግር ለማድረግ ወይም የትምህርት ቤት ስራን ለመስራት ዕርዳታ መጠየቅን፣ ትዕዛዛትን መታዘዝን ለመማር እና ለማወቅ እርዳታ መጠየቅን፣ ልዩ የሆነ ጥበቃ፣ እና ጤነኛ ለመሆን እርዳታ መጠየቅን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ)።

| | |
|---|---|
| | ልጆቹ ለሌላ ሰው ለምሳሌ፣ ለቤተሰብ አባላት፣ ለጓደኞች፣ ወይም ለጎረቤቶች የፀለዩበትን ጊዜያቶች እንዲናገሩ ያድርጉ። |
| | የሰማይ አባትን እርዳታ ስንጠይቅ የምንጠቀማቸው ልዩ ቃላቶች *እንጠይቀሃለን* ነው። ልጆቹ እነዚህን ቃላቶች እንዲደግሙት ያድርጉ። |
| መዝሙር | "አመሰግንሃለሁ፣ ውድ አባቴ" የሚለውን ቃላቶች ሁለተኛ ቁጥር በሉ ወይም ዘምሩ። ልጆች ቃላቱን እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው እና የሰማዩን አባት ምን መጠየቅ እንደሚችሉ ይንገሯቸው።<br><br>እርዳኝ፣ ጥሩ፣ እንድሆን ዛሬ፣<br>እናም እንድንታዘዝ ለአባቴ እና ለእናቴ።<br>ውድ በሆነው፣ በኢየሱስ ስም፣<br>እጠይቅሃለሁ እንድትባርከኝ። |

**ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳደረገው፣ ዘወትር መፀለይ አለብን**

| | |
|---|---|
| የመምህሩ አቀራረብ | ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ወደ ሰማዩ አባት መፀለዩን አስገንዝቡ። ከትንሳኤው በኋላም፣ ወደ ሰማዩ አባት ፀልዮአል። ኢየሱስ የኔፊ ሕዝቦችን በጎበኘበት ጊዜ፣ አስተማራቸው እናም ባረካቸው። ለሕዝቡም ፀለየ እና እነርሱም መፀለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው። |
| ስዕል | ኢየሱስ ጋር ሲፀልይ የሚያሳየውን ስዕል 3-61፣ ያሳዩ።<br><br>ኢየሱስ ክርስቶስ ህዝቦችን በዙርያው እንደሰበሰበ እና እንዲንበረከኩ እንዳደረገ መፅሐፈ ሞርሞን እንደሚነግረን ይግለፁ። በምድር ላይ ሲንበረከኩ፣ እርሱም በመንበርከክ ወደ ሰማዩ አባት ፀለየ። መልካም የሆነ ፀሎት ስላደረገ ሰዎቹ ቃሎቹን ሲሰሙ በደስታ ተሞሉ።<br><br>ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ግሩም ነገሮችን ካስተማራቸው በኋላ፣ እንደ እርሱ መፀለይ እንዳለባቸው አስተማራቸው። |
| የቅዱሳን መፃህፍት ውይይት | እርሱ በመሐከላቸው እንደጸለየው በቤተክርስቲያኑ መጸለይ እንደሚገባቸው ተናገረ። እርሱ ብርሀን ነው ምሳሌም ሆነልን (3ኛ ኔፊ 18፥16ን ይመልከቱ።) |

- የዚህ ጥቅስ ቁጥር ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔፊ ህዝቦች ምን እንዳስተማራቸው ነው የሚነግረን? (እንዲፀልዩ አስተማራቸው።)

ኢየሱስ ክርስቶስ የኔፊ ሕዝቦችን ትቷቸው እንደሄደ፣ ለሁለተኛ ጊዜ ግን እንደተመለሰ ይግለጹ። ሲመለስም፣ የኔፊዎችን ደቀመዛሙርቶች ስለረዳቸው የሰማዩን አባት ለማመስገን እንደገና ፀለየ። ህዝቡን እንዲባርክ የሰማዩን አባት ጠየቀ። ኢየሱስ ክርስቶስ ከኔፊዎች ጋር በነበረበት ጊዜ ብዙ ጊዜ ፀልዮአል። አንዳንድ ጸሎቶቹ በመፅሀፈ ሞርሞን ተመዝግበዋል። ያደረጋቸው አንዳንድ ፀሎቶች በጣም ጥሩ ስለሆኑ ሊፃፉ እንዳልቻሉ መፅሐፈ ሞርሞን ይነግረናል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ኔፊዎችን እንዳስተማረ እና ዘወትር ወደ ሰማዩ አባት እንደፀለየ እኛም እንደዚያው ማድረግ እንዳለብን ይግለፁ።

- ወደ ሰማይ አባት መፀለይ የምንችለው መቼ ነው? (መልሶችን ይፍቀዱ፣ እናም ልጆቹ መፀለይ የሚችሉበትን የተለያዩ ጊዜያቶች ይወያዩባቸው፣ ሁሌ ጠዋት እና ማታ፣ በምግብ ጊዜያት፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር፣ ወይም በችግራቸው ጊዜ ወይም የተለየ ዕርዳታ የሚፈልጉበትን ጊዜ ያጠቃልላል።)
- የሰማዩን አባት ስናነጋግር የምንጠቀማቸው የተለዩ ቃላቶች ምንድን ናቸው?

"አመሰግንሃለሁ" እና "እጠይቅሃለሁ" የሚለውን ልጆቹ እንዲደግሙት ያድርጉ። ለፀሎት ሌላ ተገቢ የሆነ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ልጆቹን ያበረታቷቸው። "አንተ፣" እና "ወደ አንተ።" የሚሉትን ለመጠቀም መለማመድ ይችላሉ።

**ማጠቃለያ**

ተሳትፎ

ያዘጋጁትን ወረቀት እና እርሳስ ወይም ከለር ለልጆቹ ይስጧቸው። እያንዳንዱን ልጅ ስለሚያመሰግነው ነገር እና ስለ ምን እንደሚፀልይም በእያንዳንዱ ግማሽ ወረቀት ስዕል እንዲስል ጠይቁ።

የአስተማሪ ምስክርነት

የፀሎት ምስክርነትዎን ለልጆቹ ያካፍሉ። የሰማዩን አባት ለማመስገን እና ዕርዳታ ለመጠየቅ መፀለይ መቻል ታላቅ በረከት መሆኑን ይግለፁ። ልጆቹ ፀሎታቸውን ዘወትር እንዲሉ ይጋብዟቸው፣ በማንኛውም ጊዜ እና በየትኛውም በሚፈልጉት ቦታ መፀለይ እንደሚችሉ ያስታውሷቸው።

ለመዝጊያ ፀሎት ሲዘጋጁ፣ ፀሎት የሚያደርገው ሰው የሰማዩን አባት ስለምን ማመስገን እንዳለበት ልጆቹ ሐሳብ እዲያቀርቡ ያድርጉ። እንዲሁም ስለ ምን መጠየቅ እንዳለበት ሃሳብ እንዲያቀሩቡ ያድርጉ።

ልጆቹ ያቀረቡትን ሃሳቦች መጠቀምን በማስታወስ፣ ራስዎ የመዝጊያ ፀሎት ያድርጉ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “ለአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. የሚከተለውን ግጥም ተግባሮቹን በማሳየት በቃል ያንብቧቸው። ከዚያም ተግባሮቹን በማሳየት፣ ከልጆቹ ጋር ይድገሙት።

   እግዚአብሔር፣ እናመሰግንሃለን፣ ለደማቁ የፀሐይ ብርሃን፣ (ክንዶችን ማንሳት፣ ጸሐይን ለመስራት ጣቶችን ማነካካት)  
   በማለዳ ብርሃን ለሚዘምሩ ወፎች፣ (እንደሚበሩ ወፎች ክንድን መዘርጋት)  
   በየቦታው ላሉት ደስተኛ ልጆች፣ (ፈገግታ ማሳየት)  
   እና ለሰማዩ አባት የፍቅር እንክብካቤ። (ለፀሎት እንደሚደረገው፣ ራስን ማጎንበስ፣ እጆችን ማጣጠፍ)

2. የትንሹ ልጅ ፀሎት እንዴት መልስ እንዳገኘ በራስዎ አባባል የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ

   የስምንት አመት ልጅ በሃኪም ቤት በቀዶ ጥገና ጠረጴዛ ላይ ነበር። ወላጆቹ ሞተዋል፣ ነገር ግን መፀለይን ተምሯል። ቀዶ ጥገናው ከባድ እንደሆነ ያውቃል። ማን ቀዶ ጥገና እንደሚያደርግለት ዶክተሩን ጠየቀ፣ “ዶክተር፣ ቀዶ ጥገና ከማድረግህ በፊት፣ አትፀልይልኝምን?” በማለት ጠየቀ፣ ቀዶ ጥገና አድራጊው በአድናቆት ወደ ልጁ በመመልከት እንዲህ አለ፣ “ለምን፣ እኔ ልፀልይልህ አልችልም።”

   ከዚያም ትንሹ ልጅ የሚረዱትን ሌሎች ዶክተሮችን ጠየቀ፣ እያንዳንዳቸውም አንድ አይነት መልስ መለሱለት። ከዚያም ልጁ እንዲህ አለ፣ “ለእኔ የማትፀልዩልኝ ከሆነ፣ እኔ ለእራሴ እስከምፀልይ ድረስ አትጠብቁኝምን?” በማለት ጠየቃቸው በቀዶ ጥገናው ጠረጴዛ ላይ በጉልበቱ በመንበርከክ፣ እጆቹን አጣጠፈ፣ እናም እንዲህ አለ፣ “የሰማይ አባት፣ እናት አባት የሌሉኝ ትንሽ ልጅ ነኝ፣ ነገር ግን ክፉኛ ታምሚያለሁ እነዚህም ዶክተሮች ቀዶ ጥገና ሊያደርጉልኝ ነው። እባክህን በትክክል እንዲሰሩት እርዳቸው እናም፣ የሰማዩ አባት አሁን፣ እንዲሻለኝ ካደረክ፣ መልካም ልጅ እሆናለሁ። እንዲሻለኝ ስላደረግክም አመሰግናለሁ።”

   ፀልዮ ሲያበቃ፣ በነርሶቹ እና በዶክተሮቹ ዓይኖች ላይ እንባ ነበር። ልጁም ጠረጴዛው ላይ በመጋደም እንዲህ አለ፣ “አሁን ዝግጁ ነኝ።” (Adapted from George Albert Smith, *Sharing the Gospel with Others,* sel. Preston Nibley [Salt Lake City: Deseret Book Co., 1948], pp. 144–45.)

3. ለእያንዳንዱ ልጅ በቁራጭ ወረቀት በአንዱ ግማሽ ላይ የሳምንት የፀሎት ሰሌዳ ይስሩ እናም ጠዋት እና ማታ ፀሎቱን ሲያደርግ ምልክት ማድረግ ይችላል። በሌላኛው የወረቀት ግማሽ፣ እያንዳንዱ ልጅ ሲፀልይ የራሱን ስዕል እንዲስልበት ያድርጉ። እያንዳንዱን ልጅ በቤቱ ውስጥ የፀሎቱን ሰሌዳ ማየት በሚችልበት ቦታ እንዲያስቀምጠውና ጠዋት እና ማታ ምልክት ማድረግን እንዲያስታውስ ይጋብዙ።
4. የመጀመሪያውን የዕምነት አንቀፅ ከልጆቹ ጋር ይከልሱት።

# ዘለዓለማዊ ቤተሰብና ቤተመቅደስ

ትምህርት
35

**ዓላማው** ቤተሰቦች ለዘለዓለም በአንድነት መሆን እንደሚችሉ ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. "ቤተሰቦች ለዘለዓለም አንድላይ መሆን ይችላሉ" (የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ ገፅ 188) እና "ደስተኛ ቤተሰብ" (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 198)፣ የሚሉትን ቃላቶች ለማለት ወይም ለመዘመር ተዘጋጁ። የሁለቱም መዝሙሮች ቃላት በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ላይ ተጠቃለዋል።
2. በዚህ ትምህርት ውስጥ፣ በቤታቸው ውስጥ እናት እና አባት ለሌላቸው ልጆች አስቡላቸው። ደግሞም የቤተክርስቲያን አባል ያልሆኑ ወላጆች ወይም ወንድም እና እህት ላላቸውም አስቡላቸው።
3. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፥ ስዕል 3-5፣ አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ፣ በአቀራቢያዎ የሚገኘውን የሚገኙ ቤተመቅደስ እና ብዙ የሌሎች ቤተመቅደሶችን ስዕሎች፣ ከሆነ (ወይም ስዕል 3-62፣ የፖርትላንድ ኦሪገን ቤተመቅደስ [62617] ይጠቀሙ)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ሰማያዊ እና ምድራዊ ቤተሰቦች አሉን**

የአትኩሮት ተሳትፎ "ደስተኛ ቤተሰብ" የሚለውን ቃላቶች በሉ ወይም ዘምሩ።

የስዕል ውይይት ወደዚህ ምድር ከመወለዳችን በፊት፣ በተቀበው መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እንደ ወንድም እና እህት ሁላችንም በአንድላይ እንኖር እንደነበር ለልጆቹ ይግለጹላቸው። ከተወዳጅ የሰማዩ ወላጆች ጋር የሰማይ ቤተሰብ ክፍል ነበርን።

አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ የሚያሳየውን ስዕል 3-5ን፣ ከፍ በማድረግ ይያዙ። ልጆቹ እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ያውቁ እንደሆነ ይጠይቋቸው። አዳም እና ሔዋን በምድር ላይ የመጀመሪያ ወላጆች እንደሆኑ ንገሯቸው። የሰማይ አባት አዳም እና ሄዋን ልጆች እንዲኖሯቸው ነገራቸው። በዚህ ምድር ላይ የመጀመሪያ ቤተሰብ ነበራቸው።

የሰማይ አባት አዳም እና ሔዋንን እና ልጆቻቸውን እንደሚወዳቸው ይግለፁ። አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ወንጌል እንዲያስተምሩ ነገራቸው። በእኛ ጊዜም፣ የሰማዩ አባት ልክ እንደ አዳም እና ሔዋን ልጆች እንዳደረገው፣ እነርሱንም ወደ ቤተሰብ እንደላካቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ሁሉንም ልጆች ይወዳል እናም ሁሉም ወላጆች ልጆቻቸውን ወንጌል እንዲያስተምሩ ነግሯቸዋል።

ከዚህ ምድር በሞት ስንለይ፣ የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በሰማይ እንደገና እንደ ቤተሰብ እንድንኖር ይፈልጋሉ። ይህ የሚሆንበትን መንገድም አሳይተውናል።

**በቤተመቅደስ፣ ቤተሰቦች ለዘለዓለም መተሳሰር ይችላሉ**

- ቤተመቅደስ ምንድን ነው?

ልጆቹ ስለ ቤተመቅደሶች የሚከተሉትን ሐሳቦች እንዲያውቁ ይርዷቸው፡

1. የተቀደሱ ህንፃዎች ናቸው።
2. እያንዳንዳቸው የጌታ ቤት ይባላሉ።
3. የሰማይ አባት በቤተመቅደሶች ውስጥ ለእኛ ስላለው ዕቅድ ብዙ ነገሮችን እንማራለን።
4. በቤተመቅደሶች ውስጥ፣ ለሰማይ አባት ልዩ የሆኑ ቃሎችን ወይም ቃልኪዳኖችን እንገባለን፣ የሰማይ አባትም ልዩ የሆኑ ቃልኪዳኖችን ይገባልናል።

ብዙ የተቀደሱ እና ጠቃሚ ነገሮች በቤተመቅደስ ብቻ ሊከናወኑ እንደሚችሉ ይግለፁ።

ስዕሎች

የቤተመቅደሶችን ስዕሎች ያሳዩ።

- ከሰማይ አባት ቤተመቅደሶች አንዱን አይታችሁ የምታውቁ ስንቶቻችሁ ናችሁ?
- ወደ ቤተመቅደስ ስትመለከቱ ምን ይሰማችኋል?

ልጆቹ ስለአዩአቸው ቤተመቅደሶች እንዲናገሩ ያድርጉ። ቤተመቅደስን ያላዩ ልጆች አንድ ቀን እንደሚያዩ ተስፋዎን ይግለፁላቸው። ሁሉም ልጆች በቤታቸው አመቺ በሆነ ቦታ ላይ የቤተመቅደስ ስዕል፣ እንዲኖራቸው ያበረታቷቸው።

የመምህሩ አቀራረብ

በቤተመቅደስ፣ ባል እና ሚስት ለዘለዓለም አንድ ላይ እንዲሆኑ የሚረዳቸውን ስርአት እንዲከናወንላቸው ማድረግ እንደሚችሉ ይግለፁ። ይህም መተሳሰር ወይም የቤተመቅደስ ጋብቻ ይባላል። ባልና ሚስቶች ከቤተመቅደስ ውጪ ለዚህ ሕይወት ብቻ ከተጋቡ፣ ወደ ቤተመቅደስ በመሄድ መተሳሰር እና ጋብቻቸው ለዘላለም እንዲፀና ማድረግ ይችላሉ። ልጆቻቸው ከእነርሱ ጋር በመተሳሰር ለዘለዓለም የቤተሰባቸው ክፍል ይሆናሉ። ይህ ልዩ የሆነው በረከት የተሰጠው በቤተመቅደስ ለተሳሰሩት እና እዚያ የገቡትን ቃልኪዳን ለጠበቁት ብቻ ነው። ልጆቹ ምን ያህል ቤተሰቦቻቸውን እንደሚወዱ እና ለዘለዓለም አብሮ መኖር እንዴት ግሩም እንደሚሆን ያስታውሷቸው።

የሰማይ አባት ሁሉንም ሰዎች እንደሚወድ ይግለፁ። ቤተመቅደስ ያልገቡትንም ቤተመቅደስ ከገቡት እኩል ይወዳቸዋል። ሁሉም ቤተሰቦች በቤተመቅደስ እንዲተሳሰሩ ይፈልጋል። ብዙ ቤተሰቦች አሁንም በቤተመቅደስ እንዳልተሳሰሩ ይግለፁ። ይሁን እንጂ፣ እነዚህ ቤተሰቦች ራሳቸውን በአግባቡ ካዘጋጁ ወደ ቤተመቅደስ መሄድ ይችላሉ። ልጆች በብቃት መኖር እንደሚችሉ ንገሯቸው እናም ሲጋቡ ወደ ቤተመቅደስ በመሄድ ለመተሳሰር እና የራሳቸውን ዘለዓለማዊ ቤተሰብ ለመጀመር ይችላሉ።

መዝሙር

ልጆቹን "ቤተሰብ ለዘለዓለም አንድ ላይ መሆን ይችላል።" የሚለውን መዝሙር የመጀመሪያ ቁጥርና አዝማች ያስተምሯቸው። የመዝሙሩ ቃላቶችን ይወያዩባቸው። ልጆች በመቆም መዝሙሩን እንዲዘምሩ ወይም እንዲሉት ያድርጉ።

**ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብቁዎች መሆን አለብን**

የመምህሩ አቀራረብ

የቅድስና ሕይወት የሚኖር ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባል እና (የቤተመቅደስ መግቢያ ፍቃድ ቀጽ) ከጳጳሱ ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ ፍቃድ ያገኘ ወደ ቤተመቅደስ መሄድ እንደሚችል ይግለፁ። ወደ ቤተመቅደስ የሚሄዱ ወደ ጌታ ቤት ለመግባት ብቁ መሆን አለባቸው።

መዝሙር

"ቤተሰቦች ለዘለዓለም በአንድላይ መሆን ይችላሉ" የሚለውን መዝሙር ሁለተኛ ቁጥር ቃሎች ይወያዩባቸው። ከዚያም ልጆቹ በአንድ ላይ ቃላቶቹን እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው።

ውይይት

- ወደ ቤተመቅደስ ለመሄድ ብቁ ለመሆን እንዴት ልትዘጋጁ ትችላላችሁ?
- ወላጆችህ ብዙውን ጊዜ ሊመላለሱ በሚችሉበት የቤተመቅደስ አቀራቢያ ቤተሰቦችህ የሚኖሩ ከሆነ፣ ይህን እንዲያደርጉ እንዴት ልትረዳቸው ትችላለህ?

ልጆቹ ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ የሚዘጋጁበትን መንገዶች እንዲወያዩ ያድርጉ። የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎችን በመጠየቀ ወደቤተመቀደስ ለመሄድ ለመዘጋጀት ምን ማድረግ እንዳለባቸው እንዲያውቁ ይርዷቸው፣

- ገንዘብ ስታገኝ ወይም ስትቀበል ማድረግ የሚገባህ ምንድነው? (አስራትን መክፈል።)
- እሁድ ማድረግ የሚገባህ ምንድንነው? (ወደ ቤተክርስቲያን ስብሰባዎች መሄድ እና የሰማይ አባትን ማምለክ።)
- ወላጆችህን፣ ወንድሞችህን እና እህቶችህን መንከባከብ ያለብህ እንዴት ነው? (በደግነት እና በፍቅር።)
- ታማኝ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? (እውነትን መናገር እና አለመስረቀ።)
- አካልህን እንዴት መንከባከብ አለብህ? (ጥሩ ምግብ መብላት። የጥበብ ቃልን መታዘዝ።)
- ስለ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ሊሰማህ ይገባል? (ውደዳቸው፣ ትዕዛዛቶቻቸውን ታዘዝ፣ እና የሕያውን ነቢይ ትምህርት ተከታተል።)
- ሌሎችን መንከባከብ የሚገባን እንዴት ነው? (እርስ በእርስ በመዋደድ።)

የሰማይ አባት ልጆች መልካም ኑሮ እንዲኖሩ እናም ወደ ቤተመቀደስ ለመሔድ ብቁ እንደሆኑ እንደሚፈልግ ይግለፁ። የሰማዩን አባት ትዕዛዛት ከታዘዙ እና መልካም የሆነውን ለማድረግ ከሞከሩ፣ ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ እና ልዩ የሆኑ በረከቶችን ከሰማዩ አባት ለመቀበል ብቁ ይሆናሉ።

የእምነት አንቀፅ

በአስራ ሶስተኛው የእምነት አንቀፅ መሰረት የሰማዩ አባት እንድናደርግ የሚጠብቅብንን ከልጆቹ ጋር ይከልሱ። እነዚህን ነገሮች ማድረግ ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ እንዲዘጋጁ እንደሚረዳቸው ይግለፁ።

**ማጠቃለያ**

ልጆቹ ቤተሰብ ለዘለዓለም በአንድ ላይ እንዲሆኑ የሚፈቀደውን ዕቀድ የሰማዩ አባት እንደሰጠን እንዲያውቁ ይርዷቸው። የሰማዩ አባት ስለሚወደን፣ በቤተመቀደስ የሚሰጡት በረከቶች ሁሉ ልጆቹ እንዲኖራቸው ይፈልጋል። በመላው ዓለም ብዙ ቤተመቀደሶች አሉ፣ ስለዚህም በዓለም ላይ ብዙ ልጆች የመተሳሰር ወይም ከቤተሰቦቻቸው ጋር ለዘለዓለም አንድ የመሆን በረከቶች ሊኖሩዋቸው ይችላል። ልዩ ልዩ የሆኑ የቤተመቀደሶች ስዕሎችን እንደገና ይጥቀሱ። የቤተክርስቲያን የአባላት ቁጥር ሲያድግ፣ ቤተክርስቲያኑ ብዙ ቤተመቀደሶችን በዓለም ሁሉ ላይ እንደሚሰራ ይግለፁ።

- ስለ ቤተመቀደሶች ለቤተሰብህ ምን መንገር ትችላለህ?

ልጆቹ የተማሩትን ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዲካፈሉ ያበረታቷቸው። (ቤተሰብ እንደሚቃወሙ ካመንክ ስለዚህ ነገር ጥንቁቀ ሁን።)

ምስክርነት

ስለ ቤተመቀደሶች ምስክርነትዎን ይስጡ። ቤተሰቦች ለዘለዓለም አንድላይ የመሆን በረከት ሊኖራቸው የሚችልበተ ብቸኛው መንገድ በቤተመቀደስ መተሳሰር እንደሆነ ይግለፁ። ስለ ቤተመቀደስ ጋብቻ በረከቶች እና ወደ ቤተመቀደስ ለመሄድ ከተዘጋጁ ለልጆች ስለሚመጣው ደስታ ምስክርነትዎን ይስጡ። (ቤተመቀደስ እስከአሁን ሄደው የሚያውቁ ከሆነ፣ ጳጳሱን ወይም ቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን፣ ወይም ተፈቅዶለት ቤተመቀደስ ሄዶ የነበረ አንድ ሰው ወደ ክፍል መጥቶ ትምህርቱ ሊያበቃ ሲል የቤተመቀደስ በረከቶችን ምስክርነት እንዲሰጥ ሊጠይቁ ይችላሉ።)

ልጆቹ በዚህ ሳምንት ለቤተሰቦቻቸው ደግ ነገሮችን በማለት እና ወላጆቻቸው የጠየቁቸውን በማድረግ ቤተሰቦቻቸውን ደስተኛ ለማደረግ እንዲሞክሩ ያበረታቷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ። የሰማዩ አባትን ለቤተሰብ እና ለቤተመቀደስ በረከት እንዲያመሰግንም ሀሳብ ያቀርቡ።

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በተሻለ መንገድ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የአስተማሪ መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜ" የሚለውን ይመልከቱ።

1. እያንዳንዱ ልጅ ለእያንዳንዱ የቤተሰቡ አባል አንድ ቁራጭ እንዲኖረው በቂ ቁራጭ ወረቀቶችን ያዘጋጁ። ማጠባቂያ ወይም ፕላስተር እና እስክሪፕቶ ያምጡ።

   ለእያንዳንዱ ልጅ በሁለት ቁራጭ ወረቀቶች ይጀምሩ፣ እና በአንዱ ላይ *እናት* እና በአንዱ ላይ *አባት* ብለው ምልክት ያድርጉበት። ሁለቱን በሰንሰለት ያገናኟቸው።

   ቤተሰቦቻቸው በተጋቡበት ወቅት፣ እንደ ሰንሰለት አንድላይ መቀራኘታቸውን ለልጆች ይንገሯቸው። ከዚያም በቤተሰባቸው ላሉት ለእያንዳንዱ ልጆች ማያያዣ እንዲጨምሩ ልጆቹን ይርዷቸው። ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ማያያዣ ሲጨመር፣ የሰንሰለቱን ክብ ያድርጉት። የቤተሰባቸው አባላት በቤተመቀደስ አንድ ላይ ሲተሳሰሩ፣ ሁሉም ለዘለዓለም በአንድ ላይ እንደሚቀራኙ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ዘለዓለማዊ ቤተሰብ መሆን ይችላሉ፣ ልክ ክቡ ለዘለዓለም እንደሚቀጥለው።

2. የሚከተለውን የጣት ጨዋታ ከልጆቹ ጋር ይጫወቱ።

   (በተዘጋ ቡጢ ይጀምሩ)<br>
   ይህች እናት ናት፣ (አውራ ጣትን አውጣ)<br>
   ይህ አባት ነው፣ (ጠቋሚ ጣትን አውጣ)<br>
   ይህ ረጅሙ ወንድም ነው፣ (መኻከለኛው ጣትን አውጣ)<br>
   ይህች እህት ናት፣ (የቀለበት ጣትን አውጣ)<br>
   ይህ ልጃችን ነው፣ (ትንሿን ጣት አውጣ)<br>
   ኦ፣ ሁሉንም እንዴት እንወዳቸዋለን። (ጣትን በመዘረጋጋት እጅን ወደ ላይ ማውጣት)

3. "ደስተኛ ቤተሰብ" በሚለው መዝሙር ይህን ተጨማሪ ቁጥር ለልጆቹ ያስተምሯቸው።

   ኢየሱስን እወዳለሁ፣ ይወደኛል<br>
   ቤተሰብን ይወዳል፣ አዎ<br>
   ታያለህ፣ ቤተመቀደስን እንሰራለን<br>
   ለዘለዓለም አንድላይ እንሆናለን።

4. በክፍልዎ ውስጥ ከቤተሰቡ ጋር ለመተሳሰር ወደ ቤተመቀደስ የመሄድ ልምድ ያለው ልጅ ካለ፣ ልጁ ወይም ወላጆቹ ስለ እዛ እንዲናገሩ ማድረግ ይፈልጉ ይሆናል።

# ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን ማሳየት

ትምህርት

36

**ዓላማው** ልጆቹ እርሱ እንዲያደርጉ የሚፈልገውን በማድረግ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን እንዲያሳዩ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. በፀሎት ያጥኑ እናም የዮሐንስ ወንጌል 14፥15ን ለማንበብ ይዘጋጁ።
2. በስድስት አነስተኛ ቁራጭ ወረቀቶች፣ ከሚከተሉት ፍንጮች አንዱን ይፃፉ፥
   ሀ. ፍንጭ 1፥ ይወደናል።
   ለ. ፍንጭ 2፥ ልክ እንደ እኛ በመስመጥ ተጠመቀ።
   ሐ. ፍንጭ 3፥ በልጅነቱ የአናጢነትን ስራ መስራት ተማረ።
   መ. ፍንጭ 4፥ ህጻናት ልጆችን ይወዳል እናም ይባርካቸዋል።
   ሠ. ፍንጭ 5፥ እርስ በእርስ እንድንዋደድ አስተምሮናል።
   ረ. ፍንጭ 6፥ ለእኛ በመሞት ንስኃን መግባት እንዲቻል አደረገ።

   ክፍሉ ከመጀመሩ በፊት፣ እያንዳንዱን ፍንጭ በክፍሉ ውስጥ የሆነ ቦታ ይደብቁት።
3. "እርስ በእርስ ተዋደዱ" የሚለውን መዝሙር ለመዘመር ተዘጋጁ *(የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 136)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ላይ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፥
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ እና ወረቀት ወይም ካርድ
   ሐ. ስዕል 3-9፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (62572፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 240)፣ ስዕል 3-23፣ ልጁ ቅዱሳን መፅሐፍትን ሲያነብ፣ ስዕል 3-25፣ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ፣ ስዕል 3-26፣ ልጁ አስራት ሲከፍል፣ ስዕል 3-27፣ ባለሶስት ጎማውን ብስክሌት ማጋራት (62317)፣ ስዕል 3-59፣ ቅዱስ ቁርባንን ማሳለፍ (62021)፣ እና ስዕል 3-60 ልጅቷ ስትፀልይ (62310)።
   መ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ኃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

### ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል

የአትኩሮት ተሳትፎ — ከትምህርቱ ጋር የተዛመዱ ብዙ ፍንጮችን በክፍሉ ውስጥ እንደደበቁ ይግለፁ። ልጆቹ በጸጥታ እንዲፈልጓቸው ያድርጉ። ፍንጮቹ ሁሉ ከተገኙ በኋላ፣ ልጆቹ በደረጃ ከአንድ እስከ ስድስት እንዲያስቀምጧቸው ያድርጉ ወይም ይርዷቸው። ከልጆቹ ጋርም ያንብቧቸው። ከእያንዳንዱ ፍንጭ በኋላ ያላቸውን አስተያየቶች ይጠይቋቸው።

- እነዚህ ፍንጮች ስለማን ናቸው? (ኢየሱስ ክርስቶስ።)

ስዕል እና ውይይት — ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳየውን ስዕል 3-9፣ ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ብዙ ነገሮችን ስላደረገልን እንደሚወደን እንደምናውቅ ለክፍሉ ንገሯቸው።

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገው ምንድን ነው? (ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዛትን፣ ነቢያትን፣ ቤተክርስቲያኑን፣ እና የክህነት ስልጣን ስርዓትን እንደሰጠን ልጆቹ እንዲያውቁ ይርዷቸው። በሀጢአት ክፍያው ምክንያት፣ ስህተት ስለምንሰራው ነገር ንስኃ እንድንገባ አስቻለን እናም አንድ ቀን ከሰማይ አባት እና ከእርሱ ጋር ተመልሰን መኖር እንችላለን።)

ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ድንቅ በረከቶች በመስጠት ፍቀሩን እንዳሳየን ይግለፁ። እያንዳንዳችን ለእርሱ እና ለሰማዩ አባት ልዩ ነን።

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀሩን እንዳሳየን እና እኛም ፍቀራችንን ለእርሱ ማሳየት እንደምንችል ይግለፁ። “ፍቀርን ለኢየሱስ ክርስቶስ በ—ማሳየት እችላለሁ” የሚለውን ሐረግ በጥቁር ሰሌዳ ወይም በቁራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ፣ እና ድምጽዎን ከፍ በማድረግ ያንብቡት፡፡ ከዚያም ዛሬ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን የምናሳይባቸውን መንገዶች እንደሚወያዩ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ማንበብ ለሚችሉ ልጆች፣ ሲወያዩባቸው በጥቁር ሰሌዳው ላይ እነዚህን መንገዶች ይዘርዝሩ። ዕድሚያቸው ትንሽ ለሆነ ልጆች፣ የተወያዩበትን ርዕስ ለማሳየት ቀላል ስዕሎችን መሳል ይችላሉ።

### ትዕዛዛትን በመታዘዝ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀራችንን እናሳያለን

መጽሐፍ ቀዱስ እና የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

የዮሐንስ ወንጌልን 14፥15ን ሲያነቡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን ለማሳየት ሌላውን መንገድ እንዲያዳምጡ ክፍሉን ይጠይቁ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ትዕዛዛቱን በመጠበቅ፣ እንደምንወደው እንደምናሳየው ነግሮናል። ስንጠመቅ፣ ትዕዛዛቱን ለመታዘዝ ቃል እንገባለን። ትዕዛዛቱን ስንታዘዝ፣ እንደምንወደው እናሳያለን። “ትዕዛዛትን መጠበቅ፣” የሚለውን ይጻፉ ወይም ፈገግ ያለ ፊት፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ወይም በወረቀት ዝርዝር ላይ ይሳሉ።

የስዕል ውይይት

- ትዕዛዛት ምንድን ናቸው? (ደስተኛ እንድንሆን ሊረዳን ከሰማይ አባት እና ከኢየሱስ ክርስቶስ የመጣ ህግ ነው።)
- ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀራችንን ለማሳየት ልንጠብቀ የምንችለው አንዳንድ ትዕዛዛት ምንድን ናቸው?

ሁሉንም ልጆች ተነስተው እንዲቆሙ ማድረግ ይችላሉ፣ ከዚያም እያንዳንዱ ልጅ አንድ ትዕዛዝን ከጠራ ወይም ከጠራች በኋላ መቀመጥ ይችላሉ። (ስለ አንዱ እንኳ ማሰብ ያልቻሉትን ልጆች ለመርዳት ይዘጋጁ።)

ልጆቹ የቤተክርስቲያን ስብሰባዎችን መካፈል፣ በቀዱስ በቁርባን ጊዜ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማሰብ፣ አስራትን መክፈል፣ እውነት መናገርን፣ መፀለይን፣ ከቀዱሳን መፃሕፍት መማርን፣ ቤተሰቦቻችንን በቤት ውስጥ መርዳትን፣ እና ወዘተ. እነዚህን የመሳሳሉትን ሀሳቦች ሲያቀርቡ ተገቢ የሆኑ ስዕሎችን ያሳዩ።

### የቤተክርስቲያንን ንብረት በመከባከብ ፍቀራችንን ለኢየሱስ ክርስቶስ እናሳያለን

ታሪክ

ልጆቹ ኪም ፍቀሯን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንዳሳየች ታሪኩን እንዲያዳምጡ እንደሚፈልጉ ይግለፁላቸው፣

ኪም በምትኖርበት አካባቢ በጣም መጥፎ ዓውሎ ነፋስ ነፈሰ። የኪም ቤተሰቦች ከአዲሱ የፀሎት ቤት አቀራቢያ ስለሚኖሩ፣ ጳጳሱ ለአባቷ ከአውሎ ነፋሱ በኋላ ሕንፃውን እንዲያይ፣ ደወለለት። ኪም እና አባቷ በዛፍ ቀርንጫፍ ዙሪያ በንፋስ የወደቀውን በመንገዳቸው በመልቀም ወደዚያው አብረው ሄዱ። የአንዳንዱ ቤቶች መስኮቶች ፈራርሰዋል፣ አንዳንድ የተጎዱ መኪናዎችም አለፉ። ኪም የፀሎት ቤቱም ፈርሷል ብላ ተጨነቀች።

ወደ ፀሎት ቤቱ ሲቃረቡ፣ ቢያንስ አንድ ትልቀ መስኮት በአውሎ ነፋስ መሰባበሩን ማየት ቻሉ። ከጭቃ፣ ከቀጠሎች፣ ከቆሻሻ፣ ከቀንበጦች፣ እና ከትናንሽ ቀርንጫፎች ጋር ውስጡን የዝናብ ውሃ አጥቦታል። የኪም አባት ለመግባት የሚያስተማምን መሆኑ እስኪያረጋግጥ ውጪ እንድትጠብቀው ጠየቃት። የቀረውም ህንጻ የተበላሸ አይመስልም እያለ በመግለፅ ወዲያው ተመለሰ። አንድላይ ወደ ፀሎት ቤቱ ገቡ። የኪም አባት የተበላሸውን በይበልጥ በቀርብ

ለማጥናት ዙሪያውን ሲመለከት፣ ኪም ስራ መስራት ጀመረች። ሳይነገራት፣ ቀጠሎችን፣ ቀንበጦችን፣ ትናንሽ ቀርንጫፎችን፣ እና በዓውሎ ንፋሱ ወቀት ወደ ውስጥ የገባውን ቆሻሻ መልቀም ጀመረች።

የኪም አባት የሚረዳው የቀርዱን ሌላ አባል አገኘ፣ እና ወዲያውም መስኮቱ ተሸፍኖ አገኙ። ወንዶቹ መስኮቱን ለመከላከል ሲሰሩ፣ ኪም የፅዳት ስራዋን ቀጠለች። ወዲያውም ምንም ሳይቀር ሁሉም ቀርንጫፎች እና ቀጠሎች ከመንገድ ውጪ ተጣሉ። የኪም አባት እንድታርፍ ወደቤት ሊወስዳት ጠየቃት፣ ነገር ግን ኪም የፀሎት ቤቱን ማፅዳቱን ፈለገች። ጭቃውን ሲያፀዱ እና ወለሉን እና ግርግዳውን ሲያጥቡ እዚያው ቀይታ ሰራች።

- ኪም ፍቅሯን ለኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየችው እንዴት ነበር? (የፀሎቱን ቤት ለማፅዳት በመርዳት።)
- ስራው ካለቀ በኋላ ኪም የተሰማት እንዴት ይመስላችኋል?

የፀሎት ቤትን እና በውስጡ ያለውን ዕቃ በመጠበቀ መርዳት የምንችልበተ ብዙ መንገዶች እንዳሉ ይግለፁ። የፀሎት ቤታችንን በመጠበቀ መርዳት እና በፅዳት እና በጥሩ ሁኔታ ለመጠበቀ የተቻለንን ማድረግ እንችላለን። ሕንፃዎችን ላለማመሰቃቀል ነገሮችን ባለመተው ወረቀቶችን መልቀም እንችላለን። የመዝሙር መፅሐፎችን እና ቀዱሳን መፃሕፍትን በጥንቃቄ እና በክብር መያዝ እንችላለን። አንዳንድ ጊዜ የፀሎቱን ቤት ወይም መሬቱን ለማፅዳት ከተለዩ ፕሮጀክቶች ጋር መርዳት እንችላለን። እያንዳንዱ ሰው በአንዳንድ መንገዶች የቤተክርስቲያንን ንብረት በመንከባከብ መርዳት ይችላል።

“የቤተክርስቲያንን ንብረት መንከባከብ፣” የሚለውን ይጻፉ ወይም “ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን በ—ማሳየት እችላለሁ” ከሚለው ሀረግ ስር በጥቁር ሰሌዳው ላይ ወይም በወረቀት ቀለል ያለ የፀሎት ቤት ይሳሉ።

### ሌሎችን ስንወድ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን እናሳያለን

መዝሙር

በጣም ጠቃሚ የሆነውን ትዕዛዝ ለመማር ልጆች በጥንቃቄ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው።

“እርስ በእርስ ተዋደዱ” የሚለውን የመዝሙር ቃላት ከክፍሉ ጋር ይበሉት ወይም ይዘምሩት።

ውይይት

- ይህ መዝሙር ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንሰራ የሚፈልገውን ምን ይነግረናል? (ኢየሱስ በወደደን መንገድ እርስ በእርስ እንድንዋደድ።)
- አዲሱ ትዕዛዝ ምንድን ነው? (እርስ በእርስ ተዋደዱ።)
- *ደቀመዝሙር* የሚለው ቃል ምን ማለት ነው? (ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያምን እና የሚከተል ሰው ማለት ነው።)
- ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምትከተል እና እንደምታምን ሰዎች እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? (ለሌሎች ፍቀርን ካሳየህና በምታደርጋቸው ሁሉ ትክክለኛውን ለማድረግ ከሞከርክ ነው።)

በምድር ላይ ከኖሩት ከማንም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በጣም ደግ እና አዋቂው ሰው እንደሆነ ይግለፁ። እርሱ እንደወደደው የምንወድ ከሆነ ሌሎችን መውደድ አለብን። የዚህ መዝሙር ቃላቶች እውነት ናቸው፣ የተገኙትም ከመፅሐፍ ቀዱስ ነው። ኢየሱስም እንዲህ አለ፣ “እንደወደድኳችሁ—እርስ በእርስ ተዋደዱ” የዮሐንስ ወንጌል 13፥34ን ይመልከቱ፣ ደግሞም 15፥12፣ 17ን ይመልከቱ)። በጣም እንደሚወደን እናውቃለን። በዚያው ዓይነት ፍቀር ሌሎችን መውደድ አለብን፡ ሌሎችን በመውደድ፣ ኢየሱስንም እንደምንወደው እናሳየዋለን።

“ሌሎችን መውደድ፣” የሚለውን በዝርዝራችሁ ስር ይጻፉት፣ ወይም የልብን ስዕል ይሳሉ።

### ማጠቃለያ

የቤተክርስቲያንን ንብረት በመንከባከብ፣ ትዕዛዛትን ስንጠብቀ፣ እና ሌሎችን ስንወድ ኢየሱስ ክርስቶስን መውደዳችንን እንደምናመለክት ይግለፁ። በምናደርገው ነገር ፍቀራችንን ለኢየሱስ እናሳያለን።

ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ እና ወረቀት ወይም ካርድ ይስጧቸው። “ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን በ—ማሳየት እችላለሁ” የሚሉትን ቃላቶች በወረቀታቸው ላይ በደንብ መጻፍ የሚችሉትን ልጆች እንዲገለብጡ ያድርጓቸው። ይህንን በዕድሜያቸው አነስተኛ በሆኑ ልጆች ወረቀቶች ላይ መፃፍ ይፈልጉ ይሆናል። ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን ለማሳየት በዚህ ሳምንት የሚያደርጉትን አንድ ነገር እንዲስሉ ወይም እንዲፅፉ ልጆቹን ይጋብዟቸው። በሚቀጥለው ሳምንት በዚህ የተግባር ስራ ላይ እንዴት የተሻለ እንደሰሩ መስማት እንደሚፈልጉ ይግለፁ። በሚቀጥለው ሳምንት ወረቀታቸውን ቤት ይዘው እንዲሄዱ እና ማየት በሚችሉበት ቦታ እንደ ማስታወሻ እንዲያስቀምጡት ልጆቹን ያበረታቷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በተሻለ መንገድ የሚሰራውን ይመረጡ። በትምህርቱ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. ባቄላ የያዘ ከረጢት ወይም ሌላ ለስላሳ ነገር ለመወርወር ያምጡ። ልጆቹ በክብ በወለሉ ላይ እንዲቀመጡ ያድርጉ። የሚከተለውንም ይጠይቋቸው፡

   ኢየሱስን ትወዱታላችሁ? እንደምትወዱት እንዴት ያውቃል?
   ትክክለኛውን ምረጡ እሱም ያሳየዋል።

   ይህንን ቁጥር ከልጆቹ ጋር ያንብቡት፣ ከዚያም አንድ ስም ይጥሩ እና ስሙ ለተጠራው ልጅ የባቄላውን ከረጢት በቀስታ ወርውሩ። የተጠራው ልጅ ለእየሱስ ክርስቶስን እንደሚወደው ለማሳየት ማድረግ የሚችለውን አንድ ነገር መናገር አለበት። ከዚያም የባቄላውን ከረጢት ወደ አንተ መልሶ ይወረውረዋል። እያንዳንዱ ልጅ ተራው እስኪደርስ ይቀጥል።

2. “እርስ በእርስ ተዋደዱ” የሚለውን መዝሙር ይዘምሩ። ወይም ይበሉ ፍቅር፣ የምትለዋ ቃል ጋር በደረሱ ቁጥር ቃሉን በመዘመር ፋንታ በደረታቸው ላይ (እጃቸውን በማቀላለፍ) ክንዳቸውን እንዲያጣምሩ ያስረዷቸው። ይህ ማለት በምልክት ቋንቋ ፍቅር ማለት ነው። ለሁሉም የሰማይ አባት ልጆች ፍቅርን እና መግባባትን ማሳየት አለብን። “እወድሃለሁ!” የሚለውን የፍቀርን ምልክት በማድረግ እንዴት በምልክት እንደሚያሳዩ ልጆቹን ያስተምሯቸው፣ ከዚያም ወደ አንድ ሰው ይጠቁሙ። ቤት ሲደርሱ ይህንን ለቤተሰብ አባላት እንዲያሳዩ ሃሳብ ያቀርቡ። በእውነት ፍቀርን የማሳያ መንገድ እንደ ኢየሱስ ደግ በመሆን እንደሆነ ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

3. ከልጆቹ ጋር የሚከተለውን የድርጊት መዝሙር ይዘምሩት ወይም ይበሉት፡ “ኢየሱስ ሁሉንም ውደዱ ብሏል” (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ ገፅ 61*)።

   ኢየሱስ እያንዳንዱን ሰው ውደዱ ብሏል፣ (ክንዶች ይዘረጋሉ)
   በደግነትም፣ ተንከባከቧቸው፣ (ወደጎረቤትህ ዙር፣ ፈገግ በማለት ተጨባበጥ)
   ልብህ በፍቅር ሲሞላ፣ (እጆችን በልብ ላይ ጫን)
   ሌሎች ይወዱሃል። (ሁለቱንም ክንዶች ዘርጋ ከዚያም ወደ ደረትህ አምጣቸው)

4. ለእያንዳንዱ ልጅ ሶስት ወይም ከዚያ በላይ አነስተኛ የልብ ቅርፅ ያለው ወረቀት ይቁረጡ። ልጆቹ እነዚህን የልብ ቅርጾች ፍቅርን ለማሳየት በዚህ ሳምንት መጠቀም እንደሚችሉ ይግለፁላቸው። ለአንድ ሰው ጥሩ የሆነ ነገር መስራትና ልብን መተው አለባቸው። ሌሎችን መርዳት ኢየሱስ እንድንሰራው የሚፈልገው አንድ ነገር ነው። ልጆቹ ማድረግ የሚችሉትን ብዙ የደግ ነገሮችን ምሳሌ ይስጧቸው። ከክፍሉ አባላት ጋር እነዚህን ጥቂት የደግነት ድርጊቶች ለመጫወት ይወስኑ ይሆናል።

5. በሚገባ ያልተጠበቀ ማንኛውንም የመዝሙር መፅሀፍ ዋርድዎ ካለው፣ ለልጆቹ ያሳዩአቸው እና እንዴት እና ለምን መጠበቅ እንዳለባቸው ይወያዩ።

# ሌሎችን በማገልገል ኢየሱስ ክርስቶስን አገለግላለሁ


ትምህርት

37

**ዓላማው** ሌሎችን በማገልገል ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀርን ማሳየት እንደሚችሉ ልጆቹ እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. በፀሎት ሞዛያ 2፥17ን እና የሉቃስ ወንጌል 10፥30–37ን ያጥኑ፣ እና እነዚህን ጥቀሶች ለልጆቹ ለመግለፅ ይዘጋጁ።
2. እኛ ስንረዳ የሚለውን መዝሙር ለማንጎራጎር ይዘጋጁ (የልጆች የመዝሙር መጽሀፍ፣ ገፅ 198) እና "ስጥ፣' አለ ትንሹ ምንጭ" የሚለውን (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 236)።
3. ለ ጳጳሳችን የሚለውን መዝሙር ቃላት ለማለት ወይም ለመዘመር ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ* ገጽ 135)።
4. ጳጳስዎን ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንትዎን ስለ ልጅነት ጊዜው ያነጋግሩ። በልጅነቱ ሌሎችን የረዳበትን አንዳንድ መንገዶች እንዲነግርዎ ይጠይቁ። ልጆቹ ማንን እንደሚገልጹ መገመት እንዲችሉ ስለ እርሱ አጠር ያለ ንግግር ያዘጋጁ። ከተቻለ፣ የጳጳስዎን ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንትዎን የልጅነት ምስል ይዋሱ። (ስለ ጀማሪ ፕሬዚዳንት ወይም ስለ ሌላ መሪ ይህንን ንግግር ማዘጋጀት ይችላሉ።)
5. ከስር በተመለከቱት ምሳሌዎች አይነት ለእያንዳንዱ ልጅ ከወረቀት የተሰራ አበባ ያዘጋጁ። በጀርባው ላይ አጭር መልዕክት ለመጻፍ ተለቀ ያድርጉት።



6. የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች፥
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን እና መጽሐፍ ቅዱስ።
   ለ. የሚገኝ ከሆነ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ መጠጥ መምጠጫ ወይም ዱላ።
   ሐ. የሚገኝ ከሆነ፣ ብርሀን የሚያሳልፍ መለጠፊያ።
   መ. ለእያንዳንዱ ልጅ ከለር ወይም እርሳስ።
   ሠ. የአበባ ማስቀመጫ ወይም ጠርሙስ።
   ረ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   ሰ. ስዕል 3-63፣ መልካሙ ሳምራዊ (62156፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 218)።
7. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሀሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

**ሌሎችን በማገልገል ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን እናሳያለን**

**የአትኩሮት ተሳትፎ**

ባለፈው ሳምንት ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን ያሳዩበትን አንዱን መንገድ እንዲገልፁ ልጆቹን ጠይቋቸው (ትምህርት 36ን ይመልከቱ)። ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን ማሳየት ስለሚችሉበት አንድ መንገድ የበለጠ መስማት እንደሚፈልጉ ይግለፁ።

የሚጫወቱት ጨዋታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን የምናሳይበትን በጣም ጠቃሚ የሆነ መንገድ እንዲያውቁ እንደሚረዳቸው ለልጆቹ ይግለፁላቸው። አንድ መዝሙር እንደሚያንጎራጉሩ ይግለፁ። የመዝሙሩን ስም የሚያውቁት ሲመስላቸው፣ እጃቸውን ሊያወጡ ይችላሉ። የሚያንጐራጉሩትን ማቋረጥ ይችላሉ እና መዝሙሩ ምን እንደሆነ አንድ ልጅ እንዲገምት ይጠይቁት ወይም መዝሙሩን በሙሉ ማንጎራጎርዎን እስከሚጨርሱ ድረስ እንዲጠብቅ ይጠይቁት።

እኛ ስንረዳ የሚለውን መዝሙር ያንጎራጉሩ። ልጁ የመዝሙሩን ስም ከገመተ በኋላ፣ ይህንን ጥያቄ ይጠይቁ፥

- ይህ መዝሙር ስለምን የሚናገር ነው? (እርዳታ)

*እርዳታ* የሚለው በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉት።

ስጥ፣ ይላል ትንሹ ምንጭ የሚለውን ያንጎራጉሩ። ልጆቹ የመዝሙሩን ስም ከገመቱ በኋላ፣ ይህንን ጥያቄ ይጠይቋቸው፥

- ይህ መዝሙር ስለምን የሚናገር ነው? (ስለመስጠት።)

በ*እርዳታ* ስር *መስጠት* የሚለውን ይጻፉ።

- መስጠት እና መርዳት የሚል ሌላ ቃል ማሰብ ትችላላችሁ? (ማገልገል። እንደ አስፈላጊነቱ እስከሚገምቱ ድረስ ተጨማሪ ፍንጮችን ይስጧቸው።)

ሌሎችን መርዳት መስጠትን እና መርዳትን እንደሚያጠቃልል ይግለፁ። ብዙውን ጊዜ ለሌሎች በመስጠት እና በመርዳት እናገለግላለን።

**የእምነት አንቀፅ**

የሚከተለውን የአስራ ሶስተኛውን የእምነት አንቀፅ ክፍል ልጆቹ አንድ ላይ እንዲደግሙት ይርዷቸው፥ "ለሁሉም ሰው መልካምን በማድረግ . . . እናምናለን።"

**ጥቅስ**

ሞዛይ 2፥17ን ያንብቡ። በመፅሐፈ ሞርሞን ዘመን ይኖር የነበረው፣ ንጉስ ቢኒያም፣ ወገኖቻችንን ስናገለግል፣ እግዚአብሔርን ማገልገላችን እንደሆነ አስተማረ (ሞዛይ 2፥17ን ይመልከቱ)። ይህ ማለት ሌሎችን በፈቃደኝነት ስናገለግል፣ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስንም ማገልገል እንደሆነ ይግለፁ። እርስ በእርስ በማገልገል የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምንወዳቸው ማሳየት እንችላለን።

**ስዕል እና ታሪክ**

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ሲናገሩ ሲያስፈልግ፣ ስዕል 3-63ን፣ መልካሙ ሳምራዊን የሚለውን ያሳዩ፥

ኢየሱስ ክርስቶስ በመልካሙ ሳምራዊ ታሪክ እርስ በእርስ ስለማገልገል አስተምሯል። ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ይጓዝ ስለነበረው ሰውዬ ተናገረ። በመንገድም፣ ልብሶቹን በወሰዱበት ወንበዴዎች ተጠቃ፣ ደበደቡት እናም በሞት እና በህይወት መካከል ትተውት ሄዱ። አንድ ካህን ወዲያው መጣ እና፣ የቆሰለውን ሰው ተመለከተ፣ እናም ገለል ብሎ አለፈ። ከዚያም ካህናቱን በስራ የሚረዳቸው፣ አንድ ሌዋዊ መጣ፣ ነገር ግን እሱም ሰውየውን በመሸሽ ገለል ብሎ አለፈ።

በመጨረሻ፣ በአይሁዶች ከሚጠሉ ህዝቦች፣ አንድ ሳምራዊ መጣ፣ የተጎዳውን ሰው ለመርዳት ቆመ፣ ቁስሉን አጠበለትና አሰረለት። ሳምራዊው ሰውዬውን በራሱ አህያ ላይ አስቀምጦት፣ ወደ

እንግዶች ማደሪያም ወሰደው፣ እና ምሽቱን በሙሉ አብሮት ቆየ። በማግስቱ፣ ሳምራዊው የእንግዳ ማደሪያ ጠባቂውን ከፈለው እና የተጎዳው ሰው ገንዘቡ ከሚሸፍነው በላይ እንክብካቤ ከፈለገ፣ ተመልሶ ጨምሮ እንደሚከፍል ነገረው።

- ካህኑ እና ሌዋዊው ቁስለኛውን ሳይረዱት ያለፉት ለምን ይመስልሃል? (ትክክለኛ መልሶች የሚከተሉትን ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡ ቸኩለው ሊሆን ይችላል። ቁስለኛውን ሰው ፈርተው ይሆናል። በሌላ ሰው ችግር መረበሽ አልፈለጉም ይሆናል።)
- እርዳታችንን የሚፈልጉትን ሰዎች አንዳንዴ ለምን እናልፋቸዋለን?

በችግር ላይ ያሉትን ሰዎች በመርዳት ልጆቹ መልካም ሳምራዊያን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይግለፁላቸው። አንድ ሰው እርዳታ የሚፈልግበትን አንዳንድ ሁኔታዎችን ይንገሯቸው፣ እናም እንዴት እርዳታ እንደሚያደርጉ በጨዋታ መልክ እንዲያሳዩ ያድርጉ። ለምሳሌ፡ የሚከተሉት አይነት ሁኔታዎችን ይጠቀሙ ይሆናል፡

- በወለሉ ላይ ሁሉ አሻንጉሊቶች አሉ፣ ህፃኑ እያለቀሰ ነው፣ እናም እናትህ ራት ለማዘጋጀት እየሞከረች ነው።
- ጉረቤት አዲስ ልጅ ገብታለች። ከተለየ አገር ነው የመጣችው እናም ቋንቋህን በደንብ አትናገርም። ለመጫወት ስትወጣ፣ ብቸኛ ትመስላለች።
- እህት ካስትሮ ወደ ቤተክርስቲያን በየሳምንቱ ትመጣለች፣ ነገር ግን ማንም ያስተዋላት አትመስልም። አሮጊት ነች፣ ዘወትር ብቻዋን ነው የምትቀመጠው፣ እናም የተከፋች ትመስላለች።
- የምትወደው መጫወቻ ስለተሰበረ ትንሿ እህትህ ተናዳለች።

ሌሎችን በፍቃድ ስናገለግል ኢየሱስ እንደሚደሰት ይግለፁ። ለሌሎች ሰዎች አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ለልጆቹ ሃሳብ ያቀርቡላቸው።

**በእርሱ ቤተክርስቲያን በማገልገል ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርን ማሳየት እንችላለን**

የሚቀርብ ስዕል

ሌሎችን በየሳምንቱ በመርዳት ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያገለግሉ እንደ ጀማሪ ክፍል አስተማሪዎች፣ መዘምራኖች፣ ኦርጋን ተጫዋቾች፣ ካህናት እና ቁርባንን የሚያሳልፉ ዲያቆኖች የመሳሰሉት እና ሌሎች ብዙ ሰዎች በቤተክርስቲያን እንዳሉ ይግለፁ።

ከተቻለ፣ የጳጳሱን እና የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱን የልጅነት ስዕል ያሳዩ፣ ማን እንደሆነ ግን ለልጆቹ አይንገሯቸው።

ይህ በዋርድዎ ወይም በቀርንጫፍዎ አንድ ጠቃሚ ሰው ለመሆን ያደገ ሰው የልጅነት ፎቶግራፍ እንደሆነ ይግለፁ። በየሳምንቱ በዋርድዎ ወይም በቀርንጫፍዎ ሰዎችን በደስታ የሚያገለግል ሰው እንደሆነ ይናገሩ።

የመምህሩ አቀራረብ

የሰበሰቡት መረጃ በደንብ ስለሚያውቁት ሰው እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ሌሎችን በልጅነቱ እንዳገለገለ ይግለፁ። ማን ሊሆን እንደሚችል ልጆቹ እንዲገምቱ ያድርጉ። አስፈላጊ ከሆነ፣ በትክክል እስኪገምቱ ድረስ ብዙ ፍንጮችን ይስጧቸው። (ለምሳሌ፣ ትክክለኛውን እንድንመርጥ ይረዳናል፣ ችግሮች ሲኖሩብን ይረዳናል፣ አስራታችንን ለእርሱ እንሰጣለን።)

ጳጳሱ በየሳምንቱ ብዙ የአገልግሎት ሰዓታት ለዋርዱ አባላት እንደሚሰጥ ይግለፁ። እርዳታ የሚያደርገው እሁድ ብቻ አይደለም ነገር ግን በሳምንቱ ሌሎች ቀናትም ነው።

- በዋርዱ ያሉትን ሰዎች በመርዳት፣ ጳጳሱ የሚያገለግለው ሌላ ማንን ነው? (እግዚአብሔርን።)
- ጳጳሱ ሲያገለግል ፍቅርን የሚያሳየው ለማን ነው? (ለኢየሱስ ክርስቶስ እና በዋርዱ ላሉት ሰዎች።)

መዝሙር

ለጳጳሳችን የሚለውን መዝሙር ቃላቶችን ልጆቹ እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ያድርጉ።

ትጉህ እንደ ሰው መሆን እንደሚችለው፣
ጳጳሳችን ነው።
ሊያነጋግረኝ ጊዜ አለው፣
ጳጳሳችን ነው።
መልካም ቃላት ይናገራል
ለልጆችም ሁልቀን።
በሁሉም መንገድ እንርዳው፣
ጳጳሳችን ነው።

ጌታን ሲያገለግል ደስተኛ ነው፣
ጳጳሳችን ነው።
የዋርዳችን አባት ነው፣
ጳጳሳችን ነው።
ጥሩ እንድንሰራ ይረዳናል
በሰማይ አባታችን ፊት።
በሙሉ ኃይላችን እንወደዋለን፣
ጳጳሳችን ነው።

**ማጠቃለያ**

ተሳትፎ

ጳጳሱ ስለሰጣቸው የአገልግሎት ሰዓታት ልጆቹ የአመሰግናለሁ ስጦታ እንዲሰጡት እንደሚፈልጉ ይግለፁላቸው። ለእያንዳንዱ ልጅ አበባ፣ እርሳስ፣ እና የመጠጥ መጠጫ ወይም ዱላ ይስጡ። ልጆቹ ለኢየሱስ ክርስቶስ ፍቀር የሚያሳዩበትን መንገድ በአበባው አንድ ጎን እንዲጽፍ ወይም ስዕል እንዲስሉ እናም ስማቸውን እንዲፈርሙ ይጠይቋቸው። በመጨረሻ፣ በግንዶቹ ላይ የመጠጥ መጠጫዎችን ወይም ዱላዎችን ይለጥፍ።

ሁሉም ከጨረሱ በኋላ፣ አቀርቦቶቹን ሰብስቡ እና እያንዳንዱ ልጅ አበባውን ባመጣችሁት በአበባ ማስቀመጫ ወይም ጠርሙስ እንዲያስቀምጡ ያድርጉ። ከልጆች ጋር፣ አንድ የክፍል አባል ከትምህርት በኋላ ለጳጳሱ የወረቀት አበባ እንዲሰጥ ይምረጡ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በተሻለ የሚሰሩትን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ ለተጨማሪ መመሪያ፣ የአስተማሪ መርጃዎች በሚለው ውስጥ የክፍል ጊዜ የሚለውን ይመልከቱ።

1. የቤተክርስቲያኑ ሰባተኛ ፕሬዚዳንት ስለነበረው ስለ ሂበር ጄ ግራንት የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ እና ሌሎችን እንዴት እንዳገለገለ ይወያዩ።

   የሂበር አባት የሞተው ሂበር የዘጠኝ ቀን ልጅ እያለ ነበር። እናቱ በጣም ድሃ ነበረች እና እራሷን እና ትንሹ ሂበርን ለማስተዳደር በጣም አስቸጋሪ ጊዜ ነበራት። ለሌሎች ሰዎች በመስፋት እና ማደሪያ ቤት በማከራየት ትረዳቸው ነበር። አንዳንዴ ካለማረፍ ለብዙ ሰዓታት ትሰፋለች እና አሮጌ ሞድ የሆነውን የስፌት መኪና መርገጫ በችግር ነበር የምትገፋው። ሂበር ብዙውን ጊዜ ከስፌት መኪናው ስር በመዳህ መርገጫውን ይገፋላታል። በሶልት ሌክ ሲቲ ክረምቱ በጣም ቀዝቃዛ ነበር፣ እናም ሂበር ለሙቀት የሚሆነው፣ አንድ ስስ አሮጌ ኮት ብቻ ነበረው። የሚያሞቅ ኮት እንዲኖረው ይጓጓ ነበር፣ ነገር ግን ለምግብም እንኳ በቂ ገንዘብ እንደሌላቸው ያውቃል። ሂበር እናቱ ለልደቱ ያዘጋጀችለትን የሚሞቅ የክረምት ኮት እንደ ስጦታ ስታበረክትለት ደስ ብሎት ነበር። አዲሱ ኮቱ በጣም ታላቅ ዋጋ ያለው ንብረቱ ነበር። ከጥቂት ሳምንት በኋላ፣ ሂበር ወደተላከበት ለመድረስ ሲቸኩል፣ በእርሱ መጠን የሚሆን ልጅ በብርድ ሲንቀጠቀጥ ተመለከተ። ልጁም ስስ የሆነ ሹራብ ነበር የለበሰው፣ እናም ሂበር የሞቀ ኮት አለማድረግ እንዴት እንደሚሰማ አስታወሰ። ሂበር አዲሱን ኮቱን አወለቀ እና ልጁ እንዲያደርገው ሰጠው። ከዚያም ሌላ ኮት ቤት ስላለው ልጁ እንዲወስደው ነገረው።

ልጆቹ ይህንን ታሪክ በተራ በጨዋታ መልክ እንዲያሳዩት ማድረግ ይችላሉ እና ከዚያም ብዙዎቹ ሁኔታዎች እንዴት እንደሚሰሙ ይግለፁ።

2. እኛ ስንረዳ የሚለውን መዝሙር ሲያንጎራጉሩ ልጆቹ በክብ ቁጭ ብለው ለስላሳ ነገር ወይም ኳስን እንዲያስተላልፉ ያድርጉ። ማንጎራጎርዎን ሲያቆሙ፣ ኳሱን ወይም ለስላሳ ነገሩን የያዘው ወይም የያዘችው አንድን ሰው የሚረዱበትን መንገድ ይናገራሉ። ልጆቹ የሚረዱበትን መንገድ ለመናገር ሁሉም ተራ እንዳገኘ ወይም እንዳገኘች እርግጠኛ ይሁኑ።

3. ልጆቹ ከክፍሉ ከመውጣታቸው በፊት ፈገግ ያሉ ፊቶችን ወደታች ገልብጠው በልጆቹ ላይ አስይዙ ወይም ለጥፉ። ለአንድ ሰው ደግ የሆነ አገልግሎት ሲሰጡ፣ ፈገግ ያለውን ፊት ወደላይ እንዲገለብጡ ይንገሯቸው።

ትምህርት
38

# ንጹህና ቅዱስ መሆን እችላለሁ

**ዓላማው** ልጆችን ንፁህ እና ቅዱስ የመሆን ፍላጐት እንዲኖራቸው ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. 3ኛ ኔፊ 27፥27፤ ሞርሞን 1፥1–4፤ 13–17፤ 2፥1፤ 16–19፤ እና ትምህርት እና ቃልኪዳን 100፥16 በፀሎት ያጥኑ።
2. "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ወይም እንዲሉ ልጆቹን ለመርዳት ይዘጋጁ። (የልጆች መዝሙር መፅሐፍ፤ ገፅ 160)፤ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
3. የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፥
   ሀ. የሚገኝ ከሆነ፤ ለእያንዳንዱ ልጅ መፅሐፈ ሞርሞን እና ትምህርት እና ቃልኪዳን።
   ለ. የሚገኝ ከሆነ፤ ጨው እና በርበሬ (ሙሉ) መነስነሻ።
   ሐ. የተ.ም. ጋሻ እና ቀለበት።
   መ. ስዕል 3-34፤ ሞርሞን ሰሌዳዎቹን ሲጠርዝ (62520፤ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 306)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሐሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ሞርሞን ንፁህ እና ፃድቅ ነበር**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ያመጡትን የጨው እና የበርበሬ መነስነሻ ያሳዩ። ትንሽ ጨው በእጅዎ ላይ በተን ያድርጉ፤ እናም ለክፍሉ ያሳዩ። በእጅዎ ንፁህ ጨው እንደያዙ ያስረዱ። ንፁህ ነው፤ ምክንያቱም ከጥሩ በስተቀር በውስጡ ምንም ስለሌ፤ ንፁህ ጨው።

በእጅዎ ባለው ጨው ላይ ጥቂት በርበሬ ይበትኑ። ጨው አሁን ንፁህ አይደለም ምክንያቱም ከጨው ሌላ ለሆኑ ነገሮች ነፃ አይደለም። ሰዎች ስህተት የሆነ ወይም መልካም ያልሆነ አስተሳሰብ በአዕምሮአቸው ሲያስገቡ ወይም ስህተት ወይም መልካም ያልሆነ ነገር ሲያደርጉ፤ በፍፁም ንፁህ ሊሆኑ አይችሉም። ልክ እንደ ጨው እና እንደ በርበሬው ድብልቅ ናቸው። ንፁህ ሰዎች በሁሉም ጊዜያት መልካም አስተሳሰብ ለማሰብ እና የተቀደሰ አድራጎት ለማድረግ እንደሚጥሩ አጥብቀው ያሳስቡ።

የቅዱሳን መጽሐፍት ታሪክ

ከመፅሐፈ ሞርሞን ንፁህ እና ፃድቅ ስለነበር ስለ አንድ ሰው እንደሚናገሩ ይግለፁ። የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

ሞርሞን ወጣት ልጅ ሆኖ፤ እንደ ዐዋቂ ሰው ይታይ ነበር። ሞርሞን የአስር ዓመት ልጅ ብቻ በነበረበት ጊዜ፤ ሲያድግ ዐዋቂ ሰው ሲሆን የኔፊን ሰሌዳዎች ለመያዝ ኃላፊነት እንደሚሰጠው ተነገረው። የኔፊዎች ታሪክ በእነዚህ ሰሌዳዎች ተመዝግቦ ነበር። ሕዝቦቹን እንዲጠብቅ እና በሀያ አራት ዓመቱ፤ ታሪካቸውን እንዲፅፍ ተነገረው። ይህ ምን ዓይነት አስፈላጊ ኃላፊነት እንደነበር እንዲያገናዝቡ ልጆቹን ይርዷቸው።

- ሞርሞን፣ በአስር ዓመቱ፣ እንደ ሁለተኛ መዝገብ ጠባቂ እንዲመረጥ ያደረጉት ችሎታዎች ምንድን ናቸው ብለህ ታስባለህ? ሞርሞን ምን ዓይነት ልጅ ነበር? (ልጆቹ መልሶቹን እንዲወያዩባቸው ያድርጉ። እንዲረዳቸው፣ ሞርሞን 1፥1–2ን ያንብቡ። በሕዝቦቹ ዕውቀት መሰረት ስለተማረ ሞርሞን ጥሩ ተማሪ እንደነበር ልጆቹ እንዲገነዘቡ ይርዷቸው፣ ትሑት ልጅ፣ ማለትም ቁም ነገረኛ እና ታማኝ ነበር፣ እናም ለማወቀም ፈጣን ነበር (ሞርሞን 1፥1–2 ይመልከቱ)። ይህም ማለት ስለ ብዙ ነገሮች ያስተውል እና ያውቅ ነበር። ሞርሞን የሰማይ አባትን ይወድ እንደነበር እና ንፁህ እና ቀዱስ ያደረገውንም፣ ትዕዛዛት ይታዘዝ እንደነበር ይግለፁ። በኔፊ ሰሌዳዎች ላይ ባሉት በተቀደሱት ፅሑፎች የሰማይ አባት ሞርሞንን ማመን እንደሚችል ያውቃል።)

ሞርሞን የአስራ አምስት ዓመት ልጅ ሳለ፣ ግሩም የሆነ ልምድ እንደነበረው ይግለፁ። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ተጎብኝቶ ነበር (ሞርሞን 1፥15ን ይመልከቱ)።

- ሞርሞንን ብትሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለበት ቦታ እንዴት የሚሰማህ ይመስልሀል?
- ሞርሞን ንፅህ እና ቀዱስ የነበረው በምን መንገዶች ነው? (በጥቁር ሰሌዳ ላይ መልሶቻቸውን ልትዘረዝር ትችላለህ።)

በሞርሞን ዘመን ብዙዎቹ ሰዎች በጣም ኃጢአተኞች እንደነበሩ ይግለፁ (ሞርሞን 1፥13–14ን ይመልከቱ)። ሞርሞን ህዝቦቹ ፃድቀ እና ደስተኞች እንዲሆኑ ንስኃ እንዲገቡ እና እንዲጠመቁ ፈለገ (ሞርሞን 3፥2ን ይመልከቱ)። ህዝቦቹ ንስኃ እንዲገቡ ነገራቸው፣ ነገር ግን አላዳመጡም።

- ሞርሞን ጻድቀ ለመሆን ከሞከሩት ጥቂት ሰዎች አንዱ በመሆኑ ምን የተሰማው ይምስላችኋል?

ሞርሞን ሰሌዳዎቹን ሲጠርዝ የሚያሳየውን ስዕል 3፥34፣ ያሳዩ።

ሞርሞን እንደታዘዘው የህዝቦቹን ታሪክ በብረት ሰሌዳ ላይ እንደፃፈ ይግለፁ። እናም ሌሎች ሰዎች የፃፉትንም ታሪኮች አቀናጅቷል።

- ሞርሞን የፃፈውን ታሪክ የምናገኘው የትነው?

የመፅሐፈ ሞርሞንን ቅጂ ያሳዩ እና በርዕሱ ላይ ሞርሞን የሚለውን ስም ለልጆቹ ያሳዩአቸው። መፅሐፉን ስላቀናጀና ስለተጠነቀለለት እናም ፃድቀ ሰው ስለነበረ የተሰየመው በሞርሞን ስም እንደሆነ ይግለፁ።

**በአስተሳሰባችን፣ በአነጋገራችን፣ እና በምግባራችን ንፁህ መሆን እንችላለን**

የቀዱሳን መፃሕፍት ውይይት

- እንዴት ንፁህ ልንሆን እንችላለን?

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለብን የጠየቀንን ለልጆች ይንገሯቸው። ከዚያም እንደ እርሱ መሆን እንዳለብን መለሠ (3ኛኔፊ 27፥27ን ይመልከቱ)።

- ምን ዓይነት ህዝቦች መሆን አለብን?

ኢየሱስ ክርስቶስ ያሰበው፣ ያለው፣ እና ያደረገው ነገር በሙሉ መልካም እንደነበር ለልጆቹ ይግለፁላቸው። በትክክል እርሱን ለመምሰል፣ ኢየሱስ አስቧል፣ ብሏል፣ እና አድርጓል ብለን የምናስበውን አይነት ነገር ለማድረግ፣ ለማሰብ፣ እና ለመናገር መጣር አለብን። መቼም ስህተት የሆነ ነገርን ለማድረግ ስንፈተን፣ “ኢየሱስ እንዳደርግ የሚፈልገው ምንድን ነው?” ብለን ራሳችንን መጠየቀ አለብን። ይህ ንፁህ እና ቀዱስ ሆነን እንድንቆይ ይረዳናል።

የት.ም. አርማ እና CTR ቀለበት

ለልጆቹ የት.ም. ጋሻ እና ቀለበትን ያሳዩ። ቀለበቱ እና አርማው ኢየሱስ የሚፈልገውን እንዲያደርጉ እንዲያስታውሱ ሊረዳቸው እንደሚችል ያስታውሷቸው። ዘወትር መልካምን ነገር በመምረጥ ስህተት ከሆኑ ሀሳቦች እና ምግባሮች ራሳቸውን ነፃ ሲያደርጉ፣ ራሳቸውን ንፁህ እና ፃድቀ አድርገው ይጠብቃሉ።

መዝሙር

ልጆቹ “ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ” የሚለውን መዝሙር ቃላቶች እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው።

ታሪክ

አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ትክክል የሆነውን ነገር ስላደረገችው ልጅ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፤

ዴቢ የምትወደው አጎቷ በዴቢ እና በቤተሰቧ የቤተክርስቲያን አባል መሆን በጣም ነው ያዘነው። ለአመት ገደማ ሊጎበኛቸው አልፈለገም። በመጨረሻ ሲመጣ፣ ዴቢን ተራራ ላይ በመውጣት ጉዞ ከቤተሰቡ ጋር እንድትካፈል ጋበዛት። ዴቢ ተደስታ ነበር።

ወደተራራ በሚወጡበት ሁለተኛ ቀን፣ ዴቢ ኮዳዋን በመጣል ሰበረችው። ፀሐዩ በድምቀት ያንፀባርቅ ነበር፣ እናም ቀስ በቀስ ዴቢ ከሌሎቹ ወደ ኋላ ቀረች። አፏ ድርቀት ስለተሰማው፣ የሚጠጣ ውሃ ፈለገች።

ከላይ ከተራራው ላይ ሌሎቹ ቆመው ከቀርቀሮዎች ሲጠጡ ማየት ትችል ነበር። እና እሷም የሚጠጣ ለማግኘት ተጣደፈች።

ወደ ተሰበሰቡት ስትራመድ፣ “የሚጠጣ ውሰጂ፣ ዴቢ” በማለት ከእነርሱ አንዱ ተጣራ።

ከዚያም ያ ሰው የቢራ ቀርቀሮ በእጁ እንደያዘ ተመለከተች። በመጀመሪያ፣ ዴቢ የምታስበው ሁሉ ምን ያህል ተጠምታ እንደነበር ነው። ዴቢ ወንጌልን ተምራለች እናም ተጠምቃለች፣ እና ቢራ መጠጣት እንደሌለባት ታውቃለች። እንደገናም ምን ያህል ተጠምታ እንደነበር አስታወሰች። ዴቢ ትክክለኛውን ነገር ለማድረግ ፈለገች። ከተጠመቀች ጊዜ ጀምሮ ትጥራለች እናም ትዕዛዛቱን ለመጠበቅ እንድትችል ጸልያለች። አሁን ጠንካራ ለመሆን እርዳታን ፈለገች።

“ቢራ አልጠጣም። እባክህ፣ ሌላ ነገር ይኖርሃል?” አለች ዴቢ፣ በቀጥታ ወደሰውየው አይኖች በመመልከት።

ለደቂቃ አጎቷ ዮሐንስ የተናደደ ይመስል ነበር። ከዚያም እንዲህ አለ፣ “ዴቢ ሞርሞን ነች። ሌላ የሚጠጣ ነገር እንስጣት።” ከዚያም በመቀጠል፣ “አዝናለሁ፣ ዴቢ” አለ፣ ዴቢም ትዕዛዛትን ስለጠበቀች ደስተኛ ነበረች።

ውይይት

- ዴቢ ንፁህ እና ቅዱስ ሆና ለመቀየት ያደረገችው ምንድን ነበር?
- ዴቢ ትክክለኛውን ከመረጠች በኋላ የተሰማት ምን ይመስላችኋል?
- ዴቢ ለአጎቷ እንዴት ነበር ጥሩ ምሳሌ የሆነችው?

ታሪኮች እና ውይይት

በአስተሳሰባቸው፣ በአነጋገራችን፣ እና በምግባራቸው ንፅህ እና ፃድቅ መሆን ስለፈለጉ ልጆች ሶስት ታሪኮችን ሊነግሯቸው እንደሆነ ለክፍሉ ይንገሩ፤

1. የሬያን አዲስ ጎረቤቶች ወደሚቀጥለው በር ሲዛወሩ፣ ከእነሱ በዕድሜ እኩል ከሚሆነው ቴይለር ከሚባል ልጅ ጋር ጓደኛ ሆነ። በአጠቃላይ ዘወትር አብረው ይጫወቱ ነበር። አንድ ቀን ጎረቤት ካሉ ከሌሎች ወንዶች ልጆች ጋር ውጪ ኳስ ይጫወቱ ነበር። ቴይለር ቡድኑ በጨዋታው እየተሸነፈ ስለነበር በጣም ተናደደ መጥሮ ቃላት መናገር ጀመረ በሌሎቹ ቡድኖች ላይም መሳደብ ጀመረ። ከዛ በኋላ ወንዶቹ ልጆች ሔዱ ምክንያቱም በድጋሚ ጨዋታ ሊኖራቸው ስለማይችል እና ከቴይለር ጋር መጫወት ስላልፈለጉ። ሬይን ቴይለርን ለማነጋገር ቆየ። በዚያ ዓይነት መንገድ ለሌሎች መናገር ስህተት እንደሆነ ወላጆቻቸው እንዳስተማሯቸው ለቴይለር ገለፀለት። እንደዚያ ዓይነት ቃላት መስማት አይፈልጉም አለው። ከዚያም መጥሮ ቃላትን ሳይጠቀም መጫወት ከፈለገ፣ ሌሎቹ ወንዶች ተመልሰው መጥተው እንደገና እንዲጫወቱ እንደሚጠይቃቸው ሬይን ለቴይለር ነገረው።
    - ሬይን ንፁህ እና ፃድቅ መሆኑን ያሳየው እንዴት ነበር? (አልተሳደበም፣ እናም መሳደብ ትክክል እንዳልሆነ እንድማር ሌላውን ልጅ ለመርዳት ሞከረ።)
    - መሳደብ ስህተት የሆነው ለምንድን ነው? (የሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በደግነት እንድንናገር እንደሚፈልጉ ይገለፁ። ያለፍቀር ወይም በንዴት ስማቸውን እንድንጠቀም አይፈልጉም፣ “ስማቸውን በከንቱ አነሱ” ተብሎ እንደተጠቀሰው። የሚሳደቡ መጥፎ ምሳሌ ያስቀምጣሉ። የስድብ ቃላት ደግ ያልሆኑ ቃላቶችን በአዕምሮአችን እና መጥፎ ስሜትን በልባችን ሊያኖሩ ይችላል።)
2. አንድ ቀን ኮርቢይ ውጪ ሲጫወት፣ እርሱ እና ብዙዎቹ ጓደኞቹ ሌላ ልጅ ወደመጫወቻው ሜዳ ማዕዘን ጠራቸው። ይህ ልጅ ጥቂት ሲጋራዎች በኪሱ ነበሩት። ልጆቹ ሊያጨሱዋቸው እንዲሞክሩ ፈልጎ ነበር። ሁሉም ልጆች የሚያደርጉትን ባለማወቅ እርስ በእርስ ተያዩ።

በመጨረሻም ኮርቢይ ማጨስ እንደማይፈልግ ተናገረ እናም እምቢ አለ። ሌሎቹ ወንዶች ልጆችም ደግሞ ማጨስ እንደማይፈልጉ ተስማሙ።

- ኮርቢይ ንፁህ እና ፃድቅ እንደነበር ያሳየው እንዴት ነበር? (ማጨስ እምቢ አለ።)
- ይህ ሌሎችን ወንዶች ልጆች የረዳው እንዴት ነበር?
- አንተ እዚያ ብትሆን ኖሮ ምን ታደርግ ነበር?

3. ጌሪ ጓደኛው ቤት መፅሄቶችን እየተመለከተ ነበር። የጌሪ ጓደኛ በመፅሔቱ ውስጥ መጥፎ ስዕሎችን አገኘ እና ጌሪ እንዲመለከተው ፈለገ። ጌሪ መፅሔቱ ውስጥ ያሉት ምን ዓይነት ስዕሎች እንደሆኑ በተገነዘበ ጊዜ ጥሩ ስሜት አልተሰማውም ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚያ ዓይነት ስዕሎችን እንደማይመለከት ያውቃል። ጌሪ ማየት አልፈልግም አለ፣ እናም ውጪ ወጥተው እንዲጫወቱ ሐሳብ አቀረበ።

   - ጌሪ ፃድቅ የነበረው እንዴት ነበር? (መጥፎ የሆኑትን ስዕሎች መመልከት እምቢ አለ።)

አንዳንድ መፅሔቶች፣ መፅሐፎች፣ ፊልሞች፣ እና የቴሌቪዥን ትዕይንቶች የተቀደሱ እንዳልሆኑ እና የሀጢአት አስተሳሰቦችን ሊሰጡን እንደሚችሉ ይጠቁሙ። ጌሪ እንዳደረገው አዕምሮአችንን ንፁህ ማድረግ እና በተቀደሱ አስተሳሰቦች መሙላት እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ይጥቀሱ።

ውይይት

የምናያቸው ፊልሞች እና የቴሌቪዥን ክፍል ጊዜዎች በምናደርገው ምግባራችን ላይ ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ ይግለፁ። እነዚህ ክፍል ጊዜዎች በአዕምሮአችን ውስጥ በፍፁም የሌሉትን ሃሳቦች ሊያኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሃሳቦች እንደ ክፍል ጊዜው መልካም ወይም መጥፎ ሊሆኑ ይችላሉ።

- በፊልም ወይም በቴሌቪዥን እንዳያችሁት አንድ ሰው ለመሆን አስመስላችሁ ታውቃላችሁን?

ይህ አንድ ሰውን ለመምሰል መሞከር ማለት እንደሆነ ይግለፁ። በፊልም ጀግና ነው ብለህ የምታስበውን ሰው ለመምሰል መሞከር ብዙውን ጊዜ ቀልድ ነው።

- እኛ እንድንመለከታቸው መልካም ያልሆኑ የፊልም እና የቴሌቪዥን ትዕይንቶች አሉን? (አዎን።)
- የሚታዩ መልካም ፊልሞች ወይም የቴሌቪዥን ትዕይንቶች አሉን? (አዎን።)

ልጆቹ የሚወዱትን አንዳንድ ነገሮች ስም እንዲጠሩ ያድርጉ። ከዚያም በጣም የሚወዱትን የፊልም ወይም የቴሌቪዥን ጀግና እንዲያስቡ ያድርጉ። የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲመልሱ ያድርጉ፣

- ጀግናችሁ ዘወትር ህግን ይታዘዛልን?
- ጀግናችሁ የመሐላ ቃልን ተጠቀሞ ያውቃልን?
- ጀግናችሁ ሁልጊዜ ቀድስና ያለው ነውን?
- ጀግናችሁ በአለባበሱ እና በምግባሩ ትህትና ያለው ነውን?

ከእነዚህ ጥያቄዎች ለማናቸውም አይደለም የሚለውን መልስ ከመለሱ፣ ምናልበት የበለጠ ፃድቅ የሆነ አንድ ሰው ጀግናቸው እንዲሆን ለመምረጥ መፈለግ አለባቸው።

ልጆቹ ምን ዓይነት ፊልም እና የቴሌቪዥን ትዕይንቶች ለማየት እንደመረጡ ለወላጆቻቸው እንዲናገሩ ሐሳብ ያቀርቡላቸው። የሚያዩት ክፍል ጊዜ በውስጡ መጥፎ ነገሮች ካሉት፣ ጣቢያውን መቀየር፣ ቴሌቪዥኑን መዝጋት፣ ወይም የፊልም ቲያትሩን መተው እንደሚችሉ አጥብቀው ያሳስቡ።

መንፈስ ቅዱስ በመጥፎው እና በመልካሙ መካከል ያለውን ልዩነት እንድናውቅ እንደሚረዳን ለልጆቹ ያስታውሷቸው። ስለ አንድ ነገር መጥፎ ወይም ጥሩ ያልሆነ ስሜት ካለን፣ መንፈስ ቅዱስ ስህተት መሆኑን እየነገረን ነው።

**ማጠቃለያ**

የአስተማሪው ምስክርነት

አስተሳሰባችንን፣ አነጋገራችንን እና ምግባራችንን ንፁህ እና ቅዱስ የማድረግ ጥቀሙን ምስክርነትዎን ይስጡ። ፈተና እንኳ ሲመጣ ንፁህ እና ፃድቀ ሆነው ለመቆየት የሚችሉበት ልምድዎን ያካፍሉ ይሆናል። ያ ደስታ የሚመጣው፣ ለማድረግ አስቸጋሪ ቢሆንም እንኳ ፃድቀ በመሆን እንደሆነ ልጆቹ እንዲያውቁት ይርዷቸው።

መልካምን እንዴት እንደሚመርጡ አስቸጋሪ ጊዜ ሲኖራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያስቡ፣ እንዲሉ፣ እና እንዲሰሩ የሚያደርጋቸውን ዘወትር እንዲያስቡ ልጆቹን ይጋብዟቸው።

ጥቀስ

ትምህርት እና ቃልኪዳን 100፥16ን ለክፍሉ ያንብቡ። እኛ ንፁህ እና ቅዱስ እንድንሆን የሰማይ አባት ያሳደገን ህዝቦች እንደሆንን ይግለፁ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜ” የሚለውን ይመልከቱ።

1. በአካባቢያችን ያሉት ሰዎች ፃድቃን ባይሆኑ እንኳን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሞርሞን እንድንሆን እንደሚፈልግ ይጠቀሙ። የአስራ ሶስተኛውን የእምነት አንቀፅ ሰሌዳ በመጠቀም፣ ሰዎች የሚለውን ቃል የመጀመሪያ ክፍል በአንድነት እንዲደግሙት ክፍሉን ይርዷቸው። በጎ አድራጊ ማለት ደግ መሆን እና ታማኝ መሆን፣ እውነተኛ፣ ንፁህ መሆን እና ደግ አድራጊ ማለት ንፁህ እና ፃድቀ መሆን ማለት ነው።

   ይህንን የእምነት አንቀፅ ልጆቹ እንዲያስታውሱት ያበርታቷቸው።

2. ልጆች እና ወላጆች የትኛውን ፕሮግራም መከታተል መልካም እንደሆነ አስቀድመው ካቀዱ መጥፎ ፕሮግራሞችን ማየትን ማስወገዱ ቀላል እንደሆነ ይግለፁ።

   ለልጆቹ ብዙ የተለያዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ወይም ፊልሞችን ያቀርቡላቸው እና እያንዳንዱን መከታተል መልካምን መምረጥ እንደሆነ ይጠይቋቸው።

3. ልጆቹ “ሁለት ጆሮዎች አሉኝ” የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ እና በተግባር እንዲያሳዩ ይርዷቸው (*የልጆች የመዝሙር መፅሐ*ፍ፣ ገፅ 269)።

   ጆሮ አሉኝ እውነት ለመስማት፣ (ወደ ጆሮዎች አመልክት)
   ዓይኖች መልካም ለማየት። (ወደ ዓይኖችህ አመልክት)
   እግሮች አሉኝ
   ወደሚገባቸው የሚወስዱኝ። (በቦታ መጓዝ)
   ልጠቀማቸው እሞክራለሁ
   በስራዩ (መጥረግ ወይም ሌላ ስራን በምስራት ማመልከት)
   እና ጨዋታ። (ኳስን መለጋት ወይም ሌላ ጨዋታን መጫወትን ማሳየት)
   የሰማይ አባትን አመሰግናለሁ (እንደመፀለይ አድርገህ እጆችን አንድ ላይ አድርግ)
   እንደዚህ አድርጐ ስለፈጠረኝ።

   ከንፈሮች አሉኝ ቸር ለመናገር (ወደ ከንፈሮች ጠቁም)
   እጆች እንዲሰሩልኝ (እጆችን ወደላይ አንሳ)
   እነዚህ ሁሉ ተወዳጅ ረዳቶች
   የሰማይ አባት የሰጠኝ። (ወደራስህ ጠቁም)
   ልጠቀምባቸው እሞክራለሁ
   በስራዩ (መጥረግ ወይም ሌላ ስራን በመስራት ማመልከት)
   እና በጨዋታ። (ኳስን መለጋት ወይም ሌላ ጨዋታን መጫወትን ማሳየት)
   የሰማይ አባቴን አመሰግናለሁ (እንደመፀለይ አድርገህ እጆችን አንድ ላይ አድርግ)
   እንደዚህ አድርጐ ስለፈጠረኝ።

4. ልጆቹ “የምትወደውን መዝሙር አንጎራጉር” የሚለውን መዝሙር ቃላት እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ያድርጉ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 152)።

   በአጋጣሚ ቁንቁህ
   በጥያቄ ተሞልቶ ብታገኘው፣
   መጥፎ ሃሳብ በአዕምሮህ ቢመጣ
   ጥሩ ሃሳብ ይህ ነው
   የምትወደውን መዝሙር ዘምር፣
   በብርታት እና በሃይል ዘምረው፣
   አዕምሮህን ሲያጠራ ታየዋለህ።
   የምትወደውን መዝሙር ዘምር።

   ይህ መዝሙር አስተሳሰባቸውን እና ንግግራቸውን ንፁህ ለማድረግ እንዴት ሊረዳቸው እንደሚችል ከልጆቹ ጋር ይወያዩ።

ትምህርት

# 39 ለወላጆቻችን ፍቅርን ማሳየት

**ዓላማው** ልጆቹ ለአባቶቻቸው እና ለእናቶቻቸው ረዳት እና ታዛዥ በመሆን ፍቅርን እንዲያሳዩ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ኦሪት ዘፀአት 20፥12 እና ሞርሞን 8፥1 በፀሎት ያጥኑ።
2. "ደስተኛ ቤተሰብ" የሚለውን መዝሙር ክፍሉ እንዲዘምር ለማድረግ ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሀፍ*፣ገፅ 198)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
3. በቤት ውስጥ ወላጅ ለሌላቸው ወይም ወላጆቻቸው ሌላ ያልተለመዱ ሁኔታዎች ላሏቸው ልጆች ያስቡላቸው)።
4. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ትንሽ የባቄላ ከረጢት ወይም ኳስ።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ልጅ የቤተሰብ ዛፍ ቀጂ (በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ  የተጠቃለለውን ናሙና ይመልከቱ)።
   መ. ስዕል 3-34፣ ሞርሞን ሰሌዳዎችን ሲጠርዝ (62520፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 306)፣ ስዕል 3-35፣ ሞሮናይ ሰሌዳዎቹን በኮሞራ ኮረብታ ሲደብቅ (62462)፣ የወንጌል ስዕል ኪነጥበብ ጥራዝ 320)፣ እና ስዕል 3-5፣ አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**የሰማይ አባት ለወላጆቻችን ስለ እኛ ኃላፊነት ሰጥቷቸዋል**

የአትኩሮት ተሳትፎ አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ የሚያሳየውን ስዕል 3-5፣ ያሳዩ።

- ይህ የማን ስዕል ነው? (የአዳም፣ የሔዋን፣ እና የልጆቻቸው።)
- የሰማይ አባት አዳም እና ሔዋን ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ የፈለገው ምንድን ነበር? (ወንጌልን። ይህንን በቅርቡ በክፍል ውስጥ እንደተወያያችሁበት ለልጆቹ ያስታውሷቸው፣ ትምህርት 35 ይመልከቱ።)

አንድ ቀን ወደ እርሱ እስኪመለሱ ድረስ እንዲንከባከቧቸው እና እንዲያፈቅሯቸው የሰማይ አባት ለወላጆቻችን ልጆችን መስጠቱን ይግለፁ። ከዚህ ሕይወት በኋላ ከእርሱ ጋር ለመኖር እንዴት ብቁ እንደምንሆን ሁላችንም እንድንማር ይፈልጋል። የሰማዩ አባት ወላጆች ለልጆቻቸው ትዕዛዛቶችን እንዲያስተምሯቸው እና የልጆቻቸውን ፍላጎቶች እንዲጠብቁ ይጠብቅባቸዋል። ይህ ለወላጆቻችን ታላቅ ሃላፊነት ነው።

ለእያንዳንዱ ልጅ የቤተሰብ ዛፍ ቀጂ ይስጡ። እያንዳንዱ ልጅ ግንዱ ላይ የወላጆቹን ስሞች ወይም ፊቶች እንዲሁም በቅርንጫፉ ላይ የራሱን እና የማናቸውንም ወንድሞቹን እና እህቶቹን የመጀመሪያ ስም ወይም ፊቶች እንዲስል ያድርጉ ወይም ይርዱ።

ውይይት
- የሰማይ አባት ወላጆችን የሰጠን ለምንድነው? (እንዲያፈቅሩን እና እንዲንከባከቡን እንዲሁም ትዕዛዛቱን እንዲያስተምሩን።)

ልጆች ለወላጆች ፍቅርን ማሳየት እንደሚችሉ የሰማይ አባት እንደሚያውቅ ይግለፁ። የሰማይ አባት ይህን ማድረግ እንዳለብን ነግሮናል (ዖሪት ዘፀአት 20፥12 ይመልከቱ)። ለወላጆቻችን ፍቅርን የምናሳይበት ብዙ መንገዶች አሉ።

**ረዳት በመሆን ለወላጆች ፍቅርን እናሳያለን**

ታሪክ

ረዳት በመሆን ለወላጆች ፍቅርን የማሳያ አንዱ መንገድ መሆኑን ለክፍሉ ይግለፁ። የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ደግመው ይናገሩ፣

ኤማ እናተየዋ እንደሚያማት መናገር ትችላለች። እናተየው የደከመች ትመስላለች እናም ለማረፍ ብዙ ጊዜ ትቀመጣለች። አንዳውም የእናተየው ድምፅ ለኤማ ታናናሽ ወንድሞች፣ ለዳዊት እና ለዮሐንስ ስትናገር የደከመ ይመስላል። ኤማ እናቷ ለእርሷ ያደረገችላትን ነገሮች ሁሉ አሰበች እናም እናቷ እንዲሻላት መርዳት እንድትችል ተመኘች።

- ኤማ እናቷን ለመርዳት ማድረግ የምትችለው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

ኤማ ከታናናሽ ወንድሞቿ ጋር በመቀመጥ ከእነርሱ ጋር ተጫወተ ነበር። በፀጥታ እና በደስታ እንዲጫወቱ ረዳቻቸው። ከዚያም እናተየው ትንሽ እንቅልፍ ታገኝ ዘንድ ረዳቻቸው እነርሱን ዕረፍት እንዲያደርጉ በማስተኛት ረዳቻቸው። በኋላም ኤማ መጫወቻቸውን በማስቀመጥ ረዳቻቸው።

እናቷ ምሳ ማዘጋጀቷን በጨረሰች ጊዜ፣ ኤማ ዳዊት እና ዮሐንስ እጃቸውን እንዲታጠቡ እና ለፀሎት እንዲዘጋጁ ረዳቻቸው። እናቷ ወደ ኤማ ፈገግ በማለት በደንብ አቀፈቻት።

“ዛሬ ታላቅ ረዳት በመሆንሽ አመሰግንሻለሁ፣” በማለት እናቷ በኤማ ጆሮ ሹክ አለች።

ውይይት
- ኤማ ፍቅሯን ለእናቷ ያሳየችው እንዴት ነበር?
- ኤማ እናቷን ከረዳች በኋላ ምን የተሰማት ይመስላችኋል?
- እናቷ ምን የተሰማት ይመስላችኋል?

ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ልጅ የባቄላውን ከረጢት ይወርውሩ እና ከሚከተሉት ጥያቄዎች አንዱን ይጠይቁ። ልጁ ከመለሰ ወይም ከመለሰች በኋላ፣ የባቄላውን ከረጢት መልሰው እንዲወረውርልዎ ያድርጉ። ለእያንዳንዱ ልጅ ሁለቱንም ጥያቄዎች እንዲመልሱ ዕድል ይስጡ።

- እናቴ እና አባቴ ፍቀራቸውን ለኔ ለማሳየት ምን ያደርጋሉ?
- ለእናቴ ወይም ለአባቴ ፍቅርን ለማሳየት ምን ማድረግ እችላለሁ?

**ታዛዥ በመሆን ፍቅርን ለወላጆቻችን እናሳያለን**

ውይይት

መታዘዝ ለወላጆቻችን ፍቅርን ማሳየት የምችልበት ሌላኛው ጠቃሚ መንገድ መሆኑን ይግለፁ።

ታሪክ

ስለ አናንድ እና አባቱ የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፣

ወደ ኋላ ላይ አናንድ ፍየሎችን እንዲጠብቅ ተደረገ። በመጨረሻም ፍየሎቹ በተራራው ላይ ሣር ሲግጡ እነርሱን ለመጠበቅ እድሚው የደረሰ ነበር። አናንድ የስምንት ዓመት ልጅ ነበር እናም የፍየልን መንጋ የመጠበቅ ኃላፊነትን በጉጉት ይጠብቅ ነበር።

አናንድ እርሱ እና ውሻው ኑሚ ሁልጊዜ ማለዳ ፍየሎቹን እንዴት አንድ ላይ እንደሚሰበስቡ እና ሌሎች እረኞች የመንደሩን ፍየሎች በብዛት ሳሮች ወደሚገኙበት ወደ ተራራው የእግር መንገድ ሲወስዱ እንዴት እንደሚከተል ያስብ ነበር። ማምሻው ላይ አባቱ ወደ ተራራው በመምጣት አናንድን እና ኑሚን ፍየሎቹን ወደ ቤት በመመለስ ይረዳቸዋል።

አባቱ እንዲህ አለው፣ “አናንድ፣ የተራራውን የእግር መንገድ በጭራሽ አትልቀቅ። አንድ ፍየል ቢጠፋብህ፣ ጥራው፣ ነገር ግን በጭራሽ የእግር መንገዱን እንዳትለቅ። ተራራው አስቸጋሪ እና በጣም አደገኛ ነው። ልጄ፣ የምለውን ማድረግ አለብህ። የተራራውን የእግር መንገድ በጭራሽ እንዳትለቅ።”

ከዕለት ወደ እለት የአናንድ አዲሱ ኃላፊነት እየቀለለ መጣ፤ እናም በተራራው ላይ ያሳለፋቸውን ሰዓታት መውደድ ጀመረ።

አንድ ቀን ከሰዓት በኋላ፤ አናንድ አባቱ ሊረዳው ለመምጣት እንደዘገየ ተገነዘበ። ፍየሎቹን ሰብስቦ አባቱን ለመገናኘት የእግር መንገዱን ወደታች መውረድ ለመጀመር ወሰነ። በኑሚ እርዳታ፤ ወዲያውኑ ፍየሎቹን ሰበሰባቸው። የጎደሉበትን ሶስት ፍየሎች—ሱማ፤ ትልቁ ሴት ፍየል፤ እና ሁለቱ ግልገሎቿን ለመፈለግ ተበሳጭቶ ነበር። ምን ማድረግ ነበረበት? አናንድ ምናልባት ሱማ ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ወስደዋት ወደነበረው ከፍ ወዳለው የእግር መንገድ ሄዳ ይሆናል ብሎ ወሰነ። እሷን ለመፈለግ መሄድ አለበት፡፡

ኑሚ ሌሎቹን ፍየሎች እንዲጠብቅ በመተው፤ በተራራው የእግር መንገድ ወደላይ መውጣት ጀመረ። ወዲያው ሱማን እና ልጆቿ በርቀት በተራራው የእግር መንገድ በትንሽ የሳር ሜዳ ተመለከታቸው። ብዙ አለቶችና ቁጥቋጦዎች ነበሩ፤ እና አናንድ በእርሱና በሱማ መካከል ምን እንደነበረ ማየት አልቻለም። አናንድ መንገዱ ላይ መቆየት እንዳለበት ያውቃል ስለዚህ ተጣራ፤ ነገር ግን ሱማ ርቃ ተጓዘች።

መጨለም ጀመረ፤ ወዲያውኑ አናንድ ሶስቱን ፍየሎች በጭራሽ ማየት አልቻለም። አንድ ነገር መደረግ እንዳለበት ያውቅ ነበር፤ ስለዚህም ሊከተላቸው ወሰነ። በእርግጠኝነት ሊያገኛቸው እና ወደ እግር መንገዱ ሊመለስ ይችላል።

የእግር መንገዱን ለመልቀቅ ሲዘጋጅ፤ አባቱ፤ “አናንድ፤ የተራራውን የእግር መንገድ በጭራሽ መልቀቅ የለብህም” ያለውን አስታወሰ።

አናንድ አባቱን መታዘዝ እንዳለበት ያውቃል፤ ስለዚህ ቁጭ አለና አንድ ግዜ እንደገና ሱማን መጣራት ጀመረ። በድንገት፤ በሳሩ ውስጥ ኮሽታ ሰማ። እናትየውን ፍየል እና ሁለት ልጆቿን ለማየት ወደ ላይ ተመለከተ። በመጨረሻም ወደ እርሱ መጡ።

አናንድ ወደ እግር መንገዱ፤ አባቱ ሊፈልገው ተከትሎት ወደሚመጣበት ቦታ ነዳቸው። እነርሱም አንድ ላይ በኑሚ መሪነት ፍየሎቹን ወደ ቤት ወሰዷቸው።

በሚቀጥለው ቀን አናንድ ሱማን ወደ ጠበቀበት ቦታ አባቱን ወሰደው። የአናንድ አባት በአቀራቢያው ወዳለው ጥሻ ወሰደው እና ቀጥ ያለ ሰርጥ አሳየው። አናንድ ሱማን ተከተሎ ቢሄድ ኖሮ ወደ ሰርጡ ሊወድቅ ይችል ነበር። አናንድ አባቱን በመታዘዙ እና በማክበሩ በልቡ አመሰገነ።

ውይይት

- አናንድ ስለ አባቱ የተሰማው ምን ይመስላችኋል? (ይወደው ነበር።)
- አናንድ ፍቅርን ለአባቱ ያሳየው እንዴት ነው? (የእግር መንገዱን ባለመልቀቅ አባቱን ታዘዘው።)
- አባቱን መታዘዝ አናንድን የረዳው እንዴት ነበር? (በእግር መንገዱ በመቆየቱ ዳነ።)

አንዳንድ ጊዜ ወላጆቻችን አንዳንድ ነገሮችን እንድናደርግ ለምን እንደሚነግሩን እንደማንረዳ ይግለፁ። ፃድቅ ወላጆች ልጆቻቸውን ይወዳሉ እናም ለእነርሱ የተሻለውን ይፈልጋሉ። ልጆች ወላጆቻቸውን መታዘዝ እና የሚጠይቋቸውንም መስራት ይገባቸዋል። ወላጆቻችንን ስንታዘዝ፤ ፍቅራችንን ለእነርሱ እናሳያለን።

መዝሙር

“ደስተኛ ቤተሰብ” የሚለውን መዝሙር ቃላት ይበሉ ወይም ይዘምሩ።

**ሞሮናይ፤ ለአባቱ ለሞርሞን ፍቅርን አሳይቷል**

የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ እና ስዕሎች

መፅሐፈ ሞርሞን ለወላጆቻቸው ታዛዥ እና ረዳት በመሆን ፍቅርን ስላሳዩ ሰዎች ብዙ ታሪኮች እንዳለው ለልጆቹ ይንገሯቸው። አንዱ ታሪክ ስለ ነቢዩ ሞሮናይ ነበር።

ሞሮናይ በኮሞራ ኮረብታ ሰሌዳዎችን ሲደብቅ የሚያሳየውን ስዕል 3-35፤ ያሳዩ። ልጆቹ ስለ ስዕሉ የሚያውቁትን ይጠይቋቸው። የወርቁን ሰሌዳዎች ሞሮናይ እንደቀበረው ይንገሯቸው። ከዓመታት በኋላ፤ እንደመላዕክ ሆኖ ለዮሴፍ ስሚዝ የት እንዳሉ ለማሳየት ተመልሷል። የሞሮናይ አባት ነቢዩ ሞርሞን ነበር። ከሞሮናይ ስዕል በመቀጠል፤ ሞርሞን ሰሌዳዎችን ሲጠርዝ የሚያሳየውን ስዕል 3-34፤ ያሳዩ።

ሞርሞን ታሪኮችን አንድ ላይ ለመሰብሰብ እና በሰሌዳዎች ላይ ለመመዝገብ በሰማዩ አባት እንደተመረጠ ይግለፁ። የተጠየቀውን ማንኛውንም ነገር በማድረግ ለሰማይ አባት ሁልጊዜ ፍቀሩን አሳይቷል። ልጁ ሞሮናይም፣ እንደዚሁ እንዲያደርግ አስተምሮታል። ሞርሞን ሞሮናይን ይወደው ነበር እናም ደስተኛ እንዲሆን ይፈልግ ነበር። የሰማይ አባትን መውደድ እና መታዘዝ ሞሮናይን ደስተኛ እንዲሆን እንደሚረዳው ያውቅ ነበር፡፡

ሞሮናይ ከጎለመሰ በኋላም እንኳ፣ ሞርሞን ልጁ የሰማይ አባትን እንዲወድ ማስተማሩን ቀጠለ። ሞሮናይ አባቱን ወደደ እና ምሳሌውን ለመከተል ፈለገ።

ለአባቱ በነበረው ታላቅ ፍቅር ምክንያት፣ ሞሮናይ የአባቱን ትምህርት ታዘዘ። ስለዚህም ዓለም በሙሉ የአባቱን ትምህርት እንዲያውቅ አባቱ ያስተማረውን ነገር ፃፈ። ሞርሞን የወርቅ ሰሌዳው ተጽፎ ከማለቁ በፊት ሞተ፣ ስለዚህም ሞሮናይ መዝገቡን ወስዶ ጨረሰው።

ጥቅስ እና ውይይት

ሞርሞን 8፥1 ለክፍሉ ያንብቡ።

- ሞሮናይ ሞርሞንን የታዘዘው ለምን ነበር? (ስለሚወደው።)
- ሞሮናይ ለአባቱ ፍቅርን ያሳየው እንዴት ነበር? (ትዛዥ እና ረዳት በመሆን።)

**ማጠቃለያ**

ውይይት

- የሰማይ አባት ወላጆችን ለምን ሰጠን? (እንዲወዱን፣ ትዕዛዛትን እንዲያስተምሩን፣ እና እንዲንከባከቡን።)
- ለወላጆቻችን እንደምንወዳቸው እንዴት ማሳየት እንችላለን? (ታዛዥ እና ረዳት በመሆን።)
- የአናንድ፣ የኤማ፣ እና የሞሮናይ ታሪኮች በምን መንገድ ይመሳሰሉ ነበር? (በእነዚህ ታሪኮች ውስጥ በሙሉ፣ ባለ ታሪኮቹ ታዛዥ እና ረዳት በመሆን ፍቅርን ለቤተሰባቸው አሳይተዋል።)

የአስተማሪው ምስክርነት

የወላጆችን አስፈላጊነት እና ፍቅርን ለእነርሱ ስናሳያቸው ስለሚመጣው በረከት ምስክርነትዎን ይስጡ። በሚቀጥለው ሳምንት ለወላጆቻቸው ፍቁራቸውን ማሳየት የሚችሉበትን አንድ መንገድ እንዲመርጡ ልጆቹን ይጋብዟቸው።


አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በተሻለ ሁኔታ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ ወይም እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪው መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ከክፍሉ ጋር “ቤተሰብ ለዘለዓለም አብረው ይሆናሉ” የሚለውን መዝሙር ዘምሩ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 188)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
2. ልጆቹ ፍቅርን ለወላጆቻቸው እንዴት ማሳየት እንደሚችሉ ለማሣየት ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ።
3. “መምህር፣ እችላለሁ” የሚለውን ጨዋታ ከልጆቹ ጋር ይጫወቱ። ወደ እርሶ በመዞር ሁሉም በሰልፍ እንዲቆሙ ያድርጉ። (የልጅ ስም) በመጠቀም አረፍተ ነገር ይስሩ፣ ለምሳሌ እናትህን ሳህን በማጠብ እርዳ በሚሉበት ጊዜ። “ልጁ መምህር፣ እናቴን ሳህን በማጠብ ልርዳት? ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር ማለት አለበት። ልጁ ይህን ካለ፣ “አንድ ረዥም እርምጃ ወደፊት ተራመድ፣ ይበሉት” እና ልጁ ወደ እርሶ ይራመዳል። መጀመሪያ ጥያቄውን ከመጠየቁ በፊት ልጁ ወደፊት ከተራመደ፣ ወደ ኋላ መመለስ፣ ወይም ከእርሶ መራቅ አለበት። መጀመሪያ እጅዎን ሊነካ የቻለ ልጅ አሸናፊ ነው።



# ቤተክርስቲያን ውስጥ ማምለክ

ትምህርት

40


---

**ዓላማው** ልጆቹ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን የማምለክ ፍላጎት ለማጠንከር ነው።

---

**ዝግጅት**

1. ኦሪት ዘፀዓት 20፥8 እና ትምህርት እና ቃልኪዳኖች 25፥12 በፀሎት ያጥኑ።
2. እንደተብራራው ባለ አራት ጫፍ ኮከብ ያዘጋጁ። በጨዋታው ለመጠቀም በወረቀት ቦርሳ ውስጥ ያስቀምጡት።




3. "ወደቤተክርስቲያን ስሔድ" የሚለውን መዝሙር ልጆቹ እንዲዘምሩ ወይም ቃላቱን እንዲሉ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 157)።
4. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. ትምህርት እና ቃልኪዳኖች።
   ለ. የወረቀት ቦርሳ።
   ሐ. ስዕል 3-25፣ ወደቤተክርስቲያን መሔድ፣ ስዕል 3-59፣ ቅዱስ ቁርባንን ማሳለፍ (62021)፣ ስዕል 3-64፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ መፀለይ፣ ስዕል 3-65፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ መዘመር፣ ስዕል 3-66፣ በቤተክርስቲያን ውስጥ ማዳመጥ፣ ስዕል 3-67፣ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል።
   መ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሀሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹን በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

### እሁድ የተለየ ቀን ነው

የአተኩሮት ተሳትፎ

“ወደ ቤተክርስቲያን ስሔድ” የሚለውን መዝሙር ልጆች እንዲዘምሩ ወይም ቃላቶቹን እንዲሉ ይርዷቸው።

ዘወትር ደስታ ይሰማኛል
ቤተክርስቲያን ስሄድ።
ኦርጋኑ በእርጋታ ሲጫወት፣
በቀስታ እቀመጣለሁ።
አባላትን ሰላም እላለሁ
ቤተክርስቲያን ስሔድ።

ድምፄን ከፍ አድርጌ እዘምራለሁ
ቤተክርስቲያን ስሔድ።
እጄን አጣምሬ ዝቀ በማለት፣
ፀሎት ሲፀለይ አዳምጣለሁ፣
አላወራም ግን አስተውላላሁ
ቤተክርስቲያን ስሔድ።

ቤተክርስቲያን ስሔድ
ስለ ሰማዩ አባቴ አውቃለሁ።
ላመሰግነው ለሁሉም ተክል፣
ስለቤተሰቤ፣ ጓደኞቼ፣
ቤተክርስቲያን ስሔድ
ለማያቸው አስደሳች ነገሮች።

ስለሰማይ አባት እና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ የምንማርበትን ጊዜ በየሳምንቱ እንደሚያስፈልገን የሰማዩ አባት ማወቁን ይግለፁ። እሁድን ለእኛ ልዩ ቀን አድርጎ ፈጥሮታል፣ ለቅዱስ ቁርባን እና ለጀማሪ ክፍል ስብሰባ የምንሔድበት ቀን ነው። እሁድ የምንጠባበቀው፣ የደስታ ቀን እንዲሆንልን እግዚአብሔር ይፈልጋል። ወደቤተክርስቲያን መሄድን ስንመርጥ፣ ትክክለኛውን ነገር እየመረጥን ነው።

### ቤተክርስቲያን ልዩ ቦታ ነው

ታሪክ እና ውይይት

ወደ ቤተክርስቲያን መምጣት ጭራሽኑ እንዲያቆም የሚያደርግ ችግር ስለነበረበት ልጅ ታሪክ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ስሙም በኋላ ላይ የበላይ ባለስልጣን ቫን ፌዘርስቶን ነበር። ቫን ፌዘርስቶንን ወጣት በነበረበት ጊዜ፣ ቤተሰቦቹ በጣም ደሃ እንደነበሩ እና ብዙ ልብስም መግዛት የማይችሉ እንደነበሩ በመግለፅ ታሪኩን ያስተዋውቁ።

“ቤተክርስቲያን ሲሔድ የማደርገው አንድ ጥንድ ጫማ ነበረኝ። በጣም ምርጥ ጫማ አልነበረም። ከሶሉ ስር ቀዳዳ ስለ ነበረው፣ [ከእህል ሳጥን] ትንሽ ካርቶኖች ቀርጬ እንደ ውስጥ ሶል እለጥፋቸው ነበር። ወደ ቤተክርስቲያን ስሔድ ሁለቱን እግሮቼን መሬት ላይ በማድረግ እቀመጥ ነበር፣ አንድ እግሬን በማንሳት በእህል ሳጥኑ [ካርቶን ላይ ያለውን ፅሑፍ] ከጫማዬ ስር አንድ ሰው እንዲያይ አልፈልግም ነበር። በዚያ ሁኔታ ወደ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ፣ እናም እነዚያ ጫማዎች እስኪያልቁ ሁሉም ነገር መልካም ነበር። ከዚያስ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ነበር። ቀዳሚ እንደነበር አስታውሳለሁ፣ ‘ወደ ቤተክርስቲያንም መሄድ አለብኝ። በቤተክርስቲያኗ ውስጥ እኔ አንድ ሰው ነኝ። በእርግጥ ስለ እኔ ያስባሉ።’ ስል አሰብኩኝ። ያንን በደንብ ማሰቤን አስታውሳለሁ፣ እና አንዳንድ ጎረቤቶች ወደሰጡን ትንሽ የጫማ ሳጥን ሄድኩኝ። ከውስጡ ፈለኩኝ፣ ነገር ግን ለእኔ የሚሆነኝ ያገኘሁት አንድ ጥንድ ጫማ ብቻ ነበር . . . የነርስ ሴቶች ጥንድ ጫማ ነበር። ‘እንዴት እነዚያን አደርጋለሁ?። ቤተክርስቲያን ውስጥ በመጠቋቆም ይስቁብኛል፣ ስል አሰብኩ። ስለዚህ ላላደርጋቸው እና ወደ ቤተክርስቲያን ላለመሄድ ወሰንኩ።”

- በወንድም ፌዘርስቶን ቦታ ብትሆን እንዴት ይሰማሃል?
- ምን ታደርግ ነበር?

ብዙ ልጆች ምላሽ እንዲሰጡ ይፍቀዱላቸው፤ ከዚያም ታሪኩን ይቀጥሉ፤

“ሊሊቱን፤ እና በሚቀጥለው ጠዋት አሰብኩኝ— መሄድ እንዳለብኝ አውቃለሁ!— ምን ማድረግ እንዳለብኝ ወሰንኩ። በጣም በማለዳ ወደእዚያ አፈጥንና ማንም እዚያ ከመድረሱ በፊት ወደፊት በመጠጋት እቀመጣለሁ። ‘ማንም እግሮቼን እንዳያይ [ከመቀመጫው] ስር አደርጋቸዋለሁ፤ እና ከዚያም ሁሉም እስኪወጡ እጠብቃለሁ። እነርሱ ከሄዱ ከግማሽ ወይም ከሆነ ሰዓት በኋላ ወደ ቤት በመሮጥ እመጣለሁ፤’ ስል አሰብኩ። ያ ነበር ዕቅዴ። ከግማሽ ሰዓት ቀደም ብዬ ወደ ቤተክርስቲያን ገሰገስኩ፤ እናም ተሳካልኝ። ማንም እዚያ አልነበረም። እግሮቼን ከወንበሮቹ ስር አደረኩ። ወዲያው ሁሉም ገቡ፤ እና ከዚያም ወዲያውኑ በድንገት አንድ ሰው፤ “አሁን ወደ ተለያዩ ክፍሎች እንሂዳለን፤” ሲል ንግግር አደረገ ወደ ክፍሎች እንደምትሄዱ ረሳሁኝ፤ ስል . . .ደነገጥኩ። አስተናባሪዎች ወደመተላለፊያው መምጣት ጀመሩ፤ ወደ እኛ መስመር ደረሱ፤ እና ሁሉም በመነሳት ሄዱ። እኔ ግን እዚያው ቁጭ አልኩ። መንቀሳቀስ አልቻልኩም። አንድ ሰው ጫማዬን እንዳያይ ማድረግ እንደማልችል አውቃለሁ። የኅብረተሰቡ ግፊት ግን ኃይለኛ ነበር። ያ ሁሉ ስብሰባ እኔ እስክንቀሳቀስ በመጠበቅ የቆመ ይመስላል፤ ስለዚህ መንቀሳቀስ ነበረብኝ። ከመቀመጫዬ ተነሳሁኝና ክፍሉን በመከተል ደረጃውን ወረድኩኝ።

“በዚያን ቀን እስከዛሬ በህይወቴ ከተማርኩት ውስጥ ታላቁን ትምህርት መማሬን አስባለሁ። ወደታችኛው ክፍል ሄድኩ፤ እና አስተማሪው በትልቁ ግማሽ ክብ ሰርተን እንድንቀመጥ አደረገን። እያንዳንዱ ጫማዬ የግማሽ ሜትር ዲያሜትር ፈለገ እንደት አፍሬ እንደነበር ልነግራችሁ አልችልም። አትኩሬ ተመለከትኩ፤ ነገር ግን፤ ታውቃላችሁ፤ በእዚያ ክፍል ከነበሩት የስምንት እና የዘጠኝ ዓመት ልጆች አንዳቸውም አልሳቁብኝም። አንዳቸውም ወደ እኔ አላዩም። ማንም ወደ ጫማዬ አልጠቀመም። መምህሬም አልተመለከተም። ተጀምሮ እስከሚያልቀ እመለከት ነበር። ወደ እኔ የሚመለከት እንዳለ ብዬ አትኩሬ ተመለከትኩኝ—። በእርግጥ እነዚያን ለቤተክርስቲያን ማድረግ የነበሩብኝን የነርሶች ጫማ ተመልክተዋቸዋል። ያልሳቁት ግን በተፈጥሮ ጥሩ አመለካከት ስለነበራቸው ነው፤ (ቫን ጂ. ፊዘርቶን, “Acres of Diamonds,” 1974፤ ከዓመቱ ንግግሮች [ፕሮቮ፦ ብሪገሀም ያንግ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፤ 1975]፤ ከገፅ. 351–52)።

- ወንድም ፊዘርስቶን ልጅ ሳለ የነርሶቹን ጫማ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሔድ ለማድረግ ፈቃደኛ የነበረው ለምንድን ነበር? (ምክንያቱም ወደቤተክርስቲያን ለመሄድ በጣም ስለሚፈልግ ነበር።)

ወጣት ቫን ፊዘርስቶን ቤተክርስቲያንን መከታተል በጣም ጠቃሚ መሆኑን እንደሚያውቀ ይግለፁ። ምንም እንኳ ቤተሰቦቹ ለእርሱ ጥሩ ጫማ መግዛት ባይችሉም፤ በየሳምንቱ ወደቤተክርስቲያን ለመሄድ ደስተኛ ነበር። ቆንጆ ጫማ እንኳ ባይኖረውም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ የበለጠ ጠቃሚ እንደነበር ወሰነ።

### የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን ለማምለክ ቤተክርስቲያንን እንካፈላለን

ጥቁር ሰሌዳ እና ስዕሎች

በመላው ዓለም ወንዶች እና ሴቶች ልጆች እንዲሁም ወላጆቻቸው ዘወትር እሁድ ቤተክርስቲያን እንደሚካፈሉ ይግለፁ። ቤተክርስቲያንን ስንካፈል እንዲሁም በማዳመጥ እና በመማር በምንሳተፍበት ጊዜ፤ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እናመልካለን። ወደ ቤተክርስቲያን መሄድን የሚያሳየው ስዕል 3-25፤ ያሳዩ። ሊያመልኩ እንደሚሄዱ ይግለፁ።

*ማምለክ* ብለው በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ልናመልክ የምንችልበት ብዙ መንገድ እንዳለ ይግለፁ። ቅዱስ ቁርባን ማሳለፍን የሚያሳየውን ስዕል 3-59፤ ያሳዩ።

ቅዱስ ቁርባንን ስንወስድ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምናስታውስ ልጆቹን ያስታውሷቸው። ከተጠመቅን፤ ዘወትር እርሱን ለማስታወስ እና ትዕዛዛትን ለመታዘዝ የገባነውን ቃልኪዳን እናድሳለን። በቤተክርስቲያን ስንገኝ ከምናመልክባቸው በጣም አስፈላጊ መንገዶች አንዱ ቅዱስ ቁርባንን መውሰድ ነው።

ከቅዱስ ቁርባን ስዕል በመቀጠል፤ በቤተክርስቲያን መዘመርን የሚያሳየውን ስዕል 3-65፤ ያሳዩ።

ጥቅስ

መዝሙርን በስሚት ስንዘምር፤ ፍቅራችንን ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደምንገልፅ ይጠቁሙ። ካልዘመርን፤ እነርሱን የማምለክ ዕድልን እናጣለን።

ለልጆቹ ትምህርት እና ቃልኪዳን 25፥12ን ያንብቡላቸው። ከልብ በሆነ መዝሙር ነፍሴ ትደሰታለች ብሏል ጌታ። የቅዱሳን መዝሙሮችን ለእርሱ ፀሎት ነው፣ እና ከበረከት ጋርም እንደሚመለስ ጌታ ተናግሯል። መዝሙሮቹን እና የተቀደሱ መዝሙሮችን ለእርሱ ስንዘምር የሰማይ አባት እንደሚደሰት ያሳስቡ።

የስዕል ተሳትፎ

ስዕል 3-64፣ ከመዝሙር ስዕል በመቀጠል፣ በቤተክርስቲያን መፀለይን የሚያሳየውን ያሳዩ።

በቤተክርስቲያን ሳለን ብዙ ፀሎቶችን እንደምናዳምጥ ይግለፁ። ሌላ ሰው ፀሎት ሲያደርግ፣ አይናችንን መጨፈን፣ እራሳችንን ዝቅ ማድረግ፣ እና የሚባለውን መስማት እንዳለብን ለልጆቹ ያስታውሷቸው።

- በፀሎታችን መጨረሻ ላይ ምን እንላለን? (አሜን።)
- ለምን "አሜን" እንላለን? (የተባለውን እንደምንስማማ እና እንደምንደግፍ ለማሳየት።)

በቅዱስ ቁርባን አገልግሎት ወቀት በፀጥታ መፀለይ እንደምንችል ይጠይቁ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስናስብ፣ የሰማዩ አባት ትክክለኛውን እንድንመርጥ እና ትዕዛዛትን ለመታዘዝ እንዲረዳን መጠየቀ እንችላለን።

ስዕል 3-66፣ ከፀሎት ስዕል በመቀጠል በቤተክርስቲያን ማዳመጥ የሚለውን፣ ያሳዩ።

የተሳትፎ ውይይት

- በቤተክርስቲያን አያዳመጥን እንደሆነ እንዴት ማሳየት እንችላለን? (በጸጥታ በመቀመጥ፣ ባለማውራት፣ እና ተናጋሪውን ወይም አስተማሪውን በመመልከት።)

በቤተክርስቲያን ሳለን ማዳመጥ ያለብንን አንዳንድ ሰዎች ልጆቹ እንዲጠሩ ያድርጓቸው። ለእያንዳንዱ ዛሳብ ጣትን ወደላይ እንዲያነሱ ይንገሯቸው። ተቀባይነት ያላቸው መልሶች፡ በጀማሪ ክፍል ወይም በቅዱስ ቁርባን ስብሰባ ተናጋሪን፣ ቅዱስ ቁርባንን የሚባርክ ወጣት ሰውን፣ በክፍል ወይም በስብሰባ የሚፀልይ ሰውን፣ እና አስተማሪን ያጠቃልላሉ።

ታሪክ

ስዕል 3-67፣ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል የሚያሳየውን ያሳዩ። ነቢይ እና የቤተክርስቲያኑ አስራ ሁለተኛ ፕሬዚዳንት እንደነበሩ ይግለፁ። ስለ እርሱ የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፡

የቤተክርስቲያን መሪ ከሶልት ሌክ ሲቲ ለጉባኤው ቅዱሳን መፃሕፍትን ማንበብ እንዳለባቸው ሲናገሩ በሰማበት ጊዜ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል ገና ልጅ ነበር። መፅሐፍ ቅዱስ በፍጹም አንብቦ እንደማያውቅ ተገነዘበ፣ ስለዚህም እንደሚያነበው ዕቀድ አቀደ።

ስፔንሰር ቤት በመሄድ በከፍታ ላይ ባለችው ትንሽ ክፍሉ ውስጥ ገባ እና የከሰል ዘይት ፋኖሱን አበራ እና በዚያኑ ዕለት ምሽት የዘፍጥረትን የመጀመሪያ ምዕራፍ አነበበ። አስቸጋሪ ቢሆንም፣ ሌሎቹ ካደረጉት፣ እርሱም እንደሚያደርገው ያውቅ ነበር።

ከዓመት በኋላ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ሁሉንም ምዕራፍ አነበበ። ሲጨርስም፣ ዕቀድ ዐቀዶ ከግቡ በመድረሱ ጥሩ ስሜት ነበረው። (See Spencer W. Kimball, "Planning for a Full and Abundant Life," *Ensign,* May 1974, p. 88.)

- ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል መፅሐፍ ቅዱስን ለማንበብ የወሰነው ለምን ነበር? ምክንያቱም (በቤተክርስቲያን ተናጋሪው እያንዳንዱ ሰው ቅዱሳን መጻሕፍትን ማንበብ እንዳለበት ሐሳብ ስላቀረበ ነው።)
- በቤተክርስቲያን ከተናጋሪው ትዕዛዝን እንድትጠብቅ ወይም ስለ ወንጌል የበለጠ እንድትማር የረዳህን ወይም የገፋፋህን ምን ሰምተሃል?

**ማጠቃለያ**

ጨዋታ

ያዘጋጁትን ኮከብ ያሳዩ። ዛሬ ስለተናገሩት የማምለክ አራት መንገዶች ወደተፃፈበት ይጠቁሙ። ኮከቡን በወረቀት ቦርሳ ውስጥ እንደሚያደርጉት እና ለእያንዳንዱ ልጅ ኮከቡን ከቦርሳው ውስጥ ለማውጣት እድል እንደሚሰጡ ይግለፁ። ከዚያም እነርሱ ከያዙት ኮከብ ነጥብ ላይ ስለቃሉ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ይመልሳሉ።

የሚከተሉት አንዳንድ የቀረቡ ኃሳቦች ናቸው። አንድ ዓይነት ነጥብ በየጊዜው ሲመረጥ አንድ ዓይነት ጥያቄ ይጠይቁ። ለእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር ብዙ የተለያዩ መልሶች ካሉ፣ ይህ ጨዋታ

እያንዳንዱ ልጅ እንዲሳተፍ ብዙ ዕድሎችን እንዲሰጥ መድገም ይቻላል። *ማዳመጥ፡* በቤተክርስቲያን ውስጥ ልናዳምጣቸው የሚገባን አንዳንድ ሰዎች እነማን ናቸው? (ጳጳሶች፣ ቅዱስ ቁርባንን የሚባርክ ካህን፣ ንግግር የሚያደርጉ አባላትን፣ እና የጀማሪ ክፍል አስተማሪዎችን።)

*መዘመር፡* በቤተክርስቲያን ውስጥ ለመዘመር የምትወደውን አንድ መዝሙር ጥራ። (ልጁ የመረጠውን መዝሙር ክፍሉ እንዲዘምር ይፈልጉ ይሆናል።)

*መፀለይ፡* በቤተክርስቲያን ውስጥ ፀሎት ያደረግንበትን አንድ ጊዜ ጥራ። (የመክፈቻ ፀሎት፣ የህብስት ፀሎት፣ የውሃ ፀሎት፣ የመዝጊያ ጸሎት፣ የፀጥታ ፀሎቶች፣ ወይም በጀማሪ ክፍል የመክፈቻ እና የመዝጊያ ጸሎት።)

*ቅዱስ ቁርባን፡* በቅዱስ ቁርባን ወቀት ማድረግ የምትችለውን አንድ ነገር ጥራ። (ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማሰብ፣ መፀለይ፣ በአክብሮት መቀመጥ፣ ፀሎቶችን ማዳመጥ፣ ወይም የጥምቀት ቃልኪዳኖችን ማስታወስ።)

**የአስተማሪ ምስክርነት**

በትክክለኛው መንገድ ማምለክን በመምረጥ ታላቅ የሰላም በረከቶች፣ በሳል የወንጌል ዕውቀት፣ እና ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ ቀረቤታ ሊመጣ እንደሚችል ምስክርነትዎን ይስጡ። በሚቀጥለው ስብሰባቸው ልጆቹ የበለጠ በጥንቃቄ እንዲያዳምጡ ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

---

## ገንቢ ተሳትፎዎች

ከሚከተሉት ተሣትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ የተሻለ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚህኑ እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. በአንዱ ጫፍ ላይ ቁልፍ የታሰረበትን መሐረብ ያዘጋጁ። መሐረቡን ሊጥሉት እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። መውደቁን ከሰሙ እጃቸውን እንዲያነሱ ይንገሯቸው። እጃቸውን ያነሱትን በደንብ በመስማታቸው ምክንያት ያመስግኗቸው። ቁልፉን ከጫፉ የላቁና መሐረቡን እንደገና ይጣሉት። በዚህ ጊዜ ከሰሙ እጃቸውን እንዲያወጡ ልጆቹን ይጠይቋቸው።

   መሐረቡ ሲወድቀ በጥንቃቄ እንዳዳመጡ ሁሉ ዘወትር በጥንቃቄ ማዳመጥ እንዳለባቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው። ምንግዜም አንድ ሰው ለእነርሱ ንግግር ሊያደርግ ሲቆም፣ ጳጳስ ወይም የጀማሪ ክፍል ፕሬዚዳንት ወይም የጀማሪ ክፍል ልጅ ንግግር ሲያደርግ፣ ማዳመጥ ያስፈልጋቸዋል። በክፍላቸው ውስጥ አስተማሪዎቻቸው ከፊታቸው ሲቆሙ፣ አስተማሪዎቻቸው የሚሉትን መስማት ለመቻላቸው ማዳመጥ አንዱ ምልክት ነው። ጠቃሚ የሆነ ነገር ማዳመጥን በፍፁም መተው እንደሌለባቸው ለልጆቹ ያስታውሷቸው፣ ስለዚህም የሚባለውን በጥንቃቄ ማዳመጥ አለባቸው።

2. የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፡

   ካረን ወደ ጀማሪ ክፍል መሔድ ትወድ ነበር። አንድ እሁድ፣ የካረን አባት እንዲህ ብሎ ጠየቀ፣ “ዛሬ በጀማሪ ክፍል ምን ተማርሽ፣ ካረን?” ካረን ለአፍታ አሰበች፣ ከዚያም “አላስታውስም፣ አባባ፣” አለች ስታስበው፣ በጀማሪ ክፍል ውስጥ ጊዜውን በሙሉ በሚቀጥለው ቀን በሳሊ ልደት መገኘት እንዴት ግሩም እንደሚሆን እያሰበች እንደነበር አስታወሰች። በጀማሪ ክፍል ውስጥ በጭራሽ አላዳመጠችም!

   አባቷ እንዲህ አለ፣ “ካረን፣ ወደ ጀማሪ ክፍል በመሄድሽ ደስተኛ ነኝ፣ ነገር ግን እኔ እና እናትሽ ደግሞ እዚያ ስትሆኚ አክብሮት ያለሽ እንድትሆኚ እንፈልጋለን።”

   “ነገር ግን ፣ አባባ፣ ዝም ብዬ ነበር!”

   “ዝም በማለትሽ ደስተኛ ነኝ፣ ካረን፣ ያ ግን የአክብሮት አንዱ ክፍል ብቻ ነው። ሁሉንም ነገር ማዳመጥ እና በሁሉም ነገር መሳተፍ ያስፈልግሻል። ፀሎት ሲደረግ፣ ስለ ፀሎቱ እራስሽ ፀሎቱን እንደምታደርጊ አድርገሽ ማሰብ እና ከዚያም አሜን ማለት አለብሽ። ስትዘምሪ፣ ስለ መዝሙሩ ቃላት ማሰብ አለብሽ። አስተማሪሽን በጥሞና ማዳመጥ አለብሽ። በሁሉም ነገር ስትሳተፊ፣ ለሰማዩ አባት ቀረቤታ ይሰማሻል። ያም አክባሪ መሆን ማለት ነው።”

3. በክፍልዎ ውስጥ የማይመጣ ወይም ተሳትፎው ዝቅተኛ የሆነ ልጅ ካለ፣ ለዚያ ልጅ ደብዳቤ ለማዘጋጀት ከክፍሉ ጋር አብረው ጥቂት ጊዜ ይውሰዱ። ልጁ ያላገኘውን ነገር እነርሱ ግን በቤተክርስቲያን ያደረጉትን ነገር በመጠቀም ሃሳብ በማቀረብ ልጆቹ እንዲረዱዎት ያድርጉ። ልጁን በክፍልዎ ውስጥ ማየት እርሶ እና ልጆቹ እንደናፈቃችሁት በደብዳቤ ይፃፉለት። እያንዳንዱ የክፍል አባል በደብዳቤው ላይ እንዲፈርም ያድርጉ። ደብዳቤውም እንዲላክ ያድርጉ።

4. ልጆቹ "የፀሎት ቤት በሮች" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 156)።

   እሽ፣ ፀጥ በሉ።
   የፀሎት ቤት በሮች እንዲህ ይላሉ
   ይህ የፀጥታ ቦታ ስለሆነ፣
   እሽ፣ ፀጥ በሉ።
   በሰንበት እዚህ እንሰበሰባለን
   ስለ ኢየሱስ ልንማር፣ ልንፀልይ
   በፀሎት በሮቹ ውስጥ እንግባ፣
   እሽ፣ ፀጥ በሉ።

# ጾም ወደ ሰማይ አባትና ኢየሱስ ክርስቶስ ያቀርበናል

ትምህርት

41

**ዓላማው** ጾም ወደሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያቀርባቸው እንደሚችልና ልዩ ለሆኑ በረከቶች መጾም እና መጸለይ እንደሚችሉ ይረዱ ዘንድ ልጆችን ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. የማርቆስ ወንጌል 9፥17–29 እና ትምህርት እና ቃልኪዳኖች 88፥76 በፀሎት ያጥኑ።
2. ከጾም እሁድ ቀደም ብሎ ባለው እሁድ ይህንን ትምህርት ማስተማር ጥሩ ይሆናል።
3. አካባቢዎት የሚገኝ ከሆነ፣ *ከቤተሰብ የቤት ምሽት የተሟላ ቪዲዮ* ላይ (53276) *[Family Home Evening Video Supplement]* "የፆም ህግ" (4 ደቂቃ፣ 10 ሰኮንድ) የሚለውን ለማሳየት ይዘጋጁ።
4. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፥ በወረቀት ቁርጥራጮች ላይ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ያዘጋጁ እና በማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጧቸው፥
   - መጾም ማለት ምን ማለት ነው?
   - መፆም የሚገባው ማነው?
   - በጾመን ጊዜ ለጳጳስ ወይም ለቀርንጫፍ ፕሬዚዳንት የምንሰጠው ገንዘብ፣ ምን ይባላል?
   - ጳጳሱ በጾም ብኩራቶቻችን ምን ያደርጋል?
   - ለጾም አንዳንድ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
   - ጾም እንዴት ነው የሚረዳን?
   - የጾም እሁድ መቼ ነው?
   - ጾም ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚያሳየው ምንድን ነው?
   - አንተ ወይም አንድ የምትወደው ሰው እርዳታ ቢፈልግ ለመፆም ፈቃደኛ ነህን?
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅቶች ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ጸሎት እንዲያደርግ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲሰሩ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ጾም ማለት ለጽድቅ አላማ ያለ ምግብ እና መጠጥ መቆየት ማለት ነው**

የአትኩሮት ተሳትፎ

"የጾም ህግ" የሚለውን ለልጆቹ ያሳዩ።

የሚከተለውን ገጠመኝ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

አንድ እሁድ ማለዳ ፊሊፕ እናቱ ቅዱሳን መፃሕፍትን እያጠናች ወዳለችበት ማዕድ ቤት በመጣደፍ ገባ።

"ርቦኛል"፣ "ለቁርስ ምን አለ?" በማለት ጠየቀ።

የፊሊፕ እናት በሃዘኔታ ወደ እርሱ በመመልከት እንዲህ አለች፣ "አባትህ ታሟል።"

የፊሊፕ አባት በአደጋ ቆስሏል፣ እናም ሆስፒታል ታሞ ገብቷል፣ መንቀሳቀስም አይችልም።

ፊሊፕ አይኖቹ በእንባ እንደተሞሉ “ተሽሎታል ብዬ አስቤ ነበር፣” ሲል መለሰ።

እናቱ በቀስታ እንዲህ ስትል ተናገረች “ፊሊፕ፣ አባትህ ዛሬ እምነታችንን እና ፀሎታችንን ይፈልጋል። አባትህ እንዲሻለው አሁን በፀሎት ወደሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ መቀረብ ያስፈልገናል።

“ይህንን ለማድረግ፣” የፊሊፕ እናት ቀጠለች፣ “ዛሬ የተወሰኑ ምግቦቻችንን አንበላም። ያለምግብ እና መጠጥ እንቆያለን። ለአባትህ ያንን ለማድረግ ፈቃደኛ ትሆናለህ?”

“አዎን፣ እሆናለሁ፣” በማለት ፊሊፕ መለሰ።

- ለጽድቅ ዓላማ ያለምግብ እና መጠጥ መቆየትን ምን እንለዋለን? (ጾም።)

በመፆም፣ የሰማዩ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምንወዳቸው እና እንደሚረዱን እንዲሁም ፀሎታችንን እንደሚሰሙ እምነት እንዳለን እንደምናሳይ ይግለፁ።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ መፆም ለእኛ ከባድ መሆኑን ያውቃሉ። በምንጾም ጊዜ፣ ፀሎታችን ልባዊ እንደሆነ እና እርዳታቸውን በእውነት እንደምንሻ ያውቃሉ።

**ውይይት**

ሕፃናት ልጆች እና በሽተኞች ጾም እንደማይጠበቅባቸው ይግለጹ። ከተጠመቁን በኋላ መፆም እንጀምራለን። ይህ ለተጠመቁት የሚፈለግባቸው ነገር ስለሆነ፣ ለመጠመቅ ብቁ በሆኑበት ጊዜ ለመፆም ማሰብ መጀመር አለባቸው።

ቢያንስ በየወሩ አንድ እሁድ የቤተክርስቲያኑ አባላት ሁለት የምግብ ጊዜያትን እንዲጾሙ መጠየቃቸውን ይግለፁ። በዚህ ወቀት፣ አንበላም ወይም አንጠጣም። ይህን ልዩ ቀን በየወሩ የጾም እሁድ እንለዋለን።

የኋለኛው ቀን ነቢያቶቻችን ደግሞ ለችግረኞች እንድንሰጥ መጠየቃቸውን ይግለፁ። እየጾምን ሳለ ሣንበላ ወይም ሣንጠጣ ቢያንስ የቀጠብነውን የገንዘብ ልክ ለቤተክርስቲያን እንድንሰጥ ጠይቀውናል። የምንሰጠው ገንዘብ የጾም ብኩራት ይባላል፣ እናም ለድሆች እና ለችግረኞች ልብስ እና ምግብ ለመግዛት ይጠቀማል።

- የጾም ብኩራቶቹ ምንድን ናቸው? (ድሆችን ለመርዳት ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ገንዘብ።)
- ይህ ገንዘብ ለምን ይጠቀማል? (ምግብን፣ ልብስን፣ እና ሌላ አስፈላጊ ነገሮችን ለመግዛት።)

ፊሊፕ እና ቤተሰቡ ለፊሊፕ አባት እንዳደረጉት፣ በማንኛውም ጊዜ ለእርዳታ መፀለይ እና መፆም እንደምንችል ይግለፁ። እኛ እና የምንወዳቸው ሰዎች ሁልጊዜ የሰማይ አባትን እርዳታ እንሻለን፣ ነገር ግን በቤተሰባችን ውስጥ አንድ ሰው በጣም የሚታመምበት ወይም የምንፈታቸው የተለየ ችግሮች የሚኖሩብን ጊዜያቶች አሉን። ያን ጊዜ ከጾም እሁድ ውጪ እንደሚለን።

**የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ**

ጾም እና ጸሎት እንዴት ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚያውቅ ይጠቁሙ። የሚከተለውን ታሪክ ከማርቆስ ወንጌል 9፡17–29 ላይ በራስዎ አባባል ይናገሩ። ታሪኩን ተናግረው ከጨረሱ በኋላ፣ ልጆቹ በጨዋታ መልክ እንዲያቀርቡት ይፈልጉ ይሆናል።

አንድ ቀን ኢየሱስ ክርስቶስ እና ደቀመዛሙርቶቹ አንድ ላይ ነበሩ፣ እና በዙሪያቸውም ብዙ ሕዝብ ከበዋቸዋል። አንድ ሰው ከዚያ ከተሰበሰቡት ውስጥ ወደ ኢየሱስ መጣ። ይህ ሰው ለብዙ አመታት በጣም ታሞ ስላለ ልጁ አሳዛኝ ታሪክ ለኢየሱስ ነገረው። ይህ ሰው ልጁን እንዲባርኩለት የኢየሱስን ደቀመዛሙርቶች ጠይቆ ነበር፣ ነገር ግን በረከታቸው አልፈወሰውም ነበር። እንባ ባዘለ አይኑ፣ አባትየው ኢየሱስ ልጁን እንዲፈውሰው ጠየቀው። ልጁ ሊፈወስ እንደሚችል ያውቅ ነበር። ኢየሱስም በሽተኛውን ልጅ ፈወሰ፣ እጁንም ይዞ አነሳው፣ እናም በእግሮቹ አቆመው። ልጁም ተፈወሰ።

ደቀመዛሙርቶቹ ተደነቁ። ሰውየው ልጁን ከወሰደው በኋላ፣ ደቀመዛሙርቶቹ በረከታቸው ይህንን ልጅ ለምን እንዳላዳነው ኢየሱስን ጠየቁት። ይህንን ልጅ ለማዳን፣ ከፀሎት የበለጠ ማድረግ እንደሚያስፈልጋቸው መለሰላቸው። መጾም ያስፈልጋቸው ነበር።

የሰማዩ አባት ዘወትር ፀሎታችንን እንደሚሰማ ለልጆቹ ይንገሯቸው፣ ነገር ግን ለመፆም ፈቃደኞች ስንሆን ብቻ፣ ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት በእነርሱ ላይ እምነት እንዳለን እናሳያለን።

**ጾም ወደ ሰማዩ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የበለጠ መቀረባችን እንዲሰማን ሊረዳን ይችላል**

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ

ለመፆም እና ለመፀለይ ፈቃደኞች ስንሆን፣ የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን እንደምንወዳቸው እንደምናሳይ እና እርዳታቸውን መቀበል እንድንችል ወደ እነርሱ ለመቀረብ እየሞከርን እንደሆነ ይጠቁሙ።

ታሪኮች እና ውይይት

ጾም እና ፀሎት ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት እንደሚያቀርባቸው ልጆቹ እንዲገነዘቡ ለመርዳት፣ የሚከተሉትን ታሪኮች እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው።

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

ወቅቱ የፀደይ ወራት ነበር እናም በሸለቆው ያሉ ገበሬዎች ተጨንቀዋል። ደረቅ ክረምት ነበርና፣ አዝርዕታቸውን ለመዝራት ዝናብ ይፈልጉ ነበር።

የስቴክ ፕሬዚዳንቱ ልዩ የሆነ የጾም ጊዜ ለመያዝ ወሰነ፣ እና እያንዳንዱ ጳጳስ ይህንኑ ለዋርዱ አባላት እንዲያስታውቅ ጠየቀ። የሚያስፈልጋቸውን የተለየ እርዳታ መቀበል ከመቻላቸው በፊት ሰዎቹ ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ መቀረብ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቅ ነበር። በስቴኩ ውስጥ ከሁሉም ሥፍራ ስቴክ ያሉት ሰዎች በጾም እና በፀሎት ለመቀላቀል ወደ ስብሰባው መጡ። እህል መዝራት እንዲችሉና የዘሯቸው ይበቅሉ ዘንድ ዝናብ ወይም በረዶ እንዲጥልላቸው ጸለዩ። ቢጠብቁ ቢጠብቁ የሚፈልጉት እርጥበት ግን አልመጣም።

ወራቶች አለፉ። ሰዎቹ መፆም እና መፀለይን ቀጠሉ። በመጨረሻም፣ የስቴክ ፕሬዚዳንቱ ሌላ ስብሰባ ጠራ። "አዝርዕታችሁን ዝሩ፣ የሰማይ አባት ፀሎታችሁን ሰምቷል፣" ሲል ለሰዎቹ ተናገረ።

ምንም እንኳ ገበሬዎቹ የዝናብ ምልክት ባያዩም፣ እንደታዘዙት አደረጉ። በጥቂት ሳምንታት ውስጥ፣ የሰማይ አባት መልስ መጣ። ከቀን ወደ ቀንም ዝናብ ዘነበ፣ እህሎችም ለማደግ የሚያስፈልጋቸውን እርጥበት ሰጣቸው። በዚያ ዓመት ገበሬዎቹ ካዩዋቸው ምርጥ እህሎች አንዱን አገኙ። (ዴቪድ ካርል ዳኒየልሰን፣ "Rain in Due Season," *Ensign,* July 1978, ከገጽ 68–69 ተመልከት።)

- የአካባቢው የቤተክርስቲያን መሪዎች ሰዎቹ እንዲጾሙ እና እንዲፀልዩ የጠየቁት ለምንድን ነበር?
- ጾም እና ፀሎት የረዳቸው እንዴት ነበር? (ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ አቀረባቸው። እህሎቻቸው እንዲያድጉ የሚያስፈልጋቸውን ዝናብም አገኙ።)

አሁን ሁለተኛውን ታሪክ ይናገሩ፥

ወጣቷ ልጃገረድ፣ ሮንዳ፣ በመኪና አደጋ ቆሰለች። ቤተሰቦቿ አስከፊውን ዜና ሲሰሙ፣ በሆስፒታል ውስጥ ጎኗ ለመሆን ተጣደፉ። ራሷን ስታ ነበር፣ ማለትም ለመናገር ወይም ለመንቀሳቀስ አትችልም ነበር።

ከቀን ወደ ቀን እንደገና እንደሚሻላት ተስፋ በማድረግ እና በመፀለይ ቤተሰቦቿ በሆስፒታል ውስጥ ይጠባበቁት ነበር። ይሁን እንጂ፣ ፀሎታቸው በቂ የሆነ አይመስልም ነበር። ፍቅራቸውን ለእነርሱ ለማሳየት እና ሴት ልጃቸውን እንዲፈውሱላቸው ለመጠየቅ ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ለመቀረብ ፈለጉ።

ቤተሰቡ ለመጾም እና ለመፀለይ ወሰነ። ዘመዶቻቸው፣ ጎረቤቶቻቸው፣ እና ጓደኞቻቸው በሙሉ በፆም ሊረዷቸው ፈለጉ። ጳጳሱ ጾሙን በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አሳወቀ፣ እናም በዋርዱ ያሉ ብዙዎች ከእነርሱ ጋር ፆሙ። ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንደቀረቡ ተሰማቸው እና ለሮንዳ መልካም ከሆነ የሰማይ አባት እንደሚረዳቸው አወቁ፡፡

በኋላ፣ በፀሎት ተንበርክከው እንዳሉ፣ የሮንዳ ወላጆች ሴት ልጃቸው እንደሚሻላት ተሰማቸው። በዚያ ማለዳ ወደ ሆስፒታል ክፍሏ ሲገቡ፣ ወደላይ በመመልከት አናገረቻቸው። በኋላም በአልጋ ላይ መቀመጥ እና መብላት ቻለች። ሮንዳ ሊሻላት ነው። ጳጳሱም ለቤተሰቡ በዛ ጾም ምክንያት፣ የዋርዱ ሰዎች አንድ ላይ መቀራረባቸውን እና ከመቼውም በበለጠ እርስ በእርስ የበለጠ ፍቅር ማሳየታቸውን ነገራቸው።

- በዚህ ልዩ በሆነው ጾም ምክንያት ምን ተከሰተ? (ልጅቷ ተባረከች እናም ደህና ሆነች። በዋርዱ ያሉትም ሰዎች ተቀራረቡ እናም እርስ በርሳቸው የበለጠ ፍቅር አሳዩ።)

አንዳንዴ የሰማይ አባት ለተጎዱ እና ለታመሙ ሰዎች ሌሎች ዕቀዶች እንዳለው ልጆቹን ያስታውሷቸው። ጾም እና ጸሎትን ተከትሎ ሳይሻላቸው ቢቀር፣ ዕውቀቱ ከእኛ ዕውቀት የበለጠ ታላቅ መሆኑን በማወቅ፣ የሰማይ አባትን ፍቃድ መቀበል ያስፈልገናል።

የአስተማሪ ምስክርነት

ልጆቹ መጾም እንዲፈልጉ የሚያበረታቸውን ልምድ በማካፈል ስለፆም አስፈላጊነት ምስክርነትዎን ይስጡ። ይህም የግል ልምድዎ ወይም በሚያውቁት ሰው ላይ የተከሰተ ነገር ሊሆን ይችላል። በፈቃደኝነት መፀለይ እና መጾም ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ለመቀረብ እና እርዳታቸውን እንደምንፈልግ ለማሳየት በጣም ጠቃሚ ከሆኑት መንገዶች አንዱ እንደሆነ ይግለፁ።

ስለ ጾም የሚያውቁትን ማንኛውንም ልምዶች ልጆች እንዲናገሩ ያድርጉት።

**ማጠቃለያ**

ውይይት

ልጆቹ ስለ ጾም እና ፀሎት የተማሩትን እንዲከልሱ ይርዷቸው። ካዘጋጁት ማስቀመጫ ውስጥ እያንዳንዱ ልጅ አንድ ጥያቄ እንዲወስድ እና ለመመለስ እንዲሞክር ያድርጉ።

- መፆም ማለት ምን ማለት ነው? (ለጽድቀ ዓላማ ያለ ምግብ እና መጠጥ መቆየት ማለት ነው።)
- መፆም ያለበት ማን ነው? (ማንኛውም የሚችል ሰው።)
- በመፆም ለጳጳሱ ወይም ለቀርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ የምንሰጠው ገንዘባችን፣ ምን ይባላል? (የፆም በኩራት)
- ጳጳሱ በጾም በኩራታችን ምን ያደርጋል? (ድሆችን እና ችግረኞችን ለመርዳት ይጠቀምበታል።)
- ለመጾም አንዳንድ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው? (ወደሰማይ አባት ለመቀረብ። ከሰማይ አባት እርዳታን ለመቀበል። ሌሎችን ለመርዳት። ትዕዛዝም ነው።)
- ጾም እንዴት ነው የሚረዳን? (ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ መቀረባችን እንዲሰማን ይረዳናል።)
- የጾም እሁድ መቼ ነው? (ዘወትር በወሩ የመጀመሪያው እሁድ ነው።)
- ጾም ለሰማይ አባት እና ለኢየሱስ ክርስቶስ የሚያሳየው ምንድን ነው? (ፀሎታችን ልባዊ መሆኑን እና በእነርሱ እምነት እንዳለን።)
- አንተ ወይም አንድ የምትወደው ሰው ዕርዳታ ቢፈልግ ለመጾም ፈቃደኛ ትሆናለህ?

ልጆቹ ስለ ፆም ለወላጆቻቸው እንዲናገሩ እና መቼ እና ለምን ያህል ጊዜ መፆም እንዳለባቸው እንዲወስኑ ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ በተሻለ መንገድ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚህኑ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ“የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. በዕድሜ አነስተኛ ለሆኑ ልጆች፣ የሚከተለው ታሪክ እና ውይይት ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፣

   የ “አን አባት ረኸም ጉዞ ላይ ነበር። ሲመለስ፣” አን ስላየችው ተደስታ ነበር። በጣም አቀፋ ሳመችው፣ እናም ከነበረበት ከተማ ያመጣውን ልዩ የሆኑ የከረሚላዎች ትንሽ ቦርሳ ሰጣት።

   ጆአን ትንሹ ጎረቤቷ ዳኒ፣ ከግቢው በስተጀርባ ወደሚጫወትበት ሥፍራ ቦርሳውን ይዛ ሮጠች። እናቱ ታማ በነበረበት ጊዜ እናቷ ዳኒን ተጠብቀው ነበር።

“ተመልከት! አባባ ያመጣልኝን።” በማለት ጆአን ጮኸች።

ዳኒ ወደ ቦርሳው ውስጥ ተመለከተ።

- ጆአን በመቀጠል ያደረገችውን ምን ታስባላችሁ?

“ምንም መውሰድ አትችልም፣” ያለች ይመስላችኋል፣ ወይስ “ትንሽ እንድትወስድ እፈልጋለሁ” ያለች ይመስላችኋል?

“መውሰድ አትችልም፣” ብትል ዳኒ ምን ይሰማዋል? እንደዚያ ብትል አባቷ ምን ያስባል? ያዝናል ወይስ ደስተኛ ይሆናል?

“ትንሽ እንድትወስድ እፈልጋለሁ፣” ብትል፣ ዳኒ ደስተኛ ይሆናልን? አባቷስ ደስተኛ ይሆናል? የሰማይ አባታችንስ ደስተኛ ይሆናል? ጆአንስ ደስተኛ ትሆናለች?

ጥሩ፣ ጆአን ያለችው፣ “ትንሽ እንድትወስድ እፈልጋለሁ፣” ነው እናም ሁሉም ተደስተው ነበር።

በፆም እሁድ ጆአን እንዳደረገቸው ማካፈል ትችላላችሁ። ያለቁርስ መቆየት ትችላላችሁ፣ እናም ባለመብላት (አብዛኛውን ልጆች የሚበሉትን ምግቦች ይጥቀሱ)፣ ለወላጆቻችሁ ገንዘብ መቆጠብ ትችላላችሁ። ከዚያም እነሱ ገንዘቡን ለጳጳስ መስጠት ይችላሉ፣ እሱም ለራበው ሰው ይሰጠዋል።

- ይህ ምግብ የሚፈልጉትን ሰዎች ደስተኛ ያደርጋቸዋልን?
- እናንተንስ ደስተኛ ያደርጋችኋል?

2. ልጆቹ እንዲጾሙለት የሚፈልጉትን የአንድ ሰው ስዕል እንዲስሉ ያድርጉ።

ትምህርት

# 42

# አስራት

| | |
|---|---|
| **ዓላማው** | አስራትን እንዲከፍሉ የልጆቹን ፍላጎት ለማጠንከር ነው። |

**ዝግጅት**

1. ትምህርት እና ቃልኪዳ 119፥3–4 እና ትንቢተ ሚልኪያስ 3፥10ን በፀሎት ያጥኑ፡፡
2. "አስራቴን ለጌታ መስጠት እፈልጋለሁ" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆች እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ለመርዳት ተዘጋጅ (*የልጆች የመዝሙር መፅሀፍ፣* ገፅ 150)።
3. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፥
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ እና ትምህርት እና ቃልኪዳኖች።
   ለ. በአካባቢዎ ያለውን የቤተመቅደስ ስዕል ያግኙ።
   ሐ. ለእርሶ እና ለእያንዳንዱ ልጅ የአስራት እና የሌሎች በኩራቶችን ወረቀቶች እና ፖስታ።
   መ. ለእያንዳንዱ ልጅ እርሳስ።
   ሠ. ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው ሳንቲሞች አስር።
   ረ. ጠርሙስ።
   ሰ. አስር ፖም (ወይም ሌላ ፍራፍሬ) ወይም ዕቃዎች።
   ሸ. ስዕል 3-26፣ ልጁ አስራት ሲከፍል፣ ስዕል 3-62፣ ፓርትላንድ ኦሬገን ቤተመቅደስ (62617)፣ ስዕል 3-68፣ የቤተሰብ ታሪክ የሚያጠኑ ሰዎች፣ እና ስዕል 3-69፣ ወንጌላዊያኖች ሲዘዋወሩ (62611)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

### የአስራት ህግ

**የአትኩሮት ተሳትፎ**

ሁሉም ማየት በሚችሉበት ቦታ አስሩ ፖሞች (ወይም ሌሎች ዕቃዎችን) ያሳዩ።

- እነዚህን አስር ፖሞች ብሰጣችሁ እና ከዚያም አንዱን ብቻ እንድትመልሱልኝ ብጠይቅ፣ ልትሰጡኝ ፈቃደኞች ናችሁን? ከሆናችሁ እጃችሁን አውጡ።
- ፖሞቹ እንዲያድጉ ያደረገ ማን ነው?
- ምድርን የፈጠረ ማን ነው?

**የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ**

ይህ ዓለም እና በውስጡ ያለው መልካም ነገር ሁሉ በሰማይ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ መሰጠቱን ትኩረት ይስጡበት። እያንዳንዳችንን ይወዱናል እናም ይጠነቀቁልናል። ትዕዛዛቶቻቸውን በመታዘዝ እና ቤተክርስቲያኗ እንድትጠናከር በመርዳት የራሳችንን ድርሻ በመወጣት ለፍቀራቸው እና ለመልካምነታቸው አድናቆታችንን ማሳየት እንችላለን።

ይህ ትምህርት ስለ አንድ ጠቃሚ ትዕዛዝ መሆኑን ይግለፁ። ይህንን ትዕዛዝ ስንታዘዝ፣ ቤተክርስቲያኗ እንድታድግ እንረዳለን።

ትምህርት እና ቃልኪዳኖች 119፥3–4 እርስዎ ሲያነቡ ልጆቹ እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። ጌታ በየዓመቱ ከምናገኘው አንድ አስረኛ የሆነውን አስራት፣ እንድንከፍል እንዳዘዘን ይግለፁ። ይህ ህግ ለዘለዓለም ይቀጥላል።

- የምንወደየው ትዕዛዝ የትኛው ሕግ ነው? (የአስራት።)
- አስራት ምንድን ነው?

በቁሳዊ የተደገፈ ትምህርት

አስራት ማለት አንድ አስረኛ ማለት እንደሆነ ሐሳቡን ይከልሱ። አስሩን ሳንቲሞችን ለልጆቹ ያሳዩ።

- አንድ ሰው ይህን ያህል ገንዘብ ካገኘ፣ ያ ሰው መክፈል ያለበት አስራት ምን ያህል ነው?

አንድ ልጅ እንዲመጣ እና ለአስራት አንድ ሳንቲም እንዲያነሳ ይፍቀዱለት።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተክርስቲያን አባላት ከሚያገኙት ገንዘብ አንድ አስረኛውን ለቤተክርስቲያን አስራት እንዲሰጡ እንደጠየቁ ይግለፁ። ያሉን ነገሮች ሁሉ በአንደኛው ወይም በሌላኛው መንገድ ከሰማይ አባታችን ስለሚመጡ፣ አስራትን መክፈል በእርግጥ አንድ አስረኛውን ለእርሱ መልሶ መስጠት ነው። አስራት የሰማዩ አባታችን ነው፣ እናም ልንከለክለው አይገባንም።

### አስራት እንዴት እንደሚከፈል

ተሳትፎ

የአስራትን እና የሌሎች በኩራቶችን ፖስታ ያሳዩ። በዋርድዎ የፀሎት ቤት ውስጥ የአስራት እና የሌሎች በኩራቶች ፖስታዎች እና ወረቀቶች የሚገኙበትን ቦታ ይግለፁ። እነዚህ ፖስታዎች አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት ከጳጳሱ ቢሮ አጠገብ ነው። የሚጠቀሙት አስራትን ለመክፈል ነው። ለእያንዳንዱ ልጅ የአስራት እና የሌላ በኩራቶችን ፖስታ እና ወረቀት እንዲሁም እርሳስ ይስጡ። ስማቸው እና የተከፈለውን የአስራት ልክ የት መፃፍ እንዳለባቸው ያሳዩ።

አስራታቸውን ሲከፍሉ፣ ወረቀቱን መሙላት፣ ገንዘቡንም በፖስታው ውስጥ ማድረግ፣ እናም ማሸግ፣ በፊት ለፊቱ ላይ ስማቸውን መፃፍ፣ ከዚያም ለጳጳሱ ወይም ከአማካሪዎቹ ለአንዱ መስጠት እንዳለባቸው ይግለፁ።

ልጆቹ ስማቸውን በፖስታዎቹ ፊት ለፊት ላይ እንዲፅፉ ያድርጉ።

ከማንኛውም ከምናገኘው ገንዘብ አንድ አስረኛውን መክፈል ወይም ለጳጳሱ አስራትን መስጠት ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ያሳስቡ።

- ብዙዎቻችሁ አስራትን ከፍላችኋል። ልምዶቻችሁን ለመናገር ትፈልጋላችሁን?

### አስራት የኢየሱስ ክርስቶስን ቤተክርስቲያን እንድታድግ ለመርዳት ይጠቀማል

ስዕሎች እና ውይይት

ልጁ አስራት ሲከፍል የሚያሳየውን ስዕል 3-26፣ ያሳዩ። ጳጳሱ ከተቀበለው በኋላ አስራቱ ምን እንደሚሆን ይግለፁ። አስራቱ ይቆጠርና፣ ወደቤተክርስቲያኗ ዋና ማዕከሎች ይላካል። ከዚያም የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ቤተክርስቲያኗ እንድታድግ ለመርዳት በተለያዩ መንገዶች ይጠቀሙባቸዋል፣ ለምሳሌ ቤተመቅደሶችን እና የፀሎት ቤቶችን እንደመገንባት፣ እኛ እናጠናበት ዘንድ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ እና ወንጌልን ለማወቅ እንዲረዳን ለሲሚናሪዎች ይጠቀሙበታል።

በአስራት ገንዘብ፣ በጌታ አስራት፣ የቤተክርስቲያናችን መሪዎች ምን እንደሚያደርጉ ሊያሳዩአቸው እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ከፖሞቹ አንዱን ይውሰዱ እና ለእያንዳንዱ የክፍል አባል እንዲበቃቸው በትንሹ ይቆራርጡት፣ እናም እንዲበሉት ያድርጉ። በዚሁ አይነት መንገድ፣ የምንከፍለው አስራት ብዙ ሰዎችን እንደሚረዳ፣ ያስረዱ።

በዓለም ዙሪያ ቤተክርስቲያኗን ለመርዳት አስራታችን ከሌሎች አባላት አስራት ጋር ይቀላቀላል። በብዙ መንገዶች ወደ እኛ ይመለሳል።

የሚከተሉትን ነጥቦች ያቀርቡ፣ እና ተመሳሳይ ስዕሎችን ያሳዩ፣

1. የአስራት ገንዘብ ለህንፃ ግንባታ እና ለፀሎት ቤቶች፣ ለቤተመቀደስ፣ እና ሌሎች የቤተክርስቲያን ሕንፃዎችን ለመጠገን የሚወጣ ወጪን ይከፍላል።
2. የተወሰነው የአስራት ገንዘብ ለቤተሰብ ታሪክ እና ለቤተመቀደስ ስራ ይከፈላል።
3. የተወሰነው የአስራት ገንዘብ የወንጌላውያንን ስራ ለመደገፍ ይጠቀማል።

አስራት እንደ ሴሚናሪ እና ሊኒስተቲዩት ፕሮግራሞች ላሉ ሌሎች ብዙ ነገሮችም ለመሳሰሉት እና ለመክፈል እንደሚረዳ ይገለፅ። አስራትን መክፈል መብት እና በረከት ነው። ለአስራት የምንሰጠው ገንዘብ ቤተክርስቲያናን እንደሚረዳ በማወቃችን ጥሩ ሊሰማን ይገባል።

ታሪክ

የአንድ ሰው አስራት ቤተክርስቲያናን ለመርዳት እንዴት እንደጠቀመ ለማየት ልጆቹ የሚከተለውን ታሪክ እንዲያዳምጡ ያድርጉ፣

ወንድም ዊልሰን ቤተክርስቲያኗ ስትጀመር መስራች ነበር። ጥሩ ጥማድ በሬዎች ነበሩት። እነዚህ እንሰሳቶች ወንድም ዊልሰንን እርሻውን ለማረስ ረድተውታል።

አንዴ አስራቱን የሚከፍልበት ጊዜ ሲደርስ፣ ወንድም ዊልሰን በቂ ገንዘብ እንዳልነበረው ተረዳ። ከአስራቱ ግማሹን መክፈል አልፈለገም። ሙሉውን ለመክፈል ፈለገ።

አንድ በሬ ብቻ እንኳ ይቀራል ማለት ቢሆንም፣ በመጨረሻ የሚወደውን በሬ ለአስራት ለመስጠት ወሰነ።

ወንድም ዊልሰን ለጳጳሱ በሬውን ሰጠ። ጳጳሱ ለወንድም ዊልሰን ለአስራቱ ደረሰኝ ሰጠው። ወንድም ዊልሰን በሬውን በማጣቱ ሀዘን ተሰማው። ነገር ግን የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን ስለሚወድ፣ በሬውን እንደ አስራት ለቤተክርስቲያን በመስጠቱ ተደሰተ።

ወንድም ዊልሰን ብዙውን ጊዜ ለአስራት ስለሰጠው በሬ ያስባል። ቤተክርስቲያናን ለመርዳት በሬው እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ይገረማል። አንድ ቀን ቤተመቀደስ በሚገነባበት በሶልት ሌክ ሲቲ ነበር። ሁለት ጥሩ በሬዎች ከባድ የድንጋይ ሸክሞችን ሲጎትቱ ተመለከተ። በሬዎቹን በስራ ላይ ማየት በጣም ስለተማረከው በደንብ ለማየት ቀረብ አለ። ያስደሰተው እና ያስደነቀው ከበሬዎቹ አንደኛው የቀድሞው የሚወደው በሬው እንደሆነ መገንዘቡ ነበር። በአስራት የሰጠው በሬ ቤተመቀደስን ለመስራት መርዳቱን በማወቁ ወንድም ዊልሰን ምንኛ ደስታ ይሰማው!

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፣ አስራትን መክፈል ወንድም ዊልሰንን የበለጠ አስደሰተው። አስራቱ ቤተክርስቲያኗን ለመርዳት የሚጠቀምባቸውን ብዙ መንገዶች አሰበ።

ወንድም ዊልሰን እንደሆነው፣ አስራታችን እንዴት እንደሚጠቀም አብዛኛውን ጊዜ ባናይም፣ አስራታችን ቤተክርስቲያናን ለመርዳት እንደሚጠቀም እናውቃለን።

### አስራታችንን በፈቃደኝነት መክፈል አለብን

መዝሙር

"አስራቴን ለጌታ መስጠት እፈልጋለሁ" የሚለውን መዝሙር ቃላት ለልጆቹ ያስተምሯቸው።

ለጌታ አስራቴን እሰጣለሁ፣
ሁሌም ስለማደርግ
ሁሉንም ስጦታ አስባለሁ
ለእኔም ለአንተም የሰጠውን።

ህይወትን ሰጠን፣ ውቡን አለም።
አስራቴ ትንሽ ቢመስልም፣
እምነቴን እና ምስጋናዬን ያሳያል
ለእርሱ፣ ለሁሉም ጌታ

- አስታራችንን ስንከፍል የሚደሰተው ማን ነው? (የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ።)
- አስራታችንን ስንከፍል ለሰማይ አባት ምንን እናሳያለን? (እንደምንወደው እና ለሰጠነ ነገሮች እንደምናመሰግነው።)

የመዝሙሩን የመጀመሪያ ስንኝ ልጆቹ እንዲደግሙት ያድርጉ። አስራታችንን ስንከፍል፣ የሰማዩን አባት እንደምንወደው እንደምናሳይ ይጠቁሙ። አስራታችንን ስንከፍል፣ በተለይ በፈቃደኝነት ስንከፍል የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ደስተኛ እንደሚሆኑ ያሳስቡ።

### አስራታችንን ስንከፍል እንባረካለን

የጥቀስ ንባብ

አስራታችንን ከከፈልን የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ሊባርኩን ቃል እንደገቡልን ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ትንቢተ ሚልኪያስ 3፥10 ያንብቡ።

የሰማይ አባት የሰማይን መስኮት ለመክፈት እና እኛን ሊባርከን ቃል ይገባልናል ማለት ምን ማለት ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

አስራታቸውን የሚከፍሉ በረከትን እንድሚያገኙ ይግለፁ። ከኋለኛው ቀን ነቢያት ከሆኑት አንዱ፣ ፕሬዚዳንት ሂበር ጄ ግራንት፣ በሰማዩ አባት እና በኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅ ዕውቀት፣ በጠንካራ ምስክርነት እና ትዕዛዛትን ለመታዘዝ በሚያድግ ችሎታ እንባረካለን ብለዋል (see Conference Report, Apr. 1925, ገጽ 10)። ሌሎቹም የኋለኛው ቀን ነቢያት አስራታችንን ስንከፍል፣ እንደምንበለፅግ ነግረውናል። *መበልፀግ* ማለት እንደ ምግብ እና መጠለያ አስፈላጊ በሆኑ ቁሳቁሶች እንባረካለን ማለት ነው።

- እነዚህን በረከቶች ትወዳቸዋለህን?

አስራታቸውን የሚከፍሉትን ሁሉንም ሰዎች የሰማይ አባት እንደሚባርካቸው ይጠቁሙ። የሰማይ አባታቸው እንደሚወዳቸው፣ እና ሁሉንም በተመሳሳይ መንገድ ባይባርካቸውም፣ አስራታቸውን ሲከፍሉ ለእነርሱ ጥሩ በሚሆነው መንገድ እንደሚባርካቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው።

ታማኝ መሆን እንዳለብን፣ ትክክለኛ እና ሙሉ አስራት መክፈል እንዳለብን፣ እንዲሁም በሰማይ አባት መታመን እንዳለብን ያሳስቡ።

**ማጠቃለያ**

ጨዋታ

ልጆች ወንበራቸውን በክብ እንዲያስተካክሉ ይርዷቸው፣ ወይም በወለሉ ላይ በክብ እንዲቀመጡ ያድርጉ። ጠርሙስን ማሽከርከር ይጫወቱ። ጠርሙሱን በክብ በተቀመጡት ወንበሮች መሐከል ላይ ያስቀምጡት። ጠርሙሱን ያሽከርክሩ። መሽከርከሩን ካቆመ በኋላ ጠርሙሱ የሚጠቁምበት ልጅ ለመስማማት ወይም ላለመስማማት ዕድሉ ይሰጠዋል። ከዚያም ያ ልጅ ጠርሙሱን ያሽከረክራል።

ጊዜ ከፈቀደ፣ ጨዋታውን ለመድገም ይፈልጉ ይሆናል።

የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ያንብቡ። ግለሰቡ ካልተስማማ፣ ትክክለኛውን ማስረጃ ልጆቹ እንዲሰጡ ያድርጉ።

1. አስራት መክፈል ትዕዛዝ ነው። (መስማማት።)
2. አስራት ማለት አንድ አምስተኛ ነው። (አለመስማማት። አስራት ማለት አንድ አስረኛ ማለት ነው።)
3. አስራታችንን ለቤተክርስቲያን እንከፍላላን። (መስማማት።)
4. አስራት የቤተክርስቲያን ህንፃዎች እንዲሰሩ ለመርዳት ይጠቀማል። (መስማማት።)
5. አስራት የሚሲዮናዊያንን ስራ ለመደገፍ፣ መፅሐፍትን ለማሳተም፣ እና በቤተሰብ ታሪክ እና በቤተመቅደስ ስራ ለመርዳት ይጠቀማል። (መስማማት።)
6. አስራት ብንከፍል ችግር የለም። (አለመስማማት።)
7. አስራታችንን ስንከፍል የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ይባርኩናል። (መስማማት።)

የአስተማሪ ምስክርነት

አስራትን በመክፈል ስላለ በረከት ምስክርነትዎን በመመስከር ትምህርቱን ያጠቃሉ። ልጆቹ ሁልጊዜ ትክክለኛውን እንዲመርጡ እና አስራታቸውን በደስታ እንዲከፍሉ ያበረታቷቸው።

የሚታደል ጽሁፍ

የአስራትን እና የሌሎች በኩራቶችን ፖስታዎች የጀማሪ ክፍል ሲያልቅ ለልጆቹ ይመልሱ።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ጸሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚሁኑ እንደክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. የአስራት ገንዘባቸውን ከሌላው ገንዘባቸው ለይተው የሚያስቀምጡበትን ልዩ የሆነ ቦታ እንዲያዘጋጁ ልጆቹን ይርዷቸው። ሳጥን፣ ትንሽ ማሰሮ ወይም ቆርቆሮ፣ ወይም ፖስታ ሊሆን ይችላል። ገንዘብ በሚያገኙበት ጊዜ፣ በመጀመሪያ አስራት ለመክፈል የሚያስፈልገውን መጠን ማንሳት እና ልዩ በሆነው ማስቀመጫቸው እንዲያስቀምጡ ይንገሯቸው።
2. የዋርዱን ወይም የቅርንጫፉን ገንዘብ ያዥ ጳጳሱ ወይም የቅርንጫፍ ፕሬዚዳንቱ አስራቱን ከተቀበሉ በኋላ በአሥራቱ ምን እንደሚከናወን እንዲገልፁ ይጋብዙ።
3. “የሰማይ መስኮቶች፣” የሚለውን የቪዲዮ የትምህርት አቀራረብ *በ የመጀመሪያው ትምህርት ቪድዮ ካሴት* 2 (53178) ያሳዩ።
4. ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀት ያዘጋጁ። የወረቀቱን አንድ ክፍል “የሰማዩ አባት” እና ሌላኛውን ክፍል “የእኔ” የሚል ምልክት ያድርጉበት። ልጆቹ ዘጠኝ ነገሮችን (ሳንቲሞች፣ ፖሞች፣ ወዘተ.) በራሳቸው የወረቀት ክፍል እና ምልክት “የሰማይ አባት” የሚል ምልክት በተደረገበት የወረቀት ክፍል አንድ ነገር እንዲስሉ ያድርጉ።

# የሰማይ አባትንና ኢየሱስ ክርስቶስን ስም ማክበር

ትምህርት

43

**ዓላማው** እያንዳንዱ ልጅ የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንዲያከብር እና እንዲያሞግስ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. ለመጀመሪያ ጊዜ ሲታይ ከንቱ በሚለው ቃል የሚያበቃውን፣ ሞዛያ 13፥15ን እና 1ኛ ሳሙኤል 3፥1–10፣ 19–20 ለማንበብ ይዘጋጁ እና በፀሎት ያጥኑት።
2. በጣም ትንሽ ህጻንን ለመወከል። በትንሽ ብርድ ልብስ የተጠቀለለ አሻንጉሊት ያምጡ (ወይም የተጠቀለለ ብርድልብስ ወይም ፎጣ ይጠቀሙ)
3. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፥
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
   ሐ. ስዕል 3-47፣ አቢናዳይ በንጉስ ኖሀ ፊት (62042፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 308)፣ ስዕል 3-67፣ ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦል፣ ስዕል 3-70፣ ልጁ ሳሙኤል በጌታ ሲጠራ (62498፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 111)።
4. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ክትትል ያድርጉላቸው።

### ስሞች አስፈላጊ ናቸው

የአትኩሮት ተሳትፎ

በትንሿ ህፃን (አሻንጉሊት ወይም ብርድ ልብስ) ላይ ፈገግ ያሉ ያስመሰሉና በክንድዎ የሚሉ ያስመስሉና በክንድዎ ውስጥ ይቀፏፏዋት። ወደ ላይ ይመልከቱ እና ለልጆቹ ይህን ይንገሯቸው፣ “ትንሽ ህፃን ልጅ ሳላችሁ፣ ወላጆቻችሁ ለእናንተ ስም መርጠውላችኋል። ያ ስም የሚወዱት እና እንዲኖራችሁ የሚፈልጉት ስም ነው።”

- ወላጆቻችሁ የተለየ ስማችሁን የሰጧችሁ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁን? (እያንዳንዱ ልጅ እንዲመልስ ይፍቀዱ። ጥቂቱ በዘመዶች ወይም በቀድመ አያቶች ወይም ልዩ በሆነ ሌላ ምክንያት ይሆናል የተሰየመው። ልጆቹ እነዚያን ስሞች ለምን እንዳገኙ ቢያውቁም ባያውቁም ሁሉም ልጆች ስለስማቸው ጥሩ ስሜት እንዲሰማቸው ይርዷቸው።
- ሰዎች ስማችሁን በቁጣ ሲጠሩት፣ ሲያሾፉበት፣ ወይም በትክክል ባይጠሩት ምን ይሰማችኋል?

ስሞች በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን ይግለፁ። ሰዎች በስማችን ይለዩናል። ስም ሰውን ለይቶ ያሣያል።

ውይይት

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ስማችንን እንደሚያውቁት ለልጆቹ ያስታውሷቸው። የሰማይ አባት በተቀደሰው ጫካ ውስጥ ለልጅ ዮሴፍ ስሚዝ የተናገረው የመጀመሪያው ቃል “ዮሴፍ” የሚለውን ስም እንደነበር ያስታውሱ። የሰማይ አባት በስሙ ነበር የጠራው። ልጁ ሳሙኤል በጌታ ሲጠራ የሚለውን ስዕል 3፥70፣ ማሳየት ይችላሉ፣ እናም ጌታ ሳሙኤልን በስሙ የጠራበትን የሳሙኤልን የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪክ (1ሳሙኤል 3፥1–10፣ 19–20ን ይመልከቱ)፣ ይናገሩ።

ስም ሰውን ለይቶ እንደሚያሳይ ይግለፁ። የምታውቀውን ሰው ስም በሰማህ ጊዜ፣ ስለእዚያ ሰው ታስባለህ። አንድ ህፃን ስም ሲሰጠው ይህ ወቀት ልዩ ገጠመኝ ነው። ህፃኑ የመልከጼዴቀ የክህነት ስልጣን ባላቸው ሰዎች ይከበብ እና ስም ይሰጠዋል እንዲሁም ይባረካል።

- የጳጳሳችንን ስም ስትሰሙ (የጳጳሳችሁ ወይም የቀርንጫፍ ፕሬዚዳንታችሁን ስም እንበል)፣ ስለምን ዓይነት ሰው ታስባላችሁ? (ምላሾችን ይቀበሉ፣ ልጆቹ ትክክለኛ የሆነ ነገር እንዲያስቡ ያበረታቷቸው።)

ልጆቹ የሚያውቋቸውን የመልካም ሰዎች ስም በመጠቀም፣ ይህንን ተሳትፎ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ መድገም ይፈልጉ ይሆናል።

የጥቁር ሰሌዳ ውይይት

*ኢየሱስ ክርስቶስ* የሚለውን ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፣ ወይም በጣም ልዩ የሆነ ስም ሊጠሩ እንደሆነ ለልጆቹ ይንገሯቸው። በሥርዓት እና በአክብሮት “ኢየሱስ ክርስቶስ” ይበሉ። ከዚያም ልጆቹ ስሙን ከእርሶ ጋር እንዲሉት ያድርጉ።

- ይህን ስም ስትሰሙ ወይም ስታዩ ምን ዓይነት ሰው ታስባላችሁ?

*የሰማይ አባት* የሚለውን ስም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉ፣ ወይም ለአዳኛችን ስም እንዳደረጉት ድምፃን ከፍ በማድረግ ይበሉት። ልጆቹ ከእርሶ ጋር እንዲሉት ያድርጉ።

- ይህን ስም ስትሰሙ ወይም ስታዩ ምን ዓይነት ሰው ታስባላችሁ? (አፍቃሪ የሆነ ሰው እና ብዙ ነገሮችን የሰጠንን ሰው።)

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ብዙ ነገሮች እንዳደረጉልን ይግለፁ። እንወዳቸዋለን። ስማቸውን ስንሰማ፣ ብዙውን ጊዜ ስላደረጉት ብዙ መልካም ነገሮች እናስባለን። ስለ እነርሱ ስናስብ ፍቀር እና ምስጋና ይሰማናል።

የምንወዳቸውን እናከብራቸዋለን እናሞግሳቸዋለን። ስማቸውን በፍቀርና በቀንነት መንገድ በመጠቀም ክብርና ሞገስን እናሳያቸዋለን።

የእምነት አንቀፅ

ልጆቹ የመጀመሪያውን የእምነት አንቀጽ አንድ ላይ እንዲሉ ይርዷቸው።

**የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም እንድናከብር ታዘናል**

የስዕል ውይይት

አቢናዳይ በንጉስ ኖህ ፊት ሆኖ የሚያሳየውን ስዕል 3-47፣ ያሳዩ።

- በዚህ ስዕል ላይ ምንድን ነው የሆነው?

ነቢዩ አቢናዳይ ሰዎችን ሲያስተምር፣ ከእግዚአብሔር ስለመጡት፣ አስርቱ ትዕዛዛት እንደነገራቸው ይግለፁ።

አስርቱ ትዕዛዛት በትክክለኛው መንገድ እንድንኖር የሚረዱን መመሪያዎች ናቸው። ሶስተኛው ትዕዛዝ የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ማክበር እና ማሞገስ እንዳለብን ይነግረናል።

የጥቀስ ውይይት

ሶስተኛውን ትዕዛዝ ሲያነቡ ልጆቹ እንዲሰሙ ያድርጉ። ሞዛያ 13፣15 ያንብቡ፣ *በከንቱ*የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ ከመጣ በኋላ ያቁሙ።

“በከንቱ” ማለት የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ክብር በሌለው መንገድ ወይም ልጆቹ ስለ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ በማያሰላስሉበት ጊዜ መጠቀም ማለት እንደሆነ ይግለፁ።

የጥቀሱን ቃላት ልጆቹ ከእርሶ ጋር እንዲደግሙት ያድርጉ።

- የሰማይ አባት ወይም ኢየሱስ ለማለት የምንጠቀማቸው ሌሎቹ አንዳንድ ስሞች እነማን ናቸው? (እግዚአብሄር፣ በሰማይ ያለው አባት፣ ያህዌ፣ ጌታ፣ ክርስቶስ፣ አዳኝ።)

ምንግዜም ከእነዚህ ስሞች አንዳቸውን ስንጠቀም፣ በክብር መጥራት እንዳለብን ልጆቹ እንዲያውቁት ይርዷቸው። እነዚህ ስሞች በንዴት ወይም በቀልድ ሁኔታ መጠራት የለባቸውም። እነዚህን ስሞች በዚህ መንገድ የሚጠቀም ሰው እየማለ ነው። እነዚህ ስሞች እንደ መሀላ ቃላት

በፍፁም መጠቀም አይገባም። የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መጠቀም የሚገባን ስንፀልይ ወይም ስለ እነርሱ ክብር ባለው መንገድ ስናወራ ብቻ ነው።

ክፍልዎት ማንበብ የሚችል ከሆነ፣ አንድ ልጅ በጥቁር ሰሌዳው ላይ *ሙገሳ* እና *አክብሮት* የሚሉትን ቃላቶች መጥቶ እንዲፅፍ ይጋብዙት። የሰማይ አባትን እና ኢየሱስ ክርስቶስን የምንወዳቸው ከሆነ፣ በፍቀር እና በቀን መንገድ ብቻ በመጠቀም ለስማቸው ሙገሣ እና አክብሮትን እናሳያለን የሚለውን ሀሳብ ያጠናክሩ።

### የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በተገቢው መንገድ መጠቀም

- የሰማይ አባትን ስም ለመጠቀም ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው? (በሥርዓት እና በክብር ስንናገር እና ስንፀልይ ነው።)

ታሪክ

አንድ እናት ለልጇ ልጅ ስለነበረችበት ጊዜ ይህን ታሪክ ነገረችው። በራስዎ አባባል እንደገና ይናገሩት።

“ ‘ትንሽ ሴት ልጅ ሳለሁ፣ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት የምሄደው ከወንድሜ ጋር ነበር። በቤቱ አጠገብ ስንሮጥ የሚያባርረንን ትልቁን ጥቁር ውሻ ለመሸሽ ዘወትር አቋራጭ መንገድ እንጠቀም ነበር። በትክክለኛው ጊዜ ብንሮጥ፣ ወደ አጥሩ እንጠጋና ደህነታችንን አስተማማኝ እናደርገዋለን። ወንድሜ መቼ እንደሚሮጥ ይነግረኛል።

“ ‘አንድ ቀን ብቻዬን ነበርኩ እናም በትክክለኛው ሰዓት አልሮጥኩም ነበር። ውሻው አስፈራራኝ፣ እና እኔም በፍርሃት በጎዳናው ላይ ደነዘዝኩ። ወደ እኔ ሲጮህ፣ [በፍርሃት] “የሰማይ አባት፣ እርዳኝ!” በማለት የቻልኩትን ያህል ድምፄን ከፍ በማድረግ ጮኽኩኝ፣’”

ልጇ ሲገልፅ፣ “በድንገት፣ ውሻው መንገዱ የጠፋበት በመምሰል እንደቆመ፣ እናቴ ልብ አለች፣ እና ለመዳን በአጥሩ ላይ ተንጠለጠለች። ፀሎቷ እንደተመለሰ አወቀች” (S. Michael Wilcox, “No Other Gods before Me,” *Ensign*, Jan. 1994, ከገፅ 22–23).

ስንፀልይ ወይም በአክብሮት ስለ እነርሱ ስንናገር የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መጠቀም እንዴት ጠቃሚ እንደሆነ ያሳስቡ።

ስዕል እና ታሪክ

ፕሬዚዳንት ስፔንሰር ደብሊው ኪምቦልን የሚያሳየውን ስዕል 3-67፣ ያሳዩ፣ እና ተወዳጅ ነቢይ እና የቤተክርስቲያኗ አስራ ሁለተኛው ፕሬዚዳንት እንደነበር ለልጆቹ ይንገሯቸው።

የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፣

አንድ ቀን ከቀዶ ጥገና በኋላ፣ ጠባቂው እየተንተባተበ እና እየተደናቀፈ እያለ ፕሬዚዳንት ኪምቦል ከሆስፒታሉ ቀዶ ጥገና ክፍል እየተገፋ ወጡ። ጠባቂው መማል እና የጌታን ስም በከንቱ መጥራት ጀመረ። ፕሬዚዳንት ኪምቦል ቢታመሙም፣ ጠባቂውን እንዲህ ሲሉ ተማፀኑ፣ “እባክህን! እባክህን! ስሙን [በመጥፎ ሁኔታ የምትጠቀምበት]ያ ጌታዬ ነው።”

ጠባቂው ፀጥ አለ። “ይቀርታ” በማለት አንሾካሾከ (“President Kimball Speaks Out on Profanity,” *Ensign*, Feb. 1981, ገጽ 3 ተመልከት)።

ውይይት

- ጠባቂው ያልታዘዘው ትዕዛዝ የትኛው ነው?
- ፕሬዚዳንት ኪምቦል ይህንን መስማት ያልፈለጉት ለምንድን ነበር?
- የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም መጠቀም ያለብን መቼ ነው?
- የሰማይ አባትን እና የኢየሱስን ስም በጎረቤት ወይም በትምህርት ቤት ሰዎች በከንቱ ሲጠቀሙት ብትሰሙ ምን ታደርጋላችሁ?

### ማጠቃለያ

ልጆቹ የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ስሞች በክብር እና በሥርዓት እንዲጠቀሙበት ያበረታቷቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ የተሻለ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚሁኑ እንደክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. የሚከተለውን የድርጊት ቁጥር ከልጆቹ ጋር ደግመው ያንብቡት፥

   ስለ ኢየሱስ በእርጋታ ተናገሩ፣
   ድምጻችሁን አለስልሱ። (ሌባ ጣትን ከንፈሮቻችሁ ላይ አድርጉ)
   ከትክክለኛ ምርጫዎቻችሁ ጋር ስሙን አክብሩ።
   የሰማይ አባታችንን ስም፣
   እንደ ፀሎት (እጃችሁን አጣጥፉ እናም ጭንቅላታችሁን አጎንብሱ)
   በታላቅ ፍቅር እና ጥንቃቄ ብቻ ሊጠራ ይገባል።


2. አንዱን ልጅ ትክክለኛ ባልሆነ ስም ይጥሩት፣ እናም የሆነ ነገር እንዲሰራሎት ይጠይቁት። ትክክለኛ ባልሆነ ስም በመጠራቱ እንዴት እንደተሰማው ለተቀሩት ልጆች እንዲያብራራ ይጠይቁት። ስሞቻችንን አንድ ሰው በደንብ ባይጠራው፣ ቢረሳው፣ ወይም በትክክል ባይጠቀመው እንዴት እንደሚያሳስበን ለመግለፅ ይህንን ልምድ ይጠቀሙ። ስሞቻችን በቁጣ ሲጠሩ መስማት እንደማንፈልግ ይግለፁ። ስሞቻችን በመጥፎ መንገድ መጠራታቸውን መስማት ያስከፋናል። ይህንን የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስም አይወዱትም። ስማቸውን ስንፀልይ ወይም በርጋታ በምንናገርበት ጊዜ፣ በክብር ብቻ እንድንጠቀምበት አስተምረውናል።

3. ልጆቹ የራሳቸውን ስም መፃፍ የሚችሉ ከሆነ፣ በባዶ ወረቀት መሃል ላይ የመጀመሪያ ስማቸውን እንዲፅፉ ያድርጉ፣ ከዚያም ዙሪያውን በአንድ ቀለም ይክበቡት፣ ከዚያም እንደገና በሌላ ቀለም እናም በሌላ፣ በስሙ ዙሪያ ክብ “ቀስተደመና” እስኪሰሩ ድረስ ይክበቡት። ልጆቹ የራሳቸውን የመጀመሪያ ስም መፃፍ የማይችሉ ከሆነ፣ ስማቸውን በወረቀቶቹ መካከል እርሶ ሊጽፉላቸው ይችላሉ እናም ስሞቹን በቀስተደመና ንድፍ ወይም በሌላ መንገድ እንዲያስጌጡ ይፍቀዱላቸው።

4. ከትምህርት 20 ላይ የአቢናዳይን የጨዋታ ሚና ይድገሙት እና አንድ ልጅ አቢናዳይን የሆነ በማስመሰል ለኃጢአተኛው ንጉስ ኖሃ “የአምላክህን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥራ” የተባለውን ትዕዛዝ እንዲደግመው ያድርጉ።

5. “የዮሴፍ ስሚዝ የመጀመሪያ ፀሎት” የሚለውን መዝሙር ቃላት ከልጆቹ ጋር በሉት ወይም ዘምሩት (*መዝሙር*፣ ቁጥር 26)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

6. ለክፍሉ የሚከተለውን የሚመስል ትልቅ የቃላት ሰንጠረዥ እንቆቅልሽ ያዘጋጁ፥




   በትምህርቱ የተገለፀውን ጠቃሚ ትዕዛዝ የሚያስታውሱ እንደሆነ ማየት እንደሚፈልጉ ለልጆቹ ይንገሯቸው። ያዘጋጁትን ረዥም ቁራጭ የቃላት ሰንጠረዥ እንቆቅልሽ ለእያንዳንዱ አምስት ልጆች ይስጧቸው። የጥቅሶቹን ቃላት በቀደም ተከተል እንዲያስተካክሉ ይርዷቸው። ከዚያም ክፍሉ ትዕዛዙን አንድ ላይ እንዲያነቡት ያድርጉ።

   ይህንን ጥቅስ በቃላቸው ማንበብ የሚፈልጉትን ማንኛውንም ልጆች ይጋብዙ።

# ለሌሎች አድርግ

ትምህርት
44

**ዓላማው** ሁሉም ልጆች ሌሎች ሰዎችን እና ዛብታቸውን እንዲያከብሩ ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. 3ኛኔፊ 14፡12 እና ኦሪት ዘፀአት 20፡15 በፀሎት ያጥኑ።
2. የጨው ሊጥ ያዘጋጁ። 2 ስኒ ዱቄት፣ 1 ስኒ ጨው፣ 1 ማንኪያ ዘይት፣ እና 3/4 ስኒ ውሃ ይደባልቁ፣ (እንደ አስፈላጊነቱ 4 የምግብ ቀለም ጠብታዎች በውሃው ላይ ይጨምሩ)። እስኪለሰልስ እና እስኪለዝብ በሳህኑ ውስጥ ቀልቅሉን ይለውሱት። ካስፈለገ 1 ማንኪያ ውሃ ወይም ዱቄት ይጨምሩ።
3. "ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ለመዘመር ወይም ለማለት ይዘጋጁ (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 160)፣ ቃላቶቹ በዚህ መምሪያ በስተጀርባ ተጠቃለዋል።
4. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. መፅሐፍ ቀዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. የት.ም. ጋሻ ወይም ቀለበት
   ሐ. ጠመኔ፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ እና ማጥፊያ።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ዛሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ አንድ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ለሌሎች አድርግ**

የአትኩሮት ተሳትፎ

ንብረት ማለት የራሳቸው የሆነ ነገር ማለት እንደሆነ ለልጆቹ ይግለፁላቸው ላምሳሌ መፅሐፍ፣ አሻንጉሊት፣ ገንዘብ፣ ወይም ልብስ። ሽልማት የሆነ ንብረት በተለየ ሁኔታ የሚወዱት ወይም ዋጋ የሚሰጡት ነገር ነው። ለሽልማት የሚሆን ንብረት የግድ ብዙ ገንዘብ የሚያስወጣ መሆን የለበትም። ለሽልማት የሚሆን ንብረት ትንሽ ዋጋ ሊያወጣ ይችላል ነገር ግን በሰጠው ሰው እና በመጣበት ቦታ ምክንያት የተለየ ትርጉም አለው።

ለእያንዳንዱ ልጅ የተድቦለቦለ የጨው ሊጥ ይስጡና እና ሽልማት ከሆኑት ንብረቶቹ የአንዱን ቅርፅ እንዲሰራ ይጠይቁት። የጨው ሊጣቸውን ለመስራት እንዲዘጋጁ ለልጆቹ ጥቂት ደቂቃዎች ይፍቀዱላቸው።

ማካፈል

ልጆቹ የጨው ሊጥ ሥራቸውን እንዲያሳዩ ይጋብዟቸው እና የሠሯቸው ንብረቶቹ የሚወክሉት ነገር ለምን ለእነርሱ ምን ያህል ማለት እንደሆኑ ይናገሩ።

- አንድ ሰው፣ ይህንን ንብረት ሳይጠይቅ፣ ቢበደር፣ ቢወስደው፣ ወይም ቢያፈርሰው እንዴት ይሰማችኋል?

ትምህርቱ እስኪያበቃ ድረስ የጨው ሊጥ ስራቸውን በጠረጴዛ ላይ ወይም በሌላ በተለየ ቦታ ላይ እንዲታይ ያስቀምጡ።

ውይይት

- ሽልማት የሆነው ንብረታችሁን አንድ ሰው ቢዋሰው፣ ያ ሰው እንዴት እንዲንከባከበው ትፈልጋላችሁ?
- ሽልማት የሆነው ንብረታችሁ ቢጠፋባችሁ፣ ያገኘው ሰው ምን እንዲያደርገው ትፈልጋላችሁ?

ሁላችንም የተሸለምናቸውን ንብረቶች ሌሎች በጥንቃቄ እና በክብር እንዲንከባከቡት እንደምንፈልግ ይግለፁ። ሌሎች ሰዎችም ለእነርሱ ሽልማት የሆኑ ንብረቶች አሏቸው፣ እናም ልዩ የሆኑ ንብረቶቻቸውን በጥንቃቄ እና በክብር እንድንከባከበው ይፈልጋሉ።

የት.ም. ጋሻ ውይም ቀለበት እና የጥቀስ ውይይት

ኢየሱስ ክርስቶስ ሌሎች ሰዎችን እና ንብረቶቻቸውን እንዴት እንደምንከባከብ እንዳስተማረን ለልጆቹ ይንገሯቸው። የት.ም. ቀለበት ወይም ጋሻ ያሳዩ፣ እና የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርቶች በዚህ አርዕስት ላይ በቅዱሳን መፃሕፍቶች ውስጥ ማግኘት እንደምንችል ይግለጹ። በ3ኛ ኔፊ 14፥12፣ ሰዎች ለእኛ እንዲያደርጉልን የምንፈልገውን ማንኛውንም ነገር፣ እኛም ተመሳሳዩን ለእነርሱ ልናደርግላቸው ይገባል ሲል ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል። *ለእነርሱ* ብሎ የሚያልቀውን ሐረግ ሲያነቡ ልጆች እንዲያዳምጡ ያድርጉ።

ይህንን ጥቀስ ከልጆቹ ጋር ይወያዩበት። ሌሎች እንዲንከባከቡን በምንፈልገው መንገድ እኛም ሌሎች ሰዎችን መንከባከብ እንዳለብን እንዲያውቁ ይርዷቸው። አንዳንዴ ይህ ወርቃማው ህግ እንደሚባል እና በቀላሉ "ለአንተ እንዲያደርጉ የምትፈልገውን ለሌሎች አድርግ።" ተብሎ እንደሚጠራ ይግለፁ።

ወርቃማውን ህግ ብዙ ጊዜ ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ ልጆቹ ደግመው እንዲሉት ያድርጉ። እኛን እንዲንከባከቡን በምንፈልገው መንገድ ሌሎችን መንከባከብ ማለት የእኛን ንብረት እንዲያከብሩ በምንፈልገው ተመሳሳይ መንገድ የእነርሱን ንብረት መንከባከብን እንደሚያጠቃልል ያስረዱ።

**ባለመስረቅ የሌሎች ሰዎችን ንብረቶች እናከብራለን**

የጥቀስ ውይይት

የሰማይ አባት ሌሎች ሰዎችን እና ንብረታቸውን እንድናከብር ማዘዙን ይግለፁ።

ኦሪት ዘፀአት 20፥15 ያንብቡ፣ ልጆቹ ይህንን ጥቀስ እንዲያብራሩ ይጠይቁ።

የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳንሰርቅ እንዳዘዙን ያሳስቡ። የአገራችን ህጎችም ከሌሎች መስረቅ ትክክል እንዳልሆነ ይነግሩናል። እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባልነታችን፣ የሰማዩ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶን ትዕዛዛት እንዲሁም የአገራችንን ህጎች በመታዘዝ እናምናለን።

የዕምነት አንቀፅ

አስራ ሁለተኛው የእምነት አንቀፅ ስለህጎች ያለንን ዕምነት እንደሚያተት ይግለፁ። "ህግን—በመታዘዝ— እናምናለን" የሚለውን ዓረፍተ ነገር ልጆቹ እንዲደግሙት ያድርጉ።

ታሪኮች እና ውይይት

አስቸጋሪ ውሳኔ ስላጋጠማቸው ስለ ሁለት ወጣት ሴት ልጆች የሚከተለውን ታሪክ ለልጆቹ ይንገሯቸው፥

ጆን እና ሱዛን ከማስቲካ ማሽን ጥቂት ማስቲካ ለመግዛት ፈለጉ። ሳንቲሙን ማሽኑ ውስጥ ከተቱ እና ድቡልቡል ማስቲካ ለማግኘት እጀታውን አዞሩት፣ ነገር ግን በሚያስገርም ሁኔታ፣ በአንድ ድብልቡል ማስቲካ ፈንታ እፍኝ ሙሉ ድቡልቡል ማስቲካ ወጣ። በተጨማሪም፣ ሳንቲማቸውም ተመለሰ።

- ይህ ለእናንተ ቢሆን ምን ታደርጋላችሁ?

የቀድሞ የቤተክርስቲያን የበላይ ባለስልጣን በሆኑት በቄስ ስቴርሊንግ ደብሊው ሲል፣ ከአመታት በፊት ተመሳሳይ ነገር እንደተከሰተባቸው ለልጆቹ ይንገሯቸው፣ ይህም ምናልባት የተጠየቁትን ጥያቄ እንዲመልሱ ሊረዳቸው ይችላል። ከዚያም የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

"[ቄስ ሲል] በመንገዱ ላይ ሲነዳ ውሀ ጠማው፣ ጥቂት ለስላሳ መጠጦች ለመግዛት መኪናውን አቆመ። በነዳጅ መሙያው ጣቢያ በነበረው ለስላሳ መጠጥ ማሽን ውስጥ አስር ሳንቲም ከተተ እና አንድ የጠርሙስ ለስላሳ አገኘ፣ ነገር ግን ሳንቲሙም ተመለሰ። ሳንቲሙን አወጣው፣

ተመለከተውም፣ በኪሱም ከተተው፣ ወደመኪናው በመመለስ ላይ እያለ፣ እንዲህ አለ፣ ለእዚህ ነገር የሚያስከፍሉት ብዙ ነው። ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ወደ መኪናው አልገባም ምክንያቱም ዝግ ያለ ትንሽ ድምፅ በጆሮው ላይ በማቃጨል በጣም አስገራሚ የሆነ ጥያቄ ጠየቀው። ጥያቄውም ሲል፣ ለአስር ሳንቲም ሌባ ልትሆን ነውን?፝ የሚል ነበር (ሃርትማን ሬክተር፣ ትንሹ፣ "Get up and Glow," *Brigham Young University Speeches of the Year* [Provo, 5 Jan. 1971], ገጽ 6)።

- ቁስ ሲል ምን ያደረገ ይመስላችኋል?

ልጆቹ ምላሹ ከሰጡ በኋላ፣ ወደ ማሽኑ እንደተመለሰ እና ገንዘቡን ወደ ማሽኑ ውስጥ መመለስ እንደጀመረ ይንገሯቸው። ነገር ግን ቁስ ሲል አሁን ሌላ ችግር አጋጠመው።

- ገንዘቡን ወደ ማሽኑ ቢመልስ፣ ምን ይከሰት ይሆን? (ሌላ አንድ ጠርሙስ ለስላሳ ሊያገኝ ነው እንዲሁም፣ ምናልባት ገንዘቡንም እንደገና መልሶ ሊያገኘው ነው።)

ይህ ችግሩን እንደሚያባብሰው ይጠቁሙ።

- እናንተ ምን ታደርጉ ነበር?

ቁስ ሲል ሳንቲሙ የእርሱ እንዳልነበረ መገንዘቡን ይግለፁ። በአንድ ጠርሙስ የለስላሳ መጠጥ ቀይሮታል። ስለዚህም የጣቢያውን ጠባቂ ፈልጉ ገንዘቡን ሰጠው።

- አሁን ጃን እና ሱዛን በማስቲካቸው እና በገንዘባቸው ምን ያደረጉ ይመስልሃል? (ሴቶቹ ልጆች የመደብሩን ኃላፊ እንዳገኙት እና ማስቲካውን እና ገንዘቡን ከመውሰድ ይልቅ የተከሰተውን ነገር እንዳስረዱት ይግለፁ።)

ጃን፣ ሱዛን፣ እና ቁስ ሲል ትክክለኛውን ነገር እንደመረጡ ያሳስቡ። የሰማይ አባትን እና የኢየሱስ ክርስቶስን ትዕዛዝ እንዲሁም የሀገሩን ህግ ለመታዘዝ መረጡ—አልሰረቁም።

የእኛ ያልሆነውን ማንኛውንም ነገር መውሰድ እንደሌለብን ይጠቁሙ።

### የሌሎች ሰዎችን ንብረት በመመለስ ንብረታቸውን ማክበር እንችላለን

ውይይት — ንብረትህ ቢጠፋብህ፣ ያገኘው ሰው ምን እንዲያደርገው ነው የምትፈልገው? (እንዲመልሰው።)

ታሪክ — የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ለልጆቹ ይንገሯቸው፣

ካቲ ወደ ትምህርት ቤት እየሄደች ሳለ በእግር መንገዱ ዳር ባለው ሣር ውስጥ የሚያንፀባርቀ በአየች ጊዜ አጎነበሰች፣ እናም የወርቀ ዛብል በሳሩ ውስጥ አየች። ቆንጆ ነበር። ባነሣችው ጊዜ፣ ይህ ዛብል ማሪያ ለልደቷ የተሰጣትን ዛብል ይመስላል ብላ አሰበች። ካቲ ዛብሉን ኪሷ ውስጥ ከተተች እና ወደ ትምህርት ቤት በፍጥነት ሄደች።

ትምህርቱ ሲጀመር፣ ማሪያ አልነበረችም። ከብዙ ቆይታ በኋላ ወደ ክፍሉ መጣች። አይኖቿ ቀልተው እና አብጠው ነበር። ስታለቅስ ነበር።

በምሳ ሰዓት ላይ ትምህርት ቤት የዘገየችበትን ምክንያት ለካቲ ነገራቻት ካቲ ልክ ካገኘችበት አካባቢ፣ ዛብሏን ጥላ እንደነበር፣ እናም ስትፈልገውም እንደነበር ነገረቻት። ካቲ ቃልም አልተነፈሰች። "እንዳገኘሁት አልነግራትም። አግኝቼዋለሁ፣ ስለዚህ የራሴ ነው፣ ብላ አሰበች"

የዚያን እለት ከሰዓት በኋላ አስተማሪዋ የማሪያ ዛብል ላይ ምን እንደደረሰ ለክፍሉ ገለፀችላቸው። ትምህርቱ ሲያልቀ ተማሪዎቹ ዛብሉን በማፋለግ ማሪያን እንዲረዷት ጠየቀች።

ካቲ የዚያን እለት ከሰዓት በኋላ ትምህርት ቤቱን ለቃ ለመውጣት የመጨረሻዋ ሰው ነበረች። በውስጧ መጥፎ ነገር ተሰማት። ማሪያ እንዴት እንዳዘነች ታውቃለች። ምንም እንኳ እሷ ብታገኘውም ዛብሉ የማሪያ እንደሆነ ታውቃለች። የእርሷ ቢሆን ኖሮ ማሪያ ዛብሉን ለእርሷ እንዴት እንድትመልስላት እንደምትፈልግ አሰበች። በፍጥነት ማሪያን ለማግኘት እና ዛብሉን ለመመለስ ሮጠች።

ውይይት

- ካቲ ለማድረግ የወሰነችው ምንድን ነው?
- ካቲ ሣብሉን ስትመልስ ማሪያን ምን የተሰማት ይመስላችኋል?
- የእናንተ ያልሆነን ነገር ብታገኙ ምን ታደርጋላችሁ?

**የሌሎች ሰዎችን ንብረት በክብር መንከባከብ አለብን**

ውይይት

- ስራዬ ብሎ አንድ ሰው ከንብረቶችህ አንዱን ቢያጠፋ ወይም ቢያበላሽ ምን ይሰማሃል?

ማንኛውንም የጠፋ ሣብት ወይም ንብረት ካገኘን ሁልጊዜ ለባለቤቱ ለመመለስ መሞከር እንዳለብን ይግለፁ። የሌሎች ሰዎችን ንብረት በፍፁም ስራዬ ብለን መጉዳት ወይም አለአግባብ መጠቀም የለብንም። ከጨው ሊጥ ከተሰሩት ነገሮች አንዱን ያንሱ እና በጥንቃቄ እንዴት መያዝ እንዳለበት ለልጆቹ ያሳዩአቸው። ልጆቹ በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት እንዲለማመዱ ከጨው ሊጥ የተሠራው ነገር ለክፍሉ ያስተላልፉት።

ታሪክ እና ውይይት

የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፣

ትሮይ እና አለን ከአቶ ግሪን ጎተራ አጠገብ ባለው ባዶ ሜዳ ላይ ይጫወታሉ። ትሮይ ድንጋይ መወርወር ጀመረ እናም አለንን ድንጋዩን ማን በርቀት መወርወር እንደሚችል ለማየት ለውድድር ጠየቀው። ጥቂት ድንጋዮች ከወረወሩ በኋላ፣ ትሮይ አንድ ድንጋይ ወረወረ እና የአቶ ግሪንን ጎተራ አንዱን ጎን መታ። በአለን ሲያሾፍበት እንዲህ አለው፣ "ጎተራውን እንደማትመታ እወራረዳለሁ።" አለን ድንጋይ አነሳ እና ወደ መወርወሩ ገደማ ነበር።

- አለን ምን አይነት ውሳኔ መወሰን ያለበት ይመስላችኋል?
- አለን ለትሮይ ምን ማለት ይችል ነበር? ("ሌላ ዒላማ እንፈልግ።")

አለን ማድረግ የነበረበትን የሚያሳይ ለታሪኩ ጥሩ መደምደሚያ የሚሆነውን ነገር ልጆቹ እንዲያስቡ ያድርጉ። አንድ ወይም በርከት ያሉ ልጆች የታሪኩን መደምደሚያ እንዲናገሩ ያድርጉ።

መዝሙር

ወንድም ሲል፣ ካቲ፣ እና አለን ሁሉም ትክክለኛውን መንገድ እንደመረጡ ይግለፁ።

"ትክክለኛውን መንገድ ምረጥ" የሚለውን መዝሙር ቃላት ልጆቹ በመቆም እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ያድርጉ።

ውይይት

ለሌሎች ሰዎች ንብረት ወይም ሣብት ክብርን ማሳየት የሚችሉበትን ሌላ መንገድ ልጆች እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። የሚያቀርቡት ሀሳብ የሚከተሉትን ሊያጠቃልል ይችላል፣

1. ያለፈቃድ በሌሎች ሰዎች ግቢ መስክ ላይ አለመረማመድ ወይም በአጥር ግቢያቸው ውስጥ አለመጫወት።
2. ንብረትን የሚያጠፉ ወይም የሚጎዱ ነገሮችን አለማድረግ፣ ለምሳሌ በግርግዳዎች ወይም በአጥሮች ላይ መፃፍ ወይም መሳል የመሳሰሉትን ነገሮች አለማድረግ።
3. በመጫወቻዎች እና በአሻንጉሊቶች በጥንቃቄ መጫወት።
4. የእኛ ያልሆነውን ነገር ሳንጠይቅ አለመጠቀም።
5. ሆነ ብሎ ንብረትን አለመስበር ወይም አለማጥፋት።

**ማጠቃለያ**

እኛን እንዲንከባከቡን በምንፈልገው መንገድ ሌሎችን መንከባከብ እንደሚገባን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ያሳስቡ። የኢየሱስ ክርስቶስን ትምህርት ከተከተልን፣ የሌሎች የሆነውን ነገር አንወስድም። ያገኘነውን ነገር ለባለቤቶቹ እንመልሳለን። የተዋስናቸውን ነገሮች ሳናጠፋቸው ወይም ሳናበላሻቸው በክብር እንከባከባለን። አንዳንዴ ወርቃማው ህግ በመባል የሚታወቀውንና በኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠውን ትዕዛዝ ለልጆቹ ያስታውሷቸው።


| | |
|---|---|
| የሚታደል ጽሑፍ እና ጥቁር ሰሌዳ | የወርቃማውን ህግ ቃላት ማስታወስ መቻላቸውን ልጆቹን ይጠይቋቸው። ልጆቹ ማንበብ ከቻሉ ቃላቶቹን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይፃፉላቸው፣ ወይም በቀላሉ ቃላቶቹን በርጋታ ይበሉት። ከዚያም አንድ ላይ በሉት በሏቸው። የልጆቹን የጨው ሊጥ ስራ ይመልሱላቸው። |
| የአስተማሪ ምስክርነት | ኢየሱስ ክርስቶስ በሚፈልግብን መንገድ መሠረት ሌሎችን መንከባከብ ጠቃሚ እንደሆነ ለልጆቹ ይመስክሩላቸው። አንድ ሰው እርስዋን በደንብ የተንከባከበበትን አጋጣሚ ያካፍሉ ይሆናል እናም ይህ እንዴት እንዲሰማዎ እንዳደረጉዎት ለልጆቹ ያስረዷቸው። እነርሱን እንዲንከባከቧቸው እንደሚፈልጉት ቤተሰባቸውን እና ጓደኞቻቸውን እንዲንከባከቡ ልጆቹን ያበረታቷቸው። |
| | አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ። |

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሣትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ የበለጠ የሚስራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ፣ እነኚህ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የአስተማሪ መርጃዎች" በሚለው ውስጥ የክፍል ጊዜን ይመልከቱ።

1. እንደሚከተሉት ዓይነት ያሉትን ሁኔታዎች ልጆቹ እንዲጫወቱ ያድርጉ፣
   - ብዙ ገንዘብ ያለበትን የገንዘብ ቦርሳ ከቤትህ ፊት ለፊት ብታገኝ፣ ምን ታደርግበታለህ? (ባለቤቱን ለማግኘት ማድረግ የሚችሉትን ነገሮች ልጆቹ በጨዋታ መልክ እንዲያሳዩት ያድርጉ።)
   - ከጓደኛህ ቤት ወደቤትህ ስትመጣ፣ በኪስህ ከጓደኛህ አሻንጉሊቶች ውስጥ አንዱን እንደያዝክ ታያለህ። ምን ታደርገዋለህ?
   - ከጓደኛህ ጋር ስትጫወት የጎረቤትህን መስኮት በድንገት ትሰብራለህ። ምን ማድረግ አለብህ?
   - ከእናትህ ጋር ዕቃ ስትገዛ የተከመሩ ቁርቁሮዎችን በድንገት ትንዳለህ። ምን ማድረግ አለብህ?
   - ከጓደኛህ ጋር ውጪ እየተጫወትክ ነበር፣ እና ጫማህ በጭቃ ተለውሷል። ወደቤቱ ስትሄድ፣ በወለሉ ላይ የጭቃ ዱካ ትተዋለህ። ምን ማድረግ አለብህ?
2. ልጆቹ የት.ም. ሀብል (ማብራሪያውን ይመልከቱ) ከክር እና ከተቀለመ ወረቀት ጋር እንዲሰሩ ያድርጉ። ሃብሎቹ ሌሎች እንዲንከባከቧቸው በሚፈልጉት መንገድ ሌሎችን ይንከባከቡ ዘንድ እንደሚያስታውሷቸው ይንገሯቸው።



ትምህርት

45

# ለቤተሰቦቼ መልካም ምሳሌ መሆን እችላለሁ


**ዓላማው** ለቤተሰቦቻቸው መልካም ምሳሌዎች መሆን እንደሚችሉ ልጆቹን እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

**ዝግጅት**

1. 1ኛኔፊ 2፥1–4፣ 3፥4–5፣ 7፣ እና 3ኛኔፊ 12፥16ን በፀሎት ያጥኑ።
2. እንደሚከተለው ያለ ትልቅ የፀሀይ ብርሃን ፖስተር ያዘጋጁ፥




3. ፖስተሩን ለመክበብ የሚከተሉትን የቃላት መስመሮች ያዘጋጁ፥




ማንበብ ለማይችሉ ህፃናት ልጆች፣ እነዚህን ችሎታዎች የሚወክሉ ስዕሎችን ለማግኘት ወይም ለመስራት ወይንም ረጂ ታዛዥ፣ ቀን፣ እና የመሳሰሉትን ሆኖ መገኘትን ማሳየት ይፈልጉ ይሆናል።

4. ለእያንዳንዱ ልጅ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የቤት ቀጂን ይስሩ ወይም ይንደፉ።

5. “ስንረዳ” የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆቹ እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ለመርዳት ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 198)፣ ቃላቶቹ በመምሪያው በስተጀርባ ተጠቃለዋል።

6. የሚያስፈልጉ ቁሳቁች፣
   ሀ. መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ለእያንዳንዱ ልጅ ከለር።
   ሐ. የት.ም. አርማ እና ቀለበት
   መ. የመሸፈኛ ማጣበቂያ
   ሠ. ስዕል 3-9፣ ኢየሱስ ክርስቶስ (62572፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 240)።

7. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም አበልፃጊ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት**

**የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲሰሩ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ጥሩ ምሳሌ ሌሎችን ስለ ኢየሱስ እንዲማሩ እና እንዲከተሉት ይረዳቸዋል**

የአትኩሮት ተሳትፎ

በክፍሉ ውስጥ በሆነ ቦታ፣ ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያሳየውን ስዕል 3-9፣ ያሳዩ።

ልጆቹ ተነስተው እንዲቆሙ፣ አይናቸውን እንዲጨፍኑ፣ እና እጅ ለእጅ እንዲያያዙ ያድርጉ። የመጀመሪያውን ልጅ እጅ በረድፍ ይያዙ። የልጆቹን ረድፍ በክፍሉ ዙሪያ ይምሩ፣ ጉዳትን እና ግራመጋባትን ለማስወገድ እንደ አስፈላጊነቱ በድምፅዎት ይምሯቸው። በክፍሉ ዙሪያ ብዙ ከዞሩ በኋላ፣ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስዕል ይምሯቸው። እርስዎን በመከተላቸው ሁሉም ወደአዳኛችን ስዕል የሚወስደውን መንገዳቸውን በደህና ማግኘት እንደቻሉ ይግለፁ። ልጆቹ ወደ መቀመጫቸው እንዲመለሱ ይጠይቋቸው።

- መሪ በጨለማ ቦታ ረዳት የሚሆነው ለምንድን ነው?
- ጥሩ ምሳሌ ማለት ምንድን ነው?

ጥሩ ምሳሌ ማለት ወደ ደህንነት የሚመራን አይነት መሪ ሊመስል እንደሚችል ይግለፁ። ልክ የመሪያቸውን ድምፅ መከተል ልጆቹን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ስዕል በደህና እንዳመጣቸው፣ እንደዚሁም የነቢይ ቃሎችን መከተል መቻልም አንድ ቀን ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ እንዲመለሱ ያደርጋቸዋል።

- ወደ ሰማይ አባት እና ኢየሱስ ለመቀረብ የረዷቸሁ ጥሩ ምሳሌዎች ምንድን ናቸው?

የጥቀስ ውይይት

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሌሎች መልካም ምሳሌዎች መሆን እንዳለብን እንዳስተማረን ይግለፁ። መልካም ስራችንን አይተው የሰማይ አባታችንን እንዲያከብሩት በሌሎች ሰዎች ዘንድ ብርሃን ይበራ ዘንድ እንደሚገባው ኢየሱስ አስተምሮናል (3ኛኔፊ 12፥16 ይመልከቱ)። ለሌሎች ሰዎች መልካም ምሳሌ ስንኖር፣ ሰዎች ሊኖሩበት የሚገባውን ትክክለኛውን መንገድ ለማሳየት በጨለማ ውስጥ እንዳለ ብርሃን እንደሆንን ይጠቁሙ።

ጋሻ፣ ቀለበት፣ እና ታሪክ

የት.ም. ጋሻ እና ቀለበት ያሳዩ። ጃያንት የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈልጉትን እንዴት እንዳደረገ የሚከተለውን ታሪክ ልጆቹን እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው፣

“ጃያንት አባል ከመሆኑም በፊት ቤተክርስቲያኗን ይወድ ነበር። አጎቱ ስለ ወንጌል ሲያወራ እና ፊጂ ውስጥ ባለችው ቤተክርስቲያን ከህንድ የመጀመሪያ አባል እንዴት እንደሆነ ሲናገር መስማት ያስደስተው ነበር።

“ወንጌላውያኖችን ካዳመጠ በኋላ፣ ጃያንት የቤተክርስቲያን አባል መሆን ይችል ዘንድ ወላጆቹን ጠየቃቸው። ፍቃዳቸውን ሰጡት፣ እናም ጃያንት የወንጌልን መሰረተ ሀሳቦች በማክበር እና ጥሩ ምሳሌ በመሆን ለቤተሰቡ ወንጌላዊ ለመሆን በጣም ሞከረ።

"ብዙም ሳይቆይ የጆያንት አባት እና ወንድም ተጠመቁ፤ እናቱ ግን አንገራገረች። የወንድ አያቷ በብንድ ነበር ውስጥ የሂንዱ ዕምነት ታላቅ ቄስ ነበሩ፤ እናም [የኋለኛው ቀን ቅዱሳን] ብትሆን ቤተሰቦቿ ምን ይላሉ ብላ ተጨነቀች። ይሁን እንጂ፤ በልጇ ምሳሌ ምክንያት፤ በመጨረሻ እርሷም የቤተክርስቲያኗ አባል ሆነች።

"አሁን ሁሉም የጆያንት ቤተሰቦች በፊጂ፤ ሱቫ፤ ባለው ቅርንጫፋቸው ንቁ ተሳታፊዎች ናቸው እናም የሰማይ አባታችንን ከማገልገል የሚመጣውን ፍቅር እና ደስታ ያውቁታል" ("A Good Example," *Friend*, Mar. 1974, ገፅ 48)።

- ጆያንት ለቤተሰቡ ጥሩ ምሳሌ ያኖረው እንዴት ነበር?
- የጆያንት መልካም ምሳሌ በቤተሰቡ ላይ ምን ተፅዕኖ ነበረው?

ወደ ት.ም. ቀለበት እና ጋሻ ይጠቁሙ። የሰማይ አባት እና ኢየሱስ ክርስቶስ እንድናደርግ የሚፈልጉትን ስናደርግ፤ ትክክለኛውን እያደረግን እና ትዕዛዛቱንም እየታዘዝን መሆናችንን ይግለፁ። ይህንን ስናደርግ፤ ሌሎችንም ደግሞ በጽድቅ መኖር እንዲፈልጉ እንረዳቸዋለን።


### ለቤተሰቦቻችን መልካም ምሳሌዎች መሆን እንችላለን

የፖስተር ተሳትፎ

የክፍሉ አባላት በሙሉ ማየት በሚችሉበት ቦታ የፀሀይ ብርሃን ፖስተር ያሳዩ። ዓረፍተ ነገሩን ከልጆቹ ጋር ያንብቡ።

በጠረጴዛው ወይም በወለሉ ላይ የቃላት ቁርጥራጮቹን ወይም ስዕሎቹን ያስቀምጡ። ለቤተሰቦቻችን ጥሩ ምሳሌዎች መሆን የምንችልበትን ልዩ ልዩ መንገዶች እንደሚነግሩን ይግለፁ።

በተብራራው መሰረት የፀሐይ ብርሃን ጨራዎችን ለመስራት በፖስተሩ ላይ የቃላት ቁርጥራጮቹን ለመምረጥ እና ለማስቀመጥ ወይም ለመለጠፍ ልጆቹ ተራ እንዲይዙ ያድርጉ። ልጆቹ እያንዳንዱን የቃላት ቁራጭ ሲመርጡ፤ ተመሳሳዩን ታሪክ ይናገሩ።




እያንዳንዱ የቃላት ቁራጭ ከተቀመጠ እና ታሪኩ ከተነገረ በኋላ፤ ልጆቹ ይሄን እንዲሉ ያድርጓቸው "__________ በመሆን ለቤተሰቦቼ መልካም ምሳሌ መሆን እችላለሁ፤" ባዶ ቦታውን ከቃላት ቁራጩ ላይ ባለው ሀረግ ወይም ቃል ይሙሉት። ለምሳሌ፤ "አስታራቂ በመሆን ለቤተሰቦቼ መልካም ምሳሌ መሆን እችላለሁ።"

ታሪኮች እና ውይይት

ታዛዥ

ኢየሩሳሌምን የለቀቁትን የሌሂ ቤተሰቦችን ታሪክ ይናገሩ (1ኛ ኔፊ 2፥1–4 ይመልከቱ)።

- የነሐስ ሰሌዳዎቹን ለማምጣት ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ሲጠይቃቸው የሌሂ ልጆች ምላሽ ምን ነበር (1ኛኔፊ 3፥4–5 ይመልከቱ)?

ሊመን እና ሊሙየል ካጉረመረሙ እና መሄድ አንፈልግም ካሉ በኋላ፣ ኔፊ እንዴት እንደተሰማው መናገሩን ይግለፁ። 1ኛኔፊ 3፡7 ድምፅዎን ከፍ በማድረግ ያንብቡ።

- ኔፊ ለወንድሞቹ ጥሩ ምሳሌ ያኖረው እንዴት ነበር?
- ታዛዥ በመሆን ጥሩ ምሳሌ እንዴት ማኖር ትችላለህ?

የሚረዳ

ብሩስ እናቱ ለቤተክርስቲያን ትንሽ እህቱን በመቻኮል ስታዘጋጅ ተመለከተ። ራሷን ገና እንደምታዘጋጅ እና ሕፃኑን እንደምታለብስ አውቋል። ብሩስ እናቱን ለመርዳት ወሰነ። ወደ ህፃኑ ክፍል ሄደ እና አለበሰው። የብሩስ እናት ስለእርዳታው አመሰገነችው። ፈገግ አለች እናም በደንብ አቀፈችውና ሳመችው።

- ብሩስ ለቤተሰቡ ጥሩ ምሳሌ ለማኖር ምን አደረገ?
- የሚረዳ ሰው በመሆን ጥሩ ምሳሌ ማኖር የምትችሉት እንዴት ነው?

መዝሙር “ስንረዳ” የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆቹ እንዲሉት ወይም እንዲዘምሩት ይርዷቸው።

ታሪኮች እና ውይይት

ቀን እና አፍቃሪ

ኬቲ እናቷ አዲሱን ህፃን ወንድሟን፣ ጢሞቴዎስን ወደ ቤት ስታመጣው በጣም ደስ ብሏት ነበር። እንደ ሌሎች ህፃናት አልነበረም። ባልተለመደ ሁኔታ የሚያንቀጠቅጠው እና የሚያርገፈግፈው፣ ሴሬብራል ፓልሲ የሚባል ችግር ነበረው። ነገር ግን ኬቲንያ አላስጨነቃትም። ጢሞቴዎስን በሙሉ ልቧ ትወደዋለች። እናቷ ስራ ሲበዛባት፣ ኬቲ ጢሞቴዎስን በማባበል መዝሙር ትዘምርለታለች። አንዳንድ ነገሮችን ለእርሱ በምታደርግለት ወቀት ጢሞቴዎስ ወደ ኬቲ ፈገግ ይላል። ጢሞቴዎስ ሲያድግ፣ በቤታቸው ፊት ለፊት በመግፊያ ልታንሸራሽረው ትወስደዋለች። አብዛኛውን ጊዜ እንዲተኛ ታለባብሰው እና እንቅልፍ እስኪወስደው ድረስ ታሪኮችን ታነብለታለች።

- ኬቲ ጥሩ ምሳሌ ያስቀመጠችው እንዴት ነበር?
- በቤታችሁ የሩህሩህ አፍቃሪ ጥሩ ምሳሌ መሆን የምትችሉት እንዴት ነው?

አስታራቂ

ኬሪ ወንድሟ ከቤት ሲወጣ በግቢ ውስጥ ባለው ዥዋዥዌ ትጫወት ነበር፣ ወንድሟም ወደ “ዥዋዥዌው በመሮጥ፣ “ከዚህ ዥዋዥዌ ውረጂ፣ ኬሪ። እኔ በፍፁም ልወዛወዝ አልቻልኩም ምክንያቱም ዘወትር እላዩ ላይ ነሽ” በማለት ይጮኽባት ጀመር።

በመጨቃጨቀ ፈንታ፣ ኬሪ እንዲህ አለች፣ “መልካም። በየተራ እንገፋፋ። በመጀመሪያ እኔ እገፋሃለሁ።”

ኬሪ ስላልተጨቃጨቀች፣ እርሷ እና ወንድሟ አብረው በመጫወት ጥሩ ጊዜ አሳለፉ።

- ኬሪ ለወንድሟ ጥሩ ምሳሌ የሆነችው እንዴት ነበር?
- አስታራቂ በመሆን በቤታችሁ ጥሩ ምሳሌ ማኖር የምትችሉት እንዴት ነው?

ይቀርታ አድራጊ

ስፔንሰር በትምህርት ቤት ሳለ፣ ትንሽ ወንድሙ በመጫወቻ መኪናዎቹ ሲጫወት እና አንዱን ጣላበት። ስፔንሰር የሆነውን ባወቀ ጊዜ፣ አልተናደደም። ይልቁንስ የጠፋውን መኪና በመፈለግ ወንድሙን ረዳው። ከዚያም ከአልጋው ስር አገኙት።

- ስፔንሰር ለቤተሰቦቹ ጥሩ ምሳሌ ለማኖር ምን አደረገ?
- ይቀር ባይ በመሆን ለቤተሰቦቻችሁ እንዴት ጥሩ ምሳሌ መሆን ትችላላችሁ?

የሚገነዘብ

ሮቤርታ እንፉሌንዛ ስለያዛት ወደ ገና በዓል ግብዣ ልትሄድ አልቻለችም። እህቷ፣ ሊንዳ፣ ሮቤርታ መሄድ ስለማትችል እንዴት ሃዘን እንደተሰማት አወቀች፣ ስለዚህ ላስቲክ ሙሉ ከረሜላ እና ለውዝ ቤት አመጣችላት። በግብዣው የሆነውንም ለሮቤርታ ነገረቻት።

- ሊንዳ ለቤተሰቦቿ እንዴት ነበር ጥሩ ምሳሌ የሆነችው?
- የልብ አዋቂ በመሆን ለቤተሰቦቻችሁ ጥሩ ምሳሌ መሆን የምትችሉት እንዴት ነው?

ራሱን የማይወድ

ቶኒ በጎረቤቱ የአትክልት ቦታ ላይ በመስራት ጥቂት ገንዘብ አገኘ። ስለ ቤተሰቡ በማሰብ የሆነ ነገር ሊያደርግላቸው ፈለገ፣ ስለዚህ ከገንዘቡ ከፊሉን ወሰደና አስደሳች ነገር ገዛላቸው።

- ቶኒ ለቤተሰቡ ጥሩ ምሳሌ የሆነው እንዴት ነበር?
- ራስ ወዳድ ባለመሆን ለቤተሰቦቻችሁ ጥሩ ምሳሌ መሆን የምትችሉት እንዴት ነው?

እውነተኛ

ያሬድ በአጋጣሚ የቀለም ቆርቆሮው ሲገጨው ኔልሰን እና ያሬድ በአባታቸው የስራ ቦታ ከእንጨት ስብርባሪ የመጫወቻ ጀልባ ይሰሩ ነበር። ትንሽ ቀለም በወለሉ ላይ ተንጠባጠበ። አብዛኛውን ወንዶች ልጆቹ አፀዱት፣ ጥቂቱ ግን በመሬቱ ላይ ተለጠፈ። አባታቸው ወደ ቤት እንደመጣ፣ ያሬድ ወደ እርሱ ሄደ እና የሆነውን ነገረው።

የያሬድ አባት በወለሉ ላይ የቀረውን ቀለም አልወደደውም፣ ነገር ግን እውነቱን ስለነገረው በያሬድ ኩራት ተሰማው። ለያሬድ ጥቂት ቀለም ማቀጠኛ ሰጠው እና ወለሉን በማፅዳት ረዳው።

- ያሬድ ለቤተሰቦቹ መልካም ምሳሌ የሆነው እንዴት ነው?
- ሐቀኛ በመሆን ለቤተሰቦቻችሁ መልካም ምሳሌ መሆን የምትችሉት እንዴት ነው?
- ፖስተሩ አሁን ምን ይመስላል? (የሚያበራ ፀሐይ።)

ጥሩ ምሳሌዎች ልክ እንደ ፀሐይ ብርሃን እንድሆኑ ይግለጹ። ለሌሎቹ ብርሃንን ይሰጣሉ እና ትክክለኛውን መንገድ ያሳዩአቸዋል።

**ማጠቃለያ**

የአስተማሪ ምስክርነት — ለቤተሰብዎ ጥሩ ምሳሌ ስለመሆን ጥቀም ምስክርነትዎን ይስጡ። የአንድ ሰው ጥሩ ምሳሌ ስለ ረዳዎት ወቀት ያሎትን የግል ልምድዎን ማካፈል ይፈልጉ ይሆናል።

የስዕል ተሳትፎ — ልጆቹ “ጥሩ ምሳሌ መሆን እችላለሁ” የሚለውን ቤታቸውን እንዲያቀልሙት እና የቤተሰባቸውን አባላት በቤቶቹ ውስጥ እንዲስሏቸው ያድርጉ። ለቤተሰቦቻቸው ጥሩ ምሳሌ ለማኖር በዚህ ሳምንት ማድረግ የሚችሉትን አንድ ነገር ሲያደርጉ ራሳቸውን እንዲስሉ ይጠይቋቸው።

ዛሬ ማታ ወደ መኝታ ከመሄዳቸው በፊት ለቤተሰቦቻቸው ማድረግ የሚችሉትን አንድ ነገር እንዲመርጡ ልጆቹን ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች** — ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ የበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚህኑ እንደ ክለሳ ወይም እንደ ማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መምሪያ፣ “የመምህሩ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. ቀላል የሆነ ካልሲ ወይም የወረቀት ቦርሳ አሻንጉሊት ለልጆቹ ያዘጋጁ። የክፍሉን ጠረጴዛ ለመድረክነት ለመጠቀም ይፈልጉ ይሆናል። ልጆቹ መጫዎቻዎችን በመጠቀም፣ በትምህርቱ የተሸፈኑትን ስምንት ነገሮች ለቤተሰቦቻቸው ምሳሌ ለመሆን ቀን በሆነ መንገድ እንዲጫወቱ ይርዷቸው።


2. "ጥሩ ሁኔታን የሚያሳዩ እንቅስቃሴዎችን ሲደርጉ፣ ለምሳሌ ወለልን መጥረግ፣ ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ፣ ከኤጲስ ቆጶሳት ጋር መጨባበጥ የመሳሰሉትን ስታደርጉ እማደርገውን አድርግ" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ዘምሯቸው ወይም በሏቸው። (*የልጆች የመዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ፣ 276)

   እማደርገውን አድርግ፣
   እኔን ተከተለኝ፣
   እማደርገውን አድርግ፣
   እኔን ተከተለኝ!
   ከፍ ወይም ዝቅ ባደርገውም፣
   በፍጥነት ወይም በዝግታ!
   እማደርገውን አድርግ፣
   እኔን ተከተለኝ!
   (© 1963 በዲ. ሲ. ጨና እና ኩባንያ። በፈቃድ ጥቅም ላይ ዋለ።)

   ሌሎች መልካም ምሳሌዎቻችንን ሲያዩ፣ ብዙውን ጊዜ የምናደርገውን ማድረግ እንደሚፈልጉ ለልጆች ይንገሯቸው።

3. የሆነ ነገር በጭናቸው ላይ ሲደርጉ ልጆቹ አይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ይጠይቋቸው። በእያንዳንዱ ልጅ ጭን ላይ ስዕል ያስቀምጡ፣ ከዚያም አይኖቻቸውን እንዲከፍቱ እና በየተራ ስዕሎቻቸውን እንዲያሳዩ እናም በስዕሎቹ ላይ ያሉት ሰዎች እንዴት ጥሩ ምሳሌ እንዳኖሩ እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። ስዕል 3-13፣ 3-23፣ 3-24፣ 3-25፣ 3-26፣ 3-27፣ እና 3-59 ከክፍሉ የስዕል ፖስታ ለመጠቀም ይፈልጉ ይሆናል።

ጥሩ ምሳሌ
መሆን
እችላለሁ



# ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘለዓለም መኖር እንድንችል አድርጓል (ፋሲካ)

ትምህርት

46

---

**ዓላማው** ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወደን፣ ለዘለዓለም መኖር እንድንችል ማድረጉን ልጆቹ እንዲያውቁ ለመርዳት ነው።

---

**ዝግጅት**

1. የማርቆስ ወንጌል 10፥13–16፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ ታሪክ የሚገኝበትን የሉቃስ ወንጌል 23 እና 4፣ እንዲሁም በ3ኛኔፊ 11 ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ኔፋይቶችን የጎበኘበትን ታሪክ በፀሎት ያጥኑ።
2. *ሕያው* የሚል የተፃፈበትን የቃል ቁራጭ ያዘጋጁ።
3. የእያንዳንዱን ልጅ ስም በተለየ ቁራጭ ወረቀት ላይ ይጻፉ።
4. "ኢየሱስ ተነስቷል" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆቹ እንዲሉት ወይም እንዲዘምሩት ለማስተማር ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 70)።
5. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፣
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. ለስላሳ ኳስ ወይም የባቄላ ከረጢት።
   ሐ. ማጣበቂያ
   መ. ጓንት
   ሠ. ስዕል 3-71፣ ስቅለት (62505፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 230)፣ ስዕል 3- 15፣ ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ (62187፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 239)፣ ስዕል 3-72፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔፊዎች ሲገለፅ (62047፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 315)፣ ስዕል 3-56፣ ክርስቶስ እና ልጆች (62467፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 216)፣ ስዕል 3-17፣ የኢየሱስ ትምህርት በምዕራቡ ክፍል ዓለም (62380፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 316)፣ ስዕል 3-73፣ ሌመናይቱ ሳሙኤል በግንብ ላይ (62370፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 314)፣ ስዕል 3-74፣ የኢየሱስ ቀብር (62180፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 231)፣ እና ስዕል 3-75፣ በመቃብሩ አካባቢ የነበሩ ሴቶች።
6. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ** አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚወደን ይረዳናል**

የአትኩሮት ተሳትፎ ኢየሱስ ልጆችን እንደሚወድ ለክፍሉ አባላት ይንገሯቸው። በዚህ በፋሲካ ማለዳ በጀማሪ ክፍል መሆናቸውን ማወቁ ምን ያህል ደስ እንደሚያሰኘው ይንገሯቸው።

ከሞት የተነሳውን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስዕል 3-15፣ በግድግዳ ላይ፣ በጥቁር ሰሌዳ ላይ፣ ወይም በሌላ ስፍራ ላይ፣ ያሳዩ።

የእያንዳንዳቸውን ስሞች በቁራጭ ወረቀት ላይ እንደጻፉ፣ እና በየተራ አንድ በአንድ እንዲመጡ እና በኢየሱስ ስዕል አጠገብ ስማቸውን እንዲለጥፉ መፈለግዎትን ይግለፁ። እያንዳንዱ ልጅ በተራው ሲመጣ "(የልጁን ስም በመጥራት) ኢየሱስ ክርስቶስ ይወድሃል" ይበሉት።

**የቅዱሳን መጻህፍት ታሪክ**

ከማርቆስ ወንጌል 10፥13–16 የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ፣ አንዳንድ እናቶች ህፃናት ልጆቻቸውን ወደ እርሱ አመጧቸው። እያንዳንዳቸውንም እንደሚባርካቸው ተስፋ አደረጉ። የኢየሱስ ጓደኞች እረፍት እንዲያደርግ ፈለጉ፣ እናቶች ልጆቻቸውን እንዲወስዱ፣ እንዳያውኩት ጠየቋቸው።

ኢየሱስ ጓደኞቹ የሚሉትን በሰማ ጊዜ፣ እንዲህ አለ፣ “ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ፍቀዱላቸው፣ እናም አትከልክሏቸው።” በሌላ አባባል፣ እንዲህ አለ፣ “ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፣ አትከልክሏቸው። ልጆችን እወዳለሁና።” እናም ሕፃናቶችን በእቀፉ አደረጋቸው ባረካቸውም።

**ውይይት**

ስዕል 3-56፣ ክርስቶስ እና ልጆችን የሚያሳየውን ስዕል ከፍ አድርገው ይያዙ። በጥንቃቄ እንዲመለከቱት እና የስዕሉ መንፈስ እንዲሰማቸው ወደ ልጆቹ ቀረብ በማድረግ ይያዙት። ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነርሱ ያለው ታላቅ ፍቅር እንዲሰማቸው ልጆቹን ለመርዳት የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ይጠይቁ።

- ልጆቹ የተሰማቸው ምን ይመስላችኋል?
- እዚያ ብትሆኑ ኖሮ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲላችሁ የምትፈልጉት ምንድን ነበር?
- እንደ እነዚህ ልጆች ከኢየሱስ ጋር ብትሆኑ ኖሩ፣ ምን ትሉት ነበር?
- ኢየሱስ እነዚህን ልጆች እንደሚወደው እናንተንም እንደሚወዳችሁ ማወቁ ምን እንዲሰማችሁ ያደርጋል?

### ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሞቷል

**የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ እና ስዕሎች**

ቅዱሳን መጻሕፍቶችን ይያዙ፣ እና መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞንን በማንበብ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለመርዳት ያደረገውን ማወቅ እንደምንችል ይግለፁ። በራስዎ አባባል የሚከተለውን ታሪክ ይናገሩ፥

ኢየሱስ ክርስቶስ ከረጅም ጊዜ በፊት ይኖር ነበር። የሰማይ አባት ወንዶች እና ሴቶች እንዲሁም አባቶች እና እናቶች ትክክለኛ ነገሮች ያደርጉ ዘንድ እንዲረዳቸው ወደ እዚህ ምድር ላከው። አብዛኛውን ጊዜ የኖረው አሁን እስራኤል በምትለው ሀገር ነበር።

ኢየሱስ ሁሉንም ሰው ይወድ ነበር። አንዳንዶቹ ሰዎች ኃጢአተኞች ነበሩ እናም አይወዱትም ነበር። በመስቀል ላይም ሰቀሉት።

ስቅለትን የሚያሳየውን ስዕል 3-71፣ ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ተሰቃየ እና ሞተ። የሚወዱት ሰዎችም በጣም አዘኑ። ሬሳውን ከመስቀል ላይ አወረዱት እና በቀንጆ ነጭ ጨርቅ ጠቀለሉት። ሬሳውን በመቃብር ውስጥ አኖሩት። መቃብር ሰዎች የሚቀበሩበት ዋሻ የሚመስል ነገር ነው። ቀስ ብለው አስቀመጡት።

የኢየሱስን ቀብር የሚያሳየውን ስዕል 3-74፣ ያሳዩ።

የኢየሱስ ክርስቶስ ጓደኞች የመቃብሩን ትልቅ ድንጋይ በማንከባለል በራፉን ፊት ለፊት ዘጉት።

የኢየሱስ ክርስቶስ ጓደኞች እንደገና በህይወት እንደሚኖር አላወቁም ነበር። ጥቂት ወታደሮች ሬሳው ወዳረፈበት መቃብር በመምጣት ይጠብቁት ነበር። ከሞተ በኋላ በሶስተኛው ቀን፣ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት፣ መላዕክቶች በመምጣት ድንጋዩን ከደጃፉ አንከባለሉት። አካሉ እዚያ አልነበረም። ወታደሮቹም በጣም ፈርተው ስለነበር ለጥቂት ጊዜ ሊንቀሳቀሱ አልቻሉም። ወዲያው በተቻላቸው መጠን ሮጡ።

በመቃብሩ የነበሩትን ሴቶች የሚያሳየውን ስዕል 3-75፣ ያሳዩ።

በዚያኑ ቀን ጠዋት ጥቂት ሴቶች ወደ መቃብሩ መጡ። እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስን ይወዱት ስለነበር በዚያን ዘመን ሰዎች እንደሚያደርጉት መልካም መዓዛ ያላቸውን ቀመሞች በሰውነቱ ላይ ሊቀቡት መጡ። ድንጋዩም ከደጃፉ ተንከባሎ አዩት። ወደ መቃብሩም ሄዱና ነጭ የለበሰ መልአክ አዩ፣ እናም ፈሩ። መልአኩም “አትፍሩ፣ እሱ እዚህ የለም፣ ተነስቷል።” አላቸው።

ከሞት ወደ ተነሳው የክርስቶስ ስዕል ይጠቁሙ።

- የኢየሱስ ክርስቶስ ጓደኞች መነሳቱን ባወቁ ጊዜ የተሰማቸው ምን ይመስላችኋል?

**የጥቁር ሰሌዳ ውይይት**

ኢየሱስ ከሞት በተነሳ ጊዜ፣ ስጋውን እንደገና ከመንፈሱ ጋር በማዋሀድ እንደተቀበለ፣ ነገር ግን አካሉ ተለውጦ እደነበር ይግለፁ።

*ሕያው* የሚለውን የቃል ቁራጭ ያስቀምጡ።

- *ሕያው* ማለት ምን ማለት ነው?

የአዳኛችን አካል ሕያው በሆነ ጊዜ፣ በፍፁም ዳግም እንደይሞት ነገር ግን ለዘለዓለም ይኖር ዘንድ አካሉ እንደተቀየረ ይግለፁ።

ኢየሱስ ከሞት በተነሳበት ጊዜ፣ ሕያው እንደሆነ፣ እና ሁላችንም ደግሞ ከሞት እንድንነሳና ሕያው እንድንሆን እንዳስቻለን ለልጆቹ ይንገሯቸው። ይህ ማለት ከሞት ከተነሳን በኋላ በፍፁም ዳግም አንሞትም ማለት ነው። ከቤተሰቦቻችን ጋር ለዘለዓለም መኖር እንችላለን።

**መግለጫ እና ውይይት**

ጓንቲ ያላጠለቁበትን እጅዎን ለልጆቹ ያሳዩአቸው እና ከመወለዳችን በፊት ከሰማይ አባት ጋር ስንኖር መንፈሶች እንባል እንደነበር ይንገሯቸው። መንቀሳቀስ (በጓንቲ ያልተሸፈነውን እጅ ጣቶችን ያንቀሳቅሱ) ማሰብ እና መማር እንችል ነበረ።

መንፈሶቻችን በምድር ላይ ሊኖሩ ሲመጡ፣ ምድራዊ አካሎች ተሰጡን። (ጓንቲውን ያጥልቁ።) አሁንም መንቀሳቀስ፣ (ጣቶችዎን በጓንቲ ውስጥ ያንቀሳቅሱት ማሰብ እናም መማር ችለናል፣ ነገር ግን የሠማይ አባት እንዲኖሩን እና እንድንከባከባቸው ድንቅ አካላቶችን ሰጥቶናል።

ስንሞት፣ አካል ከመንፈስ መለየት አለበት (ጓንቲውን ያውልቁ)። አካል በራሱ ሊንቀሳቀስ አይችልም (ጓንቲውን ያመልክቱ) ነገር ግን መንፈስ አሁንም ትኖራለች።

ከሞት ስንነሳ፣ አካል ፍፁም ይሆናል እና እንደገና ከመንፈስ ጋር ይዋሀዳል (ጓንቲውን ወደ እጅዎ ይመልሱት)። ከሞት ከተነሳን በኋላ፣ እንደገና በፍፁም ልንሞት አንችልም። ያ ማለት መንፈስ እና አካል በፍፁም ሊለያዩ አይችሉም ማለት ነው።

ኢየሱስ እያንዳንዳችንን በጣም ስለሚወደን፣ ለእኛ እንደሞተልን አጥብቀው ያሳስቡ። ኢየሱስ ለመነሳት የመጀመሪያው ሰው ነበር። እርሱ ለእኛ ስላደረገልን ምክንያት፣ ከሞት እንነሳና ዳግም ከሰማይ አባት ጋር እንኖራለን። ስለ ፋሲካ ስናስብ፣ ስለመጀመሪያው ፋሲካ ማሰብ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ያለውን ፍቅር ማስታወስ ይገባናል። ህይወቱን ለእኛ ሰጥቶናል። ተነስቷል። አሁን በሰማይ ከሰማይ አባቱ ጋር ይኖራል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ በጣም አስደናቂ በመሆኑ በየዓመቱ ፋሲካን የምናከብረው ላደረገልን ነገር እንዴት እንደምናመሰግነው ልናሳየው እንደሆነ ይጠቁሙ።

**ተሳትፎ**

ትንሽ ለስላሳ ኳስ ወይም የባቄላ ከረጢት ለልጆቹ ይወርውሩላቸው፣ በየተራ መደረግ እያንዳንዱ ልጅ ስለፋሲካ የሚያስታውሰን ታሪክ እንዲናገር ወይም እንድትናገር ያስችላል።

## ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሳኤው በኋላ ኔፊዎችን ጎብኝቷል

**የቅዱሳን መጻሕፍት ታሪክ ከስዕሎች ጋር**

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሳ በኋላ ብዙ ተከተዮቹ እና ደቀ መዝሙሮቹ እንዳዩት ቅዱሳን መፃሕፍት ስለሚነግሩን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት መነሣቱን እንደምናውቅ ለልጆቹ ይንገሯቸው።

በአሜሪካ ይኖሩ የነበሩ ፃድቅ የሆኑ ኔፊዎች እና ሌመናይቶች ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳዩት እና መፅሐፈ ሞርሞን እሱ ስለ ጉብኝት እንደሚናገር ይግለፁ። ከኢየሩሳሌም ትንሳኤው በኋላ ኢየሱስ እነዚህን ህዝቦች ጎበኘ። እርሱን የማየት፣ የመስማት፣ እና የመንካት ዕድሉን አገኙ።

ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ቀን ኔፊዎችን እንደሚጎበኛቸው ነቢያቶች ለብዙ ዘመናት እንደነገሯቸው ይግለፁ።

ሌመናይቱ ሳሙኤልን በግንቡ ላይ የሚያሳየውን ስዕል 3-73፣ ያሳዩ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከመውለዱ ከጥቂት ዓመታት በፊት ይኖር የነበረው፣ ሳሙኤል የሚባለው ሌመናይቱ ነቢይ ኢየሱስ በኢየሩሳሌም መቼ እንደተሰቀለ እና እንደተነሳ እንዴት እንደሚያውቁ ለህዝቦች እንደነገራቸው ይግለፁ። ኢየሱስ ሲሞት፣ ታላቅ ጨለማ ምድሪቷ እንደሚሸፍን፣ ከሞት እስኪነሳም ድረስ ጨለማው ለሶስት ቀናት እንደሚቆይ ገልፄል።

የሳሙኤል ሌመናይቱ ትንቢቶች በሙሉ መፈፀማቸውን ለልጆቹ ይንገሯቸው። ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ሲሞት፣ ታላቅ ጨለማ የአሜሪካንን ምድር ሸፍኗል። ኃጢአተኛ ሰዎች ጠፉ፣ ብዙ ፃድቅ ሰዎችም ስለተከሰተው ነገር እና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ለመወያየት አንድ ላይ ተሰበሰቡ። ሲነጋገሩም ሳለ፣ ከሰማይ የመጣ የሚመስል ድምፅ ወዲያውኑ ሰሙ። ለስለስ ያለ፣ የፍቀር ድምፅ ነበር። ልጆቹ ድምፁ ያለውን እንዲያዳምጡ ይጠይቋቸው። አንድ ልጅ 3ኛኔፊ 11፥7 እንዲያነብ ይርዱት፣ ወይም ራስዎ ያንብቡት። ድምፁ የሰማይ አባታችን የተደሰተበትን፣ በእርሱም አብ ስሙን ያከበረበትን ኢየሱስ ክርስቶስን ህዝቡ ሊመለከት ይገባዋል አለ። ድምፁ ህዝቡ ኢየሱስን እንዲሰሙት ነገራቸው (3ኛ ኔፊ 11፥7ን ይመልከቱ)።

- ማን እየተናገረ ነበር? (የሰማይ አባት።)

ህዝቡ ወደ ላይ ሲመለከት ነጭ የለበሰ ሰው ከሰማይ ሲወርድ መመልከታቸውን ይግለፁ። ሰዎቹም መልአክ ያዩ ነበር የመሰላቸው።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለኔፊዎች ሲገለፅ የሚያሳየውን ስዕል 3-72፣ ያሳዩ።

- በእርግጥ ከሰማይ የወረደው ማን ነበር? (ኢየሱስ።)

ኢየሱስ ለህዝቡ እጁን ዘርግቶ ነቢያት ወደ አለም ይመጣል ብለው የመሰከሩለት ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ መሆኑን እንደተናገረ ይግለፁ (3ኛ ኔፊ 11፥9–10ን ይመልከቱ)። ኢየሱስ ክርስቶስ እሱ ማን እንደሆነ ለሰዎቹ ሲነግራቸው፣ ነቢያት እሱ እንደሚጐበኛቸው የነገሯቸውን እንዳስታወሱ ይግለፁ። ተደሰቱ። ሰዎቹ ወደእርሱ እንዲመጡና በእጆቹና በእግሮቹ ያለውን የምስማር ምልክትና ጐኑ ያለውን ቁስል እንዲዳስሱት ጋበዛቸው። የተሰቀለው እና የተነሳው ያው ኢየሱስ መሆኑን እንዲያውቁ ስለፈለገ ይህን አደረገ።

ኢየሱስ በምዕራቡ ክፍለ አለም ሲያስተምር የሚያሳየውን ስዕል 3-17፣ ያሳዩ።

- ሰዎቹ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በመሆናቸው የተሰማቸው ምን ይመስላችኋል?

ሰዎቹ ለአዳኛችን በታላቅ ምስጋናና ፍቀር ስለተሞሉ ሆሳዕና! ከፍ ያለው የእግዚብሔር ስም የተባረከ ይሁን! ብለው እንደጮኹ ይግለፁ (3ኛ ኔፊ 11፥17)። በጉልበቶቻቸው ወደቁ እና አመለኩት።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለእነዚህ ህዝቦች ታላቅ ፍቀር ስለተሰማው በመሀከላቸው በመቆየት በሽተኞቻቸውን እንደፈወሰ፣ ልጆቻቸውን እንደባረከ እና እንዳስተማራቸው ይግለጹ። መፅሐፈ ሞርሞን በምድር ላይ ከእነዚህ ህዝቦች የበለጠ ደስተኛ ህዝብ እንዳልነበረ ይነግረናል።

መዝሙር

"ኢየሱስ ተነስቷል" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆቹ እንዲሉት ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው።

ኢየሱስ ተነስቷል፣
የእኛ ወዳጅ።
ተደሰተ ልባችን፣
ዳግም አለ።
ውዳሴ ለእርሱ እንዘምራለን፣
በዚህ ፋሲካ።
ኢየሱስ ተነስቷል፣
መለኮታዊው አዳኝ።
ኢየሱስ ተነስቷል፣
መለኮታዊው አዳኝ!

**ማጠቃለያ**

የአስተማሪ ምስክርነት

ኢየሱስ ክርስቶስ ስለወደደን ከሞት መነሳት እንድንችል ማድረጉን እና አካላችንን ለዘለዓለም እንዲቀይ ስላደረገ ምስክርነትዎን ይስጡ እናም ፍቀርዎን እና ምስጋናዎን ይግለፁ።

ልጆቹ ወደቤት ሲሔዱ አዳኛችን አካላችንን ለዘለዓለም ለማኖር እንድንችል ያደረገውን ለቤተሰቦቻቸው እንዲነግሩ ይጋብዟቸው።

አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ውስጥ ለልጆችዎ በበለጠ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚህኑ እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ “የአስተማሪ መርጃዎች” በሚለው ውስጥ “የክፍል ጊዜን” ይመልከቱ።

1. በትምህርቱ መጨረሻ የሚገኘውን “የኢየሱስ ክርስቶስ የሚከብብ ፍቀር፣” የሚለውን የሚታደል ጽሁፍ ቀጂ ለእያንዳንዱ ልጅ ለማደል ይዘጋጁ።

   ለእያንዳንዱ ልጅ የሚታደል ጽሁፍ ቀጂ፣ እርሳስ፣ እና ጥቂት ከለር ይስጡ። ስማቸውን በወረቀታቸው ላይ በላይኛው የቀኝ ማዕዘን እንዲጽፉ ያድርጉ ወይም ይርዷቸው።

   ከልጆቹ ጋር በክቡ የውስጥ አካባቢ ያሉትን ቃላት ያንብቡ። በክቡ ውስጥ የራሳቸውን ምስል እንዲስሉ ያድርጉ። “ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደኛል” የሚለውን በጥቁር ሰሌዳ ላይ ይጻፉ፣ እና ልጆቹ ከክቡ ስር በወረቀቶቻቸው ላይ እንዲገለብጡት ያድርጉ።

2. ልጆቹ እንዲቆሙ እና ይህንን ተሳትፎ ከእርሶ ጋር እንዲሰሩት ያድርጉ።

   ኢየሱስ የተኛበት ቦታ ይህ ነው። (ያመልክቱ)<br>
   እዩት፣ ድንጋዩ ተፈንቅሏል! (እንደገና ያመልክቱ)<br>
   ወደታች አጎንብስ። (አጎንብሱ)<br>
   ወደ ውስጥ ተመልከት። (እጆች አይኖችን ይጋርዱ)<br>
   እሱ እዚህ የለም! (ተነስ እና ቁሙ)<br>
   ኢየሱስ ተነስቷል!<br>
   ደስ ይበልህ! (በቀስታ አጨብጭብ)

ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት በመነሳቱ ምክንያት፤

አካሌ ለዘለዓለም ይኖራል።

# ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ተወልዷል (የገና በአል)

ትምህርት
47

---

**ዓላማው** ልጆቹ የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት አስፈላጊነት እንዲያውቁት ለመርዳት ነው።

---

**ዝግጅት**

1. ሄለማን 14፥3 ኔፊ 1፣ እና የሉቃስ ወንጌል 2 በፀሎት ያጥኑ። ሄለማን 14፥5 ኔፊ 1፥13፣ 21፣ እና የሉቃስ ወንጌል 2፥9–15 ለማንበብ ይዘጋጁ።
2. በትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የኮከብ እንቀቀልሽ የሚባለውን የሚታደል የጽሁፍ ቀጂ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ ያዘጋጁ። የእንቀቀልሹን ቁርጥራጮች በመቁረጥ ያውጡ፣ እና አንድ ላይ ይያዧቸው ወይም ለእያንዳንዱ ልጅ በፖስታ ያስቀምጧቸው።
3. "ከዋክብት አበሩ" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች ልጆች እንዲሉት ወይም እንዲዘምሩት ለማስተማር ይዘጋጁ (*የልጆች መዝሙር መፅሐፍ*፣ ገፅ 37) እና "ፀጥተኛ ሌሊት" (*ከመዝሙር መፅሐፍ*፣ ቁጥር 204)።
4. የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች፥
   ሀ. መፅሐፍ ቅዱስ እና መፅሐፈ ሞርሞን።
   ለ. የሚከተሉት ተቆርጠው የወጡ ስዕሎች፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት (3-11 ተቆርጦ የወጣ፣ እረኞች (3-12 ተቆርጦ የወጣ)፣ መልአክ (3-5 ተቆርጦ የወጣ)፣ እና ኔፊዎች እና ኮከብ (3-13 ተቆርጦ የወጣ)።
   ሐ. ለእያንዳንዱ ልጅ የተቀለመ ሉክ ወረቀት።
   መ. ማጣበቂያ ወይም መለጠፊያ
   ሠ. ስዕል 3-73፣ ሌመናይቱ ሳሙኤል በግንብ ላይ (62370፣ የወንጌል ስዕል ኪነ ጥበብ ጥራዝ 314)።
5. ለሚጠቀሙባቸው ማንኛውም ገንቢ ተሳትፎዎች አስፈላጊውን ዝግጅት ያድርጉ።

---

**ለትምህርቱ ዕድገት የቀረበ ሃሳብ**

አንድ ልጅ የመክፈቻ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

ልጆቹ በሳምንቱ ውስጥ የሆነ ነገር እንዲያደርጉ ካበረታቷቸው ይከታተሏቸው።

**የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በመላዕክቶች ታውጆ ነበር**

የአትኩሮት ተሳትፎ

- ልዩ የሆነ ነገር እንዲከሰት ጠብቃችሁ ታውቃላችሁ?
- ምን ነበር? (የልጆቹ መልሶች አዲስ ሕፃን መወለድን፣ ከአያቶች ጉብኝትን፣ የልደት ቀንን፣ ጥምቀታቸውን፣ እና ወዘተ. ሊያጠቃልሉ ይችላሉ።)
- ይህን መጠበቅ ረጅም ጊዜ ይመስላልን?
- በመጨረሻ ሲከሰት ምን ተሰማችሁ?

ልጆቹ ልምዶችን እንዲያካፍሉ እና ያላቸውን የአድናቀት ስሜቶችን እንዲገልፁ ዕድል ይስጧቸው። እርስዎም ለወደፊት የሚጠብቁትን ክስተት ማካፈል ይፈልጉ ይሆናል።

ከአዳም ጊዜ ጀምሮ፣ የሰማይ አባታችን በጣም ጠቃሚ ክስተት እንደሚመጣ ተስፋ ሰጥቶ እንደነበር ይግለፁ። የአለም አዳኝ የሚሆነውን፣ ልጁን ወደ ምድር ለመላክ ቃል ገባ፣ ጻድቃን ሕዝቦች ይህን ክስተት በጉጉት ይጠባበቁት ነበር። የሰማይ አባት ቃልኪዳኑን እንደሚጠብቅ ያውቁ ነበር። የኢየሱስን መወለድ ይጠባበቁ ነበር።

ጥቅስ እና ተቀርጦ የወጣ ስዕል ታሪክ

የኢየሱስን ልደት የሚያሳይ ተቀርጦ የወጣ ስዕል ያሳዩ። ልጆቹ ስለ ኢየሱስ ልደት ታሪክ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ይጠይቋቸው። እያንዳንዱ ልጅ ለታሪኩ የሆነ ነገር አስተዋፅኦ እንዲያደርግ ይርዱ።

- በዚያ ሌሊት ከቤተልሔም አቀራቢያ ባለው ሜዳ የነበሩት እነማን ናቸው? (በጐቻቸውን እየጠበቁ የነበሩ፣ እረኞች።)

የእረኞችን ተቀርጦ የወጣ ስዕል ያሳዩ።

ኢየሱስ በተወለደ ምሽት፣ አንድ መልአክ የኢየሱስን የመወለድ ጠቃሚ ዜና ሊያበስራቸው ለእነዚህ ትሁት እረኞች እንደተገለፀላቸው ይግለፁ።

የመልአኩን ተቀርጦ የወጣ ስዕል ያሳዩ።

- እረኞቹ መልአኩን ባዩ ጊዜ የተሰማቸው እንዴት ነበር? (መልአኩ በተገለፀላቸው ጊዜ እረኞቹ ፈርተው ነበር።)

መልአኩ ለእነርሱ ያን የመሰለ ጠቃሚ መልዕክት እንደነበረው እረኞቹ እንዳላወቁ ለልጆቹ ይንገሯቸው። በሉቃስ ወንጌል 2፥9–15 ላይ ምን እንደተከሰተ ለክፍሉ ያንብቡላቸው።

- ስለኢየሱስ መወለድ ዜና እረኞቹ ሲሰሙ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል?
- ስለ ኢየሱስ መወለድ ደስተኛ መሆናቸውን ለማሳየት እረኞቹ ያደረጉት ምን ነበር? (ሕፃኑን ኢየሱስን ለመፈለግ ወደ ቤተልሄም ሄዱ።)

መልአኩ የኢየሱስን መወለድ ለእረኞቹ ሊያበስራቸው በመገለጹ ምክንያት፣ እረኞቹ ኢየሱስ የሰማይ አባት ልጅ እንደሆነ እና ልደቱ በጣም ጠቃሚ እንደነበር ማወቃቸውን ይግለፁ።

መዝሙር

ለኢየሱስ ልደት ደስታ እና አድናቆት ልጆቹ እንዲሰማቸው ለመርዳት፣ “ከዋክብት አበሩ” የሚለውን መዝሙር ቃላቶች እንዲሉ ወይም እንዲዘምሩ ይርዷቸው።

ከዋክብት አበሩ፣ እረኞች አለሙ፣
ሌቱ ጨለማ ብርዳማ ነበር።
የመላዕክት ታሪክ ተዘመረ፣
እረኞች በተራራው ላይ ሰሙት።
አሀ፣ ያ ሲዘምር! ስሙት ሲደውል፣
የምድር ደስታ፣ ገናን አመጣ!
ስሙ! አሁንም እንሰማዋለን!

እዩት ድምቀቱን እና ቀርበቱን
የተባረከውን የገና ኮከብ፣
ሰባሰገልን በጉዞ ሲመራ
በበረሃው ሩቀ ጨለማ።
ውቡ አንፀባራቂ እይታ
እያበራ፣ የሚነጉድ፣
አሁንም ይመራል፣ የገና ኮከብ!
(“Stars Were Gleaming” by Nancy Byrd Turner from *Hymns for Primary Worship.* ከጆን ኖስስ ማተሚያ በፍቃድ የተወሰደ።)

የመዝሙሩን ቃላቶች ከዘመራችሁት ወይም ካላችሁት በኋላ፣ የኢየሱስን መወለድ ጠቃሚ መልዕክት የተቀበሉት እረኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ ኒፋይቶች እና ሌመናይቶችም በአሜሪካ መልዕክቱን መቀበላቸውን ይግለፁ።

**የኢየሱስ መወለድ በአሜሪካ ታወጀ ነበር**

ስዕል፣ ጥቅስ፣ እና ታሪክ

በመፅሐፈ ሞርሞን ከዳር እስከዳር፣ የኢየሱስን መወለድ ነቢያቶች እንደተናገሩ እና እንደተጠባበቁ ይግለፁ። የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አባላቶች የአዳኛችንን መወለድ ተጠባብቀዋል እናም ለብዙ ዘመናት ስለመወለዱ ፀልየዋል። የሚከተለውን ታሪክ በራስዎ አባባል ይናገሩ፥

ኢየሱስ ከመወለዱ ከአምስት አመት በፊት፣ ሳሙኤል የሚባል ነቢይ ስለኢየሱስ መወለድ ህዝቡን እንዲያዘጋጅ በእግዚአብሄር ተጠራ። በአዳኛችን እንዲያምኑ እና ንስኃ እንዲገቡ ያስጠነቀቃቸውም ነበር። ሳሙኤል ሌመናዊ ነበር። ኔፊዎች ኃጢአተኞች ሆነው ነበርና አላዳመጡትም። በሳሙኤል በጣም ስለተናደዱ ከከተማቸውም ውጪ አባረሩት። ነገር ግን የጌታ ድምፅ ወደ ሳሙኤል በመምጣት እንደገና እንዲመለስ ነገረው። በድፍረት በከተማው ግንብ ላይ ወጥቶ ሰዎቹ ንስኃ እንዲገቡ እና ለኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ነገራቸው።

ሳሙኤል ሌመናይቱን በግንቡ ላይ ቆሞ የሚያሳየውን ስዕል 3–7፣ ያሳዩ።

በአምስት ዓመታት ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር እንደሚመጣ ሳሙኤል ለህዝቡ እንደነገራቸው ይግለፁ። ለረዥም ጊዜ አስቀድሞ ሲነገር የነበረው ክስተት በርግጥ እየቀረበ ነበር። ሳሙኤል ኢየሱስ በቤተልሄም መወለዱን የሚያሳዩ አንዳንድ ነገሮች እንደሚከሰቱ ገልጿል። ኢየሱስ ከመወለዱ በፊት ቀደም ባለው ሌሊት ታላቅ ብርሃን በሰማይ ይሆናል። ደማቅ ከመሆኑ የተነሣ በምሽት ጊዜ ጨለማ አይኖርም። ሌሊቱም እንደ ቀኑ ብርሃን ይሆናል።

ሔለማን 14፥5 ለክፍሉ ያንብቡ። ከዚህ ቀደም ታይቶ የማይታወቅ አዲስ ኮከብ እንደሚወጣ፣ ይህ ለእነርሱ ምልክት እንደሚሆን ሳሙኤል ለህዝቡ መናገሩን ይግለፁ።

- ኔፊዎች እንዲጠባበቁ ሳሙኤል የነገራቸው ምንድን ነበር? (አዲስ ኮከብ።)

ሳሙኤል ሌመናይቱ ኢየሱስ ሲወለድ በሰማይ ላይ አዲስ ኮከብ እንድሚያዩ ለኔፊዎች መንገሩን ለልጆቹ ይንገሯቸው። እነዚህ ምልክቶች እንደሚመጡ በመልአክ ስለተነገረው ሳሙኤል ይህን ያውቅ ነበር።

- እነዚህን ነገሮች ለሳሙኤል እንዲነግር የሰማይ አባት መልአክ የላከው ለምን ይመስላችኋል? (ለሰዎች መንገር እንዲችል።)
- የሰማይ አባት ስለእነዚህ ምልክቶች ሳሙኤል ለኔፊዎች እንዲናገር ለመንገር የፈለገው ለምን ይመስላችኋል? (ኢየሱስ መቼ እንደተወለደ እንዲያውቁ እና ህዝቡን ወደ ንስኃ ለማምጣት ለመሞከር ነበር።)

የሰማይ አባት ስለወደፊቱ ክስተቶች ለሳሙኤል እንዲናገር መልአክ መላኩን ይግለፁ። በአሜሪካ አገር ያሉት ህዝቦች የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ እንዲጠባበቁ ፈልጐ ነበር። የሰማይ አባት ይህ ነገር በቀርቡ እንደሚሆን እንዲያዉቁ ፈልጐ ነበር።

ኢየሱስ እንደሚወለድ ሳሙኤል ለኔፊዎች ከነገራቸው ከአምስት ዓመት በኋላ፣ የቤተክርስቲያን አባላት ሳሙኤል የነገራቸውን ምልክቶች እየተጠባበቁ ነበር። የልደቱ ምልክት የሚሆነውን ጨለማ የሌለበትን ሌሊት እየተጠባበቁ ነበር። የሳሙኤልን ቃል ያላመኑት፣ ኃጢአተኛ ሰዎች፣ በተባለው ቀን ምልክቶቹ ካልታዩ ለታማኞቹ ተከታዮች እንደሚገድሏቸው ነገሯቸው።

በዚያን ዘመን የነበረው ነቢይ ኔፊ የሚባል ሰው ነበር። ኔፊ የማያምኑት ሰዎች በመረጡት ቀን ምልክቶቹ ካልታዩ በፃድቃን ህዝቦች ላይ ስለሚያደርሱት ነገር ተጨነቀ። በነበሯቸው ችግሮች ምክንያት በጣም ስላዘነ ወደ ሰማይ አባት ፀለየ። ኔፊ ቀኑን ሙሉ ፀለየ። ከዚያም የጌታ ድምፅ ወደ ኔፊ መጣ።

የጥቀስ ውይይት

3ኛ ኔፊ 1፥13 ለልጆቹ ያንብቡላቸው። ምልክቱ በዛ ሌሊት ስለሚሰጥ ኔፊ ራሱን ቀና እንዲያደርግ እና እንዲደሰት ጌታ ነገረው። ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ነቢያቶች የተነገሩትን ነገሮች በሙሉ እንደሚያሟላ ለማሳየት በሚቀጥለው ቀን ወደ ዓለም ይመጣል (3ኛኔፊ 1፥13ን ይመልከቱ።)

- ኢየሱስ ክርስቶስ እነዚህን ቃላቶች ሲናገር ሲሰማ ኔፊ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?

ኔፊ ተፅናንቶ እንደነበር እና በሚቀጥለው ቀን ኢየሱስ እንደሚወለድ እንዳወቀ ይግለፁ። በዚያኑ ቀን ሌሊት የመጀመሪያው ምልክት መጣ።

- በዚያን ሌሊት ምን ሆነ?

ልጆቹ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ያድርጉ። ምሽቱ መምጣቱን፣ ነገር ግን ጨለማ እንዳልነበር እንዲያውቁ ይርዷቸው። ሌሊቱ የማይጨልም በመምሰሉ ሰዎቹ ተደነቁ። በጣም ስለተገረሙ ወደ ምድር ወደቁ። ፃድቃን ህዝቦች ለብዙ ዘመናት የጠበቁት ጊዜ መድረሱን አወቁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊወለድ እንደሆነ አወቁ። ከዚያም ሌላ ነገር ተከሰተ።

ጥቅስ እና ተቀርጦ የወጣ ስዕል — ምን እንደነበረ ለማየት 3ኛ ኔፊ 1፥21 ያንብቡ። እንደ ነቢያቱ ቃል መሰረት አዲሱ ኮከብ መታየቱን ይግለፁ።

የኔፊዎችን ተቀርጦ የወጣ ስዕል እና ኮከብ ያሳዩ (ከተጠቀሟቸው በተቃራኒ)።

አዳኛችን እንደተወለደ ይግለፁ። አሁን አዲሱን ኮከብ በሰማይ ሲያዩ ለዘመናት የነበራቸው ዕምነት ወደ ታላቅ ደስታ ተለወጠ። ኔፊዎች ሄደው ህፃኑን ማየት ባይችሉም፣ መወለዱ ለእነርሱ ጠቃሚ እንደሆነ ያውቁ ነበር።

- የሰማይ አባት ኔፊዎች ኮከቡን እንዲመለከቱ ያደረገው ለምን ነበር? (ኢየሱስ ክርስቶስ መወለዱን እንዲያውቁ።)
- ኔፊዎች ኮከቡን ሲያዩ ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል?

ኮከቡ በኢየሩሳሌምም መታየቱን ይግለፁ። የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ ለእያንዳንዱ ጠቃሚ ነበር። ሰዎች ለዘመናት ሲጠባበቁት የነበረ ነገር ነበር፣ በእርግጥም ተከሰተ።

መዝሙር — "ፀጥተኛ ሌሊት" የሚለውን መዝሙር ቃላቶች በሉ ወይም ዘምሩ።

ብፁዕ ሌት! ቅዱስ ሌት!
ሁሉም ሰላም፣ እና ብሩህ
ለድንግል እናት እና ልጅም።
ቅዱሱ ህፃን፣ ሩህሩህም፣
ተኛ በሰማያዊ ሰላም፣
ተኛ በብሩሁ ሰላም።

ብፁዕ ሌት፣ ቅዱስ ሌት!
እረኞች ፈሩ ለማየት!
ክብር ከሰማይ ሲፈስስ፣
መላዕክት ዘመሩ ሀሌ ሉያ!
ክርስቶስ አዳኝ ተወለደ!

ብፁዕ ሌት! ቅዱስ ሌት
የአብ ልጅ፣ ፍቀርህ
የሚያበራ ጮራ ከፊትህም፣
በንጋት የማዳን ጸጋህን፣
ኢየሱስ ጌታ፣ በልደትህ፣
ኢየሱስ ጌታ፣ በልደትህ።

### ማጠቃለያ

የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ — ሁልጊዜ በገና በዓል የኢየሱስ ክርስቶስን መወለድ የሚነግረን ኮከብ ወይም መልአክ ማየቱ ለእኛ አስፈላጊ እንዳልሆነ ይግለፁ። ይህ እውነት መሆኑን እናውቃለን። ለእኛ ጠቃሚ እንደሆነ እናውቃለን። እረኞቹ እና ኔፊዎች መወለዱን ባወቁ ጊዜ የተሰማቸውን ዓይነት ደስታ ሊሰማን ይችላል። የመወለዱን ደስታ እና ፍቅር ለሌሎች በማብሰር ይህ ይሰማናል።

- የኢየሱስ ክርስቶስን የመወለድ ደስታ ከሌሎች ጋር እንዴት መጋራት ትችላላችሁ?

የአስተማሪ ምስክርነት — ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የመወለድ ጥቅም እና ፍቅርን እንዲሁም ደስታን ከሌሎች ጋር እንዴት መካፈል እንደምንችል ምስክርነትዎን ይስጡ።

ተሳትፎ

ለእያንዳንዱ ልጅ የእንቀቀልሽ ቁራጮችን ሰብስብ ይስጧቸው። እንቀቀልሾቻቸውን አንድ ላይ በማድረግ በተቀለመ ቁራጭ ወረቀት ላይ እንዲያጣብቁት ያድርጉ። ሁሉም ልጆች ከጨረሱ በኋላ፣ በኮከቡ ላይ ያለውን መልዕክት ያንብቡላቸው፣ "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድሃኒት፣ እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና" (የሉቃስ ወንጌል 2፥11)።

ውይይት

- ከመልአኩ ይህንን መልዕክት የተቀበለው ማን ነው? (በሜዳ የነበሩ እረኞች።)
- ኮከቡን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ የመወለድ ምልክት የተቀበሉት እነማን ናቸው? ኔፊዎች እና በኢየሩሳሌም የነበሩት ህዝቦች።)


አንድ ልጅ የመዝጊያ ፀሎት እንዲሰጥ ይጋብዙ።

---

**ገንቢ ተሳትፎዎች**

ከሚከተሉት ተሳትፎዎች ለልጆችዎ በተሻለ የሚሰራውን ይምረጡ። በትምህርቱ ውስጥ እነኚህሁ እንደ ክለሳ ወይም እንደማጠቃለያ ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ። ለተጨማሪ መመሪያ፣ "የአስተማሪ መርጃዎች" በሚለው ውስጥ "የክፍል ጊዜን" ይመልከቱ።

1. የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ታሪክ በጨዋታ መልክ ለማቅረብ ቀላል የሆነ ነገር ይጠቀሙ።
2. ለእያንዳንዱ ልጅ ወረቀት እና ከለሮች ይስጡ። ወረቀቱን እንደ ካርድ እንዲያጥፉት ልጆቹን ይርዷቸው። በፊት ለፊቱ ላይ *የገና በዓል* የሚለውን ቃል ይፃፉ። ከትምህርቱ ውስጥ ከተማሩት ነገር ስዕሎችን በመሳል ለቤተሰቦቻቸው የገና ካርዶች እንዲሰሩ ክፍሉን ይጠይቁ።


**ዛሬ በዳዊት**
**ከተማ መድኃኒት፤**
**እርሱ ክርስቶስ ጌታ**
**የሆነ**
**ተወልዶላችኋልና።**
(የሉቃስ ወንጌል 2፥11)





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-3

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-4

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-6

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.






© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.


3-9

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-11

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-16

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.


3-19
© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



*The Last Supper* by Carl Bloch. Original at the chapel of Frederiksborg Castle, Denmark. Used by permission of the Frederiksborgmuseum.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.






© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-32

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-35

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-42

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.






© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-51

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



3-57

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA



3-65

© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.





© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



© by Intellectual Reserve, Inc. All rights reserved. Printed in the USA.



*Burial of Jesus* by Carl Bloch. Original at the chapel of Frederiksborg Castle, Denmark. Used by permission of the Frederiksborgmuseum.





© Providence Lithograph Company



3-1



3-2




3-3


3-4


3-5



3-6





3-7


3-8


3-9


3-10


3-11


3-12


3-13